
በቀለኛው ሰላይ

2075

ስትዋርት ውድስ



ትርጉም፡ መሉጌታ ይፋሩ

ማሊዩን ግዛው

http://ethzare.wordpress.com

በቀለኛው ሰላይ

Deep Lie

ትርጉም ሙሉጌታ ይፍሩ
ሚሲዬን ገዛው

http://ethzare.wordpress.com

ሙሉጌታ ይፍሩ ነሐሴ 2000
ሚሊዬን ግዛው
የመጀመሪያ እትም ነሐሴ 2000
ፓ.ሣ.ቁ 4143

ምስጋና

ለዚህ መፀሐፍ ሕትመት ላበቃን

- ለአማረ ብርሃኑ

የኮምፒዮተር ለቀማና የገፅ ቅንብር

- ስምወርቅ አየለ

አስካር አስካርሰን ብርሀን ወደእደመቀው ሞጋግ እየተጨናቆረ ወፍ ፍለጋ አይኖቹን ያማትራል። ኮሚንሳፈፍባት ጀልባ በላይ ብርሀን ቢኖርም እሱ ካለበት ውሀ በላይ ግን ሞጋግ አጥልቶበታል። ብርሀን በሚረዋ ሞስ ውስጥ የመታፈንን ስሜት ይፈጥራል። ከጀልባው በላይ አንድ ዝይ ተመለከተና ምናልባት የአምስት መቶ ሜትር ያህል የእርይታ ርቀት ይኖራል ብሎ ገመተ። ለአስካርሰን፣ አሁን እያደረገ ለሚገኘው ነገር ይህ ሁኔታ በጣም ተስማሚው ነው።

የጀልባውን ፍጥነት ወደ በደቂቃ 1000 ዙር መለሰና ወደኢቢ ዞር ብሎ ራሱን ወዘወዘለት። ታዳጊው በስሱ ፈገግ አለና፣ ዋናውን ሰንሰለት የያዘውን ማንቂያ በመልቀቅ፣ ከውሀው ወለል በታች ምድሩን እየቧጠጠ የሚሄደውን ረጅም ፍርግርፍ ብረት ወደታች ለቀቀው። አስካርሰን የልጅ ልጁ ይህን ስራ እንዘን ባይታማበትም በሙሉ ብቃት ሊያከናውን በእርካታ ይመለከታል። ልጁ ጂንስ ሱሪና ሸሚዝ ብቻ ለብሷል። እነዚህ ወጣቶች ቅዝቃዜ አይበግራቸውም። አስካርሰን በጡንቻ የተገነባውን የተመጣጠነ የልጁን ውብ ተክለ ሰውነት በልቡ አደነቀ። የስዊድን ወጣት ወንዶች ሁሉ ከከባድ ሥራና ከከባድ ጨዋታ የተነሳ ይህን መሰል እጅም እንደሚይዙ ልጅ ሆኖ ያስብ ነበር። አሁን ቀጫጫ ጀዝባዎችና ወፍራም የሒሳብ ባለሞያዎች ብቻ ተርተዋል፣ ከኢቢ በስተቀር። ልጁ በክረምት በረዶ ይንሸራተታል በበጋ ተራራ ይወጣል ለትምህርት ቤቱም በጀልባ ቀዘፋ ይወዳደራል። የትምህርት ሰው ባይሆን ኖሮ የአካል ብቃትን የሚጠይቁ ግዳጆችን በደስታና በቅልጥፍና ይፈፅማል።

የልጁ አባት ግለትም የአስካርሰን ልጅ ስቶክሆልም ውስጥ ለየት ያለ የምሽት መዝናኛን ያንቀሳቅሳል። አስቡት! አስካርሰን አንድ ጊዜ ልጁን ሊጠይቅ ሄዶ እያለ ወደዚያ ስፍራ መስዶታል። አቤት ኪኪታው - አሁን አሁን ሙዚቃ ብለው የሚመሩት ይህንን ነው። የሚብለጨለጩት መብራቶች፣ ሙቀቱ፣ ሽታው፣ ትልቅ ለሚባል ሰው በዚህ ሥራ መተዳደር ጥሩ አይደለም። ኢቢ ይህን ዓይነት ሥራ አይሰራም፣ ለአያቱም ይህንኑ ነግሮታል። ዩኒቨርስቲ ለመግባት የሚያበቃው ብሩህ ሀሊና ባይኖረውም ግድ አይሰጠውም። ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ ከአንድ ዓመት በኋላ ወደአያቱ ይመጣና አብረው አሳ ያጠምዳሉ። ገንዘብም ያፈራሉ። የውሀ ውስጥ ተጎታች መረቡን ለመጣል ሁለት ሰዎች ያስፈልጋሉ - የሚያስግሩትን አሣ አሁን ለማንም ሠራተኛ አያካፍሉም። ልጁ ከአያቱ ጋር ጥሩ ሕይወትን ይመራል፣ ከጥቂት ዓመታት በኋላም ሁሉን ነገር ካወቀ በኋላ ረዳት ይቀጥራል፣ አስካርሰንም ሥራውን ይተውና ጀልባውን በመስጠት በትብብር አብሮት ይሰራል። ጀልባዋ ግሩም አጭም አላት። ሲያሳድሳት ይህን ሁሉ ንዋይ በማፍሰሱ አይቆጨውም። ልጁ ሊንከባከባት ከቻለ ለተጨማሪ ብዙ ዓመታት ትቆያለች። ልጁ ለአሣ ጠመዳ ሥራ ወደአባቱ በሚሄድበት ወቅት የኢቢ አባት መበሳጨቱ አይቀርም። በምሽት መዝናኛው ያን ሁሉ ገንዘብ እያተረፈ ልጁ ግን ተራ አሣ አጥማጅ ሲሆን፣ አስካርሰን ይህ ሀሳብ ፈገግ አሰኘው።

መረቡ ሙሉ በሙሉ ተዘርግቶ ሲያበቃ አስካርሰን ልጁ ወደ መዘውር ክፍሉ እንዲሄድ በእጁ ምልክት ሰጥቶት የተጠቀለለውን ቻርት ዘረጋው። «እዚህ

http://ethzare.wordpress.com

ጋ፣» አለ በጹልጹም ወፍራም ጣቱ ወረቀቱ ላይ እየጠቆመው። እጆቹ ለብዙ ዓመታት ከቀዝቃዛ ውሀ ጋር ከመኖራቸው የተነሳ ያባበጡ ናቸው። ጣቶቹ ለብዙ በጠባሳ የተሸፈኑና ተሰብረው ከቀድሞ ቅርፃቸው ውጪ የጸኑ እጥንቶቻቸው አፈንግጠዋል። ያለ አደጋ መከላከያ በአደገኛ የሥራ መሳሪያዎችና ማሽኖች ከመስራት የተነሳ የተፈጠረ ነው። «መረቡ እስኪፈነዳ የምንሞላው እዚህ ነው።»

የልጁ ቅንድብ ተጨማደደና፣ ወደሌላ ቦታ አመለከተው። «ይኼኛውስ አያቴ?» አለ ጣቱን በተጥመለመለ የባህር ላይ ኪላ መስመር እያንሸራተተ። «ይህ የተከለከለ ስፍራ ነው ይላል። ለምን ተከለከለ? ችግር ላይ ልንወድቅ እንችል ይሆን እንዴ?»

«ካርልስክሮና የሚገኘው የባር ኃይል ጦር ሰፈር ነው፣» ሲል አዛውንቱ መለሰ፣ ወደ ሞጋጉ እያመለከተው። «የሩሲያ የባህር ስር ተጎታች ተደብቀው ገብተው ፎቶ እንዲያነሱ አይፈልጉም።» አውራ ጣቱን ወደደረቱ አዞረና። «እኔ የሩሲያ አንተም እይደለህም፣ አይደል?» ልጁን ጠቀሰው። «ባህር ሀይሉም ደሞ አሥቹን ተኩሶ አይስታቸውም።»

ልጁ ሳቀ። «ካልክ፣ እኔ እስማማለሁ።»

«አሁን ግን ማስገርም ከልከል ነው። እዚህ ቦታ ላይ ማንም አያሰግርም ብለው ያስባሉ፣ ግን ይህን በመሰለ ሞጋጋማ ማለዳ፣ ጎህ ሳይቀድ መጥተህ፣ ለተወሰኑ ሰዓታት አስግረህ፣ ሞጋጉ ከመገለጡ በፊት መሄድ ትችላለህ።»

«ራዳር የላቸውም እንዴ? ሞጋጉ ራዳሩን አይከልለውም፣ አይደል?»

«እንዲታ ራዳርማ አላቸው፣ ግን እንፀባራቂውን ስላወረድኩት የእኛን አይነት የእንጨት ጀልባ የምትታይ አይመስለኝም። ቢያንስ እኔን ይዘውኝ አያውቁም። በሞጋማ ጊዜ ቢመለከቱን ብዙም አትኩሮት አይሰጡንም፣ ምክንያቱም የሩሲያ ጀልባዎች የሚመጡት ፎቶ ለማንሳት እንዲያመቻቸው ሞጋማ በሌለበት ጊዜ ነው። ደግሞ ቢይዙንም እንኳን «አንተ ሽማግሌ ሌላ ቦታ ሄደህ አጥምድ። ከማለት ሌላ አያከብዱብኝም። ከባድ ነገር አይደለም።»

አስካርሰን መያዝ አላስጨንቀውም። ይህን የባህር ክልል ከማንኛውም ስዊድናዊ ባህር ኃይል በተሻለ ጠንቅቆ ያውቀዋል። የተወለደው ከዚህ ብዙም በማይርቀው የኡትሳንጂን ደሴት ሲሆን፣ ድሮ ድሮ በነፋስ በሚገፉ ጀልባ ሆኖ አሳ ያስግር ነበር። በደሴቶቹ መሀል እየተሽሎከሎከ ከአሳ ጀልባዎቹ መሰወር ይችል ነበር። የስዊደን ባህር ኃይል በፈጣን ጀልባዎች የተጫኑ የፈለገውን ያህል ቁጥር ያላቸው ባህረኞች ቢልክ እሱን በዚህ የባህር ክልል እንደልቡ እንዳይንሸራሸር ሊያግደው አይችልም።

ለሩብ ሰዓት ያህል እየተጫወቱና መረቡን እየነተቱ በዝግታ በጀልባዋ ሲንሳፈፉ ቆዩ። ከዚያ ግን ኃይለኛ የስንጥቅ ድምፅ ተሰማና ጀልባዋ ድንገት ቀጥ ብላ ስትቆም ሁለቱም ተፈናጥረው ከውሃ መከላከያው ጋር ተላተሙ። አስካርሰን ቶሎ ብሎ ሞተሩን አጠፋና የማርሽ ጥርሱን አላቀቀው።

«ምንድን ነው ነገሩ፣ አያቴ?» ጠየቀ ልጁ።

አዛውንቱ መልስ ከመስጠቱ በፊት እንደገና የማርሽ ጥርሱን አስገብቶ በዝግታ ነዳጅ ሰጣት። ሰጥቂት ሰኮንዶች ከተጓዙ በኋላ የመረቡ ካቦ እጅግ ስለተወጠረ ጀልባዋ ድጋሚ ቆመች። «አንድ የያዘን ነገር አለ፣» አለ አስካርሰን። ቻርቱን መረመረ። «እዚህ አካባቢ የስመጠ መርከብ መኖሩን የሚናገር ነገር

የለም። ባህርተኞቹ ለዒላማ ልምምድ አንድ ነገር አስምጠው ሪስተውት እንደማይሆን ተስፋ አለኝ። የመጎተቻ ካቦውን ረዳት መጠቅለያ ላይ አስገውና እስኪ ወጥመዱን ነፃ ለማድረግ እንሞክር።» ኢቢ ፈትለክ ብሎ ተጭኑን ካቦ ዋናው ባለ ሞተር መጠምጠሚያ ላይ ጠቀለለው። አስካርሰን አሁንም ማርሹን አስገብቶ ነዳጅ ሰጠ። «አሁን፣» አለ፣ «አሁን ትንሽ ጠቅልለው።» ልጁ የመጠ ቅለያውን ቁልፍ ተጫነና ካቦው መጠቅለል ሲጀምር እያመቻቸ ይሰጠዋል። እያፈተለከ ነው አሰበ አስካርሰን፣ አሁን ያፈተልክና ነፃ እንሆናለን። ይህኛውም ካቦ ግን የብረት ያህል ተወጥሮ ጠጠረና ጀልባዋ ቆመች። «እጥፋው፣ ሞተሩን አጥፋው፣» ሲል ጮኸ። ልጁ ቁልፉን ሲነካው መዘውሩ ቆመ። «እዚያ ላይ ያዘው ሌላ ነገር ልሞክር።»

አስካርሰን ማርሹን አስገባና መረመን ወደግራ በኃይል አዞረው። «ከብ እንሰራና የመረቡን አቅጣጫ እንቀይረዋለን፣» አለው ለልጁ ጮክ ብሎ። «እንዲህ ካደረግን ከያዘው መሰናክል ይላቀቃል።» እንደሚሳካለት ተስፋ አደረገ። መረቡን በሌላ መተካት የብዙ ሺህ ክሮነር ዋጋ ይጠይቃል፣ ገንዘቡን የመድህን ዋስትናው በአብዛኛው ሊመልስለት ቢችልም፣ የብረት ማስመጪው ሲሰራ የጠፋውን ጊዜ ዋጋ እንኳን አይሸፍንም። ባለብረት መረብን ከሱቅ መግዛት አይቻልም።

ካቦውን ሳለመጨፍለቅ ጀልባዋን በሰፈው ከዞራት በኋላ ውጥረቱን ትንሽ ለማላላት ግራውን ይዞ ወደመሰናክሉ አቅጣጫ ወሰዳት። ለጥቂት ጊዜ ያህል መስመሩን ጠብቆ ቢነዳም፣ ጀልባዋ ግን ወደ ቀኝ መታጠፍ ጀመረች። የጀልባዋ ዘንግ በስተቀኝ ቢያዘነብልም መረውን ግን ወደ ግራ ወጥሮ ስለያዘው ይህ ሁኔታ ግራ አጋብቶት ጥቂት ቆየ። ጀልባዋ በሚገርም ሁኔታ፣ የጎንዮሽ ጉዞ ጀምራለች። ይህ ማለት ጠልፎ የያዛት ነገር ምንም ይሁን ምን እንቅስቃሴ ላይ ነው።

አስካርሰን መረውን ለቀቀና ወደጀልባዋ ኋለኛ ክፍል ማምራት ጀመረ። መረው ግን በፍጥነት ወደቀኝ በመሽከርከሩ፣ የጀልባዋ ድንገተኛ የአቅጣጫ ለውጥ ጀልባዋ ወለል ላይ አፈናጥሮ ጣለው። የተጠቀጠቀ ትከሻውን ይዞ እንደምንም ከወደቀበት ተነሳና «ቶሎ በል መረቡን በጥሰን መተው ይኖርብናል!» ሲል ለልጁ ጮኸለት። ጀልባዋ በተቃራኒ አቅጣጫ ተሽከርክራ ሦራችና አንድ መንገድ ያዘች። አሁን ወደኋላ እየተጎተቱ መሆናቸው ነው።

«ምንድን ነው፣ አያቴ? አለ ልጁ፣ ዋናውን መጠቅለያ የሙጥኝብሎ ይዞ። «ምን እየተፈጠረ ነው?»

«መጎተቻ ካቦውን ልቀቀው!» አለ አዛውንቱ፣ ወደጀልባዋ መቆጣጠሪያ አካል ለመሄድ እየተፍጨረጨረ። ልጁ በቶሎ ካቦውን ከመጠቅለያ ሞተሩ ላይ ፈታና ለቀቀው። አሁንም ግን ጀልባዋ ከቀድሞ ባየለ ፍጥነት ወደኋላ መጓጓቷን ቀጥላለች። በዚህ ሁኔታ የተደናገጠው አስካርሰን የኋላ ማርሽ አስገብቶ ነዳጁን እስከመጨረሻው ሰጠው። የመረቡ ካቦ እንዳይወጠር ማርገብ ይኖርበታል። ልጁ አስካርሰን ለማድረግ እየሞከረ ያለውን ወዲያው በመረዳቱ ወደዋናው መጠቅለያ አመራ። አሁንም ተጠምጥሞ ያለ ጥቂት ሜትሮች የሚገመት የመረቡ ዋና ካቦ ይታያል። አስካርሰን ጀልባዋን ወደኋላ አቅጣጫ ለማስያዝ እየጣረ፣ ኢቢ ከማኑዬያው ጋር ሲታገል ይመለከታል። ካቦውን መፍታት ከቻለ ስለሚረግብ ሊያሳቅቁት ይችላሉ፣ ከዚያ ነፃ ይሆናሉ።

http://ethzare.wordpress.com

ነገር ግን መጠቅለያው ላይ ከመጠን ያለፈ ጫና ስላረፈበት ማነቂያው ነክሶ ይዟል። ልጁ ትዕዛዝ ለመጠበቅ ሳያመነታ መጥረቢያ አምጥቶ ወደማነቂያው እጅታ ሲሰደው አስካርሰን ኮራበት። በእንድ ምት ነፃ ሲያደርገው መጠቅለያው በኃይል ተሽከረከረ። ጀልባዋ በአቷ ወደፊት ዘመም ስትል ሁለቱም ወለሉ ላይ ወደቁ። አስካርሰን ካቦው ዳግም ከመወጠሩ በፊት ለማላቀቅ ያለው ጊዜ ጥቂት መሆኑን በማወቅ ወደ መጠቅለያው ተወረወረ። ካቦውን ያዘና በእግሩ ተደግፎ ኃይል ለማግኘት ሲሞክር ድንገት የረገበው ካቦ ተወጠረ። ካቦው እና የመጠቅለያው ታንቡር መሀል የገባው እጁ ጠርመስ ማለት ሲጀምር በስቃይ ጮኸ። ለሰከንድ ያህል ይህ ነው የማይባል ህመም ከተሰማው በኋላ የካቦው ገበዎች እጁን እንደመጋዝ ሰርስረው ጣቶቹን ቆረጧቸው።

አስካርሰን ጀልባዋ ላይ ተመልሶ ወደቀና አሁን አውራ ጣት ብቻ የቀረውን ደም የሚተፋ ዱሽ እጁን በእግራሞትና በድንጋጤ ተመለከተው። በጀልባዋ ላይ እየተፈጠረ ስላለው አደጋ ሙሉ ለሙሉ ዘንግቶ በጀልባው ግድግዳ ላይ ወደተሰቀለው ቁርጥራጭ ገመዶችን የሚይዝ «የገመድ ቦርሳ» እያለ ወደሚጠራው የሸራ ቦርሳ ተፈተለከ። ወዲያው አጠር ያለ የናይለን ገመድ አውጥቶ እንድ ጫፉን በጥርሱ ይዞ እጁ መጋጠሚያ ላይ ጠመጠመውና ወጥሮ ቋጠረው። ይህን ሲያደርግ ህመሙ ከናካቴው ጠፍቶ ዱሽ እጁ እንግዳ በሆነ ሙቀት መተለትለቱ እየገረመው ነበር።

አሁን አትኩሮቱን ዳግመኛ ወደጀልባው አዞረ።በኋላ ማርሽ ሙሉ ሀይል ይዛ እየከነፈች ቢሆንም፣ ከጀልባዋ ፍጥነት በስምንት ወይ በዘጠኝ ኖት በማይል እየጨመረ በሚሄድ ፍጥነት እየተጎተተች ነው። ውሀ የጀልባዋን ኋለኛ አካል እያለፈ እያጥለቀለቃቸው ነበር። ኢቪ ከወደቀበት እየተደናበረ ተነሳ። አስካርሰን የሚያደርገው ጠፍቶት ተመለከተው። በባህር ላይ ሕይወቱን ያሳለፈው ይህን ሁሉ ጊዜ ይህን ለመሰለ ፍዙም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊያዘጋጀው አልቻለም። አሁን እስከ ጉልበቱ ድረስ በውሀ ተነክሯል። የጀልባዋ ፍጥነት የጓልዮሽ አስራ አምስት ኖት ደርሷል።

«ምንድን ነው? ምንድን ነው?» እያለ ልጁ ከውሀው ሽሽታ ድምፅ በላይ እየጮኸ ይጠይቀዋል።

አያውቅም። ካሁን በኋላ ብዙም እንደማይቀጥል ግን ታውቆታል። ከዚያም ለሀሳቡ ምላሽ ይመስል፣ ከመጠን ያለፈ የብረትና የእንጨት መወጣጠር ድምፅ ተሰማ። የመጠቅለያውን የስረኛ አካል ከጀልባዋ ጋር ካገናኙት ብሎኖች ሁለቱ አፈትልከው ወጡ።

«ኢቪ!» ጮኸ «ዞር በል! መጠቅለያው ሊፈናጠር ነው!»

«ምን?» ልጁ መልሶ ጮኸ። አሁን ግራ እንደተጋባ ነው። «ምን?»

አንድ የመጨረሻ የመገንጠል ድምፅ ተሰማና መጠቅለያው የታሰረበት የጀልባዋ ወለል አካል በሙሉ ተገንጥሎ ተነሳ። እየተጎተቱበት ባሉበት ካቦ የተያዘው መጠቅለያ ሞተር ከጀልባዋ ኋላ ተፈናጥሮ እየበረረ ልጁን ሙሉ በሙሉ ፈቱ ላይ አገኘው።

ከዚያ ግን ሁሉ ነገር ድንገት፣ በማይታመን ፀጥታ ተዋጠ ጀልባዋ ከመቅፅበት ቆመችና ባህሩ መሀል መወዛወዝ ጀመረች። ከጀልባዋ ኋላ የሚጎተተው መጠቅለያና መረብ ውሃው ውስጥ ገብተው ጠፉ። የጀልባዋ ሞተር በውሀ ተጥለቅልቆ መስራቱን አቁሟል። አስካርሰን ታፋው ላይ ውሃ ውስጥ

ሰምጦ ቆሟል። በቶሉ የኤቪ በድን እካል ዙሪያው በቀይና ግራጫ ነገር ተከቦ ወደሚንሳፈፍበት ሄደ። አስካርሰን ልጁን ክንዶቹ ላይ ተሸክሞ ከውሀው ጥቂት ብቅ ባለው የጀልባዋ የጎን መደገፊያ ላይ ተቀመጠ። ወለሉ በውሀ ቢጥለቀለቅም ጀልባዋ ግን ገና አልሰጠመችም። ከልጁ ራስ የተረፈው ጥቂት ነው። አስካርሰን የተዝለፈለፈውን በድን አቅፎ ይዞ ማልቀስ ጀመረ።

ከሞጋጉ ውስጥ ከማያውቀው ስፍራ የሌላ ጀልባ ሞተር እየቀረበው ሲመጣ ይሰማዋል ግን ግድም አልሰጠውም። ከአሁን በኋላ የልጁ ልጅን አሶች ያሉበትንና እንዴት እንደሚጠመዱ እያስተማረው የሚያሳልፈው ቀን አይኖርም። ከአሁን በኋላ የቀረው እርጅናንና ብቸኝነቱን እያስታመመ ወደሞቱ መጓዝ ብቻ ይሆናል። ሞቱን አሁኑኑ ተመኘው። እጁ መጋጠሚያ ላይ ያሰረውን ገመድ ሲስበው ተፈታ። ከጣት አልባ እጁ ጸጋመኛ ደም መንዠቅዠቅ ጀመረ።

አሁን አሳሽ ጀልባዋ ከሞጋጉ ወጥታ ፍጥነት ቀንሳለች። ከውሀው ወዲያ በከፍተኛ ማስተጋባት የኃላ ድምፅ ተሰማው። «የተከለከለ ስፍራ ላይ ነህ፣ በፍጥነት ከዚህ መሄድ አለብህ። እባክህ ተከተለኝ። በተከለከለ ስፍራ ላይ ነህ. . .» ከተጥለቀለቀው ጀልባ እጠገብ ስትደርስ ቆመች ድምፁም ፀጥ አለ። የድምፅ ማጉያ የያዘው ፀሀይ ያጠቆረው ፊት ያለው ወጣት የባር ሀይል መኮንን ከቅርብ ርቀት ላይ ተመለከተው። ፊቱ ገረጣ።

አስካርሰን የባህር ኃይሉን መለያ የለበሰውን በድንጋጤ የገረጣ ወጣት ቀና ብሎ ተመለከተውና «ገደል ግባ፣ ባህረኛው፣» አለው።

2

ሙሉ ሌተናንት ጆን ሄልደር የሚተለበስ ቅርፅ ባለው የዊስኪ ክላስ ባህር ሰርጓጅ መርከብ 184 ሰገነት ላይ ቆመና ትኩስ አየር ሳበ። ቀዝቃዛ ነው። የሶቭየት ሰሜናዊ የጦር መርከቦች የበላይ መምሪያ ከአርክቲክ ክበብ በላይ ነው። ሔልደር ባህር ሰርጓጇ መርከብ ወደቧን ይዛ ስትቆም በቅርበት ይመለከታል። ቀና ሲል አንድ፣ ሶስተኛ ደረጃ ማዕረግ ያለው ተስተካክሎ የተሰፋ የደንብ ልብስ የለበሰ ካፒቴንና ከአቋሙ ጋር የማይሄድ ሙሉ ልብስ የለበሰ ሌላ ሲቪል የወደቡን ደረጃ ወርደው የሱ ባህረተኞች ከምድር ጋር የሚያገናኘውን ትልቅ ጣውላ እየዘረጉ ወደነበሩበት ስፍራ ሲመጡ ተመለከተ። ሁለቱንም አያውቃቸውም። ሁኔታቸውንም አልወደደውም። በሶቪየት ባህር ኃይል ውስጥ በሶስትኛ ደረጃ ማዕረግ ካፒቴንና በፖለቲካ መኮንን አማካይነት የሚመጣ ቅጣት እንጂ ሽልማት አይሆንም።

ሔልደር መጀመሪያ ያሰበው፣ ምን አጥፍቶ ሊሆን እንደሚችል ነበር። በሰሜን አትላንቲክ ላይ ያደረገውን ይህን ጉዞ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ በነበረው ምሽት ከመኮንኖቹ ጋር ከመጠን በላይ መጠጥ ወስዷል፣ ግን ደግሞ ከመጠን በላይ የማይጠጣ ሰው የለም። በተለምዶ ከመኮንኖች ሁሉ እጅግ ጠንቃቃ በመሆኑ፣ ምናልባት ዜግነቱ ኢስቶኒያዊ ከመሆኑ ሌላ የሰራው ጥፋት አልታይህ አለው። ይህ የዜግነቱ ጉዳይ ግን እሱን ጥፋተኛ ለማስባል በቂ ነው።

ከሰገነቱ ወርዶ ሲቀበላቸው እኩል ተገማጠሙ። መርከቡ ላይ ለመውጣት ፈቃድ አልጠየቁም። «ካፒቴን ሔልደር ነህ?» ሲል የባህር ሀይል

http://ethzare.wordpress.com

ካፒቴይኑ ጠየቀው:: ታዲያ ሌላ ማን እሆናለሁ? አሰበ ሔልደር:: የሰውየው ደምፅ በቁጥጥር ስር ሊያውለው ላሰበው ወንጀለኛ የሚናገር ያስመስለዋል::

«አዎ፣ ጓድ ካፒቴን፣» መለሰ ሔልደር፣ በተጠንቀቅ ቆሞ ሰላምታቸውን እየመለሰ:: በዚህ ሁኔታው ወታደራዊ ደንቦችን ሲያከናውን ቂልነት ተሰማው:: ለአምስት ሳምንታት በደንቡ ገላውን ታጥቦም ሆነ ፂሙን ተላጭቶ አያውቅም:: በርግጥ እሱ ከበታቾቹ የተሻሉ የግልጋሎት ቁሳቁሶች የተሟሉለት በመሆኑ ይህን ማድረግ ባላቃተው ነበር:: ጸሩ ግን የበታቾቹ ካፒቴይናቸው እንደእነሱ ቆሻሻ ሲሆንላቸው ደስ ይላቸዋል::

«ሌኒንግራድ ወስጥ በሚገኘው የአባላት የበላይ መምሪያ ለዋና አስተዳዳሪ መኮንኑ ሪፖርት እንድታደርግ አሁኑኑ ታዘሀል፣» ብሎ ካፒቴይኑ፣ አንድ ፖስታ ሰጠው:: «ይህን ትዕዛዝ በፅሁፍ የሚያፀና እና ወደአባላት የበላይ መምሪያ የሚያስገባ የይለፍ ወረቀት ይኸውና::»

ሔልደር ፖስታውን ተቀበለ:: «አሁኑኑ» የሚለው ቃል አስገርሞታ:: ሊኒንግራድ የሚገኘው በስተደቡብ ስድስት መቶ ማይል ርቆ ነው:: «አመሰግናለሁ፣ ጓድ ካፒቴን:: ለመታጠብና ልብሴን ለመቀየር ቢፈቀድልኝ. . .» ሲፈጠር ኑሮ የነበረ ሽሚዝ ላይ ሙሉ ከጥጥ የተሰራ ቆሻሻ ልብስ ለብሷል:: ከዓይኖቹ ተግ በኩል ሔልደር አንድ ከባድ መኪና ከመሸጋገሪያው ጣውላ አጠገብ ሲቆም ተመለከተ:: መጥፎ ነበር::

«ለዚህ የሚሆን ጊዜ የለም፣ አሁኑኑ መሄድ አለብህ::»

«እንዴታ፣ ጓድ ካፒቴን:: ከክፍሌ የሚም ዕቃዬን ይገሬ ለመምጣት ቢፈቀድልኝ::

«የሚም እቃህ ለብቻው ይመጣልሀል፣» አለ ሲቪል የለበሰው፣ በጠራ ቃና::

«አረፍት ላይ ተደርገሀል፣ ሌቴናንት፣» አለ ካፒቴኑ::

የሔልደር ልብ ተስፋ ራቀው:: ሰውየው የጦር መርከብ አዛዥ ያደረገውን የካፒቴንነት የክብር ስሙን እንኳ «ካፒቴን» ብሎ ሊጠራ አልፈለገም:: ግን ደግሞ እረፍት ላይ ተደርጎ የለ:: አሁን ይህ ማዕረግ የሱ አይደለም::

«በል ቀጥል፣» አለ ሲቪል የለበሰው::

ከወታደራዊ ኃላፊነቶቹ እንፃር ከመኮንኖቹ ጋር እንኳን ሳይነጋገር ይህን መርከብ በዚህ ሁኔታ ትቶት መሄዱ ቢያበሳጨውም፣ ሔልደር ግን ደግሞ ሰላምታ ሰጠና በፍጥነት ወደ መሸጋገሪያ ጣውላው አመራ:: አንድ ባህረኛ ሰላምታ ሰጠው፣ ይህን ጊዜ ሔልደር ረጋ ብሎ፣ «ለበላይ መኮንኑ እረፍት ላይ መደረጌንና፣ ከዚህ በኋላ የሚኖሩትን መመሪያዎች አስመልክቶ የአዛዥነት ቦታው የሱ እንደሚሆን ንገረው::»

ወደከባድ መኪናው ሲቀርብ ጠባቂ ዘብ የሌለ መሰለው ስለዚህ በጎ ስሜቱን ለማጠንከር በማለት ከመኪናው ኋላ በመሳፈር ፈንታ ከሹፈሩ አጠገብ ገብቶ ተቀመጠ፣ ሹፈሩ ምንም ሳይናገረው መኪናውን ሙሉ ለሙሉ አዞረና ወደቡን ለቆ መንቀሳቀስ ጀመረ::

ከሀያአምስት ደቂቃ በኋላ ሙቀትና ቅዝቃዜን መከላከል በማይችል የመጓጓዣ አይሮፕላን ላይ ተሳፈረ:: ምልክት ከሌለባቸው አሽግ ሳጥኖች ሌላ ብቸኛ ተሳፋሪው እሱ ነበር:: ድምፁ ይሰቀጥጣል፣ መቀመጫም የለም፣

ትዝቃዜውም አያድርስ ነው:: በተነፈሰ ሕይወት አድን ጀልባ ላይ ተኮራምቶ ቆሻሻ መሀረቡን ጆሮዎቹ ውስጥ ጫፍና ጫፉን በመከተት ትንሽ እንቅልፍ ለማግኘት ሞከረ:: ሰመመን ውስጥ እየገባ ሳለ፣ እዚያው ወደቡ ላይ ለምን እንዳልገደሉት አሰበ:: ይህ ሁሉ ጭንቅ ለምንድን ነው?

አሁን ሁሉ ነገር አብቅቷል:: የአስራ ሶስት ዓመት የኮሌጅ ልምምዱ፣ የባህር ላይ ግልጋሎቱ፣ ያ ሁሉ በሰርጓጅ መርከቦች ውስጥ የሰራው እድካሚ ስራ መጪረሻው ይህ ሆኗል:: ከነበረበት የተሻለ ዘመናዊነት ባለው ሰርጓጅ ምናልባትም የታንጎ ደረጃ ባለው መርከብ ላይ እድገት አግኝቶ ሊሰራ ታጭቶ ነበር:: ውጤቱ በጣም ከፍተኛ ነው:: ከሁሉ የከፋ ሊገጥመው የሚችለው ሞት ቢሆንም፣ እሱን ወደሌኒንግራድ ወስደው አባላት መምሪያ ጋላፊ ዘንድ ለማቅረብ ይህን ሁሉ ውጣ ውረድ ማየታቸው ከሞት ማምለጡን ሹክ ብሎታል:: ፊጣን የጦር ፍርድ ቤት ክስ ይመሰርቱበትና ከማዕረግ አውርደው አስከፊ የሆነ ቦታ በዝውውር ይመድቡኛል የሚል ተስፋ ይዟል:: ባለው ዝቅተኛ የመጓጓዣ ዘዴ ስድስት ሺህ ማይል ርቀት ላይ ወደሚገኘው ቭላዲቮስቶክ ይልኩታል፣ የቀረውን ግልጋሎትም በወደቦች ላይ በጓዝ መኮንንነት ያሳልፋል:: በሶቭየት ባህር ኃይል ታሪክ ውስጥ እድሜ ጠገብ ምልክት ተደርጎ የሚታይ ይሆናል:: ከመድከሙ የተነሳ ግድ ሳይሰጠው እንቀላፋ::

አይሮፕላኑ ከማረፊያው ጋር ሲላተም ሔልደር ነቃ:: ምን ዓይነት እርኩስ አብራሪ ነው ሲል አሰበ:: ወዲያውኑ ተመልሶ ተኛ:: እምብዛም ክብር በማይስተዋልበት ቃና ስሙ ሲጠራና ቀዝቃዛ ንፋስ ሲቀበለው ደግሞ ነቃ:: አንድ የKGB ሀምሳ አለቃ አይሮፕላኑ በር ላይ ቆሞ እየጠራው ነው:: ሞተሮቹ ሲጠፉ ድምፁ ድንገት ማንባረቅ ጀመረ:: ሔልደር ቅፍፍ እያለው የብረት ደረጃዎቹን ወርዶ ወታደሩን በመከተል ወደአንደ ግዙፍ ሕንፃ አመራ፣ ዉልሟል ዝናብም ያካፋል:: ሔልደር ሰዓቱን ተመለከተ፣ ልክ እኩለ ለሊት አልቷል:: በአንድ በር ገብተው ደረጃዎች ወጡ:: በሌኒንግራድ የሲቪል አየር ማረፊያ ጣቢያ መሆኑን አወቀ:: ዘመናዊነትን በተላበሰው ንፁህና ባዶ ህንፃ ውስጥ በፍጥነት ይራመዳሉ:: ከሀምሳ አለቃውና ከሔልደር ሌላ የKGB የስደተኛ ተቆጣጣሪ መኮንኖቹን ኮስታራ ገፅታ በፈገግታቸው ለማሸነፍ የሚጥሩ ጥቂት የምዕራባውያን ሁኔታ ያላቸው ጎብኚዎች ህንፃውን ይጋራሉ:: የሔልደር አይኖች ለአፍታ ከአንዲት ቆንጆ ጉብል አይኖች ጋር ተጋጩ:: እንግሊዛዊት ትሆን? አሜሪካዊት? ጊዜ ኖሮት ይህን ማወቅ ቢችል ተመኘ:: አሁን የሚሄድበት ቦታ ቆንጆ ሴት ይቅርና ከናካቴው ሴት የሚባል ካገኛ ዕድለኛ ነው::

ሌላ ከባድ መኪና ጠበቀው:: ሔልደር በዝምተኛው ሀምሳ አለቃ ሳይረበሽ እያንሳላጀ ከተማ ገቡ:: አሁን የባህር ኃይል ኩሊጅ የሆነውን የጥንቱን የባህረተኞች ማሰልጠኛ ሲያልፉ ከእንቅልፉ ነቃ:: በልምድ ጊዜው በዚያ ቦታ የኤሌክትሮኒክስ ትምህርት መሰጫል:: አሁን የቅርስ ጥበቃ ሙዚየም አካል የሆነው የዊንተር ቤተመንግስት ፊት ለፊት የሚገኝ ትልቅ አደባባይ አልፈው፣ በዝናብ በራሱ እንፀባራቂ ጥርብ ድንጋዮች ላይ እየተንሸራተተ ወደ ጠቅላይ የአባላት መምሪያው የሚያዘልቀውን ግርማ ሞገስ የተጎናፀፈ ቅስት ዘለቁት:: ከባድ መኪናው በቅስቱ አልፎ ወደቀኝ ታጠፈና፣ ዋናውን መግቢያ በር አልፎ፣ ደግሞ ሌላ ኩርባ ከዞረ በኋላ በአንድ ዘብ ብቻ ከሚጠበቅ በር ፊት ሲደርስ ቆመ:: ሔልደር ሙርማክ ላይ የተሰጠውን ፖስታ ቀደደና የይለፍ ወረቀቱን

http://ethzare.wordpress.com

አወጣ። ዘቡ ወረቀቱን በጥንቃቄ መርምሮ፣ በይሁንታ ራሱን ወዘወዘለት ሰላምታ ከሰጠው በኋላ የሔልደርን ቆሻሻ ልብሶች ለማንጻጸሻ እፍንጫውን ነፍቶ ወደበሩ እመለከተው። ሔልደር የመኮንንነት መለዮ ባርኔጣውን ባያደርግ ኖሮ ይሀን ዘብ ማለፍ የማይችል መስሎ ተሰማው። ውስጥ ሲገባ የባህር ኃይሉን የደንብ ልብስ የለበሰች ሴት ተቀበለችው። «ካፒቴን ሔልደር፣ እባክዎን ይከተሉኝ።» ብላ ከጨዋነት በራቀ ለዛ እናገረችውና፣ በዚህ ምሽት ጥቂት መብራቶች ብቻ በበሩበት ረጅም ኮሪደር ላይ መራመድ ጀመረች።

ሌላው ቢቀር ዳግም «ካፒቴን» ተብሏል። ምናልባት ተሳስታ ይሆናል። ኩቶዳ የተሰራው የታኮ ሚማዋ ሜፍ የሩሲያ ነገስታት ያስነጠሱት ሽክላ ላይ እያረቆ ሲያንቃጭሉ የቡ ለመርከብ ሽራ የተሰራ ባለ ሳስቲክ ሶል ጫማ ከጠጣሩ ወለል ጋር እየተፋጨ ሲያንቃጭሉ እያቀለጠው ልክ እንደውሻ ቡችላ ድክ ድክ እያለ ተከተላት። የተለያየ ግልጋሎት ያላቸው ቢሮዎች የተዘጉ በሮችን እያለፉ ቢያንስ አንድ ኪሎ ሜትር የተጓዙ ያህል ተሰማው። የባህር ኃይል መኮንኗ ከመጡበት ሰፋ ወደሚል ሌላ ኮርደር ታጠፈችና በሩ ላይ «ዋና አስተዳዳሪ መኮንን» የሚል ጽሑፍ የሰፈረበትን በር አልፋ ገባች። ከጠረጴዛው ጀርባ የተቀመጠች ሌላ ሴት መግባት እንደምትችል በምልክት ስታሳያት እርምጃዋን ሳትገታ ማረፊያ ክፍሉን እቋርጣ የውስጥ በሩን አንኳኳች። አንድ ድምፅ እንድትገባ ፈቀደላት። በሩን ከፍታ፣ ሔልደር እስኪገባ ጠበቀችውና ተከትላው በመግባት በሩን በዝግታ መልሳ ዘጋችው። አጭርና ወፍራም የባህር ኃይሉ ከፍተኛ ባለስልጣን (ኮንትራ - አድሚራል) ከግዙፉ ጠረጴዛ ጀርባ ተቀምጠ እንድ ማህደር ያነባል። ምናልባት ክሰቹን ይሆናል።

ሔልደር ፊቶ ቆመና ሰላምታ ሰጠ። «ጓድ አድሚራ፣ እኔ የበላይ (ሙሉ) ሌቴናንት ሔልደር እንደታዘዝኩት ሪፖርት እያደረግኩ ነው።»

አድሚራሉ ተመለከተውና ተኮሳተረ። «አፈር ትመስላለህ።» አለው።

«በጣም አዝናለሁ፣ ጓድ አድሚራሉ፣ ጊዜ አልነበረም. . .»

«እንዴታ እንዴታ።» አለ አድሚራ ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አንድ ፖስታ አውጥቶ ለሔልደር እያቀበለው። «የምታመለክተው (ሪፖርት የምታደርገው) ሳይታጃ ውስጥ ለሚገኘው ልዩ ብርጌድ አዛዥ መኮንን አሁኑኑ ይሆናል፣» አለና ሐሳቡን በመለወጥ። «መልካም አሁኑኑ አይሁን። አንድ ሰዓት ያህል ቢኖርህ ለውጥ አያመጣም።» መሳቢያውን ከፍቶ፣ የታተመ ጥራዝ አውጥቶ ፈረመበት። ገፁን ገንጥሎ አነሳውና ለሴቲቱ ሲሰጣት፣ ወደፊት ራመድ ብላ ተቀበለችው። «ወደበላይ መምሪያው ዲፓ ውሰጂው፣ ሀምላ አለቃውን ቀስቅሺውና ጥሩ የደንብ ልብስ ስጪው። ገላውን ታጥቦ ሂሙን እንዲላጭም አድርጊው።» አድሚራሉ ወደመሳቢያው እጁን ሰደደና ጠርሙስ ቮድካና ብርጭቆ አወጣ። ደረቁን መጠጥ ከቀዳ በኋላ ለሔልደር እየሰጠው፣ «ይህ የሚያስፈልግህ ትመስላለህ።» አለ።

ሔልደር መጠጡን በአንድ ትንፋሽ ጨለጠና ብረጭቆውን ጠረጴዛው ላይ መልሶ፣ «በጣም አመሰግናለሁ፣ ጓድ አድሚራል። አንድ ነገር መጠየቅ እችል እንደሆነ. . . »

«አትችልም፣» ሲል መለሰ አድሚራል። «ከዚህ ውጣ።»

ምንም ዓይነት የጦር ፍርድ ቤት ችሎት እንደማይኖር ተሰማው፣ ከማዕረግ ስለመውረድም የተነሳ ነገር የለም። ቢሆንም ግን ለይታጃ ምን አለ?

ላትቪያ ውስጥ ምን እንዲያደርግ ነው የሚልኩት? እዚያ ባህር ሰርጓጅ መርከቦች የሉም። የባልቲክ ጦር መርከቦች ጦር ሰፈራቸው የሚገኘው ባልቲስክ፣ ሊትዋኒያ ውስጥና ፖላንድ ድንበር አቅራቢያ ነው። ላይታጃ ውስጥ የወደብ መኮንን ያደርጉታል። ያም ሆነ ይህ የቭላዲቮስቶክን ያህል አይሆንም። ቢያንስ የትውልድ ሀገሩ የገባ ያህል ይሰማዋል፣ ይህም ግን በጣም እንግዳ ነገር ነው። ከኢስቶኒያ፣ ከላቲቪያ እና ከሉትዌኒያ የሚመጡ መኮንኖች ያለልዩነት በሶቪየት ሕብረት ሌሎች ክፍሎች እንዲመደቡ ይደረጋል። የፖሊት ቢሮው በእነዚህ ግለሰቦች እጅም እምነት የለውም። በቂ የሩሲያዊ ዜግነት የላቸውም ስለዚህ በሰራዊቱ ውስጥ የሚያገለግሉት የእነዚህ ሰዎች ወጣት አባላት የሩሲያዊነት ሀገር ፍቅራቸውን የሀገር ቤት ፍቅር ሳያሸንፈው በሚኖሩባቸው ስፍራዎች ላይ ይመደባሉ።

ሔልደር ለአድሚራል ሰላምታ ሰጠና አሁንም ሴትየዋን ተከትሎ መንገድ ጀመረ። ከአንድ ሰዓት ተኩል በኋላ ዒሙን ተላጭቶና ተጣጥቦ አዲስ የደንብ ልብስ ለብሶ ሌላ አይሮፕላን ላይ ተሳፈረ። ይህኛው ግን መቀመጫና ሙቀት መስጫ ነበረው ላይታጂ ደርሰው ከማረፋቸው በፊት የአንድ ሰዓት እንቅልፍ ጨመረ። ሲወርድም መኪና ተቀበለው፣ ሌላ መሻሻል። አሁን አራት ሰዓት ከጠዋቱ ሆኗል ዳግመኛ እንቅልፍ ሳይወስደው በፊት ለማረጋገጥ የቻለው አቅጣጫቸውን ወደባህሩ ማቅናታቸውን ብቻ ነበር።

በከባድ ሁኔታ ጥበቃ ከሚደረግለት አንድ በር ፊት ደርሰው ሲቆሙ ነቃ። ከመግቢያቸው በፊት የይለፍ ወረቀቱና ፊቱ በጥንቃቄ ተመረመረ፣ ዘቡም አልቀረለትም። በተሰተካከለ ውሀ ልክ ድንጋይ ንጣፍ በተሰራው መንገድ የባልቲክን ባህር ወደታች ከሚመለከት ኮረብታ ቁልቁል መኪናውን ይዘው ጉዞ ቀጠሉ። ከፊትለፊታቸው በስተግራ ማዕበል የሚበዛበት ሀይቅ ይታያል። ሀይቁ በቀጭን ቦይ መሳይ መገናኛ ከባህሩ ጋር ተገናኝቷል። ገና ማንባታቸው ያለቀ እና በማንባታ ላይ የሚገኙ ብዙ ሕንፃዎችን አለፉ። በኮረብታው ቁልቁል ጉዞዋቸውን ሲቀጥሉ፣ ሄልደር የውሀው ጫፍ ብሉ ያሰበው ነገር፣ ከውሀው ፊት ለፊት የሚገኝ ጠፍጣፋ ማሪያ ያለው ሕንፃ መሆኑን ተገነዘበ። ያታለለው ነገር የጣሪያው ጫፎች ወደላይ የተቆለመሙ በመሆናቸው ውሀ እቅፈው ስለያዙ ነበር። በጣም ብዙ በልህት እንደወጣበት ታሰበው። በሳተላይ ፎቶግራፍ ላይ ህንፃው የባህረ ሰላጤው አንድ አካል ሆኖ ነው የሚታየው። በክረምት ወቅት ደግሞ ጥሩ የበረዶ መንሸራተቻ ሜዳ ሆኖ ሊያገለግልም ይችላል።

እስካሁን ያለፏቸው ሕንፃዎች ሁሉ እንግዳ ምዕራባዊነትና የከተማ ዓይነት አሰራር ይታይባቸዋል። የብዙ ሱቆች ስብስብ ተመለከተ ፣ተለመደውን ትንባሆና ቮድካ የሚነግዱ የባህር ሀይል መደብሮች ብቻ ሳይሆኑ፣ የነዳጅ ማደያ ጣቢያም አለ። ተመሳሳይ መጠን ካለው ሌላ ከተማ ይልቅ መኪኖች ቢበዙበትም፣ ከሲቪል መኪኖችና ከባድ ተሽከርካሪዎች ሌላ ምንም ዓይነት የሰራዊት ተሽከርካሪዎች አላየም። ትምህርት ቤት ቢኖርም፣ ልጆች የሉም የእለት ገቢያቸውን ሊያከናውኑ ዘምቢል ይዘው የወጡ የቤት እመቤቶችም የሉም። ቦታው የወታደር ጦር ሰፈርም ሆነ ተራ ከተማ አይመስልም። መድረሻቸው ላይ ከመቆማቸው በፊት አንድ የመጨረሻ ነገር አትኩሮቱን ሳበው። መኪናቸው አንድ የስፖርት መዓከልን አልፎ ሄደ። መዓከሉ ከዚህ በጣም በሚሰፋ ከተማ ውስጥ ቢሆን ተገቢ ቦታውን ባገኘ ነበር። ያለጥርጥር

http://ethzare.wordpress.com

ጂምናዝየምና የመዋኛ ገንዳ ይይዛል። እስከውሀው አጠገብ ሰላሳ ስድስት የቴኒስ መጫወቻ ሜዳዎችን ቆጠረ። እነዚህን አልፎ ረጃጅም የሬዲዮ መቀበያ አንቴናዎች ጫካ መስለው ተገተግጠዋል። ይህ ማለት ግዙፍ የባህር ላይ ሬዲዮ መልዕክትን ከመርከቦች የሚቀበል ጣቢያ አለ ማለት ነው። መኪናዋ እንስተኛ የቪሮ ህንፃ ፊት ደርሳ በቆመች ጊዜ በሶቪየት ህብረት ውስጥ ልዩ መብት ካላቸው ሰዎች መሀል እንዱ መሆኑ ታሰበው። የኮማንደርነት ልዩ መብቱ መሆኑ ነው። ከመኪናው ሲወጣ ይህ እውነታ ተገልያ ታየው። እሱን ለመስሉ ግለሰቦች ብቻ በሚፈቀደው መኪና መቆሚያ ቦታ፣ አዲስ ብርማ ቀለም ያላት 500 SE ሜርሰዲስ መኪና ቆማለች። አንድ ጊዜ ሞስኮ ውስጥ መሰሏን ተመልክቷል።

በሩ ላይ አጭርና ቀጭን በጣም ውብ የሰራዊቱ ሃምሳ አለቃ ተቀብላው ወደህንፃው አጅባ አስገባችው። ሲገባ፣ ሌላ ሀገር ያለ መሰለው። ከሚመለከተው የትኛውም ከሶቭየት የመጣ አልመሰልዕ አለው። እግር የሚያርፍበት ምንጣፍ፣ በነሀስ የተለበጡት ባለመስታወት በሮች፣ እንዲሁም የህንፃው ግንባታ ደንብ ከሶቭየት የቅርብ ዓመታት የግንባታ ጥረቶች ለየት ያለ መልክን የያዙ ናቸው። የቦታው ድባብ ሰላድኔቪያዊነት እንደሚታይበት ገመተ። ሌሎች ተመሳሳይ ባለመስታወት በሮችን ካለፉ በኋላ አስር ወይ አስራ አምስት የሚሆኑ ጠረጴዛና ወንበሮችን ወደያዘ ገላጣ ስፍራ ደረሱ። የዕሕፈት መሳሪያዎቹ የ IBM አርማ አላቸው። ከጊዜያቸው ቀድመው የተፈበረኩ የሚመስሉ ስድስት የሚሆኑ የኮምፒውተር መቆጣጠሪያዎችን ተመለከተ። ከሁሉ በላይ የማረከው ግን የወጣት ሴቶቹ ሁኔታ ነበር። የተለያዩ የሶቪየት የስራ መስኮች ላይ የሚለበሱ የደንብ ልብሶችን ለብሰው ተቀምጠዋል የተቀፋትም በክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ይላሉ። ሁሉም ባለወርቅማ ፀጉር ሲሆኑ፣ ሁሉም ሽንቃጣ ተክለ ሰውነት አላቸው፣ ከመካከላቸው አስቀያሚ የሚባል የለም። በሶቭየት ሰራዊት ውስጥ የሚገኙ ሴቶች እንደደንብ ኮስታራ ብጤ ናቸው። ሔልደር በሶቭየት ሕብረት ውስጥ ሆኖ ይህን ያህል ብዛት ያላቸው ውብ ሴቶች ያሉበት ክፍል ገብቶ አያውቅም። ሳይፈልገው በውስጡ ስሜቱ ሲቀሰቀሰበት ተሰማው። አምስት ሳምንት ሙሉ ባህር ሰርጓጅ መርከብ ላይ ካሳለፈ በኋላ እንዲህ ዓይነት ነገር መመልከት ከአቅሙ በላይ ሆነበት።

አንስተኛ መጠን ወዳለው የመቀበያ ክፍል አልፈው ገቡ። ሔልደር ሴቶቹን ለትንሽ ሲመለከት ለመቆየት እዚህ እንዲጠባበቁ ቢደረጉ ተመኘ፣ ግን አልሆነለትም። ፍጥንታቸውን ሳይቀንሱ በፀሐይ ብርሀን ወደደመቀ አራት መዓዘንማ ክፍል ገቡ። ከፊት ለፊቱ ባለመስታወት ጠረጴዛ ተመለከተ፣ ከበስተጀርባው ያለው ግድግዳ በሁለት በጣም ሰፋፊ ጥቁርና ነጭ ካርታዎች ተሸፍኗል። አንደኛው የባልቲክ ባህር የመርከብ መስመሮች የሚያሳይ ቻርት ሲሆን ሌላው የስዊድን ካርታ መሆኑን ገና ሲመለከታቸው አወቀ።

ከጠረጴዛው ጀርባ የተቀመጠ ሰው የለም። አትኩሮቱ ግን ወደበስተቀኝ ተንጣጠረና፣ ከቆዳ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች ላይ አረፈ። ከወንበሮቹ በአንደኛው ላይ የጦር መርከቦች ዋና አዛዥ (አድሚራል) ማዕረግ ያደረገ የባህር ኃይል መኮንን ተቀምጧል። ሔልደር በተጠንቀቅ ቆሞ ሰላምታ ሰጠ። «ዋና ሌተናንት ሔልደር፣ በትዕዛዝ መሰረት ሪፖርት እያደረግኩ ነው፣ ጓድ አድሚራል።» አለ።

አድሚራል ወደፊት ጎንበስ ብሎ በትልቅ መኮስተሪያ ላይ የያዘውን ሲጋራ አጠፋው። «ለኮሎኔሉ ሪፖርት አድርግ፣» አለ። ሔልደር በስተቀኙ አሻግሮ ሲመለከት የባህርና የምድር እግረኛ ሰራዊት የደንብ ልብስ የለበሰ ኮሎኔል ተቀምጠ አስተዋለ።

ሔልደር ከአድሚራሉ ባገኘው አክብሮት አልተገረመም። በሶቪየት ጦር ውስጥ ልክ እንደምሰራባቸያኑ ሁሉ፣ ማንኛውም አይነት ስልጣን የሚጠይቀው ከፍተኛውን እንጂ አናሳውን ማዕረግ አይደለም፣ የአንድ ጦር መኮንን ደረጃ የሚወሰነውም በማዕረጉ ሳይሆን በያዘው ስልጣን ይሆናል። በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት አንድ ዋና ሌቴናንት አንድን የሰራዊቱን አካል እየመራ፣ ግን ከበታቹ ያሉት የእዝ መሪዎች የሚጀር ወይንም የኮሎኔልነት ማዕረግ ያላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ሔልደር ያውቃል። ዳግመኛ ሰላምታ ሰጠ፣ «ሌቴናንት ሔልደር፣ ለጓድ ኮሎኔል ሪፖርት ያደርጋል።»

አድሚራል ተነሳ። «እሺ፣ ነገሩን ለአንተ ትቼዋለሁ፣ ቪክቶር፣» አለና ለኮሎኔሉ ተናግሮ ወጣ።

ኮሎኔሉ በእጁ ምልክት ሰጠው፣ ግን አድሚራል ሲወጣ ከመቀመጫው አልተነሳም። አድሚራሉ ከሄደ በኋላ ኮሎኔሉ ተነስቶ ወደ ሔልደር አመራ። ረጅም ሽንቃጣና ብቁ ተክለ ቁመና ሲኖረው በአርባዎቹ መጀመሪያ ላይ ይገመታል። ወጣ ያለ ግንባርና ጥቅጥት ብሉ በሶቭየት ጦር ወስጥ ከተለመደው በተሻለ ተስተካክሉ የተቆረጠ ቀይና ነጭ ፀጉር አለው። ሔልደር የሶቭየት ጦር የደንብ ልብስ የለበሰ ሀብታም ምዕራባዊ ነጋዴ ይመስላል፣ ብሎ አሰበ። ኮሎኔሉ እጁን ዘረጋለት።

«ማጆሮቭ እባላለሁ፣ ስላገኘሁህ በጣም ደስ ብሎኛል፣ ሔልደር።» አለ በታረቀ የብሪታኒያ እንግሊዝኛ ቃና።

ሔልደር እንግዳ ሆነበት። ከዚህ በፊት አንድ አዲስ አዛዥ መኮንን በእንግሊዝኛ ይቅርና፣ በዚህ አኳኋን ሰላምታ ሰጥቶት አያውቅም። ፈራ ተባ እንደማለት እየቃጣው የኮሎኔሉን እጅ ጨበጠ።

«እባክህን ተቀመጥ፣» አለው፣ ወንበር እያሳየው።

በሶቭየት ጦር ውስጥ በስልጠናና በግልጋሎት ካሳለፋቸው አስራሰስት አመታት ያተረፈው ልምድ ግን ይህን ሀሳብ በቀላሉ እንዳይቀበል ከለከሉት። ማንገራገሩን በግልፅ ተመልክቶ ይመስላል፣ ኮሎኔሉ ከት ብሎ ሳቀ።

«እባክህን፣» አለ፣ «ከደንብ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎችን መልመድ መጀመር ይኖርብሀል።» ብሎ ዳግመኛ ወደበሩ አመለከተው።

ሔልደር ተቀመጠ። ግን ወዲያውኑ ጀርባውን ከመደገፊያው ጋር ለማነካካት አልደፈረም።

«መጠጥ ያስፈልግሀል?» ኮሎኔሉ ጠየቀ። «ጂን በቶኒክ፣ ምናልባት? እባክህ መጠጥ ውሰድ።»

«አመሰግናለሁ ጓድ ኮሎኔል።» ኮሎኔሉ ተንስቶ ከምርጥ እንጨት የተሰራ ካቢኔት ከፍቶ መጠጡን አቀላቅሎ ሰጠው። ሔልደር እያመነታ ተሳነጨው። መጠጡ ውስጥ ብሩህ አረንጓዴ የተሰነጠቀ ኮምጣጤ መኖሩን ሲመለከትማ ለኮሎኔሉ ያለው አመለካከት የበለጠ ሽቅብ ተመነጠቀ። ሳትቪያ ውስጥ ኮምጣጤ ማስገባት የሚችለው ይህ ኮሎኔል ማን ቢሆን ነው?

http://ethzare.wordpress.com

ኮሎኔሉ ለራሱ መጠጥ ቀላቅሎ እዘጋጀና ከፊት ለፊቱ ተቀመጠ። «አሁን፣» አለ፣ በስሱ ፈገግ እያለ፣ «ስለራስህ ንገረኝ - ስለጓላ ታሪክና ስለአስተዳደግህ። እባክህ በእንግሊዝኛ መናገርህን ቀጥል።»

ይህንን ሔልደር ከዚህ በፊት በአንድ አዛዥ መኮንን እንዲፈጽም ተጠይቆ አያውቅም። ከዚህ በላይ ያስገረመው በመኳከላቸው ባለው ትንሽ የቡና ጠረጴዛ ላይ ከልጅነቱ ጀምሮ ያለውን እያንዳንዱን የሕይወቱን ዝርዝር ጉዳይ ለመያዙ ርግጠኛ የሆነበት ጸጥስ ያለ ማህደር መቀመጡ ነው። ምናልባት ኮሎኔሉ እንግሊዝኛ ሊናገር ሊሰማው ፈልጎ እንደሚሆን ታወቀው። «ጓድ ኮሎኔል፣ ሙሉ ስሜ ጃን ሔልደር ይባላል፣ የመሀል ስም የለኝም፣ የተወለድኩት ታሊን ውስጥ ኢስቶኒያ ባህር ጸርቻ ላይ ነው። ሰላሳ አንድ አመቴ ነው። የእንደኛና እ . . የሁለተኛ እ . . ደረጃ ትምህርቴን ያጠናቀቅኩት ታሊን ውስጥ ነው። ከዚያም ሞስኮ በሚገኘው ዩኒቨርስቲ ውስጥ እንግሊዝኛና ፈረንሰ አጠናሁ። ባደግኩበት ባህር ጸርቻ ላይ በተለምዶ የሚነገረውን ስዊድንኛም እናገራለሁ። ከተመረቅኩ በኋላ በራሴ ጥያቄ መሰረት ሌኒንገራድ በሚገኘው የባህር ኃይል ኮሌጅ ተመደብኩ። ከዚያ ከተመረቅኩ በኋላ ሙርማንስክ ላይ በሚገኘው የሰሜኑ ጦር መርከቦች ዕዝ ላይ ተመደብኩ። ለሁለት ዓመታት በጠቅላላ ግዳጆች ላይ ከቆየሁ በኋላ በባህር ሰርጓጅ መርከብ ላይ ለመሰልጠን ተቀባይነትን አግኝቼ፣ ይህን ሳጠናቅቅ በተከታታይ የዊስኪና የጁልየት ደረጃ ባላቸው ሰርጓ መርከቦች ላይ እየተመደብኩ ቆየሁ። ሞስኮ በሚገኘው የእዝ አካዳሚ ውስጥ አንድ ዓመት ከለለጠንኩ በኋላ ወደጦር መርከቦች ዕዝ ተመለስኩ። በጁሊየት መርከቦች ላይ በጉዞ አቅጣጫ ነዳፊና በዋና መኮንንነት አገለገልኩ፣ ካለፉት ሀያ ወራትም ዊስኪ 184 ሰርጓጅ መርከብን በአዛዥነት መርቼያለሁ። ግዳጁ የልምምድ እንቅስቃሴዎችን ማካሔድና በሰሜን አትላንቲክ ላይ የሚደረጉ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅትን (ኔቶ) የመርከብ እንቅስቃሴዎችን ሪፖርት ማድረግ ነበር።»

ኮሎኔሉ በግርኝ ራሰን ከፍ ዝቅ አደረገ። «በጣም ጥሩ፣ ሔልደር፣ ትንሽ ጠጠር ይላል እንጂ የአሜሪካዊ አነጋገር ለዛህ ግሩም ነው።» ብሎ ኮሎኔሉ ተስተካክሎ ተቀምጠ ከመጠጡ ተጎነጨ። «በእርግጥ አሁን የነገርከኝንና ሌላም ብዙ ነገር አውቃለሁ። ሁለቱም ወላጆችህ የሕክምና ባለሞያዎች መሆናቸውን፣ አባትህ ለናዚ በነበራቸው ተቃውሞ መሸለማቸውንና፣ እናትህ ደግሞ ብቃት ያላቸው ሰዓሊ እንደነበሩ አውቃለሁ። በ1976 አሎምፒክ ውቅት በነፋስ በሚገፋ የጀልባ ቡድን ውስጥ ሰፍራ እንደነበረህና፣ ግን ሌኒንግራድ ወሰጥ ታክሲ ነጭተህ ግራ ታፋህ ላይ የመሰነጣጠቅ አደጋ ስለደረሰብህ ለመወዳደር ሳትችል መቅረትህን አውቃለሁ። እንደእውነቱ፣ አንተም እንደምትገምተው ስለአንተ የማላውቀው ነገር የለም። ባይሆን ኖሮ እዚህ ባልተገኘህ ነበር።»

«ስለአመኔታዎ አመሰግናለሁ፣ ጓድ ኮሎኔል፣» መለሰ ሔልደር።

የኮሎኔሉ ቅንድቦች ወደላይ ተወረወሩ። «እ፣ አትኩሮቴን እንጂ፣ ገና አመኔታዬን አላገኘህም ሔልደር። ከማህደርህ እንደተረዳሁትም እዚህም ቢሆን ጥሩ ነገር እንደምትሰራ አልጠራጠርም።»

«አመሰግናለሁ ጓድ ኮሎኔል።»

«አሁን፣ ሔልደር፣ ምናልባት ስለእዚህ ቦታና እዚህ ስለምታደርገው ትንሽ ማወቅ የምትፈልግ ይመስለኛል።» ብሎ ተነሳና ክፍሉ ውስጥ

እየተንሳራደደ መናገር ቀጠለ። «እዚህም ሆነ የትኛውም ስፍራ አዛዡ እኔ ነኝ። ይህ የስፔትስናዝ መዋቅር ነው፣ ይህን ቀድመህ ገምተህ ሊሆን ይችላል።»

ሔልደር ይህን አልገመተም። ብዙ ፍንጮች ቢኖሩትና የደስታና የፍርሀት ጥምር ስሜቶች ሰንገው ቢይዙትም ቅሉ ይህ አልተከሰተለትም።

ስፔትስናዝ፣ የባህር ኃይሉ ልዩ ጦር በሶቪየት ባህር ኃይል ውስጥ ሳይቀር በጥንቃቄ የሚጠበቅ ምስጢር ነው። ሔልደር ስለዚህ ሀይል የሚያውቀው ነገር ቢኖር ከሶቪየት ወጣቶች መሀል በእውቀታቸውና በአካል ብቃታቸው ተለይተው ከተመረጡ ወንዶችና ሴቶች የተዋቀረ ልዩ ሀይል መሆኑን ብቻ ነው። ብዙ ዓይነት አስቀያሚ ስራዎችን እንዲከውኑ የሰለጠኑ የመሆናቸው ወሬ ይናፈሳል። በመርህ ደረጃ ይህ መዋቅር የባህር ሀይሉ አንድ አካል ቢሆንም፣ ቢያንስ በከፊል የሚቆጣጠረው ግን የKGB ስላላ ድርጅት ነው።

ማጆሮቭ ገለፃውን ቀጠለ። «አራቱም ማለትም የሰሜኑ፣ የፓስፊኩ፣ የባልቲኩ እና የጥቁር ባህሩ የጦር መርከቦች ዕዞች እያጸንጸቸው የየራሳቸው የተለያዩ የስፔትስናዝ ንዑስ ክኖሎች አሏቸው። እዚህ ላይፓጃ ውስጥ ያለነው ግን ከሁሉም የጦር መርከቦች ዕዝ ንዑስ ክፍሎች ከተመረጡ አባላት የተዋቀረ ልዩ ብርጌድ ነን።» ብሎ ማጆሮቭ ወደፊት ጠጋ አለ። «እዚህ ያለነው፣ የሁሉም ስፔትስናዝ ንዑስ አካላት የንጥር ንጥሮች ነን፣ ብሎ ማለት ይቻላል።»

ሔልደር ስለተደመመ ነገሩን በሀሊና ለመሳል ሞከረ።

«ወደዚህ መዘዋወርህ አሁን እንተ ስፔትስናዝ ሆንክ ማለት አይደለም፣» ቀጠለ ማጆሮቭ። «አሁንም በሰሜናዊው የጦር መርከቦች ኃይል ውስጥ ተደርገህ ትታያለህ፣ ምንም እንኳን አሁን በሶስተኛ ደረጃ የካፒቴንነት ማዕረግ ላይ የተወሰኑ ሰዓታትን ብታገለግልም ማለት ነው። እንኳን ደስ ያለህ።»

«አመሰግናለሁ፣ ጓድ ኮሎኔል።» ሔልደር ስሜቱ አፈትልኮ ሊወጣ ምንም አልቀረው። የባር ሰርጓጅ ጠቅላይ አዛዥነት ስልጣን የመጀመሪያ ደረጃ ካፒቴንነት ማዕረግን አቅፎ የያዘ ነው። ከዚህ ሌላ በዋና ሌተናንትነት ረጅም ጊዜን በብቃት አገልግሏል። አሁን አንድ ማዕረግ ዘሏል። የሶስተኛ ደረጃ ካፒቴንነት ማዕረግ በምዕራባዊያኑ ከሙሉ አዛዥነት ጋር ተመሳሳይ ነው። በአንድ የደረጃ እድገት ብቻ የክፍል ጓደኞቹን ሁሉ ደርሶ አልፏቸው ሄደ ማለት ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ተሰምቶና ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ፣ ይህ ሹመት የተሰጠው በተልዕኮው መጀመሪያ ላይ ነው።

«ከዚህ ሌላ ለክፍለ ጦር አዛዥነትም (ዲቪዥን ኮማንደር) ተመልምለሀል።» አለ ማጆሮቭ።

የሔልደር ልብ ዳንኪራ ደለቀ። ክፍለ ጦር ማለት የኔውክሌር ባህር ሰርጓጆች ማለት ነበር። መርከቦቹ በብርጌድ በብርጌድ ሆነው ይመደባሉ።

«ግን እዚህ ቦታላይ ማዕረጋችንን አንጠቀምም፣ <ጓድ> እየተባባልንም አንጠራራም፣ «አለ ማጆሮቭ። «እኔን <ኮሎኔል> እና <ጌታዬ> እያልክ መጥራት ልትቀጥል ትችላለህ። ሌሎችን ሁሉ ግን በቤተሰብ ስማቸው ትጠራለህ። አጋር መኮንኖችህን በደንብ በምታውቃቸው ጊዜ በስማቸው ትጠራቸዋለህ፣ ዝቅተኛ ማዕረጋቸውን የሚጠቁም ቃል አትጠቀምም። ግልፅ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ፣ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።»

«እም ኮሎኔል።»

http://ethzare.wordpress.com

«እዚህ ካሉት ባልደረቦችህ ሁለት ሶስተኛውን የሚሆኑት ስዊድኒኛና እንግሊዝኛን እንደእንተው የሚናገሩ ናቸው፣ የተቀሩት እንግሊዝኛና ምናልባት ሌላ አውሮፓዊ ቋንቋ ይናገራሉ። የስልጠናና የግል ጉዳይን በተመለከተ፣ አሰልጣኝህ ሩሲያኛ ብቻ የሚናገር ካልሆነ በስተቀር እንግሊዝኛን ለንግግር ተጠ ቀምበት። እንግሊዝኛህን ወደ አሜሪካናዊ ቅላጼ እያስተካከልክ መሄድህ ተፈላጊነቱ የጎላ ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግም በመኖሪያህ የአሜሪካን የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን የሚቀበል ቴሌቭዥን ተዘጋጅቶልሀል። «ማጆሮቭ ፈገግ አለ። «ስልጠናና የሶቪየት ዜግነት አስተሳሰብህ በዚህ ያልተለመደና ሙሉ በሙሉ የዘቀጠ ተዕዕኖ ውስጥ እንዳትወድቅ እንደሚከላከልልህ አውቃለሁ።»

ሔልደር መልሶ ፈገግ አለ። «እንዴታ ጌታዬ።»

«የባህር ኃይል፣ የሰራዊቱ እና የባህር ኃይል እግረኛ የደንብ ልብሶች ይለጠሀል። እነዚህን ልብሶች እየለዋወጥክ ልበሳቸው። ይህ የሚጠቅመው ይህ ተቋም የሰራዊቱ አካላት የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከል መሆኑ ለተነገራቸው ላይታጃ ውስጥ ለሚገኙ ነዋሪዎች ሲባል ነው። ከዚህ ሌላ በምዕራቡ ዓለም የተሰሩ የሲቪል ልብሶችም ይለጠሀል። እነዚህን ሥራ ላይ ሳትሆን ልበሳቸው። ልትለምደው ይገባሀል፣ ልብሱም መለበስን ይፈልጋል።»

ማጆሮቭ የማስጠንቀቂያ ጣቱን አሳየው። «በስልጠናህ ጊዜ በምንም ዓይነት ሁኔታ ከዚህ ተቋም መውጣት አትችልም። በነፋስ ጀልባ መውጣት ካስፈለገህ ከጦር ሰፈሩ አጠገብ ከሚገኘው ጨዋማ ሐይቅ ውጭ መሔድ አትችልም፣ በጦር ሰፈሩ ላይ ካልሆነ በስተቀር የተኛውንም ምድር መርገጥ አትችልም። ከውጪው ዓለም ጋር ምንም ግንኙነት አይኖርህም። ከሞትክም የምትቀበረው እዚሁ ይሆናል። ግዳጅህ እስኪፈፀም ድረስ ቤትህ ይህ ይሆናል።»

ማጆሮቭ ተነስቶ ቆመ። «እሺ፣ ለአሁኑ ይኸው ነው። ራስህን ከቦታው ጋር ለማስተዋወቅ ጥቂት ቀናት ሰጥቼሀለሁ፣ እንደአረፍት አስበው። እዚህ የሚኖርህ ቆይታ እንደማያፍንህ አምናለሁ። እዚህ ያሉ ሰልጣኞች ቦታውን እንድ ቅዕል ስም ሰጥተውታል <ማሊቡ>። ስሙ የተገኘው ካሊፎርኒያ ውስጥ ካለ እጅግ ማራኪ ስፍራ ነው።» ፈገግ አለ። «ይህን ወድጂዋለሁ። እዚህ ብዙ የሚያዘናጋህ ነገር አለ፣ ለአባላቱ በረዳትነት የሚያገለግሉት ሴቶችም የዚህ አካል ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከመካከላቸው አንዷ ወደመኖሪያህ ትወስድህና ስለጦር ሰፈሩ የተለያዩ ግልጋሎት መስጫዎች ማብራሪያ ትሰጥሀለች።»

«አመሰግናለሁ ጌታዬ፣» አለ ሔልደር። «ያለኝን ብቃት በከፍተኛ ደረጃ እንደማስመሰክር አረጋግጥልሀለሁ።» ስለግዳጁ ምንም ነገር እንዳልተነገረው ታሰበው፣ መጠየቁም ጥሩ ሀሳብ መስሎ አልታየውም።

ማጆሮቭ ፈገግ ብሎ ሔልደር ትክሻ ላይ እጁን ጣል አደረገ። «ጥሩ እንደምትሰራ ርግጠኛ ነኝ፣ ስልጠና እየገፋና ነገሮች እየጠጠሩ ሲመጡ ደግሞ፣ የክፍለ ጦር አዛዥ ትልቁ ማዕረግ፣ እንደምታውቀው የአድሚራች አዛዥ (ኮንትራ አድሚራልነት) መሆኑን አስታውስ። እዚህ በምትሰራው ስራ ከተሳካልህና ስራህም ስኬትን ካስመዘገበ፣ የማዕረጎች ሁሉ የበላይ ማዕረግን ከምታልመው በፈጠነ ልታገኘው እንደምትችል ቃል እገባልሀለሁ፣ የፍሎቲላ ኮማንደርነት ማዕረግን የማግኘት እድልህን ከግምት አላስወጣውም።» ብሎ ማጆሮቭ ትክ ብሎ ተመለከተው። «የምናገረው፣ ሔልደር፣ የምናገረው ብልጫ

ላለው መኮንን ከፍተኛ የስኬት ደረጃ ላይ ለማድረስ ዕድልን ስለሚሰጡ ሁኔታዎች ነው።»

ሔልደር አይኖቹን አርገበገበ። ይህን መሰል ዕድል የሚሰጥ ሁኔታ ጦርነት ነበር።

ከቢሮው ወጥቶ ይዛው የመጣችውን ባለወርቅማ ፀጉር ሴት ተከትሎ እንድ የሳር መስክን አቋርጠው፣ ብዙ በሮች ወዳሉት ረጅምና ዝቅተኛ ህንፃ አመሩ ከበሮቹ ወደእንደኛው መርታ ይዛው ሄደችና ወደኋላ ሸሸት ብላ እስኪሚገባ ጠበቀችው። ሔልደር እንዲህ አይነት ነገር ተመልክቶ አያውቅም። ክፍሉ በግምት የእስራአምስት ጫማ ካሬ ስፋት አለው። ከአንደኛው ግድግዳ ጋር የልብስ ቁም ሳጥን፣ የመጽሀፍ መደርደሪያዎችና ጠረጴዛ አብረው ተሰርተዋል። ድሉት ያለው የቆዳ ወንበር፣ የንባብ መብራት እና ከሳዩ ላይ ትንሽ ጥቁር ሳጥን የተቀመጠበት ቴሌቭዥን ይታያል። ወደግል መፀዳጃ ቤት የሚወስድ እንደ በር አለ። መጋረጃዎቹና የአልጋ ልብሶቹ የተሰሩት ከብሩህ የስካንዲኒቪያ ጨርቅ ነው። በጠረጴዛው ላይ የታየም፣ የኒውስዊክና የዘኢንተርናሽናል ሔራልድ ትሪቢውን የሁለት ቀን ህትመት እድሜ ያላቸው መፅሔትና ጋዜጣ ተቀምጠዋል። ክፍሉ ውስጥ ካሉት ነገሮች ሁሉ ግን ሔልደርን የማረከው አልጋው ነበር። በሆቴል ቤት ወይንም በሴተኛ አዳሪ ቤት ካልሆነ በስተቀር በጥንድ አልጋ ላይ ተኝቶ አያውቅም።

«ቴሌቭዥኑ እንዴት እንደሚሰራ ሳሳይህ፣» አለች ልጅቷ፣ ከአልጋው አጠገብ ጠረጴዛ ላይ የርቀት መቆጣጠሪያ ሳጥን እንስታ። አስነሳችውና በፍጥነት ጣቢያዎቹን መለዋወጥ ጀመረች። «እዚህ የምታገኘው ቴሌቭዥን ኒውዮርክ ሆነህ የምትመለከተውን ራሱን ነው።» አለች፣ ልዩነቱ የሰባት ሰዓት የጊዜ ልዩነት መኖሩን ነው። ከእንድ የአሜሪካን ሳተላይ የተጠለፈ ነው። ሶስት ዋና የቴሌቭዥን መረቦች፣ አራት የፊልም ጣቢያዎች፣ ስፖርት፣ ካርቱን፣ ከአሜሪካ ተወካዮች ምክር ቤት የሚተላለፍ ዝግጅትን አጠቃሉ በአንደ ላይ ሃምሳአራት ጣቢያዎች ይሏል። ለመምሪያህ የሚሆን የቴሌቭዥን መጽሔት አለ።»

«ሀምሳ አራት ጣቢያዎች!» አለ ሔልደር በአግራሞት።

«የእጅ ሰዓትህን ስጠኝ፣» አለች። ሲሰጣት፣ በምትኩ ግዙፍ ሮሌክስ ኤክስፕሎረር ሰጠችው። «ሌላ የግል ጌጣጌጦች ወይንም ንብረቶች አሉህ?» የኪስ ቦርሳውን ከአራት ዓመት በፊት የገዛውን የጀርመን ላይተር ሰጣት። ባያጠ ሰም ላይተሩን ስለሚወደው፣ የሰጣት እየቆጨው ነበር። «አትጨነቅ፣» አለች ሁኔታውን ተመልክታ «ይህን ዓይነት ብዙ ቅራቅንቦ ይሰጥሀል።» ፦ንሽ ማህደር አቀበለችው። «የዚህ ስፍራ ካርታ ነው። ለመሄድ የሚርቅህ ቦታ ያለ ከመሰለህ ያገኘኸውን ብስክሌት መውሰድ ትችላለህ። ምግብ በተቋሙ ውስጥ ባሉት ስድስት ምግብ ቤቶች በፈለግከው መጠቀም፣ ወይም ክፍልህ ድረስ እንዲመጣልህ ማዘዝ ትችላለህ። በአልጋው አጠገብ ጠረጴዛ መሳቢያ ውስጥ የምግብና መጠጡን ዝርዝር ታገኘዋለህ።»

ሔልደር በዝምታ ቆመና በዙሪያው ያሉትን ቁሳቁሶች ተመለከታቸው። በአግራሞት ተውጧል። ይህን መሰል የቅንጦት ሆቴል ዓይነት ልምድ የለውም።

ወደበሩ እመራች። «ራትሊን እባላለሁ፣ ትሪና ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ፣ ከፈለግክ።»

http://ethzare.wordpress.com

«ቆንጆ ልጅ ነሽ ትሪና፣» አለ ሔልደር፣ የሰሜት ሪሀቡን ከድምፁ ቃና ላይ ማጥፋት እየተሳነው።

ሳቀች። «ውይ እዚህ ያሉት ሴቶች ሁሉ ቆንጆ ናቸው። ቢሮው ውስጥ ያለነው ደግሞ ሁላችንም የጂምናስቲክ ስፖርተኞች ነን።» ሚስጥር አዘል ፈገግታ ለገሰችው። «ማጆሮቭ ለሴቶች ጅምናዝየም ልዩ እትኩሮት ይሰጣል።» አለችና የበሩ ሰደፍ ላይ ተደገፈች። «ከሁለት ሰዓታት በኋላ ከሥራ እወጣለሁ። ከፈለግህ ተመልሼ ልመጣ እችላለሁ።»

ሔልደር እምንታውን ገለፀላት። «ብትመጪ መጣም ደስ ይለኝ ነበር፣» አለ በሚንቀጠቀጥ ድምፅ። ማሊቡን ሊወደው ነው።

ዳግም ፈገግ ብላ በሩን ዘጋችው። ሔልደር በረጅሙ አየር ሳበና በቀጥታ ወደ ቴሌቭዥኑ አመራ። ራዘር የተባለ ሰው ሁሉም ነገር በራሱ ላይ እንደደረሰበት እያጋነነ ዜና ያነባል።ₒ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ምቾት በጥቂቱ የራቃቸው መስለው፣ ከጋዜጠኞች የሚሰነዘሩላቸውን ከባድ ጥያቄዎች በሳቅና በትከሻቸው ሰብቀት እያጀቡ ይመልሳሉ። ሔልደር ተቀመጠና ጣቢያ መለዋወጥ ጀመረ። ደርቲ ሀሪ የተባለ አደገኛ ፖሊስ የሳን ፍራንሲስኮን ከተማ ወደጦርሜዳ ቀጠና ሲለውጣት፣ አቆን ከፍቶ ለአንድ ሰዓት ያህል ሲመለከት ቆየ።

ትሪና ተመልሳ ስትመጣ ሔልደር ተኝቷል። ቀስቀሰችው።

ካትሪን ሩል፣ ቨርጂኒያ ላንግሊ ውስጥ በCIA የበላይ መምሪያ ዘወትር እሮብ በሚደረገው የኤክስኮም ሁለት (EXCOM TWO) ስብሰባ ላይ አብዛኛውን ጊዜ በዝምታ ተቀምጣ ስትከታተል ቆየች። ከስብሰባው በኋላ መዛግብቶቹን ከትውስታዋ ማህደር ታገኛቸዋለች። ምንም ነገር አያመልጣትም።

ኤክስኮም አንድ የተዋቀረው ከCIA ኃላፊ፣ ከምክትሉ፣ ከጠቅላላ ሀላፊው እና ከአራቱ የተልዕኮዎች ምክትል ሃላፊዎች ማለትም ከስለላ፣ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ከአስተዳደር ሃላፊዎች ነው። አነሰም በዛ ከሁለቱ የበላይ አካላት ከተውጣጡ አባላት የተዋቀረ ነው ማለት ይቻላል፣ ከተልዕኮዎች አካል፣ ከሀቡዕ ሀይልና ከስለላ፣ ከገሀዱ የምርመራ ሀይል ናቸው። እነዚህ የሁለት ኃይሎች አካላት በውስጠ አዋቂዎች «ካምፓኒው» እና «ኤጀንሲው» በመባል ይታወቃሉ።

ማንኛውም ወጣት መኮንን በየትኛውም እንጃ ውስጥ ቢሆን ምርጫ እንዲመርጥ ከተፈቀደለት የኤክሶም ሁለት አባል መሆንን ይመርጣል። ኤክሶም ሁለት የሀገር ውስጥ ጉዳይዎችን በስፋት ቢያውቅም፣ ይህን ፖለቲካ ዞር ብሎ አይመለከትም፣ ለደምቡ በሚል እንኳን ራሱን አያስጨንቅም ምክንያቱም ለዚህ የሚሆን ጊዜ የለውም።አስቀያሚው ሥራ ያለው ሁለት ውስጥ ነው። አስቀያሚ ሥራ የማይወድ ደሞ የለም። የሁለት አባላት ያለማቋረጥ በየስብሰባቸው የሚነሱ አለም አቀፋዊ አስቀያሚ ሀሜቶችን መርምረው መፍትሔ መስጠት ቢችሉም ከብሔራዊ ደህንነት ጋር ግን ፈፅሞ መቻቻል የላቸውም። ከዚህ ሌላ የካምፓኒውና የኤጀንሲው መኮንኖች አብረው የሚሰሯቸው ብዙ ነገሮች

የሚገኙብት ቦታ ነው፣ እንደእውነቱ ከሆነ ሁለቱ ቡድኖቸ ለአንድ ድርጅት እያገለገሉ መሆናቸውን የሚያውቁት በኤክስኮም ሁለት ውስጥ ብቻ ነው።

እነዚህን በመሰሉ ስብሰባዎች ላይ እያንዳንዱ አባል የመረጃ ቅንጥብጣቢዎችን ይሰነዝራል (የሙሉ ሪፖርት ቃላቱ ይጠነክራሉ)። ከሌላው የበለጠ እትኩሮት ሊኖረው የሚችለውን የራሱን ክፍል ሀሳብ ያንፀባርቃል። ሐቆቹ ከድርጅቱ የአለም ዙሪያ ጆሮ ጠቢዎች መረብ የሚቃረሙ ወይንም፣ እነዚህን ሐቆች ተመርኩዘው የሚነሱ ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳን ከፍላጎትና ካለው ጊዜ አንፃር እያንዳንዱ አባል፣ ከፍተኛ ቦታ አለው፣ ወይንም አስገራሚ ነው ብሎ የሚያስበውን መረጃ የመግለፅ ልማድ ቢስተዋልም ቅሉ፣ ከጊዜ በኋላ ከዳበሩት ደንብን የማይከተሉ መርሆች የተነሳ ግን ዝቅተኛ ወይንም ከግምት የማይጣፍ የሚባል ምንም አይነት መረጃ የለም። ዛሬ ጠዋት ዋንኛ የመነጋገሪያ ርዕስ የሆነው በMI-5:- በብሪታኒያ የፀረ - መረጃ ድርጅት ውስጥ በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ላይ የሚገኝ አንድ አባል ሶሆ ውስጥ በሚገኝ አንድ (የግብረሰዶማውያን) መዝናኛ ውስጥ በህቡዕ ሲንቀሳቀስ የነበረን የፖሊስ መኮንን «ክብርን በሚያጎድፍ ሁኔታ ድንገተኛ ጥቃት በማድረሱ» በቁጥጥር ስር መዋሉ ነበር።

«አሁንም በጣም ያስገርመኛል፣» አለ ይህን መረጃ ይዞ የመጣው አባል፣ «ማለቴ እንድ ትንሽ ለየት ያለ ባህሪይ ያለው የብሪታኒያ ስለላ ድርጅት አባል በስድስት መቶ ቀሚስ የለበሱ ወንዶች መሀል ያለምንም ስህተት እጁን በእንደ ፖሊስ ብሽሽት ላይ ማሳረፍ መቻሉ።»

«እንድ ሀሳብ መጥቶልኛል፣» አለ እንድ ሌላ አባል። «ሰውየውን ለምን ለመልካም ፈቃዳችን ምልክት ወደዚህ ጋብዘነው አስመሳይዎችን እነፍንፎ እንዲያወጣልን በየክፍሉ እናሟዙረውም? ያልከው የMI-5 ልክስክስ በአንድ ቀን ውስጥ የስለላ ማህበረሰባችንን አበጥሮ ሊያወጣልን ይችላል።» CIA ማዕረግ ላላቸው ግብረሰዶማውያን ያለው አመለካከት ከብሪታኒያ እኩዮቹ በተቃራኒ የቀዘቀዘ በመሆኑ እየለየ ሊያወጣቸው ሲጥር ብዙ ጊዜ አስቆጥሯል።

ሩል ከሁሉም ጋር አብራ ተሳሳቀች፣ ግን ተደብታለች። ሶቪየት ላይ ምርመራና ክትትል የሚያደርገው ቢሮ አዲሷ የበላይ ኃላፊ ስትሆን በድርጅቱ ውስጥ ከሁሉም በእድሜ ወጣቷ ኃላፊ እሷ ነች። በሀሳቡ ላይ ከቀድሞው ይልቅ ቁም ነገርን ያዘለ ሀሳብ ማቅረብ የምትችል መሰላት። በጠረጴዛው ዙሪያ ከመተያየትና ከወረቀት ማንሳሳት ሌላ ምንም የሚደረግ ነገር ጠፋ። «ሌላ ሀሳብ አለ?» አለ የቀኑ ስብሰባ መሪ። እይኑን ካይኗ አገናኝችው። «እሺ ሩል?»

ሁሉም መቁነጥነጡን አቆመ። ካትሪን ሩል በክፍሉ ያለችው ብቸኛ ሴት ስትሆን፣ በምክትል ሀላፊነት የሁለትን ስብሰባዎች ስትካፈል ብዙ ዓመታት አስቆጥራለች። የሷ ፅንሰ ሀሳቦች በተመለከተ ለሥራ ባልደረቦቿ ግትርና እድካሚ ትሆንባቸዋለች፣ ግን ግሩም መርማሪ ከመሆኗም ሌላ ወደስብሰባ የምትመጣው ጥሩ ነገር ይዛ ነው። ረጅም ቁመናና ቡናማ ቀይ ፀጉር ሲኖራት አብዛኞቹን ወንዶች የሚማርክ ከሥራዋ ጋር የተቆራኘ ውበት አላት። ቢሆንም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የተልዕኮዎች ምክትል ሃላፊ ከሆነው ከሲሞን ሩል ተፋትታለች። ይህ ድርጊቷ ለስለስ ያሉ የወንድ ጓደኞቿን አስደንግጦ ከአጠገቧ አጠፋቸው፣ የደፈሩትንም እምቢታዋን ገልፃ አሰናበተቻቸው። ትንሽ ወንድ ልጅ ስላላት በብቸኛ እናት ላይ የሚከሰቱ ችግሮች ሁሉ ይጫኗታል። ለወንዶች

http://ethzare.wordpress.com

የምትሰጣቸው ሰበብም ልጄን ማን ይጠብቅልኛል የሚል ነው። ከዚህ ሌላ ደግሞ ፍቅሯንና ሀሳቧን ሁሉ የወሰደ ስራ አላት።

ሩል በትሪ ላይ የሚገኙ የፎቶግራፍ ስላይዶችን ወደአጉይ አንቀባራቂው መሳሪያ ወሰዳ አስገባቻቸው። «አንድ ነገር እጄ ላይ አለ፣ ስለምንኑቱ ርግጠኛ አይደለሁም፣ ግን ሁላችሁም እንድታስቡበት የምፈልገው ነገር ነው። ስለሁለት የሶቪየት ሰሞች ያወቅነውን መገምገም እፈልጋለሁ።» ፕሮጀክተሩን አበራችው። በጥንቃቄ የተሰፋ ሙሉ ልብስ የለበሰ ባለጥቁር ፀጉር ወጣት ባለቀለም ፎቶግራፍ ግድግዳውን ሞላው። መናፈሻ ውስጥ ተቀምጦ በእጠጡ እያለቀ የነበሩትን ሁለት አሜሞር ቀሚስ የለበሱ ልጃገረዶችን በአትኩሮት ይመለከታል።

«ለንደን ነው?» አለ አንድ ሰው። «በስልሳዎቹ ዓመተ ምህረት። እነዚህን አሚር ቀሚሶች የትም ብመለከታቸው አውቃቸዋለሁ።»

«የእውቀትህ ምጥቀት ዘወትር ይገርመኛል፣ ሀሪ፣» አለች ሩል። «አንተ ነህ የሰራህቸው?»

«እሀ. . . » አንድ ድምፅ ጣልቃ ገባ። «እም፣ ማነው ስሙ ፎይ ምናምን።»

«ፎይ ፊርሶቭ፣» አለ ሌላ ሰው።

«በጣም ጥሩ፣ ነቡራን። ሀሪ፣ ይህ አነጋገርህ አጠረጥረው የነበረውን ነገር እረጋግጠልኛል፣ ለንደን በነበርክ ጊዜ ስትከታተል የቆየኸውን ስለ አሜሞር ቀሚሶች እንጂ ስለ KGB አልነበረም።»

«እም፣ ይህ ፊርሶቭ ነው፣» አለ ሀሪ፣ ከተረጊ ለማምለጥ። «ያን ያህል ቦታ ያለው ሰው አይደለም። በተደጋጋሚ ተከታትለነዋል። ሰው የሚሰልል ሳይሆን ለንደንን ወደስልሳዎቹ ጊዜዎቿ ሊመልሳት የሚሞክር ነበር የሚመስለው።»

«ብዙ ተከታትለኸዋል ማለት ነው ሃሪ፣» ሩል ተመልሳ መጣች። «የሁላችሁንም ትውሲታ ልቀስትሳችሁ። ሮይ - ፈርሶቭ ማዕረጉን ለማወቅ አልቻልንም. በስልሳ ስምንትና በስልሳ ዘጠኝ ለንደን ውስጥ በሚገኘው የሶቪየት ኤምባሲ ዝቅተኛ ተፈላጊነት ነበረው። የሚንቀሳቀሰው የባህልና ስፖርት አማካሪነት ሽፋን ሲሆን በአብዛኛው ወደስፖርቱ ያመዝናል። ለኔሬ ሙዚቃ ወይንም ለተበባዊ ዳንስ ብዙም ትኩሮት ያለው አልነበረም። ሀሪ አልተሳሳተም፣ ከምንም ዓይነት ተልዕኮ ጋር አገናኝተነው አናውቅም። ጊዜውን የሚያሳልፈው የእንግሊዛዊያንን ባህል በመለማመድ ነበር። ሁልጊዜ ፊልም ይባል፣ የቅንጦት ሙሉ ልብሶችና ጫማዎችን ያሰራል። ወደአስኮት ሔደ፣ ስኮትላድ ውስጥ ወፍ እያደነ ቆየና፣ በመርከብ ተሳፈረ። ራሱን የፖላንድ ክበርቴ በማስመሰል በተሳካ ሁኔታ አለፈ፣ ከሚናገረው እንግሊዝኛ ይልቅ የእንግሊዛዊ ባህሪው ያይል ነበር። በጥሩ ሁኔታ ዘልቆ ገባ። ስለእሱ እንቅስቃሴ የሚታወቅ ነገር ቢኖር ዘወትር በየቀኑ ላለፉት ሶስት ወራት ምሳ ሲበላ የቆየው ካርልተን ክለብ በተባለ የለንደን ሆቴል ውስጥ መሆኑ ብቻ ነው።

«የትሮይ ክለብ አይደለም?»

«ብትክክል፣ እግኝተውትም አያውቁም። ሁሉም አባል ነው ብለው ያስቡ ነበር። ከእኛ ሰዎች መሀል እንዱ ግን ምሳ ተጋብዞ ሳለ ሮይን ተመልክቶ

የሚጠጣው ሾርባ ትን ብሎት ሊሞት ነበር። ፊርሶቭም በመጨረሻ በእይኑ ጠቀሰው። ይህ የኛ ሰውም ለእስተናባሪው ነገሩን አልገለፀም።»

«ግሩም ነው፣» አለ አንድ ሰው ከልብ በመነጪ እድናቆት ተውጠ።

«ከስልሳ ዘጠኝ በኋላ እንብዛም ትኩረት አልሰጠነውም። በሰባ ሁለት በሙኒክ ኦሎምፒክ ላይ የሲቶች ጂምናስቲክ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ታየ። እውነታው ግን የፖለቲካ መኮንን መሆኑ ነበር። ካይል ውስጥ በተደረገው የኑቆስ ጀልባዎች ውድድር ላይ የነሀስ ሜዳሊያ አግኝቶ ነው በቀጥታ ወደዚያ የሄደው።»

«ውይ፣ የድርጅቱ አባላት ለምንድነው ኦሎምፒክ ላይ የማያሸንፉት? ለምንድነው ሜዳሊያዎቹን ሁሉ KGB የሚሰበስባቸው?»

«ፊርሶቭ ለአንድ ዓመት ያህል በሰባሶስትና በሰባአራት የተባበሩት መንግስታት ውስጥ ገብቶ ቆየ፣ እዚያም ለንደን ከነበረው እንቅስቃሴው ጋር ሲነፃፀር እናሳ ቦታ ይዞ ቆየ። በሰባ አራትና በሰባ አምስት ለአስራ ስምንት ወራት በባህል መኮንንነት ሰዶካልም ውስጥ ቆየ። ኒውዮርክ ውስጥም ሆነ ስቶኮልም ውስጥ ምንም ልዩ ነገር አላገኘንበትም።» በፍጥነት ሌሎቹን ፎቶግራፎች በተከታታይ አለፈቻቸው። «ከዚያ ወደሀገሩ ሄደ፣ ተጨማሪ ስልጠና ለማግኘት ነው ብለን ገምተናል። ከዚያ በኋላ ከአይታችን ተሰውሮ ቆይቶ በመጨረሻ፣ በአንድሮፖቭ ቀብር ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ካፒቴን ወይንም የኮሞዶሬ፣ የባህር ሀይል የደንብ ልብስ ለብሶ ተገኘ። በዚያን ወቅት ለባሏ ሞት ስታለቅስ ከነበረችው ከሚሲስ አንድሮፖቭ ሌላ በቀብሩ ላይ የተገኘው እሱ ብቻ ባይሆን ኖር ሳናስተውለው ባለፍነው ነበር።»

«ይህ የሚያጠያይቅ ነው፣» አለ አንድ ሰው። «ከዚያ በኋላስ በእሱ ላይ የተገኘ መረጃ አለ?»

ሩል ጥያቄውን ችላ ብላ ማሽኑን አጠፋችው። «ለሁለተኛው ስም ፎቶግራፍ የለንም። ምንም ፎቶግራፍ የለውም።» ብላ ወደመቀመጫዋ ተመለሰች። ይህኛው ቪክቶር ሰርጌቪች ግጆሮቭ ይባላል።

ክፍሉ ውስጥ ያለመረጋጋት ነገሰ። «የKGB ምክትል ኃላፊ፣» አለ አንድ ሰው።

«የመጀመሪያው ዋና መምሪያ ሊቀመንበር-የሀገር ውጭ ተልዕኮዎች፣» አለች ሩል። «ሌላ ነገር ያለው አለ?»

«አንድሮፖቭ፣ ለብሬዥኔቭ ስኬትን ባመጣለት ጊዜ እጣው ሳይወጣለት ስለቀረ፣» አለ አንድ ሰው። «የነበረውን ውዴታ ያጣ ይመስ·ኛል። ከዚህ በስተቀር፣ ስለእሱ የምናውቀው ስለአንድሮፖቭ ከምናውቀው በታች ይመስለኛል።»

ሩል ትንሽ ሀፍረት ታየባት። አንድሮፖቭ ስልጣን በያዘ ጊዜ የዜና ማሰራጫዎች የሷን ምድብ ከፍል እያብብጠለጠሉ ስሙን አጥፍተውታል። ሩል በአንድሮፖቭ ላይ ጥሩ መረጃ ያሰባሰበች ቢሆንም፣ አስተዳደሩ ግን ማንም ስለሱ የሚያውቅ የለም በሚለው ሀሳብ ገፍቶበታል። የአሜሪካንን ረጅም ልብወለዶችና የግሌን ሚለርን ዜማዎች ይወዳል ብለው የሚያወሩት ታሪኮችም እልጠቀሙም። ዛሬ ግን ቀድሞ ያጣችውን ለማካካስ ብልህት ፈጥራለች። «አሁን ከቀድሞው ይልቅ እናውቃለን፣ በጥቂቱ፣» አለች። «ከሁለት ዓመታት ጊዜማ ኤሚሊዮ አፒሴላ የተባለው የኮምፒውተር ልዩ ባለሞያን ሩሲያዊ ወንድ አያት

http://ethzare.wordpress.com

ስለነበሩት በቤት ውስጥ ቋንቋውን እየተናገረ ነው ያደገው:: የኮምፒውተር ልዩ ባለሞያ ብቻ ሳይሆን የኮምፒውተር ወንበዴም ጭምር ነው:: የኮምፒውተር ሶፍትዌርን በመስረቅ በሌላ ኮምፒውተር ላይ ጭኖ በማንቀሳቀስ ልዩ ብቃት አለው:: ይህን ሲያደርግ ሶፍትዌሩን ለፈጠሩት ሰዎች ምንም ክፍያ ያለመፈፀሙ ግልፅ ነው:: ወደ የዩናይትድ ስቴትስ ይመጣና የቅርብ ጊዜ ቴክኖሎጂ ፍሰታ የተወሰኑ የኮምፒውተር መደብሮች ላይ ከዘመተ በኋላ፣ ያገኘውን ይዞ ወደጣሊያን በመመለስ፣ የመግቢያ ኮዱን ይሰብርና ለራሱ ጥቅም እንዲመቹ አድርጎ ይቀይራቸዋል:: ሁሉንም ለማጣመር የራሱን ንድፎች አውጥቶ ይገጣጥማቸዋል::»

ሩል ዙሪያዋን ተመለከተች:: የሁሉንም ሙሉ አትኩሮት አግኝታለች:: «ብቻ፣ አፒቼላን ይኸው የKGB አባል የንግድ ልውኩ መስሎ ይቀርበዋል:: ሞስኮ የሚገኘው ቢሮዋቸው ደረጃውን ሙሉ ለሙሉ ያልጠበቀ አንድ የኮምፒውተር ሶፍትዌር እንዳለውና እያስቸገራቸው መሆኑን ይነግረዋል:: አፒቼላ ወደሩሲያ መጥቶ መሳሪያውን የረቀቀ የWP፣ የወርድስታር ፕሮግራምን ማንቀሳቀስ እንዲችል አድርጎ እንዲያስተካክላላቸውና ሰራተኞቹንም እንዲያስለጥንለት ይጠይቀዋል::»

«ውይ!» አለ እንጹ:: «ወርድስታርን ቢሞክሩት ከበፊቱ የባሰ ያቀውሳቸዋል::»

«ወርድስታርን በመቶዎች ከሚቆጠሩ የኮምፒውተር መደብሮች ውስጥ ከመደርደሪያ ላይ መግዛት ይቻላል፣» አለ ሌላው አዕንአት ባለበት እንደበት::

«አዎ ግን ሶቭየቶች በራሳቸው ኮምፒውተር ላይ ሊያሰሩት አልቻሉም:: ዘመኑን የተከተሉ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂዎች ርቀዋቸዋል:: ከIBM ጋር አብሮ ለማንቀሳቀስ የሚያስችላቸውም የMS-DOS ፕሮግራም እንኳን ገና ማንቀሳቀስ አልቻሉም:: ወደምስራቅ በሚደረጉ የመርከብ ጓዞች ላይ የጣልነው እገዳ እየሰራ ይመስላል::»

«እየሰራ ስለሚገኝ ነገር ስሰማ ደስ አለኝ፣» የሚል ምላሽ ተሰማ::

ሩል ቀጠለች:: «በርግጥ፣ ይህን መሰል ሥራ ለኢሚሊዮ ቀላል ነበርና ብዙ ገንዘብ የሚያገኝበት ዕድል ታየው:: በቀጣዮቹ አራት ወራት ውስጥ ወደ ሞስኮ ሶስት ጊዜ ሄደ፣ በአንድ ጎሦው ከሳምንት እስከ ወር ለሚገመት ጊዜ ይቆያል:: ከልጆች ዓለም መደበር ፊት ለፊት ዜርዝንስኪ አደባባይ ወስጥ ወደሚገኝ አንድ ህንፃ ተወሰደ::»

«በክርስቶስ፣ ሞስኮ ማዕከል ውስጥ ገብቶ ነበር ማለትሽ ነው?»

«የህንፃውን ምንነት ባያውቅም አዎ ገብቶ ነበር:: ዘወትርም ወደህንፃው የሚገባው ከኪሮቭ ጎዳና እቅጣጫ በኩል በመሆኑ አንድ የመንግስት የንግድ ቢሮ ውስጥ ያለ ይመስለዋል:: ከቢሮው ኃላፊ፣ ጓድ ሞጆሮቭ ከሚባል ሰው ጋር ከተዋወቀ በኋላ ሲሥራ የሚሆነው የተንጣለለ መስኮት አልባ የስብሰባ አዳራሽ ተሰጠው:: ቴክኖሎጂን የሚወደው ማጆሮቭም በተደጋጋሚ እየመጣ ሲሰራ ይመለከተዋል:: ኢሚሊዮ የሰራውን የተወሰነ አካል የሚያስጨርሰውን ቁሳቁስ እየያዘ በቪየና በኩል ከጣሊያን ሞስኮ ሲመላለስ ቆየ:: የኛ ኢሚሊዮ ቂል አልነበረም ጨዋታውን በብልጠት ነበር የሚጫወተው:: ስለስራው ለማንኛውም ሩሲያዊ ምንም ነገር ለማስተማር አልፈቀደም፣ የወርድ ስታር ፕሮግራሙን ለእነሱ እንዲስማማ አድርጎ ከሰራላቸው በኋላም መቼም ቢሆን ሊፈቱት

በማይችሉት ኮድ ቆልፈዋለሁ ይላል:: ስለዚህ ሊቀዱት አይችሉም:: በመሳሪያው ላይ በሚሰራ ሰራተኛም በቀላሉ የርማን ፊደላትን ወደ ላይሪሊክ ፊደላት መቀየር የሚችል የቁልፍ ልዩ ሰሌዳ አዘጋጀለት:: መመሪያዎቹንም ወደቋንቋቸው ከተረጎመ በኋላ የቢሮ ፀሐፊዎቹን አለማመዳቸው:: ግን ነገሮች ከተበላሹ ተመልሰው ወደኢሚሊዮ መሄዳቸው ነው:: በጣም እንዳበሳጫቸው እገምታለሁ::»

«ማጆሮቭ? ይህ ጣሊያናዊ ለእኛ ምን አደረገልን?»

«ስለ ጓድ ሞጆሮቭ በደስታ አወራልን፣ በሱሀሳብ ነገሮችን በፈለገው ጊዜ ለማግኘት ከመቻሉና ከአኗኗሩ በመነሳት ይህ ሰው በሶቪየት የንግድ ተልዕኮ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አለው ብሎ ይገምታል:: እንደውም በእንግድነት በማጆሮቭ ግብዣ የሳምንቱን መጨረሻ ከራሚያ ውስጥ በሚገኝ የቅንጦት ሆቴል ውስጥ አሳልፏል:: እንደገመተው ከሆነ ይህ ግብዣ የተደረገለት ከቴክኒክ ምስጠሮች የተወሰኑትን አሳልፎ እንዲሰጥ ለማሳመን ነበር:: ኢሚሊዮ የፈለገውን ዓይነት ውድ መጠጥ ሲጠጣና ከፈለጋት የቢሮው ሴት ጋር ሲዝናና ከቆየ በኋላ የያዘውን ቴክኖሎጂ እንደማያቀምሰው ግልፅ ሲያደርግለት፣ ግንኙነታቸው እንደቀድሞው የሰሪና የእሰሪ ሆነ::»

«እሺ ማጆሮቭስ?»

«በጣም መልከ መልካም ነው፣ ሴቶቹን ይወዳቸዋል በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ሴት ያስፈልገዋል:: ሁል ጊዜ ባለወርቅማ ፀጉሮቹን ይመርጣል:: ሽክ ያለ አለባበስ አለው:: የታረቀና ተግባቢ ባህሪይ አለው:: ውድና ከምዕራቡ ዓለም የመጡ ነገሮች አያስችሉትም:: በቅንጦት ሆቴሉ ውስጥ በፖርሽ 928 መኪና ሲዝናና ነበር:: አብሮ ለመሆን አስደሳች ነው፣ ቮድካውን የሚነካበት አይፈልግም፣ ግሩም በራስ የመተማመን ባህሪይ አለው::»

«ይኸው ነው? አፒቼላ የሰጠን መረጃ ይኸው ብቻ ነው?»

«ማጆሮቭ ለአፒቼላ ያሳየው ይህንኑ ብቻ ነው::»

ሀሪ መናገር ጀመረ:: «አንድ የቀረ ነገር አለ፣ የለም እንዴ ሩል?»

«አዎ አለ:: ሮም የሚገኘው ጣቢያችን ለኢምሊዎ አፒቼላ የተወሰኑ ፎቶግራፎችን ሲያሳየው አሚሊዮ ከመቅፅበት ለየው::»

«የማጆሮቭ ፎቶግራፎች የሉም ብለሽን ነበር::»

«የሉም:: የሮይ ፊርሶቭ ግን ብዙ ፎቶግራፎች ነበሩ::»

«እህህህ. . .»

«እውነትም እህ:: ለጓድ ፊርሶቭ የሰጠነው ግምት ዝቅተኛ ነበር:: በKGB መዋዕል ንዋይ በቅንጦት የሚኖር ማንም ሰው ለገንዘባቸው ተገቢውን ግልጋሎት እየፈፀመ መሆኑን ማወቅ ነበረብን:: አሁን እንደገመትኩት ለንደን በነበረ ጊዜ እዚያ ያለውን የKGB ጣቢያ እየመራ ነበር::»

«ፊርሶቭ ወይንም ማጆሮቭን ሁላችንም ደግመን ብንመረምረው የሚሻል ይመስላል::»

ሩል ወደ ወንበሯ ተመለሰች:: «መጀመሪያ ፈልገን ልናገኘው ይገባል:: ተሰውሯል::»

«መቼ?»

«በትክክል ርግጠኛ አይደለሁም:: ስለማጆሮቭ ላገኝ የቻልኩትን መረጃ ሁሉ ብፈትሽም ብዙ ነገር አላገኘሁም:: ልክ ከአብዮቱ በኋላ በዘርዚንስኪ እገዛ

http://ethzare.wordpress.com

ስር በሌኒን ቼካ ውስጥ ማጆሮቭ የሚባል ሰው ነበር፣ እሱ ግን የኛን ማጆሮቭን ለመሆን የእድሜው መግፋት አይፈቅድለትም። እናሳ ቦታ የነበረው ቢሆንም የሚንቀሳቀሰው በስታሊንና በቤሪያ ስር ነበር።»

«በነውጡ ጊዜ እንዴት ሆነ?»

«ታሪኩ የሚለው ስታሊን ራሱ በጥይት ገድሎታል ነው።»

«እሀ።»

«ከለንደኑ በፊት ስለፊርሶቭ የምናውቀው ነገር አለ?»

«ለእንድሮፖቭ የግል ቀረቤታ ነበረው የሚል ጭምጭምታ ብቻ ነው።»

«ስለማጆሮቭ ሌላ ምንም መረጃ የለም?»

«ስለማጆሮቭ የምናውቀው አሁን የነገርኳችሁን ብቻ ነው በሞስኮ ማዕከል ምክትል ኃላፊ መሆኑን፣ እና በፊርሶቭነቱ የምናውቀው መረጃ አለ። አሁን ግን በርግጥ፣ ሁለቱ እንድ መሆናቸውን ስላወቅን በተሻለ ልንመረምረው እንችላለን። ሁሉም ምድቦች እሱን በተመለከተ በተለይ ከሁለቱ ስሞች የእንዱ ማንነት ጎልቶ ስለታየባቸው ጊዜያት፣ የቻሉትን ሁሉ እንዲያጠናቅሩ እፈልጋለሁ።»

በጠረጴዛው ዙሪያ የእሺታ ጉምጉምታ ተሰማ።

«በአሁኑ ወቅት ያልተፈታው የዚህ ሰው እንቆቅልሽ፣ የእንድሮፖቭ ምክትል መሆኑን እናውቃለን፣ ከሰማነውም በመነሳት ወራሹ እሱ ይሆን ነበር። ታዲያ ለምን ስልጣኑን አልወረሰም? አሁን የKGB የበላይ ለምን አልሆነም? የሚለው ጥያቄ ነው።»

በክፍሉ ውስጥ በሀሳብ የተሸበበ ፀጥታ ነገሰ። ሀሪም፣ «ኬት፣ አንድ መላ ምት ይኖርሻል ብዬ እጠብቃለሁ።» አለ።

በአዎንታ ራሷን ወዝውዛ። «ከመላምትም የተሻለ ነገር ያለኝ ይመስለኛል።»

«የጉልምስና ሕይወትህን በሙሉ በKGB ውስጥ ያሳለፍክ ሰው ከሆንክ፣ የKGB የበላይ ከመሆን የላቀው ምንድን ነው?»

ሩል ራሷን ግራ ቀኝ ወዘወዘች። «አላውቅም፣ ግን ማወቅ የምንችል ይመስለኛል፣ በጣም አትኩሮትን መሳጭ ሁኔታ ላይ ልንሆን እንችላለን። ይህ ሰው ብዙ ነው፣ በዙሪያችን ከሃያ ዓመታት በላይ የፈለገውን ሲያደርግ ቢቆይም እኛ ግን በሕይወት መኖሩንም እናውቅም። አሁን ምን ሊያደርግ እያቀደ እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ። ጥሩ ነገር ሊሆን አይችልም፣ ይችላል?»

«በእንድሮፖቭ ቀብር ላይ የባህር ኃይል ዩኒፎርም ለብሶ ነበር ብለሻል?»

«አዎ፣ ግን እኛ እስከምናውቀው ድረስ ከባህር ኃይሉ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ምንም እንኳ በግል ከእንድሮፖቭ ጋር በቀጥታ ቀረቤታ ቢኖረውም፣ ትልቅ የስልጣን ደረጃ ላይ የተቀመጠ አልነበረም። እንድሮፖቭ ሲቀመንበር ከሆነ በኋላ፣ ለእንድ በጣም እጥጋቢ ምክንያት ተደብቆ ቆይቶ ቀብሩ ላይ የተገኘውም ከአከብሮቱ እንፃር ይመስለኛል። ከዚያም ወዲያውኑ ተሰወረ።»

«መልካም፣» አለ ሀሪ፣ ይህን ጉዳይ ለሁሉም ክፍሎች ብናሰራጨው ጥሩ ይመስለኛል ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ባሉን ግንኙነቶች ላይ ይህ ምስጢር በተለይም በብሪታኒያውያን በኩል እንዳይወጣ መጠንቀቅ አለብን። በሰባሁለት

ዓ.ም ሙኒክ ሄዶ ስለነበር፣ ከአሸባሪዎች ጋር ግንኙነት እንዳለው ለእስራኤላውያኑ ፍንጭ ብጤ እንሰጣቸዋለን፣ ይህ በላዩ ላይ እንዲነሱ ስለሚያደርጋቸው፣ ምናልባት ሶቭየት ህብረት ውስጥ ባለ መረባቸው አማካይነት ከእኛ በፊጠነ ጊዜ ስለእሱ መረጃን ሊያገኙ ይችላሉ። እንደውም ለእስራኤላውያኑ ማጆሮቭ እሱ መሆኑን ልንነግራቸው የምንችል ይመስለኛል።»

«በእስራኤል የስለላ መረብ ውስጥ የሶቭየት ሰርጎ ገቦች የሉም፣» አለ ሌላው።

«እንድ ነገር ይቀራል፣» አለች ሩል። «ነገሩ የሩቅ ህልም ነው፣ በደንብ መሰረት እንድታደርጉት ልጠይቃችሁ እንደምችል አውቃለሁ፣ ግን በሶቭየት ህብረት ውስጥ በሚገኙ የቅንጦት መኪኖች ላይ ለምን ጠቅላላ ምርምራ አንጥልም? የተለየ ነገር የሚታይባት ማንኛዋም የቅንጦት መኪና ስትታይ የምናስቀምጠው ሰው ታርጋዋንና ያለችበትን ስፍራ ይልክልናል፣ በቃ።»

ሌላ የስምምነት ጉምጉምታ ተሰማ።

«ሌላ ሀሳብ አለ?» ጠየቀ ሰብሳቢው። ምላሽ ጠፋ። «መልካም፣ ማጆሮቭን ፈልገን እናገኘዋለን።»

4

ሩል ተቀመጠችና አለቃዋ በላብ ሲጠመቅ ትመለከታለች። ግዙፉ የምክር ቤት ችሎት ክፍል፣ በዝግ ችሎቱ ውስጥ ለተሰበሰቡት አስራ ሁለት የሚሆኑ ሰዎች ከመጠን በላይ ቢሰፋም፣ ከዚህ ሌላ ለጉዳዩ የሚሆን ክፍል ግን አልተገኘም። በተለይ አለን ኒክሰን ከሁሉም ይልቅ ደቃቃ መስሎ ይታያል። ሩል ሲቁነጠነጥ ማየቱ እያሰደሰታት ነው። የስለላ ምክትል ዳይሬክተሩ ኒክሰን፣ የCIAን ተግባራት አብዛኛውን ይቆጣጠራል። ጥናትና ምርምር፣ ሳይንሳዊና ጦር መሳሪያ ነክ ጥናት፣ የምስል ምርመራ፣ ማዕከላዊ የመረጃ አገልግሎትና ሌሎችንም ብዙ አካላቱን ይመራል። ከዚህም በላይ፣ በተለይ ለመንግስት ባለስልጣናት፣ ለአስተዳደር፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የበላይ አካላት የቃል አቀባይነቱን ስፍራ የሚይዘው እሱ ነው። ጨዋ አስተዳዳሪ፣ ቀልጣፋና፣ ጎበዝ ፖለቲከኛ ቢሆንም፣ በስሩ ለሚከናወኑ ተግባራትና ለተጓዳኝ አካላትና ለበላይ አለቆቹ የሚተላለፉ የጥናት ውጤቶች ያለው እውቀት አናሳ ነው። ሩል የምትመለከተው፣ ልክ ለእንባቢያን የሚፈልጉትን መፅሐፍት እንዲሚያቀረብ ግን ስለመጽሐፍቱ ምንም አይነት እውቀት እንደሌለው የቤተመጽሐፍት ባለሞያነው።

የጂዎርጂያ ክፍለ ግዛት ዲሞክራት፣ የምክር ቤት አባል ካር ረዳት፣ ዊልሲ፣ በስለላ ጉዳይዎች ምክር ቤቱ ለመረጠው ኮሚቴ ሊቀመንበር ለሆነው ለካር በደብቅ ወረቀት ሲያሳልፍለት ሩል ተመለከተች። ሴናተሩ (የምክር ቤት አባሉ) ወረቀቱን ተመለከተና ራሱን በመስማማት ወዘወዘ። «ሚስተር ኒክሰን፣» አለ፣ መነጽሩን አውልቆ አፍንጫውን እያሻሸ፣ ይህ ሁኔታ የአንድ እክል ምልክት ነው «እቢሮዬ ሁሉን ነገር መስራት የምትችል ትንሽ ኮምፒውተር አለችኝ። ሰራተኞቼ ይጽፉባታል፣ ሒሳብ ይሰሩባታል፣ በሷ ለብዙ ሺህ ሰዎች ደብዳቤ ይልኩባታል፣ ብቻ ልታስበው የምትችለውን ነገር ሁሉ ያደርጉባታል።»

http://ethzare.wordpress.com

ገና የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገራቸውን ተንፍሰው ሳይጨርሱ ነበር፣ ሩል አንድ ዶሴ ከፍታ በፍጥነት አንድ ነገር ከውስጡ መፈለግ የጀመረችው።

«ያቺ ነገር ታዲያ ዋጋዋ ከሶስት ሺህ ዶላር በታች ነው፣ ቀጠሉ ሴናተር ካር። «በየቀኑ፣ ጋዜጣ አንስተን ስናነብ፣ ከምፒውተሮች እየረከሱ መምጣታቸውንና፣ ቀድሞ ጊዜ አንድን ክፍል ይሞሉ የነበሩ ማሽኖች አሁን ኪስ ውስጥ መግባት መቻላቸውንና ዋጋቸውም መርከሱን እንረዳለን።»

ሩል በትልልቅ ፊደላት በታይፐ የተፃፈ ወረቀት ለኒክሰን አሳለፈችለት፣ እሱም ፊቱን በመሀረብ ከጠረገ በኋላ በፍጥነት ማንበብ ጀመረ።

«እሁን፣ ይህ ሁሉ እየሆነ፣» አሉ ሴናተሩ። «CIA የኮምፒውተር እድገትን ለማራመድ፣» ወረቀታቸውን መልከት እደረጉ፣ «. . . አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር ለምን ለማውጣት ፈለጉአሰቡ አንድ አዲስ ኮምፒውተርን ለመስራት ሳይሆን እድገቱን ለማራመድ ብቻ።»

ከአለን ኒክሰን ዋና ችሎታዎች መሀል አንዱ በአንድ እይታ ብቻ አንድ ወረቀት አንብቦ፣ ወረቀቱ የያዘውን ቃል በቃል መናገር መቻሉ ነው። ለረጅም ጊዜ አያስታውሰውም፣ ግን እስከሚናገረው ድረስ ማስታወስ ይችላል። «በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሴናተር፣» ሲል ጀመረ፣ «የጠቀሱት የገንዘብ መጠን የኮምፒውተሩን አካላት ብቻ ያጠቃለለ ወጪ ሳይሆን፣ የኮምፒውተሩን የመቆጣጠሪያ መዋቅር (Operating System) አሁን ካሉበት መዋቅሮች ሁሉ ደህንነቱ ተወዳዳሪ በሌለው ሌላ መዋቅር የመተካት ሥራን ያጠቃልላል። ይህ በአንድ የኮምፒውተር አብዮት ጊዜ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ችሎታዎች እንድናገኝ ያስችለናል። ለምሳሌ፣ የማኛውንም ሌላ ኮምፒውተር የመቆጣጠሪያ መዋቅር የሶቭየቶችን አጠቃልሎ፣ በልጦ ሊሰራ፣ ማኛውንም ዲስክ ወይንም ቴፕ ወይንም የሌላ የማኛውንም ኮምፒውተር ተቀፅላ ተቀብሎ መረጃን ለማንበብ ስለሚያስችለን፣ እስከዛሬ ድረስ በሳይንሳዊ ልብወለዶች ላይ ብቻ የምናገኛቸውን የግንኙነት ስልቶች አሳናፅፎን ወደ ቀጣዩ ምዕተ አለም ሊያሸጋግሩን ይችላል። ሴናተር ይህ የእድገት እርምጃ በዩናይትድ ስቴትስ የወደፊት የመረጃ አሰባሰብና ምርመራ ላይ የተደረገ ፈሰስ ነው . . .» እያለ ኒክሰን፣ በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ከቀረበለት የሩል ምላሽ በመነሳት ንግግሩን ቀጠለ።

ሩል ረዳቱን ሊን ተመለከተች። ቅንድቡን የሚያክ መስሉ ሰላምታ ብጤ ሰጣት። እሷ ግን በተቻላት ሁሉ ኮስተር ለማለት ሞከረች።

በኋላ፣ ከኮሚቴው ክፍል ስትወጣ፣ ሊ ደርሶባት ጎን ጎኗ እየተራመደ «በጥሩ ሁኔታ ይመጣል ተብሎ የተጠበቀ ነው፣» አለ።

በሀዘኔታ ፈገግታ ለግሳው። «ጥያቄው ይሰነዘራል ተብሎ ለመገመት እያስቸገርም፣ ሚ/ር ሊ።»

ፊቱን እጨማደደው። «ውይ» አለና ሰው እንዳልሰማቸው ለማረጋገጥ ዙሪያውን ቃኘ። «ዛሬ ለምን ራት እንበላም?»

ሩል ቆመችና ፊቷን ወደሱ አዞረች። «ሚስተር ሊ፣ አስደነገጥከኝ። አንተም ሆንክ እኔ እንደምናውቀው ከአንተ ጋር በአንድ ላይ ለመገኘት ይቅርና በሌሎች ሰዎች መሀል ባገኘህ እንኳን ግልፅ የአመለካከት ግጭት በመካከላችን ይፈጠራል።»

«ግሩም እራት አዘጋጅቻለሁ፣ ሁለት ጠርሙስ ክሩግ 66 ደሞ ፈልጌ አግኝቻለሁ።»

«እውነትህን ነው ሚስተር ሊ፣ በምርጥ ነገሮች አታለህ ከኔ ጋር ድብቅ ግንኙነት ልትጀምር የምትችል ይመስልሀል?»

«እንወራረድ።»

«ስንት ሰዓት ላይ?»

«አንድ ተኩል?»

«ሁለት አድርገው፣ የምጨርሰው ሥራ አለኝ።»

ሩል እቤቷ ስትደርስ ሁለት ሰዓት ሊሞላ ምንም አልቀረው። የመልዕክት መተበያ ማሽኑ ሳያነሳው በፊት፣ የሚጮኸውን ስልክ ለማንሳት ተንደረደረች። «ሀሎ»።

«ካትሪን ነሽ?» ስሟን በዚህ መልኩ እያዝተተ የሚጠራው አንድ ሰው ብቻ ነው።

«ሀሎ ሳይመን፣» አለች ትዕግስት እያጣች፣ ጫማዋን ወርውራ የልብሷን ቁልፎች መፍታት ጀመረች። «መውጣቱ ነው፣ አስፈላጊ ነገር ነው? ፒተር ደህና ነው?»

«አዎ፣ ደህና ነው። ጓሮ ስጋ እየጠበስን ነው። «ሳይመን በረጅሙ አየር ሳበ። እንደእውነቱ ከሆነ የምደውለው ስለፒተር ጉዳይ ነው፣ ሚሲ እና እኔ ሚይን ውስጥ ቤተሰቦቿ ጋብዘውን ለሁለት ሳምንታት ያህል መሄዳችን ነው፣ እና ከቻልሽ. . .»

«እዚህ ላይ አቁም፣ ሳይመን፣» አለች ሩል፣ በጠባር ዝቅተኛ ድምጿ። «አንተ ከሄድክ ፒተርም ይሄዳል፣ ስምንታችን ያ ነበር።»

«መልካም፣» ሲሞን ተንተባተበ፣ «እንዲህ አይነት እቋም ይኖርሻል ብዬ አልገመትኩም፣ እንደውም በበጋ ወቅት ልጅሽን ማግኘት ትፈልጊያለሽ ብዬ አስቤ ነበር፣ ግን የእናትነት ስሜትሽን በትክክል እንዳልተረዳሁት ገባኝ።»

«ይህን ሽሙጥህን በኔ ላይ አትሞክረው፣ ሳይመን፣» ስለሚያበሳጨው፣ በከፉ ቃላት ስታናግረው ደስ ይላታል። «አባቱ ነህ፣ ለለውጥ ያህል አባትነትህን ልታሳይ ሞክር። ማለቴ፣ አንተ ዘንድ ከመጣ ገና አስር ቀኑ ነው፣ አንተ ደግሞ ከላይህ ልታወርደው ትሞክራለህ።»

«የምትይውን ለማድረግ እየሞከርኩ አይደለም፣ ካትሪን፣ ብቻ ሚሲ እና ፒተር እንዳንድ ጊዜ. . .»

«በሚስትህ ላይ ለማሳበብም አትሞክር። ሚሲ እና ፒተር እንደሚሰማሙ አውቃለሁ። ያልተስማማችሁት አንተና ፒተር ናችሁ ወይ አንተ ብቻ ነህ። ልጁን ሰው ለማስደሰት የሚጓጓ ልጅ ነው፣ የአንተን ተቀባይነት ለማግኘት ሲል በእቶን ላይ ይሄድልሀል፣ አንተ ግን የተረገምህ ግድየለሽ ስለሆንክ ነው።»

«በይ፣ ይህን ድጋሚ አትጀምሪው ካትሪን፣ እኔ ስለልጁ እያሰብኩ ነው።»

«ምን ጥርጥር አለው ሳይመን፣ በበጋው ወቅት በዋሽንግተን ሙቀት እንዲቀልጥልህ ትፈልጋለህ፣ ያውም በሕፃናት መዋያ፣ ስራ ላይ ስሆን እዚያ እንደምተወው ታውቃለህ።»

http://ethzare.wordpress.com

«ታዲያ ለምን ስራሽን ትተሽ በድጎማው እያኖርሽ ልጅሽን በደንቡ እታሳድጊም::»

«ምክንያቱም ሺህ ጊዜ ደግሜ እየነገርኩህ ያንተን የተረገመ ድጎማ እልፈልግም:: ቤቱና የልጅ ድጋፍ ድጎማ አገኛለሁ፣ አንተ ያኔ ዩኒቨርስቲ እስገብተኸው ልብስ ስፈት ባለሞያህ ዘንድ ልትወስደውና መኪኖች ምናምን ልትገዛለት እስክትጀምር ድረስ ይኸው ይበቃኛል:: እስከዚያ እችለዋለሁ:: እስከዚያ ድረስ ግን ሳይመን፣ ለምን የራስህን ልጅ ለማግኘት አትሞክርም? እሱ በጣም ሳበዝና ማራኪ ልጅ ነው፣ አብረኸው መዋል ብትጀምር ልትወደው ትችል ይሆናል::»

«ስለዚህ ለሁለቱ ሳምንታት ፒተርን አልወስደውም እንዳልሽ ልቁጠረው::»

«ከአባቱ የሚያስፈልገውን የማህበራዊ ግንኙነት ልምድ እንዲያጣም አልፈልግም::»

«ደህና ሁኝ ካትሪን::»

«ለፒተር እንደምወደው ንገረው::» ብላ ስትመልስ ቀድሟት ስልኩን ዘግቶታል:: «ርጉም!» ብላ ልብሷን እየጎተተች ያለጫማ ወደ ሳይኛው ቤት ተጣደፈች:: ሙሉ ልብሷን ቁምሳጥን ውስጥ ወርውራ የውስጥ ልብሶቿን አወለቀችና ለፀጉሯ መሸፈኛ የፕላስቲክ ቆብ ይዛ ወደሻወሩ ዘላ ገባች:: ከእስር ደቂቃ በኋላ የንጣ ሱሪ፣ የመንገድ ጫማና የቴኒስ መጫወቻ ሽሚዝ ለብሳ ከቤቷ መውጣት ጀመረችና፣ ቆም አለች:: በሩጫ ወደላይኛው ክፍል ተመልሳ፣ ከሻንጣዋ የማጆሮቭን ፎቶግራፎች አውጥታ ቦርሳዋ ውስጥ ወተፈቻቸው:: ብትሞክር አትጎዳም::

በረጅሙ እየተነፈሰች፣ ቦርሳዋን እያወዛወዘች፣ ስለምታሳልፈው ምሽት እያሰበች በጆርጅታውን ጎዳና ላይ በፍጥነት መራመድ ጀመረች:: ሙቀቱ አሁንም ከአግረኛ መንገዱ ላይ እየተነነ ነው፣ ግን የቀኑ ሀሩር በማብቃቱ ተመስገን አሰኛት:: ሙቀት አትወድም:: ከመንገዱ በተቃራኒ ዛፍ ተደግፎ የቆመ አንድ ሰው የሷን አቅጣጫ ተከትሎ ግን ፍጥነቱን ቀንሶ ኋላ እየቀረ መራመድ ጀመረ:: መልከት አደረገችው፣ አርባዎቹ የአድሜ ክልል ውስጥ ገብቷል፣ አጭር ወፍራምና ዱልዱም ተክለ ቁመና አለው:: ፀጉሩ ጥቅጥቅ ያለ ጥቁር ሲሆን ጥቁር ክፈፍ ያለው መነፅር አድርጓል:: ደብዛዛ ቡናማ ሙሉ ልብስ ለብሷል:: ረጅም ጊዜ ቢያልፉትም፣ የስለላ ድርጅቱን የክትትትል ስልቶች ስልጠና የወሰደ ማንም ሰው በአንድ ነገር ይገረማል:: አላፊ አግዳሚውን እየቃኘች ዳግም የማያገኘውን ሰው ዝርዝር ሁኔታ ማስታወስ::

በጎዳናው ጥቂት ከተጓዘች በኋላ፣ ከሷ ጋር የሚመሳሰል የፈዴራል ቤትን ደረጃዎች ሮጣ በመውጣት ደውሉን ተጫነችና፣ በራሷ ቁልፍ ውስጥ ገባች::

«ቤቶች!» ተጣራች፣ ሰውየው የት እንደሄደ ለማረጋገጥ መጋረጃውን ከፍታ ወደውጭ ባለመመልከቷ ራሷን እያደነቀች::

«ኩሽና!» አሱም ተጣራ፣ ሳሎኑንና መመገቢያ ክፍሉን አልፋ ከቤቱ በስተጀርባ ወደሚገኘው ኩሽና ስታመራ፣ የቢላዋ ኳኳታና የጃዝ ሙዚቃ ይሰማት ነበር::

«እ. . . ሽንኩርት፣ «አለች ወደሱ እየተራመደች፣ ሙዚቃ ማጫወቻው የድሮ የማይልስ ዳቪስ አልበምን ያስዜመዋል::

«ሽንኩርት ሆነሽ ቅሪ፣» አለ፣ ቢላዋውን ወደግራ እጁ አዘዋውሮ ቀኙን ወደወገቧ እየሰደደው:: «ባሮ ሽንኩርት ነው::» ሳማት:: «ሽንኩርት የሚገባው ሀምበርገር ላይ ነው እንጂ ጣፋጭ ዳቦ ላይ አይደለም:: «እንደገና ሳማት፣ ቢላዋውን ጥሎ ሁለቱንም ክንዶቹን ወገቧ ዙሪያ እየጠመጠማቸው:: «ጡት ማስያገኛ ሳታደርጊ ስትቀሪ ደስ ይለኛል::» አለ::

«አውቃለሁ፣» መለሰች፣ «ዛሬ ለሽማግሌው ኒክሰን ያንን ቀላል ጥያቄ በማቅረብህ ሽልማት ይገባሀል ብዬ አሰብኩ::» ሲያቅፋት ደስ ይላታል፣ ግን ካልተጠነቀቀች ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ስለሚሆኑ፣ የተዘጋጀው ምርጥ ራት ገደል ገባ ማለት ይሆናል:: «እዚህ ቦታ መጠጥ ለማግኘት እንዲት ልጅ ምን ማድረግ ነው ያለባት?»

«ምንም፣» አለ፣ ወደማቀዝቀዣው እያመራ:: «አሁን መጠጡን ታገኚና ሌላውን በኋላ ታደርጊዋለሽ:: «ከማቀዝቀዣው ጠርሙስ ሻምፓኝ አውጥቶ መክፈት ጀመረ:: «ቀኑን እንዴት ዋልሽ?»

«ውይ፣ ጥሩ ቀን ባላለፍኩ ነበር፣ ግን ሳይመን ልክ እቤት ስገባ ደወለልኝ:: ከቢሮ ስወጣ ተመልክቶኝ ደቂቃ ቆጥሮ የደወለ መሰለኝ::»

«የቢሮ ሰው የማግባት አደጋዎች:: ለክፉ የሚሰጥ እንዳልሆነ ተስፋ አለኝ:: ፒተር ደህና ነው?»

«ውይ እንዴታ:: አባቱ ለሁለት ሳምንታት ወደባር ሀርበር ሄዶ አዲሶቹን አማቾቹን ለማስደሰት ሲል ከጀርባው ሊያወርደው ሞከረ:: ታውቃለህ እያረጁ ነው:: ሳይመን ዘወትርም ቢሆን ተሰፋ የሚጣልበት አይነት ሰው ነው::»

«ሳይመን እሮጌ ወላጆቿን እንደሚማርክ ማሰብ ነበረብኝ::»

«አያቅተውም:: ሳይመን ይህን ማድረጉን እያውቅበትም::»

«ታዲያ ሳይመን ይህን ያህል ከርፋፋ ከሆነ ለምን አገባሽው?»

«ውይ እኔ እንጃ:: ወጣትነቴና ችኮልነቴ ይመስለኛል:: እሱ በዕድሜ በጣም ይበልጠኛል፣ በጣም ልሰልስ ነው::» ትከሻዋን ሰበቀች:: «እሱ ሮም ውስጥ የጣሊያ አዛዥ ነበር፣ እኔ ደግሞ ከሀገር ውጭ ተልዕኮ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ መውጣቴ ነበር:: ፍቅር በፍቅር ነበርን፣ ሁለት የአሜሪካ ስለላ አባላት እጅ ለእጅ ተያይዘው ከምሽቱ ስምንት ሰዓት ትሬቪ ፏፏቴ ውስጥ ሲዋኙ ይታይህ:: በጋብቻ ከኔ ጋር መቆየት የፈለገው እስካረግዝለት ድረስ ብቻ ነበር:: ከዚያ የባህል ወግ አጥባቂነቱ እሸነፈው:: ሥራዬን ትቼ፣ በሙዚቀኞች ቦርድ ውስጥ እያገለገልኩ፣ ብዙ ግብግቦችን እንዳዘጋጅለት ይፈልጋል:: ስንት የወጥቤት መመሪያ መጽሐፍት እንደሰጠኝ ብነግርህ አታምነኝም:: ፒተር ከተወለደ በኋላ ለመጀመሪያ የልደት በዓሉ ፓሪስ ውስጥ ኮርደን ብሉ ላይ የሚሰጥ ትምህርት አገኘሁ ሥራዬን ትቼ ፊቴን ወደዚያ የማዞር መስሎት ነበር::»

«እኔ ብሆን እይኔንም አላሽም፣» ዊል ሳቀ::

«እውነት ትተወዋለህ? እራት የምታዘጋጀው እሷ ብትሆን ያላማ ሲጋና በርገንዲ እንጂ ጣፋጭ ዳቦና ሻምፓኝ እንደማይሆንላት ታወቃት::

ሊ በሁለት ብርጭቆዎች ሻምፓኝ ሞላ:: «ለጤናችን» አለ ከብርጭቆዋ ጋር እያጋጨ::

http://ethzare.wordpress.com

«ዋው፣» አለች፣ የሚኩረፈረፈው ጋዝ እፍንጫዋን እያስቆጣው። «ይህን ከየት አገኘኸው?»

«ከምክር ቤት አባሉ። እሳቸው ከየት እንዳገኙት እንዳልጠይቅ ፈራሁ፣ ከእንድ የሀገር መከላከያ ባለስልጣን ሊሆን ይችላል።»

«ግሩም ነው። የቆየ ሻምፓኝ እወዳለሁ። «ብርጭቆዋን ከፍ አደረገች።

«ለሀገር መከላከያ ባለስልጣን።»

«መቼም ሁለታችንንም ቀጥሮ የሚያሰራን እሱው መሰለኝ። ዛሬ ያንን በጀት ለማስወጣት የራስሽን ሚና ተጫውተሻል።»

«ስማ፣ ያ ኮምፒውተር ያስፈልገን ነበር-እየህ፣ አስታወስከኝ።»

የማጆሮቭን ፎቶግራፎች ከቦርሳዋ አወጣች። «በጀልባ የቡድን ጉዞዎችህ ላይ ይህን ፊት አይተኸው ታውቃለህ? በካዊስ ዊክ፣ እንደዚያ ዓይነት ነገር።»

ሊ ፎቶግራፎቹን ተቀብሎ በጥንቃቄ አጠናቸው። «ማነው እሱ? ከሰላዮቻችሁ እንዱ?»

«ከእነሱ ሰላይዎች እንዱ ነው፣ ፊርሶቭ ይባላል። እሁን ከዚህ ፎቶ በአስራ ሁለት ወይ በአስራ አምስት ዓመት ያረጃል፣ ምናልባት እየሸበተ ይሆናል። ክብደቱም ይጨምር ይሆናል። የማይሰማ ብሪታኒያ ቋንቋ ይናገራል፣ እንዳንድ ጊዜ የፖላንድ ከበርቴ ነኝ ይላል።»

«ከጀልባ ላይ ጉዞ ጋር ምን ያገናኘዋል?»

«በሰባ ሁለቱ አሎምፒክ ጊዜ ለሶቭየት የጀልባ ውድድር ላይ ተሳትፏል» ለተወሰነ ጊዜ ለንደን ላይ ቆይቶ፣ ካውስ ላይ መርከብ መሳፈሩን መረጃው ይጠቁማል።

ሊ ራሱን በእሱታ ወዘወዘ። «እላውቀውም። ወደካዊስ የሔድኩት በሰባ ሁለት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከዚያም በሰባ ዘጠኝና በሰማንያ ካዊስዊክ ላይ ተገኝቻለሁ በእድሚራሉች ዋንጫ ዓመታት። ሶቭየቶች ይህን መሰል የንፋስ ጀልባ ጉዞ እያደርጉም፣ የምስራቁ ክፍል ሀገሮችም ማናቸውም ቢሆኑ ይህን አልለመዱም፣ ስለዚህ እኔ በነበርኩባቸው የጀልባ ቡድኖች ውስጥ እሱን የማየት እድሌ የጠበበ ነው። መጥፎ ሰው ነው?»

«ነው፣ ሌላ መጥፎ ነገር አለ?»

«ምን እየሰራ ነው?»

«ማወቅ የፈለግኩት ይህንኑ ነው። የእኔ ሰዎች ከሚያደርጓቸው ተግባራት አንዱ፣ የሚከታተሏቸው ሰዎች የደረሱበትን ማወቅ፣ የህይወት ታሪኮቻቸውን በየጊዜው ማደስ ነው። ግን የሱን ያህል ተፈላጊነት ላለው ሰው፣ ከእይታ ተሰውሮ በጣም ለረጅም ጊዜ ቆይቷል። መረጃ ባይኖረኝም፣ እያደረገ ያለውን ነገር ለማወቅ የማንገባበት ጉድጓድ መኖር እንደሌለበት ይሰማኛል።»

«የሚመስጥ ሥራ ነው፣» አለ። «ትወጂዋለሽ አይደለም?»

አዎንታዋን በምልክት አሳየችው። «መጀመሪያ ላይ በሕቡዕ የመንቀሳቀስ ሥራዬን ለመተውና ወደ ላንግሊን ለመምጣት በተገደድኩ ጊዜ ተናደድኩ፣ ግን እውነቱን ለመናገር፣ ለመስክ ሥራ ከሰለጠኑ ጥቂት ሴቶች መሀል አንዷ በመሆኔ ይህን ሥራ አዘውትሬ ለመስራት እንደማይፈቅዱልኝ ቶሎ ገባኝ። በሮሙ ተልዕኮ ላይ ከተሳሳኪነት ያለፈ ሥራ አልነበረኝም፣ ከዚያ ግን ሳይመጣን አግብቼው፣ እሱም እድገት ሲያገኝ፣ ብቸኛው ተመራጭ ስፍራ ላንግሊ ብቻ ሆነ።

ደሞም በጣም ተሳካልኝ። አንድ ቦታ ላይ ኤምባሲ ውስጥ ሆኜ ከማገኘው የተልዕኮዎች እይታ የተሻለ እይታን አገኘሁበት። ከዚህ ሌላ መኪናዬን ከማስነሳቴ በፊት ስሩን ከመፈተሽ ተገላገልኩ። ደግሞም፣ የአይነት ለውጡን እወደዋለሁ፣ አንድ ቀን ችሎት ላይ አንተን እረታህለሁ፣ በሌላ ቀን ደግሞ ማጆሮቭን የመሰሉ ሰዎችን አሳድዳለሁ።»

«ማን?»

«ውይ. . . ይህ የፊርሶቭ ትክክልኛ ስም ነው። ይህን መናገር አልነበረብኝም ከገደቤ በላይ እየለፈለፍኩ ነው።

«ይቅርታ፣ እያነፈነፍኩ አስቸገርኩሽ።»

«አይደለም። ልናገረው ፈልጌ መሰለኝ፣ ደሞ አንተን ላምንህ እችላለሁ።» በስራዬ ውስጥ አንድን ሰው ማመን ያልተለመደ አይነት ስሜትን ይፈጥራል። ይህ ናፍቆኝ ነበር።

«ታዲያ ያም ሆነ ይህ፣ እዚህ ሥራ ውስጥ እንዴት ገባሽ?»

«መልካም፣ የባርናርድና የኮሎምቢያን ህግ ተምሬ ሳበቃ፣ ሕግን መማር እንደማልፈልግ ድንገት ተከሰተልኝ፣ ንግድ ውስጥም መግባት አልፈለግኩም» ብሩክ ኪርክላድ፣ ባርናርድ አብራኝ ትማር የነበረችው የመኝታ ቤት ጓደኛዬ ኮሎምቢያ የሚገኘው የሩሲያ ጥናቶች ፕሮግራም አባል ነበረች፣ አትኩሮቴን ገዛችው። በመጨረሻ አመቴ ግማሽ ላይ የትኛው እንደሆኑ ባላውቅም ከፐሮፌሰሮቼ አንዱ የስለላ ድርጅቱን የምልመላ ፎርም ሰጡኝ፣ ከተመረቅሁኩ ከአንድ ወር በኋላም በኪንቲኮ የባህርና የምድር ጦር ሰፈር አውቶማቲክ መሳሪያዎችን መተኮስና በእንድ ምት ሰውን የመግደል ስልጠና መውሰድ ጀመርኩ።

«ጠንቀቅ ብል ይሻለኛል።»

«በጣም ትክክል።»

«እንቺ ማጆሮቭን እንደምትከታተይው ሞስኮ ውስጥም እንቺን የሚከታተል አንድ ሰው ያለ ይመስልሻል?»

ሳቀች። «ለሀገር ውጭ ሥራ ላይ ስለነበርኩ፣ ሊኖር ይችላል። ሁለት ባላጋራዎች በእንድ ኤምባሲ ውስጥ ማን ዋናውን ሥራ እየሰራ እንደሆነ ይተዋወቃሉ። ምናልባት ሮም ውስጥ ሰውነቴን እያነከኩ ያነሱኝ አሳፋሪ ፎቶግራፍ ይኖራቸው ይሆናል።»

«ወይም እንቺና ሳይመን ትሬቫይ ፋፋቴ ውስጥ ስትዋኙ።»

«እሱም አሳፋሪ ነው። ቦሪስ ምናልባት እስካሁን ስለዚያ ፎቶግራፍ ትርጉም ለማወቅ እየለፋ ይሆናል።

ሳቀና ወደማብሰሉ ተመለሰ። «ስሚ፣ ሂጂና በረንዳው ላይ ተቀመጪና እኔ ይህን እንድጨርስ እድል ስጪኝ። በግማሽ ሰዓት ውስጥ ይደርሳል።»

ሩል ብርጭቆዋን ሞልታ በተካፋች በሩ አልፋ በድንጋይ የተከበበውን መናፈሻ ቁልቁል ወደሚያሳየው በረንዳ አመራች። ኩሽናው ውስጥ ሲንቀሳቀስ እንዲታያት ሆና ተቀመጠች። ሲያበስል ማየት ትወዳለች፣ በዚህ ሥራ ጎበዝ መሆኑ ከሱ ጋር አይሄድም። በስራው ጎበዝ፣ አልጋ ላይ ጎበዝ፣ ባጠቃላይ እሷን በማስደሰት ጎበዝ ነው። በሕይወቷ በዚህ ወቅት የምትፈልገው እሱን ነበር፣ ደስተኛና ቀልደኛ ነው፣ ግን ከስተር ማለትም ያውቅበታል፣ ሳያስጨንቃት ግን በጣም ይወዳታል። እምላክ ይመስገን ፊት አይደለም። ፊት ወንዶች

http://ethzare.wordpress.com

እንገሽግሸዋታል፣ ስለንብረት ክፍፍላቸው ያላዝናሉ፣ ዳግመኛ ለማግባት እጅግ ይስገበገባሉ። ዊል ግን እግብቶ አያውትም፣ የትዳር ሁሳብ ባያስደነግጠውም የማግባት ሁሳብ ግን የለውም። ከፒተር ጋር ከሆኑ ይስማማሉ፣ ግን በልጁ አስታኮ ከሷ ጋር ያለውን ፍትር ለማጥፍ ብሉ ከመጠን በሳይ እያጫውተውም። ግዙፍ ጡንቻማ ወንድ ነው። እሷ እምስት ጫማ ከአስር ኢንች ቁመት አሳት፣ እሱ ግን ይበልጣታል፣ ታኮ ጫማ ስታደርግም ይበልጣታል፣ ይህን ትወደዋለች። ስሳሳ ስምንት እመቱ ነው፣ በእድሜ የእራት ዓመት ታሳቋ ነው። ይህ ልዩነት ትክክል ነው ብላ ታስባለች።

ደህንነቱንም የሚጠብቅ ሰው መሆኑ ለሷ ቀሳል ነገር አይደለም። የተገናኙት ከሁለት ወራት በፊት በአንድ የከተማው መደብር ነበር። እንደሌሎች የህግ ሪዳት መስሏት፣ ለሌሎች የምትነግረውን ነገረችው፣ ይኸውም የግብርና ሚኒስትር ጠበቃ መሆኗን (ይህ ብዙውን ጊዜ ስለራስዋ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ይዘጋሳታል)። ሁለቱም እንዳቸው ሌሳቸው ምን እንደሚሰሩ ሳያውቁ ቆይተው በመጨረሻ በእንድ የኮሚቴ ችሎት ሳይ ተገናኙ። የሀሳብ ልዩነት ያለመጣጣም ሊኖር እንደሚችል ታውቋታል፣ ምክንያቱም የሷ ሥራ ከፊሉ ተጨማሪ የመንግሥት በጀት ማስገኘት ሲሆን የሱ ደግሞ እንዳታገኝ መከሳከል ነው። ግን የስርቆሽ ነገር ይጣፍጣል። ከሊሞን ጋር ከተፋታች ጀምሮ ከድርጅቱ ሰራተኛ ወንዶች ጋር ሳለመውጣት ሕግ ብትቀርዕም፣ ለማያውቋት የውጭ ሰዎች መዋሸት ደግሞ ሰልችቷታል። ትክክለኛ ምሳሽ የሆነሳት ዊል ነው። የመጨረሻው የደህንነት ጥበቃ ይሰፍ አለው። ቀደም ብሳም የFBI መረጃውን አንብባለች፣ ይህን በማድረጓ ውስጥ ውስጡን ፀፀት ይሰማታል። ስለ ሥራ ብዙም አያወሩም፣ አንዳንድ ጊዜ ግን አንድ ነገር፣ ማለትም እንደማጆሮቭ ያለ ጉዳይ ስሚቷን ሲኮረኩረው ምስጢሩ የትም እንደማይደርስ ስለምታውቅ ትተነፍስለታለች።

ቺካጎክ ባሀረ ሰሳጤ ሳይ ባለው ጀልባው አንድ ሁለት ጊዜ ሰግረዋል፣ ግን ብዙም አየወጡ አይዝናኑም ይህ ብዙም ለውጥ አያመጣም፣ ዋሽንግተን ውስጥ የሚያውቋቸው ሰዎች እፍኝ አይሞሉም። ዊል ማብሰል ይወዳል፣ እሷ ደግሞ ቤቱን ትወደዋለች።

የሻግውን ብርሀን ለማድመቅ ሲል የመመገቢያ ቤቱን መስኮት መጋረጃ ዘግቶ ጠረጴዛውን አስናድቷል። እንከን የለሽ ውብ እራት ነበር፣ ምግቡም መጠ ጡም ያስደስታል።

«ያምሳክ ያለህ፣ በጣም ሽጋ ነው፣» አለች። «ስማ፣ በመንግስት ደሞዝ እንዲህ የተንደሳቀቀ ሕይወት እንዴት ትኖራለህ ብዬ ብጠይቅህስ? ማለቴ ይህ ቤት የራስህ ነው እይደለም?»

ፈገግ አለ። «አዎ የራሴ ነው፣ እና አዎ ልትጠይቂኝ ትችያለሽ።» ከወይኑ ተሳጨ። «ከቤተሰቤ የወረስኩት ትንሽ ሀብት አለኝ፣ ከዚህ ሌላ አሁንም ከአባቴ ጋር የሕግ ሽርክና አለኝ። ሽርክናው ሊ እና ሊ ይባላል።»

«ጆርጂያ ውስጥ ከተማው - ምን ነበር ጀሌኖ?»

«ጥሩ ታስታውሻለሽ።»

«አባትህ፣ ሌተናንት የከተማ አስተዳደር ነበሩ? የከተማ አስተዳደር?»

«ሁለቱንም። ለጥቂት ጊዜ ከፖለቲካ ወጥቶ፣ በሀግና በቤተሰባችን እርሻ ሳይ ሰርቷል። ግሩም ሰው ነው፣ ፕሬዚዳንት መሆን ነበረበት።»

«ለምን አልሆኑም?»

«ግድረግ ያለበትን ለማድረግ ያን ያህል አጥብቶ የፈለገው አይመስለኝም። በሚቀጥለው ዓመት ሪፐብሊኩን አብኒን ተቀናቅኜ ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ እንድወዳደር ይፈልጋል።»

«ለምን አትወዳደርም? ጥሩ ሴናተር ይወጣሃል።»

«ውይ፣ ሥራውን እንደምትወደው ነው፣ የምርጫ ቅስቀሳውን ግን የምወደው አልመሰለኝም። ያን ያህል ጥብስ ሲጋ በልቼ መኖር እችል እንደው አሳውቅም። ከዚህ ሌላ አብኒ በጣም ደካማ ነበር ሴናተር በመሆኑ በግዛቱ ውስጥ ከሚገኙ ዲሞክራቶች አብዛኞቹ ሊወዳደሩት ይፈልጋሉ። ሀይለኛ የዲሞክራቶች ተቀዳሚነት ይኖራል።

«የአባትህ የፖለቲካ ጓደኞች ከጎንህ አይቆሙልህም?»

«ጥቂቶቹ የሚደግፉኝ ይመስለኛል። የሱ ጠሳቶች ሁሉ እንደሚነሱብኝ ርግጠኛ ነኝ።»

«ሴናተር ካርስ ይደግፉሀል?»

«ምናልባት። አልጠየቅኳቸውም ግን ይህን ርዕስ በተደጋጋሚ እንስተውታል። «ኬት፣ አብረን ጉዞ ለመውጣት የሚያቢቃ ትውውቅ ያለን ይመስልሻል?»

ፈገግ አለች። «እንዴታ አለን እንጂ። ምን አሰብክ?»

«ለንደን የሚገኝ ጓደኛዬ ጀልባ ገዝቷል። በሚቀጥለው ወር ክፉብረሳው ተረክቦ፣ በፊላንድ ምዕራባዊ ባህር ዳርቻ አድርጎ፣ እያሰገረ እንግሊዝ ይዞት ሊመጣ አስቦ ነበር ግን ሥራው ይህን የመዝናናት ሀሳቡን ወድቅ አደረገው። አስከኮፐንህገን ድረስ ይገፍልህ እመጣለሁ ብየዋለሁ። ባቲክ ሳይ በጀልባ ተጉዤ አሳውቅም፣ በኔ ሳይ ጥሩ መሆን አለበት። ስዋን የተባለች ጥሩ ጀልባ ናት። የአርባ ሁለት ጫማ ርዝማኔ አሳት፣ ሙሉ መገልገያዎች አሏት፣ ራሷን በራሷም መቅዘፍ ትችላለች። ሁለታችን በቀሳሉ ልንቆጣጠራት እንችላለን። እንድ ሳምንት ገደማ እንበልና አስር ቀን ቢወስድብን ነው። መምጣት ትፈልጊያለሽ?»

ሩል ለጥቂት ጊዜ አሰበችበት። በቼሳፒክ ሰርጥ ሳይ ያሉት ቋጥኞች ያስደስቷታል፣ ግን የጀልባ ጉዞን የሚልን ያህል አትጓጓትም፣ ደግሞም ከመጠን ካሳለፈችው መጨረሻዋ አብሳይ መሆን ነው፣ ለዚህ ደሞ እሱ ይበልጣታል። እጅግ የምትጓጓለት አይነት መዝናኛ አልመሰል አሳት። «ልንዝርህ፣» አለች። «ትንሽ ልምድ እስካገኝ ድረስ የጀልባ ጉዞው ይለፈኝ፣ ኮፐንህገን ሳይ እጠ ብቅህለሁ። ይህስ ምን ይመስልሀል?»

ሙሉ ፈገግታ ለገሳት። «እሺ፣ ግሩም። በቃ ረዳቶችን ከሆን ቦታ አሰባስባለሁ።»

ድንገተኛ የቅናት ጦር ወጋት። እንስት ረዳቶች ማለቱ እንዳልሆነ ተሰፋ አደረገች።

ለሊት ስምንት ሰዓት ሊሆን ቢል እሱን ሳትቀሰቅስ ከአልጋው ወጣችና ልብሷን ለበሰች። ከሱ ጋር መተኛት ያስደስታታል ግን እሱ ቤት ከእንቅልፏ መንቃትን አትወደውም። ምናልባት የእንከን የለሽ አስተዳደጓ ቅሪት ዳግም እየጠራት ይሆናል። የፊት ለፊቱን በር ድምፅ ሳታሰማ ዘግታ ወደራሷ ቤት መራመድ ጀመረች። ከርቀት የመኪኖች ድምፅ ይሰማል፣ በዚህች ቅልጭ ያለች ትንሽ መንገድ ሳይ ግን ከሷ በቀር ሌላ መንገደኛ የለም። አለ እንዴ?

http://ethzare.wordpress.com

ሩል የጫማ ሶል ከመንገዱ ጋር ሲፋጭ የሰማች መሰላት:: ቆመች:: የራሷ የእግር ኩቴ ማሚቶ ይሆን እንዴ? የርምጃዋን ፍጥነት ትንሽ ጨመረች፣ የራሷ የእግር ኩቴ ማሚቶ ይሆን እንዴ? የርምጃዋን ፍጥነት ትንሽ ጨመረች፣ የመንገድ ጫማዎቿ የቆዳ ተረከዝ ከሲሚንቶው ጋር እየተሳተሙ እናውን ጎዳና በሚያስተጋባ ድምፅ ይሞሉታል:: መታጠፊያው አጠገብ ደርሳ ወደራሷ ሀንፃ ስትታጠፍ የቅድሙ ድምፅ ከወዲያኛው የመንገዱ ጥግ ደግሞ ተሰማት:: በተመሳሳይ ጊዜ እንድ መኪና ከኋላዋ እንድ ስፍራ ላይ ተንቀሳቀሰ:: በመንገዱ ተቃራኒ ጠርዝ ሌላ ሰው መኖሩን ለማረጋገጥ አንድ ጊዜ ዞር አለችና ተመልከታ በፍጥነት ራሷን መለሰችው:: ከአንድ ዛፍ በስተጀርባ ቆሟል፣ መንገዱ ባዶ ይመስላል:: ከመንገዱ ላይ በስተኋላዋ የመንገድ መብራቶች ብዙም ከሌሉበት ቦታ በዝግታ ወደእሷ የሚመጣ ባውዛምቹን ያጠፋ መኪና ተመለከተች::

አሁንም ፍጥነቷን ጨምራ ታስባለች:: ዋሽንግተን ውስጥ ዘራፊዎች መኖራቸውን እግዜር ያውቃል፣ ግን ጆርጅታን ውስጥ? በዚህ ሰዓት? ለማንም ዘራፊ ቢሆን የሰው ዘር የሚገኝበት ጊዜ አይደለም:: ቤቷ ለመድረስ የቀሯትን ሀምሳ ርምጃዎች ከሩጫ ባልተለየ ሁኔታ ፉት ብላቸው፣ ደረጃውን ወጣችና ቁልፎቿን ፍለጋ ቦርሳዋ ማተራመስ ጀመረች:: መኪናው በሀምሳ ርምጃ ርቀት ላይ ቆመ፣ የሾፈሩ ቅርፅ ይታያታል::

በመጨረሻ በሩ ተከፈተላትና ሹልክ ብላ ቶሱ ገባች:: ወዲያውኑ ኮሪደሩ ላይ ወደሚገኝ ጠረጴዛ በማምራት የታችኛውን መሳቢያ ከፈተችና ዘጠኝ ሚሊ ሜትር አውቶማቲክ ሽጉጥ አወጣች:: አቀባብላው መጠበቂያውን አላቀቀችና ወደመስኩቱ አመራች:: የመጋረጃውን ጥግ ስትገልጠው የመኪናው የፊት ለፊት መብራቶች ቦግ አሉና፣ እያቋረጣቸው የነበረውን የሰው ቅርፅ ብርሀናቸውን ለቀቁበት:: ለሰከንድ ያህል ብቻ ብትመለከተውም፣ የቅድሙ ሰው መሆኑን አልተጠራጠረችም::

መኪናው ሳይቸኩል ተንቀሳቅሶ ሄደ፣ ሲቆም ተሰማት ከዚያም እንድ ኩርባ ላይ ወደቀኝ ታጠፈ:: ግድግዳውን ተደግፋ የልብ ምቷ እቦታው እስኪመለስ ጠበቀች:: ዘራፊዎች አይደሉም:: ለእፍታ ያህል ብቻ፣ ማጆሮቭ እየተከታተለችው መሆኗን የማወቁን ሀሳብ ይዛ ስትደሰት ነበር፣ አሁን ግን እሷን እያሳደዳት መሆኑን ነው::

የማይመስል ሀሳብ ነበር፣ ግን ሀሳቧን ጨርሳ ስትተኛ ሽጉጡ ከእጇ መዳፍ አልወጣም::

5

ሔልደር የእግር አውራ ጣቶቹን ይበልጥ ከስር ባለው መንሸራተቻ ስትራፕ ላይ ቆንጥጦ አሳረፈ:: ፊን የተባለችው ትንሽ ከላይ ክፍት የሆነች ጀልባውም ከሳን እና ከሳኗ ውሃ እና ሌላ በየብስ ላይ ያለ ነገር ሁሉ እያፈናጠቀች ገሰገሰች:: ይህች የፊን ጀልባ አዲስ ስትሆን እሱም ግዜውን አግኝቶ በደምብ ካሰበት የባሕር ሁኔታ እና ከራሱ ዘይቤ ጋር ካለማመዳት ከዚህ የበለጠ ጥሩ ውጤትን ሊያመጣባት እንደሚችል ተማመነ:: እንግዲህ የጀልባ መሪ ከጨበጠ አራት ዓመታት ያለፉ ስለሆነ ባሁን ሰዓት የዚህችኛዋን መሪ ሲጨብጥ

ምንም ሳይሆን ንፁህ ደስታ ነው የተሰማው:: ከዚህ ቀደም በእንዲህ ዓይነቱ ንፁህ ደስታ የተፍነከነከበት ግዜ ለማስታወስ ሞከረ:: አልቻለም::

ምን ይህ ብቻ እንዲህ እንደ አሁኑ ዘና ብሎ የሚያውቅበትን ግዜም ነው ማስታወስ ያቃተው:: አዎን! ምናልባትም እንደዚያ ዓይነቱን ግዜ አሳልፎ ስለማያውቅ ይሆናል በጭንቅላቱም የሚታወስ አጋጣሚ የጠፋው:: ያለፈውን ሳምንት ያጠፋው ሩጫ በማድረግ፣ በንባብ፣ እጅግ በጣም አስደሳችና አስደናቂ የሆኑ የአሜሪካ ቴሌቭዥን ስርጭቶችን በማየት፣ እጅ የሚያስቆረጥሙ የሰካንዲኒቪያ እና የፈረንሳውያን ምግቦችን በመመገብ፣ ብሎም ትሪና ጉሊንን በመወሰብ ነበር:: ይሁን እንጂ በዚህ ምንም ያተረበሸ፣ ፍፁም ሰላማዊ በሚመስለው የሕይወት ዘይቤ ጸመና ውስጥ አንድ የሚንቀሳቀስ፣ እርፌ አልቆምም የሚል ፍንጣቂ ነበረ፣ ለዚህ እንዲህ አሁን እንዲህ ለመፍነከነክ በመታደሉ አንድ የሚከፍለው ነገር መኖር አለበት:: ሕይወቱን ሙሉ በሶቭየት ኅብረቶች ዘይቤ ከመኖሩ እና ከበርካታ ሥፍር ቁጥር የለሽ ተሰፋ አስቆራጭ አጋጣሚዎች አንፃር አሁን መክፈል የሚጠበቅበት ዋጋ ይከብዳል ብሎ ማመን አልቻለም:: ልክ ለዚህ ሐሳቡ እፀፋ ምላሽ ይመስላል ኮሎኔል ማጆሮቭ የያዘው ነጭ የኢሊክትሪክ ጋሪ በእይታው ገባ! ጋሪው አቀበታማ በሚመስለው መንገድ አድርጎ ለመዝናኛ የሚውሉ ጀልባዎች በሚቆሙበት ጸርቻ ጋ ሲደርስ ሄልደርም ኮሎኔሉ ወደ እሱ እየመጣ መሆኑን አወቀ:: አዎን ይሄንን አዲሱን አዛዥ ኮሎኔል አንድ ታምር ሊያሳየው ይገባል!

ልክ ወዲያውም ያችን ትንሽ ክፍት ጀልባን ወደ ቁልቁል መርቶ አነስተኛ ጀልባዎች ወደሚቆሙባትና ወደሚያገግሙበት ጸርቻ ወሰጻት:: ከዚያም ረግታ መቆም ባለመቻል በምትታወት በዚያች ፊን ጀልባው ላይ በመቆም ከስሩ ዝቅተኛ በሚባለው የውሃ ምህጻር ላይ ተንሸራሸረ:: ከርሰ ጎደኞች የተወለኑት በዚያ ቦታ የነበሩትም የሚሠሩትን ሁሉ አቁመው ድርቅ ብለው መቅረት ዓይነት በእግራሞት አፋቸውን ከፍተው ያዩት እንደነበረም ከፍተኛ ኩራት እየተሰማው ነው ያስተዋለው:: እሱም ወደ ጎን ወደ ጎን በማለት መንሸራሸሩን ቀጠለ ታዲያ አሁንም እንደቆመ ነበረ:: ከዚያም ጀልባዋን በዚህ አስደናቂ ዘይቤው በመምራት እስከ ጉልበት ድረስ ጥልቀት በነበረው ውሃ ላይ አቆማት:: እነዚያ ጓደኞቹና ሌሎች አፈሰር አባላትም ለተወሰነ ጊዜ አፋቸውን ከፍተው ሲያዩ ቆይተው ወደየጀልባዎቻቸው ተመለሱ::

ታዲያ ትንሽ ጀልባን በኤሌክትሪክ ጋሪው አስሮ መጎተት እንደጀመረ ማጆሮቭ በራሱ ኤሌክትሪክ ጋሪ ተንሸራተተና መጣ:: እንደምን አድረሀል ሄልደር፣ አለ ኮሎኔል:: «ድንቅ ትርዒት ነው ባክህ»

ሔልደር ይህንን አስተያየት ችላ እንዳለ መሰለ:: «እንደምን አደርክ፣ ጌታዬ:: ምን መንሸራሸሬን ማለትህ ነው? ነፋስ በትክክለኛ አቅጣጫ ሆነልኝና ነው እኮ»

ማጆሮቭ ሳቀና ወደ ጋሪው በእጅ ምልክት መራው:: ትንሿ ማሽንም ወደ አቀበቱ ቀጠለች:: «ቀድሞውንም ቢሆን እኮ እንዲህ ያለው አስደናቂ ሚዛን የመጠበቅ እና ትክክልኛ የአቅጣጫ ስሌትህ ነው ትኩረቴን ወደ አንተ እንዳደርግ ያደረገኝ፣» አለ ኮሎኔል:: «እንደው ይህንን ስንግርህ በጣም እንደምትደሰት አልጠራጠርም፣ ሄልደር:: ግን በዚህ በባህር ኃይሉ ኮሌጅ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት የመግቢያ ፊተና ወስደህ ከተቀላቅልክን ጀምሮ በጠ

http://ethzare.wordpress.com

ፈር አሪየንቴሽን ሙከራዎች ከታዩት ሁሉ ላይ ያለ ውጤት አምጥተሀል:: ምን ይሀ ብቻ! በጣም የሚገርመው ደግሞ ዓለማችን ያወደሰውን ዩሪ ጋጋሪንም በትንሽ ነጥብ በለጥ ለማለት መቻልህ ነው:: ዩሪ ጋጋሪን እስከዚያ ድረስ ሪከርዱን ይዞት ቆይቶ ነበር»

ሔልደር በርግጥ የመግቢያ ፈተና ውጤቶቹን አያውቅም ነበር ግን ፈታኞቹ ደስ እንደተሰኙበት አስታውሷል:: ከዚያ በኋላ በፈለጉት ዓይነት ማሽን ላይ ያስቀምጡት፣ በፈለጉት አቅጣጫ ያሿዙሩት እሱ ግን ወደ ላይ መውጫ ቀዳዳ ማግኘት በፍፁም አይቸግረውም ነበረ::

ማጆሮቭ ቀጠለ:: «በርግጥ በባሕር ሰርጓጅ መርከብ እና በጠፈር ቡድኖች መሀከል የተወሰነ አተካራ እና ፉክክር መኖሉ አልቀረም:: የጠፈር ቡድኖች ጥሩ እጩዎች ነበሯቸውና አሸንፈዋል:: በማሸነፋቸው ደስተኛ ነኝ፣ እነርሱ ባያሸንፉ ኖሮ አንተም ከኛ ጋር እንደ አሁኑ ሳይሆን መሬትን ዛቢያ ስትዞር በተገኘህ ነበር::

«እመበግናለሁ፣ ኮሎኔል፣» አለ ሔልደር በሙገሳው ሞቅታ እየተሰማው:: ይገርማል! ባለፉት ዓመታት እንደፈለገ ላቅ ያለ ሥራ ቢሰራም እንኳ ተገቢው ምስጋና አንዳንዴ ካልሆነ በቀር ሳይቸረው ነበር የቀረው:: ማጆሮቭ ጋሪውን ላብ ለመከላከል በየሚረዳ ጭንቅላት ላይ የሚደረግ ጨርቅ ያሰሩ የተወሰኑ ተግበስብሰው የሚሄዱ ሰዎች እንዲሻገሩ ገታ እደረገው:: ሰዎቹም ኮረኮንቹን መንገድ ተሻገሩ:: «ለመሆኑ አሁን ልምምድ እያደረክ ነው?» ሲል ጠየቀ:: በነገራችን ላይ ብቁ ልትሆን ይገባል»

«አዎን ኮሎኔል:: በየቀኑ ነው የምሮጠው:: የተወሰነ ደህና ስልጠና ባገኝ ግን ደስ ይለኛል. . . አጠገቤ የሚያሠራኝ ኃደኛ ምንም የለኝም እንጂ»

ማጆሮቭ ራሱን በእምንታ ነቀነቀ:: «በተወሰነ መልኩም ቢሆን የብቸኝነት ስሜት እየተሰማህ እንደሆነ ገብቶኛል:: ሴሎቹ በደምብ ክፍለ ጊዜ ኖሯቸው እየሄዱ እየሰለጠኑ ሲሆን አንተም ከነገ ጀምሮ ትቀላቀላቸዋለህ:: ሆኖም አብዛኛው የስልጠና ግዜህ አሁንም በብቸኝነት እንደሆነ ልንግርህ እወዳለሁ:: ይልቅ ዛሬ ሚ/ር ጆንስን እንድታገኘው እፈልጋለሁ:: አለና ጋሪውን በአዲስ ቅያስ ይዞ በመግባት ወደ አንድ ዝቅ ወዳለ ሕንፃ ጋ ወስዶ አቆመው:: «ተረት የሚነግርህ ሰውዬ ነው ሚ/ር ጆንስ ያልነው:: ሔልደር ለመሆኑ አፈ ታሪክ ምን እንደሆነ ታውቃለህ?»

«ያው በታሪክ የሚታወቅ እየተወራ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፣ እሱን ለማለት ፈልገህ ነው?»

«አዎን ትርጉሙ ልክ ነው ግን ለአንተ የምንጠቀመው በጣም የግላዊ ጉዳይ አድርገን ነው::» አለና ማጆሮቭ ሕንፃው ፊት ቆሞ ሳይወርድ ቀረ:: «እንግዲህ ወደ ፊት የምትመደብበት ሥራ ወደ ውጭ ሀገር ሊወስድህ ይችላልል:: እና ውጭ ብትሄድ ደግሞ ስለራስህ ግልፅ የሆነ የማንነት መግለጫ መስጠት ይኖርብሀል:: በዚህ የተነሣም ሚ/ር ጆንስ አዲስ ማንነት ፈጥሮ አዘጋጅቶልሀል:: ልክ እሱ ሲነግርህ ፈጠን ብለህ ታጠናውና እሺ ብለህ ትሸመድደዋለህ:: ያ ብቻም አይደለም ያንን ማንነትህን ነው ማሳየት እና መኖር ያለብህ:: ይህን ሳታደርግ ብትቀር ዝም ብለህ ፖሊስ እጅ እንድትወድቅ እንፈልግም፣ ይኼ ማንነት ግን ለተወሰኑ ቀናት ከፖሊስ ያድንሀል:: አንተ ደግሞ ከጥቂት ቀናት በላይ አትፈልግም:: ሔልደር ልክ ኮሎኔሉ ሲወጣ

ተከትሉ ወጣ እና ቀጥ ብለው ወደ ሕንፃው አንድ ቢሮ ሄዱ:: ሰማያዊ ሱፍ ያደረገ ዴስክ ላይ ተቀምጦ የነበረ ሰውዬ አገኙ:: «ይኼ ነው ሚ/ር ጆንስ ሰውየው ይኸውልህ» በማለት ማጆሮቭ ሔልደርን ጠቁሞ አመለከተው::

«ካርል ቤንግት ስዊንሰን» ሲል ጆንስ መልሰ ሰጠ:: «እባክህ ተቀመጥ፣ ሚ/ር ስዊንሰን::» አለው ሔልደር:: «ካርል ብዬ ብጠራህስ?»

ሔልደር ተቀመጠ:: «እሺ፣ ትችላለህ» አለ::

«እንግዲህ በዚሁ ቀልጠፍ ባለውና በሚገባ በሚያስተናግደህ ጆን እጅ ትቼህ እሄዳለሁ፣» አለ ማጆሮቭ:: «ነገ ከርሱ ጋር በርካታ ክፍለ ግዜዎችን ከማሳለፍህ በተጨማሪ ሌሎች ከፍሎችን እንጀምራለን:: ያኔ እንገናኛለን::» ማጆሮቭ ከክፍሉ ሲወጣ ሔልደርም ወደ ሚ/ር ፎንስ ፊቱን መለሰ::

«እባክህ ወደዚህ ና፣ ካርል» አለ ጆንስ ካሜራ ወደ ተተከለበት የክፍሉ ጥግ ቦታ ይዞት ሄደ:: «እንዚህን ልብሶች ልበስ፣» አለና ለሔልደር እንደ እጀ ጠባብ ዓይነት ሱሪም የሰጠው ሲሆን የራሱ ክፍል ውስጥ ከነበረው የልብስ ማስቀመጫም ወዲያውኑ ያወቀው ነበረ:: ልክ የተባለውን እደረገና ከእንድ ስክሪን ፊት ለፊት ፎቶ ለመነሳት ቆመ:: ጆንስም ፓላሮይዱን ከካሜራው ላይ ነቀለውና ሽፋን ወረቀቱን በመገንጠል ፊልሙ ሙሉ እስኪሆን ድረስ ጠበቀ:: «በጣም አሪፍ ነው» አለው «አስተያየት ስጥ ካልከኝ» ከዚያም በእራቱ ጉርድ ፎቶግራፎች ጎላ እንድ የሆነ ማንነም መታ:: "Sam's Fast Foto, Grand entral Statin, New York City," ይላል የማንተሙ ጽሑፍ:: ጆንስ በእንድ ትልቅ ወረቀት ላይ አራት ሆነው የወጡትን ፎቶዎች ቀደደና ለሄልደር በእስክሪብቶ ገፋ አደረገለት:: «ይኸውልህ ይኼ የአሜሪካዊ የይለፍ ወረቀት ለማግኘት የምታስገባው ማመልከቻ ቅጽ ነው:: በራስህ እጅ ጽሑፍ ሞልተህ መፈረም አለብህ:: ከዚያም በታይፕ የተፃፈውን ወረቀት ሰጠው:: «ይኼ ደግሞ ትክክለኛውን መሙላት ያለብህን መረጃ የያዘ ነው»

ሔልደት እስክሪብቶውን ያዘና በፍጥነት ማመልከቻውን እየሞላ በዚያም ሔልጋ ኤሪክሰን እና ቤንግት ስዊንሰን ከተባሉ ሰውድናውያን ስደተኞች ጻሉዝ የሚባል ቦታ ላይ የተወለደ እንደሆነ የሚያትተውን አዲስ ማንነቱን በዚያው አጠና:: የሚኖርበት ቦታ በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ 73ኛው ጎዳና ላይ መሆኑንም ተረዳ::

ጆንስ ተሞልቶ ያለቀውን ፎርም ያዘና ለእፍታ ያህል ከክፍሉ ወጣ ብሎ ደግሞ ተመልሶ መጣ:: «ጥሩ» አለ:: «ይህ ማመልከቻ ከነገ ወዲያ በኒውዮርክ ከተማ 5ኛ አደባባይ በሚገኘው ቢሮ ነገ እንዲገባ ይደረጋል:: አንተም በሳምንቱ ማብቂያ ላይ ውጤቱን ታገኘዋለህ:: ተዝቢ የሆኑት የውጭ ማጉተም እና ቀን ቀጥር ምናምን በኋላ ይጣላሉ::» ከዚያ ደግሞ ከመሳቢያ ውስጥ የሆነ የብር ቦርሳ አውጥቶ ለሔልደር አቀበለው:: ከእንሽላሊት ቆዳ የተሠራ ጠቆር ያለ ሲሆን ልክ በእንድ ሰው የኋላ ኪስ ውስጥ ረዘም ያለ ግዜ የቆየ ያህል ጠመም ብሏል:: «ከፈተውና በክሬዲት ካርዱ ጀርባ ላይ ፊርም» ሔልደር ቦርሳውን በመክፈት የአሜሪካን ኤክስፐሬስ ካርድ፣ ቪዛ፣ የገበያ ቦታ መግዣ ካርድ አወጣ:: ከዚህ በተጨማሪም እንድ በኒውዮርክ የክልል መንግሥት የተሰጠ የመንጃ ፈቃድ ላይ ፈረመ:: ይኼ የመንጃ ፈቃድ ላይ እንደፈረመበትም ጆን ለብዶ መልሶ ሰጠው:: ከዚህ ውጭ እንድ ትንሽ ሞርምትምት ያለ የማኅበራዊ ዋስትና ካርድም ነበር::

http://ethzare.wordpress.com

«እነዚህ በማንኛውም ጊዜ ሊለዩህ የማይገቡ ሌሎች ነገሮች ናቸው፤» አለ ጆንስ በዴስኩ ሌሎች ዕቃዎችን እየገፋለት:: «ይኼ ከሚኔሶታ ዩኒቨርስቲ የተሰጠ ቁልፍ ነው የአፓርታማህና እና የፖስታ ሳጥንህን ትከፍትበታለህ::» ሔልደር ቁልፎቹን ኪሱ ከተተ:: «ይኼ ደግሞ ሰዓሊዎች የሚጠቀሙበት ራዲዮግራፍ የተባለ እስክሪብቶ ነው:: ስዕል መሳል እንደምትችል እገምታለሁ:: ሔልደር ራሱን በእምነታ ነቀነቀ:: ጆንስ ወዲያውኑ እሳዩ ላይ የኒውዮርኩ እቃ አቅራቢ መደብር ማኅተም እና ስም ያለበትን አንድ መሳያ ነጭ ልሙጥ ወረቀት ገፋ አደረገለት:: «አየህ አንዳንዴ ባይተዋር በምትሆንበት ቦታ ላለህ ቁጭ ብለህ ሞንጪር ማድረግ ጥሩ ዘዴ ነው:: አንተም ጠቃሚ ሆኖ ታገኘው ይሆናል::»

ሔልደርም እስክሪፕቶውን አንስቶ አገላበጠና በደምብ ተመለከተው:: «ምን. . . ይኼም እንዳያቸው ከመጡት የጦር መሣሪያ አንዱ ነው እንዴ?»

ጆንስ ሳቀ:: ኧረ በፍፁም እንደዚያ አስደናቂ ነገርም አይደል፣ በዚህ ዓይነቱ እስክሪብቶ የሚጽፉ ሰዎች ለሌላ ለብዙ ነገርም ይጠቀሙበታልና ነው ሳሳይህ የፈለኩት:: አየህ አንተ ያው ለትርፍ ስትል ሥዕሎችን የምትሰራ ሰዓሊ ነህ:: ገብቶህል?» ጆንስ ልክ ይህንን ከተናገረ በኋላ አንድ የሆነ ወፈር ያለ የወረቀት ጥራዝ ዴስኩ ላይ አውጥቶ አስቀመጠ:: «ይኼ እጅግ በጣም ዘርዘር ያለው የሕይወት ታሪክህ ነው:: ባርግጥ ይህንን ታሪክ ቃል በቃል ልቅም አድርገህ ካሁኑ ባጭር ግዜ ሽምድደህ መጪረስ እንዳለብህ ዳግመኛ ማሳሰብ የለብኝም፣ ግን ከዚያ በላይ ዋናው ቁምነገር ልክ በዚህ ጥራዝ ላይ እንደተመለከተልህ ዓይነት ሰው ሆነህ መኖርህ ላይ ነው:: ያ ብቻም አይደል ታዲያ፣ ዝርዝሮቹን በደምብ በተለያዩ አቅጣጫዎች ማየትም ይጠበቅብሀል:: ለምሳሌ አንድ የምታየው ነገር ቢኖር ወላጅ እናትህ እንደሆኑ ተደርገው እዚህ ላይ የተቀመጡት ሴት በልጅነታቸው በሆነ አደጋ የተነሳ እፍንጫቸው ጉዳት ሊደርስበት እንደቻለ ነው:: ግን አንተ በዚህ ብቻ ሳትወሰን ነገሩን በማስፋት ለምሳሌ፣ «እማዬ ምንም እንኳን አፍንጫዋ ይሰበር እንጂ እጅግ በጣም ሩህሩህና ለስላሳ ሴት ነች::» ብለህ ልታሰፋው ትችላለህ:: እና ለዚህ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም በውስጥ ተጠቅሰው ለምታገኛቸው አዲስ የማንነት መገለጫዎችህ የሕይወት ታሪክ ዝርዝር ማውጣት ይኖርብህል:: እና ይኼ እኛ አሁን ፈጥረን ከጨፍን በኋላ ጠርዘን የሰጠንህ አዲስ ማንነትህ ለሰዎች ልክ እውነተኛው ማንነትህ የሚመስለው አሁን ያልኩህን ፈጠራ ስትጠቀም ብቻ ነው»

«እሺ ጥሩ፣ ተግባብተናል»

«መልካም፣ አሁን እንግዲህ በቅጡ ትረዳው ዘንድ ታሪኩን ሳሳይህ:: ያው ቀደም ሲል እንደነገርኩህ ሙሉ ስምህ ካርል ቤንግት ስዌንሰን ነው:: እናትና አባትህ ከስዊድን በ1948 ወደ አሜሪካ መምጣታቸውን በሚኔሶታ ለዘመናት የኖሩ ዘመዶችህ ሊመሰክሩ ይችላሉ:: የሥነጥበብ ት/ቤት ገብተህ ትማር ነበር. . . በሚኔሶታ:: ታዲያ የመመረቂያ ዓመትህ ልክ ጀምሮ በፀደዩ ወራት ሁለቱም ወላጆችህ በድንገተኛ የአውሎ ነፋስ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: ከእርሱ የወረስከውን መሬት ሸጥክና ኒውዮርክ ከተማ ገባህ:: እዚያም ሰዓሊ ሆነህ በሞያህ ስኬትን ለማግኘት ትጸክር ጀመር:: ነገር ግን አልተሳካክለህ፣ ለምን ቢባል ያ ክውርስ ሽያጭ አግኝተህ ይዘህ የመጣኸው ብር እያለቀብህ ነበረ፣ በኋላም ለንግድ የሚሆኑ የሥዕል ሥራዎችን መስራት ጀመርክ:: ልክ

ስትጀምረው ሥራው በጣም ፈታኝና ከባድ ነበረ፣ በኋላ ግን ቀስ በቀስ ስምና ዝና ማግኘት ጀመርክ እና ባሁን ሰዓት ጥሩ ደረጃ ላይ ትገኛለህ:: ባለፈው ዓመት መጪረሻ ላይ ሰሚኒያ አራት ሺህ ዶላር ያህል ማግኘት ቻልክ:: ግሪንዊች ቪሌጅ ውስጥ ባለ ቤዝመንት ትኖራለህ፣ ሥዕሎቹን የምትሠራው በግል ስቱዲዮህ ነው:: ባብዛኛው ብቻህን ነህ ፀጥታ እና ሰላም ባለው ሁኔታ ትሰራለህ፣ በርካታ እንደ አንተ ቤት ባላቸው ስቱዲዮዎች ውስጥ ሥዕልን ከሚሰሩ ጋር ትተዋወቃለህ:: ሥራህን የምትሠራው ሥራዎቹን በሚያመጣልህ አንድ ወኪልህ ነው እንጂ ደምበኞችህን በአካል አታገኛቸውም::

«ግን እኔ የምለው፣» አለ «አንድ ሰው ባልታሰበ ሁኔታ ይኼንን ቢያጣራስ?»

«ግድ የለህም ይኼ ተዓማኒነት ኖሮት ይዘልቃል፣» አለው ጆንስ

የሚሳካበት ዋንኛው ምክንያት ደግሞ ካርል ስዌንሰን በእውነትም ያለ ሰው በመሆኑ ነው:: አንተ ይህን የተሰጠህን ተልዕኮ ለመወጣት እዚህ በምትቆይበት በተወሰነው ግዜ ከኒውዮርክ ከተማ ለእረፍት ወጣ ይላል:: ያኔ ነው እንግዲህ አንተ እሱን የምትሆነው:: እሱ ደግሞ ለዚህ አንተ እሱን መስለህ ለምታደርገው ነገር ሁሉ ትብብሩን ያሳያል፣ ያንንም የሚያደርገው ወዶ አይደለም፣ በኮዲይን እና ሔሮይን እደንዛዥ ዕፆች አቅሉን እስከሚስት ድንዝዝ ያለ በመሆኑ እና እነዚህን ነገሮች በፈለገው ግዜ የሚያቀርቡለት ሰዎች የእኛ ደጋፊዎች በመሆናቸው ነው:: ኧረ ሳልረሳ. . .» አለና ጆንስ ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አንድ ትንሽዬ ቴፕ መቅጃ አወጣና የሆነ ወረቀት ለሔልደር አተበለው:: «በል ወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ነገር በድምጽህ አንብበው እና በቴፕ ይቀረጽ:: እባክህን ደግሜ ደጋግሜ የማሳስብህ ነገር ቢኖር ከእሜሪካው ያን የአንጋገር ዘይቤዎች መህክል ግነት የሌለበትን የመካከለኛውን ምዕራብ ዓይነት የጪዋ ቃላት አጣጣልና አነባበብ ብቻ እንድትጠቀም ነው»

ሔልደርም ልክ እንደተባለው ወረቀቱን አነሳውና ማንበቡን ቀጠለ:: «ታዲያስ እንደምን ውለዋል? ካርል ስሜንሰን ነኝ:: ጓደኛዬ ከሆኑ ለተወሰኑ ሳምንታት ያህል ለእረፍት ወጣ ብያለሁ:: ስለዚህ ስምዎን እና ቁጥርዎን ይተውልኝ ስመለስ እደውልልዎታለሁ:: ነገር ግን ዘራፊ ወይ ቤት ሰርሳሪ ሌባ ከሆንክ እዚሁ ዶበርማስ ራት ልበላ ሂጂ ነውና አሁን ባትሰቆ ይሻላል::

ጆንስ ካሴቱን ኪሡ ከተተ:: «እንግዲህ ይኼ አሁን ያነበብከው ነገር በስዌንሰን የቤቱ ቴሌፎን ላይ ይቀረጽና ይገጠማል» ሔልደር ቀሪውን የቀትር በኋላ ግዜ ከጆንስ ጋር አሳለፈ:: የራት ሰዓት ሲደርስም ዘአጉል ሁኔታ ባንድ ጊዜ ሁለት ስብዕና ያለው ሰው መሆኑ ተሰማው::

«እንዴት ነህ ካርል? ደህና አመሸህ?» አለች ራጉሲን በመጠጥ ቤቱ ውስጥ ከነበረው በርጪማ በእንዱ ላይ ዘርፈጭ ብላ እያረፈች ሳለች በተንኮል ዓይነት እየተመለከተችው:: ጥሩ የፈረንሣውያን ምግብ ከመልካም መስተንግዶ ጋር በሚያቀርበው ካፕሪንስ ማሊቡ እየተመገበ ነበረ::

ተገርሞ ነበር:: «እንደዚያ መሆኔን ታውቂያለሽ ማለት ነው?»

ካምፓሪ ከሶዳ ጋር አዘዘች:: «ለምን አላውቅም:: እኔማ ያንን መሽምደድ ያለብህን ነገር እንድረዳህ ተመድቤ እኮ ነው:: ኮሌጅ ሳለህ በየትኛው የወንድማማችነት ክበብ ውስጥ ነበር የታቀፍከው?»

http://ethzare.wordpress.com

ሔልደር ራሱን ነቀነቀና ትንሽ መረር ያለ ገጽታ ያለው ለመምሰል ሞከረ። «እኔ በወንድማማች ክበብ ውስጥ አልገባሁም፣ ራሱ ወንድማማችነት ክበብ የሚለባው ሐሳቡ እጉል አስቂኝ ነው የሆነብኝ»

«ኧረ ባክህ? ግን እኔ እንድ የሆነ ፓርቲ ላይ ፍሬሽ ሳለህ ያየሁህ ይመስለኛል»

ነገሩ እውነት ቢሆን ኖሮ ሊሰማው የሚችለውን የውጋት ስሜት ገመተው። እናም እንደዚህ ነበረ የሚሆነው ማለት ነው። «ሚኒሶታ ነበርሽ እንዴ?»

«ብቃ ቶሎ ነው የምትረሳው፣ ካርል። ፍሬሽ ሳለን እኔ እና እንተ በስርቆሽ የነበረንን የወሲብ ግንኙነት አታስተውሰውም? ምነው ትንሽም ቢሆን ስሜቴ ተጎዳ እኮ»

ሔልደር ይህን ጊዜ ፈገግ አለ። «አይ ይኼንን እንኳን አስታውሰው ነበር። የፍሬሽማን ዓመት ጊዜዬ ያን ያህል የሚታወስ እና ደስ የሚል አልነበረም። ፓርቲዎች ላይ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ተገኝቻለሁ ግን ጨረታ አልወጣብኝም። እነሱ ይፈልጉ የነበሩት አትሌቶችን እንጂ እንደ እኔ ያሉትን የሥነጥበብ ተማሪዎች አልነበረም።

«እንግዲህ» አለች የምግብ ሜኑውን እየከፈተችው። «የፍቅር ሕይወት ተነፍጎህ እንደቆየህ ለማየት ግዜ አልወሰደብኝም። እኔ ደግሞ ነገሮችን አስተካክላለሁ።

Pate maison እና coq au vin አገዘው በመመገብ በ Beaune-Greaves አወራርደው ሲጫወቱ ቆይና ከዚያም በዚያ ደስ በሚል የምሽት ድባብ እጅ ለእጅ ተያይዘው በእግራቸው ለመንሸራሸር ወጡ። ለሔልደር የገረመው ነገር ቢኖር አሁንም ቢሆን ከርሷ ጋር ፍቅር ለመሥራት በፍፁም የማይታክተው መሆኑ ነው፣ ምን ይህ ብቻ እሷም እንዲሁ ነበረች። አሁንም እንደቀድሞው ስሜታቸው ኖሮ ግን በሌላ በኩል ግንኙነታቸው በተወሰነ መልኩ እየተቀየረ ነበር። ፊቷን በእጁ ሞምቅ አድርጎ ይዞ ወደ ራሱ በማስጠጋት ቀስ፣ ለስለስ አድርጎ ከዚያ ደግሞ ጥብቅ አድርጎ ይዞ በስሜት ልጥጥ አድርጎ ሳማት። እሷም ስሜት ውስጥ ገብታ ነበረና ልክ እንደ ፈረንሣውያኑ ምላሷን አፉ ውስጥ አስገብታ እና በጥርሶቿም ነክሳ እያደረገችው ሳመችው ግን ከራሱ ራቅ አደረጋት፣ ለእፍታ ያህል ተመለከታትና በድጋሚ ለስለስ አድርጎ ሳማት።

ዓይኖቿን ብልጥጥ ብለው ተከፍተው ከናፍሮቿ እየተንቀጠቀጡ ተመለከተችው። «ግን እኮ ይህንን ነገር መፈጸም እንደሌለብን ታውቃለህ፣ አይደለም? እንተ እኮ ለምትወጣው ግዴታ ስልጠና ስትወልድ አሁን ያደረግነውን ነገር የሚጨምር አይደለም። ይኼ ተልዕኮህ ካበቃ በኋላ መተያየትም የለብንም እኮ»

«ኧረ ግጥም አድርገን እንተያያለን» አላት ፍርጥም ብሎ።«በኔ ይሁንብሽ ምን አለ በይኝ። «ለምን እንደሆነ አላውቅም»አለችው፣ «ግን አምንህለሁ። በእውነት ይኼ አሁን ያልከው ነገር ይሆናል? ልናሳካው እንችላለን?»

«ማጆሮቭ ይህ ግዳጅ ካለቀ በኋላ ምንም ነገር እንደሚቻል ቃል ገብቶልኛል። ማጆሮቭን ደግሞ አምነዋለሁ»

ጭንቅላቷን አዙራ ትከሻው ላይ ደገፍ አደረገችው። «ማጆሮቭ ሊያሳካው ይችላል፣ ይኼንንማ ማንም አይጠራጠርም»

«ሚጆሮቭን የፈለገውን እደርግለታለሁ፣» አለ ሔልደር። በችሎታዬ እሱን ማስደመምን ዋንኛ ስራዬ አደርገዋለሁ። እና ታዲያ ያ ሲጠናቀቅ እሱ ደግሞ በተራው ቃል በገባው መሠረት የፈለኩትን ያደርግልኛል»

«እም፣ ያደርጋል» አለች ሰንፍ ባለ መልኩ። «ሁለታችንም ማጆሮቭ የሚፈልገውን እናድርግለት»

ረዘም ላለ ግዜ ጭለማ ውስጥ እንደተቃቀፉ ቆዩ።

6

ሩል ኮምፒውተሩን በሚይዘው የጠረጴዛዋ ተርሚናል ላይ ቁጭ ብላ ቁልፏን አስገባች። የኮምፒውተሩ ምስል መቆጣጠሪያ ወይንም ሞኒተር ሲሟሟቅ ቀኑ እና ሰዓቱ ከላይ ጥግ ላይ በስተቀኝ በኩል መጣ ይህም እንድ ዐረፍተ ነገር ነበር።

ሽማግሌውን ኮዝሞን ማንነትሽን ንገሪው

ልክ ወዲያውኑ ባለ አስር ዲጂት የሆነውን ቁጥር ኪቦርዱ ላይ መታች። ያን ግዜም ኮምፒውተሩን የፈለሰፈው ሰው በወቅቱ ጭንቅላቱ ውስጥ ስለመጣለት ካልሆነ በቀር በሌላ በምንም ምክንያት ሊባል በማይችል መልኩ ኮስሞ ተብሎ ይጠራ የነበረው ይሽው ኮምፒውተር ቁጥሩን እስኪያሬጋግጠው ድረስ ለእፍታ ያህል ቆየት አለና ከዚያም መቅዳት ጀመረ። ሩል ልምድ ያላት ናትና የኮምፒውተር አጠቃቀሟን ማህደር በመመልከት ብቻ አንድ በዚህ ማዕከል ያለ ሰው ምን ዓይነት ፕሮግራምና መች እንደተጠቀመች ሊያውቁባት እንደሚችል ለእፍታ ያህል ቢሆን አልተጠራጠረችም።

ደህና አደርሽ ወሮ ሩል። በሚት ተንስተሻል። ምን ልታዘዝ?

ሩል ፕሮግራሞች ተጠቃሚን ማብሸቅ በመጀመራቸው ያን ያህል መበሳጨቷን ትታለች። እንዲህ ከማሰብ ይልቅ እንዲያውም ኮዝሞን ልክ በእውን እንዳለ ሰው አድርጎ መቁጠሩን መርጣለች ወዲያው IDMUG ብላ ፃፈች።

REVIEW የሚል ነገር ታይፕ አድርጋ ፃፈችና መለሰችለት። የፋይል ቁጥሩ አልነበራትም ግን አንድ ሰው ፎቶግራፍ ሪቪው ታደርጋለች ብሎ ቢያምን ምኗ ሞኝ ናት ይላል። እሷ ግን ፎቶዎቹን በሳምንት የተወሰነ ቀናት ሪቪው ታደርጋለች።

ዜግነት? ጥያቄው ቀጠለ።

ሶቭየት በማለት በታይፕ ጽፋ መለሰችለት።

ክልል?

D.C

ጾታ?

ወ

ዓይነት

N/A

ሕጋዊ ነህ?

http://ethzare.wordpress.com

አዎን::
Interval?
እንድ ኢንተርቫል ፅፋ አስገባች::
ቆም ለማለት PAUSE ለመቀጠል C እንዲሁም ከፕሮግራሙ ለመውጣት ስትፈልጊ ESC መጫን ትችያለሽ::
በየ እንድ ሴኮንኩ ኢንተርቫል የሶቭየት ኤምባሲ ወንድ ሠራተኛ የፊት ምስል በኮምፒውተር ስክሪኑ ላይ መታየት ጀመረ:: ሩል በዚህ ዓየነቱ ልምምድ ብዙ ስለቆየች ረዘም ያለ ግዜ እንድን ምስል መመልከት በፍፁም አላስፈለጋትም:: የፊት ምስሎቹ ሲመጡ በቅርበት ተመለከተቻቸውና ቅርፁን የፊቱን ዓይነት ከመመርመር በቀር ምንም ሳታደርግ ታሳልፈዋለች:: በዋሽንግተን መቀመጫውን ባደረገው የምስራቁ ብሉክ ኤምባሲ ላይም እንዲሁ ምርመራ አደረገች:: ምንም የለም::
እሺ ሌላ የቀረሽ አለ ወ/ሪት ሩል?
የለም፣ ብላ ታይፕ አድርጋ ዓፈችና መለሰችለት::
ግን ለምን ከሥራ በኋላ ተገናኝተን አንጠጣም? ብሏት እርፍ!
ኮዝሞ ሴቶች ሲመጡ እንዲህ ማለት ለምዷል:: የኮምፒውተር ማዕከሉ ዳይሬክተር ይህንን ታውቅ ይሆን ወይ ስትልም ራሷን ጠየቀች:: ምናልባትም አሷው ራሷ ነች እንዲህ እንዲያደርግ የወሰነችው:: ተንኮለኛ!
ሂድ ጥፋ እሺ፣ ብላ ታይፕ አድርጋ ጻፈችና ተርሚናሉን አጠፋችው::
ኮዝሞን በተመለከተ አንድ ደስ የሚል ነገር ቢኖር ስሜቱን መጉዳት የማትችሉ መሆኑ ነው:: አንዳንዴ ግን ምነው ስሜቱን መጉዳት በተቻለ ብላ መመኘድ አልቀረም:: አዲሱ የኮምፒውተር ግኝት በድምጽ መልዕክት ማስተላለፍ የሚቻልበትን መንገድ ያመቻቻል ተብሏል:: ግን ሩል ይህንን ያን ያህል ለማግኘት መናፈቋን እርግጠኛ መሆን አልቻለችም::
ልክ እንደ ሁልግዜው ችግሯን በተመለከተ አምክሀኖታዊ ወደ ሆነ ድምዳሜ ከመድረሷ በፊት ስሚድ ምን እንደነበረ አወቀች:: ተጨንቃለች:: አመክሀኖታዊ በሆነ መንገድ ስታስብ ምንም የሚጠቅም ነገር አላገኘችም:: በመጀመሪያ ነገር የፊት ገፁ ራሱ ተስሎ አይቀረጽላትም:: ፊቱ እኮ ኮምፒውተሩ ላይ መምጣት ነበረበት:: የሁሉም ተቃዋሚ ሕጋዊ የሆነ አካል የቪዛ ፎቶግራፍ ኮምፒውተሩ ላይ አለ፣ መኖር ብቻም አይደለም በየቀኑ አዳዲስ ነገሮች ካሉ ይጨመርበትና ተሻሽሎም ይቀርባል:: ስለላ የሚባለው ነገር ሕጉ-ወጦቹ በፍፁም የማይሰሩት ነው፣ ስለላ የሚባለው ነገር እጅግ ሲበዛ አደገኛ እና ለሕይወታቸውም የሚያሰጋ በመሆኑ ይህንን የሚሰሩቱ ሕጋዊ መሆናቸው ፈጽሞ አያጠራጥርም:: ይህ ቢሆንም ታዲያ ያ ፊቱን ያየችው ሰው እዚህ ስብሰባ ውስጥ ሊገኝ አልቻለም:: የሚከታተሉት ዊልንም አልነበረም፣ እሷ ነው እንዲያውም ሂድ መጣ እያሉ በርቀት የሚያጅቧት:: ደግሞ የሚገርመው ሁለት ብቻ መሆናቸው ነው . . . ይህ ደግሞ ለዚህ ነው ተብሎ አጉል ሰበብ ሲደረደርለት በማይችል መልኩ ሲበዛ ደረጃውን የጠበቀ የስለላ እና ክትትል ሥራ ነው:: ብቻ የሆነው ሆኖ ዛሬ ማታ ዊልስ ጋ ትመጣ ይሆናል ብላ ጠብቃ ይሆናል፣ ምናልባትም ደግሞ ሌሎች ሁለት የጨለመው እስኪነጋ ብለው የሆነ ቦታ እያደፈጡ ይሆናል:: ምናልባት ነው ይኼ::

ምን ማድረግ እንደሚገባት አውቃለች፣ ወደ አለን ኒክሰን ቢሮ በመውረድ ጉዳዩን ሪፖርት ማድረግ:: ይኼ የአካሄድ ጉዳይ ነው የሚሆነው፣ አዎን በቃ! ወደ ቅርብ አለቃ በመሄድ ባንድ ጉዳይ ላይ ሪፖርት ማድረግ ! ተነሳች:: በአለን ፊት ገጽ ላይ የነበረውን ስሜት ማንበብ ችላለች፣ ነገሮችን እየገመተች ነበረ፣ አሁንም ስሜት ውስጥ ናት:: ጥርሷ አፋጨች:: ቢሆንም ማሸናቸን በደምብ መመልከት ይኖርባታል:: ቀን ተሌት የፊለጉትን እስከሚያገኙ ድረስ ቤቷ የሚሰልሏት ሰዎች ይመድብባትና ያስጠብቋታል:: አመነታች:: ወደ ዊልስ እንኳ ልትሄድ መደወልም ተሳናት:: አዎን አትችልማ! የሰላይ ነገር እየታወቀ! ስልኳን ጠልፈውት ይሆናል:: በሪፖርተር ላይ ደግሞ የሷ ስም እንዲኖር አልፈለገችም:: ስለዚህ ተመልሳ ወደ ጓላ ዴገፍ ብላ ተቀመጠች:: ለተወሰኑ ሳምንታትም ቢሆን ከሱ ጋር መገናኘቷን ማቋረጥ አልፈለገችም:: ፒተር አባቱ ጋ ስለሄደ አሁን ጓደኛ አለኝ ብትል እንኳ ዊል ነበረ ባጠገቧ ያለው:: ብቸኛው የሚያስደብራት እሱ ነው ማለት ሳይሆን ግን እንዲያው አሰኝቷት የምትደውልለት ማለት ነው:: የሰላይ አለቆቹ ሰላዮቹን በደምብ ለመመልከት እንዲቀላቸው እሷ እርፋ እንዳትቀመጥ፣ ይልቁንም እንድትንቀሳቀስ ነው የሚፈልጉት:: እሷ ስትንቀሳቀስ ማኅበራዊውን የሰታቴ ድስት ታማስለዋለች ጉዳዩ ካለቀ በኋላም ድስቱ ይንተከተካል በኋላም ማንሳት የማትፈልጋቸው በርካታ ስልኮች፣ መቀበል የማትፈልጋቸው ድግሶች ተከታትለው ይመጣሉ:: ኡፍ!!!! የተወሰኑ ተነባብረው የተቀመጡ ኬብሎችን በማንሳት ማየት ጀመረች:: በቃ አዎን ነገ ጉዳዩ ላይ ብታስብበት ነው ጥሩ:: ስካርሌት ኦ ሐራ የማንም ቂል አይደለችም!
ኬብሎቹን በፍጥነት አነበበቻቸው፣ ከኤምባሲ የሚመጡ ነገሮችን ነው የያዙት፣ በየቀኑ ከማቢያው የሚመጣውን ነው የያዙት፣ ድርቆሽ፣ የገለባ ቅጠል እንዲሁም የስለላ ብስባሽ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ደስ የሚልም አይደል:: የተወሰኑ ብትንትን ብለው የመጡ መረጃዎች ብቻ ታዩዋት ይህ ግን በዚህ ምክንያት ነው አይባልም:: IRA እንደሚጠረጥረው ከሆነ 2000 የሚሆኑ የአሜሪካ ስሪት ለእንግሊዛውያን ልዩ የአየር ኃይል ታስበው የተዘጋጁ ኢንግራ ሰብግሽን መሣሪያዎች ሱሪይ ከምትገኘዋ የአልዴርሾት ዴፖ ማከማቻ ተሰርቀዋል፣ የጀርመኑ ቡንዴስታንግ አባል የሆነች አንዲት እንስት ቦን ከሚገኝ አንድ የአፓርትማ ክፍል ውስጥ ሽሽጋ እና ደብቃ ያስቀመጠቻት የሴት የክንፈር ወዳጅ እንዲሁም በተወለደችበትና ባደገችበት ክልል ደግሞ ባል አላት:: ሩሲያውያኑ በዩኒቨርስቲዎቻቸው ውስጥ የስዊድን ቋንቋ የማስተማሩን ነገር በጣም አጠናክረው ተያይዘውታል በሞስኮ ዩኒቨርስቲ ባለው የኬሚስትሪ ላብ መተላለፊያ ላይ ያለው ቦታ በጣም የሚሰነፍጥ የሽንት ጠረን አምጥቷል፣ በሁለት የሶቪየት እገረኛ የባሕር ኃይል ማሰልጠኛ ካምፖች ያሉ ልብስ ማጠቢያዎች በላምንት በሚያጥቧቸው ሸሚዞች ብዛት ላይ ያልተጠበቀ እና ብዙ ዝቅ የማለት ነገር አጋጥሟቸዋል በእንዱ 16 በሌላኛው ደግሞ እስከ 20 በመቶ ያህል የመውረድ አዝማሚያዎች ታይተዋል:: ከነዚህ በተጨማሪም አንድ ማጥመጃ መረቦቹ በሶቪየት ባሕር ሰርጓጅ መርከብ ውስጥ ተገኝተዋል የተባለ ስዊድናዊ ዓሣ አጥማጅን በተመለከተ ጋዜጦች በፊት ገፆቻቸው ላይ ከዘገቡ በኋላ «የፔርስኮፕ ፍርሀት» የሚል እና በስቶኮልም የተጠራ ስሜት ተፈጥሯል::

http://ethzare.wordpress.com

ይኼን ሁሉ ስታየው በጣም የተለመደ እና አሰልቺ ቢመስልም 12 ሰዓት ላይ ይኼንን ሁሉ ኬይብል ይዛ ወደ ቤቷ ስትሄድ ከሌሉቹ የተሻለ ቀን ማሳለፏን አልተጠራጠረችም።

ወደ ቤቷ ስትሄድ በኋላ ማሳያ መስታወቱ እያየች ነበረ ግን ምንም የለም። ምናልባት እኮ ትተዋት ይሆናል። ወይንም ደግሞ የተሻለ የአሠራር ዘዴ ቀይሰው ይሆናል።

7

አስካርሰን ቀደም ሲል የግራ እጁ የነበረውን እና ባሁን ሰዓት ፍፁም ሌላ የሚመስለውን የሰውነት ክፍሉን ያጥ ብሉ በታላቅ ፍርሀት ተመለከተ። ታዲያ እንዲህ ደፍሮ ይህንን የሰውነት አካሉን ሲመለከት የመጀመሪያ ጊዜው ነበረ። ጉድ! የቀረው አንድ አውራ ጣት ብቻ ነው! ከዚህ ቀደም ጣቶቹ በተቆረጡበት እና ዱሽ በሆነው ቦታ ላይ ጀልባውን በእደጋ ካጣበት ግዜ በኋላ ባሉት ሳምንታት ቀዶ ጥገና ተደርጎለታል። ይገርማል! አሁንማ የጣቶቹ መጋጠሚያ አጥንት እንኳ አልነበረም። ቀደም ሲል ገና ጉዳቱ ሲደርስበት ከነበረው ከፍተኛ የሆነ የደም መፍሰስ እና ከቀዶ ጥገናው ሲያገግም ሕመም ማስታገሻ እንክብሎችን በፍፁም አልወስድም ብሎ ነበረ። በዚያን ወቅት ይህን ያደረገው ሕመሙ እና በውስጡ የነበረው ታላቅ ቁጣ ብቻ ቀሪ መጽናኛዎቹ የነበሩ ስለመሰለው ነው።

ሐኪሙ ዱሽ የሆነበትን ቦታ በጥንቃቄና ቀስ ብሎ በጥጥ ፋሻ አሰረውና እንጥቱ ላይ ፋሻውን አነጥለት። «አይ ከእንግዲህ ሽፋን ልብስ አያስፈልግም፤» አለ። «ሙሉ በሙሉ ቁስልህ እስከሚፈወስ ድረስ ከግድት ለመከላከል ሲባል ብቻ ነው በዚያ ላይ እብጠቱም እስኪያበቃ። ስለዚህ ቁስሉ እስኪፈወስ ይኼ ባንገትህ ላይ የተንገተው ፋሻ ይቆይ። ሲሻልህና ደህና ስትሆን ሰው ሰራሽ አካል ልናደርግልህ የምንችልበትን መንገድ እንፈልጋለን።»

«አህ?» የሚል ቃል አወጣ አስካርሰን።

«ይኼ እንግዲህ ሰው ሰራሽ ወይ ከፊል እጅ ማለት ነው አውራ ጣትህን ተክቶ ትንሽ ከግድረግ ያለፈ ምንም ጥቅም አይኖረውም፣ ሆኖም ግን ሥነ-ውበታዊ መሻሻልን በእንተ ሳይ እንደሚያመጣ አረጋግጥልህለሁ»

አስካርሰን በባዶነት ስሜት ወጣቱን ሰው አፈጠጠበት።

ዶክተሩም የራሱን እጅ ወደ ላይ በማንሣት አውራጣቱን ወዘወዘው። «ሰው ሰራሹ አካል ሲገጠም አውራ ጣትህን በደምብ መጠቀም ትችላለህ በዚያ ላይ ያ ዱሽ የሆነው ቦታም እንትን አይመስልብህም. . . ማለቴ ቆንጆ ሆኖ ይታያል።»

አስካርሰን ብድግ አለና ሱሪውን ወደ ላይ በደህናው እጁ ከፍ ከፍ አደረገው። ልብሱ እላዩ ላይ ሰፍቶበታል ለምን ቢባል ቀላል የማይባል ክብደት ነው የቀነሰው። «አመሰግናለሁ ዶክተር፤» አለ። «መቼም በጣም ነው የረዳኸኝ፣ እንክብካቤህም ሽጋ ነበረ፣ እግዜር ይስጥልኝ»

ገነር ኮሪደር ላይ ሁኖ ይጠባበቀው ነበረ። በመኪና ማቆሚያው ቦታ ሲደርሱም አንድ ሰው በፍላሽ ካሜራ ፎቶ ያነሳው ሲሆን አንድ ሌላ ሰው ደግሞ

ጥያቄዎች ሊያሻሽላቸውበት ሞክረ እሱ ግን ገፋ አድርጓቸው በመሀከላቸው በማለፍ ገነር ቮልቮ ውስጥ ገባ። ቀደም ሲል ስለ አደጋው ጋዜጦች በስፋት ያወሩ የነበረ ቢሆንም ባሁን ሰዓት ግን ጋብ ያለ መሰሉት ነበረ። በስዊድን ውስጥ የባሕር ሰርጓጅ መርከቦች ጉዳይ ከፍተኛ ዜና ሲሆን በዚህ ሰበብ አደጋ የደረሠበት ብቸኛው ሊገኝ የሚችለው ሰው አስካርሰን ከመሆኑ አንፃር ጋዜጠኞቹ ዘለው ቢሰፍሩበት አያስገርምም። «ጃረ ሞቼ በተቀበርኩ፤» አለው ለገነር።

ገነር ብረጅሙ ተነፈሰና ራሱን በእምንታ ነቀነቀ። ከስቶክሆልም ከተማ በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደሚገኝ አንድ የማዘጋጃ ቤት ይዞታ የሆነ መቃብር እየተሽሎከሎከ ነድቶ ሄደ እና እዚያ ሲደርስም ቆመ። አስካርሰን ከመኪናው ወረደና ልጁን ተከትሎ በሁለት ሊሎች ቦታዎች መሀከል ተሰንቅሮ ወደሚገኝ አንድ ትንሽ መሬት ደረሱ። ልሙጥ በሆነው ደንጊያ ላይ ያለውን ስም እና ቀንም አፍጥጠ ተመለከተ። «በቃ ልታደርግ የምትችለው ከፍተኛው ነገር ይኼ ነው?» የሚል ጥያቄ አቀረበለት።

ገነር ከንፈሩን ነከሰ እደረገና ወደ ሌላ አቅጣጫ ተመለከተ። «አባዬ፣ እኛን እኮ እኛን እኮ በስቶክሆልም አንድም ቤተክርስቲያን አውቅና አትሰጠንም። ማንም ሰው እዚህ እንደዚህ ነው የሚቀበረው እና የሚንቁን፣ አሳንሰው የሚያዩን ምናምን እንዳይመስልህ»

«አዝናለሁ ልጄ» አለ አስካርሰን።

«እሱንም እንደምንናፍቀው አስብ» አለው ገነር። «ስለ ኤልሳ ስታስብም ይኼንን ነገር አስታውስ፣ እሷም በደምብ ነው የተቀበለችው። ግን እሷን በተመለከተ ያንተን አርዳታ እሻለሁ።

«እኔማ ከመንገዷ ዞር አልላታለሁ» አለ አስካርሰን። «ቤት መሄድ ነው ያስኘኝ ይልቅ» በማለት ወደ መኪናዋ ተመለሰ።

«ይኼውልህማ. . . ስማኝ አባዬ. . . ከእኛ ጋር እንድትኖር ነው ፍላጎታችን። እንተ በሆስፒታል ሳለህ አጋርታማ ከፍሉን ሸጥነውና በርካታ ደሴቶች ባሉበት ቦታ ላይ ሌላ ቤት ገዛን። በጣም ነው የምትወደው።»

አስካርሰን ራሱን ነቀነቀ። «አይ ተውት፣ እኔ ለምን ሸክም ልሁንባችሁ ልጆቼ? ብቻችሁን መኖር እንደምትፈልጉ አውቃለሁ»

«አይደለማ አባዬ፣ ያንተን ንብረቶች ሁሉ አምጥቼ እንድ ክፍል አድርጌልሀለሁ፣ ያ ክፍልም ያንተ ነው። እዚህማ ምንም ቀረኝ አትልም»

አስካርሰን በድንገት ከቀዬው በግድ የመነሳት እና የመከፋት ስሜት አጠቃው። ባለቤቱ በሞተች ጊዜ ቤቱን ሸጦ በዚያው መንደር አቅራቢያ ወደሚገኝ ቤት ገብቶ ነበረ።

መጀመሪያ ሰሞን በጣም ባይተዋርነት ተሰምቶት እንዲሁም ፍፁም እንግዳ ሆኖበትም ነበረ። ይሁን እንጂ ቤት የሚጠብቅለት ሰው አልነበረውምና ሲውል የግዱን ለመደው። ያው አሁን ቤት አልባ ነው።

«ባክህ ለጥቂት ግዜም ቢሆን ና እኛ ጋ አባዬ ያንን በደሴቶች ቦታ መሀከል የገዛነውን ቤት በጣም ነው የምትወደው፣ በዚያ ላይ የራስህ ክፍል ይኖርሀል፣ ምን ነካህ አባዬ እንዴ. . . ውሃው ላይ እኮ ነው ኑሯችንን ያደረግነው፣ በጣም ደስ ይላል የራስህ ቤት ከሆነ የምትፈልገው ደግሞ ከጀልባው የዋስትና ገንዘብ አለ። እኔ በማስቀምጥበት ባንክ ሳንተም በስምህ ሂሣብ ከፍቼልሀለሁ።»

http://ethzare.wordpress.com

አስካርሰን ምንም አላለም። ሞንቀላቱን በመኪናው ወንበር ራስ ማስደገፊያ ላይ አድርጎ ዓይኖቹን ጨፈነ። ባለፉት ሳምንታት እንድ ነገር ደርሶበታል። ገነርን ለመቃወምና ለመቋቋም የሚሆን በጎ ፈቃድና ብርታት አልነበረውም። ስለዚህ ወደ እሱ ከገነርና ከልጆቹ አቅጣጫ ይነፍስ የነበረው ነፋስ እጁን በመስጠት ያደረጉኝን ያድርጉኝ ሲል ወሰነ።

የተባለው ቤት ጉስታበስበርግን አልፎ የሚገኝ ሲሆን ልክ ገነር እንዳሰው ነበረ፣ ቤቱ የተሠራው ውሃው ላይ ነው በዚያ ላይ አካባቢው እጅግ በጣም ያምራል። በሳሉኑ ወይንም እንግዳ መቀበያ ክፍሉ ውስጥ ሰዓሊዎች እየሠሩ ሲሆን ኢልሳም ለወንድ የሚሆን መሳቢያ ያለው ቁምሣጥን ሥራን ትቆጣጠራለች። ስታየው ደንግጣ ነበረ። ኢልሳ በወጣትነት ዘመኗ ሞዴል የነበረች ሲሆን አሁን እንዲህ ሥልጥ ብላ ወደ አርባዎቹ ከገባች በኋላም ያ የወጣትነት ምስኪን ውበቷ አሁንም ሳይረግፍ አለ። አስካርሰን እንደታዘበው በፊቷ ላይ እዚህና እዚያ ጨምደድ ያሉ ቆዳዎች ኖረው በዚያ ላይ አለቅጥ ሜክአብ ብትጠቀምም እንዲሁም ጂንሷም በጣም ጥብቅ ያለባት ቢሆንም አሁንም ታምራለች። ጉንጩ ላይ እንድትስመው ተመቻቸላት።

«አባዬ እንዴት ነህ?» አለችው።

በዚህች በደምብ በማያውቃት ሴትዮ አባዬ ተብሎ መጠራቱን ብዙም አልወደደውም። ባለፉት በርካታ ዓመታት ጥቂት ግዜ ብቻ ነው ተገናኝተው የሚያውቁት።

«ክፍልህ ዝግጁ ነው፣ ናማ ላሳይህ አባዬ» በማለት ወደ ላይ መርታው ደረጃውን ወጥተው በኮሪደር በኩል ጥግ ላይ ወዳለ አንድ ሰፊ ክፍል ገቡ። ይህ ክፈል ደስ በሚል ሁኔታ ቀለም ተቀባብቶ ያማረ ሲሆን እንዲያውም እውነት ለመናገር ከሌሎቹ ክፍሎችም በላይ ዓይነግቡ እና ማራኪ ነበረ። በፊት ከነበሩት የሕንፃ ክፍል ይዘዋቸው የመጡት የቤት እቃዎች ቤቱን አልሞሉትም። ልብሶቹን ቁም ሣጥን ውስጥ የሰቀሉለት ሲሆን በመልበሻ ጠረጴዛው ላይ ደግሞ ትንሽ ወርቅ ቅብ ዋንጫ ነበረ።

ኢልሳ እነሳችውና አቀበለችው። «ኤቤ እምና በቀዘፋ ውድድር አሸንፎ የተሸለመው ነው በጣም የሚወደው ስፖርት ነው»

አስካርሰል ልክ ሲይዘው ለስለስ ያለው ብረት እጁ ላይ ተሰማውና እላዩ ላይ የተቀረፀበትን ጽሑፍም አነበበ።

«አባዬ ያው እንግዲህ ትንሽ ረፍት አድርገህ ትረጋጋ ዘንድ ብቻህን ለተወሰነ ግዜ እንተውህለን» አለ ገነር። «ትንሽ ጋደም ብትል የምትጠላ አይመስለኝም»

«ኩሽና የተጣደው ሻይ እንደደረሰ መክሰስ ብጤ እንበላለን፣» አለችው ኢልሳ ደግሞ። በፈለክ ሰዓት ብቅ በል አባዬ»

አስካርሰን ራሱን በእምንታ ነቀነቀ። በመስኮቱ ፊት ለፊት አንድ ነቅነቅ የሚል ወንበር ነበረ። ወደ መስኮቱ ተራምዶ ሄደና ቁጭ ሲል በመስኮቱ ውሃው ፊት ለፊቱ ታየው። የኤቤ ዋንጫ አሁንም እጁ ላይ እንዳለ ነው። በተለየ ፕላኔት ላይ እርፎ ሊሆን ይችላል። ከሕይወቱ ቀላል የማይባል ግዜውን ከስዊድን ደቡባዊ ክፍል ከሚያውቃቸው ሰዎች፣ ቦታዎች ብሎም ጀልባዎች ጋር ነው ያሳለፈው። እና አሁን በዚህ ፍፁም በማያውቀው ባይተዋር ቤት እንግድነት ተሰማው። የገዛ ልጁ እና የእንጀራ ልጁ እንኳ ባዳ ሆኑበት በመስኮቱ ውሃውን

አሻግሮ በባልቲክ ያሉ ቋጥኝማ ደሴቶችን ተመለከተ። አዎን ከሚያየው መሀከል የማያውቀው የመሰለው ውሃው ብቻ ነው። ዋንጫውን እንደጨበጠ በወንበሩ ላይ ወደ ፊት ወደኋላ ረጋ ብሎ ነቅንቅ አለ። በውስጡ በመቀጣጠል ላይ ያለው ንዴት አንድ የሆነ ማብረጃ መንገድ እስከሚያገኝ ድረስ አይለቀውም። እንባ ከዓይኖቹ ኮለል ኮለል በማለት መልኩን ቀይሮ ጭራሽ አሁን ደግሞ ገርጥቶ በነበረው ፊቱ ላይ ፈሰሱ። ሲያለቅስ የመጀመሪያ ግዜው ነበረ። ከዚህ በኋላ ደግሞ እያለቅስም።

8

ሩል ቢሮዋ ተቀምጣ እንዳለች በትካዜ ስሜት መስኮቱ መደገፊያ ላይ በመጠውለግ ላይ ያሉትን ተክሎች ትመለከታለች። ውጭ ደግሞ በቨርጂኒያው የገጠርማ መሬት ላይ በጣም በብዛት ተከማችቶ የሚታየው አረንጓዴና ለም የሆነ ምድር ይህን ውስጧን በጥቁር ሀዘን ለመሙላት የምታደርገው ጥረት ላይ የሚቀልድባት መሰለ። የእነዚህን ተክሎች ስም አታውቅም ግን ሞሊ የተባለች በዲፓርትመንት ፀሐፊነት የምታገለግልና ያለችበት ክፍልም የብሔራዊውን ተክሎች ጋርደን የሚመስል ጓደኛዋ «እነዚህን ተክሎች እንኳ መግደል አትችይም» ብላታለች።

ተሳስታለች። እሷ የሰውነት ቆዳዋ የተወሰነ የማይታይ መርዛማ ጉምን በላብ እንደሚያጠፋ እና በዚህ የተነሣም አረንጓዴ የሆነ ነገርም ከርቀት የመመለስ ችሎታ እንዳላት ነው የተማመነችው። እሷ እንግዲህ ኦርጅናሊዋ Black Thump መሆኗ ነው ይኼ የመጠውለግ ችሎታ በሙያ ሕይወቷም ዘልቆ የገባ ነው የመሰላት ለምን ቢባል ማጆሮቭ አሏት የምትሰራው ምርምር ፍሬ አልባ ወደሆነ ድምዳሜ ሳይደርስ አልቀረም። የኢጀንሲውን ኮምፒውተሮች ያለ ፈቃድ ተደብቃ በረበረች፣ ሳረነረች፣ እስከ CIA ምስረታ ድረስ ወደ ኋላ ዘልቀው በ1950ዎቹ ውስጥ የተቀዱ ቴፖችን አደመጠች ከዚያ በፊት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ቀርተው የተገኙት የOSS ፋይሎች ብቻ ነበሩ የቀሩት። በ1930ዎቹ ውስጥ ስታሊን የቀይ ጦሩን ክፍል እና የኮምዩኒስት ፓርቲውን ክፉኛ አዳክሞትና በድርጅታዊ አሠራር እሽመድምዶት ስለነበረ በወቅቱ ስለላዊ ጸሰሳ የሚባለው የቀረበ ነገር የሚከናወኑት የውጭ ጉዳይ ሚ/ሩ እና ዋንኛው ጦር ብቻ ነበሩ። ታዲያ እያንዳንዳቸው ለራሳቸው በወቅቱ አጣዳፊ ብለው ባሰቧቸው ጉዳዮች ዙሪያ ብቻ ነበረ ስለላዊ ጸሰሳቸው የታጠረው በዚያ ላይ ማጎደሮቹ የት እንዳሉ እግዜር ብቻ ነው የሚያውቀው።

ስለ ማጆሮቭ ለ EXCOM TWO ካቀረበችው ሌላ እንድም ተጨማሪ ጥሬ ሐቅ እና መረጃ ለማቅረብ ያልቻለች ሲሆን ያንን እንደ ስሜት ቀስቃሽ ወይንም የምግብ ፍላጎት መክፈቻ ለመጠቀም እስባ ከሆነ እውነት ለመናገር ማንም የራበው አልነበረም ማስታወሻዎቿን ወደ መከላከያ ሚ/ር የደህንነት እና ሰለላ ልዩ ንዑስ ክፍልና የብሔራዊ የደህንነት ቢሮ በመላክ መረጃ ይሰጣት ዘንድ ከጠየቀች ሰንበትበት ብትልም ከሁለቱም ቢሮዎች እስከ አሁን ከዝምታ በቀር ምንም ያገኘችው የለም።

http://ethzare.wordpress.com

ከዚህ በመቀጠልም እዚያው ቢሮዋ ጉብ ብላ እንዳለች በጠረጴዛዋ ላይ ቦታ አጣብቦው የነበሩትን ሪፖርቶች እና የቴሌግራም መልዕክቶች አገላበጠች። የሚት ሥራዎችን ለእስጠኚ ቡድን አባላት ያከፋፈለች ሲሆን እሁን የቀራት የራሷን ማቴሪያል በማንበብ በርካታ መረጃዎችን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለማግኘት መጣር ነበረ። ይኼ ደግሞ አስደሳች እና አስደናቂ የሆኑ የልብ ወለድ እና የፊልም ስክሪፕት ደራሲዎች የሚያውቁ ከሆነ ስለላ ከሚባለው ነገር ውስጥ እስከ 90 በመቶውን ያጠቃልላል። ያም ማለት ማንበብ፣ ማስታወስ፣ ማገናኘት፣ መተንተን እና አልፎ አልፎ ደግሞ በራስም አንድን አዲስ ነገር ማግኘት። ታዲያ እንዲህ ባሉ ቀኖች ነው አንዳንድ ግዜ የውጭ አገር ሥራ መስራት የሚያሰኛት። ለምን ቢባል እዚያ ቢያንስ ቢያንስ በውጭ የምትገናኛቸውና ሊጠ ቅሟት የሚችሉ በርካታ ሰዎችን ልታገኝ ትችላለች፣ ልክ ይህን ግዜ በጅ ሲቀረቀር ሰማች።

ቀና ስትል ማርቲን የተባለ ግን የማታውቀውን ሰው ተመለከተች። ይኼ ሰው በዓይን ታውቀዋለች እገጂ በዚህ ኤጀንሲ የሥራ ክፍሉች የትኛው ውስጥ እንደሚሠራ እግዜር ይወቀው።

«እንደምን አደርሽ ወሪ ሩል?» አላት ሰውየው። «ቀደም ሲል የጠ ቅሽኝን አንድ መረጃ ነው ይዤ የመጣሁት» በማለት አንድ ትልቅ ኤንቨሎፕ ሶስታ አሳያት።

«እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ፣ ግባ እስኪ ቁጭ በል» አለችው ከዚያ ብትንትኑ ከወጣ ሐሳቧ የሚያቋርጣት ማንኛውም ነገር ትፈልግ ስለነበረ በሱ መምጣት ተደሰታ «ለመሆኑ ምንድን ነው ታዲያ ያመጣህልኝ?»

ማርቲን ከኤንቨሎፑ ላይ በፎቶግራፍ መልክ የተለጠፈ ማጎተም መሰል ነገር ገነጠለ። «በሳተላይ የተነሣ፣ ከሶስት ቀናት በፊት፣ ላቲቪያን ኮስት ላይ» ይላል።

ለመሆኑ በላቲቪያ ኮስት ዙሪያ ምን ይምጣልኝ ብላ ጠይቃ ነበር? «እስኪ እንየዋ» አለች ሪፖርቶቿን እና የተሌግራም መልዕክቶቿን እየሰበሰበች ወደ መሳቢያው በማስገባት ጠረጴዛውን ነፃ እያደረገች።

ማርቲን ፎቶግራፉን ፊት ለፊቷ ዘረጋው። «ይኼ የላይፓጃ ደቡባዊ ክፍል ነው።

«ምምምም፣» አለች ሩል።

ማርቲን ጠቀሞ አመለከተ። ይኼኛው ማዕበል የሚበዛበት ሐይቅ ግን በባልቲክ ማዕበል የሚባል ነገርም የለም። ወደ ባሕሩ የሚገባው በዚህ ጋ ነው።

ሩል ከዚህ በመቀጠል ሰፋ ብለው በመደዳ ወዳሉ በሐይቁ ጫፍ የሚገኙ ሕንፃዎች አመለከተች። «ይኼኛው ጀልባዎች የሚቆሙበት ጻርቻ ወደብ ነው?» በማለት ወደ ጻርቻው አመለከተች።

«አዎን ልክ ነው እንደዚያ ዓይነት ነገር ነው። የተካበደ ነገር አይደለም ለመዝናኛ ብቻ የሚጠቀሙባቸው ጀልባዎች ናቸው። ግን ይገርምሻል በእጎራባቹ ላይ ያለው ማንኛውም አገልግሎት ለማግኘት የሚቻልባቸው የስፖርት ኮምፕሌክሶች ናቸው ያሉት።» አለና ማርቲን አሳያት። «ቴኒስ ኮርት፣ ሚጻማ የግሰልጠኛ ቦታዎች፣ የሶከር መጫወቻ ምናምን ነው ያለው በጣም ሰፊ ነው። ከዚያ በተጨማሪም ሯጮች በተሰያዩ አትጣጫዎች ያሉ ሲሆን አትሌቲክ የግይሰሩት አግሪኖች የመሩአና የጫሕር ኃይሉን ልብስ ነው ለብሰው ያሉት

አንዳንዶቹን እንዲያውም ማዕረጋቸውን ከዚህ ላይ ሁነን በማንበብ መረጻት እንችላለን።

«የዩኒት ልምምድ ይመስላል ይኼኖው፣» አለች ሩል በማዕረግ ተከፋፍለው የቆሙ ሰዎችን በማመልከት። «እይደለም፣ ሩጫ ላይ ያሉ ሰዎች ናቸው» ሲል ማርቲን ምላሽ ሰጣት። «ለላብ መከላከያ የሚሆን ልብስ ለብሰው ነው ያሉት»

ሩል ራሷን በእምንታ ነቀነቀች። «ለመሆኑ ከነዚህ አሁን ካየናቸው ውስጥ እኔ ቀደም ሲል የትኛው ነበር እንዲመጣልኝ የጠየቅኩት?»

ማርቲን ከሕንፃዎቹ አጠገብ ወዳለ አንድ የመኪና ማቆሚያ ጠቆመች። «በጣም ደስ የሚል መኪና ነው። መርሰዲስ ነው ወይ 380 ወይ ደግሞ ባለ 500 ሞዴል SE ሊላን ነው ብርማ የብረት ቀለም ቅብ ያለው ነው። ሩሲያውያኑ በማንኛውም መኪና ላይ ይህን መሰል ቅብ አይጠቀሙም በሞስኮው የጀርመን ኤምባሲና በርካታ የቆንጽላ ጽ/ቤቶቹ በቀር በሞስኮው ከሶስት በላይ መርሰዲስ የለም። ለነገሩ ማንስ ማርቸዲስ ልንዳ ይላል?»

ሩል መኪናውን አፍጥጣ ተመለከተች። «ታርጋ ቁጥራቸውን ከላይ ማየት አለመቻሉ ያሳዝናል፣ ግን በዚህ አንድ ነገር እናረጋግጣለን። NSA ደውለን ለምን አንግሉን እንዲያሻሽሉልን አንጠይቃቸውም? የተወሰኑ የሕንፃ መግቢያዎችን አልያም ደግሞ ማን ያውቃል የሰው ፊት ልናይም እንችላለን ብቻ ምንም ሆነ ምን በመኪናዎቹ ላይ የተለጠፉትን የታርጋ ዓይነቶች መመልከት አፈልጋለሁ። ሩሰያውያኑ ለሁለም ታርጋ ኮድ አላቸው. . . ኮድ ዲፕሎማቲክ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የንግድ ባለሥልጣን፣ ጋዜጠኛ ወዘተ ይላሉ. . . በዚያ ላይ የከተማው ስምም ይፃፍበታል።

ማርቲን ትከሻውን በግድ የለሽነት ነቀነቀ። «የሚቀጥለው የሳተላይት ግለፊያ በዚህ ቦታ ላይ መች እንደሚያበቃ አላውቅም በዚያ ላይ የተነሱትን የተለየ እንግል ለመጠበቅ ስልጣኑም የለኝም። እና ኒክሰን ወይንም DDI ያሉ ሰዎች ናቸው ያንን ግድረግ የሚችሉት።»

ጥሩ እንደዚያ ከሆነ ጥያቄ ማቅረቡን ለእኔ ተወው፡ በጣም እግዜር ይስጥልኝ ማርቲን። የትም ላይሄድ ይችላል ግን ማን ያውቃል? ግን ለማንኛውም ይኼንን እኔው ጋ ልትተውልኝ ትችላለህ?»

«አዎ ግን ሩይሉ ውስጥ እሱን ተክቼ ለማስቀመጥ ጥብቅ ደረሰኝ ያስፈልገኛል»

ሩል በዚህ መሠረት የሩይል ቁጥሩን ቁኑን እና ፎቶግራፉን የሚጠቅስ ደረሰኝ አዘጋጀችለትና ማርቲንም ሄደ። ከዚህ በመቀጠል ለNSA በአላን ኒክሰን ፊርማ ላይታጃ የሚባለው ከተማ ላይ ስለላ እንዲካሄድ የሚጠይቅ ደብዳቤ ፅፋ ለፀሐፊዋ በታይፕ እንዲያዘጋጅላት ሰጠችው። «በል ይኼንን ፈጠን አድርገህ ሥራልኝ እሺ፣ ጂፍ» አንድ በሠራተኛ ጉዳይ ንዑስ ክፍል ያለ ቀልደኛ ብጤ ባለሞያ ወንድ ፀሐፊ መድቦላታል። ፀሐፊዋ ደግሞ ከሳም ባነሰ ስሜት ነበረ ይኼንን አሁን የሰጠችውን ነገር የተቀበለው።

«ግን በቅድሚያ ሳምንታዊ የተከለሱ ሪፖርቶች ብሠራልሽ አትመርጪም?» ሲል በታይፕ መፃፊያው ላይ እንዲጽፈው ቁጭ አድርጋለት የነበረውን እንስቶ እያወጣወዘ ተጎሜነጪ።

http://ethzare.wordpress.com

«ባክህ ጀፍ፣ ጂኒ ጃንካ አብዝተህ ይህንን ባትሠራልኝ የሳተላይት ይለፍ ፈቃድ ነው የሚቀርብኝ፣ ስለዚህ መንጫነጭ ትተህ ትሠራለህ አትሠራም?»

ይህንን ሲለማ በረጅሙ ተንፍሶ ማሽኑ ላይ ወረቀት ሰክቶ ጠቅ ጠቅ ማድረጉን ጀመረ።

ሩልም ወደ ጠረጴዛዋ ተመልሳ ቁጭ በማለት ፎቶግራፉን ተመለከተችው። ይኼ በፎቶግራፉ ምስል የተመለከተችው ሰፊ ክልል የስልጠና ማዕከል ግቢ ሊሆን እንደሚችል ያስቀመጠችውን ግምቷን በቀላሉ ልትተወው አልቻለችም በዚያ ላይ ጥርጣሬዋን ከምር በመውሰድ ለማረጋገጥ የምትጥርበትን ልምድ ፈጥራለች። በርግጥ ከሚችሉት የስልጠና ፋሲሊቲዎች አንፃር ይኼኛው ግቢ ውስጥ ያሉት ቤቶች በጣም በዝተዋል። ስለዚህ እዚህ ግቢ ውስጥ እንድ የሚሰጥ ትምህርት መኖር አለበት።

አተኩራ በመሮጥ ላይ የነበሩት ወንዶች ላይ አፈጠጠች። አትሌቶች በማዕረግ ተከፋፍለው ልምምድ የሚያደርጉበት ሁኔታ በሶቭየት ጎብረቶች ዘንድም ቢሆን የለም፣ ለምን ቢባል እንደዚያ ከሆነ ልምምድ በጣም ሲበዛ ወደ ግለሰባዊ ደረጃ ወርዶ ሊታቀድ ነው ማለት ስለሆነ ነው፣ ይህ ደግሞ እይሆንም። ስለዚህ ይኼ አሁን በፎቶግራፍ ምስሉ ላይ ያየችው ግቢ የወታደራዊ ተቋም መሆን አለበት። እነዚህ ሲሮጡ ያየቻቸው ወንዶች ሰልጣኞች ናቸው። ግን ልምምድ የሚያደርጉት ለሚቀጥለው አሊምፒክስ ውድድር አይደለም። በዴስኳ መሳቢያ ውስጥ አጉልቶ የሚያሳይ ሌንስ አግኝትና ፎቶግራፉ ላይ አድርጋ ተመለከተች። ግን ምንም ወታደራዊ ነው የሚያስብል ፍንጭ አጣች፣ መተኮሻ ቦታ እንኳን የለም። ይኼ እንዲያውም እልህ የሚያሲዝ ነው፣ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ካምፕ ቢሆን በርግጠኝነት ለመተኮሻ የሚሆን ቦታ ይኖረዋል፣ ተኩስ እኮ የኦሎምፒክ ውድድሮች አንድ አካል ነው።

በመቀጠልም ሌንሱን በግቢው መጠነ ዙሪያ አካባቢ ወዝወዝ እያደረገች ተመለከተች። ድርብ አጥር መኖሩን በማስተዋል በሁለቱ አጥሮች መሀከል ያለው ቦታ የፈንጂ ማምከን እንደተካሄደበት እርግጠኛ ሆነች። ታዲያ በስፖርት ማሰልጠኛ ቦታ ላይ ማን አበድ ነው ሁለት አጥር የሚያስፈልገው? ጀልባዎቹን ስትመለከት ምነው ዊልስ አጠገቤ በኖረና ስለ ጀልባዎቹ ባስረዳኝ ስትል ተመኘች። እነዚህ ጀልባዎች ስትመለከታቸው ለመዝናናት ብቻ የተሰሩ ነው የሚመስሉት። የተወሰኑ ከዳርቻው አጠገብ ታስረው የቆሙ የውድድር ጀልባዎች ያሉ ሲሆን ራሱ ፎቶግራፉ ላይ ባለ ስኬል በመታገዝ በዚህ ባሕር ዳር አጠገብ ያለው ትልቅ የሚባል ጀልባ ወደ ሰላሳ እምስት ሜትር ግድም እንደሚሆን አወቀች። ከባሕር ዳሩ ላይ ያለው ቦታ ኮንክሪት በሚመስል ነገር ገደብ የተበጀለት መሆኑን ስታስተውል ደግሞ ግራ አጋባት። በፓርክ ውስጥ ያለን የሐይቅ ጫፍ እስታወሳት ግን ደግሞ እዚህ ቦታ ላይ ሣር የሚባል የለም ያለው ነገር ዳርቻን ያጣበበው ለስለስ ያለ ተፈረካካሽ ድንጊያይ ብቻ ነው። ውሃውን ዳርቻው ላይ እንዲህ ለመገደብ የሚያስፈልግበትን ምክንያት ከምንም አንፃር ብታስበው ትርጉም አልሰጥ አላት።

ጀፍ ማስታወሻውን ይዞ መጣ። «ይኼንን ለሚ/ር ኒክሰን ልስጠው እንዴ?» ሲል ጠየቃት።

«አይ ተወው እኔው ራሴ እሰጠዋለሁ፣» አለች ወረቀቱን እየተቀበለችው። «አንተ ወደ ክለሳ ስራዎቹ ብትመለስ ይሻላል።» አለች ከዚያም

በኮሪደሩ አድርጋ ፍፁም ምቹ እና የተቀማጠለ ወደነበረው የኒክሰን ቢሮ አመራች።

በሩ ዝግ ነበረ። ፀሐፊውም ተመቻችታ ተሽከርካሪ ወንበሯ ላይ ጉብ እንዳለች ጥፍሯን ትሞርዳለች። «ከሰው ጋር ነው እንዴ?» ስትል ሩል ጸሐፊዋን ጠየቀቻት።

«እሱ እንኳ አይደለም፣ ግን ማንም ቢመጣ እንዳታስገቢ የምሠራው ሥራ አለኝ ነው ያለው።» አለቻት ወጣቷ ፀሐፊ። ይህንን ተናግራ በሆነ የሴረኝነት ስሜት ወደፊቷ ደገፍ አለች . . . ፀሐፊዋ። «ይሽውልሽ፣ ማለት በእኔ እና ባንቺ መሀል ይሁን ግን የሌንዳይግተንን መጽሀፍ እያነበበ ያለ መሰለኝ። ስለዚህ እኔ ጆን ጋ ልሂድ እንቺ እኔ ስለሌለሁ ምንም ያላወቅሽ በመምሰል በርግደሽ ግቢ»

ሩል በልጅቷ ፍጥነት እና ብልሀት ከልቧ ሳቀችና ፀሐፊዋ ከአጠገቧ እስክትርቅ በመጠበቅ በሩን እንድ ግዜ ብቻ ኪ ኪ አድርጋ ኒክሰን ምላሽ መስጠት ከሚችልበት ፍጥነት በላይ በመሆን በርግዳው ገባች። እግሮቹን ጠረጴዛው ላይ አድርጎ ዘና ብሎ ሲያነብ ነበረና በድንገት በሩ ሲበረገድ እግሮቹን ከጠረጴዛው ላይ ሲያነሳ ከነ ወንበሩ መሬት ዘሞ ሊል ምንም አልቀረውም ነበረ በዚህ ድንገተኛ ነገር ተደናግጦ በወሰደው እርምጃም መጽሀፉን ወለሉ ላይ ጣለው።

«በስመ! አብ ምነው በጣም ነው ያስደነገጥሽኝ»

«ይቅርታ ግን እንድ ግዜም ቢሆን እንኳኩቼ እኮ ነው የገባሁት»

በድንጋጤና ፍጹም የሚሠራውን በማጣት ጠረጴዛው ላይ ተነባብረው የተቀመጡ ወረቀቶችን በደመነፍስ መነቃቀራቸው። «እሺ በሠላም ነው? ምን ፈለግሽ? ሲል ብስጭቱ ሳይለቀው ጠየቀ።

«ለNSA በሳተላይት ፎቶ እንዲያነሱልን በፃፍኩት ማስታወሻ ላይ ፊርማህን ፈልጌ ነው»

«የምን ፎቶ ነው ለመሆኑ?»

«በሶቭየት ጎብረት ባሉት ልዩ መኪኖች ላይ ክትትል ተደርጎ መረጃ እንዲጠናቀር ያልጠየኩት ሰው የለም፣ በዚህ መሠረት ነበረ እንዱ ላቲቪያን ኮስት ላይ በሳተላይት የተነሣ ፎቶ ይዞልኝ የመጣው። በጣም ስሜት የሚያጭር ትንሽ ግራ የሚያጋባም ቦታ ነው። በባዶ ዓይን ሲታይ ስፖርታዊ ልምምድ የሚደረግበት ማሰልጠኛ ይመስላል ግን አረ የሚገርም ነገርም አለው። በመኪና ማቆሚያው ላይ እንድ ግርቼዲስ ቆማለች ግን የጀርመኑ አምባሳደር እንዲህ ያለውን ቦታ እንደማይጎበኝ እርግጠኛ ነኝ ስለዚህ የዚህችን መኪና ታርጋ ኮድ ማንበብ እንችል ዘንድ ከአንግል ላይ የሚነሳ ሌላ የሳተላይት ፎቶ ሊኖር ይገባል ብዬ ነው ይህንን ጥያቄ ማቅረቤ» አለችና ሜሞውን ሬቱ አስቀመጠችለት።

ኒክሰን የጣመው አይመስልም። «ለመሆኑ በሳተላይት የሚነሣ ፎቶ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ ታውቂያለሽ?»

እሷ በርግጥ ለሳተላይት ፎቶ የሚያስፈልገውን ወጪ የምታውቅ ሲሆን እሱ ግን እንደማያውቅ እርግጠኛ ነች። «አይ አላን. . . እንዴት መሰለህ? እኛን የሚያስከፍሉን መስሎህ ከሆነ እያስከፍሉንም በነሱው በጀት ነው የሚሠራው። አይዞህ ምን እንተ ደግሞ!» ስትልም አደፋፈረችና አባበለችው። «እንዲያውም

http://ethzare.wordpress.com

እነዚያ ሥራ ፈት ቁጭ ብለው ደመወዝ መብላት የለመዱ ሰነፎች የሚሰሩት ያገኛሉ»

«ይኼ ማለት ያ . . . ማን ነበረ ስሙ? ፈንሶቭ ነው?»

«ፈርሶቭ ነው፣ ማጆሮቭ። የተወሰነ መረጃ አጠናቅሬ በሱ ማንነት ዙሪያ ከዚህ ቀደም ልኬልሀለሁ። በ HUMINT መረጃ አንዲጠናቀርም ጠይቄያለሁ ግን በዚህ ብዙም ተስፉ አልሰንቅኩም። ባለፉት የተወሰኑ ዓመታት በሕቡዕ የሚጠ ናቀርን መረጃ በተመለከተ ብዙም በለስ ቀንቶኝ አያውቅም። እንዳንድ ግዜ ሴናተር ካር እና የሚመራው ኮሚቴ ትክክል ናቸው ብዬ አስባለሁ. . . ኤጀንሲያችን ኮሚያስፈልገው በላይ ገንዘብ በሐርድ ዌር ላይ ፈሰስ ሲያደርግ እነዚያን ጥሩ ግን ከዘመኑ ጋር የማይሄዱ ሰላዮቻችሁን ለማሰልጠን የሚያወጣው ገንዘብ ፈሰስ ደግሞ በጣም እናላ ነው።» በማለት በነገር ጎሸም አደረገችው።

እናቷን፣ «ይኼ ማጆሮቭ የምትይው ግን እውነት እንነጋገርና በስሜትና በሐሳብ ያለብሽ ቁጥር ብጤ ነው አይደል? አሁንም አሁንም ማጆሮቭ ያሰኝሻል. . . ከዚያ ዝም ብለሽ በሰያፍ አንጣጥሮ መተኮስ ብቻ ነው፣ ወይ ጉድ!»

ብድሩን መለስ ማለት ነው። «አይ በሰያፍ ዝም ብሎ የሚመታ አይደለም፣ እላን» ጉንጯ በንዴት መቅላቱን አልተጠራጠረችም። «እንተ እንዳልከው አይደለም ማጆሮቭ የመጀመሪያው ዳይሬክቶሬት ቺፍ ነበረ። እና በእኔ ክልል ውስጥ ያለ ነው»

«ነበረ ብትይ ይቀላል እኮ። ባሁን ሰዓት እዚያ ክልልም አይገኝም። ምናልባትም ጉላግ ውስጥ ይሆናል፣ ለሰራው ሐጢያት ዋጋ እየከፈለ»

ሩል በግድ የለሽነት ትከሻዋን ነቀነቀች። «ምናልባት ይሆናል. . . እም ምናልባትም ደግሞ ላይሆን ይችላል። ግን ማጆሮቭ የት እንዳለ ማወቁ ጉዳይ የለውም። እንዲያውም እኔ ስለ እሱ አውቃለሁ ከምለው ትንሽ ነገር ተነስቼ ማለት የምችለው በጣም የፈጠነ ሰው መሆኑ ነው። እኔ በስራቸው ከልባቸው ያልሆኑ በደመ ነፍስ የሚሰሩ ከርፋፎች ናቸው የሚመቹኝ፣ እሱ ከርፋፋ እንዳልሆነ ደግሞ ግልጽ ነው። ይህ ሰው የትም ሆነ የት ጥሩ እንደማያስብ አረጋግጠልሃለሁ።»

«አህ . . . ጥሩ በቃ እሺ» ሲል ኒክሰን በረጅሙ ተንፍሶ እስክሪፕቶ አነሳ። እሰይ! ሊፈርም ነው። «ይኸው ግን የምፈራው ስለ በጀት አዋዋል ጉዳይ የሆነ የማስጠንቀቂያ ጽሑፍ እንዳይደርሰኝ ነው የምፈራው። እነዚህ ሰዎች ለሰው እንደማይተኙ ታውቂያለሽ መቼም» በማለት ወረቀቱን ፈረመው።

ሩል ከመመንጨቅ ባልተናነሰ ሁኔታ ወረቀቱን ከእጁ መንትፋ ወደ በሩ በፍጥነት አመራች። «እግዜር ይስጥልኝ አላን። በቃ ጣጣ የለውም በሰላም ያልቃል»

«ስሚ ከይት» አለና አስቆማት። ኡፍ! ምናባቱ ፈለገ ደግሞ?።

«አንድ ጥሩ ወይ ተጨባጭ ፍንጭ ካላገኘሽበት በቀር ከዚህ በኋላ እንዲህ የተንቦራቀቀ የበጀት ጥያቄ ይዘሽብኝ አትምጪ። ሰማሽኝ? ዝም ብዬ አንቺ በዚያ . . . አዎ በስሚት በፈጠርሽው ነገር ምን በወጣኝ ገንዘብ ይባክን ብዬ የምፈርመው፣ ባለፈውም እንዲህ ነው ጭቃ ውስጥ የጨመርሽኝ»

«አረ አላን ጣጣ የለውም አልኩህ እኮ፣ በኔ ይሁንብህ» አለችውና ከቢሮው ጉንጯ በንዴትና በድንጋጤ ፍጹም አጋም መስሎ አርሮ ወጣች። ባለፉት ግዜያት ቀደም ሲል በሶቭየት GRU ውስጥ ተቀጥሮ ያገለግል የነበረን

እና በልብ ደም መላሽ ቧንቧ ብልሽት የተነሣ በድንገት ጠረጴዛው ላይ ሞቶ በተገኘው ሰው ጉዳይ ላይ ክትትል ስታደርግ ነበረ ይህ ሰው የሞተው ከሁለት ዓመታት በፊት ነበር። ኒክሰን በቁጥጥሩ ስር ሊያደርጋት ሲያስብ ይኼንን ነገር መልሶ መሳልሶ ያነሳባትና ያስበረግጋታል። ግን ይኼኛው እንደዚያ የሷን ድክመት የሚያሳይ አይሆንም ስትል አሰበች። ይኼስ የሞተ ሳይሆን ሕያው በሆነ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ነው። «ሴት በስሚቷ ነው ዝም ብላ የምትሰለው» ይላል ኒክሰን፣ ታዲያ እሷም ታግሳ ችላ መኖር ካለባት ነገሮች ይኼ የሱ አነጋገርና ጉንተላ እንዱ ነው።

9

ሔልደር ከሴሎች ሃምሣ የሚጠጉ ሰዎች ጋር በመሆን ወደ ትንሹ የስልጠና ማሳያ አዳራሽ ገባና ፊት መደዳ ላይ ተቀመጠ። እዚህ ከደረሡ ባሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ከሴሎች ጋር ለስልጠና ሲገናኝ የመጀመሪያው ነበረ። ወደ ሴሎች ሲመለከትም ከዚህ ቀደም ያልገጠመውን መመሳሰል አየ። መቼም አሥራ አምሥት ያህል አባል ክልሎች፣ የተለያዩ ቋንቋዎች እና ብሔር ብሔረሰቦች ካሉባት የሶቭየት ጎብረት የተውጣጣ ጦር በርካታ ልዩነቶችን ያንጸባርቃል ተብሎ ነው የሚጠበቀው። ከነዚህ ሰልጣኞች አብዛኞቹ የሩሲያን ቋንቋ እንደሚናገሩና በመሠረታዊ የትዕዛዝ ዓይነቶች ስልጠናው እንደሚሰጥ ያውቃል። እዚህ ቦታ ላይ ሰልጣኞች የሚናገሩት የሩሲያን ቋንቋ ብቻ ሳይሆን እንግሊዝኛን ወይንም ስዊድንኛን ይናገራሉ። ሲታዩ ደግሞ የቡድኑ አባላት ከስካንዴኒቪያ ወይንም ደግሞ ቢያንስ ከሰሜን አውሮፓ የመጡ ነው የሚመስሉት።

ከአዳራሹ ፊት ሙሉ ጥቁር ከሆነው ግድግዳ አንዳንድ ከዚህ በፊት ታይተው የማይታወቁ የተካተቱባቸው የጦር መሣሪያ ዓይነቶች አሉ። በእያንዳንዱ የወንበር እጅ ማሰደገፊያ ላይ ደግሞ በጀት አውሮፕላን ዲቪል ወይንም ወታደሮች የሚያደርጉትን ዓይነት የጆሮ ማዳመጫ ተቀምጧል። ልክ እንደተመቻቹም ማጆሮቭ የሚሊቴሪ ልብስ ግጥም አድርጎ እንደለበሰ ሁለት የጦር መሣሪያ ሳጥን የያዘ አንድ ሌላ ሰው አስከትሎ ገባ።

«እንደምን አድራችኋል፣ ወንድሞች፡» አለ መጠነኛ ፈገግታ እየታየበት። «በዚህ ሰዓት እናንተ ጓደኞቻችን በስምሪቱ ወቅት የምትይዟቸውን እና የምትታጠቋቸውን አነስተኛ የጦር መሳሪያዎች የማዘጋጀቱን ሥራ መጨረሳችንን ለመግለጽ እወዳለሁ። እንግዲህ ጓዶች ዘመቻችን የሚከናወነው በሶስት ሞገዶች ነው፣ እነዚህም ሰርጎ-ገብ፣ አስደንጋጭ ድንገተኛ ሥራዊት እና መደበኛው ሥራዊት በሚባሉት ነው። ማጆሮቭ ሁለት ትናንሽ አውቶማቲክ ሽጉጦችን እነሳና ለታዳሚው ይታዩ ዘንድ ከፍ አድርጎ ያዛቸው። «ሰርጎ-ገብ የሚባለውን ኃይል የምትመሩት ጓዶቻችን ምክንያቱን መግለጽ በማያስፈልግና ግልጽ በሆነ ሳቢያ ከጎን ሽጉጥ የሚደረግ መሣሪያ ብቻ እንድትይዙ ይደረጋል። እንግዲህ ምክንያቱ ግልጽ ነው ብያለሁ በድንገት በተቀናቃኝ እጅ ብትወድቁ መሣሪያው ምንም ትኩረት እንዳይስብ ነው፣ በዚህ የተነሣም በጣም የታወቀ የሚባለውን የWalter PPK ልትታጠቁ ትችላላችሁ ይህም ከማካሮቭ ጋር

http://ethzare.wordpress.com

ተመሳሳይ ነው. . . ወይንም በተገላቢጦሹ እስቡት ልበል?» ከታዳሚው መሀከል በዚህ ሰዓት ዝቅ ባለ ድምጽ ሳቅ ተሰማ:: ይህም የሆነበት ዋንኛ ምክንያት የቡድኑ አባላት የሶቭየቱ ማካሮቭ የ Walter PPK ቀጥተኛ ግልባጭ እንደሆነ አሳምረው በማወቃቸው ነው:: ማጆሮቭ አሁንም ንግግሩን ቀጠለ. . . ወይንም ደግሞ ባሬታ ሞዴል 84 የሚባለውን ድርብ እርምጃ መውሰድ የሚችል ጦር መሣሪያ እንድትታጠቁ ይደረጋል:: ይህም እስከ 9 ሚሊ ሜትር አጭር ካርትሪጅ የሚተኩስ ነው:: የሚሰሟችሁ የጦር መሣሪያዎች በሙሉ ሲታዩ ከዚህ ቀደም ጥቅም ላይ የዋሉ ይመስላሉ ግን የማረጋግጥላችሁ ነገር ቢኖር እያንዳዱ ሽጉጥ ተፈታትቶ መፈተሹን እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በአዲስ መልክ መታደሱን ነው:: አብዛኞቻችሁ እነዚህን መሣሪያዎች ባንድም ሆነ በሌላ ጊዜ ተኩሳችኋቸው ታውቁ ይሆናል ስለዚህ ነፃ መረጃ በመስጠት ግዜያችሁን አልሻማም::»

ማጆሮቭ ሽጉጦቹን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና ሌላ ሔልደር ከዚህ ቀደም የማያውቀውን ሽጉጥ ደግሞ አነሳ:: «ከዚህ ቀጥሎ» የምናየው ደግሞ በድንገተኛው አስደንጋጭ ሠራዊት የሚያዙትን መሣሪያዎች ይሆናል:: እንግዲህ እነዚህ ጋ የታጠቁት መሣሪያ ቢታይ ባይታይ ችግር አይኖርብንም:: ጓዶች! ይህኛው SIG- Sauer ሞዴል P226 ሲሆን የጦር መሣሪያው አምራች በሆነው የስዊድን ፋብሪካ ማለትም Schweizerishe Industrie Gesellschaft አማካይነት የተመረተ ነው:: ግን ብቻቸውን ሳይሆን ከምዕራብ ጀርመኑ J.P. Sauer እና ልጁ ኩባንያ ጋር በመተባበር ነው የተሠራው:: ይህ ሽጉጥ በ SIG ሲመሰረት ለአሜሪካ በተለይም ከሳን ሽንጥ የሚደረግ መሳሪያ ምርት ፉክክርን እንዲያግዝ ተብሎ ነበረ:: በእርግጥ አሜሪካውያኑ ይህን ለማምረት ጥማ ድረስ መሄዳቸው የለየለት ደንቁርናና ሞኝነታቸውን ያመላክታል:: በተለይ በእኔ በጣም በእውቀት በታገዘ አስተያየት መሠረት ይህን የመሰለ አውቶማቲክ ጥራት ያለው መሳሪያ አይገኝም:: P226 በ9 ሚሊ ሊትር ፓራቤለም የሚተኩስ ሲሆን ባለ 15 ዙር ያህል ይሄዳል::» ይህን ግዜ ከተመልካቹ የአድናቆት አይነት ጉርምርምታ ተሰማ::

ማጆሮቭ ሽጉጡን መልሶ ጠረጴዛው ላይ በማድረግ አንድ አጠር ያለ መሣሪያ በአንድ እጁ በማንሳት በሌላኛው ደግሞ ወፈር ያለ ጥቁር ሲሊንደር አነሳ:: «አሁን የምንሄደው ደግሞ ከነዚህ ካየናቸው ይበልጥ ጉጉትን እና ስሜትን ወደሚፈጥሩ መሳሪያዎች ይሆናል፣ ጓዶች» ከዚያም የተወሰኑ አዳዲስ መሣሪያዎች ታዩ:: «ይኼኛው ምናልባትም በዝና ሳትሰሙት የማትቀሩት ኢግራም ሞዴል ወይንም MAC 10 በመባል የሚታወቀው በቀላሉ ሊያዝ የሚችል አውቶማቲክ መሣሪያ ነው:: እንደዚህ ያሉትን ድንቅ መሣሪያዎች እስከ 2000 በሚደርስ ቁጥር አብዝተን ቅንነት በጎደለው መንገድ ገዝተናል:: ይኼ የጦር መሣሪያ የተወሰኑ ጥቅሞች አሉት:: ምንም እንኳ ለምሳሌም እንበልና እንደ እስራኤሉ Uzi አጭር ቢሆኑም ባለ 45 ካሊበር ካርትሪጅ መተኮስ የሚችሉ መሆናቸው ራሱ ትልቅ ነገር ነው:: በዚያ ላይ ከ 30 ዙር በ 1100 እና 45 ዙር ድረስ በደቂቃ ብቻ መሸፈን ይችላሉ:: እዚህ ላይ ያለው ሲሊንደር መደበኛው ድምፅ አልባ አይነት አይደለም፣ ይልቁንም ጥይቱ በሙሉ ፍጥነቱ ተጉዞ ከድምጽ አልባው የሚመጣውን ነገር ማስወገድ እንዲችል የሚያደርገው አፋኝ ነው:: ተቀናቃኞችሁ ሊሰማ የሚችለው ነገር ቢኖር ጥይቱ ሲያልፍ

ጩኸቱ ከተለመደው የድምጽ ፍጥነት በላይ መሆኑን ነው:: በዚህ ዓይነት ደግሞ እናንተ ከየት አቀጣጫ እና ሁኔታ ላይ ሆናችሁ እንደምትተኩሱ ጠላት በፍፁም ለመናገር የማይችልበትን ሁኔታ ይፈጥራል:: ይኼ ደግሞ አሁን ስልጠና በመውሰድ እየተዘጋጃችሁለት ካለው ዘመቻ ጥቅሞች ውስጥ አንዱ ይሆናል:: ይኼ የጦር መሣሪያ ግልጽ በሆነው የገጠራማ ቦታ ላይ በሚሠሩ የሰራዊታችን አባላት የሚያዝ ሲሆን እዚያ ደግሞ የአፈሙዝ ድምጽና ሌላ ጩኸት በቀላሉ ያለንበትን ቦታ ለጠላት የማስታወቅ ዕድሉ ስላላቸው ያንን ያስቀራሉ:: ከዚህ በመቀጠልም ሃምሣ ዓለቃ ፔትሮቭ» በማለት አጠገቡ ወዳለው ሰው እያየ ራሱን በእምንታ ነቀነቀና፣ «አጠቃቀሙን ያሳያችሁና እናንተ ደግሞ በጓደኞቻችሁ ፊት በየተራ እንድታሳዩ ያደርጋችኋል:: እንደምትወዱት እምናለሁ::

ማጆሮቭ ይኼንን በቀላሉ የሚያዝ አውቶማቲክ መሣሪያ መልሶ አስቀመጠና ሌላ ሔልደር ከዚህ ቀደም ያየው የማይመስልን መሣሪያ አነሳ:: በዚህ ሰዓት ከተመልካቹ የሚደመጡ አስተያየቶች ነበሩ:: ከዚህ ቀደም በእንድ ጫፉ ሶስት ጫማ የሚሆን እና በሌላው ደግሞ ሰድስት ጫማ የሚደርስ መሣሪያ አይቶ የሚያውቅ ከመሀከላቸው የለም:: ስለዚህ ይህ ነገር ማኑጣጠሪያ እና በመሀከሉ ደግሞ ሽጉጡን ደግፎ መያዣው ባይኖር መሣሪያም አይመስልም ነበረ:: «እንግዲህ አሁን የምንቀጥለውና የምናየው ደግሞ በከተማ ከልሎች በሚንቀሳቀሱ አባላቶቻችን የሚያዙትን የጦር መሣሪያዎች ነው በ1982 የአሜሪካ የጦር ኃይሎች በጦርነት ላይ ከፍተኛ ጥቅም ሊሰጥ የሚችል ጠ ብመንጃ Close Assault Weapons Syatem በሚል ፕሮግራ አማካይነት ጀመሩ:: በዚህ ፕሮጀክት ዙሪያ በርካታ የጦር መሣሪያ አምራቾች ፍላጎት እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን ሥራዎቹን በሚገባ ያያችሁለትና የምታውቁለት የምዕራብ ጀርመኑ ኼክለር እና ኮች ይህንን የሚመስሉ መሣሪያዎች ፈልስፏል:: የተወሰኑትም ወደ እኛ የመጡ ይመስላሉ:: አንድ የሩሲያ ስቴት አርድናንስ ይህን ሐሳብ ይበልጥ በማሳደግ ያጠናከረው ሲሆን እስከ አሁን ድረስ የተወሰነ አስተማማኝ በቀላሉ የሚያዝ አውቶማቲክ የተኩስ ጠብመንጃ ነው ያለን::» ልክ ማጆሮቭ የጦር መሣሪያውን ከፍ አድርጎ ሲያዘው ከተመልካቹ መሀከል የማቃተት ድምጽ ተሰማ::

ማጆሮቭ ንግግሩን ቀጠለ:: «በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ የሆኑ የጦር መሣሪያዎችንም እምርተናል:: ከነዚህም መሀከል ልዩ ፀረ-ፐርሶኔል ክኅላ ተኳሽ የሚባለው መሣሪያ ይገኝበታል:: ሌላው ደግሞ CS ጋስ ካርትሪጅ ሲሆን በተጨማሪም እስከ 30 ሚሊሜትር ድረስ የሚደርስ ሶሊድ ተስፈንጣሪ /እንድ ከሩብ ኢንች ማለት ነው/::» ልክ ይህን ግዜ ከተመልካቹ ሌላ የማቃተት ድምጽ ተሰማ:: ማጆሮቭ ወፍራም ቁራጭ የጥይት ሰቶክ አነሳና ወደ ጦር መሣሪያው ማጠራቀሚያ ከተተው:: «ከ24 ዙር ክሊፕ አንድ ግዜ ወይንም በሙሉ አውቶማቲክ በደቂቃ ብቻ 500 ዙር ያህል ይተኩሳል::» ሲል አስታወቀ:: «ስለዚህ በአርባ ሜትር ርቀት ላይ እንድ ጊዜ የተተኮሰው ጥይት እስከ 900 ሚሊ ሜትር /ሶስት ጫማ/ ድረስ ይሄዳል:: በዚያ ርቀትም እያንዳንዱ ጥይት ከተለመደው 7.65 ሚሊሜትር በጣም ላቅ ያለ በ50 በመቶ የሚበልጥ ቀሪ ጉልበት ይኖረዋል ማለት ነው:: ከዚህ በተጨማሪም በእንድ ውሱን ቦታ ላይ ለምሳሌም እንበልና ከተማ መሀከል ባለ መንገድ እያንዳንዳቸው ሁለት ክሊፕ

http://ethzare.wordpress.com

የያዙ ስድስት ሰዎች መደበኛ እግረኛ ጦርን ከ10 ሴኮንድ ባነሰ ግዜ ውስ
ያደባያሉ ማለት ነው::

በዚህን ሰዓት ለእፍታ ያህል በእጻራሹ ፀጥታ የሰፈነ ሲሆን ወዲያ
ግን ተመልካቹ በጭብጨባ ቀወጠው:: ወታደር ጓዶችም ከመቀመጫቸ
ተነሱ::

ቆመው እያጨበጨቡ እያለም ማጆሮቭ የጦር መሣሪያዎች
በተመለከተ ሹመት ለተሰጠው የሃምሳ አለቃ ጓድ ራሱን በአዎንታ ነቅነ
ምልክት ሰጠው:: ወዲያውም ከማጆሮቭ ጎላ የነበረው ባዶ ግድግዳ ወደ ላ
ተከፍቶ ሙለ በሙሉ መብራት የነዘረበት 50 ሜትር የሚሆን የመተኮሻ ቦታ
አሳየ:: ልክ ይህን ግዜ ጭብጨባው ቀጥ ብሉ ቆመ:: በድንገተኛው ጭብጨ
ተሰቦ የተነሳው ሔልደርም ሆኑን የሆነ የመሳብ ስሜት እየተሰማው ቁጭ አ
ሌሎችም ጓዶች የሱን ፈለግ ተከትለው ተመልሰው ዘርፈጭ በማለት ተቀመ
ከራንጁ 40 ሜትር በሚሆን ወረድ ብሉ ባለ ቦታ ላይ ደርዘን የሚሆኑ ከኮርኒ
ጋ ሰውነታቸውን በገመድ የተያያዘ ሰዎች ወጡ:: ለእፍታ ያህል ሔልደ
ራሳቸውን የማያውቁ መስሉት ነበረ ግን የተሰቀሉበትን እና የተንጠለጠሉበት
ሁኔታ በደምብ ሲመለከት እንድ የሆነ ነገር መሞታቸውን አሳወቀውና ተመለሽ
እለ ለራሱ::

«ጓዶች እባካችሁ የጆሮ ማጻመጫዎቻችሁን አድርጉ፣» አለ ማጆሮ
እና እነሱም አደረጉ:: ወዲያውም አውቶማቲክ መሣሪያ አውጥቶ ከግራ ወ
ቀኝ አንዴ በ24 ዙር ወደ ራሳዎቹ ጥይቶች ሲያርከፈክፍ ራሳዎቹ
ተንገጫግጪው ደም ክፉኛ ተረጨና ወጻደቁ:: ልክ ከሊፑ ሲያልቅም ማጆሮ
ከመሣሪያው አወጣውና በሌላ ተክቶት ተኩሱን አሁንም ደግሞ ከቀኝ ወደ ግ
ደገመው::

ሔልደር ዓይኑን ለመጨፈን ሞከረ ግን አልቻለም:: ያንን የጆሮ
ማጻመጫ እድርገም የተኩስ እሩምታውን ለማመን የሚያስቸግር ዓይነት ብራቂ
ነበረው:: በዚያ ላይ እነዚያ ራሳዎች ከመጠን በላይ ነው የሚንገጫገጩት
የሚደንሱት ይህም የሚተኮስባቸው እንዲህ ከአንድ ቦታ ሳይሆን ከደርዘን በላይ
የሆኑ ሰዎች ከተለያየ አቀጣጫ ጥይት ሲያዘንቡባቸው እሱን ለመከላከል ብለው
ያደረጉት ነበረ የሚመስለው:: ሁለተኛው የጥይት ክሊፕ ሲያልቅ ከራሳዎች
ሶስቱ ጭንቅላታቸው ተቆርጦ ነበር፣ ሌሎች እግራቸው ተቀንጠሰ፣ ሁለት
የሚሆኑት ደግሞ ሰውነታቸው ግማሹ ተቆርጦ ጠፉ ለረጅም ሰዓት ማንም
አልተንቀሳቀሰም:: ከዚያም ልክ ማጆሮቭ ሲያያቸው እጩ ጓዶችም በጆሯቸ
ላይ አድርገውት የነበረውን ማድመጫ በማም ጎተት እያሉ አወለቁት::

«ጓዶች፣» አለ ማጆሮቭ ረጋ ባለ የድምጽ ቃና:: «ተቀናቃኞቻችን
እንደዚህ የሉ አዳዲስ መሣሪያዎችን ስንጠቀም እንዴ ይየን እንጂ ከዚያ በኋ
በሕይወታቸው ፈርተው የማያውቁትን ያህል ይፈሩናል::»

ሔልደር ስልጠና የወሰደባቸውን እንቅስቃሴዎች ሁሉ እጅግ በማም ፈ
ንክሮ በግሉ ይለማመድባቸው ጀመር:: ለምሳሌም በራሱ ግቢ ውስጥ ተከለሉ
የቆመን ነገር በመምታት ዙሪያ ሁል ግዜ የተለያዩ የሽወዳ ድርጊቶችን ሊፈጽ

ከሚችለው ጆንስ ጋ በመሆን በየቀኑ ልምምድ ያደርግ ነበር:: ልምምድ ሲያደግ
በኢንግራም አውቶማቲክ አንዲሁም በኖርማል አውቶማቲክ መሣሪያዎችም
ሞምር ነበረ:: ከዚህ በተጨማሪም Walter PPK የተባለውንም በግሉ እየያዘ ይጠ
ቀማል:: በየቀኑ ለሁለት ሰዓታት ያህል በቋንቋ መለማመጃው ክፍል ጆሮው ላይ
ማድመጫ አድርጎ በአብዛኛው ትልቅ ተቀባይነት ያለውንና ጠራ ያለውን
የመካከለኛው ምዕራብ አሜሪካን ያነጋገር ዘይቤ ሲለማመድ ይውላል:: በየቀኑ
ደግሞ ሁለት ጊዜ ያህል የመፈንጠርና በድንገት የንፋስ ያህል ሽው የማለትን
እንቅስቃሴ ይሰራል:: ከአንድ የዩክሬን ዜጋ ጋር በመሆንም የሚያቆስልና
በሰውነት ላይ ቀላል የማይባል የመቁጥቁጥ ነገር የሚያደርስ የልምምድ ክፍለ
ግዜ ለሁለት ሰዓታት ያህል ያከናውናል:: ማታ ማታ ከትሪና ጋር ነው
የሚያመሽው ሁለቱ በማሊቡ በሚገኙ በርካታ ሬስቶራንቶች በመሄድ ይደንሳሉ፣
ራት አብረው ይበላሉ፣ ፊልሞችንና ዜናዎችን ይከታተላሉ:: ትሪና ሙሉ በሙሉ
ማለት ይቻላል እሱ ጋር ነው የምትኖረው /ምንም እንኳ እሱ ክፍል የግል
ንብረቶቿን ባታመጣና ባታስቀምጥም:: እንግዲህ በዚህ ወቅት በባህር ኃይሉ
አፐሬሽንና ዘመቻ ክፍል ያለው ሙያ አብቅቶ ሙሉ በሙሉ ለስለላ በሚውል
ተግባር ላይ ስልጠና እየወሰደና ልምምድ እያገኘ እንደሆነ እየተሰማው የመጣው
ታዲያ ልክ በዚህ ግዜ ነበር:: አንድ ቀን ማጆሮቭ እዚህ ቋንቋ ማሰልጠኛ ክፍል
ውስጥ መጥቶ በጎልፍ ጋሪ «እፈልግህለሁ» ብሉ የወሰደው::

«እሺ ባክህ እንዴት ይዞህል?» ሲል ማጆሮቭ ወደ ደቡብ መስሉ ዳርቻ
መሬት ፈጠን ብሉ በመራመድ ሲጠጉ ጠየቀው::

«ቆንጆ ነው፣ ጥሩ ነው፣ ጌታዬ» ሲል ሔልደር ምላሽ ሰጠው:: «ብጣም
ባተሌ እየሆንኩኝ ነው፣»

«መልካም፣ መልካም» ማጆሮቭ ፀሃይ ፊቱን እንዳይወለውለው
የአሜሪካውያን ቤዝቦል ተጫዋቾች የሆነውን ኮፍያውን ክፈፍ ዝቅ አደረገው::
«እውነት ለመናገር ከሆነ በዳርቻው ላይ ሲኖርህ የሚገባን ስልጠና በሙሉ
አግኝተሀል:: ሚ/ር ጆንስ እንደነገረኝ ከሆነ ስልጠናዎቹን በብቃት
ተከታትለሀል:: እንግዲህ አሁን በድጋሚ ወደ ባህር ትገባለህ»

ምንም ቀስ ሳይሉ በሁለት ለባህር የሚረዱ ልብሶችን በለበሱ ሰዎች
የሚጠበቅ መግቢያ ገቡ:: ሰዎቹ ኢንግራም ማርክ 10 የተባለውን መሣሪያ
እያንዳንዳቸው ታጥቀዋል:: ያመሩትም ሔልደር ገና ወደ ማሊቡ ለመጀመሪያ
ግዜ ሲመጣ ወዳስተዋለው በውሀ የተሞላ ጣሪያ ነበር:: ይህ ቦታ ከባህር ከፍ
ብሉ ባለው መሬት ላይ ያለ ሲሆን ሔልደርም በዚያ ፊን በተባለ የሚቀዝፍ
ጀልባ ሲጓዝ እንኳን ሊደርስበት ያልቻለ ነበር:: ከጣሪያው ደረጃ ወረዱና
ማጆሮቭ ጋሪውን አቆመው:: ከዚያም ሔልደር በሆነ በር ተከትሉት ሁለቱም
ገቡ:: ልክ በበሩ ውስጥ ሲያልፉም ትንፋሹ ቀጥ ሊል ነበር ልክ ከፊቱ ሁለት
መቶ ሜትር ላይ የሰርጓጅ መርከብ ቤተ-ሙከራዎች ነበሩ:: ውስጥ ሦስት
መኝታ ቤት ያላቸው ሰርጓጅ መርከቦች ነበሩ:: ውስኪ እና ደረጃ ክፍሉች
ያሏቸው ናቸው:: ሔልደር ከዚህ በተጨማሪም ጉዟቸውን ቀጥለው ሲያቋርጡ
ትልቅ የታይፈን ደረጃ ያላቸው መኝታ ቤቶች ተመለከተ፣ እነዚህ በሶቭየት
የጦር መርከብ ታሪክ ውስጥ ትልቁቹ የሚባሉት ነበሩ:: ከዚህ ሌላ ደርዘን
ወይንም ከዚያ የሚበልጡ እነስተኛ ሰርጓጅ መርከቦች ነበሩ:: እነዚህ ደግሞ
በባህሩ ስረኛ ወለል ላይ ምርምር ከማካሄድ ጀምሮ እስከ ሰራዊት አጭቆ

http://ethzare.wordpress.com

እስከመጫን ድረስ ተግባሮችን ሊፈጽሙ የሚችሉ ናቸው። አራተኛ መደብ የሚባሉ ሌሎች ሁለት እንስተኛ ሰርጓጅ መርከቦችም ያሉ ሲሆን ከታች የተጫኑባቸው ማንሻዎችም ሲታዩ ጫፋቸው የተቆረጡ እስመስሏቸዋል።

ሔልደር ደርቆ ነበር የቀረው። እስካሁን ድረስ ማሊቡ በነበረው ቆይታው እንኳ ይህ ቦታ SPETSNAZ ማሰልጠኛ በተጨማሪ የሰርጓጅ መርከብ ጣቢያ ስለሆኑ ምንም የሚየወቀው ወይንም የጠረጠረው ፊጽሞ አልነበረም። በባሕሩ አሻግሮ ማዕበል ያለበት ሀይቅ ባልቲክ ባሕርን የሚገናኝበትን ተመለከተ። እዚህ ጋ የሚደርስ ወይንም ከዚህ የሚወጣው ሁሉ በጥልቀት ተጉዞ ካልሆነ እንደማይመጣም አወቀ።

«መቼም ከምታየው ነገር አብዛኛው ከዚህ ቀደም የምታውቀው እንደሚመስልህ እጠብቃለሁ፣» አለው ማጆሮቭ።

«አዎን፣ ጌታዬ» ሲል ሔልደር ምላሽ ሰጠ። ውጪ ሄጂ ሰልጥኖለሁና እዚህ ያለው ከዚያ . . . በቀር እውቀዋለሁ በማለት አጠር ወዳለ በመጫኛዎች የታጨቀ አንስተኛ ሰርጓጅ መርከብ አመለከተ። «. . . ያንን ማለቴ ነው ምንም ሆነ ምንም እሱን ብቻ አላውቀውም።

«አይ ይኼማ ስታየው የሚመስልህን ነው በቃ» አለው ማጆሮቭ። «የተቆረጠ አራተኛው መደብ ነው።» ወደ ዝርግ ሰሀን መሰሉ ትልቅ የመርከብ አካል ሄዱና ቆሙ። «እና ደግሞ» አለ ማጆሮቭ «ያንተ ነው።»

ሔልደር እዚያው በቆመበት አንስተኛውን ሰርጓጅ መርከብ ተመለከተ። እንግዲህ መሠረታዊ በሆነ መልኩ ሲታይ የክበብ አጋማሽ መስመር ስፋቱ ሁለት ሜትር የሚሆን፣ ርዝመቱ ስድስት ሜትር በቅርጽ ደግሞ እንደአፍንጫ ነው። ሁለት መደብ መሳይ ነገሮች አሉት ስለዚህ ሲታይ ትልቅ አባጨጓሬ ይመስላል። በሁለቱም በኩል የተለያዩ መጠኖች ያሏቸው የብረት ጠርሙሶች ነበሩ። ከዚህ በተጨማሪ ከሩቅ የሚሰሩ ፊት ላይ ያሉ ማጥበቂያዎችም አሉት።

«አራተኛ መደብ የሚባለውን ዓይነት በመውሰድ አሳጥረነውና ለዚህ ለተፈለገው ሥራ ትርፍ ነው የሚባል አካል ሁሉ ቆረጥንበት ባሁን ሰዓት የናፍታ ክፍሉ የለም፣ በጥልቀት ሰጥሞ ሲሄድ አየር ለመሳብ የሚያስችለው ትዩብም የለም። የአክስጅን ጠርሙስ ግን ስላለ በከሩዝ ፍጥነት የሚጓዝበት ሰዓት የቡድኑን አባላት በሕይወት ለማቆየት ያህል ይረዳል። ከዚያ ሌላ ደግሞ እያንዳንዳቸው 20 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ የኒኪል ካድሚየም ባትሪ ሴሎች አሉ። ሞነቶቹን በተመለከተ እነሱን የምትጠቀምበት የእያንዳንዱ አምስት ደቂቃ ጊዜ የእንድ ሰዓት ያህል መሄጃ ጊዜህን ታቃጥላለህ። ይህ በፍፁም ልትዘነጋው የማይገባህ ወሳኝ ነጥብ ነው።

«አዎ ልክ ነው ጌታው» ሲል ሔልደር ምላሽ ሰጠ። መደብ አራት የሚባለውን ወዶታል። እንድ ሰው ነው የሚሠራው ይህም ልክ በባህር ውስጥ ሰጥሞ እንደሚሄደው ፕሌን ነው። ቁጭ ብሎ ሁለት ሰዎችን ከማዘዝ ይሻላል። ብቻ ያም ሆኖ ግን በዚህ በመደብ አራት ላይ አራት የሚሠሩ ሰዎች ያስፈልጋሉ። «ሁለት ሰዎች አሉ ነው ያልከው?»

ማጆሮቭ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ፣ «ያ እኮ ብዙ አካሉን የቀነስንበት አንዱ ምክንያት ነው። ይህ ደግሞ በተቻለ መጠን ቀለል እንዲል አስበን ነው።»

«ለመሆኑ ከኔ ጋር የሚሄደው ሰውዬ ማን ነው?» ሲል ሔልደር ጠየቀ። በዚህ ጉዳይ ላይ አማራጭ አይሰጠኝም ሲል አሰቧል።

ማጆሮቭ ወደ አንስተኛ ሰርጓጅ መርከቡ አካል ተጠጋ። ከዚያም ከወደቦቹ አንዱን ተመለከተ። «ይሽውልህ ሰውዬህ» በማለት የእጅ መዳፉን ዘርግቶ ሰሀን መሰል አካል ላይ ጠፍጠፍ በማድረግ ፈገግ ብሎ ተናገረ። ከሰርጓጅ መርከቡ ላይ ያለው ሃኝ ተከፈተና አንድ ጊዜ ቀደም ያለው ሰመሆኑ ያልተጠራጠረው ሰው ወጣ።

በመጀመሪያ ሔልደር ይህን ፊት የት እንደሚያውቀው ሊመጣለት አልቻለም ነበረ ግን ከገርግ ሰሐን መሰል አካሉ በመንሰላሉ ወደ ላይ ሲወጣና ሲመጣ ወዲያው ተከሰተለት። የስፖርት ቁምጣ እና ቲ-ሸርት መልበሱ የሚያስታውቅ ሰው ለስለስ ባለ ሁኔታ መሬቱ ላይ ዘልሎ በመውረድ ቆመ። ይህን ሲያደርግም የዓለም አቀፍ ብቃትን ያስመሰከረ አትሌታዊ ችሎታን አሳየ።

«ሻምበል ሶስተኛ ደረጃ ሔልደር በል ተዋወቃት መ/ቃ ሶኮሎቭ ትባላለች» አለ ማጆሮቭ ፊቱን በፈገግታ አፍክቶ።

«እንደምን አለሽ ሶኮሎቭ፣» አለ ሔልደር እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ።

«ሔልደር እንደምነህ፣» አለች እሷም እጁን አፈፍ እያደረገች በመያዝ።

እጇ በጣም ሞምቅ ያደርጋል፣ ጠንካራም ነው፣ ሔልደር ምንም ቢሆን ከዚህ ቀደም ያየውን ተራርቆ ያሉ ዓይኖች፣ ግራጫማ ፀጉር፣ በጣም የተስተካከለ መንጋጭላ ወዘተ ሳያይ ማለፍ አልቻለም። ይህች ለሔልደር ተመድባ የመጣች ሴት በ1980ው አ.ሊ.ምፒክ ውድድሮች ሞስኮ ላይ ሲደረጉ በሴቶች ምድብ በ10 ዓይነት ውድድሮች መቅረብ የቻለችና በተለይም የክሮሞዞም ፈተና በማለፍ ዓለምን በወቅቱ ያስደመመች ነበረች። « እንግዲህ ሶኮሎቭ ያንተ ምክትል፣ የምህንድስና ጉዳዮች ኃላፊ፣ የግንኙነት ኃላፊ፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በተመለከተ አማካሪህ ብቻ ምን ልበልህ እንድ ሰው ሁና ይህንን ሁሉ እንድታከናውን ነው የመረጥናት፣» በማለት ማጆሮቭ ዳግመኛ ፊቱን በፈገግታ አፈካው። «በትራኩም ላይ ቢሆን ልክ ከዚህ ቀደም እንደነገርኩህ በውድድሮች ላይ ያሳየችውን ብቃት እያሳየች እንደምትቀጥል ታያለህ፣»

«እንደማይ እርግጠኛ ነኝ፣» አለ ሔልደር እሷን በማየት ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

«እኔም ተስፋ አደርጋለሁ፣» አለች እሷ። ግን ፈገግም አላለች።

«ሶኮሎቭ አንስተኛ ሰርጓጅ መርከቦችን በተመለከተ በሚደረጉ ሞዲፊክ ለውጦች ላይ አተኩራ ነው ስትሰራ የቆየችው፣»አለ ማጆሮቭ ግሽኑን በባለቤትነት ስሜት መታ መታ እያደረገው። «ይልቅዬ ለምን ጥቅም እንደሚውል ሳሳይህ፣» በማለት ሔልደርና ሶኮሎቭን ወደ ሌላኛው አቅጣጫ እየመራ። «ያው መቼም እንደምታውቀው መያዝ የሚያስፈልጋቸው ለትግል የሚሆኑ መሣሪያዎች በመደብ አራት ላይ ደረጃቸውን የጠበቁ ባይባሉም ለዚህ ግዳጅ ግን አስፈላጊ ናቸው፣» ልክ ይህንን ከተናገረ በኋላ በመጠን ስፋት ዙሪያ ግማሽ ሜትር የሚሆን የማይዝግ ብረት ሲሊንደር ጋ ደረሱ «ይሄ እንግዲህ መሣሪያችሁ ሊይዝ የሚችለው ነው፣» አለና፣ «ወይንም አሁን ካልኩት ብዙም ያተለየ ነው። ይሄ አሁን የማሳያችሁ ምሳሌ በኮንክሪት ነው ውስጡ የተሞላው፣ እና በመሠረቱ የተሟላ ነው ቢባልም የመጨረሻ ሙከራ እየተደረገበት ነው። ሰሞኑን በጥቅም ላይ ሊውል ታስቦ የተሠራ የራዲዮን ማሰራጫ ሲሆን በውሀ ውስጥ በትክክለኛ አቀማመጥ ሲሆን በአቅራቢያ ከሚገኝ ሰርጓጅ መርከብ

http://ethzare.wordpress.com

የተልዕኮ እና የውሃውን የይዘት ምልክት መናገር ይችላል። ከዚያም ክፍ በግፊትና ወደ ውሃው እናት በመውጣት በሰርጓጅ መርከብ ላይ ላሉ የተሳያዩ ንብረቶችና ክፍሎች ራዲዮ ስርጭት ያደርጋል። ሔልደር ትንሽ ኮስተር ሲል ቅንድቡም ወረደ። «እኔ እስክ አሁን ድረስ የሚመስለኝ° አሁን ባለው የራዲዮ እና ናቪጌሽን ቴክኖሎጂ በማንኛውም ቦታ ላይ ለመድረስ የጥቂት ሜትሮች ጉዞ ብቻ የሚጠይቅ ነበረ።» አለ።

«ልክ ነው አሉ።» አለው ግጆሮቭ ፈጥን እያለ። «ይሁን እንጂ ይህኛው ባሕር ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ነገሮችን እንዲለይ ተደርጎ የተሠራው በግይኑቱ ብቸኛው የሆነው መሣሪያ ከሞላ ጎደል መደበኛ በሆኑና በተለመዱ ሁናቴዎች ውስጥ የሚያጋጥሙ መንጪሳዊ መሰናክሎችን እንዲያልፍ ተደርጎ የተሰራ ነው። ከዚህ ሌላም ይህ መሣሪያ ለምሳሌም እንደ የውሃ እፍጋት፣ ጨዋማነት ቅርብ ተልቶት ወይተ ባላቸው ቦታዎች ላይም ችግሮችን መለየት እንዲችል ተደርጎ የተሠራ ነው። በዚህ ላይ እመነኝ፣ በቃ አሁን ከዚህ በላይ ምንም ልንገርህ አልችልም።»

«እሽ እርግተ ነው፣ ኮሎኔል» ሲል ሔልደር ምላሽ ሰጠ። «ምንም ሆነ ምን የእኔ ሥራ ነገሩን በተሞና መረዳት እና ከዚያም መተግበር እንጂ ለምን ተሰራ ብሎ መጠየቅ አይደለም፣»

«ትክክል ብለሀል፣» አለ ግጆሮቭ። «አንተ ለማረፍ ከምትፈልግበት ቦታ ርቀት ባለ ቦታ ላይ ከአንስተኛው እናት ሰርጓጅ መርከብ ትወረወራለህ። ከዚያም ወሰልጠንክበትና በደምብ በምታውቀው አቅጣጫን የመለየት ቴክኒክ በመታገዝ ያንን አደጋ ጠቋሚውን ከሚፈለገው ቦታ ሃምሳ ሜትር ያህል ርቀት ላይ ታደርግና ወደ እናት አነስተኛ ሰርጓጅ መርከብህ ትመለሳለህ። አንተ እና ሶኮሎቭ በሞም ጥሩ ቅንጅት ትፈጥራላችሁ ብዬ ነው የማስበው፣ በዚህም ረክቻለሁ። አንተ ቦታዎችን በመለየት እና እጅግ በሚያስደንቀው የአትጣጣ መጠቆም ችሎታ እሷ ደግሞ በቴክኒክ ድጋፉ ጥሩ ውጤት ታመጣላችሁ።»

«እናመሰግናለን ኮሎኔል»

«ወሰልቺክ ከግዕበልግው ሐይቅ ውጭ ለስልጠና የተመቻቸ ሁኔታ በግግኘታችን ዕድለኛ ነን እላለሁ፣» አለ ግጆሮቭ። ግዳኛችሁን በዚህ ቀን ይጀምራል ብዬ መናገር አልችልም. . . በርግጥም ምናልባት ጥቂት ሰዓታት ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ የቀሯችሁ። ወይንም ደግሞ ግን ያውቃል ጥቂት ደቂቃዎችም ይሆናሉ. . . ግን ዞሮ ዞሮ የምንገራችሁ ዋናው ጉዳይ ቢኖር በግናችውም መልኩ ዝግጁ ሆናችሁ እንድትጠባበቁ ነው፣ ካሁን በኋላ ሶስት ሳምንት ግዜ ይኖራል።»

ሔልደር ራሱን በእምንታ ነቀነቀ። «እኔ እንኳ በዚህ ዓይነቁ የግዜ ሰሌዳ አጠቃቀም ችግር የለብኝም፣» አለ ሶኮሎቭን እየተመለከታት፣ «ልክ እንደታቀደው የመሣሪያ አሰራሮቹን አሰተላልፋለሁ።»

ሶኮሎቭ መበብ ያሉ ዓይናጅን ቢሔልደር አቅጣጫ ወረወረቻቸው። «በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ምንም ችግር አይኖርም፣» አለች ቀዝቀዝ እና ቀለል ባለ የሙዚቃ ቃና ያለው በሚመስል ድምጽ። «በዚያ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ።»

«መልካም እንግዲህ፣» አለ ሔልደር። «እንደዚያ ከሆነ ኮሎኔል ሙሉ በሙሉ በእኛ ላይ እምነት መጣል ትችላለህ ማለት ነው።

«እኔም ከእናንተ ከሁለታችሁ መስማት የፈለኩት ይህን መሰሉን ዝግጁነት ነው፣» አለና ግጆሮቭ ፈጥን ብሎ ሔልደርን ትክሹ ላይ በግበረታታት ዓይነት መታ መታ አደረገው። «ይልቅዬ ሂሮውኑ ሶኮሎቭን በአነስተኛው ሰርጓጅ መርከብ አጠቃቀም ዙሪያ አስልጥናት፣» አለው።

ሔልደር በግርምት ተመለከተው። «እንዴ! ቆይማ ይቅርታ ኮሎኔል ግን እኮ ሶኮሎቭ ባሕር ሰርጓጅ መርከቦችን ሞይፊክ በመሥራቱ ተሳትፋለች በትል የሰማሁህ መስሎኝ ነበረ»

«እምን፣ ሰምተኸኛል» ሲል ግጆሪጆቭ እየሳቀ መለሰ። «ሞይፊክን እና መሣሪያዎቹን በተመለከተም ትረዳህለች። ግን አንተ እኮ በሰርጓጅ መርከብ ዙሪያ ሰፊ ልምድ አለህ፣ ሶኮሎቭ በሰርጓጅ መርከብ ተጉዛም አታውቅ።»

በስመ አብ! ሔልደር ቢቸግረው ጭው አለ። ይህንን መርከብ እንግዲህ ብቻውን /ምክንያቱም እሷ አታውቅም/ ደብ ወደ ባሕሩ ዝቅተኛ መሰል 50 ሜትር ያህል በመምራት ወደ እናት ሰርጓጅ መርከቡ መመለስ ይኖርበታል፣ ታዲያ በዚህ ወቅት እብራው የምትኖረው ሲታፍ ተጉዛ የማታውቅ ተሬ ነች በዚያ ላይ ሶስት ሳምንት ሰልተና ምን ልታመጣ? ሔልደር እንዲህ በጉጭጩ መገረሙ የታወቀበት ይመስል ሶኮሎቭም ሣልታ ክችና ተናገረች። ሔልደር ገድ የለህም በኔ ይሁንብህ የምትጠብቀኝን ያህል በብቃት እወጣዋለሁ። በሥራ ላይ በቆየሁባቸው ወቅቶች ለበርካታ አስቸጋሪ ነገሮች ስልጠና ያገኘሁ ቢሆን ባንዱም ግን ወድቄ አላውቅም።»

ሔልደርም ወደ እሷ ፊቱን መለሰ። «እኔ ብዙምችን ል. . . እምን በሰርጓጅ መርከብ ጉዞ ዙሪያ አስልጥናለሁ፣ ታዲያ ከማናቸውም ውድቀት ሊጋተሞኝ አላውቅም፣» አላት። «እና ልክ ነሽ ሶኮሎቭ እንቺም እትወድቂም።»

ግጆሮቭ ሁለቱንም እየተመለከተ ፈጥን አለ፣ ግን ሳይናቹ አልነበረም። «መልካም እንግዲህ» አለና፣ «እንዳችን ሌላችንን በደምብ እንደምንረዳ ተመልክቻለሁ፣»

11

ሩል ሰላሳ እምስተኛ የልደት በዓሏን በምታከብርበት ሣት ላይ ወደ ኢጀንሲው ስትገባ ወደ ዋናው ቢሮ የሸኛት ድብ የሚመስል ከዚህ ቀደም ሳላውቀው አልቀርም ብላ የተጠራጠረችው ሰው ነበር። «ኢድ ራውልስ እኔ አላምንም» በማለት ተጣራችና ማነው ብሎ ገራ በመጋባት ዞሮ ድንብርብሩ ሲወጣ ላቀችበት።

«እንዴ! እንዴ! እንቺ!!!!!!» ራውልስ በማኑረምረም ዓይነት ተናግር አቀፋትና ሳማት። «እንዴት ነሽልኝ እባክሽ?» እሷ የተከበረች ፀሐፊ ባልች እሱ ሮም ጣቢያ ነበረ። «ካለፈው እንደማይሻለኝ እሙታለሁ፣ ይልት አንተስ? ቤቲስ?»

ፈገግ አለ። «እኛም ካለፈው አይሻለንም ብንል ወደ እውነቱ ፀደምብ ቀርበናል መሰል። በተለይም አንድ ላይ ሁነንማ ተይ።» አለና ጠቀሳት። «እንቺን የማመሰግንባቸው ብዙ ነገሮች አሉ።»

ሩል ትዝ ሲላት ሳቀች። ኢድ ራውልስ ሮም በነበረበት ሰዓት የአምባሳደሩን ሚስት በማግኘ አብሯት መሲብ ይፈጽም ነበረ። ግን ታዲያ

http://ethzare.wordpress.com

ይኼ ኩባንያው ውስጥ ያሉት አሰቆቹ የወደዱለት ነገር አልነበረም። የሆነ ሆኖ ግን ትልቁ ችግር የመጣው ከሚስቱ ነው። ይህች አለሁ አለሁ ባይ ኃይለኛ የማትበገር ሴት ባሏን አሳምራ ታውቀው ነበረ ታዲያ በፈረንሣውያን ተደርጎ በማይታወቅ መልኩ አንድ ቀን በሴሊት እንደለመደው አምባሳደሩ መኖሪያ ሲሄድ በጭለማ በመያዝ ቁምጣዋኗ ከትታ ቤቱን ሲመጣ መጠጥ ቀድታ ጨዋታዋን አቀለጠችው፣ እሱ ቁም ሳጥን ውስጥ ወብቆት ላብ በላብ ሆኖ ልብሶቿ መሀል መከራን ያያል። በዚህ የተነሣም ኢድ ፈሪሀ እግዚአብሔር ወይንም ቢያንስ ቢያንስ ፈሪሀ ቤቴን እንበለው በውስጡ ተቀረፀ፣ ያም በቂ ነበረ።

«እውነትም ስፖርት ትሰራለህ፣»በማለት ሳቀችበት። «ቤቴን መቼም በዚያ ሌሊት ይዞህ ቢሆን ኖሮ የተመኘኸው ቀርቶ ቲበር ውስጥ ከዓሶቹ ጋር ነበረ የምታድረው።» ነገር ግን ይህ ስትል ከሥራ የመባረር ዕድሉ ከፍተኛ የነበረ ቢሆንም ስለዚያ ጉዳይ ሆነ ብላ ምንም ሳታነሳ ቀረች። ታዲያ እንግዲህ ከዚህ አሳዛኝ አጋጣሚ በኋላ እርጋታን የተላበሰው ግን በባሕሪው ትንሽ ዘብረቅ ያለ የነበረው ኢድ ራውልስ ከዚህ ቀደም በC/A ውስጥ ማንም ቢሆን አድርጎታል ከሚባለው በላይበርካታ አፐሬሽኖችን በሶቭየቶች ላይ በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል። እንደውም በዚህ የተነሣ በኩባንያ ውስጥ ባሁን ሰዓት በሳይመን ተይዞ የሚገኘው ም/ዳይሬክተርነት ስልጣን የሱ ሊሆን ይገባ ነበረ እስከማለት የደረሱ በርካታ ናቸው። «ታዲያ ምን እግር ወደ ላንጅሊ ጣለህ?»

«ለሥራ ጉዳይ፡» አላት ራውልስ። ሩልም ከዚህ አልፋ መጠየቁ ምንም ዋጋ እንደማይኖረው በፍጥነት ተረዳች። «እኔ የምልህ አዝናለሁ ግን ስላንቺ እና ስለሳይመን ጉዳይ ሰምቼ ነበረ፣ በእውነት በጣም ያሳዝናል»

«አረ ባክህ? እንግዲያውስ አንተ ብቻ ነህ የሰማኸው፡» ስትልም ወዲያው መለሰችለት፣ «እኔን እና ሳይመንን ጨምሮ ማለት ነው። ያው በሥጋዊ ሕይወትህ አይቀሬ ከሚባሉት ስህተቶች አንዱ ነው። ግን ጥሩ ልጄን ከዚህ ሁሉ ጉድ አወጣሁ። ሌላው ጉዳዩን በጣም የከፉ የሚያደርገው እሱ ነው»

«አይ ግን ይቅርታ አድርጊልኝና ላጤ ሆኖ መኖር ላንቺ ሳይስማማ አይቀርም። ለምን ቢባል ይበልጥ ስሜታዊ ስትሆኚ ነው የምትታዪው፡»

«አመሰግናለሁ፣ ጌታው። ሴት ልጅ በ35ኛ ዓመት በዓሏ ላይ ይህንን ብትሰማ ነው ደስ የሚላት»

«እንዴ! አንቺ እስኪ አትቀልጂ! 35 ሞላሽ? በይ በይ በዚህ ዓይነቱ ጨዋታ እስከዚህ ዕድሜሽ በመግፋትሽ እንኳን ደስ ያለሽ። እኔ ግን ላልደብቅ የምንግርሽ ሳይመን የቤት እመቤት ያደርግሻል የሚል ፅኑ እምነት የነበረኝ መሆኑን ነው። ወዲ ሰሶቭየት ቢሮ ስትገቢ ነው ይህንን የሰማሁት፣ ታዲያ ፈነጠዝኩ።»

«አመሰግናለሁ ኢድ፣ ላጤነቱና ብቸኝነቱ ደስ ብሎኛል። ማለት ቢያንስ አብዛኛውን ግዜ ደስ እንዳለኝ ነው። እዚህ ዴስክ ላይ ሳጭበረብር ከምውል ከናንተ ጋር አንድ ነገር ስሰራ ብውል ነው ደስ የሚለኝ።

ኮሪደሩን አብረው በግለፍ ሩልም አሳንሰር አብራው ጠበቀች። «ልጆችህ መቼም አሁን ኮሌጅ እንደገቡ አልጠራጠርም»

ራውልስ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ። «ሚሊ ገብታለች። ኤዲ በዚህ ዓመት ነው የጨረሰው። በመስከረም ያገባል»

«የሚገርም ነው፣ ግን እኮ አንተ ለዓያትነት በጣም ዕድሜህ አነሰ»

«እታምኝኝም ዮኔ ጣፋጭ፣ ግን በወረሀ ጥር 50ኛዬን ያዝኩ እኮ አምን ደነገጥሽ እኔም ይኼ ደስ አለኝ»

«እና ታዲያ መካከለኛው የዕድሜ እርከን ላይ መድረስን እንዴት አገኘኸው ባክህ? እኔም ከተቂት ዓመታት በኋላ እዚያ መድረሴ ስለሆነ ነው መጠየቁ።»

ልክ ይህን ግዜ የአላንሰሮቹ በር ተከፈተና ራውልስ ገብቶ በሩን እንዳይዘጋ ሳፍታ ያህል ያዝ አደረገው። «ግን ይኸውልሽ አድምጪኝ፣ ነፍሴ። እኔ ያኔ 35 ዓመት ላይ ሳለሁ ገና መካከለኛ ዕድሜ ላይ ነኝ ብዬ አስብ ነበረ። አሁን ግን ሃምሣ ስለሞላኝ፣» በማለት በሩን ሆነ ብሎ ለቀቀው። «35 እውነትም መካከለኛ እድሜ እንደሆነ አውቃለሁ።» በማለት የጀመረውን ዐረፍተ ነገር ሲጨርስ ፈገግ ባለው ፊቱ ላይ በሩ እንደፈለገው ተዘጋለት።

ሩል በአኳኋኑ ተገርማ እዚያው ባለችበት ቆማ ራሷን ነቅነቅ በማድረግ አሰበችና ወድያው ወደ ቢሮዋ ገሰገሰች። hImagery Analysis የመጣው ማርቲን እየጠበቃት ነበረ። ግን እሷ ፍውም ምቹ ተሽከርካሪ ወንበር ላይ የቀን እንቅልፍ ሸለብ አድርጎት ነበረ። ሩል ቀስቅሳ ከማስነሳቷ በፊት ለሁለቱም ቡና ቀዳች።

«አሀ. . . ይቅርታ ምን ባክሽ እንቅልፍ ይዞኝ ወንበርሽ ላይ ተጋደምኩ፣» አላት ገና በመንቃቱ እየተጨናበሰ። «ትናንት ሌሊቱን ሙሉ ቁጭ ብዬ ስሰራ ነው ያደርኩት እና ከእንድ ከግማሽ ሰዓት በፊት ነው ይኼ የመጣው አንዴ እየሁት ግን ቤት ሄጀ ከመተኛቴ በፊት ቢያንስ ሳሳይሽ ብዬ ነው» አለና ኤንቨሎፕ ያለ ነገር ወደ እሷ አወጣ።

ሩል ጠረጴዛዋ ላይ ያለውን አስተካክላ ቦታውን በማጥራት ማጉሊያ መነጽሯን አወጣች። ማርቲን ደግሞ ከኤንቨሎፑ ውስጥ ያንን በሳተላይት የተነሣውን አመጣው። «አሁን ይበልጥ አንግል ባለበት ሁኔታ ነው ተነስቶ የመጣው፣» አለ ወደ ሆነ አቅጣጫ እየጠቆመ። «ይሁን እንጂ ያኑ ፎቶ ሳይ ደግሞ መርሰዲሷ በሳን በኩል ነው የምተታየው፣ እና ቷርጋዋን ማየት አይቻልም። ግን ያ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የተሻሉ ዝርዝሮችን አግኝተናል። እስኪ ተመልከቺው።»

ሩል ማጉሊያ መነጽሯን ልክ እሱ ባለበት አቅጣጫ አስተካከለች። ለእፍታ ያህልም ያንን ቦታ ደጋግማ ተመለከተችው። «ምንድን ነው? የጎልፍ ጋሪ?»

«እኔም ሳየው እንደዚያ ነው የመሰለኝ፣ ግን ከዚህ ቦታ በጣም ቀረብ ያለው የጎልፍ ኮርስ ያለው ፌንሳንድ ነው፣ ብቻ እሱን ተይው ደግሞስ በሶቭየቶች ግዛት ውስጥ የጎልፍ ጋሪ ተገኘ ቢባል እንኳ ያስኬዳል እንዴ?»

«እዎን፣ እሱስ አያስኬድም።» አለች ሩል እያሰበችበት። «ሰምቼ አላውቅም፣ ሩሲያ ውስጥ ጎልፍ፣ እይሆንም»

«ሌላ ትኩረትሽን የሚስብ ወይ ያስገረመሽ ነገር አይተሽ ይሆን?» ሲል ማርቲን ጠየቀ። ሩል በድጋሚ ተመለከተች። «እዎን ሁለት ሰዎች አሉ። እንደኛው የጎልፍ ወይ የቤዝ ቦል የሚመስል ኮፍያ አድርጓል»

«እዎ፣ ግን እሱን ማለቴ አይደለም። ዘብ የቆመውን ሰው ተመልከችው፣»

http://ethzare.wordpress.com

ሩል ተመለከተች። የጎልፍ ጋሪው ወደ ትንሽ በር የሚያመራ ሲሆን ያ በርም ቦታውን ከቀሪው የግቢው ቦታ የሚለየው ይመስላል። አንድ መለዮ የለበሰ ሰው ትከሻው ላይ አግድም መሳሪያ አንጠልጥሏል። ከዚያ በጓሳ ታልፎ ሲኬድ ግን የባሕሩ ጫፍ እንጂ ሌላ ምንም የለም። «ለመሆኑ ጋሪው ወዴት ነው የሚሄደው?» ስትል ሩል ጠየቀችው። «ምንም ትርጉም አይሰጥም እኮ። አንድ በሌላው በኩል ድንጋያማ የውሃ መሬት ካልሆነ በቀር ሌላ የሌለው የሚጠበቅ በር? ታዲያ ይኼ ምን ይባላል?»

«አይደለም፣ ይዝውልሽ እኔ እንደዚያ ማለቴ አይደለም።» አላት ማርቲን ትዕግስት እያጣ። «እስኪ ዘቡ ያነገበውን መሣሪያ ተመልከቺው። እና ምንነቱን መናገር ትችያለሽ? ሩል መነጽሯን ባለበት ቆሞ ጋሪውን ሰላምታ ይሰጥ ወደነበረው ዘብ አደረገችው። መሣሪያው አሁንም ጀርባ ላይ ይታያል። «ትንሽ ደብዝሏል ግን . . . እንዴ በስመአብ ማርቲን፣ ኢንግራም አውቶማቲክ እኮ ነው የሚመስለው!»

«ቡዚ የሚሉት ሊሆን ይችላል እኮ» አላት ማርቲን፣ «ሆኖም ግን በቡዚ ላይ እንደዚህ ያለውን ማፈኛ አይቼ አላውቅም። እንዲያውም Mac 10 ነው የሚመስለኝ። አንድ ሌላ ተጨማሪ ነገር ደግሞ ላንሳ። ከዚያ እሄዳለሁ። ወደ ውሃው ሲያመለክት በፎቶግራፍ ጫፍ ላይ ያለን ቦታ ነበረ ያሳየው «እስኪ ይህንን ተመልከቺው»

ሩል ማጉሊያ መነጽሯን ወደ ተባለው ቦታ በማመልከት በጣም አተኩራ ተመለከተች፣ ያየችውን ነገርም ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ሞከረች። በውሃው ላይ አንድ ነገር አለ፣ አንድ ትንሽ የሆነ ነገር ነው። ይህ ነገር በውሃው አካል ላይ በግለፍ እንዲያውም ለስለስ ባለው የውሃው አካል ላይ ምልክት እየፈጠረ ነው። «አባዬ ዓሣ አጥማጅ ነው፣ አለችው ሩል። እና ይህንን ነገር ሳየው ትንሽ Whatchamacalits የሚባለውን . . . ማለትም አባዬ እንዴ መሳተቻ ገመድ የሚጠቀምበትን ነው የሚመስለው። አባዬ አሁን ያልኩህን እና ይህንን የምታሳየኝን የሚመስል ገመድ በውሃው አናት ላይ ያስቀምጣል። እና እሱን ነው የሚመስለው ትልቅ ሆነብኝ እንጂ። አባዬ በሱ ግን ምንም ይዞ እንደማያውቅ አስታውሳለሁ።»

«እዎን እንደዚያ ነው የሚመስለው፣» ሲል ማርቲን ስምምነቱን ገለጸ። «ግን ይኼኛው ተለቅ ይላል። እንደውም እኔ ዝምብዬ ሳየው ለሰርጓጅ መርከብ በመባል የተሠራ የጥቃት ፔርስኮፕ ነው የሚመስለው፣»

ሩል አተኩራ ተመለከተችው። «እርግጠኛ ነህ?»

ማርቲን ሳቀ። «እረ ቅንጣት ታህል እርግጠኛ መሆን አልችልም፣ ግን እስኪ ይህንን ደግሞ ተመልከቺው።» በማለት ከዴስኩ ላይ አንድ ካርታ ዘረጋ። «የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የስዊድን ወይም የፊንላድ ለመርከብ ሲባል የተሠራ ካርታ የለም ግን ካየር ላይ የተነሣ ለባሕር ጉዞ የሚያገለግል አገኘቻለሁ። እዚህ ጋ የሳልኩት አራት ማዕዘን ይታይሻል? ይኼ በሳተላይት በተነሣው ፎቶ ላይ ኮርድኔቶቹ የሚይዙት ቦታ ነው። ወፋችን ከሰሜን ምዕራብ ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ነው የምትንቀሳቀሰው በዚህ የተነሣ ነው የቦታው አራት ማዕዘን እይታ ትንሽ ጋደድ ያለው። እዚህ ጋ ደግሞ ባልቲክ አለ፣ ከዚያ ደግሞ የላቲቪያ ባሕር ዳርቻ ከዚያ ደግሞ በዳርቻው ውስጥ ላይፓጃ ኤዘርስ የተባለው ውሃ ማለትም የውሃ አካል አነስተኛ ቁራጭ ነገር ነው። እዚህ ጋ ደግሞ ጠበብ

ያለ መግቢያ አለ ምናልባትም ተፈጥሯዊ ነው ግን ደግሞ በሌላ በኩልም መርከቦች እንዲዘልቁበት በመባል ተሻሽሎ ባዲስ መልክ የተሠራ ሊሆንም ይችላል ምናልባ ሰርጓጅ መርከቦች ከዚህ ይሆናል የሚለቀቁት።»

ሩል በፎቶግራፉ ላይ ያለውን ነገር ተመለከተችው። «ግን እኮ ፔርስኮፕ ለመባል በጣም መጠኑ አነሰብኝ» አለችው።

«ለጥቃት የሚሆን ፔርስኮፕ ነው፣» ሲል ማርቲን ደግሞ ምላሽ ሰጠ። «ሰርጓጅ መርከቦች ለአጠቃላይ ጥቅም ሲባል የተሠራ ፔርስኮፕ አላቸው ግን በቦታው አቅራቢያ የጠላት መርከብ ቢኖር እንዲህ በጣም ያነሰ ዓይነት ይጠ ቀማሉ፣ ይህም በጠላት በደምብ ሊታይ የማይችል ነው። እንደውም እንደኔ ከሆነ መጠኑ ለተባለው ዓላማ በጣም ትክክለኛ ነው።»

ሩል በሳተላይት በተነሳው ፎቶ ላይ ዙሪያውን ተመለከተች። «ለመሆኑ በዚህም ሆነ በሌላው ፎቶ ላይ የሰርጓጅ መርከቦችን ማቆሚያ ሊያመላክት የሚችል ነገር አይተህል?»

ማርቲን ራሱን ነቀነቀ። «አላየሁም፣ ያ ነው እንግዲህ ቀደም ሲል የሰጠ ሁትን ግምት አጠራጣሪ የሚያደርገው ወደ ቁራጩ የውሀ አካል ሰርጓጅ መርከብ ልከው ካልሆነ ማለት ነው። ግን እዚህ ጋ ምን ሊሠሩ እንደመጡ በምን ይታወቃል?» ተነሥና ጀኬቱን ታግሎ ማለት በሚቻል ሁኔታ ለበሰው። «እንግዲህ ይህንን መገመቱ የኔ ሥራ አይደለም። እኔ ምስሎችን ማየት ነው ሥራዬ፣ እንቺ ነሽ ትንተና የምትሰጪው፣ ሥራሽም ያ ነው። ይልቅ ቤት ሂጂ ልተኛ።»

«እመሰግናለሁ ማርቲን፣» አለችው ሩል። «ከመሄድህ በፊት ይህንን ስላሳየኸ ኘ በጣም ነው የማመሰግነው በዚያ ላይ ይኼንን የኢሮቻርት ስላሳየኸ ኝም እመሰግንሀለሁ»

«ይህማ የአገልግሎቱ አካል እኮ ነው፣» አላት። ይኼ የCIA እንክብካቤ አንዱ አካል ነው»

ሩል ቁጭ እንዳለች የሳተላይቱን ፎቶግራፍ እና የጎልፍ ጋሪውን ብሎም ኢንግራሙን ተመለከተች። ምናልባትም ፔርስኮፑን ወይንም ደግሞ መርሰዲሱንም ጭምር ተመልክታ ይሆናል። ምናልባትም በጣም ሚት ስለሆነ እና እሷም የመነቃቃት ስሜት ስለተሰማት ሊሆንም ጭምር ይችላል። ወይ አለቆጀ ብዙም የማይወዱት ስለሆነ፣ የሴትነት ስሜቷ ይሆናል። ወይ ደግሞ ትንሽ ቀኝበር አድርጓት ይሆናል፣ ግን በርካታ የተበታተኑ መረጃዎች በጭንቅላቷ ውስጥ ነበሩ፣ ከዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ አንድ የሆነ እንኳር ነገር እንዳለም ይታወቃል።

ኮስሞውን አነሳችና የጣቢያ ሪፖርቶችን ተመልክታ መቃረሚን ጀመረች። የኮምፒውተር ባለሞያዎቹ በሥራቸው ተጠምደው በሆነ ስትል ፀለየች ለምን ቢባል ጠረጴዛዋ ጋ መጥተው ከሆነ እነዚያን ወሳኝ የሆኑ ወረቀቶች ሁለተኛ አታገኛቸውም። ፓ ዕድለኛ ነኝ ጃል። ከሪፖርቶቹ የተወሰኑ አጋጣሚዎችን መረጠችና ወደ ማተሚያው አስገባቻቸው። ከዚያም NEXIS ወደ ተባለ የኮምፒውተር ወኪል በመደወል ከጥቅምት ወር 1981 ጀምሮ ያሉ በርካታ ዜናዎችን አወጣች። ከምሳ ሰዓት በፊትም አስቂኝ የሆኑት ያተለቀሙትን በርካታ ሪፖርቶች በሙሉ በእጇ አስገባች። ብቻ ያ ብጥስጥስ ያለው መልክ ያልያዘው ነገር አሁንም በውስጧ እንዳለ ነው። እንዳመነችውም እርግጠኛ ናት።

http://ethzare.wordpress.com

ከዚያም ያወጣቻቸውን፣ በሳተላይት የተነሣውን ፎቶግራፍ፣ የአየር ፎርቱን በመያዝ ያለ የሌላትን ተስፋ በመሰነቅ ወደ አላን ኒክሰን ቢሮ አመራች።

12

ሔልደር ምቾቱ በማይደላ የፐላስቲክ መቀመጫ ላይ ተቀምጦ መዝገቡን ድጋሚ መረመረው። ቀላል ሰርጓጅ መርከቧን ከሶኮሎፍ ጋር ደህና አድርጎ ፈትሿል። በመርከቧ ላይ የሚገኙ የኤለክትሮኒክስና ሌሎች መሳሪያዎችን ማንቀሳቀስ እንደምትችል ያውቃል። የባህር ሰርጓጅ መርከቦች ልምድ የሌላት መሆኑ ግን ረብሾታል።ግን የባር ሰርጓጅ መቆጣጠሪያዎች አቀማመጥ ምንም ችግር ለመፍጠር የሚፈቅድ አይደለም። መርከቧን መንዳትና አቅጣጫዋን መቆጣጠር እንዲሁም የግንኙነት መስመሮችን ማንቀሳቀስ ትችላለች። መቀመጫቸው ፊትና ኋላ መሆኑን ወዶታል፣ ይህን ቀፋፊ ፈቷንና የሙት ዓይኖቿን ፊት ለፊት ለመመልከት አይገደድም። ከበላዩ በስተግራ የተሰቀለ መስታወት አለ፣ ይህ የኋላ እይታ የሚጋብዝ አቅጣጫን አልያዘም። ከሌላ ረዳት ጋር ቢሆን እንዲስተካከል ትዕዛዝ ባስተላለፈ ነበር፣ ሆኖም ከቫለሪ ሶኮሎቭ ጋር ስለሆነ ይህን አቅጣጫ መያዙ አስደስቶታል። ደሞ ጠረን አላት። ወደመርከቧ ገብተው ገና አምስት ደቂቃ ሳይሆናቸው ቦታው በሚሰነፍጥ ሽታ ተሞላ።

ፊት ለፊት ወዳሉት ወደቦች ተመለከተና በየተራ በህሊናው ቀረፃቸው። ከፊሉ የመስታወት እንፀባራቂ መመልከቻዎች ከውሀ በታች ሲሆኑ፣ የሳይኖው ክፍሎች ደሞ ከውሃ በታች ናቸው። የጥገና አባላቱ ገጽታዎች መልሶ አፈጠጠበት። ከመሀከላቸው አንዱ አውራጣቱን አሳይቶ ማበረታቻ ሰጠው። እሱም በተመሳሳይ ምልክት ምላሹን ሰጠ «ለመጥለቅ ዝግጁ፣» አለ፣ ለራሱም ለሶኮሎፍም እየተናገረ።

«ዝግጁ፣» አሉት።

ካፒቴይን ወይንም ሌላ የመርከበኝነት ማዕረግ አስቀድማ ስላልጠራችው ተበሳጭቷል፣ ንዲቱ እንዲታይበት ግን አላደረገም። አላስፈላጊ የሆኑ ቃላትን ከናካቴው መጠቀም የምትፈልግ አይደለችም። «እየጠለቅን ነው፣» ብሎ በስተቀኙ ወደሚገኙት መቆጣጠሪያ ቁልፎች እጁን ዘረጋ። ቁልፎቹን ተጫናቸው። አስገምጋሚ ድምጽ ተሰማና ሰርጓጅ መርከቧ በፍጥነት ትሰምጥ ጀመር። ሁለት ሜትር ላይ ስትደርስ ጠለልህን ያዝ ብሎ ለራሱ ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ፣ ጣቶቹና ሰርጓጅ መርከቧ ትዕዛዙን ፈፀሙለት። ለአንድ የባህር ሀይል ረዳት ቡድን ትዕዛዝ መስጠት ተሳምጓል። ብዙ ጊዜ ስለሚወስድበት ይህን መተው ይኖርበታል። በድንገተኛ ሁኔታ ጊዜ ትዕዛዝን ማስተላለፍ ብቻ የሰከንድ ሽራፊ ማባከን አይፈልግም። ተንሸራታቹን የፍጥነት መቆጣጠሪያ ሁለት ኖቶች ላይ አደረገው፣ ይህ ፍጥነት ከመንሳፈፊያ የሶስት ኖቶች ፍጥነቱ ያነሰ ቢሆንም መርከቧን በጥሩ ሁኔታ ለመቆጣጠር ግን በቂ ነው። አነስተኛ ድምጽ ከተሰማ በኋላ ወዲያውኑ ባህር ሰርጓጅ ከመጠለያዋ ወጣች የመጠለያውን ጣሪያ

እንዳለቀ ደብዛዛ የፀሐይ ብርሀን ወደባህር ሰርጓጇ ገባ። የውስጡ ቀይ መብራት አላስፈላጊ ሆኑ። «የነን መብራቶቹን እጥፊያቸው፣» አለ።

ምንም ነገር አልተፈጠርም። ራሱን አዞረና ቀና ብሎ በመስታወቱ ወደ ሶኮሎፍ ተመለከተ። ፊት ለፊት የምትመለከት ትመስላለች። «ሶኮሎፍ፣ የውስጥ መብራቶቹን እጥፊያቸው፣» እንደመንቃት ብላ ለጥቂት ጊዜ ግራ መጋባት እየታየባት ቆየችና፣ ቁልፎቹን ተጫንቻቸው። «አመሰግናለሁ፣» አለ በቀዘቀዘ ስሜት፣ «እንድ ትዕዛዝ በምሰጥሽ ጊዜ በቶሎ እንድትፈጽሚ እፈልጋለሁ፣ ገባሽ?» ከኋላው እንደሆነች ድንጋጤዋ ታወቀው።

«እምን ጌታዬ፣ በጣም አዝናለሁ።»

ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል የባህር ጠር ሰፈር ክልሉን ለቅቆ እስኪወጣ ድረስ አንድ አቅጣጫ ይዞ ቆየ፣ ከዚያም ያለበትን ቦታ ለማረጋገጥ ያህል ቻርቱን መልከት አደረገ፣ ሰርጓጅ መርከቡን ወደደቡብ አዞረውና ማጥለቂያ መዘውሩን በጥቂቱ ገፋ አደረገው። የጥልቀት መለኪያ መቆጠሪያው አራት ሜትር፣ ከዚያም ስድስት ሜትር ተነበበ። የሰርጓጇ ውስጥ እየጨለመ ሄደና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎቹ አረንጓዴ አንፀባራቂ ሆነው መታየት ጀመሩ። በእንድ እግሩ ራዳሩን ረገጥ ሲያደርገው መርከቧ ከመቅጽበት ምላሽ ሰጠች። የግራውን ራዳር /አቅጣጫ መቀየሪያ/ ሲሞክረው እሷም ዞረች፣ መስመሩን ያዘ፣ ጸጋመኛ ተስተካክላ ከተሰራችው የዚህች መረከብ ሌላ ስራት ይልቅ ይህቺን መቆጣጠሩ ይቀላል። ከውሀ በታች የመብረር ስሜትን የሚያጎናጽፍ መሆኑን ወደደው። የጥልቀት መቆጣጠሪያውን ሲነካው ተጨማሪ ሁለት ሜትር ወደታች ወረደች። መሳሪያው ላይ ከበላዩ ስምንት ከበታች የአራት ሜትር ጥልቀት ያለው ውሀ መኖሩን ያመለክታል። በቻርቱ ላይ እንደሚታየው ሐይቁ ወደ ደቡብ እየራቀ ሲሄድ ጥልቀቱ እየጨመረ እንደሚመጣ ያመለክታል። ከስሩ የአራት ሜትር ጥልቀትን እየጠበቀ ሰርጓጇን ወደታች መንዳቱን ቀጠለ በክፍላቸው ውስጥ ያለው ብርሀን የባሰ ጨለመ።

«እ. . . እ መቆጣጠሪያዬን ማየት አልቻልኩም፣» አለች ሶኮሎፍ። ድንጋጤ ይስተዋልባታል።

«መልካም፣ የራስሽን የመቆጣጠሪያ መብራቶች አብሪ፣ መንቀሳቀስ ከመጀመራችን በፊት ማድረግ ያለብሽ ነገር ነበር።» ጥሩ መስተካከል ያስፈልጋታል።

«የመቆጣጠሪያ መብራቶቹ ማብሪያ ማጥፊያ አይታየኝም።» አለች ቶሎ ብላ።

«እዚያ ኋላ ባትሪ የለሽም?» ሲል ቆጣ ብሎ ጠየቃት።

የመንኳኳት ድምፅ ተሰማና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከሰርጓጅ መርከቧ ነጭ ግድግዳ ላይ የተንፀባረቀ ብሩህ ነፀብራቅ ታየ። «ይኸው፣ ማብሪያ መጥፊያውን አገኘቼዋለሁ።» አለች፣ ባትሪው ጠፋና፣ ሙሉ ጭለማ ዋጣቸው።

ሔልደር የመርከቧን ሀይል አቋረጠና ሐይቁ ወለል ላይ ወርዶ ዘው እስከምትል ድረስ ዝም አላት። «ግሩም ነው፣» አለ። «አሁን የምሽት መመልከቻ ብርሀኑን አጥፍተሽዋል። እስከሚመጣ ድረስ እዚሁ እንቀመጣለን።»

«ይቅርታ ካፒቴን፣» አለች በለሆሳስ። «በጣም አዝናለሁ። አላወቅኩም።»

ጥሩ። አሁን ቢያንስ ካፒቴን ብላ እየጠራችው ነው፣ ይህን እንድታደርግም አልጠየቃትም። የሀይል መስጫውን ሙሉ በሙሉ ሰጥቶት

http://ethzare.wordpress.com

ወደላይ ጉሥ ጀመሩ። ሰርጓጅ መርከቧ ወደኋላ ዘመም ብላ ሽቅብ ስትወነጨፍ፣ ሶኩሩፍ በረጅሙ ስትተነፍስ ሰማት። ፈገግ ብሎ ሁለት ሜትር ጥልቀት ላይ ደርሶ ቆመ። ትንሽ እንቃቅቷታል፣ አሁን ታዲያ በዚህ መርከብ ላይ ከተሳፋሪነት በላይ ቦታ እንዲኖራት ለማድረግ አንድ መንገድ መፈለግ አለበት።

13

ፍል፣ ከአለን ኒክሰን ፊት ለፊት በጠረጴዛው ትይዩ የተቀመጠችው ቆራጥ ልብ ይዛ ነበር። አንድ እጅግ ጠቀሜታው የጎላ ነገርን መያዟን ደመነፍሷ እንደነገራት ሁሉ፣ ይህ ውይይታቸው አንድ ውጤትን ያምጣ አያመጣ እንደሁ የሚወሰነውም ይኸው ነገር መሆኑ ታውቋታል። እሷና ኒክሰን ሌሎችም ሰዎች ሆነዋል። እሷ በስራዋ ልምምድ፣ ስልጠና፣ ብልሀትን ፈጣን ውሳኔ ሰጪነትን እንዲሁም ድፍረትን አግኝታለች። ግን እርምጃዎቿ ምን አይነት ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ሊያመጡ እንደሚችሉ መገምገም አስቸግሯታል። ኒክሰን በገምጋሚና በመዛኝነት ሳይሆን፣ የሰለጠነው በበላይ አመራር ትምህርት፣ የሚመራው ፖለቲካ ነው፣ ስለስለላ ሁኔታዎች ቅድም ምርመራ የሷን ያህል ብቃት ባይኖረውም ወጪ ለማግኘት ወይንም እርምጃ ለመውሰድ ፈቃድ ለመጠየቅ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ተሳስቶ እያውቅም። አሁን አትኩሮቱን ማግኘት ከቻለች፣ ቀጣይ ችሎትን ከማንና እንዴት ማግኘት እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል። በረጅሙ እየር ሳበችና መናገር ጀመረች።

«አለን፣ ርዳታህን እፈልጋለሁ፣» ሀሳቧን ከመግለጽ ይልቅ በተግጽኖ መጀመሩ ከሁሉ የተሻለ መስሎ ታይቷታል።

«እንዴታ፣ ኬት። የፈለግሽውን ላደርግ እችላለሁ።» ብሎ ኒክሰን እግሩን ጠረጴዛው ላይ ሰቅሎ እጆቹን አጣመረ። ፍል ይህ አኳኋኑ በጎ ፈቃደኝነቱን የሚያመለክት መሆኑን ጠንቅቃ ከልምዷ ታውቃለች። ከዚያም፣ «ጉዳዩ ስለማጆሮቭ ነው እንዴ?» አለ። ችግር መጣ። ስለዚህ ጉዳይ ቀድሞውንም አልተቀበላትም ነበር።

«ከፊሉ ነው፣» አለች። «ግን ከዚያም በጣም ይሰፋል» ከመጀመሪያው እንዲብራራልህ ፍቀድልኝ። ይህን ነገር እንደምታቀው እውቃለሁ፣» /አብጠርጥሮ ያውቀዋል/ «ግን፣ ለኔም ሆነ ለአንተ ሲባል ይህን ጉዳይ ማያያዝ ይኖርብኛል፣ ስለዚህ ታግሰህ አዳምጠኝ።»

ኒክሰን በማስተዋል ራሱን ከፍ ዝቅ አደረገላት።

«በአክቶበር 1981፣ የሶቭየት ህብረት ንብረት የሆነች ዊስኪ ደረጃ ያላት ሰርጓጅ መርከብ ስዊድን የባህር ዳርቻ አካባቢ በሚገኝ በጥብቅ የሚጠበቅ የጦር ሰፈር አጠገብ ትዘዋወራለች። እንደምታስታውስ ይህ ክስተት በአለም ዙሪያ ትልቅ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ ሰንብቷል። ከዚያ በኋላ በተለያዩ የስዊድን ግዛቶች ላይ ብዙ የሰርጓጅ መርከብ /ሾፒሪስኮፕ/ የውሀ በላይ የርቀት መመልከቻዎች ተስተውለዋል። ስቶኮልም ላይ ምሳ ለመመገብ የወጣ አንድ የስዊድን የባህር ኃይል መኮንን በከተማዋ ሀል የፔሪስኮፕ ጀልባ ተመልክቷል። ይህ የሆነው ሶስት የአሜሪካ የጦር መርከቦች እዚያ በነበሩ ወቅት ነው። ይህን መሰል ነገሮች ተስተውለዋል።»

የኒክሰን ቅንድቦች ወደ ላይ ተሰጠጡ።

«አሁን፣ ይህ ሙሉ በሙሉ አዲስ ክስተት አይደለም፣ የሶቭየት ባህር ሰርጓጆች በስዊድን የውሀ ክልሎች ላይ መታየታቸው ለብዙ ዓመታት ሲነገር የቆየ ነበር። እኛ የገመትነው፣ የወዳጅነትም፣ የጠላትነትም መንፈስ በሌለበት ሁኔታ መኮንኖቻቸውን ጠንከር ያለ ልምምድ እየሰጧቸው ነው ብለን ነበር። በዓመት ሀያ ጊዜያት ገደማ ይመላለሳሉ። ግን ከ «ዊስኪ በቋጥኞች ላይ» (Whiskey on the rocks) ገጠመኝ በኋላ ቁጥራቸው በዓመት ወደሁለት መቶ አሻቀበ፣ ጥቂቶቹም ልዩ የሚያደርጋቸው ሁኔታዎች ነበራቸው።»

«እንዴት?» አለ፣ ኒክሰን ይህን ሁሉ ያውቃል ብላ እንደምታስብ ዘንግቶ።

«በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሰርጓጅ መርከቦቹን ፊት ለፊት በሚጋፈጧቸው ጊዜ እንደድሯቸው እገሬ አውጪኝ ባለው አልፈረጠጡም። ባልተለመደ ተደጋጋሚነት፣ እየተባረሩ ሳይቀር ወደስዊድን ግዛት የበለጠ እየሰረጉ ይገባሉ ሁለተኛ ሰርጓጅ መርከቦቹ ብቻ ሳይሆኑ፣ ጠላቂ ዋናተኞች ከላያቸው ላይ እየወረዱ በዋና ደረቅ መሬት ድረስ መግባታቸው፣ ተቀባይነት ያላቸው ሪፖርቶች ደርሰውናል። ጥቂት ሚሊሽያዎች ቢተኩሱባቸውም ይዘዋቸው ግን አያውቁም። ከሁሉም በላይ የሚገርመው ግን እኛም ሆንን ስዊድኖች፣ የእኛ መንግስትና ሰራዊታችን እንዲሁም የስለላ ሀይሎቻችን፣ የእነሱ መንግስትና ሰራዊታቸው እንዲሁም የስለላ ሀይሎቻቸው፣ የሶቪየት ህይል ይህን ለምን እንደሚያደርግ የሚያብራራ ተዓማኒ መላምቶችን ማቅረብ አለመቻላቸው ነበር። ብዙ ግላምቶች ነበሩ-ከስልጠና ጀምሮ እስከቀልድና ጨዋታ ሊሆን ይችላል የሚሉ-ግን ሶቭየቶች ከዚህ በሚያገኙት ጥቅምና ከሚያጡት ነገር ሚዛን አንፃር ምክንያታዊነታቸው የሚዋጥ አልሆነም። ለምሳሌ፣ ሰርጓጅ መርከቦቻቸው ስዊድን ውስጥ በተያዙ ጊዜ የአለም መገናኛ ብዙሀን በገሀድ አዋርደዋቸዋል፣ ግን ይህ አልገታቸውም እንደጠቀስኩት ይህ አልገደባቸውም፣ እንደውም ከዚያ ሁኔታ በኋላ ቁጥራቸው በእስር እጥፍ ጨምሯል።»

«ልክ ነሽ፣ ነገሩ በሙሉ በርግጥ ግራ የሚያጋባ ነበር። ለምን እያደረጉት እንደሆነ የሚያብራራ አዲስ መላምት አለሽ?»

ፍል እጇን ወደላይ አነሳች። «አዲስ ባይሆንም፣ የቀድሞውን የሚደግፍ ሌላ ሀሳብ አለኝ። ግን ታገሰኝ፣ እዚህ ላይ የምናክላቸው ሌሎች ጥቂት ሀሳቦችም አሉ። በጣም የተበታተኑ ቢሆኑም፣ ተሰብስበው እንደ ምስልን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይህም ከዚህ ሁሉ ነገር ጀርባ ያለው ማጆሮቭ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል።

ኒክሰን እግሩን ከጠረጴዛው ላይ አወረደና ቀጥ ብሎ ተቀመጠ። ምንም ስሜት አይነበብበትም።

ፍል ሁለቱን የሳተላይት ፎቶግራፎቿን ጠረጴዛው ላይ አኖረቻቸው። «እዚህ የሚታየን የሚመስለው በጣም ለየት ያለ የሠራዊት ማሰልጠኛ ጦር ሰፈር ነው። የሚገኘው በላቲቪያ /ካሉት/ በሀር ዳርቻ ላይታጃ ውስጥ ሲሆን፣ ልዩ የሚያደርገውም ሌላ ነገር አስመስለው ሲገነቡት ብዙ ጣጣ ማለፋቸው ነው።» ወደ ጥንድ አጥሩና ስልጠና ላይ እየሮጡ ያሉትን መኮንኖች አለመለከተችው። «ማጆሮቭ ዋጋቸው ውድ የሆኑ የሌሎች አገሮች መኪኖችና የሌሌክትሮኒክ ውስብስብነት ያላቸውን ቁሳቁሶች እንደሚያፈቅር እናውቃለን፣ እዚህም ጦር ሰፈር ወስጥ፣ አስተውል፣ ማርሴዲስ 500 ኤስ ኢ አውቶሞቢል

http://ethzare.wordpress.com

ትታያለች። ይህች መኪና ከሞስኮ ውጪ አትሸኝም። ከዚህ ሌላ የጎልፍ መጫወቻ ጋሪ፣ ይሆን ታያለህ?»

ኒክሰን ከጠረጴዛ መሳቢያው ትልቅ ማጉያ መስታወት አወጣና የጎልፍ ጋሪዋን መረመራት። ሩል ፎቶግራፉን በጣቷ እየጠበጠቸች። «እዚህ ጋሪ ላይ ካሉት ሁለት ሰዎች አንዱ፣ ግለት ኮፍያ ያደረገው ማጆሮቭ ነው ብዬ የጓጓት ደመወዜን እወራረዳለሁ። የማጆሮቭ እዚህ መገኘት ደግሞ የዚህ ጦር ሰፈር አሰፈላጊነት የትየለሌ ያደርገዋል።»

«ሌላስ ምን ይዘሻል፣ ኪት?» ጠየቀ ኒክሰን።

«ትንሽ ግምት ያለው፣ ግራ የሚያጋባ ግን ከሌሉቹ ሁኔታዎች ጋር የሚገጣጠም ነገር አለኝ። በሁለቱ የባህርና የአገረኖ ጦር ሰፈሮች ያሉት የልብስ ንጽሕና ቤቶች ድንገት፣ የሚያጥቧቸው ሽሚያቾ ቁጥራቸው እጅግ ቀነሰ። ማለት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መኮንኖች ዋይሌላ ስፍራ ዝውውርን አግኝተዋል። ሌላው፣ ባለፈው ወር ከብሪታኒያ የጦር መሳሪያ ጄፖ ውስጥ ሁለት ሺህ የእንግሊ ማርክ 10፣ ሁለት ሺህ ጠብመንጃዎች ተሰርቀዋል-ይህ ዘብ፣» የሳተላይት ፎቶግራፉን ጠቆመችው፣ «የያዘው ጠብመንጃ ኢንግራ ማክ ነው። ሌላው፣ በሌኒንግራድና በካሊኒንግራድ መሀል የሚታወቅ የሶቪየት ባህር ሰርጓጅ መርከብ ጦር ሰፈር የለም፣ ብቃቱ የተረጋገጠው የምስል ምርመራችን ግን እዚያ በፖላንድ ድንበር አቅራቢያ የሚታየው ነገር የባህር ሰርጓጅ የውሀ በላይ የርቀት ማሳያ መሳሪያ መሆኑን ይገልፃል። ሌላው፣ ይህንን እባክህ ጠለቅ ብለህ ተመልከተው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ሶቭየቶች ድንገት በዩኒቨርስቲዎቻቸውና በየቋንቋ መማከላቸው የስዊድንኛ ቋንቋ ትምህርት በሚያስገርም ሁኔታ አሟጠፈውታል። አንድ ነገር ልንገርህ አለን። ስዊድን ውስጥ ካልሆንልክ በስተቀር ስዊድንኛ በዓለም እጅግ አላስፈላጊው ቋንቋ ነው።»

ኒክሰን ቀና ብሎ ተመለከታት፣ «ወደየት እያመራሽ ነው ኪት?»

ሩል ከጾሲዋ አንድ የዜና ቅጻጅ አወጣች። «ይህ፣ በአሁኑ ወቅት የርያል ስዊድን ባህር ሀይል የበላይ አመራር የሆኑት የምክትል አድሚራል ቤንት ሹባክ ንግግር የቃል በቃል ግልባጭ ነው። አንድ የውጭ ሀይል ከስዊድን ጋር ጦርነት ለመግጠም ዝግጅት እያደረገ ነው። ይላል።» ሩል ጋዜጣውን አስቀመጠችና ኒክሰንን ተመለከተችው። «ይህ፣ ሶቭየቶች በስዊድን የውሀ ክልሉች ላይ ምን እየሰሩ ነው ለሚለው ከተቀመጡት ብዙ መላምቶች አንዱ ብቻ ነው። ግን እየተደረገ ያለው ነገር የሁኔታውን ክብደት ያጠነክረዋል ብዬ አስባለሁ፣ አይመስልህም?»

ኒክሰን ለአፍታ ያህል ግራ በመጋባት ተውጦ ተመለከታት፣ ከዚያም እንደምንም ተናገረ። «ግን ለምን? ሶቭየቶች ያለጦርመሳሪያ ፍልሚያ የማስፋፋት መርህቸውን ድንገት ሰርዘው ለስተኛውን የዓለም ጦርነት ለመቀስቀስ የሚያስችል ነገር ለመጀመር ፈለጉ?»

«ሶስተኛው የዓለም ጦርነት ለመቀስቀስ? ኮማን ጋ? ከእኛ? ስዊድን እንደሁ ከስዊትዘርላንድ ባልተናነሰ መሀል ሰፋሪ ናት። ጠላትም ወዳጅም የላትም። እስኪ፣ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (NATO) ጣልቃ ለመግባት ፈለገ እንበል፣ እኛ እንዲት እናደርጋለን? የሶቪየትን የስዊድን ወረራ ለመከላከል የሚያስችለን የአገረኖ ሀይል በቦታው የለንም፣ ስለዚህ የኒውክሌር መሳሪያዎችን ለመጠቀም እንገደዳለን። ስምንት ሚሊዮን ስዊድናውያንን

ከሶቭየት አገዛዝ ለማዳን ሲል አውሮፓን ብሎም አለምን ሊያጠፋ የሚችል የኒውክሌር ጦርነት ኤቶ ይቀሰቅሳል ብለህ ታስባለህ?»

የኒክሰን ዓይኖች ማተኮር የተሳናቸው መሰሉ። የመናገሪያው ያጣ ይመስል ፀጥ ብሎ ተቀመጠ። ከዚያም ራሱን ገዛ። «ኪት፣ ስለዚህ ጉዳይ ከሌሉች ሰዎች ጋ መነጋገር ይኖርብኛል። የያዝሽው ይህ ብቻ ነው?»

«ባለኝ ስልጣን ሳገኘው የቻልኩት ይህንን ብቻ ነው። ሀይል ልታገኝልኝ የምትችል ከሆነ ብዙ ተጨማሪ ነገር ይገር መምጣት እችላለሁ።» ረጋ፣ ቀዝቀዝ ብላ ለመታየት ጥረት አደረገች። «ተመልከት አለን፣ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደመሠረተ ቢስ ወሬኖ ሆኜ መታየት አልፈልገም፣ የያዝኩትን ነገር ሁሉ በመረጃ ላይ የተመሰረተ መላምት ነው ብለህ እንደምትነግራቸው አንተም ሆንክ ማንም እናውቃለን። ጓሩ ግን የስለላ ምርመራ ሒሳብ የሞላበት የፊዚክስ ትምህርት አይደለም፣ የተወሰኑና የማይለዋወጡ የተፈጥሮ ህጎችን ተመርኩዞ የሚንቀሳቀስ አይደለም እንዳንድ ጊዜ፣ ከጥንቆላ የሚለየው በጥቂቱ ብቻ ሆኖ ይገኛል፣ ይህን ታውቃለህ ነገር ግን ልምዴን መሠረት በማድረግ፣ አንድ ነገር እየተከናወነ ነው ብዬ እንደማምን ልነግርህ ግዴታ አለብኝ። ማስረጃ ላቀርብለት አልችልም፣ አንተ አንድን ሰው ማሳመን ችለህ አንድ ዓይነት ተጨባጭነት ያለውን መረጃ ማስገኘት የሚችል ህቡዕ እንቅስቃሴ የማታስጀምር ከሆነ ግን በማስረጃ ላስደግፈው ይላነኖል።»

«ምን ዓይነት እንቅስቃሴ እንዲጀመር ትፈልጊያለሽ?»

ሩል ከዚህም በላይ ያውቃል። ሳይመን ሩል የተልዕኮዎች የበላይ ሃላፊ በሆኑት በዚህ ርዕስ ላይ ይህን መሰል ምክሯን ስታቀርብ ቢሰማ አይገርመውም። «ይህን ለመወሰን ከኔ ይልቅ ብቃቱ ያላቸው ሰዎች ድርጅቱ ውስጥ ይገኛሉ፣» አለች። «ይህን ጉዳይ በሚመለከቱት ወቅት፣ የሚፈልጉትን ዓይነት መረጃ ራሳቸው ያውቁታል፣ ለተገቢው መረብ ተልዕኮውን ያከፋፍሉታል። ሀሳቤን እንዳቀርብ አብሬህ እንድሄድ ትፈልጋለህ? ቢያምናት ኖሮ ከሷ የተሻለ ማድረግ እንደሚያቅተው ታውቃለች። ግን ያመናት መስሏታል።

«አይሆንም፣ እኔ ራሴ ባደርገው የሚሻል ይመስለኛል፣ ቢያንስ ለአሁኑ።» አለና፣ ፎቶግራፎቹንና ዶሴዎቿን አንድ ላይ ሰብስቦ ተነስቶ ቆመ። «አሁን አንድ ሰው ላንጋገር ነው፣ ስለዚህ ከኔ መልዕክት እስኪደርስሽ ድረስ ቢሮሽ ቆዪ። ስለዚህ ጉዳይ ከአንቺ ሌላ የሚያውቅ አለ?»

«ትንተብጣቢዎቼን ብቻ። ሁሉንም የሰጠሁት ለአንተ ብቻ ነው።»

«ጥሩ። ስለእግዚአብሔር ብለሽ፣ ስለዚህ ሁኔታ ለማንም ቃል እንዳትናገሪ።» ብሎ ኒክሰን ዶሴዋን ይዞ አቆመችበት ትቷት ከቢሮው ወጥቶ ሄደ።

ሩል በተደጋጋሚ በረጅሙ አየር አየሳበች አስወጣች። ተሳክቶላታል። አለን ኒክሰንን አግኝታዋለች፣ አሁን ከሷ እሱ እግር ላይ ገብታለች። ቀስ እያለች ወደ ቢሮዋ ተመለሰች። እሱ ጡረታ ሲወጣ የሱን ቦታ መተካት ትፈልጋለች፣ ይህ ተልዕኮ ደግሞ ይህን ለማግኘት ይረዳታል። ይህ እንክን የሌለው፣ ትልቅ ስራ መሆኑ ታውቋታል፣ አንደ ሰው ያውም እድለኛ ከሆነ በሥራ ዘመኑ ሊያገኘው የሚችለው ብቸኛ እድል። እሷ እድሏ ተቃንቶላታል።

http://ethzare.wordpress.com

ሔልደር ማስደገፊያና ወረቀቱን በእጁ እንደያዘ ዳግመኛ በቀላሏ ሰርጓጅ መርከብ ዙሪያ ተንሳራደደ። ቀና ሲል ማጆሮቭ በግዙፉ የሰርጓጅ መርከብ መጠለያ ውስጥ ወደእለበት ሊመጣ ተመለከተው። ማጆሮቭ ይህን አይወደውም። እቅድ ለማውጣት የተፈጠረ ሰው ነው፣ እቅድህ ስህተት ነው መባልን አይወድደውም።

«ደህና እደራችሁ፣ ሔልደር፣» አለ ማጆሮቭ። «ሶኮሎፍ።»

«ደህና እደርክ ጌታዬ፣» አሉ ሔልደርና ሶኮሎፍ በእንድ ድምጽ።

«ምንድን ነው ችግሩ?» ጠየቀ ኮሎኔሉ።

«ችግር እንደማይኖር ተስፉ አለኝ፣ ጊታዬ፣ «መለሰ ሔልደር። «የመንሳፈፊያ ክብደቷ ከዋና ክብደቷ ያንሳል የሚል ግምት ነበረኝ።» እንደእውነቱ፣ ሀምሳ ኪሎ ወይም ከዚያ በላይ ይመዝናል። እዝናለሁ፣ መናገር ነበረብኝ። ይህ ችግር ያመጣል?»

«ያን ያህል ችግር የለውም ኮሎኔል፣» አለች ሶኮሎቭ ጣልቃ ገብታ።

ሔልደር ሴትየዋ ላይ እንባረቀባት። «ሶኮሎፍ፣ በተጠንቀቅ ቁሚ!»

ግለሪ ሶኮሎቭ በተቻላት ቀሰስተኝነት እያለገመች የተባለችውን አቋም ያዘች። ያንቺን አስተያየት በምፈልግበት ጊዜ እጠይቅሻለሁ፣» አለ ሔልደር። ፊቱን ወደ ማጆሮቭ በማዞር፣ «ጌታዬ፣ ስለረዳቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ትክክለኛ የመንሳፈፊያ ክብደቷ ርግጠኛ ነህ? ከጠጣር ኮንክሪት በላይ ክብደት ያለው ምንድን ነው?»

«ዩራኒየም 235፣» መለሰ ማጆሮቭ።

«ምን?» አለ ሔልደር፣ አግራሞቱን መሸሸግ ተስኖት።

«አትጨነቅ ሔልደር፣» አለ ማጆሮቭ። «የወጣለት ዩራኒየም ነው። ከብረት እርሳስ ይከብዳል፣ የተንሳፋፊው ነዳፊዎች የመርከቧን ሚዛ ለመጠበቅ በጣም ከባድ መሠረት ይፈልጋሉ። ውጤት እንዲኖረው ከተፈለገ ተንሳፋፊው ቀጥ ብሎ መቆም ይኖርበታል። ክብደቱ ሰርጓጅ መርከቧ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ ያደርሳል?»

«ጌታዬ፣ ከዚህ ክብደት አንፃር፣ ሰርጓጁ እንደፈለገች ለመንቀሳቀስ ያዳግታል። ሌላ ሃምሳ ኪሎ ከተጨመረ፣ ተገቢ የሆነ የእንቅስቃሴ ነፃነትን ለማምጣት የመጥለቂያ ዝርነቹን የአቅጣጫ ማስተካከያውን /ራዳር/ ክብደት መጨመር አለብን። ሶኮሎፍ በዚህ ሀሳቤ አትስማማም፣» በመቀጠል «ሶኮሎፍ፣ ሀሳብሽን አሳውቂ።»

«በጭራሽ አልስማማም ኮሎኔል፣» አለች ሶኮሎፍ፣ በተጠንቀቅ እንደቆመች። ዝሙን ጭነን ሶስት ቀን ለሙከራ በቆየሁባቸው ጊዜያት ሰርጓጁ ከመቆጣጠሪያዎቹ የሚደርሳትን ትዕዛዞች በበቂ ሁኔታ ታከናውናለች።»

«ሔልደር?» ጠየቀ ማጆሮቭ ፊቱን ወደሱ እያዞረ።

«አዎን ጌታዬ፣ ሰላጤው ውስጥ ካሉት ሁኔታዎች አንፃር ሰርጓጁ በቂ ምላሾችን ትሰጣለች፣ ደሩ ግን ለዚህ ተልዕኮ በፍልሚያ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ እንደሚኖርብኝ ተገንዝቤያለሁ።»

«ያልከው ትክክል ነው፣» አለ ማጆሮቭ።

«ስለዚህ በጠላት እየተሳደድን ወይንም ጥልቀት ውስጥ ጥቃት እየተሰነዘረብን እያለን የሚለውን ከግምት ማስገባት እንዳለብኝ አሰብኩ። በአሁኑ ሁኔታ ለፍልሚያ የሚሆን ቀልጣፋ እንቅስቃሴ የማድረግ ብቃት የላትም። ሌላ ሀምሳ ኪሎ ከተጨመረ ደግሞ ብቃቷ ከዚያም በታች ይወርዳል። እንደእጋጣሚ እንተ የሰጠሽኝ የእንቅስቃሴ ገደብን የሚወስኑ ቁጥሮች የተሰሉት ለትክክለኛ ክብደቱ መሆኑ የተነሰተልኝ መሰለኝ?»

ማጆሮቭ በሀሳቡ ተስማማ። «የተሰሉት በተልዕኮው ስልሳ በመቶ የተንሳፋፊውን ክብደት ለመሸከም እንደምትችል ተደርጎ ነው። በመልስ ጉዞው ላይ ይህ ክብደት አይኖርብህም።»

«ጌታዬ፣ አሁንም መቃወም ይኖርብኛል፣» አለች ሶኮሎቭ። «አሁን ሰርጓጅ መርከቧ አሁን እንኳን ብቃቷ ቀንሷል፣ ተጨማሪ ሀምሳ ኪሎ ብዙ ለውጥ የሚያመጣ መስሎ አይታየኝም።»

«ይህን ማየት ያልቻልሽበት ምክንያት፣» አለ ሔልደር እያቋረጣት፣ «እንቺ መቆጣጠሪያዎቹ እካባቢ ስላልነበርሽና፣ ሀሳብሽን የሚደግፍ ምንም አይነት የሰርጓጅ መርከብ ልምድ ስለሌለሽ ነው።»

«ሔልደር፣» አለ ማጆሮቭ። «ለሰርጓጇ አስፈላጊ ናቸው የምትላቸውን ማስተካከያዎች እንዲደረግ መመሪያ ስጥ፣ ሰራው የሚወስደውን ጊዜ በትንሹ አስልተህ አሳውቀኝ።»

«ጌታዬ፣» አለች ሶኮሎፍ አሁንም ጣልቃ ገብታ፣ የመጥለቂያ ዝርግ ብረቶቹንና የአቅጣጫ መቀየሪያውን ክብደት ለመጨመር፣ ሶስት ቀናት ይፈጅል።

«ስህተት፣ ሶኮሎቭ፣» አለ ሔልደር፣ «ሥራው አስኪያበቃ እንቅልፍ ስለማትተኚ፣ የሚፈጀው አንድ ቀን ተኩል ይሆናል፣ ስለዚህ አሁኑኑ ሰራ ጀምሪ።»

«እሺ ጌታዬ፣» አለች ሶኮሎቭ ጥርሷን ነክሳ፣ ከዚያም ተሽከርካራ እየተራመደች የተቀሩትን የጀልባዋን ሰራተኞች ጠራች።

«ኮሎኔል ማጆሮቭ፣» አለ ሔልደር በስስቸ መንፈስ። «ሶኮሎፍን በሌላ ሰው እንድትተካልኝ ልጠይቅህ እገደዳለሁ። የሰርጓጅ መርከብ ልምድ የሌላት ከመሆኗም በላይ ብዙውን ጊዜ ትዕዛዝ አታከብርም። በግለለጥነው የጦር ሰርጓጅ መርከብ ቡድን ውስጥ ብትሆን ኖሮ እስካሁን የቶርፒዶ አፈሙዝ ላይ ጠምጇ በተኮሰኳት ነበር።»

ማጆሮቭ ሳቀና የሔልደርን ጀርባ ቸብ ቸብ አደረገው። «አውቃለሁ ሔልደር፣ ይህ ይመጣል ብዬ ጠብቄያለሁ፣ በጥሩ ሁኔታ እየያዝካት መሆኑን ልነግርህ እገደዳለሁ። ዳሩ ግን ይህን ተልዕኮ ስናዘጋጅ ከግምት ያስገባናቸው ሌሎች ሁኔታዎች አሉ። ግለሪ ሶኮሎቭ አሉምኒክ ላይ ከተቀጻጀችው ድል የተነሳ ብሔራዊ ጀግና ናት። የስፖርት ጀግኖች በሀገራዊ ህይወታችን ላይ ምን ዓይነት ሚና እንደሚጫወቱ የምታውቅ ይመስለኛል፣ ይህ ተልዕኮ በሚጠናቀቅ ጊዜ ሀገራዊ ዝና ያላቸው ግለሰቦች የተልዕኮው እንድ አካል ሆነው መታየታቸው አስፈላጊ ነው። ይህም ሆኖ፣ ተልዕኮው ከተጠናቀቀ በኋላ ግን በየትኛውም አይነት ሌላ ተልዕኮ ላይ ዳግመኛ እንደማታገኛት ቃል ልገባልህ እችላለሁ። ፋብሪካዎችን፣ ትምህርት ቤቶችን እየጎበኘች የሰራተኞችንና የተማሪዎችን መንፈስ በመቀስቀስ ሥራ ትወጠራለች። እመነኝ፣ ዝነኛ ብትሆንም ቅሉ፣

http://ethzare.wordpress.com

ለስራው ሙሉ ቂታት ባይኖራት ናሮ ለልንተ ባልመደብኳት ክበር ለሰርጓጅ መርከቶች የሚሆን ልምድ የሌላት መሆኗን እውቃለሁ፣ ግን ሚናዋ ቴክኒካዊ ነው፣ ከዚህም ሌላ አስቸጋሪ ግዜ ካሳቸው ባህርተኞች ጋር ልምድ ያለው እንደእንተ አይነት ኮማንደር ለእንዲት ሲት እንደግያንስ እውቃለሁ።» ሔልደር ዳግመኛ ትክሹው ላይ ቾብ አደረገው። «ማስተካከያውንና ስልጣናውን አጠ ንክረህ ንፋብት። እሁንም ኾና ጊዜ አለህ፣ ሰዓቱ ሲደርስ ዝግጁ ትሆናለህ።» ሌላ ውይይት መጀመር ስላልፈለገ ቶሱ ወደ በሩ ተራመደ።

ሔልደር እንድ ሰሜት ደረቱን ቀስር እንደያዘው ወደሰርጓጅ መርከቡ ፊቱን አዞረ። ስልቫስሪ ሶሉ-ቭ የክረውን እጅግ ወሳኝ አስተያየት ለመግለጽ ጊዜ አልሰጠውም። በሰርጓጅ መርከቧ ውስጥ ሆነው ከውሀ በታች ሶኮሱፍ ፈርታ ክበር፣ ስልጠናው እየቀጠለ ሲሄድም ከዚህ ፍርሀቷ የተላቀቀች እትመስልም። ሔልደር የሷ ፍርሀት አስፈርቶታል።

•

15

ሩል በማቶቿ የመስኩቱን ክፍከሉት እየቆረቆረች ሳትፈልገው ወደለልኩ ትመለከታለች። ከእንድ ሰዓት በላይ አልፏል። ኒክሰን ሳይኖው ፎቅ እንድ ክፍል ውስጥ ስብሰባ ላይ መሆኑን ታውቃለች፣ ምክንያቱም ሁለት ጊዜ ፀሐፊው ወንድ ደውላ ቢሮው ያለመኖሩ ተነግሯታል። ጊዜው የሚያበረታታ ነው። አለፀች ወሳኟን ለኒክሰን ያቀረበችው በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነበር። የበለጠ በተነጋገሩበት መጠን ለመላምቷ ያላቸው እምነት ይጨምራል። ለዊል ሊ በደወለች ጊዜ ሰዓቱ ወደሁለት ሰዓት እየተጠጋ ነበር።

«ሀሎ።»

«ሀሎ!»

ስም መጠያየቅ አላስፈሊጋቸውም በድምጽ ጠንቅቀው ይተዋወቃሉ።

«ስማ፣» አለችው፣ ስሚቷን ለማለዘብ እየጣረች። «ዛሬ እራት እጋብዝሀለሁ-አንተ የፈለግህበት ቦታ።»

«እንዳልሽ ይሁን። ፓሪው ውስጥ ሳሲር ሬስቶራት፣ ሁለት ተኩል ላይ ይሁን?» ሳቀች። «አንተ ሁለት ተኩል ላይ እዚያ አድርሰንና እገላለሁ።»

«እሠ። እንደዚያ ከሆነማ አፍ ጎዳና ላይ ያለው ማይለን ብላች እናድርገውና ሁለት ሰዓት ላይ መጥቼ እወስድሻለሁ።»

«ያዱቢ ካርድ እንደሚቀበሉ ተሰፉ አለኝ፣ ደመወዝ እስከ አስራአምስት ቀን ይቆያል።»

«የዱቢ ካርድ የማይቀበል ቦታ ወስጀሽ መጠቀሚያ አደርግሻለሁ? ብቻ ግን፣ አይሆንም ካሉ፣ እስከደመወዝ ድረስ የግል ቼክሽን ይዘው እንዲቆዩ አደርጋቸዋለሁ።»

«ሁልጊዜ ቅንጦት ትወዳለህ።»

«እውቀሽኛል። የምናከብረው ምንድነው?»

«ግታ እነግርሀለሁ። በነገራችን ላይ የተሳካ ነገር ነው።»

«ከስው መደራደር ታውቂበታለሽ እየደለም?»

«ሁለት ሰዓት። ጠረጴዛውን ቀድመህ ያዘው።» ስልኩን ዘጋችው፣ ቦር አለችና በድንጋጤ ዘለለች። አለን ኒክሰን ቢሮዋ በር ላይ ቆሟል።

«አለን፣ ቀልቤን ገፈፍከው።»

ኒክሰን ምንም አልተናገረም፣ ዐይን ዐይና ተተመጠ። ጸጪዋን ወረዶላዋ ላይ ወረወረው። ኹታው ምንም ሰሜት ሳይታይበትም፣ ፊቱ ግን ትንሽ ተልቷል።

ዝም ሲላት እሷ መናገር ጀመረች። «ረታሀኛው፣» አለች።

«አልሆነልኝም፣» አለ ኒክሰን የአፍንጫውን ወርዝ እያሻሸ። «ከጪዋታው ውጪ ተደረግኩ። ኮሚሳ ተባረርኩ። ከሶርቱ ታገድኩ። ተመልካቹ በወንበር ስላልደገፉኝ እድለኛ ነኝ።»

ሩል ለምቦጫን ጣለችው። «ሳይመን አፋመልበትም?»

«ሳይመን ምንም ቃል አልተነፈሰም። ሁሉን ነገር የተናገረው ዋና የላፊው ነው።»

«ዋና የላፊው፣ በክርስቶስ! አለን ኛ በዚህ ደረጃ እያለ መቼም ወደዋና የላፊው አልሄድከም።»

«አልሄድኩም፣ የሄድኩት ወደላይመን ነው። እያዋራሁሀቱት ሁለት ደቂቃ እንደፈጀሁ፣ ጳይሬክተሩ ከፍሉ ገቱ። ሰላም ብሉ ሶሚይድ ያሀል ክበር ሳይመን፣ የሶቭየት ቢሮ ምን ዓይነት ምርመራ እንደሚያደርግ ቅንጭ እንዲገለጥለት በሚል ከመጀመሪያ እንድጀምር አደረገኝ።

«ይሄ ዲቃላ፣» አለች ሩል፣ ፊቷን እጀጅ ውስጥ እያስገባች። «ጳይሬክተሩስ ሙያዊ ብቃት የለውም።»

«ያስቃል፣» አለ ኒክሰን፣ «ጳይሬክተሩም እኔን እንደዚሁ ክበር የተናገረኝ። ድምፁ እየጨመረ ሲመጣ፣ ንዲቱ ታወቃት። «ቀጥሬን ሲጥሬው ሳይመን ሩል እየተመለከተ ክበር፣ አለ ኒክሰን። «ይህን አልመደድክትም?»

«አዝናለሁ አለን፣ ለኔ ስትል እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ይመግባትህ አዝናለሁ።»

«እኔም አዝናለሁ፣» አለ እየተነሳ፣ «ሙሚኝ፣ ይህን ደንሚ አላደርገውም።» አለ፣ ጠረጴዛዋ ላይ ያለውን ዶሲ እየደበደበ። «ይህን ሚይው ኪት። በዚህ ላይ መስራትሽን ተይና ወደተሰመደ ስራሽ ተመለሺ። ስለ ግሎርቫ አንድ መረጃ ከተገኘ፣ ፋይሉ ላይ ጪምረው፣ እኔ ግን ልስግው አልፈልግም።»

«ተመልከት አለን፣» አለች ተስፉ ባጣ መፍጨርጨር፣ «አንድ ሌላ ነገርም አለ በማላከሆሽ ቃለ መጠይቆች በአንዱም ላይ የማጅርቫ አልተጠቀሰም። ማንም ስለእሱ በዚያን ሰዓት የመየቀ ያለ አይመስኝም፣ በዚህም ይህን የሚያስደርግ ምክንያት እንዳልነበር እምታለሁ፣ ማላከሆሽም በዘጎ ፈቃደኝነት ያደረገው ምንም ነገር የለም። ይህንን ከቃለ መጠይቁ ፀድን መሪ ማገኘት አንችልም? ይህንን ብቻ ማድረግ እንችልም?»

«ስሚ ኪት፣» ኒክሰን ቁጣ አለ። «ይህ ድርጅት ከሌድ ፊውልስ የበለጠ የቃለ መጠይቅ ባለሞያ ኖሮት አያውቅም፣ የእሱ ሬፖርቶች ላይ ከሌለ፣ ማላከሆሽ እንጎል ውስጥም አይኖርም።»

ታጂያ የቡድን መሪው ለካ ሌድ ፊውልስ ነው ብላ አሰበች። የመጪረሻ ሬፖርቶቹን እያዘጋጀ ላይሆን አይቀርም እዚህ የገባረው።

ኒክሰን ወደበሩ አመራ። «ይህንን እንደማትተይ አውቃለሁ፣» ብለ በንዲት። «ቦልሺቪክነት ስለሚያጠቃኝ ቀጥተኛ ትዕዛዝን የምትተይይ አይደለሽም። ይህን ልንገርሽ፣ ኪት ከክሬ በፊት ወይ በኋላ አሊያም በስራ ላይ

http://ethzare.wordpress.com

ሆነሽ ለዚህ ጉዳይ እንድ ደቂቃ እንኳን እጠፋች የሚል ወሬ ብሰማ፣ ይህን ህልምሽን ለማጠንከር በሚል የወጪ ጥያቄ ማቅረብሽን ሰው ቢነግረኝ ቢሮውን መውሰድ ብቻ ሳይሆን፣ ከህላፊነት ቦታሽ ላይ እነሳሻለሁ፣ ሰማሽኝ? በፐርሶኔል ክፍል ከምልምሎች ጋር እንድትሰሪ ነው የማደርግሽ! ገባሽ?»

ሩል ገባኝ ሰማለት ራሷን ወዘወዘች።

ኒክሰን በሩን ከፍቶ ወጣና መልሶ ዘጋው።

ሩል እጎንብሳ ራሷን ክንዶጀ መሀል አስገባችው። እንድ ነገር ብልጭ ብሉላት በችኮላ ገብታበታለች። ስሜቷ ሚዛናዊነቷን እንዲያሽንፍ ፈቅዳለታለች፣ ከአለቃዋ ጋር የገነባችውን የብዙ ዓመታት መልካም ግንኙነት ንዳዋለች፣ ስሟ የፖለቲካ ተገዢ የሆነው ዳይሬክተር ዘንድ ደርሷል፣ ስለዚህ የአምላክ ያለህ ጭለማ ውስጥ ተዘፍቃለች። ይህ ወደግል ማህደሯ ይገባል፣ ለብዙ ዓመታት እየተነሳ ይተገትጋታል። ከሁሉ የከፋው ደሞ፣ ሳይመን ይህን እንደዘንግ ተጠቅሞ እሷን ከድርጅቱ የሚያስወጣበትን ዕድል ይሰጠዋል። ብዙ ችግር ላይ መውደቋ ታወቃት።

ኒክሰን ግን አልተሳሳተም፣ እትተወውም። ትልቅ ቦታ አለው ብላ አሰባለች። መጠንቀቅ ይኖርባታል እንጂ እትተወውም። ስልኩን እነሳች።

«ስሚዝ።»

«ማርቲን? ኬት ሩል ነኝ።»

ትንሽ ጠበቃት። «አቤት ኬት?»

«ስማኝ፣ የሳይፓጃን ቦታ የሚያሳዩ ተጨማሪ የሳተላይት ፎቶግራፎች ትገለብጥልኛለህ?»

ዝምታው ዘገየ። «ስሚ፣ ሩል፣ ይቅርታ፣ ግን አሁን በእንቺ ላይ የእገዳ ትዕዛዝ ደርሶኛል።»

«ምን?»

«እም፣ ከሰላሳ ሰከንዶች ካልበለጠ ጊዜ በፊት።»

ማመን ተሳናት። «ምን ያህል ስፋት ያለው?»

«ስካንዲኔቪያንና የባልቲክን ሰርጥ የሚያጠቃልል።»

«በደረጃ ሰንት?»

«አንድ።»

ተራገመች። ምናልባት ዳይሬክተሩ ራሱ ይሆናል ያሳገዳት። «በምን ስልጣን?»

«ሰንፍላወር።»

«ሰንፍላወር?»

«እዚህ የተፃፈው የሚለው ነው።»

ረጅም ዝምታ ተተካ። «አላውቅም፣ ሩል

ሩል እንደመንፈራገጥ አደረጋት። በድርጅቱ ውስጥ፣ ረጅም ዝምታ ተከትሎ «አላውቅም፣» ማለት፣ «እኔን ከምትጠይቂኝ ይልቅ አሳምረሽ ታውቂዋለሽ።» ማለት ነበር።

«ይቅርታ ማርቲን፣ አመሰግናለሁ።»

«እንድታስተካክይው እመኛለሁ፣ ኬት። ብረዳሽ ደስ ባለኝ።»

«አውቃለሁ።» ሁለቱም ስልኩን ዘጉት።

በእንድ ቢሮ የበላይ ሀላፊ ላይ የእገዳ ትዕዛዝ? ተሰምቶ አይታወቅም። ይህ ከባድ ችግር ነው። ከምስል ምርመራ እንዳያልፍ ተመኘች። የዳይሬክተሩ ንዲት እገዳውን ጠቅላላ እገዳ ላይ አድርሶት ከሆነ፣ እስከቀጣዩ ተሰዓት ድረስ አላስፈላጊ ተውሳክ ተደርጋ መታየት ትጀምራለች። ዶሴውን እሻንጣዋ አስገብታ፣ ለመውጣት ተጣደፈች።

በጭንቀት ነፍሳ በዝግታ ወደቢቷ መኪናዋን እያሽከረከረች ሔደች። ቤቷ እንደደረሰች እንደምንም ወደመኝታ ክፍሏ አመራችና አልጋዋ ላይ ተወረወረች። ጥቂት ቆይታ ነቃች። ድምጽ ሰምታ ነው። የበሩ ደወል ነው? በከፊሉ ጭለማ እየተደናበረች ወደታችኛው ክፍል አመራች። ደወሉ አሁንም እንቃጨለ። ደርሳ በሩን ከፈተች። ዊል ሲ የእራት ልብሱን ለብሶ ቆሟል።

ሔልደር በሬዲዮ ኮምፓሱ ላይ ያለውን እቅጣጫ ጠቋሚ መርፌ ከተመለከተ በኋላ የጉዞ መስመሩን በሁለት ዲግሪ ለማስተካከል ራዳሩን /መሪውን/ ወደቀኝ መለስ አደረገው። ሰርጓጅ መርከቧ ወዲያውኑ መስመር ያዘች። ክብደት የተጨመረለት ራዳር ስራን እየሰራ ነው። የመጥለቂያ ዝርግ ብረቶቹ ግን አላረኩትም። ዳግመኛ መስተካከል ይኖርባቸዋል።

ያለብርሀን እገዛ፣ በማስመሰል የተቀናበሩ የፍልሚያ ሁኔታዎች ውስጥ መጀመሪያው ምሽት ልምምድ እየተደረገ ነው። መርከቧ የምትገኝበትን ስፍራ የሚገልፁ ቁጥሮችና (Coordinates) በመጨረሻ መድረሻው ላይ የጠላትን አትኩሮት ላለመሳብ ተብሎ ዝቅ ባለ ድምጽ ከሚንጣጣው የሬድዮ ግንኙነት ምልክት፣ እንዲሁም በዋናው ሰርጓጅ መርከብ ውስጥ ካለችው ኑጥብ የምታህል ቀይ መብራት በስተቀር ሌሎች መቆጣጠሪያዎቹ ሁሉ ዝግ ናቸው። ኮምፓሱን እየተመለከተ ያጸምጣል። ሌላ ድምፅ እንደሰማ በትንሹ አስተካከለው። ከዚያ፣ ጥቅጥቅ ካለው ጭለማ ውስጥ በተከፈቱት በሮች በኩል ብቻ ለመታየት ከሚችል የመርከቧ የኋላ ክፍል ቀይ መብራቷ ብልጭ አለች። ከመዓከሉ በእምስት ዲግሪ ርቀት ላይ በጭለማ ወደ እናት ሰርጓጇ ከቀረበ በሯን ስቶ ከግድግዳዋ ጋር ተጋጭቶ ከባድ ድምጽን ሊፈጥር ወይም ዋናዋን /እናት/ ሰርጓጇን ሙሉ ለሙሉ ለድት ሊያልፍ ይችላል።

ሀይሏን ቀነሰና ትንሿ ሰርጓጅ ዋናዋ ሰርጓጅ ወለል ላይ እንድታርፍ ካደረገ በኋላ የሀዲድ መንሸራተቻ ጎማዋን አውርዶ በሀዲዱ ሽቅብ ወጣ። ገብቶ በሩ ከተዘጋ በኋላ እናት ሰርጓጇ ተነስታ ስትንቀሳቀስ ተሰማው። ከበስተኋላው ሶኮሌፍ ቁና ቁና ስትተነፍስ ሰማና ደስ አለው። በውሀ እንደተከበቡ፣ እናት ሰርጓጇ ከቀጠሮ ቦታቸው እስክትንቀሳቀስ እየጠበቁ በዚያ ጭለማ ለተጨማሪ አራትና አምስት ደቂቃ ተቀምጠው ቆዩ። ከዚያ ግን ድንገት የታመቀ አየር ትስ እያለ ድምጽ ካሰማ በኋላ የከፍላቸው መብራት በርቶ አጥለቀለቃቸው። ሔልደር በኋላ መስታወቱ ሶኮሌፍን ሲመለከታ ፊቷ በላብ ተጠምቋል። አሁንም ፖለቲካ ቦታ ባይኖረውና በሌላ ሊተካት ቢችል ተመኘ። ፖለቲካ ግን በፓርቲ ውስጥ ቦታ እንዳለው ሁሉ በሠራዊቱ ውስጥም ቦታ ይኖረዋል።

በዋናው ሰርጓጅ ውስጥ ያለው የውሀ ጠለል እየወረደ ሲሄድ፣ ሔልደር በመስታወት መስኮቱ በኩል ማጆሮቭ ሁለት እውራ ጣቱን በድል አድራጊነቱ መኩራቱን ሊነግረው አሳየው። ከበላዩ ያለውን መክፈቻ ለማዞር ወደላይ እጁን ዘረጋ።

http://ethzare.wordpress.com

«አይሆንም!» አለች ሶኮሎፍ በሰላ አንደበት:: «ክፍሉ ውስጥ ገና ውሀ አለ::» ዞር ብሎ ተመለከታት:: «መመሪያ አትሰጪኝ ሶኮሎፍ::»

«እኔን የሚመለከት መመሪያ ነው፣ ካፒቴን፣» አለችው::

«በማንኛውም አይነት ሁኔታ መመሪያ እንዳትሰጪኝ፣» ብሎ ጠበቅ አድርጎ ነገራትና እሺታዋን በምልክት አስክታሳየው ድረስ ትክ ብሎ ተመለከታት:: የግፊት ማመቂያ መዘውሩን እሽክረክረውና፣ መዝጊያውን ከፍቶ ተነስቶ ቆመ:: አሁንም ገና ክፍሉ ውስጥ የሶስት ጫማ ከፍታ ያለው ውሀ አለ፣ ግን ሰውነቱን ለማፍታታት ፈልጓል:: አዲስ መቀመጫ እንዲዘጋጅለት ቢያደርግም፣ ቦታው ግን አሁንም አይመችም:: በተከፈተው በር በኩል ወጣና ውሃው እስኪደርቅ ድረስ ከሰርጓጅ መርከቧ በላይ ተቀመጠ:: የግፊት ማመቂያ መዘውሩ ሲሽከረከር ከተመለከተ በኋላ ማጆሮቭ ወደውስጥ ገባ::

«እንደኛ ነህ ሔልደር፣» አለ ብሩህ ፈገግታውን እየመገበው:: «የጠላ መንፈሳችሁን አብርዱና ወደመልበሻ ክፍሉ እንድትመጡ የምነግራችሁ ነገር አለኝ::» ብሎ በሩን ክፍቱን እንደተወው ወደዋናዋ ሰርጓጅ መርከብ ተመለሰ::

ሔልደር ሶኮሎፍን አስክትሎ፣ በትንሿ ሰርጓጅ አካል ላይ ተንሸራተተና በሩን አልፎ ውሀ ካረጠበው የእናት ሰርጓጇ ወለል ክፍል ወጣ:: ሌሎች ሁለት የጥገና ሰዎች እነሱን ተክተው ገቡና:: ወዲያውኑ የትንሿን ሰርጓጅ ባትሪዎች መሙላት ጀመሩ የጁሊየት ደረጃ ያላት ሰርጓጅ መርከብ የፊት ለፊት የቶርፒዶ /የውሀ ውስጥ ተወንጫፊ ሚሳኤል/ ክፍል በዚህ የትንሽ ሰርጓጅ ማስገቢያና ማስወጫ ክፍል ተተክቷል:: ሔልደር በመርከቧ ውስጥ እየተራመደ እያለ፣ እንደተለመደው ክፍሉ ያለቶርፒዶ እንቀሳቃሽ ቡድኑና ያለ ቶርፒዶዎቹ ባዶነቱ ታሰበው:: ሰርጓጅ መርከቧ የያዘችው እነስተኛ ሰርጓጅ መርከብን ለማስወንጨፍና ለማሳረፍ ብቻ የሚበቃ ቁጥር ያላቸውን ሰራተኞች በመሆኑ በንፅፅር ሲታይ የሚኖሩት በተንጣለለ ሰፊ ቦታ ላይ ነው:: ካፒቴይኑ የራሱ የሆነ መኝታ ክፍል አለው፣ ሔልደር የዊስኪ ደረጃ ሰርጓጅ መርከብ እዛኛው በነበረበት ጊዜ ይይዘው ከነበረ ጠባብ ክፍል ጋር ሲነፃፀር የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት አለው፣ መልበሻ ክፍሉም ከቀድሞው ይልቅ ይሰፋል:: ሔልደርና የሰርጓጅ መርከቧ ዋና አዛዥ ጠረጴዛው አጠገብ ይጠብቋቸዋል፣ የባህር ላይ መስመሮችን የሚያሳይ ትልቅ ካርታ ተዘርግቷል:: የወጥ ቤት ሰራተኛው በኩባያዎች ሾርባ ከሰጣቸው በኋላ ቡድኑ ብቻውን ቀረ::

«እስካሁን ድረስ፣» አለ ማጆሮቭ፣ «ስትሰለጥኑ የቆያችሁት ለምን እንደሆነ አታውቁም:: አሁን ግን የተልዕኮአችሁን ዝርዝር ሁኔታ የምታውቁበት ጊዜ ነው:: ተልዕኮአችሁ ውስብስብነት እንደሌለው ስነግራችሁ በደስታ ነው:: «በቅርበት የሚገኘን የአንድ የባህር ዳርቻ መዝናኛ ጠርዝ ከካርታው ላይ በጣቱ ጠቆመና ጣቱን ወደባህር ዳርቻው ማንሸራተት ጀመረ::

ቻርቱ የስዊድን የባህር ዳርቻ ላይ የሚገኘው የስቶኮልም አርቺፔጋሉን የሚያሳይ መሆኑ ለሔልደር አላስገረመውም::

«ከሔልሲንኪ የምትመጣውን የቫይኪንግ መርከብ ድምጽ ከእናንተ ሞተር ድምጽ ጋር ለማቀላቀል እሷን እየተከተላችሁ ወደስቶኮልም መቃረቢያ ትገባላችሁ::» ማጆሮቭ የመርከቧን የጉዞ መስመር በጣቱ እየተከተለ የስቶኮልምን መንገድ ሁለት ሶስተኛ ያህል ከሸፈነ በኋላ ቆመ:: «እናት ሰርጓጅ መርከቧ እዚህ ትራህላቬት የተሰኘ ሰርጥ ላይ የመረከቧን የጉዞ መርከብ በመተው ትገኝጠላለች::

«እለና፣ ስድስት የሚሆኑ ደሴቶች ወደከበቡት የውሀ ክልል እመለከታቸው:: «የመድረሻ ጊዜያችሁ ዜሮ ሶስት መቶ ሰዓት ገደማ ይሆናል፣ ግን በዚህ የዓመቱ ወቅት ብዙም ጭለማ ስለማይኖር የቀኑ ሰዓት እንብዛም ለውጥ አያመጣም:: እዚያ ሰርጥ ውስጥ እናት ሰርጓጅ መርከቧ የባሀሩ ወለል ላይ ታርፍና ደረጃ አራት እንቅስቃሴ ውስጥ ትገባለች::»

ልክ ማጆሮቭ ተጣዩን ፀረፍተ ነገር መናገር ሲጀምር፣ ሔልደር እያደረገ ያለው በጎና ትልቅ ቦታ ያለው መሆኑ ድንገት ተገለጠለት:: ከብዙ ዓመት ስልጠናና ልምምዱ በኋላ አሁን ወደተግባር መሸጋገሩ ነው:: እያንዳንዷን የማጆሮቭን ቃላት መከታተል ጀመረ::

«አሁን፣ ሔልደር፣ የአርቺፔላጎን ደሴቶች ተከትለው የተቀመጡትን ምልክቶች እየተከተልክ የደቡብ ምዕራብ አቅጣጫን ይዘህ የሻክሰንን ከተማ ታልፍና፣ በደቡብ በኩል በእንድ ሰፊ የውሀ ቦዲ አልፈህ ወደገሳጣ ውሀ ትወጣለህ:: በዚያ ሰዓት ሌሎች ብዙ መርከቦች ስለማይኖሩ ቀላል ነገር ይሆንልሀል፣ ወደባህር ጠለሉ ቀርበህ ለመጓዝም ያስችልሀል፣ ቀጣዩን ምልክት ለማግኘት የከውሀ በላይ የርቀት ማሳያህን /ፔሪስኮፕ አዘውትረህ ተጠቀም:: ዳሩ ግን ያለማቋረጥ እንዳትጠቀምበት አበክሬ ሳሳስበኝህብህ ምክንያቱ ግልጽ መሆኑን እያሰብኩ ነው::» ፈገግ አለ:: «ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ስዊድናች ፔሪስኮፕን በአይነ-ቁራኛ እንዲከታተሉ አስተምረናቸዋል::»

ካናሉን /ቦዩን/ ከውሀ በታች ሆኖ ማለፍ ብዙ ችግር እንደሌለው ተስማማ::

ማጆሮቭ ቀጠለ:: «እዚህ ቦታ ከደረስክ በኋላ ዳግመኛ የደቡብ ምዕራብ አቅጣጫን ትይዝና ዋናውን ካናል ሳትለቅ የብራቭኪን ከተማ ከጀልባህ በስተቀኝ አልፈህ እዚህ ነጥብ ላይ ትደርሳለህ:: ቦታው ላይላ ቫርታን የተባለ የውሀ ክልል ነው:: እዚህ ላይ ጓዝህን ታራግፋለህ::»

ሔልደር ትንሽ እንደማንዘፍዘፍ አለው:: የማጆሮቭ ጣት ከስቶኮልም እምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ አረፈ::

«ከዚያ፣» አለ ማጆሮቭ፣ «በመጣህበት መንገድ ወደእናት ሰርጓጇ ትመለሳለህ:: የባትሪዎችህና የእክስጂን አቅርቦትህ የሚሟጠጠው በሀያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ በመሆኑ እናት ሰርጓጇም የምትጠብቅህ ያንኑ ያህል ጊዜ ይሆናል:: በዚያን ጊዜ ውስጥ ላትመለስ ከቀረህ እንደከዳህ ወይንም እንደተያዝክ ካለዚያም እንደተገደልክ እንቆጥረዋለን:: እዚህ እንደምትመለከተው መጓዝ የሚኖርብህ መንገድ ርቀት አስራሁለት ኪሎሚትር ብቻ ነው:: በአማካይ የሶስት ኖት ፍጥነትህ ይህን ርቀት ለመጨረስ ከሶስት ሰዓት ያነሰ ጊዜ ቢወስድብህ ነው፣ ስለዚህ የተመቸ ሁኔታ ይኖርሀል:: ይህ ምቾት ግን ተልዕኮው ላይ ምንም አይነት ነገር አይገጥምህም የሚል ትርጉም የለውም::

ማጆሮቭ ከተቀመጠበት ተነሳና እያወራ መንጎራደድ ጀመረ:: «በ1981 ከተፈጠረው የዊስኪ በቋጥኞች ላይ (Whisky-on-the- rocks) ክሰተት ጀምሮ፣ ስዊድናች ባህር ሰርጓጅ መርከቦችን አድኖ የመያዝ ችሎታና ብቃታቸውን አዳብረዋል:: በሰግንያ አንድ፣ አራት ሰርጓጆቻቸንን በደሴቶች በተሞላው የውሀ ክልላቸው ውስጥ እግኝተዋቸው ግን ሁሉም አምልጠዋል፣ አሁን ግን ብቃታቸው ከዚያን ጊዜው የተሻለ መሆኑን ማስታወስ ይኖርብህል:: እጅግ አስከፊ ሁኔታዎችን ለመጋፈጥ መዘጋጀት አለብህ፣ ምንም ነገር ቢፈጠር ግዳጅህን

http://ethzare.wordpress.com

ፈጽመህ መውጣት ይኖርብህል፣ ይህን እደግመዋለሁ፣ ግዳጅህን ፈጽመህ መውጣት ይኖርብህል። ጓዙን ማራገፍህ ለተልዕኮአችን ስኬት እጅግ ወሳኝ ነው፣ እድላችን አንድና አንድ ነው። ሳይላካልህ ከቀረ ለሌላ ተልዕኮ የሚሆን መሳሪያ የለንም። ጓዙ በትክክል ሳይቀመጥ ቢቀር.የመቶዎች ምኴልባትም የብዙ ሺዎች የሶቪየት ሰራዊት አባላት ሕይወት ትልቅ አደጋ ውስጥ ይገባል።»

ዝም አለና ወደሔልደርና ሶኮሎፍ ዞሮ ፊት ለፊት ተመለከታቸው። «ይህ ግለት ተንሳፋፊ ጓዙን በትክክል ካላማራገፍ የከፋ ነገር መኖሩን ያሳያል ግለትም አንዳችሁ በስዊድናውያን እጅ ውስጥ ከገባችሁ። በማንኛውም ምክንያት ትንሿን ሰርጓጅ ትታችሁ ለመሔድ ብትገደዱ፣ ሁለታችሁም በጥንቃቄ የተቀናበረ ታሪክ ይዘጋጅላችኋል፣ ወደፊንላንድ ለመግባት የሚያስችላችሁ ቀጣይ መመሪያም ይደርሳችሁና፣ ወደግሊቡ እንድትወሰዱ ትደረጋላችሁ። የባህር ዳርቻው ላይ አብራችሁ መሆን የለባችሁም፣ ታሪካችሁ የሚናገረው ብቻችሁን እንድትጓዙ ነው። ሁለታችሁም ቀደም ብሎ ሽጉጥ ተሰጥቷችኋል። ከመሄዳችሁ በፊት ሁለት ካርታ ጥይትና በሕይወት ለመቆየት የሚያስችሉ ሌሎች መገልገያዎች ይሰጣችኋል። ሁለት ካርታ ጥይት የሚስፈልጋችሁ ሁኔታ ውስጥ ከገባችሁ ተጨማሪ ሊያስፈልጋችሁ የመቻሉ ዕድል የጠበበ ነው የሚል ግምት ተወስዶ ነው፣ ይህ የተደረገው። ከዚህም ሌላ፣ እንዴት ባለቀምጠው ይሻላል? በሕይወት ላለመቆየት የሚያስችሏችሁ ነገሮችም ይሰጣችኋል።» ማጆሮቭ ራሱን ግራ ከቀኝወዘወዘ። «አይደለም፣ ዙሪያ ጥምጥም መሔድ አያስፈልግም። በደረቁ ልንገራችሁ። በስዊድኖች እጅ ከወደቃችሁ የራሳችሁን ሕይወት ማጥፋት ይኖርባችኋል። ከሁለት አንዳችሁ ይህን በማድረግ ብቃታችሁ ላይ ምንም አይነት ጥራጥሬ ካላችሁ፣ አሁኑኑ አሳውቁኝ።» ቅንድቦቹን ከፍ አደረገ።

«ጥርጣሬ የለኝም፣ ኮሎኔል» አለች ሶኮሎፍ ከመቅጽበት።

«ምንም የለኝም፣ ኮሎኔል፣» በማለት ሔልደር አስተጋባ። ግን ራሱን ለማጥፋት መድረስ የለበትም። ይህን ተልዕኮ በሕይወት ያጠናቅቃል፣ እንደምንም ብሎ

«ጥሩ፣» አለ ማጆሮቭ። «አንድ ተጨማሪ ነገር ይቀራል። በተንሳፋፊ ጓዙ ላይ እየተደረገ ያለው ስራ ተጠናቋል። ነገ ማሊቡ ይደርሳል፣ ሶኮሎፍ ደሞ በትንሿ ሰርጓጅ ላይ ያሉት መቆንጠጫዎችና በጓዙ ማሸጊያ መሀል ምንም አይነት የግንኙነት ችግር እንዳይኖር ወዲያውኑ ታረጋግጫለሽ።»

«እሺ ኮሎኔል፣» መለሰች ሶኮሎፍ።

ሔልደር በትክክለኛው ተንሳፋፊ ጓድ ልምምድ ያደርጉ እንደሁ ለመጠየቅ ሲዘጋጅ፣ ማጆሮቭ አቋረጠው።

«ለሚቀጥሉት ሶስት ቀናት ጥሩ የአየር ሁኔታ ይኖራል፣ የሚል መረጃ ከአየር ሁኔታ መኮንኑ ደርሶኛል፣» አለ። «ባለፉት ቀናት ብዙ ሰርታችሁ፣ ዝግጁነታችሁን አስመስክራችኋል። ነገ ምሽት ትሔዳላችሁ።»

የሔልደር ልብ ምቱን አቆመ። አልተዘጋጁም። የመጥለቂ ዝርግ ብረቶቹን መጠን ስለመጨመር ሀሳቡን ለመናገር አልቻለም፣ የሶኮሎፍ ነገርም ከሁሀ በታች ራሷን መቆጣጠር ሳትችል ቅር አሰኝቶታል። ግን አልተንጫነጨም። ሶኮሎፍም ሆነ ትንሿ ጠላቂ መርከብ ዝግጁ ይሁኑም አይሁኑ ማጆሮቭ ግን መዘጋጀቱ ታውቆታል። ሶኮሎፍን መልከት አደረጋት። እሷ ግን

የምትናገረው ጠፍቷት ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከተ። ሔልደር ራሱን አበረታትቶ ተናገረ። «መልካም፣ ጌታዬ። ዝግጁ ነን።»

«ጥሩ፣ ጥሩ፣» አለ ማጆሮቭ፣ እጆቹን እያፋተገ። «አሁን መሔድ ትችላላችሁ። ለሊቱን ጥሩ እረፍት አድርጉና፣ ጠዋቱንም ስራ አትግቡ። ጓዙ በ14:00 ሰዓት ጠላቂዋ መርከብ ውስጥ ይገባል።»

ሔልደርና ሶኮሎፍ ተነስተው ወደሰርጓጅ መርከቧ ዋና በር አመሩ።

«አሀ፣ ሔልደር፣» አለ ማጆሮቭ፣ የዘነጋው ነገር ያለ ይመስል፣ «ለትንሽ ጊዜ ቆይ፣ ላወያይህ የሚፈልገው የግል ጉዳይ አለ።»

«እንዴታ ጌታዬ፣ እሺ» አለ ሔልደር።

ማጆሮቭ፣ ሶኮሎፍና የጠላቂዋ ተቆጣጣሪ መልበሻ ክፍሉን እስኪለቁ ድረስ ጠበቀና መናገር ጀመረ። «ሔልደር እንተ መፈፀም ሊኖርብህ የሚችል አንድ ሌላ ተጨማሪ ግዳጅ ይቀራል።» ገጽታው ላይ ምንም ስሜት አይነበብም። «ከዩናይትድ ስቴትስ በተለየ መልኩ፣ ስዊድን በ1980 የሞስኮ አሎምፒክስ ላይ ተካፍላ፣ ዝግጅቱ ሙሉ በሙሉ በቴሌቭዥንና በጋዜጣ ተሳልኧል። ስለዚህ፣ የሶኮሎፍ ፊት ለስዊድን ህዝብ አዲስ ስለማይሆን እሷ ደረቅ መሬት መርገጥ ሊፈቀድላት አይገባም። ሰርጓጅ መርከቧን ለቅቀህ ለመሄድ ከተገደድክ እሷ እንደማትወጣ ማረጋገጥ ይኖርብህል ገባህ? በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከገባህ እንድትገድላት።»

ሔልደር ለእፍታ ያህል ካመነታ በኋላ ምላሽ ሰጠ። ሊያደርገው ይችል እንደሁ አሰበ። በየስልጠና ክፍለጊዜያቸው ወቅት ሶኮሎፍን ለመግደል የፈለገባቸው ጊዜያት ነበሩ። ያ ጊዜ ከመጣ ግን ሊያደርገው ይችል ይሆን? ጨካኝ ነፍስ ገዳይ መሆን ይችል ይሆን? ሊያስብበት ይገባል። ለጊዜው ግን ማጆሮቭ ስለጥርጣሬው እንዲያውቅበት ማድረግ አልፈለገም። «እሺ፣ ኮሎኔል፣ በደንብ ተረድቼዋለሁ፣» አለ።

17

ሩል የተዘበራረቀ ህሊናዋን መስመር ለማስያዝ እየጣረች የእራት ልብሱን የለበሰው ሰው ላይ አፍጥጣለች።

«ህይ፣ አስታወስሽኝ?» ዊል ሊ ጠየቃት።

ውይ ያምላክ ያለህ ለፈንጠዚያ የታሰበ የራት ቀጠሮ ነበራት ነካ። በጭንቀቷ መሀል ረስታዋለች። ልትናገር ስትል፣ ሁለት ነገሮች አቆሟት፣ የስልኩ ቅጭልታ እና አሁን ከቢቷ ፊት ለፊት ባለው መንገድ ላይ የሚንሳራደደውን ቀደም ብሎ ሲከታተላት የነበረ ሰው መመልከቷ። የዊልን እጅ ይዛ ስባ አስገባችው። ስልኩ ደግሞ ያንቃጭላል። «አንድ ጊዜ ቆየኝ፣ ዊል፣» ብላ ስልኩን አነሳችው። «ሄሌ።»

«ከአንድ የድሮ ሰላይ ጋር ራት ብትበይ ደስ ይልሻል?» ሲል ኤድ ራውልስ እየተሳዘዘ ተናገረ። «ቢሮ ላገኝሽ ሞክሬ ነበር፣ ግን ሄደሻል።»

ሩል ይህን አልጠበቀችም፣ ግን ድንገት ህሊናዋ ጠራና ሳታመነታ መናገር ጀመረች። «ውይ እዎ ኤድ፣ ዛሬ ካንተ ጋር ራት ብበላ ደስ ይለኛል።» የዊልን ገፅታ ሲቋጠር መልከት አድርጋ፣ እንዳይናገር በእጇ ምልክት ሰጠችው። «መቼና የት እንደሆነ ብቻ ንገረኝ።» ህሊናዋ በፍጥነት እየሰራ ነው።

http://ethzare.wordpress.com

«ጆርጅታውን ውስጥ ትንሽ ቤት ተከራይቻለሁ። የቤተመንግስት ምቾት ባይኖረውም ጓሮው ላይ የሥጋ መጥበሻ ምድጃ አለው። ለምን የተፈጨ ስጋ ጥብስ እላዘጋጅልሽም?»

«ግሩም ይመስላል፣» አለች አድራሻውን እየፃፈች። «ከኔ ቤት የሚርቀው ትንሽ ነው። ስንት ሰዓት ላይ?»

«በፈለግሽ ጊዜ። እንደነገሩ ልበሺ።»

«በሀያ ደቂቃ ውስጥ እደርሳለሁ፣» አለች። ሰልኩን ዘግታ ወደዊል ፈቷን አዞረችና፣ ምን ላድርግ በሚል አኳኋን እጆቿን እንሳቻቸው። «ቆየኝ፣ የእብደት እንደሚስመስልብኝ አውቃለሁ፣ የእራት ቀጠሮ እንዳለንም አውቃለሁ. . .»

«እንደማስታውሰው ለመፈንጠዝ ነበር፣» አለ በደረቅ እንደበት። «የራት ቀጠሯችን እንደተጠበቀ ቢሆን ኖሮ የሚያስፈነጥዘን ምን እንደነበር ንገሪኝ? ደሞስ ኤድ ማንነው?»

ፊቱን በእጆቿ መሀል አስገባችው። «ተመልከት፣ የፈንጠዚያው ምክንያት ወደ ትልቅ ችግር ምክንያትነት ተለውጧል፣ አሁን የደወለው በህቡዕ ክፍል ውስጥ የሚሰራና ይህን ችግር ለማስተካከል ሊረዳኝ የሚችል ብቸኛ የድሮ ጓደኛዬ ነው። እባክህን፣ ተረዳኝ፣ እባክህን። የወደፊት የሥራ ህይወቴ በሙሉ ከባድ አደጋ ላይ ወድቋል፣ ይህን መፍታት ይኖርብኛል።»

ገጽታው እጅ የመስጠት ፈገግታን ተላበሰ። «እሺ፣ እንዳልሽ ይሁን። ከማጆሮቭ ጋር የተያያዘ ነገር ነው?»

«ሁሉም ነገር ከማጆሮቭ ጋር የተያያዘ ነው፣ ዘርዝሬ ባጫውትህ ደስ ባለኝ ነበር፣ አሁን ግን አልችልም። ወደዚያ ሂጂ ይህ ሰው እንዲረዳኝ ማሳመን ይኖርብኛል፣ ከእሱ የምፈልገውን ሲያውቅ ርዳታ ሊያደርግልኝ መፍቀዱን ርግጠኛ አየደለሁም።»

«እኔ ልረዳሽ የምችለው ነገር አለ?»

አሰብ አደረገች። «እም። ምሽቱን እዚሁ አሳልፍ፣ ቴሌቭዥን ተመልከት ወይ እንብብ ቶሎ ልመለስ እችል ይሆናል፣ ግን አትመኝ። እንበልና እስከ እምስት ሰዓት ካልተመለስኩ ወደቤት ሂድ ጠዋት እደውላለሁ። እሺ?»

ትክሻውን ሰበቀ። «እሺ፣ ሌላ የምሰራው የተሻለ ነገር የለኝም። ቤቱ ውስጥ የሚበላ ነገር አለ?»

«ፍሪጅ ሙሉ ምግብ አለ፣ የቆየ ዶሮም አለ፣ ለምግብነት ይሁን አይሁን እርግጠኛ አይደለሁም።»

«የሚሆነውን እደርጋለሁ። አንቺ ተዘጋጂ።»

«ግሩም።» የኮረደሩን መስታወት ተጠቅማ ገጽታዋን አሰማመረችና በርሳዋን ይዛ ወደበሩ መሄድ ከጀመረች በኋላ። የሚከታተላት ሰውዬ ከቤቷ ውጪ እንደሚጠብቃት ታውቃለች። ኤድ ቤት ድረስ እንዲከተላት አልፈለገችም። በቤቷ ጓሮ ወጥታ እንክብካቤ የጎደለውን መናፈሻ አለፈችና፣ የጎረቤቷን መናፈሻ ከሷ ጋር የሚለያየውን አጥር አንዱን እንጨት ነቅላ ሾልካ አለፈች። በጥንቃቄ የተያዘውን የጎረቤቷን መናፈሻ አቋርጣ ከቤቱ ጀርባ ወዳለ ተከሉች በር ሄዳ አንኳኳችው። ቴሌቭዥን ሲመለከቱ የነበሩ አዛውንት መጥተው ከፈቱላት።

«ካትሪን ሩል እባላለሁ፣» አለች ለማታውቃቸው አንግዳ፣ «የምኖረው ከእርስዎ ቤት ጀርባ ነው፣ በፊት ለፊቱ የቤቴ በር መውጣት አልፈለግኩም። ሰሞኑን አንድ የሚከታተለኝ ወንድ አለ እና እንዲያገኘኝ አልፈለግኩም። በእርስዎ በር ብወጣ ቅር ይሰኛሉ?»

«ምን ችግር አለ፣»ግራ የተጋቡት ሰውዬ በጨዋነት መለሱላት፣ «እባክሽን ግቢ።» እየመሩ በፊት ለፊት በራቸው አስወጧት።

«በጣም አመሰግናለሁ፣» አለች እጇን እያውለበለበች።

«ምንም አይደለም፣» መለሱ። «በፈለግሽ ጊዜ አለሁልሽ። ውብ ልጃገረድ በራን ካንኳኳች ብዙ ሰንብቼያለሁ፣» አሉ።

በጊ ጎዳና ላይ በሚገኝ ከመሬት ስር መኖሪያ ወደሚገኘው የኤድ አፓርትመንት ለመድረስ አስር ደቂቃ አልፈጀባትም። ደወሉን ስትደውል ኤድ ራውልስ እሮጌ ካኪ ሱሪና ሸሚዝ ለብሶ ከፈተላት። ጉንጯን ሳማችና «ግቢ። የሚያኩራ አይደለም፣ ገና በዚህ ሳምንት ነው የተከራየሁት። ባለ ሶስት ክፍል ቤቱን በፍጥነት አስጎበኛት። ከበላይኛው ፎቅ የሚኖረው ባለቤትየው እንደነገሩ አሳምሮታል። «ቤቲ ወደዚህ መጥታ እስከምታሳምረው ድረስ ለጊዜው አይከፋም። መጠጥ እንደምትፈልጊ ታስታውቂያለሽ።»

«በርበን በበረዶ ለማግኘት የማላደርገው የለም። ወደ ላንግሊ መመለስህ ነው?»

አምንታውን በምልክት አሳያት። «ግን አልተረጋገጠም። ጥቂት ቀናት ያህል ሥራ አልጀምርም። ወደ ጓሮ እንሂድ። «ከቤቱ በስተጀርባ ወደሚገኝ በረንዳ እየመራ ወሰዳትና መጠጧን እንደያዘች እንድ ወንበር ላይ አስቀመጣት።

ውጪው ደስ ይላል፣ የጀምበሯ ውጋገን ገና አልከሰመም፣ ግን የቀኑ ሙቀት በርዷል። ልክ እንደእሷ የአትክልት ስፍራ እንክብካቤ የሚፈልገው መናፈሻ ውስጥ ንቦች ይራወጣሉ። «መጠየቅ የለብኝም፣ ኤድ፣ ግን ስራው ምንድን ነው?»

«ውይ አታስቢ፣ ከሚስጥር የተፈረጀ አይደለም። የተልዕኮዎች ተባባሪ ምክትል ዳይሬክተር።»

«ቆንጆ ቦታ ነው ኤድ፣ የምክትልነቱን ቦታ መያዝ ነበረብህ፣ ይህን ሁሉም ሰው ያውቃል።»

ራውልስ ሳቀ። «አሁን ይሄን ተንኮልሽን ተይ። ለሳይመን ማገልገል ቅር አያሰኝም። እሱና እኔ ወትሮም እንግባባለን። ያንቺን ያህል በቅርበት ባላውቀውም አንቺ ከምታውቂው ጊዜ በላይ አውቀዋለሁ።

«እዝናለሁ ኤድ፣ አስተያየቴን በላይመን ላይ ወቀሳ ለመሰንዘር ልጠ ቀምበት አላሰብኩም። ባይፈልግህ ኖሮ ይህን ስራ እንደማታገኘው አውቃለሁ፣ ስለዚህ ታማኝነትህን የመለገስ ግዴታ አለብህ።»

ራውልስ ትከሻውን ሰበቀ። «ያም ሆነ ይህ፣ አሁን ከጎዳና ላይ ሥራ እላቀቃለሁ።

ደሞም ለዚህ ሥራ እድሜዬ እየገፋ ነው፣ ከዚህ ሌላ ቤቲ ወደዋሽንግተን መመለሱን በጣም ወዳዋለች። እስከ ጡረታዬ ድረስ እዚሁ ለመኖር አስበናል።»

http://ethzare.wordpress.com

«እስካሁን እንተን ተከትላ እለምን መዞሩ የሰለቻት ይመስለኛል፣ እኔ እሷን ብሆን ወደአሜሪካ መመለሴን በጣም እወደው ነበር።»

«ከተመለስን ሁለት ዓመታት ያህል ሆኖናል። በምስራቁ አንድቆይ የሚያስገድድ ተልዕኮ ላይ ነበርኩ። ኒውዮርክ ውስጥ ነበርን፣ ቪሌጅ ላይ ቤት ተከራይተን በሳምንቱ መጨረሻ ላይ እሄዳለሁ። ዳግመኛ ወጣት የሆንን ያህል ተሰማን፣ ከተጋባን በኋላ ቪሌጅ ውስጥ ለጥቂት ወራት ኖረናል።»

«ማላኮቭ ማራኪና አትኩሮትን የሚስብ ተልዕኮ እንደነበር እገምታለሁ፣» ስትል፣ ሩል፣ ገጽታው አግራሞት ሞላበት። ጂዎርጅ ማላክሆቭ፣ ከድቶ ወደዩናይትድ ስቴትስ የገባ የKGB ብቸኛ ከፍተኛ ባለስልጣን ሲሆን፣ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ምክትል ዳይሬክተርነት ሽፋን የኒውዮርክ ቅርንጫፋቸውን የመራ ሜጀር ጀኔራል ነው። መክዳቱ በአሜሪካና በሶቪየት መሀል ያለው ግንኙነት ላይ ሰፊ ከፍተትን ፈጥሯል። ለ CIA ከተመሰረተ ጀምሮ ካስመዘገባቸው የስለላ ድሎች ሁሉ ከዋንኞቹ ተርታ የሚቆም ሆኗል።

ራውል ትከሻውን ሰበቀ። «አትኩሮትን የሚስብ ሥራ ነበር፣» አለ ከአሜሪካ እንዳልወጣም እድርጎኛል። ከመስክ ሥራ የሚያስወጣ ግሩም ተልዕኮ ነበር። «መጽሔቶቹን ሳነብ ነበር። አስገራሚ ነው። ያንን ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማጠናቀር እንጠቀምበታለን። ልትኮራ ይገባሀል። አንድን መርማሪ የሚያረካ መረጃን የሚሰጥ ሥራ ነው።»

«እውነቱ ግን እድሌ መሆኑ ነው። ማላክሆቭ እኔ እንድመደብለት ጠየቀ።»

«ትቀልዳለህ፣ ለምን?»

«ስቶኮልም ቅርንጫፍ በነበርኩበት ጊዜ በጥቂቱ እንተዋወቅ ነበር። እሱ እዚያ የሚገኘው የሶቪየት ኤምባሲ የጣቢያ ሀላፊ ነበር፣ ግን አላወቅነውም። ማህደሩ እንደሚናገረው፣ ዋና ፀሐፊ ይመስለኝ ነበር። ቤቲና እኔ በአንድ ወቅት በዋናው ቤተመንግስት በተደረገ እራት ግብዣ ላይ ከሚስቱ ጋር ሆኖ አንድ ጠረጴዛ ተጋርተናል። ሁለታችንም ወደናቸዋል፣ ግን በዲፕሎማሲያዊ የኮክቴይል ገብጥዎች ላይ በአጋጣሚ ከመገናኘታችን በስተቀር በደንቡ ተገናኝተን አናውቅም። እንደምታውቂው፣ የሶቭየት ዲፕሎማቶች ብዙም ከሰው አይቀላቀሉም።

«ከዚያስ ምን ተፈጠረ?»

«ምንም። ለስምንት ዓመት ያህል ነው? እም ምንም ሳይፈጠር ቆየን ከዚያም ቤልግሬድ ውስጥ የጣቢያ ሀላፊ ሆኜ ሳለሁ፣ ወደኒውዮርክ ተመልሼ እንድመጣ የሚገልፅ አስቸኳይ ቴሌግራም ደረሰኝ። አንድ ነገር አበሳጨቹ ለትጣት የሚፈልጉኝ ነበር፣ የመሰለኝ። ኬኔዲ ላይ ተቀብለውኝ፣ ማንሀተን ወደሚገኝ የድርጅቱ ጥብቅ የደህንነት ቢሮ ወሰዱኝና፣ ማላክሆቭ አንድ የኮክቴል ግብዣ ላይ ለተባበሩት መንግስታት አምባሳደራችን መክዳት እንደሚፈልግ መናገሩን ነገሩኝ። ሳሚና ፕሬዚዳቱም ግሩም ነው ብለው ተሰማሙና፣ መጀመሪያ ግን ለሁለቱም ወገኖች መስራት እንደሚኖርበት ነገሩት። በእጃቸው ስለሆነ ምንም ምርጫ አልነበረውም። አደርገዋለሁ አለ፣ ግን ከኔ በስተቀር ማንም እንዳያዝዘው እንደሚሻ ገለፀ። በእቋሙም ፀና፣ እኔ በአካል እዚያ እስክደርስ ድረስ ምንም እንቅስቃሴ አላደረገም። ብስመው ደስ ባለኝ።

ለአንድ ዓመት ገደማ በስራ ቆየ። በመጨረሻ ግን የሞስኮ መዓከል መጠራጠር ስለጀመረ ለመልቀቅ ተገደደ። ለሱ ተልዕኮ መስጠት ለኔ ቀላል ነበር።»

«የክርስቶስ ያለህ፣ ትልቅ ርምጃ ነው።»

«እውቀሽዋል፣ የኔ ቆንጆ። በዚህ ሰው ሥራ ላይ መራመድ የምችለውን ርቀት ተራምጀያለሁ። ሽማግሌውን ራውልስ የሰማይ መና ወረደለትና አሁን ላግሊ ውስጥ የአመራር ቦታ ሊይዝ ሆነ።» ከት ብሎ ሳቀ። «የምልሽ፣ በጡረታ ከፍያዬ ላይ ትልቅ ልዩነት እንደሚያመጣ ርግጠኛ ነኝ። ቤቲ ገና ካሁኑ ባህማ ደሴቶች ላይ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶችን ለመግዛት እየተነጋገረች ነው።

«ይህ ዕውብ ነው፣ ኤድ፣» ሳቀች ሩል። «ለጥሩነትህ የሚገባ ክፍያ ነው።»

«እመሰግናለሁ የኔ ጣፋጭ።» ብሎ ራውልስ የበሰለውን ስጋ ገለበጠው። «የሶቭየትን ቢሮ ሃላፊነት ማግኘትሽን ስሰማ ኮራሁብሽ።»

«ማስታወሻህ ደርሶኛል፣ ኤድ እመሰግናለሁ።»

«ለወጣት መኮንኖች ትልቅ ሀላፊነትን መሰጠት በጀመሩ ጊዜ ለእኛም ተስፋ ይኖረናል። ስራውን ወደድሽው?»

ሩል ፈገግ አለች። «ትንሽ የሀይል እንቅስቃሴ ቢኖረው ብዬ የምመኝባቸው ጊዜያት አሉ። ያን ግዜ ከህቡዕ ክፍሉ መልቀቄ ይቆጨኛል፣ ግን ወድጀዋለሁ።»

ራውልስ ጥብስ ስጋውን መረመረው። «ይዘሽው መቆየት ትችያለሽ?»

ሩል ቀጥ ብላ ተቀመጠች። «ስለዛሬ ተሰዓቱ ሰማህ?»

«ሰማህ ወይ?» አለ በድንፋታ። «እዚያው ነበርኩ።»

«ኒክሰን፣ ሳይመንና ዳይሬክተሩ ባደረጉት ስብሰባ ላይ?»

ራሱን በአዎንታ ወዘወዘላት። «ሁሉ ነገር ጠፍ ነው የገባሁት። ልወጣ ስሞክር ግባ የሚል ምልክት ሰጡኝ። ሪፖርትሽ የሚለውን ባልሰማም የዳይሬክተሩን ምላሽ ግን አድምጬያለሁ። በጣም ተቆጥቶ ነበር። የስጋ ጥብሶቹን ሰሀኖች ላይ ገልብጦ ሰላጣ አዘጋጀና ምግቡን ጠረጴዛው ላይ አኖረው። «ነይና ተያያዥው።»

እሱ ወይኑን ሲቀዳ ሩል ወንበር ስባ ተቀመጠች። «አለን ዝርዝር ሁኔታውን እልነገረኝም፣ ግን ጠቅላላ ሁኔታው ገብቶኖል ብዬ አስባለሁ። የስካንዲኒቪያን ክልልን የሳተላይት ምስሎች እንዳላገኝ እገዳ አላልፈውብኛል- ቢያንስ ያን ያህል ስፋት ያለው ቅጣት ለመሆኑ ተስፋ አለኝ።»

ራውልስ መስማማቱን በምልክት ገለፀላት። «ዳይሬክተሩ ይህን ሲያደርግ እዚያ ነበርኩ። ከስካንዲኒቪያ አያልፍም። በእንድ የቢሮ ሀላፊ ላይ ጠቅላላ የእገዳ ትዕዛዝ አያስተላልፍም፣ ምቾት የሌለው ቦታ ያስቀምጥሻል እንጂ።»

ሩል የቀዳላትን ወይን ተጎነጨች። «እም፣ ኒክሰን ይህን ነገር ጠቅሶልኝ ነበር። ስለካምፓስ ምልመላ እንስቶልኛል።»

ራውልስ ወደኋላ ተለጥጦ ከልቡ ሳቀ። «እም እንደዚያ አይነት ነገር ነው የሚሆነው አይደል?»

«ዳይሬክተሩ ያን ያህል ደንዝ ነው እንዴ?»

«ሊሆን ይችላል። ዳይሬክተሮች ግን ይለዋወጣሉ፣ ፕሬዚዳንቱ ከተለወጠም በቦታው ያለው ዳይሬክተር ይለወጣል። የፓርቲዎችን ይቅርና፣

http://ethzare.wordpress.com

የአስተዳደር ለውጥን እንኳን መቋቋም አይችልም። ለጥቂት ጊዜ በክብር አብሬው ችዬው መኖር የሚኖርብኝ ይመስለኛል፣ ግን ባብዛኛው ጫናው የሚያርፈው ሳይመን ላይ ነው።» ራውልስ ከወይኑ በረጅሙ ጠጣለት። «ሳይመን ያንን ቦታ የሚፈልገው ይመስለኛል።» አለ። «የአሁኑ ፕሬዚዳንት ተከታይ እንደዚህኛው አይነት ዳይሬክተር ሳይሆን መያዊ ብቃት ያለውን የሚመርጥ ከሆነ፣ ቦታውን ለማግኘት ይሞክር ይመስለኛል።»

«እንዲ፣ እም፣» አለች ሩል፣ «ሳይመን ቢያገኘው ደስ ይለዋል። «እስከ አሁን ድረስ ይህን ስልጣን ሊያገኘው እንደሚችል አስባ አታውቅም ነበር፣ አሁን ግን ይህ ሀሳብ ረበሻት። «አንተ ደግሞ የተልዕኮ ክፍሉን ቦታ ታገኛለህ፣ አይደለም?»

«ማን ያውቃል? ሳይመን ለምክትልነቱ የሚሾኝ ከሆነ ምናልባት አገኘዋለሁ።» ራውልስ የጎረሰውን ስጋ ጥብስ በወይን አወራረደው። «ጥያቄው አንቺስ ምን ትሆኚያለሽ የሚለው ነው፣ ኪት? የቀድሞ ባለቤትሽ የCIA ዳይሬክተር በሆነበት ቦታ ላይ መበልፀግ ትችያለሽ?»

ሩል ትከሻዋን ሰበቀች። «እውነቱን ልንገርህና ኤድ፣ እኔን የበለጠ ያላሰቡኝ መጪዎቹ ጥቂት ዓመታት ሳይሆኑ መጪዎቹ ጥቂት ሳምንታት ናቸው። ስካንዲኒቪያ ውስጥ አንድ ነገር እየተደረገ ነው፣ እና. . . »

ራውልስ እጁን እጎና ዝም አሰኛት። «እዚህ ላይ አቁሚ፣ ሩል። በዚህ ጊዜ ስለዓለም የመሰለኝ አስተያየት መስማት አልፈልግም። እኔ የገለጽኩልሽ ነገሮች ወደየት እንደሚያመሩና ማን እንደሚቆጣጠራቸው ነው። ስለዚህ ጉዳይ መስማት ካለብኝ ግን ከዜና ማሰራጫዎች ብሰማው እመርጣለሁ።»

ሩል ፍርሀት ወረራት። «ልክ ነህ፣ የመጨረሻ መፍጨርጨር ላደርግ እየሞከርኩ አይደለም። ብዙ ችግር ውስጥ ስለሆንኩና ዙሪያዬን ጭለማ ስለዋጠኝ ብቻ ነው። ከዚህ ሌላ የሥራ ጊዜ እንዳይኖረኝ መረጃ እንዳላገኝ ተከልክያለሁ። ያውም ትክክል መሆኑ ለሚሰማኝ አንድ ጉዳይ።»

ራውልስ እንደገባው ለማሳየት ራሱን ወዘወዘ። «እኔም በጊዜዬ ያልሽውን አይነት ስሜት ተሰምቶኝ ያውቃል።»

«ታዲያ ምን አደረግህ?»

ሳቀ። «ሙጭጭ አልኩበት። እንዳንድ ጊዜም ውጤትን አገኝበታለሁ። ሌላ ጊዜ ደግሞ እቀጣበታለሁ።»

«እኔም እዚያ ገደማ ነኝ፣ ይህንን ግን ልተወው አልችልም። ይህ እጅግ፣ እጅግ ከፍተኛ አስፈላጊነት አለው ብዬ አስባለሁ፣ ኤድ።»

«እምኚሻለሁ፣» አለ። «አስተዋይ መሆንሽን አውቃለሁ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥም ብዙም ባላገኝሽ እንኳን፣ የሰማሁት ጥሩ ነገሮችን ነው። እኔ በዳይሬክተሩ ቦታ ብሆን ኖሮ ቢያንስ አዳምጥሽ ነበር።»

«አመሰግናለሁ።» ሩል ቡና ቀድቶ እስኪጨርስ ጠበቀችውና ወደፊት ጠጋ አለች። «ስማ ኤድ፣ በአሁኑ ሰዓት ለምን ሀሳቤን ማዳመጥ እንደማትችል ይገባኛል ግን ከፈቀድክ ትንሽ ምክርና ርዳታ ብትሰጠኝ ይጠቅመኛል።» ውለታዋ እንዳለበት ታውቃለች፣ ግን ይህን አስታውሳው ስርዓት ያጣች ሆና መታየት አልፈለገችም።

«ምክር? እሺ። ርዳታ? ይህ በምትፈልጊው የእርዳታ አይነት ይመስናል።»

ሩል በረጅሙ እየር ሳበች። «መጀመሪያ፣ ኮስሞስ መረጃ መሳከል መግባት የሚያስችለኝ የኮምፒውተር ይለፍ ቁጥር ያስፈልገኛል። ከአሁኑ ሁኔታ አንፃር፣ የታሴን የይለፍ ኮድ ከተጠቀምኩ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ አሁንም እየሰራሁ መሆኔን በምርመራ ያውቁና ቅጣቴን እቀበላለሁ። የሌላ ክፍል ሰራተኛን የይለፍ ቃል ነው የምፈልገው፣ ነገሮች እየገፉ ሲመጡም ቁጥጥር የማያደርጉበት የሚስጥር ቁጥር ቢሆን ይመረጣል።»

ራውል በትንሹ ፈገግ አለ። «እሺ፣ አትግፊው፣ በቃልሽ ያዥው።» አስር ቁጥሮች ያሉት ኮድ ነገራት። «ያገኘው?»

ሩል ቁጥሩን በሆዷ ደገመችው። «ይዜዋለሁ። ያንተ ነው? ይህንን አንተ ላይ መጫን አልፈልግም።»

በአሉታ ራሱን ወዘወዘ። «የሳይመን ነው። እንዴት አገኘሽው እንዳትይኝ።»

ሳቀች። «የሰው ሚስጥር ታነፈንፋለህ።»

«ያሰለጠኑኝም ሚስጥር ለማነፍነፍ ነው። አሁን ይህን ለመተው እድሜዬ አይፈቅድልኝም። ሌላስ ምን ትፈልጊያለሽ?

ሩል ከቢሷ ውጪ ስለሚጠብቃት ሰውዬ አሰበች። «መካኒክ እፈልጋለሁ፣ ሁለገብ የሆነ ጥሩ መካኒክ።»

ራውልስ ኮስትር አለ። «የሀገር ውስጥ ጉዳይን ሚስጥር ልታወጪ አይደለም ነው እንዴ?» CIA የሀገር ውስጥ ተልዕኮዎች ስልጣን ያለው FBI ነው። CIA የሀገር ውስጥ ህገወጥ ተልዕኮዎችን ቢያደርግም ተቀጥቶ አልፏል።

ራሷን በአሉታ ወዘወዘች። «የምፈልገው ለመከላከያ ተግባራት ብቻ ነው፣ ቃል እገባለሁ።»

ራውልስ አሰብ አደረገ። «ዳኒ በርጊስ የሚባል ሰው አለ፣ ከተወሰነ ጊዜ በፊት አብረን ነበርን። ዋሽንግተን ውስጥ የአደጋ ጊዜ ሳይረኖችን፣ የጥበቃ ውሾችንና ማንም ሰው የፈለገውን ነገር ሁሉ የሚያቀርብ የደህንነት ጥበቃ አገልግሎት ይሰጣል። አብረን ቀሳል አይሮፕላኖችን እናበር ነበር። በድርጅቱ ይታወቃል፣ የማይታወቅ ስልክ ተጠቅመሽ፣ ቢግልስ እንደላከሽ ንገረው። ቢግልስ እያለ ነበር የሚጠራኝ።»

«አንድ ሌላ ነገር አለ፣» አለችው፣ ይህኛው ግን ከበድ ይላል። «በማላክሆቭ የቃለ መጠይቅ ሪፖርቶች ላይ ማጆሮቭ አልተጠቀሰም። ያለጥርጥር ይህ ስም ተነስቷል። ሰውየውኮ ዋና ጠቅላይ ዳይሬክቶሬት ነበር!»

ራውልስ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ። «ሪፖርቶቹ ላይ ከሌለ፣ አልተነጋገርንበትም።» ሩል ይህ ያለመሆኑን ታውቃለች። ኤድ፣ ይህ ከበድ ስለሚል ልወያይበት አልችልም ማለቱ ነው። ኤድ በህጉ መሰረት እየተመራ ነው፣ ግን የምትጠይቀውን በትክክል ማግኘት ከቻለች፣ ሕጉን አሳን እንዲጠቅማ አድርጎ ሊተረጉመው ይችላል። «ማላክሆቭ የያዘው መረጃ ሁሉ ተወስዷል አይደለም?»

«ባዶውን እስኪቀር፣ እመኚኝ።»

«ለቀቃችሁት?» አዲስ ማንነት ሰጥተውት አንድ ቦታ አስቀምጠውት ከሆነ ዕድሏ ከድቷታል ማለት ነው።

«በቅርብ ጊዜ እንለቀዋለን፣» መለሰላት።

http://ethzare.wordpress.com

ማላከሆቭ ቃለ መጠይቅ የተደረገለት ከኒውዮርክ በተወሰነ ርቀት ላይ መሆን እንዳለበት ታውቃለች፣ ይህ ባይሆን ራውልስ ሚስቱን እዚያ አኑሮ በሳምንት መጨረሻዎች ላይ እየመጣ ሊጠይቃት ባልቻለ ነበር። ሌላ ስፍራ ሊወስዱት ከሆነ ግን ትንሽ ዕድል ይኖራት ይሆናል። ጥቃቷን ሰነዘረች። «ኤድ፣ ማላከሆብን ማናገር እፈልጋለሁ። አብሬው አንድ ሰዓት እንድቆይ ፍቀድልኝ።» ራውልስ አለማንገራገሩ አስገረማት።

«ከቬርሞንት፣ ስቶዊ አንድ ማይል ርቀት ላይ በዋናው መንገድ በስተደቡብ፣ አንድ የቴክሳኮ ጣቢያ አለ። እሁድ ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ እዚያ ጠብቂኝ። ማንም እንዳልተከተለሽ እርግጠኛ ሁኚ። ፖሊሮች ራሳችው ቤንዚን የሚቀዱበት ቦታ ገብተሽ ነዳጅ ሙይ። ቢጫ ጂፕ መኪናን ፈልገሽ አግኚ፣ ሹፌር ብቻ ይኖረዋል። በርቀት ተከተይው። ወደ አንድ መኖሪያ ቤት ያደርስሻል። እስር ሰዓት ላይ ወደቴክሳኮ ጣቢያው ተመለሺ። ይህን ካደረግሽ ለአርባ አምስት ደቂቃ ያህል ታናግሪዋለሽ።»

«አመሰግናለሁ ኤድ።»

«ወደቤት መሂድ ሳትፈልጊ አትቀሪም፣» አለ ኤድ ከተቀመጠበት እየተነሳ። ፊት ለፊቱ በር ላይ ስትደርስ ቆመች። «ኤድ፣» አለችው፣ «ሰንፍላወር ምንድን ነው?» ራውልስ ከመመለሱ በፊት አመነታ። «እኔ እንጃ ኪት።»

ሩል እቀፈችውና ወጣች። በፍጥነት ወደጎረቤቷ መኖሪያ አመራች። እሷን በማየታቸው ቢገረሙም በመናፈሻው እየመሩ ወሰዷት። በጓሮ በሯ ስትገባ የሞዛርት ሙዚቃ ሲንቆረቆር ተሰማት። ዊል መጽሀፍ ጭኑ ላይ አስቀምጦ ያንጎላጃል። ቀስ ብላ ቀሰቀሰችው።

«ታዲያ እራቱ እንዴት ነበር?።» ጠየቃት።

«በጣም ምርጥ ሥጋና ብዙ ርዳታ፣ አመሰግናለሁ፣» መለሰች፣ በስሱ እየሳመችው። «በላህ?»

«የቀዘቀዘ የአትክልት ፒዛ። ፍሪጅሽ ውስጥ አስራ ሁለት የሚሆኑ አገኘሁ።»

«አንተ ቤት ካልመጣሁ የምበላው አሱን ነው፣ ቅርፄን የምጠብቀው በዚያ ነው። ስማ፣ ብትቆይ ደስ ይለኛል፣ ግን አእምሮዬ አያርፍም ስለዚህ ለጨዋታ የምመች አይደለሁም። ቅር ይልሀል?»

«የሚገባኝ ወንድ በመሆኔ እድለኛ ነሽ፣» አለ ተነስቶ እየተንጠራራ፣? «ሌሎች ወንዶች ቢሆኑ የወሲብ ፍላጎታቸው ሳይሞላ ወደቤት መላካቸው ይቅርና ለእራት ውድ ሆቴል ውስጥ ተጋብዘው ሱፋቸውን ሽክ ብለው ለብሰው መጥተው፣ ፍፃሜያቸው የያም ፒሳ መብላት ሆኖ አንቺ ግን ከሌላ ሰው ጋር ጥብስ ስጋሽን የመብላትሽን ነገር በቀላሉ ባላለፉት ነበር።»

«ምን ያህል እድለኛ እንደሆንኩ አውቃለሁ፣» አለች ክንዶቿን ወገቡ ዙሪያ እየላከች፣ «ግን ያለሁበትን ሁኔታ ቢያንስ አሁን ልነግርህ አልችልም ለኔ በጣም ትልቅ ነገር ነው፣ ምናልባትም ለሌሎች ብዙ ሰዎችም ጭምር፣ ወደመውጫው በር ቀስ እያሉ ሄዱ። ቆመች። «የተቀረውን ሳምንት መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ነው የማሳልፈው፣ እሁድ ደግሞ ከክተማ መውጣት አለብኝ። በሳምንቱ መጀመሪያ ላይ ልደውልልህ እችላለሁ?»

«እሁድ እለት በስቶኮልም በኩል ወደፊንላንድ እንደምሔድ ረሳሽው?»

«ውይ አምላኬ ልክ ነህ፣ እኔም ኮፐንህገን ላይ ልጠብቅህ ተስማምተናል።»

«በነገራችን ላይ፣» አለ፣ ወደኮቱ የውስጥ ኪስ እጁን አስገብቶ የአየር መንገድ ካርድ እያወጣ፣ የኮፐንህገን ትኬትሽና የሆቴል መያዣ ወረቀትሽ ይሄውልሽ፣ ምናልባት እኩል የማንደርስ ከሆነ፣ ኮስተር አለ። «የመምጣት እቅድሽን አልሰረዝሽውም አይደለም?»

«እንዲታ እመጣለሁ እንጂ ዊል። እንደውም ለትንሽ ጊዜ ከቪሮው መራቁ ጥሩ ሊሆንልኝ ይችላል። ግን ይህ የማጆሮቭ ጉዳይ እጁ ላይ ስላለ፣ በመጨረሻው ሰዓት ልሰርዘው እንደምችል ልትገነዘበኝ ይገባሀል።»

«ይሁን እሺ፣» ብሎ ተነፈሰ። «የምትችይውን እንደምታደርጊ አውቃለሁ።»

«በእግርህ ነው የመጣኸው?»

«አዎ።»

«ግራ ቢያጋባህም፣ መጀመሪያ እኔ ልውጣ። እንተ ሁለት ደቂቃ ጠብቅና ሂድ፣ እሺ?»

«እንዳልሽ፣» አለ ትከሻውን እየሰበቀ። «እንቅልፌ ስለመጣ ስለምታደርጊው ነገር ማሰብም አልችል።» ሳማት።

የበረንዳውን መብራት አበራችና፣ ከዊል በተቃራኒ አቅጣጫ በፍጥነት መራመድ ጀመረች። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የጋዜጣ መሸጫ ማሽን ስታገኝ ጋዜጣ ገዝታ ወደቤቷ ተመለሰች። የሚከተላትን ሰውዬ ፍለጋ አላማተረችም፣ አንድ ስፍራ ተወሽቆ እንደሚሆን ታውቃለች። ግን ቢያንስ ዊልን ተከትሎ አይሄድም። ስለዊል ማንነት እስካሁን የማያውቅ ከሆነ ዛሬ ምሽትም ሊያውቅ አይችልም።

የዚያን ምሽት ብዙም እንቅልፍ አላገኘችም። ስታስብ አደረች።

18

ሔልደር የወሰደው ሻወር ርጥበት ሳይደርቅ በውድ የመታጠቢያ ቤት ጋዎን ተሸፋፍኖ፣ ስሜቱን ሊመረምር ይሞክራል። የኩራት፣ የማስተዋል፣ የደስታ፣ የጉጉትና ሀይለኛ የፍርሀት ስሜቶች ተደበላልቀውበታል። የለመደው ስሜት ነው።

ይህንን ስሜቱን ከዚህ ቀደም ይለማው ከነበረ ስሜቱ ጋር ለማነፃፀር ሞከረ። በባህር ሰርጓጅ ስልጠና ትምህርቱ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የማምለጫ ተገንጣይ ተንሳፋፊው ውስጥ ሲገባ፣ መጀመሪያ ለቅኝት ሲወጣ፣ በካፒቴንነት ማዕረግ መጀመሪያ ለቅኝት ሲወጣ ተሰምቶት ከነበረው ስሜቱ ጋር አወዳደረው። ከእነዚያ ስሜቶቹ ጋር ብዙም አይመሳሰልም። ይህ ስልጠና ወይ ልምምድ ሳይሆን ወታደራዊ ተልዕኮ ነው። አንድ ጥይት ባይተኮስ እንኳን ይህ የሔልደር የመጀመሪያ ፍልሚያ ይሆናል።

አሁን ይህን ስሜት ከጥንት ጊዜው አስታወሰው፣ ከመጀመሪያ የሴት ጓደኛው ጋር ሳለ የተሰማው ነበር። ከስታሊን በስተደቡብ የሚገኙ አክስትና አጎቱን ለመጠየቅ ወደእርሻቸው የሔደው በአስራሰድስት ዓመቱ ነበር። ልጅቱ በአንድ ዓመት የምትበልጠው የነሱ ልጅ ናት። የመጀመሪያውን ወሲብ

http://ethzare.wordpress.com

የሚፈፅመው ከእሷ ጋር እንደሚሆን የታወቀው ገና እንዳገኛት ነበር። ለብዙ ቀናት ስታቃልደውና ስትተሻሸው፣ ያሰበው ጊዜ እስኪደርስ በጉጉት ጠብቋል። በመጨረሻ ግዜ ከእንድ ጋሪ በሰተጀርባ ሽራ ላይ ተገናኙ። የሽራ ሽታ እስከዛሬ ድረስ ስሜቱን ይቀሰቅስበታል። አሁንም ይህ ስሜቱና ትዝታው ሲደበላለቁ የወሲብ ስሜቱ ተቀሰቀሰበት።

በሩ ላይ የጣት ጥፍሮች ሲንጣጡ ድምጽ ተሰማና ትሪና ገብታ በሩን ዘጋችው። «ስለምን እያሰብክ ነው?» አለችው እየሳቀች ከጎኑ ስር አብጦ ወደሚታየው አካሉ እያመለከተችው።

«ስለአንቺ፣» ፈገግ አለ። «ነይልኝ።»

እግረ መንገዷን ልብሶቿን እያወላለቀች ወደአልጋው ሄዳ በወፍራሙ ጋዋን ውስጥ ገብታ ተወሸቀች። «እውልቀው፣» አለች። «ይህ እንዲወልቅ እፈልጋለሁ።» አንድ እግሯን በላዩ ላይ አሻግራ ወደያውኑ ወደውስጧ አስገባችው። «መሄድህ ነው» አለች። «ነገ ልትሄድ ነው።» ቀስ እያለች ቅኝት ተከትላ ትወዛወዛለች። «መሄድ ትፈልጋለህ አይደለም?»

«አም፣» አለ፣ አልፎ አልፎ ሀያሉን ሲጠቀም ቅኝቱን እያደፈረሰ እብሯት ይወዛወዛል። «በጣም እፈልገዋለሁ። ግን አንቺን መተው አልፈልግም።»

«ትመለሳለህ፣» ስትለው ድምጿ የለቅሶ ቃናን ተላብሶ ነበር።

«አም፣ እም እመለሳለሁ። እመለስልሻለሁ።»

«ቃል ግባልኝ።»

«እመለሳለሁ።»

እንድ ላይ ርካታ ላይ ደረሱ። በኋላም በእራት ፈንታ እየደጋገሙ ፍቅር ሲሰሩ ቆዩ።

* * *

በቀጣዩ አለት ማለዳ ሔልደር ሲነቃ፣ ትሪና የለችም። ወደያውኑም በሩ በኃይል ተንኳኳ። ልብስ ፍለጋ ተደነባበረ። ሚስተር ጆንስ በፍጥነት ገባ።

«እሺ፣ ደህና እደርክ ሚስተር ስዊንስን፣» አለ በሚፍለቀለቅ ስሜት። «ዓዝህን ስታሰናዳ ሳግዝህ ነው የመጣሁት።» ትልቅ፣ ባለውህ መልክ የፐላስቲክ ፖስታ ከፍ አድርጎ አሳየው። «ሁሉ ነገር እዚህ ውስጥ ነው የሚገባው። ሁለት ሙሉ ቅያሪ ልብስ፣ አንድ ጫማ እና የግል ቁሳቁስ እንዲሁም የተሰጠህን የጦር መሣሪያ መያዝ ይኖርብህል።» ሁለት የጥይት ካርታዎች አሳየውና የፐላስቲክ ቦርሳው ውስጥ ከተታቸው። «አሁን ታጥቀህል። ከሰላሳ ጥይት በላይ የማይፈጅ ችግር ውስጥ ላለመግባት ተጠንቀቅ፣» ፈገግ አለ። ትንሽ የፐላስቲክ ፖስታ አሳየው። «ይህ፣ ያንን መሠል ሁኔታ ውስጥ ከገባህ የምትጠቀምበት ይሆናል። ፖስታውን ትቀድደውና ውስጡ የሚሟሟ ሀምራዊ ነገር ታገኛለህ። በላይኛው ድድህና በጉንጭህ መሀል አስገብተህ ትደዘዋለህ፣ ላይሟሟ ላልተወሰነ ጊዜ እዚያው ተጣብቆ ይቀራል። የከፉ ሁኔታ ካጋጠመህ እውጥተህ ታኝከውና ትውጠዋለህ። ወዲያውኑ ራስህን ትስትና በእጭር ጊዜ ውስጥ ትሞታለህ። በፍፁም አያሰቃይም፣ እንደተነገረኝ ከሆነ በጣም አስደሳች ነው። ራሴ ሞክሬው አላውቅም፣» ከት ብሎ ሳቀ። «አሁን አወላልት አለባበስህንና ዓዝ አሰነዳድህን መቆጣጠር አለብኝ።»

ሔልደር ልብሱን እውልቆ ቀሳል የመሮጫ ጫማና ልብስ ለወጠ። እንድ ውህ የማያስገባና ሌላ የሚሞቅ ጃኬት፣ ሁለት ሱሪዎች፣ ካናቴራዎችና ካልሲዎች አስገባ። የመፀዳጃ ቁሳቁሶቹን በጥንቃቄ እየመረጠ የፐላስቲክ ናይለን ቦርሳው ውስጥ ሲያስገባ ጆንስ በቅርበት ይመለከተዋል። ጆንስ ወደጠረጴዛው በማምራት፣ የስዕል ደብተር፣ ልዩ የስዕል ብዕር እና የሔልደርን የኪስ ቦርሳ ይዞ መጣ። የጠመንጃ ፈቃዱንና የዱቤ ካርዶቹን በጥንቃቄ መረመረና አንድ ወረቀት አሳየው። «ይህ ግሪንዊች ቪሌጅ ከተባለ በሰባተኛው ጎዳና ላይ ከሚገኝ የቻይናውያን የልብስ ንጽህና መስጫ የተሰጠ ደረሰኝ ነው።» ከውስጥ ኪሱ ፓስፖርት አወጣና ገለጠው። «ጥሩ ፎቶ ነው? ፈርምበት»

ሔልደር ፓስፖርቱ ላይ ፊረመና ገጾቹን እየገላለጠ መሀተሞቹን ተመለከተ። «ስዊድን የደረስኩት ዛሬ ነው?»

«በትክክል፣ ከሀገር ውጭ ጉዞ ስታደርግ የመጀመሪያህ ነው።» አለ ጆንስ።

ሔልደር ፓስፖርቱን፣ የኪስ ቦርሳውንና የስዕል መሳሪያዎቹን የፐላስቲክ ሻንጣው ውስጥ ከተታቸው። ከዚያም ጆንስ ሻንጣውን ትልቁ የፐላስቲክ ፖስታ ውስጥ አስገብቶ ዚፑን ዘጋው። «እዚያ ስትደርስ እንተ ካርል ስዊንሰን ነህ፣» አለው። «እንሒድ?»

ሔልደር በማጆሮቭ የጎልፍ ጋሪ ከጆንስ ጋር ከውህው ጋር ተመሳስለው ወደተሰሩት የሰርጓጅ መርከብ ማኖሪያዎች በኮረብታ ቁልቁል ተጓዙ። ዘቦቹ በሮቹን አልፈው እንዲገቡ ምልክት ሲሰጧቸው ጆንስ ጋሪዋን ወደተንሳለለው የሰርጓጅ መርከብ መጠለያ አስገብቶ አቆማት። ማጆሮቭ ሰላምታ ሲሰጣቸው መጣ።

«ደህና እደርክ ሔልደር፣» አለ ብሩህ ፈገግታ እያሳየ። «ጆንስ እንጻዘጋጀህ ገብቶኛል።»

«እንዴታ ጌታዬ ዝግጁ አድርጎኛል፣» መለሰ ሔልደር። «አዲስ ሰው የሆንኩ ያህል እየተሰማኝ ነው።»

«ጥሩ ጥሩ፣ አሁን መጥተህ ጓዝህን ተመልከት። «ብሉ ማጆሮቭ መጠ ለያውን አቂርጦ እየመራቸው የከንከሪት ደረጃዎቹን ወርዶ ወደጁልየት ደረጃዋ ሰርጓጅ መርከብ ወሰዳቸው። የፊት ለፊት በሯ ክፍት ነው፣ ትንሿ ሰርጓጅ መርከብ ቦታዋን ይዛለች፣ ከፊት ለፊቷ ሔልደር ሲሰለጥንበት ከነበረው ጓዝ በስፋት ትንሽ የሚበልጥ ተንሳፋፊ ክብና አጭር በርሜል መሳይ ነገር ተቀምጧል። እንደተለማመደበት ተመሳሳዩ ክብረት የተሰራ ሳይሆን ከዚህ በፊት ተመልክቶት የማያውቀው ፕላስቲክ መሰል ቁስ ሽፍኖታል። በግራና ቀኙ የትንሿን ጠላቂ መርከብ መቆንጠጫዎች የሚገጥሙ ማቀፊያዎች አሉት።

ሔልደር የትክክለኛው ሽክም መጠን ከመለማመጃው መብለጡ አሳሰበው።

«ክብደቱ ምን ያህል ነው?» ጠየቀ።

ማጆሮቭ ለአፍታ ያህል ንዴት ታየበት። «ከመለማመጃው በስድስት ኪሎ ያህል ይበልጣል። እንደማያስቸግርህ እተማመናለሁ።»

ሔልደር ግን ሙሉ በሙሉ በራሱ አልተማመነም። አይነት አራት (Type Four) የመቆጣጠሪያ ሀይሎጅን በሙሉ ተጠቅማ ባለፈው ስልጠና ላይ ባላት ሀይል ሁሉ ስትንቀሳቀስ እንደነበር ተሰምቶታል። በትክክለኛው ሽክም

http://ethzare.wordpress.com

እስካልሰራ ድረስ ርግጠኛ ሊሆን አይችልም፣ ማጆሮቭ ደግሞ መዘግየትን የሚፈቅድ አይመስልም። ሊናገር ሲል የቫለሪ ሶኮሎፍ ድምጽ ከኋላው ተሰማው።

«ምንም ችግር አይኖርም ኮሎኔል፣» አለች በጠጣር ድምፅ።

ሔልደር ፊቱን አዙሮ ቢገላመጥም አላናገራትም። «ልቆጣጠረው የምችል ይመስለኛል ጌታዬ፣» አለ።

«መልካም፣» መለሰ ማጆሮቭ። «አሁን፣ እንጀምር። ሶኮሎፍ መቆንጠጫዎቹና ማቀፊያዎቹ በትክክል ይገጥማሉ?»

«እምን፣ ኮሎኔል። ሁሉም መልካም ነው።»

«ከሆነ ጓዙን ሜኑታ።»

ሶኮሎፍ ሙሉ የሰውነት መሸፈኛ ለብሰው አቅራቢያቸው ለቆሙ ሶስት ሰዎች ምልክት ሰትሰጥ ከባዱን ሽክም እየገፋ ወደትንሿ ጠላቂ መቆንጠጫዎች አስጠጉት። ሔልደር፣ ሰዎቹ ቢጫ የጨረር መመርመሪያ ፋሻዎችን ማጥለቃቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከተ። ከባድ የጨረር መጠን ካገኘ ፋሻው ወደሰማያዊነት ይለወጣል። ማጆሮቭ እንዳለው ጓዙ የዩራኒየም 235 ዝቃጭ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ጥንቃቄን ባልፈለገ ነበር፣ ግን በጥንቃቄ የተነሳ ጠብ መፍጠር አልፈለገም። ሶኮሎፍ አይነት አራት ጠላቂዋ ውስጥ ገብታ መቆንጠጫዎቹ ከማቀፊያዎቹ እስኪዋደዱ ድረስ ስታስተካክል ቆየች። ከዚያም የጠ ላቂዋንና የሶስቱን ሰዎች ሀይል በመጠቀም፣ ጓዙን አንስተው ሔልደር ወደውጭ ከሚመለከትበት መስታወቷ ስር ካለው መጫኛ ላይ አስቀመጡት። ከውሀ ስር ሲገቡ የጓዙ ክብደት ስለሚቀልል ያለሰዎቹ እርዳታ በጠላቂዋ መቆንጠጫዎች ብቻ ማንቀሳቀስ እንደሚችሉ ተሰሩ አደረገ።

ሶኮሎፍ ከጠላቂዋ ውስጥ ስትወጣ የጁልየት እናት ሰርጓጁ በር እያቷጨ ተዘጋ። የጠላቂዋ ተቆጣጣሪ ወደ ማጆሮቭ መጥቶ ሰላምታ ሰጠ። «ወደ ቀጣዩ ርምጃ ለመሸጋገር ተዘጋጅተናል፣ ኮሎኔል።» አለ።

«ግሩም ነው ካፒቴን፣» አለ ማጆሮቭ በፈገግታ። ወደ ሔልደር ዞሮ እጁን ያዘው። «እሺ ሔልደር፣» አለ በጋለ እንደበት። «አሁን ስትሰለጥንበት የቆየኸውን ለመፈፀም ዝግጁ ነህ። በጥሩ ሁኔታ እንደምታከናውነው አውቃለሁ።» ማጆሮቭ ወደሶኮሎፍ ተመለከተና የሔልደርን እጅ ጨመቅ አደረገው። «የተሰጡህን መመሪያዎች በሙሉ አስታውስ።»

«አስታውሳለሁ፣ ኮሎኔል፣» አለ ሔልደር። «ይህን እድል በማግኘቴ አመሰግናለሁ።»

«መልካም እድል፣ ሶኮሎፍ፣» አለ ማጆሮቭ እየጨበጣት።

ሔልደርና ሶኮሎፍ የዋና ሰርጓጇን ተቆጣጣሪ ተከትለው ወለሏ ላይ እንደወጡ ሁለት ሰዎች ጠባቡን መሸጋገሪያ ግውላ አነሱት። ቆልማማው ሰገነት ላይ ወጡና ሰርጓጇ ከማረፊያዋ የኋሊት መንቀሳቀስ ስትጀምር በቆሙበት ቀሩ። ወደኋላ ዞራ ፊቷን ወደሐይቁና ባሻገሩ ወደአለው የባልቲክ ባህር ስታዞር፣ ሔልደር የአንደኛ ደረጃ ካፒቴን ልብስ ለብሶ ከማጆሮቭ ጋር የሚነጋገር አንድ የሚያውቀው ሰው ተመለከተ። ሔልደር ሰውየውን ማየቱ እስደንግጦታል እንደውም መጀመሪያ ላይ የተሳሳተ መስሎት ነበር። ከዚያ ግን ሰውየው ከማጆሮቭ ጋር ለመነጋገር የጎንዮሽ ሲዞር ትክክል መሆኑን አወቀ። በሰርጓጅ መርከብ ትቢት ውስጥ አብረው ነበሩ፣ ባለፉት አመታትም ሙርማስክና እኔ ሌሎች ወደቦች ላይ በአጋጣሚ ተገናኝተዋል። ስሙ ጉሺን ሲሆን በሶቭየት ባህር

ሀይል ውስጥ እጅግ ዝነኛ ወይንም ዝናቢስ ከሚባሉ መኮንኖች አንዱና ዋንኛው ነው። በኦክቶበር 1981፣ ከሚስጥራዊ የስዊድን ባህር ኃይል ጦር ሰፈር አቅራቢያ የውስኪ ማዕረግ ያላት ሰርጓጅ መርከብን ያንቀሳቅስ ነበር። ለአንድ ሳምንት ያህል ሰርጓጅ መርከቧ ተይዛ እዚያው ቀረች። በተያዙት ሰርጓጅና የሶቭየት ባህርተኞች ቡድን ጉዳይ ላይ ሶቭየቶችና ስዊድናች ድርድር አደረጉ። በመጨረሻ፣ ሶቪየቶች ሰርጓጇ በተወሰነ ደረጃ እንድትፈተሽ ፈቀዱና ከምድር ተጎትታ በሶቭየት መርከቦች ታጅባ ወደሀገሯ እመራች።

ማንኛውንም የሶቭየት የባህር ሀይል መኮንን ይህን ታሪክ ያውቃል። ጉሺን ማዕረጉ ተገፎ በውርደት ከሶቭየት ሠራዊት ተባረረ፣ ጉላግ ውስጥ ረጅም የትልበት ሥራ እስርም ተፈረደበት። የእሱ ስም ብቃት ስለሌለው መኮንን የሚሰጥ ቅፅል ስም ሆኗል። ግን፣ አሁን የሙሉ ካፒቴይን ዩኒፎርም ለብሶ፣ የሶቭየት ባህር ሰርጓጅ ተልዕኮዎች በስዊድን ጠቅላይ አዛዥ ጋር በቅርብ እየተነጋገረ ነው። ሔልደር በጁልየቷ የሰገነት መሰላል ሲወርድ ግራ መጋባት ነግሶበታል። የሰርጓጅ መርከቧ አዛዥ ከውሀ በታች ለመጥለቅ ትዕዛዝ ሰጠ።

ምን እየተፈጠረ ነው?

19

ሩል እሁድ ጠዋት በመኪናዋ ወደናሽናል እየር ማረፊያ በማምራት ወደኒውዮርክ የሚበር የምስራቁን አውሮፕላን ተሳፈረች። ከማላከሆቭ ጋር ስላላት ቀጠሮ በደስታ እያሰበች የኋላ ማሳያ መስታወቷን ለመመልከት አልተጨነቀችም። አይሮፕላኑ ኒውዮርክ ውስጥ ከማረፉ ከጥቂት ጊዜ በፊት ወደመፀዳጃ ክፍሉ ለመሄድ ተነሳች። በአይሮፕላኑ መተላለፊያ ጎማሽ ላይ ስትደርስ ባለችበት ደርቃ ቀረች። ከመስኮት አጠገብ በሚገኝ መቀመጫ ላይ፣ ያ ሲከተላት የነበረ ሰውዬ ተኝቶ ያንኮራፋል። ለጥቂት ሰከንዶች ቆም ብላ እየተመለከተችው፣ ገፅታውን በህሊናዋ ማህደር እየመዘገበች ቆየች። አምስት ጫማ ከዘጠኝ ወይ ከአስር ቁመት ገመተችው፣ ክብደቱ ቢበዛ መቶ ዘጠና ሲሆን ጥቂት የኩፍኝ ቁስል ቀሪጀቶች ያለበት የገረጣ ፊት አለው፣ ፀጉሩ የተቆረጠው እንደነገሩ ሲሆን ከበላዩ ተመልጦ ሊያልቅ ጥቂት ቀርቶታል። ታጥቦ የሚለበስ የበጋ ሙሉ ልብስ ለብሷል፣ እድሜው አርባ አምስት ገደማ ሲሆን፣ በዋሽንግተን የምስራቅ አውሮፓ ኤምባሲዎች ውስጥ አስቀያሚ የሚባሉትን ስራዎች የሚሰሩ ሰላይዎችን ይመስላል። ምናልባትም ጥርሱ ያለቀና መጥፎ የጥርስ ህክምና የተደረገለት ይሆናል። አጠገቡ ባለው ባዶ ወንበር ላይ ተቀምጣ ከእንቅልፉ ሲነቃ ልታስደነግጠው አስባ ተወችውና ወደ መታጠቢያ ክፍሉ መራመዷን ቀጠለች።

ላ ጉዋርዲያ እየር ማረፊያ ላይ ከመቸኮሏ የተነሳ ከሰገነቱ ጋር ተላተመች ከተከታታይዋ ተሰውራ የኒው ኢንግላንድ የበርሊንግተን እየር ለመሳፈር ያላት ጊዜ ከእንድ ሰዓት በታች ነው። የታክሲ ሰልፉ ላይም ከሱ በተቻላት ርቃ ቀድማው መሰለፍ አለባት። አልሆነላም። ታክሲዋ መንቀሳቀስ ሲጀምር፣ ለራሱ ታክሲ ሾፌር ገንዘብ ሲሰጠውና፣ ቀጣዩ የታክሲ ሰልፈኛ በዚህ ሰልፉን የማይጠብቅ ታክሲ ላይ ቁጣውን ሲያዘንብበት ተመለከተች። ለሹፌሯ ገንዘብ ሰጥታ ከኋላዋ ያለውን ታክሲ እንዲሰወርበት ልትነግረው አሰበች፣ ግን

http://ethzare.wordpress.com

ተኪታይዋ እንደሚከተላት ግመቷን እንዲያውት አልፈለገችም። «ወደ ሚትሮፖሊታ ሙዚየም፣ አለች።

የመኪና ጭንቅንቅ የለም ህዝርና ከማግሽ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ የተባለው ዩታ ደረሱ። በስፋፊ ደረጃዎቹ ላይ እየተጣደፈች ወደኋላዋ ሳትመለከት ወደሙዚየሙ ገባች። ክኋላዋ እንደሚናር አውቃለች። በአባሳት ጠረጴዛው ላይ የአባልነት መታወቂያዋን አሳይታ የመግቢያ የደረት ምልክት ተቀበለች። እሱ ግን የአባልነት መታወቂያ ስለግይናረው ከሌላው ሰው ጋር ትኬት ለመግዛት እንደሚሰለፍ ርግጠኝነት ተሰምቷታል። በፍጥነት ዘቡን አልፋ ወደ አዳራሹ መሀል ዘለቀችና ቆሎ ወደቀኝ ታጥፋ ሙዚያሙ መደብር ውስጥ ገብታ ትጠ ባበቅ ጀመረች። ሰልፉ ረዝም ሳይሆን አይቀርም፣ ከአምስት ደቂቃ ገደማ በኋላ ኑውራቱን ከአንድ የግሊያ ሳጥን መስታወት ላይ ተመለከተች። እያተጣደፈ አልፏት ጄደ። ግራ ተጋብቶ ተስፋ አስኪያጣ ድረስ አሰራ አምስት ሰክንዶች ያህል ሰጠችውና ከመደብሩ ወጥታ ሙዚያሙን ለቅቃ ሔደች። እዚህ ስፍራ ተከትሏት መግባቱ ቂልነቱን አሳያት። አንድ መግቢያ ባለው ሕንፃ ውስጥ ስትገባ በሩ ላይ ሆኖ መጠበቅ ነበረበት። እንዲት ሴትንና ሶስት ልጆችን የሚያራግፍ ታክሲ እግኝታ በሌላ ግማሽ ሰዓት ወደላጉዋርዲያ ተመለሰች። ሰውየው እንደግይከተላት አረጋግጣለች። ተባባሪ እንደለሌውም አውቃለች። አደርፐላኑ ላይ ስትወጣ፣ በረጅሙ አየር እየሳበች ራሷን ለማረጋጋት ሞከረች። የሚከተላትን ሰው ልትሰወርበት ባትችል ኖሮ የበርሊንግተን በረራዋ ስለሚያመልጣት ከማላከፉቭ ጋር የነበራት ቀጠሮ ላይ መገኘት ባልቻለች ነበር።

በርሊንግተን ስትደርስ መኪና ተከራይታ ወደ ስቶዊ አመራች፣ አነዳሷን ከጊዜው ጋር እያመጣጠነች ነበር። በክረምት ወራት የበረዶ መንሸራተቻ ሆነው የሚያገለግሉ ያገጠጡ የተራሮች ጎኖችን አልፋ፣ ለቢጋው የተዘጉትን በተራራ ቅርፅ የተሰሩ ሞቴሎችን አልፋ ተጓዘች። ወደደቡብ የሚወስደውን መንገድ አገኘችው፣ የቴክሳኮ ነዳጅ ማደያ አይታዋን ሲገባ አንድ ሰዓት ደቂቃ ጠበቀችና ወደጣቢያው ለመድረስ የቀራትን ጥቂት መቶ ርምጃዎች ተጉዛ መኪናዋን አቆመች። ከእሷ ሌላ መኪና የለም። ከመኪናዋ ወጥታ ነዳጅ ሞላች፣ ታንከሯ ለመሙላት ሩብ ያህል ብቻ ይቀረው ስለነበር ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም። እየሞላች ግን የሚጠብቃትን ሰው ፍለጋ ላይ ታች ታማትራለች። መንገዱ ግን ፀጥ አረጭ ብሏል። ወደግደያ ጣቢያው በግምራት የነዳጅ ሒሳቧን ከፍላ ስትመለስ፣ መንገዱ ጥግ የቆመ ቢጫ ጂፕ መኪና ተመለከተች። ሹፈሩ ቦታ ላይ ኤድራውስ ተቀምጧል። ምንም ምልክት ሳይሰጣት ወደ ደቡብ አቅጣጫ ተፈተለከ። በችኮላ ወደ መኪናዋ ገብታ ከአይታዋ ሳይጠፉ ግን በርቀት እየተከተለችው ማሽከርከር ጀመረች። በስተደቡብ አቅጣጫ የሶስት ወይ የአራት ማይል ርቀት ስትከተለው ቆየች። በአምስት ወይ በስድስት ደቂቃ ጉዟቸው ላይ ሌላ ምንም መኪና ያለማየድ ገርሟታል። በበረዶ መንሸራተቻ ከተሞች የበጋ እሁድ ቀን ጭር ያለ መሆኑ ታሰባት።

ራውልስ ወደ ግራ ታጠፈ፣ ከዚያም ወደቀኝ ወዲያውኑ መንገዱን በመተው ከአንድ አነስተኛ ቀይ የትምህርት ቤት ህንፃ ፊት ቆመ። ህንፃው የጎፋስ አትጣጫ ጠጭሚ ያለውና በነጭ የተከፈፈ የደወል ሰንጉት ይታይበታል። ሩል ከምትኖበት የአንድ ማይል አንድ አራተኛ ርቀት ላይ ኤድ ከመኪና

ወርዶ ወደትቢቱ ሲያመራ ተመለከተች። እሷም መኪናዋን ከሺፑ አጠገብ አቁማ ወጣች። ቀኑ ሞቃት፣ ፀሐያማና ረዥ ያለ ነው። ከህንፃው በላይ ያለው የአየር ሁኔታ ጠጭሚ ወደ ምስራት ተስቱን ወድር ላይኔታንት ተጋድሟል። የፊት ለፊቱ በር ወለል ብሎ ተከፍቷል። ሩል ዘልቃ ገባች። አጭር አሪደርን አልፋ አንድን የተዘጋ በር ከፈተችና አንድ የትምህርት ክፍል ውስጥ ገባች። ሕንፃው በትምህርት ቤትነት ማገልገሉን ግቶ በግልፅ ይታያል። ወስተቆጂ ከፍ ብሎ የተሠራ መድረክ ሲኖር በአስተግሪ መንበርና ወረዲፃ ፋንታ፣ እውን ወደአነስተኛ ኩሽናነት ተለውሟል። ባይው የትምህርት ቤት ክፍል እውን አስራ ሁለት የሚሆኑ በቆጻ የተሰበሙ ቁሳቁስ ይሟል። በክፍሉ ዙሪያ ያሉት ተቁር ሰሌዳዎች አሁንም ቦታቸው ላይ ናቸው። በአንድ ጥግ ጎድጓዳ ሠድ ያለው የእንጨት ግብስያ ተቀምጧል። የግተጀተጣው በር ሲከፈት አይኖጀ ወደኩሽናውና ወደ መድረኩ ተሰረቁ። እድ ራውልስ ነገስ ብሎ የመደርደሪያውን የታችኛው አካል በአይኖቹ ይፈትሻል።

«ቢራ ትፈልጊያለሽ?» አላት።

«ለስላሳ አለ?»

አረንጓዴ የቢራ ጠርሙስና የክክላ ቆርቆሮ ይዞ መድረኩን በግጺረተ ወዳለችበት አመራ። «ድምፅ መቅረጫ ይዘሽዘል?» ሲል ጠየቃት፣ የመድረኩን ደረጃዎች ወርዶ ለስላሳውን እያቀበላት።

«አልያዝኩም።»

«ጥሩ። ማስታወሻ መያዝም አትችይም። ቦርሳሽን እዚው ተይው፣ ጀሚ ሩል ይህ ከባድ መረጃ ነው፣ ከዚህ የምታገኚውን ነገር ወድርጅቱ ውስጥ በምታተርቢው ሪፖርትም ሆነ ንግግር ላይ መጠቀም አትችይም፣ ገባሽ?»

ሩል ራሷን በእሺታ ወዘወዘች። ውይይታቸው ይህ ገደብ ላይጣልበት ደስ ይላት ነበር፣ ግን ራውልስም የራሱን ደህንነት መጠበቅ ይናርበታል። ይህን ተገንዝባለች። ቦርሳዋን መድረኩ ጫፍ ላይ እንራ ተከትላው ወደፈትለፈቱ በር ተመለሰች። ከዚህ ቀደም አልፋው የመጣችው በር ላይ ደርሶ ቆመ። «ግን እንደሆንሽና ምን እንደምትፈልጊ አያውቅም፣ ግን ከዚህ ተነስቶ የሚደርፀት ስፍራ የሚወሰነው ለእንቺ በሚሰጣቸው መልሶች ሊሆን እንደሚችል ጠርተጅል።

«ለዚህ አመሰግናለሁ ኤድ፣» አለች።

«እሷኋኑ ተለውጧል፣ ራሱን በከረጢት ልሸፍነው አስቢ ነበር፣ ግን ያንን ባደርግ ናሮ ተፈላጊ ሰው ነሽ ብሎ ባሳሰበ ነበር። ደረጃዝን ከፍ ለማድረግ ብዙ አይኑን በዉርቅ ለመሸፈንም አስቢ ነበር፣ ከዚህ ቀደም ባደረጋቸው ቃለ መጠይቆች ወቅት ግን ይህን ማድረጌ እንብዙም አልተሳካልኝም። የሚናንረውን ሰው ማየት ከቻለ፣ ምቾት ይሰማዋል፣ የበለጠ ያመራል፣ የምልክት ንግግር ጫጠ ቀምም ይተዋል። ይህ የተለመደ ሁኔታ ይመስለኖል። ለረጅም ጊዜ ግፅረግ ይዞ በመቆየቱም ለክብር ምላሽን ይሰጣል። ከመጀመሪያው እንስቶ እንደክፉ የምራ ባልደረባዬ እንጂ እንደክፎ ስለግልመለከተው፣ ውጤት አስኝተልኖል። ከሌሎች በጣት ከሚቆጠሩ ግለሰቦች ጋር ስለግንኙነት ላይንስ (Communication) እና ስለ ኮምፒውተር አካላት ተወያይቷል። ግን ዘጠና በመቶ ውይይቱን ያደረገው ከኔና ከመቅረፅ ድምፅ ጋር ብቻ ነው። እዚህ ስፍራ ላይ ፎት ከምታዩዋውና ምንብ ከምታስለው ወይዘር በስተቀር ከሴት ሲኖኝ እንዲ

http://ethzare.wordpress.com

የመጀመሪያው ነሽ። የወሊብ ፍላጎቱ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ያታዊ ሀይልሽን በመጠ ቀም ልታግባቢው ትችያለሽ። ማለቴ ነገሩ አላፋሪ መስሎ ካልታየሽ።»

ሩል ይህን አባባሉን ችላ አለችና፣ «ሲዋሽ የሚታይበት ልዩ ምልክት አለው?» ይሄው አላውቅም። የሚዋሽ ከሆነ ተከናበት ስለሚሆን ልዩ ምልክት አያሳይም ሌላ ነገር የቀረ አለ?»

«የለም።»

«እሺ።» ራውልስ ሰዓቱን ተመለከተ። «ወደኒውዮርክ የሚበረውን የመጨረሻውን አይሮፕላን መያዝ ካለብሽ ከዚህ የምትነሺው ከአርባ ደቂቃ በኋላ ይሆናል።»

«እሱም ወዲያው ከዚህ እንደሚነሳ ገምቼያለሁ።» ማላከሆቭ ይህን ቦታ ሊለቅ ባይዘጋጅ ኖሮ እዚህ እንድትመጣ እንደማይፈቅድላት ታውቋታል።

ራውልስ ፈገግ አለ። «አንቺ አየር ማረፊያው ከመድረስሽ በፊት ይህንን ክፍለ ግዛት ለቅቆ ይሄዳል።» በሩጌ ከፍቶ ወደኋላ ራቅ አለ። «መልካም እድል።»

ሩል ወደውስጥ ስትገባ፣ በሩ ከኋላዋ ሲዘጋ ተሰማት።

20

ሔልደር አይኖቹን ከፍቶ ያዳምጥ ጀመር። የሰርጓጅ መርከቧ መለስተኛ የማላዘን ድምፅ፣ ቢሔልሰንኪ-ስቶኮልም ተጓሂ የዕቃ አመላላሽ መርከብ ሞተር ጩኸት ተውጧል። መርከቧና ሰርጓጇ እንደ እናትና ልጅ አላ ነባሪ በጥቂት ሜትሮች ርቀት ላይ ላይና ታች ይንሳፈፋሉ። ሁለቱም በስቶክሆልም በደሴቶች የተከበበ የውሀ ክልል ላይ አቋርጠው ተከታትለው እየተመሙ ነው።

ሔልደር ከኮሪደሩ አቅጣጫ የሰው ዱካ የሰማ ቢመስለውም እሱ ዘንድ ግን የመጣ ሰው የለም። ሰዓቱን ተመለከተ። ጊዜው ደርሷል። ለሊቱን ሙሉ በሰመመን ነው ያሳለፈው። ከተልዕኮው ሌላ ነገር ለማሰብ አይኖቹን ከድኖ ሲጥር ነው የነጋው። ትሪና ራጉሊን ወደሀሳቡ ከዘለቀችባቸው ጊዜያት በስተቀር ግን ሌላ ነገር ማሰብ አልተቻለውም። በሚቀጥሉት ስምንት ሰዓታት ውስጥ ከእሱ ሊጠበቁ ስለሚችሉ ርምጃዎችና ድርጊቶችን ሁሉ ጠንቅቆ በተደጋጋሚ ሽምድጿቸዋል። አሁን ያለካርታው ርዳታ መድረሻ ነጥቡን ማግኘት እንደሚችል ተሰምቶታል። ቻርቱ ሀሊናው ውስጥ ታትሟል። እያንዳንዱ ተንሳፋፊ ምልክት፣ ጥልቀት ያለውና የሌለውን ስፍራ እያንዳንዱን ጠንቅቆ ያውቃል። የትኛውም የሶቪየት መኮንን ለአንድ ተልዕኮ ከዚህ በላይ ተዘጋጅቶ እንደማያውቅ ርግጠኛ ሆኗል። ይህም ሆኖ ግን የፍርሀት ውጋቱ ያለማቋረጥ ይጠቀጥቀዋል። ከቀበሮ ጉድጓድ ላይ ቀና ሲል ጠላቱ ወዳለበት ሲገሰግስ የተመለከተ ወታደር ይህ ስሜት እንደሚሰማው ታውቆታል ይህን ስሜቱን ሊቆጣጠርበት የሚችልበት ብቸኛ መንገድ አፍኖ በማስቀረትና የታዘዘውን ለማስፈፀም ቁርጥ ውሳኔ ላይ በመድረስ መሆኑን አምኖበታል። ደህንነት ብሉ ነገር ይቅርበት፣ ደግሞስ ሰዎች ለብዙ ምዕተ ዓመታት ራሳቸውን ወደፍልሚያ ሲያስገቡ የኖሩት ደህንነታቸውን ችላ በማለት አይደለም እንዴ?

ዳሩ ግን እዚህ ውሳኔ ላይ በደረሰ ቁጥር፣ ትሪና ወደሀሳቡ ትመጣና ታፈርስበታለች። እና እንደገና «ሀ» ብሎ ይጀምራል። በወደፊት ሕይወቱ ብዙ

የሚጠብቀው አስደሳች ነገር ስላለ ደህንነቱን ችላ ማለት አይችልም። ማሊቡ ላይ እየጠበቀችው ነው፣ ይህ ሀሳብ ከተልዕኮው በልጦ እንዳይታየው ለማድረግ ተፍጨረጨረ።

ጸጋመኛ የኮቴ ፯ጥ፯ጥታ ሰማ። አሁን ግን አልተሳሳተም። ሔልደር እግሮቹን በድንክ አልጋው ላይ አውርዶ ወለሉ ላይ እንዳኖረው፣ መጋረጃውን የገለጠው ባህርተኛ መናገር ጀመረ።

«ጊዜው ደርሷል፣ ጌታዬ። ከእቃ ጫኝ መርከቧ ተለይተን ወደታች እየጠለቅን ነው።»

«ከትንሽ ጊዜ በኋላ አብሬው እንደምሆን ለካፒቴኑ ንገረው።» አለና ሔልደር የመሮጫ ሚማና ልብሱን ቀይሮ የተመሰነ ትርፍ ሙቀት ካስፈለገው በሚል ትከሻው ላይ ወፍራም ጃኬት ጣል አደረገ። የድንገተኛ እደጋ ልብሱን የያዘውን ትልቅ የፕላስቲክ ከረጢት አንድ ክንዱ ስር የካርታ መያዣውን ከሌላኛው ክንዱ ስር አስገብቶ ወደኮሪደሩ አመራ። ቫለሪ ሶኮሎቭ በተመሳሳይ ሂኔታ ታጥቃ ከእፍታ በኋላ ከአጠገቡ ከሚገኘው ሌላ መኝታ ክፍል በመውጣት ተከተለችው። ለቅዕበት ያህል መልክት ያደረገው የተከፋና የተኮሳተረ ገፅታዋ አላስደሰተውም። ሳትሰናከል ይህን ተልዕኮ እንደምትወጣ ተስፋ አደረገ። ነገሮች ካሰገደዱት፣ እንዲገድላት ከማጆሮቭ የተሰጠውን ትዕዛዝ መፈፀም ይችል እንደሆነ አሰበ። ምንም ይሁን ምን እንድን ሰው ያለምክንያት ሳያስበው መግደሉን አልፈቀደም።

ቁርስ ተዘጋጅቶ ወደሚጠብቃቸው ማረፊያ ክፍል ፊት ለፊት እየመራ ገባ። ትኩስ ቮርባ፣ በጭስ የደረቀ ጥንቸል፣ ጥቁር ዳቦና ሻይ ተዘጋጅቶላቸዋል ደስ ብሉት ተመገበ፣ አመጋገቡ አስገርሞታል። ሶኮሎቭ ግን ነካክታ ተወችው። ብዙም አልተነጋገሩም። ሔልደር ቶሎ ምግቡን ጨርሶ ተነሳ። «ዛሬ መብላት ከፈለግሽ ከአሁኑ የተሻለ ጊዜ አታገኚም፣» ብሏት ከክፍሉ ወጣ። ከአስር ደቂቃ በኋላ ተመለሰ። ካፒቴይኑ ወደማረፊያ ክፍሉ ገባ።

«አንተ በተዘጋጀህበት ጊዜ እኛም ዝግጁ እንሆናለን፣» አለ ሔልደር።

ካፒቴይኑ የመስማማት ምልክት ሰጠው። «ገብታችሁ ቦታ እስክትይዙ ድረስ እኛ የውሀ ውስጥ ራዳር ቅኝታችንን እናጠናቅቃለን። በዙሪያችን ምንም ነገር ከሌለ ጉዞ ትጀምራላችሁ።»

ሔልደር ፊት እየመራ እናት ሰርጓጇን አቋርጦ «አይነት አራት» ሰርጓጅ ፓልባቸው ወደምትገኝበት በልዩ ሁኔታ ወደተዘጋጀው የማስወንጨፊያ ክፍል አመራ። መጀመሪያ ሶኮሎፍ እንድትሳፈር ምልክት ሰጣት፣ ከዚም በመሰላሉ ሽቅብ ተከትሏት ወደላይኛው በር አመራ። ከረጢቱንና የቻርት መያዣውን ከስሩ ካለው መቀመጫ ላይ ጣለና እግሮቹን ወደሰርጓጇ ሰደዳቸው። ልክ ዘሎ ሊገባ ሲዘጋጅ አንድ ነገር አይኖቹን ሳበው። በክፍሉ ወለል ላይ የወደቀና ጓዙን ይጭኑ የነበሩት ሰራተኞች እጥለቅለቀዋቸው ከነበሩት ቢጫ ባንዲጆች መሀል አንዱ ነው። አሁን ግን ቢጫ አይደለም፣ ሰማያዊ ሆኗል።

«ጌታዬ፣» ሲል ከመርከቧ ሰራተኞች አንዱ በተከፈተው በር በኩል ጮኸ ተናገረ፣ «ተቆጣጣሪው መነሳት ትችላላችሁ ብሏል። ገብታችሁ እንደጨረሳችሁ ውሀውን እንለቀዋለን። መልካም ዕድል።»

ሔልደር የተረበሸውን ልጅ ጩኸት ስላልጠበቀው ደነገጠ። ሁለት እውራ ጣቱን አሳይቶት መስማማቱን ከገለፀለት በኋላ፣ ትንሿ ሰርጓጅ ውስጥ

http://ethzare.wordpress.com

ገብቶ የላይኛውን በር ዘጋውና፣ የግራት መስጫውን መዘውር እሽከረከረው። ከረጢቱን ከመቀመጫው ስር ወሽቀና ትንሿን የካርታ ማኖሪያውን ከፈተ። አንዱን ካርታ ከርኑ አጠገብ ባለው ጠረጴዛ ላይ በመቆንጠጫ እንዳያያዘ፣ አንድ ጉድባ ተከፍቶ ውሃው ትንሿ ሰርጓጅ ወዳለችበት አካል ሲገባ ድምፅ ተሰማው። ከሶኮሎፍ ጋር ለመጪረሻ ጊዜ የተልዕኮውን ቅደም ተከተል መረመሩ። ይህንን ያደረገው ሁሉ ነገር ቦታውን መያዙን ለማረጋገጥና እሷንም ለማረጋጋት በማሰብ ነበር። ቁልፎቿን ስታበራራ ተሰማው፣ ከዚያም ቀይ መብራቶቹ ወደአረንጓዴ ተለወጡ።

«ዋናው መቆጣሪያ ላይ አልጠፉ ያሉኝ አንድ ቀይ መብራት አለ፣» አለች ሶኮሎፍ ድንገት። «ይህ ማለት መቆንጠጫዎቹ አይሰሩም ማለት ነው።»

ሔልደር በሆዱ ተራገመ፣ መቆንጠጫዎቹ አይሰሩም ማለት ተልዕኮው አይሳካም ማለት ይሆናል። «ሳጥኑን ፈትሺው፣» አለ በረጋ አንደበት። «ምናልባት ሀይድሮሊኩ ሳይሆን ማብሪያ ማጥፊያው ብቻ ይሆናል የተበላሸው።»

ግድግዳው ላይ ከሚገኝ ክፍተት ውስጥ መፍቻ ለማውጣት እጇን ስትዘረጋ በስተቀኙ ተመለከታት። «አንድ ጊዜ ቆየኝ፣» የማብሪያ ማጥፊያው ሳጥን ተከፍቶ መልሷ እስኪደርሰው በጉጉት ይጠብቅ ጀመር። «አዎ፣ አዎ!»አለች። «ማብሪያ ማጥፊያው ነው፣ ከቦታው የተላቀቀ ገመድ አለ።»

«ታዲያ ጠግኚዋ፣» አለ ሔልደር ትዕግስት ባጣ መንፈስ። ውሀ የፊትለፊቶቹን የዋናዋን ጀልባ ወለሎች አጥለቅልቋቸዋል። የትንሿ ሰርጓጅ አካል በከፊልም እውሀው እየጠለቀ ይገኛል።

«ተስተካክሏል፣» አለች ሶኮሎፍ፣ አንደበቷ ላይ የተወሰነ የድል አድራጊነት መንፈስ እየተነበበባት። «መብራቶቹ ሁሉ የእንቅስቃሴ ዝግጁነት አረንጓዴ እያበሩ ነው።» አሁንም እጇ ወደፊት ተቀሰረና መፍቻውን ቦታው መለሰች።

ከበስተጓላቸው አንድ ስፍራ ላይ ለስለስ ያለ የሚያቋጭ ድምፅ ተሰማ። የማስወንጨፊያና የማሳረፊያ ክፍሉ መዝጊያ በዝግታ ተከፈተና ዝርግ የበሩ ብረት ተዘርግቶ ወለሉ ላይ አረፈ። ሔልደር የትንሿን ሰርጓጅ የፊት ለፊት አምፖሎች አብርቶ የሀዲዱን ታኮ ከፈተው። የሀይል መቆጣጠሪያውን ወደፊት ሲገፋው ሰርጓጇ ከክፍሉ ወጥታ ትራልሀቬት በተሰኘው ሰርጥ ውስጥ ገባች። ከእናት ሰርጓጇ ሙሉ በሙሉ እንደወጡ፣ ትንሿን ሰርጓጅ አቆመና የሀዲድ እግሮቿን ሀይል አጠፋው። ለዚህ የሚያስፈልገው ሀይል ዋናውን ሞተር ከሚያንቀሳቅሰው ሀይል በሶስት እጅ ያይላል። የፊት ለፊት ፓውዛዎቹንም ሞምር አጠፋቸው። «አስር በመቶ የመጥለቂያ ሀይል፣» አለ ለሶኮሎፍ።

«አስር በመቶ የመንሳፈፊያ ሀይል፣» ብላ ደገመችለትና፣ የራሷን መቆጣጠሪያ መነካካት ጀመረች። ሰርጓጇ መንቀሳቀስ አልጀመረችም።

ያ የተረገመ ስልሳ ኪሉ ተንሳፋፊ ነው፣ ብሉ አሰበ። «ሀያ በመቶ የመንሳፈፊያ ሀይል፣» አለ፣ ትዕዛዙን ፈፀመች። ሰርጓጇ ከባሀሩ ወለል ላይ መነሳት ስትጀምር ሔልደር ሁለቱን ቀዛፊ መዘውሮች አስነሳቸው። ሰርጓጇ ቀስስ እያለች ወደፊት መሄድ ጀመረች። ዘንጉን ወደኋላ ሲስበው ያገኘው ምላሽ እጅግ የተወሰነ ብቻ ነበር። ይሄ የተረገመ ትርፍ ክብደት። የሞተሩን ሀይል ጨመረው፣ ይህን ጊዜ ሰርጓጇ ወደላይ መነሳት ጀመረች። ወደባህር ጠለሉ እየወጡ ሳሉ፣ ከመቆጣጠሪያዎቹ የሚያገኘውን ምላሽ ፈተሸ። የመጥለቂያ ዝርግ

ብረቶቹ ወደላይ ለመውጣት የሚግዳቸው ከመሆኑ ሌላ ምንም ችግር አላገኘም። ይህም የተከሰተው ያለ እቅድ ከተጨመረባቸው ክብደት የተነሳ ነው። ይሆን ችግር መቋቋም አይከብደውም፣ ግን የባትሪ ሀይሉን ሊያሟጥጥበት ይችላል። ቢሆንም ግን ብዙ ሀይል ይቀረዋል። በፍጥነት ስሌቶቹን ከሰራ በኋላ የስድስት ሰዓት የጉዞ ጊዜው ወደስምንት ሰዓት ከፍ እንደሚል ተገነዘበ፣ በግምቱ መሠረት ግን የአስራ ዘጠኝ ሰዓት የመንቀሳቀሻ ሀይል አለው። ከትርፍ ክብደቱና ከጥሩ ቅልጥፍናና ፍጥነት ጋር በቂ ሀይል ይሆናል።

እናት ሰርጓጇ ከሰላሳ አምስት ሚትር ውሀ ስር ተጓታለች። የጥልቀት መቆጣጠሪያውን እየተመለከተ ትንሿ ሰርጓጅ መርከብ ሰላሳ ሜትር ድረስ ከፍታ እስኪኖራት ጠበቀ። ከዚያም የከውሀ በላይ የርቀት መመልከቻን እንቀሳቅሶ፣ የመመልከቻው ጫፍ ከውሀው ጠለል በላይ እስኪወጣ ድረስ ሰርጓጇን ከፍ አደረጋት። በፍጥነት ፔሪስኮፑን /የከውሀ በላይ የርቀት መመልከቻ/ 360 ዲግሪ /በሙሉ ክብ/ በማዞር ዙሪያውን ቃኘ። በክፊል አርክቲኩን ምሽት ደብዛዛ ብርሀን እየተጠቀመ ሲመለከት በዙሪያው ሌላ መርከብ ያለመኖሩን አስተዋለ። እይታን ወደፊት ለፊት ካዞረ የተቀመጠውን የመጀመሪያውን ብርሀን አገኘው። መርከቡ ብቻውን አቅጣጫዋን ይዛ እየተጓዘች መሆኑ ሲያረካው፣ ስዊድንን ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከታት። በዝቅተኛ የሩቅ ርቀት ላይ በተመለከተው መልክዐምድር በስተቀር ምንም ነገር አጣ ከዚህ በቀረበ የውሀ ክልል ውስጥ ሲገባ ደግሞ ለመመልከት ወሰኖ፣ ፔሪስኮፑን አወረደው።

«አቅጣጫችንን ይዘናል፣ ሶኮሎፍ፣» አለ በክፊል ራሱን ወደሷ እያዞረ። «ሪፖርት አድርጊ።»

«ሁሉ ነገር ትክክለኛ ሁኔታ ላይ ነው፣ ካፒቴን፣» አለች።

አንደበቷ ላይ የከበሬታ ቃና ይሟል፣ ከመነሳታቸው በፊት ከአበራት እርጋታ የበለጠ ርጋታን ተጎናፅፋለች።

ምንም ነገር ላይከሰት ሶስት ሰዓታት ተቆጠሩ። ሔልደር ፔሪስኮፑን አልፎ አልፎ ለጥቂት ሰከንድ ያህል ብቅ እያደረገ ያለምንም ችግር አቅጣጫውን ይዞ ቆየ። ከባሀሩ ዳርቻ ምቾት የሚንፀባረቅባቸው መኖሪያ ቤቶችን ተመለከተ፣ አንዳንዶቹ እጅግ ውብ ሆነው የተሰሩ ናቸው። በደብዛዘው ብርሀን ውስጥ አልፎ አልፎ የመንገድ መብራቶች ብልጭ ይላሉ፣ ግን የሚንቀሳቀስ ነገር የለም። እያንዳንዱ ስዊድናዊ ከእኩለ ሌሊቱ ብርሀን በሚለያየው ጥቁር የጭለማ መጋረጃ ተሸፍኗል። ሁሉም እንቀላፍተዋል። ጎህ ሙሉ ለሙሉ ሲቀድ፣ የመጀመሪያውን ጠባብ ቦይ አልፈው ገላጣ የውሀ ክልል ውስጥ ገቡ። ቦዩን አልፈው አፍታ ከቆዩ በኋላ ሔልደር የመጀመሪያውን አሳሽ ጀልባ ተመለከተ። ወዲያውኑ ሞተሮቹን እጥፍቶ ሰርጓጇ ትንሽ እንድትሰምጥ ከፈቀደላት በኋላ ውሀው ስር እንድትንሳፈፍ ተዋል።

«በሁለት መቶ ሜትር ርቀት ላይ ነው፣» አለች ሶኮሎፍ፣። የድምፅ መመርመሪያንና የጆሮ ማዳመጫ ከጆሮዋ ጋር አጣብቃ። «ሁለት ከሀምሳ፣ ሶስት መቶ፣ አምስት መቶ።»

ሔልደር ሞተሮቹን እስነስቶ ዳገመኛ የፔሬስኮፕ ጥልቀት ላይ መጓዝ ጀመረ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ ሌላ አሳሽ ጀልባ አገኘ፣ ከአንድ ሰዓት በኋላ ደግሞ ሌላ። ገላጣውን የውሀ ክልል አልፎ ወደቀጣዩ ቦይ ከገባ በኋላ ሌሎች ጀልባዎች አላጋጠሙትም። የቅዱስ ሆርጋንን ደሴት ወደኋላው በመተው

http://ethzare.wordpress.com

በደቡብ ምዕራብ አትጣጫ ነው። በተነሳ ልክ በስምንት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ትንሿን ሰርጓጅ ጀልባ ይዞ ስቶኮልም በስተምስራቅ ወደሚገኘው የሲላ ቫርታን ጉላግ የውሃ ክልል ገባ ከሩቅ ሶስት የንግድ መርከቦች ይንሳፈፋሉ፣ ከበስተጓላው ደንኖ ኑቱተ አሀላ የምትታይ ሌላ ጀልባ ትታያለች። የስቶኮልም ህንፃዎችን መመልከት ሲጀምር ሰርነ መግባቱ ስለታወቀው ልቡ በሀሴት ተሞላ።

ላይወድ በግዱ ፔሬስኮፑን እውርዶ ፍጥነቱን በመቀነስ ከመቅፅበት ጥልቀት መጨመር ጀመረ። ከዚያ ግን ሶኮሉፍ መናገር ጀመረች።

«ከጓላችን ሰባት መቶ ሜትር ርቀት ላይ ጀልባ በፍጥነት እየተጠጋን ነው።»

እቡ ጀልባዋን ላይመለከተው በፊት እሷ ለምን በድምጽ እንዳላወቀችው እስቦ ተናደደ። የቀራቸው ነገር ቢኖር ተስማሚ ስፍራ ፈልገው ጓዙን መልቀቅ ብቻ ነው። የሰርጓጅ መርከቧ ፓውሳዎች አብርቶ ጠበቀ። ከባህር ወለል ሰላሳ እንድ ሜትር ላይ ደርሰዋል። የሰርጓጇን ፍጥነት ቀነሰና ወደ ወለሉ በዝግታ እንድትወርድ አደረጋት። ለዚህ ተግባር እንከን የማይወጣለት ረባዳ የቋጥኝ ወለል ነው። የምድር ላይ ተሽከርካሪ ጎማዎቹን ስራ በማስጀመር ወደፊት ከአስር ሜትር ለማይበልጥ ርቀት እንቀሳቀሳት። የእምላክ ያለህ፣ ደረሰ ማለት ነው! ቦታው እንከን የለውም! ከዚህ ሌላ የቀለለ ምን ነገር አለ? «ጓዙን መልቀቁ ነው፣» አለ ሒልደር።

«ጀልባው አራት መቶ ሜትር ርቀት ላይ በዝግታ እየተጠጋ ነው፣» አለች ሶኮሉፍ፣ ድምጿ ላይ ውጥረት እየተነበባት። «ፍጥነት በግምት አስራአምስት ኖት ይደርሳል፣ እየቀነሰ ነው።»

አስራአምስት ኖት? አላሽ ጀልባ ነው። ሌላ በዚህ ፍጥነት የሚሄድ ምን ጀልባ ይኖራል? ሁሉን ነገር አጠፋፍቶ ዘና ብሎ ተቀመጠ። «ፀጥታ፣» አለ፣ «ከሪፖርቶች በስተቀር።»

«ጀልባው መቶ ሜትር ርቀት ላይ ደርሷል፣ ፍጥነት የማይለዋወጥ አስር ኖት አለች ሶኮሉፍ።

ሒልደር የድምጽ ማጉያ መሳሪያው አላስፈለገውም። አሁን የጀልባዋ ሞተሮች ድምጽ በፍልፅ እየተሰማው ነው። ከበላያቸው አልፎ ሄደ።

«ጀልባው በአስር ኖት ፍጥነት እየተንጠለጠለን ነው፣» አለች ሶኮሉፍ፣ ድምጿ ላይ ትንሽ እርጋታ እየተመለሰ። «ሶስት መቶ ሜትር ርቋል፣ ርቀት እየጨመረ ነው።»

ሒልደር ቀጥ ብሎ ተቀመጠ። «ጓዙን ለመልቀቅ ተዘጋጂ፣» አለ። «ወደ ሀይድሮሊክ ሾፈላሽ ግፊት የሚበላ ኃይል/ ኃይል ተሸጋገረ።»

«ወደሀይድሮሊክ ኃይል ተለውጧል፣» መለሰች ሶኮሉፍ፣ ቁልፎች እየነካች። «ዝግጁ።»

ሒልደር የመቆንጠጫዎቹን ማንቀሳቀሻ ዘንጎች ይዞ ጓዙን አነሳው። ውሀው ወደላይ ሲለጠጡ ያለብዙ ችግር ተነሳለት። ወደፊት ሲገፋው ጓዙ ከትንሿ ሰርጓጅ ወደፊት ተንቀሳቅሶ መቀመጫውን ለቀቀ። መቆንጠጫዎቹን ወደታች ሲስባቸው ጓዙ ባህሩ ወለል ላይ አረፈና የአሸዋ ብጥብጭ ወደላይ አስነሳ። መቆንጠጫዎቹንም ቦታቸው መለሳቸው። «የሀይድሮሊክ ሀይሉን አጥፊው፣» አለ።

«የሀይድሮሊክ ሀይሉ ጠፍቷል፣ ሞተሮቹን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ሙለ የባትሪ ሀይል አለ፣» አለች ሶኮሉፍ።

ሒልደር የእንቅስቃሴና የአትጣጫ መቆጣጠሪያ ሰሌዳውን ተመለከተ። «ሀምሳ ሰምንት ዲግሪ፣ ሀያ ሁለት ደቂቃ፣ አስር ሰከንድ ሰሜን፣ አስራ ሰምንት ዲግሪ አስራ ሁለት ደቂቃ፣ ሁለት ሰከንድ ምስራቅ፣» አለ ጮክ ብሎ፣ በዚሁ ጊዜ የአትጣጫ ማመልከቻ ቁጥሮቹን (Log Book) በማስታወሻ ደብተሩ ላይ እያሰፈረ በቃሉ ያዛቸው። ቁጥሮቹ ሀሊናውን ሰርስረው ከመግባታቸው የተነሳ ጸግመኛ ምንም ነገር የዚህን ያህል ማስታወስ እንደማይችል ታሰበው። የእምላክ ያለህ፣ ተሳክቶሊታል! ይህንን መሳትጡ የጠሩ ማሽን ስዊድን የውህ ክልል ውስጥ ይዞ ገብቶ ያመጣውን ጓዝ አፍንጫው ስር አስቀምጦላቸዋል!

«አንድ ጀልባ ከፊት ለፊት በርቀት እየቀረበ ነው፣» አለች ሶኮሉፍ ድንገት «ፍጥነቱ በግምት አስር ኖት።» ድምጿ ተርገበገበ። «ያምላክ ያለህ፣ ተመልሰው የመጡ መሰለኝ!»

ሒልደር መጀመሪያ በሀሳቡ የመጣለትን ጓዙን ርቆ መሄድ ነበር። መቆጣጠሪያዎቹን ጨምድዶ፣ እንድታንሳፍፈው ከጠየቃት በኋላ፣ ሰርጓጇ ሶስት ወይ አራት ሜትር ያህል ከተነሳች በኋላ ወደፊት ገፍ ጀመረ። «ለይነት አራት፣ ጠላቂዋ ሽክሟ ስለቀለለላት ከጓዙ በላይ አልፋ ወደ ላይላ ቫርታ ግልጽ የውህ ክልል ተመነጨፈች።

«ምን እያደረግክ ነው?» ሶኮሉፍ ልትሮህ ምንም አልተራት። «ወደስቶኮልም እየሄድክ ነውኮ!»

«እሱን አውቃለሁ ሶኮሉፍ፣» መለሰ ሒልደር፣ ጥርሶቹን እንደነከሰ። «ነፃ እስክንሆን ድረስ ወደዚያ ቦይ መሄድ አልፈለግኩም» መላወሻ በሌለው የውህ ክልል ውስጥ መያዝ አያዋጣንም። አሁን ዝም በይና ተረጋጊ። ያንቺ ስራ አብቅቷል፣ በሰላም የመመለሱ ስራ የኔ ነው።»

«አብደሀል!» አለችው፣ አሁን ግን ድምጿ ያምባርቃል። «ጓዳቸችንን ጨርሰናል፣ አሁን ከዚህ ወተተን ወደ እናት ሰርጓጇ እንመለስ»

ሒልደር ሰርጓጇን ያለምንም ድምጽ በመንዳት ተግባሩ ላይ ማተኮር ፈለጓል። «አትረበሺ ሶኮሉፍ፣ እፍሽን ዝኒ! ይህ ትልዝዝ ነው፣ ወደድምጽ መቆጣጠሪያው ተመልሰሽ እንዳንድ ሪፖርቶችን ስጪኝ።»

ለጥቂት ጊዜ ፀጥታ ሰፍኖ ቆየ፣ ከዚያም ሶኮሉፍ፣ «አሁን ከኋላችን እየመጡ ነው! በላያችን ላይ አልፈው ተመልሰው እየመጡ መሆን አለባቸው!»

ውይ አምላኬ፣ ሒልደር አሰበ፣ ለይተውናል ማለት ነው።

«ወደእናት ሰርጓጇ መመለስ ይኖርብናል!» ሶኮሉፍ ጮኸች።

ከዚያ ጓዝ የቻልነውን ያህል ርቀን ጉላግ የውህ ክልል ውስጥ መግባት አለብን፣ አሰበ። «ከሪፖርቶች በስተቀር ፀጥታ፣» አለና በሀይል ወደቀኝ ታጠፈ። «አንተ ግን ነህ. . .»

የሶኮሉፍ ጩኸት ከመጠን ባለፈ የድምፅ ኑሮተ ተቋርጦ፣ ትንሿ ሰርጓጅ ወደአንድ ጎን ተወረወረች። «ይህ የጥልቀቱ ኑሮተ ነው።» አለ ሒልደር። «ቀበቶሽን አስረሽ ተቀመጪ።»

«አንተ ቂል!» ሶኮሉፍ ጨኸች፣ አሁን ከቁጥጥሯ ውጪ ሆኗል በግልጽ ይታይባታል። «ልትገድለን ነው!»

http://ethzare.wordpress.com

«አፍሽን ዝጊ። ሮኽ ሔልደር፣ ይህንኑ ሊደግመው ሲል፣ ከመቀመጫው በስተጓላ ክንዷ በአንገቱ አልፎ ጉርሮውን እንቆ ያዘው። የሶኮሉፍ ጩኽት ምንኑቱ የማይታወቅ ሆነ፣ ሔልደርም ስሊታነቀ ምንም መናገር አልቻለም። መቆጣጠሪያዎቹን ለቀቀና በሀለት እጁ ፡ክንዷን ጨመደደው፣ ሰርጓጇ መደኪሩ ወሰል ወርዳ ተሳተመች። እንድ እጁን ከክንዷ ላይ አላቆ በእንድ እጁ ብቻ እየታገለት መቆጣጠሪያዎቹን ለማስተካከል ይጥራል። ሶኮሉፍ በንዲት ታልኮጉግለጽ፣ ከበላያቸው ግን አሁንም የጀልባው ሞተሮች ድምፅ ሲያንራ ይሰማዋል። መተንፈስ እያቃተው ስለመጣ ራሱን ወደጎን ዞር አደረገ። ትንሩኘ ግማኙት ጪኾች ክንዷ ግን ዋናውን የደምስሩን ወጥሮ ይዞታል። የክርስቶስ ያለህ፣ ይህች ሴት ከወንዶች ይልቅ ጠንካራ ነች!

ዳንሙኖ መቆጣጠሪያዎቹን ለቀቀና በሁለቱም እጆቹ ይታገላት ገባ፣ ሰርጓጇ ግን ቁልቁል ወርዳ አሁንም ከባሀሩ ወለል ጋር ተሳተመች። ይህን ጊዜ ወደመጡንቹ እጁን መለሰ። ድንገት፣ ሔልደር መዳከም ጀመረ፣ በፍጥነት እንድ ነገር የማያደርግ ከሆነ ሀሊናውን መሳቱ መሆኑ ገባው። ቀኝ እጁን ነፃ አድርጎ ወደ ሰርጓጇ የተሸፍ መሳሪያዎች ማኖሪያ ሰደደው። ምን እንደሆነ ባያውቅም እንድ ነገር እጁ ገባ። ፈጅ አለ ብሎ ወዳሰበው ስፍራ የኋሊት ሰነዘረው።

ሁሉ ነገር ከመቅፅበት የተፈጠረ መሰለ። ራሱን ሊስት ጥቂት ብቻ ሊቀረው ከበስተጀርባው የሰነዘረው መሳሪያ እንድ ነገር ላይ አረፈና የክንዷ ሀይል መሳሳት ጀመረ፣ ወዲያው በሕይወቱ ሰምቶት የማያውቀው ነጎድጓደማ ድምፅ አስተጋባና ሰርጓጇ የምትገለባበጥ መስሎ ተሰማው። መጨረሻ የተሰማው ነገር ቢኖር የሆነ ነገር ሁለቱንም ትከሾቹን እየሰረሰረ ሲገባ ነበር። ከዚያ ራሱን ሳተ።

21

ሩል ከረጅምና መብብ በግምት የሀያ አምስት ሜግ ርዝመትና የአስራ ሁለት ሜግ ስፋት ካለው ክፍል በላይ የሚገኝ አነስተኛ የደረጃዎች መጨረሻ ላይ ደረሰች። ከውጭ በኩል ከአንደኛ ፎቅ ላይ ሲሆኑ ከሚችሉ ከፍ ብለው ከተደረደሩ መስኮቶች በኩል ብርሀን ይገባል። በስተተኛ ስድስት ጥንድ የሚሆኑ ያጠረጴ መንሸራተቻ ምርኩዞችና ሜግዎች በትንሽ በርሜል ውስጥ ተቀምጠዋል። ቦታው ከዚህ ቀደም በትምህርት ቤትነት በሚያገለግልበት ወቅት መጋዘን ሆኖ ሲያገለግል የነበረ ሲሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። አሁን ግን የበረጴ መንሸራተቻ መሳሪያዎች ማከማቻ መሆኑ በግልጽ ይታያል። የነበሩትን ጥግ ያዘው በሁለት ጎን የተደረደሩ የብረት መቀመጫዎች እንዱ ላይ እንድ ሰው ተቀምጧል።

ወዳለበት በዝግታ እየተራመደች ሁኔታውን መረመረችው። በጣም ተለዋውጧል። ፎቶግራፎቹ ላይ ያሉት ምስሎች፣ እድሚው ሰልሳ የሚገመት ጥቁር ፀጉሩ ግንባሩ ድረስ ድፍት ያለ፣ ጥቅጥቅ ያሉ ትንድቡቢና የንስር ገፅታን የሚያሳብሰው ቆልማማ አፍንጫ ያለውን ሰው አስታወሷት። እፍንጫው ተሰብሯል፣ ያለስቃይ በሆነ ብላ ተመኘች። በሕክምና ጥገና አልተያረገለትም። አሁን ተደፍጥጦ፣ ሰፍቶ ተጨማትሯል የሚጀር ጀኔራል ጄምርጂ አብራሞቪች ማላክሆቭ ወላጅ እናት ብትሆን እንኳን መንገድ ላይ ብታየው አልፋው ትሄዳለች።

ፊት ለፊቱ ካለው በርጩማ ላይ ተቀመጠች። «ደህና ዋልክ፣ ጀኔራል ማላክሆቭ፣» አለችው።

«እባክሽን በዚያ ስም አትጥሪኝ፣» አለ። «አሁን. . . ሌላ ሰው ነኝ፣ ጀኔራልም መሆኔ ቀርቷል።» ድምጹ ቃና ላይ ወጥ አይልም።

«እንዳልክ ይሁን፣» አለች። «ኪርክላድ እባላለሁ፣ የመጨረት ሶቭየት ህብረት ውስጥ ስለምታውቀው አንድ ሰው ልጠይቅህ ነው።»

«የክርስትና ስም አለሽ ሚሲስ ኪርክላንድ?» አል በለሰለስ እንደበት። «ዘሱ ልጠራሽ እችላለሁ?»

ወንድ በግብጥ ላይ ሴትን የሚያናግርበት አይነት ተያቄ ስለመሰላት ትንሽ ግር ካላት በኋላ፣ ወዲያውኑ ግን ሲቶች እጠንብ ላይደርስ የተመለከ ጊዜ መቆየቱ ትዝ አላት። እግርጅን እማምራ እጀጀ ላይ ተደገፈችና ወደፊት ጪጋ አለች። «ብሩኪ ብለህ ብትጠራኝ ደስ ይለኛል።» አለች፣ የድር የትምህርት ቤት መኝታ ክፍል ጓደኛዋ ስም አዚህ ቦታ ብትጠቀምበት ቅር እንደማይላት እያሰበች።

«ተሩ። ተሩ ስም ነው። ብሩኪ።» ልክ እንደባለጪታ ጥርት ያለ ቅላጼ አለው። እንክን የለሽነቱ አስገርሟታል። እንደግንኛውም እንግሊዝኛ ተናጋሪ ሩሲያውያን ሁሉ የ«» ፊደልን አተብቶ መናገሩ ወደመቸለናው ምዕራብ አሜሪካ፣ ምናልባትም የኢሊኖይስ ወይንም የኦሪዮ ተወላጅ ያስመስለዋል። ቃላት አወራወሩ ግን ከአሜሪካውያን ይለያል። ወደአውሮፓውያኑ ያደላል።

«ታዲያ ብሩኪ፣ ስለግን ልትጠይቂኝ ነው የመጣሽው?»

«ስለ ቪክቶር ግጆሮቭ።»

ትንድቦቹ ወደላይ ተለጠጡ። «እህ! ቪክቶር ሰርጌጂችን ልግሎት ግኙተኛላ?»

ትከሻዋን ሰበቀች። «ብትንሹ። ግጆሮቭን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘህበትን ጊዜ ታስታውሰዋለህ?»

ፈገግ አለና «እንዲታ። ልክ ትላንት እንዳገኘኹት ያህል። በ1959 በጸረ እንድሮፖቭ ቢሮ ውስጥ ነበር። በጊዜው የመአክላዊ ኮሚቴው ወሬ ነበር። ስሙ ግጆሮቭ አልነበረም፣ እንድሮፖቭ ቪክቶር ሰርጌጂች. . .» በሳቅ ተውጦ ዝም አለ። «ወላጆቹን አውቃቸዋለሁ። ስለኋላ ታሪክ እንድነግርሽ ትፈልጊያለሽ? በጣም የሚገርም ነው።»

ትፈልጋለች? የክርስቶስ ያለህ፣ ተያቄ የለውም። «ሳዋክህ ንገረኝ።» አለች።

«እሺ፣ ወደ አብዮቱ መመለስ ይኖርብናል። ሰርጌይ ኢቫኖቪች ግጆሮቭ የተወለደው ፕናና ስም ካለው ወይንም ክክበር የሊንግራድ ኒጋዴ ቤተሰብ ነበር። የዊንተር ቤተመንግስት በተወረረ ወቅት የፈረሰኛ ሰራዊቱ ካፒቴን ነበር። የራሱን ሀይልም ለአብዮቱ መከላከት አቅርቧል። በዚህም የሊኒንን አተኩሮት አገኘ፣ ከአጭር ጊዜ በኋላ የሊኒን የግል ጠላቂ ሆነ። ጥሩ የትምህርት ደረጃ ያለው ግፊኪ ሰው በመሆኑም፣ ሊኒን በእሱና በሩሪያው የክበቡት ጭሰኞች የሰግይና የምድር ልዩነት የሳበው ይመስላል ሊኒን የምወደው ዘረ-ዛር (Czarist) ብሎ ይጠራው ነበር።»

http://ethzare.wordpress.com

ማላክሆቭ ከሽሚዝ ኪሱ ትንንሽ ሲጋሮችን የያዘ ፓኬት አውጥቶ አንዱን እስኪለኩስ ሩል በትዕግስት ጠበቀችው። ታሪኩ ስለሳባት ለማዳመጥ ጓጉታለች።

«ታላቁ ሌኒን የመጀመሪያ የአንጎል ህመም እስከገጠመው እስከ 1922 ፀደይ ድረስ አብሮት ቆየ። ከዚያ በኋላ ሌኒን ለእሱ ያለው ፍላጎት እየቀነሰ መጣ፣ እናም የመጀመሪያ የደህንነት ፖሊስ የሆነው ዘርዜንስኪ ቀረበው። ግን ደግሞ አንቺ ስለክሬምሊን ጠንቅቀሽ የምታውቂ በመሆንሽ ይህ አይጠፋሽም አይደለም?»

«እባክህን ቀጥል፣» አለችው፣ ስለእሷ ማወቅ የፈለገውን ወደጎን እየተወች።

«ሰርጌይ ኢቫኖቪች፣ በዘርዜንስኪ እልቅና ስር ሆኖ ሲፍጨረጨር ቆየ፣ ከዚያም በቤሪያ ስር። 1930 ገደማ ከአንዲት ወጣት ሴት ጋር፣ አረ እንደውም ልጃገረድ ነች ተዋወቀ። ናታሊያ ፊርሶቫ ትባላለች። የተወለደችው እንግሊዝ ውስጥ ሲሆን፣ ወላጆቿ የዘር አገዛዝን ሸሽተው የተሰደዱ ቦልሼቪክ ሩሲያዊያን ናቸው። ስታሊን የቴክኒክ መሀንዲስ በመሆኑና ልጅቷም ለንደን ውስጥ በስፖርታዊ ዳንስ የሰለጠነች ስለነበረች፣ ቶሎ ብለው ግብግባውን ተቀበሉ። እሷም በቦልሾይ የስፖርታዊ ዳንስ ውስጥ ተቀጠረች። በጊዜው ማጆሮቭ በእርባዎቹ መጀመሪያ የእድሜ ክልሉ ውስጥ ሲገኝ፣ እሷ ግን አስራ ስምንት ወይ አስራ ዘጠኝ ዓመት ቢሆናት ነበር። ሆኖም ጥሩ ጥንድ ወጣቶች ተጋብተው፣ እሷ በ1936 ወይ 37 ገደማ እስከወንስችበት ጊዜ ድረስ ቦልሾይ ውስጥ በዋና ዳንሰኝት ስትሰራ ቆየች። ከዚህ በኋላ ግን ነገሮች በሰርጌይ ኢቫኖቪች ላይ መክፋት ጀመሩ።»

«የስታሊን ጥቃቶች?»

ማላክሆቭ በእምንታ ራሱን ወዘወዘላት። «ያስቆጣውን ነገር ረስቼዋለሁ፣ ግን ምንም አያደርግልንም። በማንኛውም አይነት የሐሰት ውንጀላ የተነሳ በየቀኑ ሰዎች እየተገደሉ የነበሩበት ወቅት ነው። ጸሩ ግን ሰርጌይን በጥይት የመታው ስታሊን ራሱ ነው። የሚሉ የጭምጭምታ ወሬዎች ተደምጠዋል። እውነት ይሆን አይሆን፣ እያልኩ ብዙ ጊዜ አስብ ነበር።»

«ታዲያ ናታሊያና ልጇ ምን ደረሱ?»

«ገና፣ ሕፃኑ እልተወለደም፣» አለ ማላክሆቭ፣ «ሰርጌ ኢቫኖቪች ብዙ ሁነኛ ወዳጆች ነበሩባት። ጥቂቶቹም እርዳታ ሊሰጧት ወኔው ነበሯቸው። እንዴት እንደተደረገ ባላውቅም፣ ብቻ ሌኒንግራድ መግባት ቻለች። አንድ ሰው የኪሮቭን ባሌት ወጣት ዳንሰኞች እንድታሰለጥን ስራ አገኘላት። ልጁ ሲወለድ በራሷ ስም ፊርሶቭ ብላ ሰየመችው፣ በእባቷ ስምም ሮይ ብላ ትጠራው ነበር። ማንነቱ መታወቅ ስለሌለበትም ዲቃላ እየተባለ ለማደግ ተገደደ፣ ንፅህናን በሚያስረግጥ የኮሚውኒስት ማህበረሰብ ውስጥ፣ ይህ ለአንድ ታዳጊ አስቸጋሪ ነገር ይሆናል፣ ይመስለኛል። ግን፣ አባቱ ማን እንደሆነ ያውቃል ብዬ አስባለሁ።»

«ይህ በኮሚውኒስት መዋቅሩ ውስጥ ወደፊት ከመራመድ እግዶት ይሆን?» ጠየቀች። ይመስለኛል። ሞስኮ ዩኒቨርስቲ ገብቶ በቋንቋዎችና በፖርቲ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ብቃትን አዳበረ። እንደውም የኮምሶሞል ወይንም የወጣት ኮሚውኒስት ሊግ ሊቀመንበር ነበር፣ እንድሮፖቭን ያገኘውም እዚያው

ዩኒቨርስቲው ውስጥ ነው። ለኮምሶሉ ንግግር ሊያደርግ ወደ ዩኒቨርስቲው በሄደ ጊዜ ነበር፣ ቪክቶር ሰርጌይቪች ያስተዋወቃቸው። እንድሮፖቭ በወጣቱ ስለተማረከ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ጠየቀ-ዶሪ ግን ሁሉ ነገርና ሁሉ ሰው ላይ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር የሚያደርግ ሰው ነበር። ወጣቱ ማጆሮቭ ገና ዩኒቨርስቲ ውስጥ እያለ እንድሮፖቭ የትርፍ ጊዜ ስራ ሰጠው።»

«ምን ዓይነት?»

«እንድሮፖቭን እንግሊዝኛ ማስተማር፣» መለሰ ማላክሆቭ። «የዶሪ እንደሮፖቭን ዓይነት ሰፊ ዥንቅላትና አስተላሰብ አጋጥሞኝ እያውቅም። በጊዜው እንደነበሩ መሠል ፖለቲከኞች አልተማረም ነበርና፣ በዚህ ሪገድ በበታችነት ስሜት ችግር ይሰቃይ ነበር ብዬ አስባለሁ። ሁሉን ነገር ማንበብ፣ ስለሁሉ ነገር ማወቅ ይፈልጋል። የሚያነበው ነገር አብዛኛውም የተተረጎመ ሳይሆን በእንግሊዝኛ የተፃፈ ነበር። በርግጥ ማጆሮቭ ከእናቱ እንግሊዝኛን እየተማረ በማደጉ፣ ቋንቋን አጣርቶ ከመናገሩ በላይ ለዶሪ ተስማሚ አስተማሪ ወጣው በዚህን ወቅት የማውቀው እንድሮፖቭ በሳምንት ከሦስት ማለዳዎች ሌላ ስራውንና ጊዜውን ቋንቋውን ለማስተማር ሲል የሚሰዋ ነው። የእንጋገር ቃናው በጣም ግሩም ባይባልም፣ የቋንቋውን ቀልሉ ያልተዘጋጀ ወይ ያልተተረጎመ ጽሑፉን ነው። ከግል ጥንካሬዎቹን ሁሉ ትልቅ ቦታ ያለው ይህ ይመስለኛል። ለማጆሮቭም ዘወትርም ክብርና እድናቆት ነበረው።»

«ማጆሮቭን በእንድሮፖቭ ቢሮ ውስጥ ያገኘሽው በ1959 ላይ ነበር።»

ማላክሆቭ ራሱን ከፍ ዝቅ አደረገለት። «በማዕከላዊ ኮሚቴ የበላይ መምሪያ። ቢክቶር ሰርጌቪች ልክ ከዩኒቨርስቲው ሊመረቅ ሲል ይመስለኛል። ለKGB ያለውን ፍቅር ይገልፅለታል። እንድሮፖቭ ለምላ መጥቼ ይህን ወጣት እንድተዋወቀው ጠየቀኝ። በጣም ማረከኝ። የቋንቋዎች ችሎታው እሱን ለመመልመል በቂ ነበር። ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛና ስዊድንኛን አሳምሮ ይናገራል። ሌሎች የስካንዴኒቪያ ቋንቋዎችንም ይሞካክራል። ግን ብሩህ አእምሮ ያለው ከእድሜው የፈጠነ መሆኑ በግልጽ ይታያል። ቁምነገረኛ ወጣትም ነበር። ወዲያውኑ ለራሴ አንድ ተልዕኮ፣ ዋና ሀላፊ አድርጌ ሾምኩት። ከሀገር ውጭ ስለላ ፍፁም እንከን የማይወጣለት ሰው ነበር»

«እና የመለመልከው የዚያን እለት ነበር?»

ማላክሆቭ ፈገግ አለ። «እሱ የመለመለኝ ይመስለኛል። እሱና ዶሪ። የክፍሉ የበላይ በመሆን ተመረቀ፣ በሳምንት ጊዜ ውስጥም በKGB የውጭ ሀገራት ግልጋሎት ክፍል ትምህርት ቤት ወስጥ አስገባነው።»

«በስልጠናው ጊዜ ትከታተለው ነበር?»

«አልተከታተልኩትም፣ ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ ወደውጪ ሀገር ተላኩኝ፣ ነገር ግን ለእረፍት በምመጣ ጊዜ ሁሉ ስለእሱ ሂደት ሞስኮ ማዕከል አካባቢ የሚነገሩ የጭምጭምታ ወሬዎችን አሰማለሁ። ከምሰማውም ፅፁብ እውቀት ነበርው። ብዙውን ጊዜ የእጩውን የቋንቋ አሉታዎች በማስተካከል ብቻ ብዙ ጊዜ ይጠፋ ነበር። የሱ የቋንቋ ብቃት ግን የስልጠናውን ጊዜ በጣም አሳጠረለት። ከሁለት አመት በኋላም ስቶኮልም ላይ ተመደበ። እስከ 1978 ድረስ ግለትም የዋና መጀመሪያ ዳይሬክቶሬት ሀላፊ ተደርጎ እስከ ተሾመ ጊዜ ድረስ በቀጥታ ተገናኝተን አናውቅም። ረጃጅም ውይይቶችን አደረግን፣ አንዳንድ ጊዜ ብቻችንን፣ ከዚያ ለተባበሩት መንግስታት ተልዕኮ መረጠኝ።»

http://ethzare.wordpress.com

«በጊዜው እንድሮፖቭ የመጀመሪያው መመሪያ ሀላፊ አድርጎት ነበራ?»

«እንዴታ። ዩሪ ክቪክቶር ሰርጌይቪች ጋር እንግሊዘኛ ያጠና በነበረበት ጊዜ፣ ምንም እንኳን በወቅቱ እንድሮፖቭ እድሜው እርባዎቹ ውስጥ ቢገባም ቅሉ፣ ግንኙነታቸው ግን የአባትና የልጅ ያህል ጠንከሮ ምንም እንኳን ቪክቶር ሰርጌይቪች በስኬት ጎዳና ላይ ናቸው ብሉ የሚያስባቸውን ሁሉ መርዳት ውጣ ውረድ ውስጥ የሚገባ ቢሆንም እሱ ግን ዘወትርም የማጆሮቭ ዋንኛ አጋር ነበር።»

«በተለይ ማንን ይረዳ ነበር?»

«በዋንኛነት ጎርቫቼቭን። ጎርቫቼቭ በእድሜ ማጆሮቭን በጥቂት ዓመታት ይበልጠዋል፣ ግን የእንድሮፖቭም ደጋፊ ነው። በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ በነበረበት ወቅትም ከግሮማይኮ ጋር መልካም ግንኙነት ነበረው፣ ይህ ቀላል ነገር አይደለም።»

«በወቅቱ ሁለቱንም ትውልዶች በጥሩ አገልግሏል?»

«እንዴታ፣ በትክክል። የወጣቱ ትውልድ ነገሮችን የመቀየር ጽኑ ፍላጎትና የእሮጌው ትውልድ ቅዝቃዜና ብርታትን የታደለ ነው። ከሁለቱም ጋር መግባባት ይችላል።»

«በአሁኑ የአመራር ስርዓት ውስጥ ቢሆን በKGB ለመምራት ብቁ ያስመስለዋል።»

ማላክሆቭ ትክሻውን ሽቅብ ወጠረው። «ማን ያውቃል? ወደሊቀመንበርነቱ በተሸጋገረ ጊዜ በKGB የበላይ አመራርነት የእንድሮፖቭ ምክትል የሆነ መስሎኝ ነበር፣ ግን አልሆነም። ከማንኙነታቸው አንፃር በአለም ከማይገርሙ ክስተቶች መሀል የተመደበ፣ ግን አልሆነም።»

«ለምን ይመስልሀል?»

«እንድ መላ ምት አለኝ፣ ግን ተሳስቼ ሊሆን ይችላል።»

ሩል ጉዳዩን ለመስማት ቸኩለች። «መላምትህ ምንድን ነው?»

«እንድ የተሻለ ነገር አግኝቶ ይመስለኛል።»

እሁን የሷ መላምት ራሱ ድጋፍን እያገኘ ነው። ቀጣዩ ጥያቄዋ እንድ ርምጃ ወደፊት ሊያራምደው ይችላል። «ከKGB የበላይ አመራር የበለጠ ምን ይኖራል?»

«ማጆሮቭ ለራሱ እንድ ነገር ያቀደ ይመስለኛል፣ ከዚያ ሌላ ለሱ ምንም የተሻለ ነገር ሊኖር አይችልም። የእንቅስቃሴ ነፃነትን ዘወትርም በጣሙን ይፈልግ ነበር።

«የKGB የበላይ ከመሆን የተሻለ ለራሱ ምን ሊፈጥር ይችላል።»

«እኔ እንጃ፣ ግን ከመጠን በላይ ከፍተኛ ቦታ ያለው መሆን አለበት። አም፣ እንዲህ አይነት ነገር ለቪክቶር ሰርጌይቪች ይሆንዋል። ከተሳካ ወደፖሊት ቢሮው የሚያስወነጭፈው አለዚያም የመሪነት ስልጣኑን የሚያስጨብጠው ሊሆን ይችላል።»

«ያን ያህል በትልቁ ያስባል ማለት ነው? በጣም አደገኛ አስተሳሰብ ነው።»

«ማጆሮቭ የሚሳክለት በአደገኛ ነገር ነው፣ የኔ ውድ ብሪኪ። ሁሉን ነገር በእጁ የሚያስገባ ወይንም ይህን ሊያደርግ በመሞከር ራሱን የሚያጠፋ አይነት ሰው ነው። እንደሚወራው ከሆነ ችግሮችም አሉበት።»

ሩል ትንሽ ተወጣጠረች። «እስኪ ስለወሬዎቹ ንገረኝ።»

«ወደሞስኮ ቢመለስም ጊዜ፣ ቪክቶር ሰርጌይቪች የተወሰኑ ጉድለቶች እንዳሉበት ሰማሁ፣ ወሲባዊ ጉድለቶች።»

«ግብረሰዶማዊ ነው ማለትህ ነው?»

«በፍፁም። እንደውም በተቃራኒው ሴት አደበቃውም በአንድ ጊዜ ሁለትና ሶስት ሴት ያወጣል፣ ይህ ከማንም የተደበቀ አይደለም።»

«ታዲያ ችግሩ ምኑ ላይ ነው።»

ማላክሆቭ ትንሽ ተክሳተረ። «እኔ ግብረገባዊ ህይወትን የማጠብቅ ሽማግሌ ስለሆንኩ ይመስለኛል፣ እነዚህ ነገሮች ለንግግር እንኳን ይቀፉኛል።»

ሩል ወደፊት ጠጋ አለች። «እባክህን፣» አለችው።

«እሺ፣ የሚባለውማ እንዳንድ ጊዜ ነገሮች ከመጠን ሲያልፉ፣ አንዳንዴ እንደሚገድል ነው።»

«የወሲብ ጓደኞቹን ነው የሚገድለው?»

ማላክሆቭ ራሱን ከፍ ዝቅ አደረገ። «የሚባለው፣ ይህ መፈጠሩን ነው. . ከእንድ ጊዜ በላይ። ልንግርሽ የምገደደው ነገር፣ ይህን ወሬ በሰማሁ ጊዜ ለማመን የመቸገሬን ነው።»

«ለምን አልቸገረህም? ስለማጆሮቭ ምን ብታውቅ ነው ከወሲብ ጋር የተያያዘ ግድያ ይፈፅማል ብለህ ለማመን ያልተቸገርከው?»

«ግድያን መፈፀም ከባድ አይደለም፣» አለ ማላክሆቭ፣ ሀዘን ባጠላበት እንደበት «እኔም ገድያለሁ። KGB ውስጥ ለረጅም ጊዜ ከቆየሽ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መግደልሽ አይቀርም። ሰንጢውን መሰንዘር የሚችለው ግን ሁሉም አይደሉም። አንዳንድ ሰዎች ግን ይህ ያስደስታቸዋል። በእንድ ወቅት ማጆሮቭ በዚህ ድርጊት ሊደሰት ተመልክቼያለሁ።»

«ስለሁኔታው ንገረኝ እስኪ?»

ማላክሆቭ መሬት መሬት ተመለከተ። «ሶቭየት ህብረት ውስጥ የሰራዊቱ የሞት ቅጣት እንዴት እንደሚፈፀም ታውቂያለሽ?»

«በኢላማ ተኩስ ስኪዱ ይመስለኛል።»

ማላክሆቭ በእሱታ ራሱን ወዘወዘ። «አይደለም፣ የሞት ቅጣትን ለሚያሰጡ ጥፋቶች፣ የተኩስ ስኪድ ይበዛበታል፣ ለዚህ አይነቱ ወንጀለኛ የማይገባ ክብር ይሆናል። ግን ይሆናል ብሉ ለየሚያምነው ይህንኑ ነበር። የተኩስ ስኪድ ተመርጦ ይዘጋጃል፣ ወንጀለኛውም ወደእነሱ በእርምጃ እንዲሄድ ይደረጋል። ከዚያም፣ የተኩስ ስኪድ ራሱን እያዘጋጀ መስሎ በሚታይበት ወቅት፣ አንድ መኮንን ከወንጀለኛው በስተጓላ ደምጽ ሳያሰማ ይቀርበውና በሽጉጥ ሞንቅላቱ ላይ ተኩሶ ይመታዋል።»

ሩል ምንም አልተናገረችም።

በአንድ ወቅት ማጆሮቭ ይህን መሰል የሞት ቅጣት ሲያከናውን ተመልክቼያለሁ፣» አለ ማላክሆቭ አሁንም አይኖቹን ወለሉ ላይ እንደተከለ። «ወንጀለኛው ወደምዕራቡ ከድቶ ለመግባት ሲሞክር ተደርሶበት ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ነው። የተኩስ ስኪዱ ተዘጋጅቶ፣ የተመረጠው መኮንን ሰለባን ከበስተጓላው ለመቅረብ እየተዘጋጀ ሳለ፣ ድንገት ማጆሮቭ መጣና ሽጉጡን ተቀበለው። በዝግታ እያደባ ከጓላው ሲጠጋው ፊቱ ላይ የነበረው ስሜት በደስታ የሰከረ ያስመስለው ነበር። ለተወሰነ ጊዜ ጠበቀ፣ ስለባው የተኩስ ስኪዱ ለምን

http://ethzare.wordpress.com

እንደግይንቀሳቀስ በግሰብ ግር እስኪለው ጠበቀ። እሁንም ከጀርባው ምን እየተደረገ እያለ እንደሆነ ጠርጠሮ ዞር ግለት እስኪጀምር ጠበቀ ራሱ ላይ በጎን በኩል ተከሰበት። ከዚያም የወደቀበት ትቶት ሄደ። አልሞተም። ሴላ መኮንን የመጨረሻ መገላገያውን ቃታ ሳበ። ለማየት ይዘገንናል . . . እንደ ሰው የሴላ ሰውን ግድያ መደሰቺያ ሲያደርግ ማየት ዘግናኝ ነው።»

«ሩል አሁንም ምንም አልተናገረችም።

«እንድ ነገር እነግርሻለሁ፣ ብሩኪ ኪርክላንድ፣» ብሎ ማላክሆቭ ወደፊት ዘመም ብሎ ቃላቶቹን እያስረገጠ መናገር ጀመረ። «KGB ውስጥ ካሳለፍኳቸው ከሰላሳ በላይ ዓመታት ውስጥ ካጋጠሙኝ ሁሉ፣ የቪክቶር ሰርጌይቪች ግጆሮቭን ያህል ጨካኝና ምህረት የለሽ ግለሰብ ተመልክቼ አላውቅም። አጠገቡ መሆን ያስፈራኛል።

ከኋላዋ ያለው በር ተከፈተ። ዞር ስትል ኤድ ራውልስ በሩ ላይ ቆሞ ተመለከተችው። «መሄድ አለብሽ፣» አል።

ሩል መጠየቅ ስላለባት ነገር በፍጥነት አሰበች። እዚህ ደንዝዛ ተቀምጣ ይህ አዛውንት ጀኔራል ወሬውን እንደፈለገ እንዲቆጣጠረው ፈቅዳለት ቆይታለች። ድንቁም የቃለ መጠይቅ ባለሞያ፣ ተነስታ ቆመች። «እየመጣሁ ነው፣ ኤድ።» ወደማላክሆቭ ፈቷን አዞረች። «ቪክቶር ግጆሮ የፖሊት ቢሮውን ድጋፍ ካገኘ አውሮፓ ውስጥ የእግረኛ ሰራዊት ውጊያ ለማስነሳት የሶቪየት ጦርን መቀስቀስ ይችላል?»

ማላክሆቭም ተነስቶ ቆመ። «እያጻመጥሽኝ አልነበረም ማለት ነው፣ ብሩኪ ኪርክላንድ፣» አለ፣ ራሱን ግራና ቀኝ እያማታ። «ቪክቶር ሰርጌይቪች ግጆርቭ የስልጣን ጊዜውን የሚያራዝምለትን ማንኛውንም ድርጊት የመፈፀም ችሎታ አለው። በሱና እሱ በሚፈልገው ነገር መሀል የሚቆም ማንኛውም ሰው፣ ቡድንም ሆነ ህዝብ ደህንነቱ አደጋ ላይ ነው። ይህ ሶቪየት ህብረትንም ይጨምራል።»

«አመሰግናለሁ፣ ብላ ለመሄድ ፈቷን አዞረች።

«ብሩኪ ኪርክላንድ፣» አለ ማላክሆቭ፣ የደረጃዎቹ መጀመሪያ ላይ ሰትደርስ።

ሩል ፈቷን መለሰች።

ማላክሆቭ ፈገግ አለ። «ቪክቶር ሰርጌይቪች እያደረገ ያለው ምንም ይሁን ምን፣ እንደማትወጂው ቃል ልገባልሽ እችላለሁ።»

ከኤድ ራውልስ ጋር የትምህርት ቤት ህንፃውን ወጥታ ስትሔድ፣ ከተዘጉት በሮች በስተጀርባ ሲስቅ ይሰማታል። «የክርስቶስ ያለህ፣» አለች፣ «ይህ ትምህርት ተምሮ ከመውጣት አይተናነስም።» መኪናዋ ጋር ደርሳ ቆመችና ፊቷን ወደራውልስ አዞረች። «ኤድ፣ እንደ ባዶ ሀሳብ ይዘህ፣ የሙጥኝ ብለህ ስታሳድደው፣ የምታገኘው መረጃ ሁሉ ሀሳብህን የሚደግፍ ሆኖብህ ያውቃል?»

«አዎ፣» መለሰ ራውልስ፣ «አንድ ወይ ሁለት ጊዜ ደርሶብኛል።» በፈገግታ ተመለከታት። «በጣም አስፈሪ ነው፣ አይደለም?»

«ምንም አያጠያይቅም።» ክንዷን በትከሻው አዙራ ጉንጩ ላይ ሳመችው። «አመሰግናለሁ፣ ያደረግክልኝ ልገልጽልህ ከምችለው በላይ አስደስቶኛል።»

«እስታውሺ፣» «አላት፣ «የዛሬውን ጉዳይ የትኛውም ግህደር ውስጥ እያስገባውም፣ ማንኛውንም አይነት ሀሳብ ለማስደገፍ ትጠቅሽውም አትችይም።

«እስታውሳለሁ፣» አለች፣ መኪናዋ ውስጥ ገብታ ሞተሯን እያስነሳች። «ላንግሊ ውስጥ እንገናኝ ኤድ።»

«እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ፣ ኪት፣» መለሰ፣ ፈገግታው ከስሟል። ትልቅ ተስፋ አለኝ።»

ወደስቶዊ አትንታ ወደበርሊንግተን ዞረችና አይሮፕላኗ ወደሚጠብቃት ስፍራ አመራች። ወደዚህ የመጣችው መሰረት፣ ማረጋገጫን ለማግኘት ነው፣ አግኝታዋለች፣ ቀለል በማለት ፋንታ ሞንቀት ለምን እንደሰፈረባት አሰላሰለች።

22

ሔልደር እናቱ መሀል ላይ ቀዝቅዞበት ወዲያውኑ ትከሾቹ ላይ ከባድ ሀመም እየተሰማው ነቃ። ፊቱ ሲፈነዳ የደረሰ መሰለ። ያለበትን ሁኔታ ለመረዳት ሀሊናው እስኪመለስለተ ጥቂት ሰከንዶች ፈጀበት። በአይሮፕላን መቀመጫ ቀበቶዎች መልክ የተሰራው የወንበር ቀበቶ ትከሾቹን ጠፍሮ ይዞ ወደታች ገልብጦ እንጠልጥሎታል። ማሰሪያው ትከሾቹን ሰርስሮ እየገባ ነው። ከርቀት በማፊት ሀይል እየተንሿሿ የሚገባ የውሀ ድምፅ ይሰማዋል። ይህን ጊዜ ነበር፣ ትንሿ ሰርጓጅ በውሀ እየተጥለቀለቀች መሆኗንና የውሀው ጠለልም የተዘቀዘቀ እናቱ ጫፍ መድረሱ የታወቀው።

ከቀበቶው ካልተላቀቀ ውሀው ባፍና ባፍንጫው እንደሚገባ ስለታሰበው፣ በድንጋጤ የአደጋ ጊዜ የቀበቶ "ንስለቀቂያውን ሳበው። ቀበቶው ተፈታና ከውሀው ሰር ወርዶ ደፈቀው። እየተፋና በትንታ እየተሰቃየ ተነስቶ በመቆም የሰርጓጇን አሳሳቢ ሁኔታ ለመመርመር ሞከረ። ውሀ ቢሸፍናቸውም የላይኛ የክፍሉ መብራትና የመቆጣሪያዎቹ መብራቶች እንደነበሩ ናቸው። በተዘበራረቀው የ«አይነት አራቷ» ክፍል ውስጥ ውጥንቅጡ የወጣ ብርሀን ይፈነጥቃሉ።

ሔልደር ዙሪያውን ተመለከተ። ባለሪ ሶኮሎፍ በፊቷ ተደፍታ፣ ካለበት ጥቂት ጫማ ርቀት ላይ ትንሳፈፋለች። ይዞ እነሳት፣ ምናልባት ነፍሷ ይኖር ይሆናል። ከዚያ ግን እየጮኸ ለቀቃትና ተዝለፈለፈ። የብሉን መፍቻ እጇታው ከቀኝ አይኗ ውስጥ ተመስንሏል። ሌላኛው አይኗ ፈጦ ቀርቶ፣ መንጋጭላዋ ተንጠ ልጥሏል። ሔልደር እንድትለቀው ብሎ አንድ ነገር እንስቶ መሰንዘሩን ያስታውሳል። ተሳክቶለታል። ይህ እይታው ከፈጠረበት ሁኔታ ራሱን አረጋግቶ ስለራሱ ሀኔታ ማሰብ ለመጀመር ጥቂት ጊዜ ፈጀበት። ትንሿ ሰርጓጅ ከዋናው ቀጥታ መስመር በአስር ዲግሪ ያህል ዘመም ብላ በእናቷ ተገልብጣ ባህሩ ወለል ላይ ተኝታለች። ውሀውም እየገባ ያለው ከዋናው በር በኩል ሲሆን፣ በሩ አሁን የሚገኘው ከስር በመሆኑ ከሰርጓጇ መውጣት አይቻልም። በመጀመሪያዋ የ«አይነት አራት» ሞዴል ላይ ሌላ በር ነበረ፣ በዚህችኛው በመጠን አንሳ በተሰራችው ላይ ግን ይህ መውጫ የለም። መውጣት የሚቻለው በዋናው በር በኩል ብቻ ነው።

http://ethzare.wordpress.com

ሔልደር ተረጋግቶ ስለሁኔታው ለማሰብ ሞከረ። በሰርጓጇ ውስጥ ያሉት መብራቶች አሁንም እየበሩ በመሆኑ፣ ገና የባትሪ ሀይል አለ ማለት ነው። የውጪ መብራቶቹን ቁልፍ በዳበሳ እግኝቶ ተጫነው። ከሰርጓጇ ውጪ ያለው የባህር ወለል ሰርጓጇ ባዘነበለችበት አቅጣጫ እያሽቆለቆለ ይሄዳል። ይህ አቀማመጥ ቢያንስ በከፊል ሊያንዘባልላት እንደሚያስችለው አደፋፈረው። መብራቱን አጠፋና የሰርጓጇን ያዘነበለ ግድግዳ መርጦ በሙሉ ሀይሉ ገፋው። ሰርጓጇ በጥቂቱ ዘንበል ብላ ወደነበረችበት ተመለሰች። በተደጋጋሚ መግፋቱን ቢቀጥልም የሰርጓጇ ሁኔታ ግን አልተለወጠም።

ሔልደር አይኖቹን ከድኖ በእጁ ስለሚገኙት መገልገያዎች አሰበ። ሀይል አለው። አሰብ አደረገና የሞተሩን ማንቀሳቀሻ ቁልፎች በመያዝ በስተቀኝ ሀይል ሰጥቷት፣ የበስተግራውን ሀይል ቆረጠው። ሞተሮቹ በጣም አጓሩና ሰርጓጇ ወደጎን ካዘነበለች በኋላ መገለባበጥ ጀመረች። ሔልደር ለዚህ የሁኔታ ለውጥ ባለመዘጋጀቱ ያገኘውን ነገር የሙጢኝ•ብሎ ያዘ። ሰርጓጇ የበስተግራ ጎኗን ይዛ አረፈች።

ይህ ለውጥ ዋናውን በር ነፃ እንዳደረገለት አሰበ። ያውም ሰርጓጇ በሩ ላይ ተኝታ ካላስነከሰችው። ከተጣመመው በር በኩል ውሀ በሀይል ይጎርፍ ጀመር የውሀው ሀይል እንደመርፌዎች ይጋረፋል። ሔልደር በሰርጓጇ በስተቀኝ ጎን የሚገኘውን አሁን አናቱ ላይ ያለ በር ለመክፈት መታገል ጀመረ። ተከፈተና ሁለት የአክሰጂን በርሜሎች ላዩ ላይ ወደቁ። አንዱን አንስቶ በፍጥነት ፈታተሸው። አላስተነፈሰም። በርሜሉ የግፊት መቆጣጠሪያ፣ የአፍና የአፍንጫ መተንፈሻዎችን አጣምሮ ይዟል። በውስጡ ያለው አክስጅን ለአስር ደቂቃ እንደሚያበቃ ከስሌጠናው ያውቃል። ሔልደር ከዚህ በፊት በሰርጓጅ መርከብ መለማመጃ ትቢት ውስጥ ተመሳሳዩን ተጠቅሞበታል። የድንገተኛ አደጋ ትጥቁ በወፍራም ፕላስቲክ እንደታሸገ እግሩ ስር ይንሳፈፋል። ቀበቶውን እንገቱ ላይ አጠለቀና፣ ፕላስቲኩን አንስቶ እሽጉን ቀደደና መልሶ ከመዝጋቱ በፊት ከውስጠ ያለውን አየር የሚችለውን ሁሉ እየጨመደደ አስወጣው። ወደባህር ጠለል ለመውጣት ያለበት በተቻለው ሁሉ ቀስ ብሎ ስለሆነ፣ ፕላስቲኩ ውስጥ ያለው አየር ቶሎ ወደላይ ይዞት እንዲወጣ አልፈለገም። አሁንም ዙሪያውን ተመለከተ፣ የሚፈልገውን ሁሉ የያዘ መስሎታል።

ከመውጫው የሚረጨው ውሀ ሊያስቀውሰው ምንም አልቀረው። ከተወንጫፊው ውሀ ራሱን ከልሎ የሰርጓጇን ማስተንፈሻዎች ከፈታቸው። አሁን ውሀ ከንዱን በሚያህል ውፍረት እየዘለለ መግባት ጀምሯል። ያውም ከሁለት አቅጣጫ። አሁን የሰርጓጇ የውስጥ ከፍል ቶሎ በውሀ ይሞላል። በሚሞላ ጊዜ የውጪውና የውስጡ ግፊት ስለሚመጣን ዋናው በር ከተከፈተለት፣ ከፍቶ ማምለጥ ይችላል። የድንገተኛ ጊዜ እሽጉን አንስቶ ወደሰርጓጇ ግድግዳ በግምጣት ተደገፈው። የአፍ መተንፈሻውን አፉ ላይ ገጥሞ አየር ማስወጫውን ከፈተው። በግፊት የታመቀው አየር ወደሳንባው ገባ፣ ይሰራል ማለት ነው። መልሶ ዘጋውና ወሀው ሲሞሏ የሰርጓጇ በር ይከፈታል የሚል ተስፋ ይዞ ይጠ ባበቅ ጀመር። የማይከፈት ከሆነ ግን ማስተንፈሻዎቹን ከፍቶ ውሀ ያስገባው የራሱን ሞት ለማፋጠን ነው ማለት ይሆናል።

አሁን ውሀው ደረቱ ደርሷል፣ ከደቂቃ ያነሰ ጊዜ እንደቀረው አሰበ። ትሪና ራጉሲን ወደሀሳቡ ብቅ አለች። ሀሳቡን መልሶ ከሀሊናው አስወጣው።

አሁን ማተኮር የሚኖርበት ወደላይ እንዴት እንደሚወጣ ነው። በድንገት ትዝ አለውና የመርጫ ልብሱን ኪስ ከፍቶ የሲያናይድ መርዝ ብልቃጡን አወጣና ከፍታው እየጨመረ በሚሄደው ውሀ ላይ ወረወረው። በዚህ ሁኔታስ እያደርገውም። ባህር ጠለሉ ላይ ደርሶ ከተንሳፈፈ መያዙ አይቀርም፣ እስካሁን ቦታው በእላሽ ጀልባዎች ተጥሰቅልቋል። ወደሰርጓጇ የሚንፈቀፈቀው ውሀ ከበላዩ ያሉትን ጀልባዎች ሞተር ድምፅ ያፍነዋል። ከተያዘ እንደሚሆን ይሆናል፣ ግን ምንም ይምጣ ምን ራሱን እያጠፋም።

ውሀው እገፍቱ ሲደርስ የግፊት መቆጣጠሪያ የአፍ ክዳኑን በጥርሱ ነክሶ፣ እንደገና አየሩን ለቀቀውና የአፍንጫ ላይ ግጣሙን አስተካከለ። በግፊት ሀይል እየተስፈነጠረ ሳምባው የሚገባውን አየር በትግል ወደውጪ ማስወጣት ጀመረ። በሰርጓጇ ውስጥ ያለው አየር መሳሳት ስለጀመረ በጭንቅ መተንፈስ ላይ ነበረ። ዋናው መውጫ እስኪደርስ እየተንጠላጠለ ሄደና የግፊት መዘውሩን አሽከረከረው። ያለችግር ዞረለት፣ ለዚህ እምላኩን እመሰገን። በሩን ሲገፋው በከፊል ተከፈተና አንድ ነገር ያዘው። ከዚያ ወዲያ አልንቀሳቀስ አለው። የድንገተኛ ጊዜ እሽጉን አሾለከና፣ እንደምንም ታግሎ መውጣት ጀመረ። ለአፍታ ያህል፣ መውጣት የማይችል ስለመሰለው ድንጋጤ ሰንቆ ያዘው። ድንገት ሳያውቀው ግን ሾለከና መንሳፈፍ ጀመረ ነፃ ሆኗል።

እስከሚያስታውሰው ድረስ እስከአሁን የቆየው የሰላሳ ሜትር ጥልቀት ካለው ውሃ ስር ነበር። በጥልቀት አየር እየሳበና ሜትሮቹን ለመቁጠር እየሞከረ በዝግታ ወደላይ መውጣት ቀጠለ። የውሀው ቅዝቃዜ አይጣል ነው። ስለዚህ ላለማሰብ እየሞከረ ይቆጥራል። ሰላሳ ላይ ሲደርስ ውሀው የሞቀ መሰለው፣ ግን ገና ጠለሉ ላይ አልደረሰም። ዙሪያው በብርሀን ተከቧል፣ አፍታ ሳይቆይ እንደሚደርስበት ታውቆታል።

ድንገት፣ ሳምባው በግማሽ በአየር እንደተሞላ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የበርሜሉ አየር አለቀ። ገና መች አስር ደቂቃ ሞላ፣ አራት ወይ አምስት ቢሆን ነው፣ አሰበ። የሳባትን አየር አምቆ ይዟት ከቆየ በኋላ አስወጣቺ። ጠለሉ የት ነው? ውሀውን ወደሳንባው ሲስበው መሆኑን እያሰበ ሳለ ግን፣ ጠለሉ ላይ ደርሶ አየር አገኘ፣ የአፍና የአፍንጫ ግጣሞቹን ተፋቸው። ዙሪያውን ተመለከተ። ከባድ ጭጋግ አለ፣ ጥቅጥቅ ያለጭጋግ፣ በሰሱም ያካፋል። ላይያዝ መሆኑ ነው።

ከግራና ቀኙ አንድ ከርቀት አንድ ከቅርብ የሚመጡ የሞተር ድምጾች ይሰሙታል። ሔልደር ትጥቁን የያዘውን የኘላስቲክ ከረጢት ዚኘ ከፈተና በትንፋሹ ሞልቶ ለቀቀው። የሚደግፈው ነገር አግኝቷል። የአየር በርሚሉን አውልቆ እንዲሰምጥ ለቀቀው። የመርጫ ጫማዎቹንና ልብሶቹን አወላለቀ ከውስጥ ሱሪው ሌላ እርቃኑን ቢሆን በተሻለ መዋኘት ይችላል። ግን ወደየት?

በቅርቡ ያለው ጀልባ እስኪርቀው ድረስ ጠበቀና ሁለት ጣቶቹን አፉ አስገብቶ በቻለው ሀይል ሁሉ አጮጨ። ድምፁ ጭጋጉ የዋጠው ይመስል ከሰመ። ፊቱን እዙሮ ዳግመኛ አጮጨ። ድምፁ ከሰመ። አሁንም ፊቱን ወደሌላ አዙሮ ደግሞ ሞከረ። አሁን ግን የገደል ማሚቱ የተፈጠረ መሰለው። ፕላስቲኩን በልጅነቱ ዋና ሲለማመድ ተንሳፋፊ ይዞ እንደሚያደርገው እየቀዘፈ መዋኘት ጀመረ። በዙሪያ ከብ ሲዋኝ መቆየት ስላልፈለገ ሁለቱንም እግሮቹን እኩል በማወናጨፋ ተግባር ላይ አትኩሮቱን አሳረፈ። እያጮጨና እየዋኘ በእሱ ሰዓት

http://ethzare.wordpress.com

አቆጣጠር ግማሽ ሰዓት ያህል ቆየ። የፋጨቱ ማሚቶ በጥራት እያስተጋባ ጆሮው መድረስ ጀምሯል። ለአምስት ደቂቃ አረፈና ቀጠለ። ዳግመኛ አረፍት ሲያደርግ እግሩ ቋጥኝ ላይ አገኘው። ሳሩ ላይ እየዳኸ ወጥቶ ጭጋጉ ላይ አፈጠጠ። ከበላዩ፣ አንድ ትንሽ ነጭ ቤት ታየው። ቆሞ ለማረፍ ስለፈራ በውሀው ዳርቻ እየተንገዳገደ መጠለያ ፍለጋ ይባዝን ጀመረ። ከአጭር ጊዜ በኋላ፣ አንስተኛ ጀልባ እየተንሰፈፈች ወደእሱ ስትመጣ ተመለከተ።

በሩ አልተቆለፈም። ወደውስጥ ሲገባ የአምስት ሜትር ርዝማኔ ያለው የስፖርት የሞተር ጀልባ ከቤቱ ጋር ታስሮ አገኘ። ጀልባው ውስጥ ገብቶ በቆዳ ሶፋው ላይ ተዘረጋ። ከጀልባዋ የፊት ለፊት መስታወት ስር ሁለት እርጥብ ፎጣዎችን አግኝቶ ገላውን አደራረቀና ከዚያም ተጠቀለለባቸው። ሕይወቱ አለች፣ ለጊዜውም ቢሆን ከአደጋ ርቋል። በዚህ ጭጋግ ጀልባን የሚጠቀምበት አይኖርም። ሞቀው፣ እንቅልፉ እየመጣ ነው። ሰውነቱ የወንበሩን መደገፊያ እንደነካ፣ አንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ።

23

ሩል ናሽናል አየር ማረፊያ እንደደረሰች ወደአንድ የህዝብ ስልክ አመራች የስልክ ቁጥር ማውጫውን ቢጫ ገፆች ከገላለጠች በኋላ የምትፈልገውን ቁጥር መታች። እሁድ ምሽት ሶስት ሰዓት ቢያልፍም የሀያአራት ሰዓት አፐሬተር እንደሚኖር ገምታለች። አልተሳሳተችም። ሴቲቱ ጠብቂ ብላት መስመሩን ወደሌላ ቦታ መራችው።

«ዳኒ ነኝ፣» አለ አንድ የወንድ ድምፅ።

«ዳኒ በርጊስ ነህ?»

«ራሱ ነኝ። ማን ልበል?»

«ቢግልስን አስታወስከው?»

«እንዴታ በጣም እንጂ።»

«አንድ ሥራ ማሰራት ፈልጌ አንተን እንዳገኘህ ጠቁሞኝ ነው።»

«ምን ዓይነት ሥራ?»

«ቤት ማፅዳት ፈልጌ ነው። ሁለት ቤቶች።»

«እንዱ የራስሽ ነው?»

«አዎ።»

«የምትደውይልኝ ከዚያ ነው?»

«አይደለም። ቢግልስ ችግር የማያመጣ ስልክ ተጠቀሚ ብሎኛል።»

«መልካም። አድራሻሽን ስጪኝ።»

ሰጠችው።

«በምን ያህል ጊዜ ትደርሳለህ?»

«በግማሽ ሰዓት ወስጥ።»

«በሰላሳ አምስት ደቂቃ እሺ?»

«ፅዳቱን ዛሬማታ ልታደርጊው ነው እንዴ?»

«የሚመችህ ከሆነ። ግሩም ስራዎችን የምሰራው በምሽት ነው። የማናግርሽ ከመኪናዬ ሆኜ ነው፣ አሁን የሚያሰፈልገኝን ነገር ሁሉ ይዤያለሁ።»

«እሺ። ሰላሳ አምስት ደቂቃ ይሁን።»

«መልካም፣ ስምሽ ማነው?»

«ካትሪን ሩል።»

«ጥሩ ካቲ፣ እዚያ ስደርስ ደወል አልደውልም እንኳኳለሁ። ስታስገቢኝ፣ ምንም አትናገሪ። ቁመቴ ስድስት ጫማ ከአንድ ኢንች ነው፣ የቤዝቦል ባርኔጣ አደርጋለሁ፣ ትከሻዬ ሰፊ ነው፣ ማራኪ ነኝ። የከተማ ቤት ነው አይደለም? አቀማመጡ እንዴት ነው?»

«መግቢያ፣ ሳሎንና መመገቢያ ክፍሉ በዋናው ወለል ላይ ይገኛሉ፣ በታችኛው ወለል ውስጥ ኩሽናውና የጥናት ክፍሉን ታገኛለህ፣ በላይኛው ፎቅ ላይ ደግሞ ሁለት መኝታ ቤቶች አሉ።»

«ከላይኛው ክፍል ጀምሬ ወደታች እወርዳለሁ፣ ንፁህ ሲሆን እንነጋገራለን። ስንት የስልክ መስመሮች አሉ?»

«አንድ።»

«ኤክስቴንሽኖችሽስ?»

«እ፣ እምስት- እይደለም ስድስት።»

«ስንት ቴሌቭዥኖች አሉ?»

«ሁለት- መኝታ ቤቱና ሳሎኑ ውስጥ።»

«እኔ ከመምጣቴ በፊት ሁለቱንም ከፈቺያቸው። ክፍሎቹ ውስጥ ሬዲዮኖች ካሉም ሁሉንም ከፈቺያቸው።»

«ኩሽናው ውስጥ አንድ አለ።»

«መልካም። ሰላሳ አምስት ደቂቃ።»

ሩል ከመኪና ማቆሚያው ወጥተ መኪናዋን አስነስታ ወደቪታ አመራች። ከክፍል ክፍል እየተዟዟረች ቴሌቭዥንና ሬዲዮኖችን ከፈተች በኋላ መግቢያው ኮሪደር ላይ ሆና መጠባበቅ ጀመረች። ልክ በሰዓቱ በሩ ተንኳኳ። ስትከፍተው አንድ ሰው ገባ። ጨብጣው፣ «ታዲያስ፣» አለችው። ራሱን እንደገለፀላት ዓይነት ቁመና አለው፣ በተጨማሪ ደግሞ አጭር ግራጫ ፀጉርና ሁለት ሳምንት የሚሆነው ግራጫ ፂም አለው። የቤዝቦል ኮፍያው ላይ ቢኤስ የሚል ፊደል ይታይበታል። እሱ ወደላይኛው ፎቅ ሲሄድ እሷ ሳሎን ገብታ በቴሌቭዥን የድሮ ፊልም መመልከት ጀመረች። ከአርባ ደቂቃ በኋላ ጣቱን አፉ ላይ ቀስሮ ወደ ሳሎኑ መጣ ስልኩን አነሳና የሽቦውን የኤሌክትሪክ ፍሰት መጠን ከለካ በኋላ መነጋገሪያውን ማጸመጫውን ፈታው፣ ከዚያም ሁለቱንም ቦታቸው መለሳቸው።

ወደተቀመጠችበት አመራና ጎንበስ ብሎ በሹክሹክታ፣ «ዋናው የስልክ ሳጥን የት ነው?»

ሩል ሆነ ብላ ትከሻዋን ሰበቀችና በእሱታ ምልክት አሳየችው። ራሱን ከፍ ዝቅ አድርጎ ከክፍሉ ወጣ። ከአስር ደቂቃ በኋላ ወደሳሎኑ ተመልሶ ቴሌቭዥኑን አጠፋው።

«ንፁህ ሆኖልሻል፣» ብሎ፣ እጁን ኪሱ ከተተና ሁለት ትንሽ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችና አንድ ተለቅ ያለ አጭር አንቴና ያለው ጥቁር ሳጥን አውጥቶ የቡና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጣቸው። «ብዋናው መኝታ ቤትና መግቢያ በሩ ላይ ባለው ስልክ ላይ ሁለት ድምፅ ማሰራጫዎች ተገጥመውብሻል። ሁለቱም ስልኩ በተዘጋ ጊዜም መሳብ የሚችሉ ናቸው።

http://ethzare.wordpress.com

በግድግዳዎቹና በኤሌክትሪክ መሳሪያዎቹ እንዲሁም አምፖሎቹ ላይ ምንም ነገር የለም።»

ሩል ሁለቱን መሳሪያዎች አንስታ መዳኗ ላይ አገላበጠቻቸው። ሌላ ላለመኖሩ ርግጠኛ ነህ?»

«የምትከፍይኝ ለዚህ አይደለም እንዴ ሚሲስ ሩል?»

«ይቅርታ።»

«ጥራት ያለው ስራ አልተሰራም፣ ሁለት ብቻ ናቸው። ወይ በጣም ድንጉጥ ነው፣ ወይንም ሥራውን ማጠናቀቅ ከመቻሉ በፊት ያቋረጠው ነገር አለ።»

«መሣሪያው ምን ዓይነት ነው?»

«ከተራ የጃፓን ኤሌክትሮኒክሶች ላይ የተወሰዱ አካላት ናቸው፣ በየትኛውም የራዲዮ መለዋወጫ መደብር የሚገኙ ናቸው። ከሌላ ሀገር መምጣታቸውን የሚያመለክት ምንም ነገር የለም። ጥሩ መሳሪያ ነው፣ ግን ተራ ነው። ሁለቱ ትንንሽ ማሰራጫዎች በስልክ ስትነጋገሪ ባለሽበት ክፍል ከአስራ ሁለት እስከ አስራ አምስት ጫማ የክብ ስፋት ውስጥ ይቀበሉሻል፣ ከዚያም ድምፁን በስልክ መስመርሽ በኩል እታችኛው ክፍል ወዳለው ዋና የስልክ ሳጥን ይልኩታል፣ እዚያ የተገጠመው ጥቁር ሳጥንም ድምፁን በአንድ ዋት ሀይል ከፍተኛ ፍሪኩዌንሲ (VHF) ወደአየር ያሰራጨዋል። ይህ ሞገድ በሩብ ማይል ርቀት ላይ ባለ በማንኛውም ሬዲዮ መደመጥ ይችላል። እንከን የለሽ ቅንብር ባይሆንም፣ ሰውየው ግን መኪናው ወስጥ ወይንም ከአፓርትመንትሽ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኝ ሌላ አፓርትመንት ውስጥ ሆኖ ሲያዳምጥሽ ይችላል። ግን በቤትሽ ያደረገውን ለማሳካት ሲል ሌላ አፓርትመንት መከራየት ከመጠን በላይ ወጪ ይሆንበታል ብዬ አስባለሁ። ምናልባት ሲከታተልሽ ቆይቶ ሊሆን ይችላል። እንቀስቃሴዎችሽ ድግግሞሽ ያላቸው ናቸው? ቢሮ፣ የግሮሰሪ መደብር፣ በምሽት መውጣት፣ ይህን አይነት ነገር?»

«አዎ እንደዚያ አይነት ነገር ነው።»

«ስለዚህ ትልቅ ወጪ ማውጣት አያሻውም። እስከ ቤትሽ ድረስ ተከታትሎሽ ስትገቢ ከመኪናው ሆኖ ቢያዳምጥሽ ይሻለዋል። መኪናሽ የት ናት?

«ከቤቴ ፊት ለፊት ጥቂት በሮችን አልፋ ቆማለች። ቢ ኤም ደብሊዩ 320 አይ ሞዴል።» ብላው ቁለፎቿን ሰጠችውና ወጣ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ተመለሰ።

«ንፁህ ናት፣» አለ። «ነገሩ ብዙም የጎላ አይደለም። እንደሚከታተልሽ እታውቂም የሚል ግምት አለው፣ የምተደብቂው ነገር እንደሌለ ይሰማሻል ከቪግልስ ጋር የምትሰሪው ስራስ?»

«እሱ ሊሆን ይችላል።»

«በስልክ ወይንም ቤት ውስጥ ስለራስሽ ታወሪያለሽ?»

«በፍፁም።»

«እዚያኛው ቤትስ?»

ከዊል ጋር ስለግጆሮቭ ያደረገችውን ውይይት ስታስበው ጆሮዎቿ ቀሉ። «በፍፁም፣» ዋሸች።

«ያኛውን ቤት እንድፈትሽ ትፈልጊያለሽ?»

አድራሻ ሰጠችውና የዊልን መኖሪያ ቤት ቁልፍ ፍለጋ ኪሶቿን ፈተሸች።

«ጓደኛሽ ነው?»

«አዎ።»

«አሁን የት ነው ያለው?»

«ስቶክሆልም። ዛሬ ጠዋት ነው የሄደው።»

«ችግር ከሌለ አሁኑኑ አደርገዋለሁ።»

«ችግር የለም አድርገው።»

«ከአንድ ሰዓት ባነሰ ጊዜ እመለሳለሁ።» አለ።

ሩል ልብሷን አወላልቃ የሞቀ የገላ ውሀ ውስጥ ገባች። የጥፍሯን ቀለም አስለቅቃ፣ የእግሮቿን ፀጉር ተላጨችና፣ ፀጉሯን ታጥባ ምን ስትናገር ድምጿ ተቀድቶ ሊሆን እንደሚችል አሰበች። ባለፎጣ ጋዎን ለብሳ ፀጉሯን በጨርቅ እንደጠቀለለችው በርጊስ ተመለሰ። «ስለአደጋ ጊዜ መሳሪያው ሳትነግሪኝ ረስተሽዋል።» አለ ዳኒ በርጊስ።

«ውይ አምላኬ። ረስቼዋለሁ፣ ፖሊሶች መጡ?»

በርጊስ ራሱን ወዝውዞ ፈገግ አለ። «እንደእድል ሆኖ ከራሴ ስራዎች መሀል እንዱ፣ የራሴ ማስተር መክፈቻ ቁጥር አለኝ። የኔ ስራዎች ድርጅታቸው ውስጥ ብዙ መኖሪያ ቤቶች ላይ ተገመዋል። እዚህም እንድ ማስገጠም ትችያለሽ። ይህ ለዝርፊያ የሚያመች ከተማ ነው።»

«ልክ ነህ፣ ስለዚህም መነጋገር ይኖርብናል። እዚያስ ምን አገኘህ?»

«ልክ የዚህን ተመሳሳይ ትንብር፣ መኝታ ቤቱና ሳሎኑ ውስጥ። ይህ ማለት ከሁለት በላይ የማጥመድ ሀሳብ አልነበረውም፣ ሁለት ጊዜ ሊሰናከል አይችልም። ጥቁሩ ሳጥን ውስጥ ካለት ሁለት የባትሪ ድንጋዮች መሀል አንዱ አፈንግጦ ወጥቷል፣ ሰውየው ዝርክርክ ነው። እንደምገምተው ረጅም ጊዜ አልሆነውም ስለዚህ ከናካቴው አገልግሎት አልሰጠም። ሰውዬሽም ተመልሶ ሊያስተካክለው እድል አላገኘም።»

«ዳኒ፣ ስለዚህ ሰው ማንነት የምታቀው ነገር አለ? ማለቴ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ?»

«ከአንቺና ከቪግልስ የሥራ ባልደረቦች መሀል አንዱ አይደለም። የዘመኑን ቴክኖሎጂ የተከተለ አይነት ናቸው። ለእነሱ ይህ በጣም ቀላል ነው። በፍቺ ሂደት ላይ ነሽ?»

«አይ፣ ከሁለት ዓመት በፊት ነው የተፋታሁት። ለምን ጠየቅሽኝ?»

«መቼም፣ይህን ነገር የግል መርማሪ የሀገር ውስጥ ጉዳይ አድርጌ በተመለከትኩት ነበር፣ ግን ከተፋታሽ ያን ያህል ጊዜ ከቆየሽ፣ ነገሩ ሌላ ነው። በገንዘብ ወይ በሌላ ጉዳይ ላይ እየተከራከርሽ ነው እንዴ?»

«አይደለም፣ ያ በጊዜው በድርድር ተፈቷል። እሱ ልጄን አይፈልግም፣ እኔ ደግሞ ገንዘቡን አልፈለግኩም።»

«ይህ ጠላትሽን ወደአንድ ያሳንሰዋል፣ አይደለም?»

«እውነት? የውጭ ዜጋ መሆኑን የሚያመለክት ነገር አለ?»

«የተለየ ነገር የለም። ከሰራቸው ጥቂቱን ተመልክቼያለሁ። ሩሲያዊ ቢሆን አንኳን መሳሪያዎቹን በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ነገሮች ሊያዘጋጅ ይችላል፣ በተለይ ይታወቅብኛል ብሎ የሚጀፈራ ከሆነ። የሆነ ጠላት ከሆነ እንብዛም

http://ethzare.wordpress.com

አልፈለጉሽም ማለት ነው፣ ያደረጉት ጥረት በቂ አይደለም። ምናልባት ጓደኛሽ እያደረገ ባለው ነገር ውስጥ እስፈራርተው አንድ ነገር ሊያደርጉሽ አስበው ይሆናል። ይህ የሚገጣጠም ነገር ነው። ወይ ደግሞ ከቢሮሽ አንድ የወረቀት መረጃን አስገድደው ሊያስመጡሽ ይሆናል። እንቺ ላይ እምነቱን ለመጣል የሚተማመን ሰው አለ?»

«የለም?»

«እሺ፣ እንዲህ ሊሆን ይችላል ብዬ እስባለሁ፣ እሱ አልጋሽ ላይ ተኝቶ ከነበረ ፈጣን ትንፋሽና የተወሰነ ንግግር ሊደርሳቸው ይችላል፣ እንቺ እሱ አልጋ ላይ ተኝተሽ ከነበረ ግን ምንም አያገኙም። ከቤትሽ ፊት ለፊት ከመንገዱ ባሻገር የሚኖሩትን ሰዎች ታውቂያቸዋለሽ?»

«አዎ። ለሃያ፣ ለሰላሳ ዓመታት እዚያው የኖሩ አዛውንት ባልና ሚስት ናቸው።»

«ከላይኛው ፎቅ መስኮታቸው በኩል በኢንፍራሬድ ካሜራና በረጅም ሌንስ ያንቺ ቤት ይቀረፃል፣ ግን መጋረጃውን ከገለጥሽው ብቻ ነው የሚያሰጋሽ። ከጓደኛሽ መኖሪያ ቤት ግን ፎቶ ለማንሳት የቤቱ አቀማመጥ አይፈቅድም።»

በጣም ከፍተኛ እፎይታ ወረራት። ዊል እሷ አልጋ ላይ ተኝቶ እያውቅም፣ እሱ ቤት ውስጥ የተናገረችው ሁሉም አልተሰማም። «መልካም፣ አመሰግናለሁ ዳኒ፣ ምን ያልህ ልክፈልህ?»

«አንድ ሁለት መቶ ይበቃል። ይሄውልሽ፣ በአንድ ሺህ ስምንት መቶ ቤትሽ ላይ የእጁጋ ጊዜ ማመልከቻ መሳሪያ ልግጠምልሽ፣ እመኚኝ ይህ ዋጋ ርካሽ ነው። ከዚያ ሁሉንም አንድ ላይ አስብልሻለሁ። ይህን ካደረግኩ ዳግመኛ ድምፅ ማሰራጫ ሊያጠምዱብሽ ይከብዳቸዋል»

«አሃ? ታዲያ እዚያኛው ቤት ላይ እንዴት አጠመዱት?»

«ከሁለት በአንዱ መንገድ፣» መለሰ በርጊስ በድፍረት። «ወይ ቁጥሩን ያውቁታል፣ የዚህ ዕድሉ ጠባብ ነው፣ ወይ ደግሞ ጓደኛሽ አንድ ቀን መሳሪያውን ሳያስነሳ ረስቶት ዕድል ቀንቷቸዋል።»

«ሁለተኛው ይመስለኛል። እንደዚያ ዓይነት ሰው ነው። ይሁን ዳኒ፣ መሳሪያውን ግጠምልኝ።» መግቢያ ኮሪደሩ ላይ ወደሚገኝ የጠረጴዛ መሳቢያ አመራችና አንደ ቁልፍ አውጥታ ሰጠችው። «በተመቸህ ጊዜ፣» አለች። «እኔ ቀኑን ሙሉ፣ በየቀኑ ቢሮኝኝ።»

«ልክ ነሽ ሩል፣» አለ ቁልፉን ኪሱ እየከተተ። «በዚህ ሳምንት አንድ ጊዜ ልሰራው እሞክራለሁ። ራሴ እሰራዋለሁ። እ. . . ስሚ፣ ስለዚህ ሁኔታ ልታደርጊው የምትችይው አንድ ሌላ ነገር አለ።»

«ምንድን ነው?»

«ለጥቂት ቀናት ልከታተልሽ። የሚከታተልሽን ሰው አገኘውና እናግረዋለሁ።»

ለአፍታ አሰብ አደረገችበት። «አይ፣ አሁን አይደለም። ነገሩ ከዚህ በፈጠነ ሁኔታ እንዲሟሟቅ አልፈልግም። ግን ሀሳቤን ከቀየርኩ እንግሀለሁ።»
«ያልሽውን አድርጊ። ከሱ ጋር ትንሽ ብጨዋወት ደስ ይለኝ ነበር።»

«እመሰግናለሁ ዳኒ፣» ብላ ሸንችውና በሩን ዘግታው ተደገፈችው። ሰውየው አካባቢዋ ሲሆን የተሻለ ስሜት ይሰማታል። ግን እየተከታተለ ቤቷ

ውስጥ ድምፅ ማሰራጫ የሚያጠምደው ማን ነው? ፀጉሯን በጨርቁ እያደረቀች ወደላይኛው ክፍል አመራች።

24

ሔልደር ከእንቅልፉ ብንን ብሎ ነቅቶ፣ መንቀሳቀስ እያስፈራው ባለበት ቀረ። የቀሰቀሰው የጀልባ ሞተሮች ድምፅ ነው። ከቆዳ ወንበሩ ጋር የተለጠፈው ጉንጩን አልቦታል። የተፈጠረው ነውጥ አልጋውን ሲያወዛውዘው ራሱን ዝቅ አድርጎ ጠበቀ። ከዚያ ሞተሮቹ ርቀው ድምፃቸው እየከሰመ ሲመጣ ቦታው ተመለሰና። ቀና ብሎ ተቀመጠ። የጀልባ ላይ ቤቷ ከውጭ የሚገባው ብርሀን ደብዛዛ ፍንጣቂ አድምቋታል። የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ። ልክ አስራ ሁለት ሰዓት አልፏል። ግን ከምሽቱ ይሆን ከንጋቱ? ከምሽቱ መሆን አለበት ብሎ ወሰነ፣ ተልዕኮውን የጀመረበት ቀን አላለቀም።

ወደሌላ ስፍራ በቶሎ የመሄድ ፍላጎት እደረበት። እዚህ የጀልባ ቤት ውስጥ መቆየት የለበትም። የፕላስቲክ ከረጢቱን ከፈተና የናይለን ሙቅ ካፖርቱን አወጣ፣ ምሽት በመሆኑ ጠቆር ያሉ ልብሶችን መረጠ። የነሀስ ቁልፎች ያሉት ደማቅ ሰማያዊ ጃኬት፣ ግራጫ ጠቃጠቆ ያለው ሱሪ እና ጥቁር የመንገድ ጫማ፣ ሙሉ ቁልፍ ያለው ነጭ ሸሚዝና፣ ባለመስመር ከረባት። ዋናው ገላውን ቢያፀዳለትም፣ ፂሙን መላጨት ያስፈልገዋል። እዚህ ግን አያደርገውም። የጀልባ ላይ ቤቱን በር በጥቂቱ ገርበብ አድርጎ በጥንቃቄ አስተዋለ። በአቅራቢያው ከሚገኝ መኖሪያ ቤት በኩል ብርሀን ይታየዋል፣ ግን ቤቱ አካባቢ ማንም የለም። የባህር ዳርቻውን ይዞ ከጀልባው በመውጣት በፍጥነት እየተራመደ በተከረከመ ረዥም ዛፍ መሀል አለፈ። ሌላ ቤት ተቀበለው፣ በግምት በሀያ ሜትር ርቀት ላይ ነው። አንድ መንገድ መኖር አለበት፣ ከእነዚህ ቤቶች በስተጀርባ መሆን ይኖርበታል። ሰው ፍለጋ አይኖቹን እያማተረ የተከረከሙትን ዛፎች ተከትሎ መንገድ ቀጠለ። የቴኒስ ኳስ ድምፅና ሳቅ ተሰማው። ከዚያም ከቤቱ በስተጀርባ ወጣት ሴትና ወንድ የሚጫወቱበት የቴኒስ ሜዳ ተቀበለው። የተመለከቱት ቢሆን እንኳን አላስተዋሉትም። ሬንጅ የበዛበት መንገድ አገኘና በሁለቱም አቅጣጫ ተሟዙሮ ተመለከተ። ምን ይፈይድለታል? የፀሐይዋን አቅጣጫ ተመለከተና ወደዚያው አቀና። ስቶኮልም የምትገኘው በስተምዕራብ ነው። እሱም መሐድ የፊለገው ብዙ ሺህ ሰዎች መሀል ገብቶ መቀላቀል ወደሚችልበት ወደስቶክሆልም ነው። ሳይጣደፍ በፍጥነት መራመድ ጀመረ። የሚሄድበትን የማያውቅ ግን ያልተደናገጠ ሰው ለመምሰል። በግምት አንድ ኪሎ ሜትር ከተራመደ በኋላ መንታ መንገድ ላይ የሚገኝ ባለመጠለያ የአውቶቡስ ፌርማታ አጠገብ ደረሰ። የተሰቀለውን የጊዜ ሰሌዳ ተመለከተ፣ ከሀያ ደቂቃ በኋላ ወደ ስቶክሆልም የሚሄድ አውቶቡስ ይመጣል። ጥሩ ነው። መንገዱን ላይና ታች ቃኘ። ሁለት መኪኖች ተከታትለው በፍጥነት አለፉ ግን እግረኛ የለም። መጠለያው ውስጥ ተቀምጦ ሻንጣውን ከፈተና፣ የያዛቸውን ነገሮች ፈታተሸ።

አንድ ሺህ ስምንት መቶ የስዊድን ክሮነር፣ መቶ ሰባ ዶላር እና በተጓዥ ቼክ መልክ አንድ ሺህ ዶላር አለው። ለዚህ ቼክ በካርል ስዌንሰን ስም

http://ethzare.wordpress.com

ፈርሞበታል። የኪስ ቦርሳ፣ የቪዛ ካርድ እና የአሜሪካ ኤክስፕሬስ ካርድም አለው፣ ሁሉም በተገቢ ሁኔታ ያገለገሉ እንዲመስሉ የለፉ ቢሆኑም ገና እድሚያቸው ሊጋ ነው። በዚህ ቀን ከአሜሪካ ወደ ስዊደን መግባቱን የሚያረጋግጥ ማህተም ያረፈበት የአሜሪካዊ ዜጋ ፓስፖርት እና በስካንዲኒቪያ የአየር መንገድ ከስቶኮልም ወደኒውዮርክ የመመለሻ ያላገለገለ ትኬት ይዟል። ቅያሪ ልብሶች፣ የንፅህና ዕቃዎች ቦርሳ፣ የንድፍ ማውጫ ማስታወሻ ደብተር፣ የስቶኮልም ከተማ ካርታና የስዊድን ቦታ ጠቋሚ መፅሔት እንዲሁም ባለዘጠኝ ሚሊ ሜትር ሽጉጥና ሁለት ሙሉ ካርታ ጥይት። ከሽጉጥና ከጥይቱ በስተቀር እነዚህን ሁሉ በየኪሶቹ ጨመራቸው። አይፈልጋቸውም፣ ከሌሎች ንብረቶቹ ጋር ይፃረራሉ። ደግሞም ከስዊድን እየተታኮሰ የመውጣት ሀሳብ የለውም ወደቦርሳው መለሳቸው። የሚያገኘውን የመጀመሪያ እድሉን ተጠቅሞ ያስወግዳቸዋል። ከንፅህና ቦርሳው በባትሪ የምትሰራ አነስተኛ ዒም መላጫ አወጣና፣ በፍጥነት በጉንጮቹ ላይ እንሸራሸራት። ፀጉሩን በጥንቃቄ አበጠረ። በትንሿ መስታወት ላይ የተመለከተው ምስሉ ምንም ጥርጣሬን የማያስነሳ ግለሰብን ነበር።

አውቶቡሱ መጣ፣ ተሳፈረ። «ስቶክሆልም?» ሲል ሹፈሩን ጠየቀው።

ሰውየው ኦምንታውን በምልክት ገለፆ። በእንግሊዝኛ፣ «አስራ ስድስት ክሮነር።» አለ።

ሔልደር ድፍን ሀምሳ ክሮነር ሰጠውና መልሱን ተቀበለ። ሹፈሩ ያለጉትጎታ በእንግሊዘኛ ስላናገረው ደስ ብሎታል። አውቶቡሱ በስተኋላ ገደማ መቀመጫ ያዘ። በጣት የሚቆጠሩ ተሳፋሪዎች ብቻ አብረውት አሉ። በጣም ቢርበውም ይህን ሀሳብ ከሀሲናው አስወጣው። የስቶክሆልም ካርታውን ዘረጋና በጥንቃቄ ከመረመረው በኋላ ወደቦታ ጠቋሚ መፅሔቱ ተሸጋገረ። ያሰጨነቀው የምግብ፣ የመጠለያና ያለመታሰር ሀሳብ ነው። ከተማይቱ ውስጥ በሁለት እግሩ መደላደሉ አንዳረካው፣ ለድካም ተሸንፎ እንጎላጀ። ያለበት ሁኔታ ፍፁም ሰላምን አጎናፅፎታል።

የስቶክሆልም መግቢያ አቅራቢያ ነቃ። ህንፃዎቹ በአጠገቡ እያለፉት ሲሄዱ በአድናቆት ይመለከታል። ሁሉ ነገር ከሶቪየት ከተሞች በጣም ተለየበት ህንፃዎቹ እንከን የለሽና ንፁህ ናቸው። የሞስኮ ወይ የሌኒንግራድ ቢሆኑ፣ በንፅህና እና በጥሩ ሁኔታ የሚያዙት የህዝብ ንብረት ከሆኑ ብቻ ነው። ከጠበቀው በላይ ብዙ ዛፎች አሉ። ሩሲያ ውስጥ የነበሩት የከተማ ዛፎች በታለቁ ሀገር ፍቅራዊ ጦርነት ወቅት ለማገዶነት ተቆርጠው፣ የቀሩትና በምትካቸው የተተከሉት ጥቂት ናቸው። የመደብሮቹ ቁጥር ብዛትም መስጠታል፣ ጎዳናዎች በሰዎች ቢሞሉም ቅሉ ከመደብሮቹ ውጪ ሰልፍ የለም። መኪኖቹ በሙሉ የቤት ናቸው። የሰራዊቱ ተሽከርካሪዎች የሉም።

በዋናው የአውቶቡስ ፈርማታ መአከል ታክሲ ያዘና ሹፈሩን ወደጥንቷ ከተማ እንዲወስደው ጠየቀው። ከቤተመንግስቱ አጠገብ ወረደና፣ በአስራአራተኛው ክፍለ ዘመን እንደተሰሩ በሚያውቃቸው ቀጫጭን የጥንቷ ከተማ መንገዶች ላይ መራመድ ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ ሉርድ ኒልሰን ተብሎ ወደሚጠራ እንድ ሆቴል ደረሰ። ያልተያዘ ክፍል የለም፣ እንግዳ ተቀባይዋ ወጣት ግን፣ በቅርብ ወደሚገኝ ተባባሪ ሆቴል ደውላ ጠየቀችለት። «እድለኛ ነህ፣» አለችው። «አንድ ክፍል ተለቋል። በተለምዶ በዚህ የአመቱ ወቅት ትርፍ

ክፍል አይኖረንም።» ሌዲ ሀሚልተን የሚል የሆቴሉንም ስም የያዘ ካርድና አቅጣጫ ሰጠችው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፣ ከመርከብ መኝታ ቤት እንብዛም በማትገዝፍ በጣም ትንሽ፣ ግን ሽጋ መኝታ ክፍል ተወሰደ። ልብሶቹን ሰቀለና ሽጉጡን ምን እንደሚደርገው አሰበ። መሳቢያና ቁምሳጥኖቹን ሲከፋፍት በቢራና በለስላሳ መጠጦች የታጨቀ ትንሽ ማቀዝቀዣ አገኘ። ጠርሙሶቹን እንስቶ የበረዶ ሳጥኑን አወጣና፣ ከስር ሽጉጡንና ጥይቶቹን አኑሮ መለሰው። ስዊድኖች በየአለቱ የአሜሪካውያንን ጎብኚዎች ክፍሎች ይፈትሻሉ ብሎ መገመት አልቻለም። እንግዳ መቀበያው ቦታ ፓስፖርቱን እንኳን አልጠየቁትም።

ከሆቴሉ ወጥቶ ምግብ ቤት ፈለገና፣ አራት ተከታይ ያለውን ምግብ እንደ እውሬ ተመገበና በጠርሙስ ወይን አወራረደው። ከዚያም ረከቶና ጠግቦ በድካም እንደዛለ እየተሳተተ ወደክፍሉ ተመልሶ አልጋው ላይ ሲወድቅ፣ ከእረፍት ሌላ ምንም ነገር ማሰብ ተስኖት ነበር። የሔልደር የነፃው አለም የመጀመሪያ አዳሩ ያለህልም አለፈ።

25

ሩል ከለመደችው ጊዜ በላይ በእንቅልፍ አሳልፋ ኤክስኮም ሁለት ሰብስባ ላይ ለመገኘት ትጣደፋለች። ድምጽ ሳታሰማ ከመምጣቷ በፊት በጭለማ ወደተዋጠው የመሰብሰቢያ ክፍል ገባች። የምስል ጥናት ክፍሉ ፔንራም በስክሪኑ ላይ የሚታየውን እንድ የሳተላይት ምስል እያብራራ ደረሰች።

«እዚህ የምትመለከቱት ምዕራብ ሩሲያ ውስጥ፣ በኢስቶኒያና በላቲቪያ ድንበሮች አጠገብ፣ ፕላስኮቭ ላይ የሚገኘውን የሌኒን የአይሮፕላን ማምረቻ ኢንዱስትሪ ነው። የኢንዱስትሪው ግንባታ የተጀመረው ከአራት ዓመት በፊት ሲሆን፣ በማንኛውም የግምት ደረጃ የሚገባውን ያህል ግልጋሎት ባይሰጥም ለሁለት ዓመታት ያህል በሂደት ላይ ቆይቷል። ህንፃው በዐዝመት የእንድ ማይል ያህል ርዝመት፣ የእሩብ ማይል ስፋት ሲኖረው፣ ይህ ግዝፈቱ ግዙፍ የጦር ሰራዊት ማጓጓዣዎችን ለማምረት ብቃትን ይሰጠዋል። ፋብሪካው ለዚህ ተግባር የመዋል ብቃት ቢኖረውም፣ ይህን መሰል ግዙፍ አይሮፕላን እንዲያመርት ገደብ ስለተጣለበት፣ የሚያገለግለው ለጥገናና ለማሻሻያ ስራዎች ብቻ ነው። ይህ ወደቀጣዩ ያሸጋግረናል።» ፔንራም የምስሉን እንደ ጎን ብቻ አውጥቶ አሳላው ከህንፃው ውስጥ የእንድ ትልቅ አይሮፕላን የበስተኋላ ክንፍ አፈንግጦ ይታያል።

«ይህ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚገምት ሰው ይኖራል?» ጠየቀ።

«ግዙፉ የሰራዊት ማጓጓዣ ወይንም የጓዝ ማመላለሻ አይሮፕላን ይመስላል፣» ሲል እንድ ድምጽ ከጭለማው ውስጥ መለሰ።

«ከዚህ የተሻለ ሙከራ የሚያደርግ አለ? በላዩ ላይ ያልተለመደ ነገር አይታያችሁም?»

ሩል ተናገረች። «ከምንመለከተው ማስተዋል እንደሚቻለው ክንፎቹ በጣም አጭር በመሆናቸው ሊያንሳፍፉት ሀይል ያላቸው አይመስሉም» ደስ የማይል ስሜት እየተሰማት ነው።

http://ethzare.wordpress.com

«በጣም ጥሩ ሩል። አሁን ይህን ይመልከቱ።» ፔግራም ዳግመኛ ምስሉን ለወጠው። በዚህኛው ምስል ላይ፣ አይሮፕላኑ ሙሉ በሙሉ ውሀ ከመሰለ ነገር በላይ ዝቅ ብሎ ሲበር ይታያል።

«የክርስቶስ ያለህ፣ ፔግራም፣» አለች ሩል። «WIG አይደለም፣ ነው እንዴ?» « WIG ነው ሩል። ስለ WIG የምታውቂውን ንገሪን።»

«እሺ፣ ሊደረግ እይችልም ይላሉ፣ እንደውም እኛና ብሪታኒያ ነን ይህን ያልነው። ሶቪየቶች በዚህ ሀሳብ ዙሪያ ስራ የጀመሩት በሀምሳዎቹ ዓመታት ነው። እልፎ እልፎ የሞምሞምታ ወሬዎች ይደርሱን ነበር። ግን ስራ ላይ የዋለ እንዳላቸው ግን በፍፁም አላውቅም።»

«በሉ እንጂ ሰዎች፣» ሲል ሌላ የአቤቱታ ድምፅ ከሞለማው ውስጥ ተሰማ። « WIG ዎች ምንድን ናቸው?»

«የWinG-in-ground ተጽዕኖ /የከንፍ በምድር ተጽዕኖ/ የሚል ፍቺ ያለው ምህፃረ ቃል ነው።» አለ ፔግራም።

«አህ፣» አለ ሌላ ድምፅ። «እሱ ነው። እም።»

ፔግራም ቀጠለ። «የሚሰራው፣ አንድ የተወሰነ መጠን ያለው አይሮፕላን ዝቅ ብሎ በሚበርበት ወቅት፣ እንበልና በመቶ ጫማ ከፍታ፣ ከተለመደው በአምስት መቶ እጥፍ የሚበልጥ ክብደትን ለመሸከም የሚያስችለው የአየር ግፊትን ይፈጥራል በሚለው ሕግ መሰረት ነው። በእኛ በኩል ይህ ተግባር ላይ ይውላል ብሎ የሚያምን ሰው የለም- ለዚህ ነው የWIG ፕሮጀክት በጽሁፍ ደረጃ እንኳን የሌለን።»

«ታዲያ እዚህ ስክሪኑ ላይ ስለምንመለከተው የምናውቀው ምንድን ነው?» ጠየቀች ሩል። «ምን ሊሰራ ይችላል?»

«መልካም፣» አለ ፔግራም። «በላይንሳዊና በጦር መሳሪያዎች ጥናትና ምርምር ቢሮ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ስለዚህ የተናገሩት አለ፣» ብሎ ብርሀን ካረፈበት ወረቀት ላይ አንድ ነገር አነበበ።» የWIG አይሮፕላን፣ እዚህ ላይ እንደሰፈረው በግምት የሁለት መቶ ጫማ ርዝመት እና፣ የመቶ ጫማ የክንፍ ርዝመት ብቻ ያለው ነው። ከሁለት የጋዝ ተርባይን ሞተሮች ሀይል የሚቀበል ሲሆን የሁለቱ ሞተሮች ጢስ ማውጫዎች ከክንፎቹ ስር በማነጣጠር ተጨማሪ የመንሳፈፊያ ሀይልን ይሰጡታል። ከእነሱ ሌላ በጭራው ላይ የተገጠመው በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሽከረከር የአየር መምጠጫ ይህንኑ ሀይል ያግዛል። የአይሮፕላኑ አፍንጫ ከአብራሪዎቹ ከፍል በስተኋላ አስራአምስት ጫማ ያህል ርቆ መገኘቱ፣ በፍጥነት ለመጫንና ለማውረድ የአውሮፕላኑን የፊት ለፊት አካል በፍጥነት ከፍና ዝቅ ለማድረግ ያስችለዋል የሚል እምነትን ፈጥሮብናል። አይሮፕላኑ እራት መቶ ያህል ሰራዊትን ወይንም የተወሰኑ ቁጥር ያላቸውን የውጊያ ተሽከርካሪዎችን ጭኖ በዝቅተኛ ከፍታ በሶስት መቶ ኖት ባለፈ ፍጥነት መብረር እንደሚችል ገምተናል። ከአጭር መንደርደሪያዎችና ከውሀ ላይም መነሳት እንዲችል ተደርጎ የተሰራ ነው። በምስሉ ላይ የሚታየው በራሪ ኤስ ኤስ ኤን 22 ሚሳኤሉችን፣ ማለትም ከፈረንሳዩ ኤክሰሴት ጋር የሚመሳሰሉትን ከሁለቱ ክንፎች ስር የተጠመደ ይመስላል።» ከናሱ በሙሉ ፀጥታ ተዋጠ።

«ክቡራን፣» ፔግራም ፀጥታውን ሰበረው። «እየተመለከታችሁት ያላችሁት፣ እውነት ሥራ ላይ ውሎ ከሆነ- የዋለም ይመስላል? የምድርና የባህር የውጊያ መሳሪያዎችን ከፍተኛ እመርታ ነው። ሶቪየቶች ሁለቱ በእጃቸው

ይገኛሉ- የሳተላይት ምስሎቻቸው በእጃችን ነው። በፐስኮቭ ሰሜን ምዕራብ በሚገኝ ሀይቅ ላይ ሙከራ እያደረጉበት ነው። ከዚህም በላይ፣ ተሰርተው ሥራ ከጀመሩ ቢያንስ ሁለት ዓመት የሆናቸው ይመስላሉ። እኛ ግን አንድም የለንም።»

ክፍሉ ፀጥ እረጭ አለ። በመጨረሻም አንድ ድምፅ ተናገረ። ይህንን ጉምጉምታውን ጥሳ ተናገረች። «ፔግራም፣ እነዚህ ነገሮች ሁለት መሆናቸውን እንዴት አወቅን?»

«እንደተናገርኩት ሩል፣ የሳተላይት ምስላቸው አለን። የተለያዩ ቁጥሮች አሏቸው።»

«እም፣ እሱን ተናግረሀል፣ ያሳየሽን ግን የአንድ ግይል ርዝመት ያለው የአይሮፕላን ማምረቻ ፋብሪካን ነው፣ ሁለት ዊጎችን ለመስራት የሚጠቀሙት የህንፃውን ሁለት ዊጎችን (WIGS) መቶ ርምጃ ያህል አካሉን መሆኑንም ተናግረሀል? ወደፐላስኮቭ የሚገቡት ጥሬ እቃዎች ላይ ምርምርና ክትትል ተደርጓል?»

«ሀሳብሽ ምንድን ነው ሩል?»

«ሀሳቤማ፣ ዊጎቹን ለመስራት የህንፃውን የአንድ ግይል ርዝመት ተጠቅመው ግን ሙከራ ላይ ሲያውሏቸው ሁለት የተለያዩ ቁጥሮችን እየተጠቀሙ ቢሆኑስ?»

አሁንም ክፍሉን ፀጥታ ዋጠው። ፔግራም በደብዛዛው ብርሀን ፊቱ ሲቀላ ይታያል። ከፊት ለፊቱ ያሉትን ወረቀቶች ገላለጠ። «ይህንን በሰዎች በሚመራ የስለላ ቡድን መረጃ ማስደገፍ የምንችል ይመስልሻል?» ሲል መልሱ ግልፅ የሆነ ጥያቄ ሰነዘረላት።

የክርስቶስ ያለህ እንደምንችል ተስፋ አለኝ፣ አሰበች። ከሚታዩት ሁኔታዎች አንፃር በምድር ላይ የተወሰነ የስለላ ሀይል ቢላክ ጥሩ ነው።

ስብሰባው ተጠናቅቆ ሩል ከክፍሉ እየወጣች ሳለች፣ እንድ ድምጽ ከበስተኋላዋ በቅርብ እናገራት፣ «ኬት ይህን መረጃ የሚያጠናክር የስለላ ሀይል አለው ብለሽ ታስቢያለሽ?»

ሩል ፊቷን ስታዞር፣ ኤድ ሪውልስ በዚህ ፍጥነት ወደድርጅቱ ተመልሶ ስለተመለከተችው ተደነቀች። ማላከሆቭን ለሌላ ቡድን አስረክቦት መሆን አለበት ብላ ገመተች።

«አላስብም፣» አለች።

«እኔም እንደዚያው፣» መለሰ ራውልስ።

«ኤድ፣ ያ በራሪ መሳሪያ ማድረግ ከሚችለው ነገር አንፃር፣ ባልቲክ ጥሩ የመንቀሳቀሻ ቦታ ይሆንዋል ብለሽ አታስቢም?»

«ከዚያ የተሻለ ቦታ አያገኝም። እንገናኛለን ኬት።» ብሎ ፊቱን አዞረና በደረጃው ወረደ። ሩል በሀሳብ ተውጣ ቢሮዋ ልትደርስ ትንሽ ሲቀራት ሳታውቀው ከአንድ ሰው ጋር ተላተመች።

«ኬት፣ እንዴት ነሽ?»

ሩል ሀሳቦቿን ለመረዳት ሞከረች። «ጂም ጊል፣ ሮም ውስጥ ያለህ መስሎኝ ነበር። እዚህ ምን ታደርጋለህ?»

ሬል፣ ረጅም ቀጭን ሰው ሲሆን የአነጋገሩ ቃና ወደደቡብ ወሰድ ያደርገዋል። በጥያቄ ስሜት ተመለከታት። «እንዴታ አሁንም ሮም ውስጥ ነኝ፣

http://ethzare.wordpress.com

ስብሰባ ላይ ለመገኘት ለሁለት ቀናት መጥቼ ነው። ቢሮሽ ፈልጌሽ ስመለስ ነው ያገኘሽኝ። ባለፈው ሳምንት ለላኩበት ቴሌግራም መልስ አላገኘሁም። አፒቼላን መከታተሉን ተውሽው እንዴ?»

ስሙን ለማስታወስ ጥቂት ጊዜ ፈጀባት። «አፕቼላ? እንዴታ አልተውኩትም። ከእንተ የተላከ ነገር አልደረሰኝም፣ ከመጀመሪያ ሪፖርትህ በኋላ ስለ አፒቼላ ምንም አልሰማሁም።» ኤሚሊዬ አፒቼላ ጣሊያናዊ የኮምፒውተር ወንበዴ ሲሆን፣ ከማጆሮቭ ጋር ስላደረጋቸው ግንኙነቶች እያወራ ይሀን ሁሉ ጣጣ የቀሰቀሰ ሰው ነው። ጊል ትከሻውን ሰበቀ። «በቃ፣ መስመሩ ተበላሽቶ ይሆናል። ለምን እንዳልፈለግሽኝ ገርሞኝ ነው።»

ሩል ልታፋጥጠው የሚተናነቃትን ስሜት ተቆጣጠረች። «አፒቼላ ምን ሁኔታ ላይ ነው?»

«ለል ኤሚሊዮ ወደ ምስራቅ እንደሚመጣ ሌላ ግብግ ደርሶታል።»

«ግብግ? ከማጆሮቭ ማለትህ ነው?»

«እሱ የሚለው እንደዚያ ነው። ይህን ሁሉ ነገር ባለፈው ሳምንት በቴሌግራም ልኪልሻለሁ። ገና ስላላገኙት ሊሆን ይችላል።»

ሩል እንደማያገኙት አሰበች። አንድ መልእክቶቿን እየፈተሸ የሚለቅላት ሰው አለ ማለት ነው። ያንን የቴሌግራም መልዕክት የያዘባት ሰው አለ። «አሁን ንገረኝ ጂም።»

«ኤሚሊዮ ወደቪየና መብረሩ ነው- መቼ ነበር፣ ሰኞ አለት?- አይደለም ረቡዕ፣ ቪየና ላይ ወደሌኒንግራድ የሚበርበትን አይሮፕላን ይቀይራል። መመሪያ እንዲሰጠኝ ጠይቄ ነበር ኬት። ከአንቺም ሆነ ከተልዕኮዎች ክፍል መልዕክት አልደረሰኝም። ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ጣቢያው በውሸንብር ታምሶ ነበር፣ ያንቺ መልዕክት ሳይደርሰኝ ሲቀር፣ ስመጣ ሁኔታውን እያለሁ ብዬ ተውኩት።»

«ሮም ባለው ጣቢያችን ውስጥ ከአንተ በቀር አፒቼላን የሚከታተል አለ?»

«የለም፣ እሱ የኔ ብቻ ነው?»

«ወደ ሮም የምትመለሰው መቼ ነው?»

«ከሳምንት ገደማ በኋላ።»

ለደቂቃ ያህል ቢሮዬ እንግባ፣ እሺ ጂም?» ይዛው በኮሪደሩ ወደ ቢሮዋ መልሳው በሩን ከኋላዋ ዘጋችው።

«ስማ ጂም፣ ስለጉዳዩ ከተልዕኮዎች ክፍል ያናገርከው ሰው አለ?»

«የለም፣ ገና ዛሬ ጠዋት መድረሴ ነው። ገና ወደዚያ አልሄድኩም።»

«ጂም፣ አፒቼላ ወደቪየና ከመሄዱ በፊት ላነጋግረው አፈልጋለሁ። በሮሙ ጣቢያ በኩል ሳይሆን በአንተ በኩል በቀጥታ ልታገኘው ትችላለህ?»

ጊል አንድ ማስታወሻ ደብተር አወጣ። «ስልኩን እዚህ ላይ ይገዋለሁ። ሰራውን የሚሰራው ቤቱ ውስጥ ነው።»

«እሱን የግድ ማናገር ይኖርብኛል፣ ይህን ለማድረግም መዋቅሩን በትንሹ መተላለፍ ይኖርብኛል። ሆቴልህ ከተመለስክ በኋላ ደውለህለት እንዲያገኘኝ ትጠይቀዋለህ»

ጊል በሀሳብ ተዋጠ። «ይህንን ለተልዕኮዎች ክፍል እንድገልጽ አትፈልጊም?»

«ባያውቁ ይሻለኛል። ከማበሳሽት ሌላ ምንም አያደርጉም። ፀባያቸውን ታውቃለህ።»

«ታዲያ ልታናግሪው ብቻ ነው የምትፈልጊው?»

«እም። ብቻ ደውልለትና ይህን ቁጥር ስጠው።»

«እሺ እንግዲህ መልካም። ለመደወል እስክማታ ከጠበቅኩ ለሊት ስለሚሆን ከእንቅልፉ እቀሰቅሰዋለሁ። ከዚህ እንድደውል እትፈልጊም አይደለም?» ፈገግ አለ።

«ባታደርገው ይሻለኛል። እንደምደውልለትና ለክብድ ጉዳይ እንደምፈልገው ንገረው።»

«እሺ ኬት። ይገፍው እመጣልሻለሁ። ስለውበትሽ ከነገርኩት ሊያገኝሽ ይጓጓል፣ ለሴቶች የማይሆነው የለም።»

«የፈለግከውን በለው - በቃ የፈለግከውን። ብቻ ሊያናግረኝ ፈቃደኛ እንዲሆን አድርገው።»

«መልካም፣ እደውልለታለሁ።»

«ውለታህ ይኖርብኛል፣ ጂም።»

«አንድ ቀን ውለታዬን አስከፍልሻለሁ፣ በዚህ ተማመኚ።» የስልክ ቁጥሩን ፅፎ በሩን ከፈተው። «የተልእኮዎች ክፍል መሔድ አለገኝ። እንገናኛለን።»

ሩል ሻንጣዋን አነሳችና ፀሐፊዋ ወደተቀመጠችበት አመራች። «ጂፍ፣ መጥፎ ስሜት እየተሰማኝ ነው። ቤቴ ሄጀ መተኛቴ ነው። እንደሚሰማኝ ከሆነ ነገም የምመጣ አይመስለኝም። ማንም ሰው ከደወለ፣ ስልኩን እንደማላነሳው ንገራቸው። በጣም ከፈለጉኝ መልዕክተኛ ይልካሉ።»

«መልካም፣» አለና ጂፍ ወደመጽሔቱ ተመለሰ።

ሩል ህንፃውን ለቅቃ መኪናዋ ውስጥ ገባችና መጀመሪያ ባገኘችው የቤንዚን ማደያ ላይ ቆመች። ወደፓን አሜሪካ አየር መንገድ ደወለች። «የምሽት የሮም በረራ አላችሁ አይደለም? ጥሩ። አንድ መቀመጫ እፈልጋለሁ፣ የዱቤ ካርድ ቁጥሬን ልስጣችሁ።»

26

ሔልደር በድካም ዝሎና ትንሽ ሞቅ ብሎት እስከ ማለዳው አኩሌታ ድረስ ለጥ ብሎ ተኝቶ ቆየ። ሶኮሎፍ አይን ላይ የተሰካው መፍቻና አልከፈት ያለው የትንሿ ሰርጓጅ መርከብ በር በሀልሙ መጥተውበት በላብ ተዘፍቆ ተነሳ። ፊቱ ላይ የፈነጠቀው የፀሐይ በርሀን የገነት ብርሀን መስሎ ታየው። ተነስቶ ቆመና በትንሿ መስኮት በኩል የስቶክሆልምን ሰማይ ጠቀስ የሾሉ ህንፃዎች ተመለከተ። ሕይወቱ አለች፣ ደህንነቱም ተረጋግጧል።

በቀዝቃዛ ውሃ ገላውን ሲታጠብ የሀልሙና የትውስታው እስደንጋጭ ትዕይንቶች ከሀሊናው ተወገዱ። ቀለል ያለ ጃኬትና የላይኑን ሱሪ ለበሰ ሻንጣውን ሸከፈና፣ ሽጉጡን ከፍሪጁ እውጥቶ ቁርስ ለመብላት ወደታች ወረደ። እንቁላሎችንና ቋሊማዎችን እየተስገበገበ ከበላ በኋላ ሒሳቡን በክሬነር ከፍሎ ሄደ።

http://ethzare.wordpress.com

እንግዳ መቀበያው ጠረጴዛ ላይ የምትሰራውን ሴት፣ «ወደሔልሲንኪ የምትሄደው ጀልባ ላይ ቀድሜ ቦታ ለመያዝ የት መሄድ አለብኝ?» ሲል ጠየቃት።

«በስልክ ልይዝልህ እችላለሁ፣» አለችና አንድ ቁጥር ደወለች። ወዲያውኑም በምሽት የመርከብ ጉዞ ላይ አንድ ክፍል ያዘችለት። «መርከቧ የምትነሳው አሰራ ሁለት ሰዓት ላይ ሲሆን ነገ ጠዋት ሶስት ሰዓት ላይ ሔልሲንኪ ትደርሳለች። አለችው። «ትኬትህን ከጉዞው አንድ ሰዓት በፊት መርከብ ጣቢያው ላይ ማግኘት ትችላለህ።»

አመስግኗት ወጣ። በስቶክሆልም ጥንታዊ ከተማ መንገዶች ላይ እየተንሸራሸረ ነጭ ቀለም ያላቸውን ስዊድናውያንና ከተማቸውን በመመልከት ላይ ሳለ፣ ከዚህ በፊት ጊዜ ሰጥቶ ሊያስብበት ያልቻለው አንድ ነገር ተከሰተለት። የአሜሪካዊ ፓስፖረት፣ የጹሬ ካርዶችና ብዙ ገንዘብን ይዞ በአንድ የምዕራባዊያን ከተማ ውስጥ ብቻውን ነው። ታክሲ ይዞ ወደስቶክሆልም አየር ማረፊያ በመሄድ በአለም ላይ ወደፈለገበት ሰፍራ የሚወስደውን የአየር ትኬት ለመግዛት የሚከለክለው ማንም የለም። ማጆሮቭ በፍፁም አያገኘውም። ያገኘው ይሆን? የጹሬ ቁጥሮቹን ተከታትሎ ይደርስበት ይሆን? ገንዘቡ ቢያልቅስ እንዴት መኖር ይችላል? በማያውቀውም ከተማ ለጥቂት ቀናት መቆየት እንዲችል ተደርጎ ተለማምጿል፣ ግን የምዕራባዊውን ሕይወት በደንብ ስለማያውቀው ያለችግር ለረጅም ጊዜ መቆየት ይችል ይሆን? ምናልባት እድለኛ ከሆነ። ሌላ አማራጭም አለው፣ ታክሲ ይዞ ወደአሜሪካ ኤምባሲ በመሄድ ራሱን እዚያ ላሉት ባለስልጣናት አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል። ከዚህም በተሻለ ደግሞ ወደኒውዮርክ ወደዋሽንግተን መብረር ይችላል። ስለማሊቡና ስለማጆሮቭ እቅድ ከሚያውቀው በመነሳት የሞቀ አቀባበል ሊጠብቀው እንደሚችል ገምቷል። ቢሆንም ግን ስለ KGB አሰራር ስለሚያውቅ CIA ቢሆን የተለየ ሊሆን እንደማይችል ያውቃል። ያምኑት ይሆን? የሌለውን መረጃ አምጣ እያሉ ያሰቃዩት ይሆን? ድንገት ብቸኝነትና ባዶነት ወረረው።

ከዚያ ግን ስለትሪና ራጉሊን አሰበና የባዶነት ስሜቱ ለቀቀው። ማሊቡ ላይ እየጠበቀችው ስለሆነ አብሯት መሆን ይፈልጋል። ተመልሶ ከሄደ ወደፊት አብረው መኖር ይችላሉ። ጥሩ ስራ ከሰራ እድገትና ስልጣን እንደሚያገኝ ማጆሮቭ ቃል ገብቶለታል። ይህንን ደሞ አድርጓል። ጓዙን ልክ ማጆሮቭ በሚፈልገው ቦታ ላይ አኑሮታል። ሶኩሩፍ መሞቷ ለኮሎኔሉ የሚጠላው ነገር አይሆንም። የተሰጠው መመሪያ ሰርጓጁን ለቅቀው ለመሄድ ከተገደዱ እሷን እንዲገድሳት ነው፣ ሔልደርም ይህንኑ አድርጓል። የማጆሮቭን ክብር አግኝቶ በጀግንነት የመመለስ ሙሉ መብት አለው። በሶቪየት ባህር ሀይል ውስጥ ዝናና ክብር ምን እንደሚያመጣ ተመልክቷል። ተመልሶ ራጉሊንነቷ አገብቶ፣ ማዕረግ ተጨምሮለት ልጆቻቸውን በምርጥ ትምህርት ቤቶች እያስተማሩ ጥቂት የሶቪየት ዜጎች ብቻ የደረሱበትን ዓይነት ሕይወት መምራት ይችላሉ። በምዕራቡ ዓለም ይህንን ሊለጠው የሚችል ማን አለ?

ከጠባቦቹ መንገዶች ወጥቶ ገላጣ ስፍራ ላይ ሲገባ ወታደራዊ•ማርሽ አደመጠ። ካርታው ዋናው ቤተመንግስት መድረሱን ነገረው። ድንጋይ የተነጠፈበት ሜዳ ላይ ቆመው የቤተመንግሥቱን ዘበኞች የልውውጥ ሂደት ከሚመለከቱት አገር ጎብኚዎች ጋር ተቀላቀለ። የተተኩት የደንብ ልብሶቻቸውን

ለብሰው መሳሪያዎቻቸውን በየጎናቸው ያንገቡትን ወጣቶች ተከትሉ ሄደ። አውቶማቲክ ሽጉጥ ቀበቶው ስር የሻጠ የሶቪየት ሰላይ መሆኑን ቢያውቁ ምን እንደሚያደርጉ አሰበ። ምናልባት ባንድ ጉልበታቸው ሸብረክ ብለው ይተኩሱብታል። ጎብኚዎቹ በጥይቱ ድምፅ ተደናግጠው በአደባባዩ ሲራወጡ አሰቦ ከት ብሎ ሳቀ።

ትርዒቱ ሲያበቃ በረጅሙ የደረጃዎች ድርድር ቁልቁል ወደውሀው አመራና ዙሪያውን ተመለከተ። ስቶክሆልም ከሌኒንግራድ ጋር ትመሳሰልበታለች። በተለይ በከተማዋ መሀል ያለው የውሀ አካል ይሆን መመሳሰል ያጎላዋል። የድንጊያ መከለያ ግንቡን ተደግፎ ከሻንጣው የንድፍ ደብተሩን አወጣ። ቢተመንግሥቱን፣ ከፊትለፊቱ ያለውን ውሀ፣ ፈጣ የሚያሰኝ የደንብ ልብሳቸውን የለበሱ የቤተመንግሥቱ ጠባቂዎች፣ ጎዳናው ላይ የቆሙ ሽማግሌዎችንና አይኑ ሊመለከተው የቻለውን ሁሉ ሲስል ቆየ። ረሀብ ሆዱን ሲያንኳኳ ሰዓቱን ተመለከተና ከሁለት ሰዓታት በላይ ማለፉን አይቶ ተገረመ።

በደረጃው ወደላይ ተመልሶ ጥንታዊቷ ከተማ ገባ። ከዚህ በፊት አነስተኛ አደባባይ ላይ የተመለከተው የምግብ ቤት ለመሄድ አሰበ። አስተናጋጇ በመስታወት በተከበበ በረንዳ ላይ በሚገኝ ባለአራት መቀመጫ ጠረጴዛ ላይ ቦታ ሰጠችው። አደባባዩን አቋርጦ ባለው መንገድ የስዊድን አካዳሚ ይታያል። ቦታው ዝነኛ መሆኑ በግልፅ ይታያል፣ ምክንያቱም በፍጥነት እየሞላ ሄደ። ሼልደር ቢራ አዘዘና የምግብ ዝርዝሩን ተመለከተ።

«ይቅርታ አድርግልኝ፣» አለ አንድ ድምፅ።

ሔልደር ቀና ብሎ ሲመለከት መቀመጫ ያስያዘችው አስተናጋጅ ከአንድ ወንድ ጋር ቆማ አስተዋለ።

ሔልደር ፈጠን ብሎ ሰውየውን ተመለከተ። ረጅም፣ ባለጥቁር ፀጉር በሰላሳዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኝ፣ ቀለል ያለ ግን ሽክ ብሎ የተሰፋ ልብስ የለበሰ፣ ሔልደር እንግሊዛዊ ነው ብሎ ገመተው። ስዊድናዊ ፖሊስ አይመስልም።

«ችግር ከሌለ፣ ብጠብቅ ቅር አይለኝም፣» አለ ሰውየው የሔልደርን ማመንታት በሌላ መልኩ እየተመለከተ።

«አይሆንም እባክህን ተቀመጥ። በሐሳብ ሰምጬ ነው፣ ለዚያ ነው ቶሎ መልስ ያልሰጠሁት።»

«አመሰግናለሁ፣» ብሎ ሰውየው ተቀመጠ። መጠጥ አዘዘና የምግብ ዝርዝሩን አነሳ። «ይህን ቦታ ታውቀዋለህ? የትኛው ምግብ ይሻላል ትላለህ?»

ሰውየው አሜሪካዊ እንጂ እንግሊዛዊ ያለመሆኑ ከአነጋገሩ ታወቀው። ከገጠሩ የመጣ ዓይነት መሆን አለበት ብሎ አሰበ። ምናልባት የደቡብ ሰው ይሆናል፣ «አይደለም አላውቀውም፣ ጎብኚ ነኝ፣ እዚህ ስመጣ የመጀመሪያዬ ነው።»

«ብሪታኒያዊ ነህ?» ጠየቀ ሰውየው።

«አይደለሁም አሜሪካዊ ነኝ።»

«እውነት? እኔም እንደዚያው። ውልድህ የት ነው?»

«ሚኒሶታ ነው የተወለድኩት። አሁን የምኖረው ኒውዮርክ ነው።»

«ከአነጋገርህ አንድ ልለየው ያልቻልኩት ነገር አለ። የብሪታኒያ ዜጋ ነህ ብዬ አሰቤ ነበር።»

http://ethzare.wordpress.com

«ልክ ነህ ይህን እንጋገር የያዝኩት ከማውቃት የእንግሊዝ ሴት ነው። ቤተሰቦቼ ስዊድናዊ ስለነበሩ ምናልባት እሱ ትንሽ ለየት ሳያደርገው አይቀርም።»

«ስዊድንኛ ትናገራለህ?»

«ያን ያህል አይደለሁም። ቤተሰቦቼ አንዴ አሜሪካን ከረገጡ በኋላ አሜሪካዊ መሆን ፈልገው ቋንቋቸውን ተውት። እያደግኩ ስመጣ እንግሊዝኛ ብቻ እንድናገር ይወተውቱኝ ጀመር ሰምገቡ ከሆነ ግራቭላክስ የተባውን ልትሞክረው ትችላለህ፣ ይህ ማለት የተጠበሰ ዓሳ ከስናፍጭ ስጎ ጋር ማለት ነው። እናቴ ታዘጋጀው የነበረ ምግብ ነው።»

«ጥሩ ይመስለኛል።»

አስተናጋጇ ተመልሳ ስትመጣ አዘዙ።

«ታዲያ የኒውዮርክ ነዋሪ ነሃኤ አለ ሰውየው። «ከተማዋን እወዳታለሁ፣ በተለይም የምግብ ቤቶቹን። በላይኛው የምዕራቡ ጥግ ያለውን ካፌ ደ አርታስቴስ ታውቀዋለህ?»

«አላውቀውም፣ እኔ የምኖረው ግሪንዊች መንደር ውስጥ ነው፣ አብዛኛውን ጊዜዬን የማሳልፈውም እዚያ ነው።»

«በዚያ መንደርም ቢሆን ጥሩ መመገቢያ አለ። በምዕራቡ አስራሰስተኛው ጎዳና ላይ ያለውን ላ ቱሊፕን ታውቀዋለህ?»

«እሱንም አላውቀውም። የሴት ጓደኛዬ ባለሞያ ናት። ብዙውን ጊዜ እቤታችን ነው የምንበላው። የምሰራውም እቤቴ ስለሆነ እንደአንዳንድ ሰዎች ብዙ ቦታዎችን አላውቅም።» ይሄ ሰውዬ ችኮ ነው፣ አለ በልቡ።

«አልፈርድብህም፣» አለ እየሳቀ። «ለሴት ጓደኛዬ ምግብ የማበስልላት እኔ ነኝ። ስራህ ምንድን ነው?»

«አርቲስት ነኝ ሰዓሊ።»

ሰውየው የሔልደርን የንድፍ ደብተር ለማየት ተንጠራራ። «ደሞ ጎበዝም ነህ፣ ብዬ እጠብቃለሁ። ይህ በጣም ጥሩም ነው። ምን ስትሰራ እንደቆየህ መመልከት እችላለሁ?»

ሔልደር ማስታወሻውን ሰጠው።

«በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ። ስራህን ለህዝብ አሳይተህ ታውቃለህ?»

«አላውቅም። የማስታወቂያ፣ የመጽሐፍ ሽፋን ስዕሎችን ሰርቼ ባጠናቀቅኩኝ ጊዜ ለራሴ የሚሆን ብዙ ጎይል አልቀረኝም። ለራሴ የምስለው እረፍት በማገኝ ጊዜ ብቻ ነው።»

«ያሳዝናል። ስቶክሆልም ከመጣህ ቆየህ?»

«ትናንት ነው የደረስኩት፣ ዛሬ ማታ ወደሔልሲንኪ እሔዳለሁ። እዚያ ከልጅነቴ ጀምሮ የሳየኋት አንድ አክስት አለችኝ።»

«በማታውቀው ከተማ ውስጥ እያሂዚረ የሚያስጎበኝህ ሰው ማግኘት ጥሩ ነው፣» አለ ሰውየው።

«አንተ የተወለድከው የት ነው?» አለ ሔልደር፣ የቃለ መጠየቁን አቅጣጫ ከሱ ለማዞር እየጣረ።

«ጆርጅያ ውስጥ ደሴይኖ በተባለች ትንሽ ከተማ። እዚያ ከአባቴ ጋር የሀግ ሽርክና አሰኝ።»

«አንተም እረፍት ላይ ነህ?»

«ወዴት ለመሂድ?»

«ምዕራቡ ባህር ዳርቻ ላይ ፒየታርሳሪ የተባለ ስፍራ፣ ወይንም በስዊድንኛ ስሙ ጃኮብስታድ። ከዚያ የጓደኛዬን አዲስ ጀልባ ይገዙ እመለሳለሁ፣ ወደ ኮፐንህገን እወስዳታለሁ። የሔልደር የማወቅ ጉጉት ድንገት አየለ። «ምን ዓይነት ጀልባ?»

«አርባ ሁለት ጫማ ርዝማኔ ያላት፣ ስዋን የተባለች ባለአንድ የነፋስ ሸራ፣ አንተ መርከብ ትነዳለህ?»

«ውይ፣ በሚኒሶታ ሐይቆች ላይ በአነስተኛ ክፍት ጀልባዎች ቀዝፌያለሁ። በአብዛኛው በፊን ጀልባዎች።»

«ብቻህን ነው? ይህን እኔም አድርጌዋሁ፣ ግን ከፊን በመጠን የሚበልጡ ጀልባዎች ላይ ነው።»

«ስዋንን የማውቃት አይመስለኝም፣» አለ ሔልደር።

ሰውየው ተገረመ። «አታውቃትም? በአለም ተወዳዳሪ የሌላቸው የነፋስ ጀልባዎች የሚል ዝና አላቸው።»

«በሚኒሶታ ሐይቆች ላይ ብዙ ስዋኖች የሉም ይመስለኛል፣» ብሎ ሳቀ ሔልደር። ምግባቸው መጣ። እየበሉ በደስታ ሲጫዋወቱ ቆዩ። ሔልደር ሰውየውን ወዶታል። ጆንስ በሰጠው ስልጠናና በራሱ ችሎታ በመታገዝ ከሱ የሚጠበቀውን ሁሉ በመናገር የሀሊና ብቃት ደረጃውን መፈተን መቻሉ አስደስቶታል።

ቡናቸውን ጨርሰው ሒሳብ ለሁለት ከፍለው ለመሔድ ተነሱ።

«በስቶክሆልምም ሆነ በሔልሲንኪ ጥሩ ቆይታን እመኝልህሰሁ፣» አለ ሰውየው። «ደሞ መሳልህን ቀጥልበት። ጎበዝ ነህ።»

ሔልደር የሚያናግረው ሰው በማግኘቱ ደስ ብሎት ስለነበር የምሳ ቆይታቸው ሲያበቃ አልተደሰተም። «እንድ መውሰድ ትፈልጋለህ?» አለው የስዕል ደብተሩን እየሰጠው።

«ውይ አመሰግናለሁ፣ ግን ለትዝታቸው ስትል እንደምትፈልጋቸው ርግጠኛ ነኝ።»

«ከሥራዎቼ አንዱ ጆርጂያ ውስጥ በአንድ ጠበቃ ቤት መሰቀሉን ማወቁ ያስደስተኛል፣» አለ ሔልደር። ከልቡ ነበር። ሰውየው ስዕሉን የሳለውን ሰው ማወቅ እንደማይችል ሲያስበው አስደስቶታል። CIA ባያገኘው እንኳ የማንነቱ አንድ አካል አሜሪካ ይደርሳል ማለት ነው።

«መልካም፣ በጣም አመሰግናለሁ። የቤተመንግስቱ ዘቦች ያሉበትን ባገኝ ደስ ይለኛል። እሱን ልውሰድ?»

«እንዲታ፣» አለ፣ ሔልደር፣ ስዕሉን ከማስታወሻው እየቀደደ። ቶሱ ብሎ ፈርሞበት ሰጠው።

«እርስ በርስ በወጉ አልተዋወቅንም፣» አለ ሰውየው፣ «ደግሞም ቢሮዬ የማንጠለጥለው የማንን ስዕል እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ።» እጁን ዘረጋለት።

«ካርል ስዌንሰን እባላለሁ፣» አለ ሔልደር፣ እየጨበጠው።

«ስላገኘሁህ ደስ ብሎኛል፣ ካርል። ባጋጣሚ ዲሌይኖ፣ ጆርጂያ ከመጣህ ፈልገኝ። ዊል ሲ እባላለሁ።»

ጓደኝነታቸው ፀንቶ ተለያዩ።

http://ethzare.wordpress.com

ሩል የሮም ብሩህ የፀሀይ ጨረር አይኖቿን እያጭበረበራት አይናቿን በእጇ ከልላ ኤሚሊዮ እፒቼላን ፍለጋ ህዝቡን ትቃኛለች። አልተሳካላትም። ቢፒዛ ናቮና ቡና ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጣ፣ አሀጉር መቀየሯ እሚቀፍ ስሜት ተፈጥሮባል። ከዋሽንግተን የምሽት በረራውን ተሳፍራ፣ ጎህ ሲቀድ ነበር የደረሰችው። ከዚያም በቀጥታ ወደ ሀስለር ቪላ ሜደቺ ሆቴል በመሄድ እንድ ክፍል ያዘች።፣ የሆቴሉ ሰራተኞች እሷን እንኳን ባይሆን ሳይመጉን አስታውሰውታል። ለሁለት ለዓታት እየተገላበጠች እንቅልፍ አይሉት መኝታ አልጋዋ ላይ አሳለፈች። ከሀስለር ሆቴል መመገቢያ ቤቱ ድረስ ያደረገችው የእግር ጉዞ የሌላ አለም ትዕይንትን አሳይቷታል። ግን እንግዳ አልሆነባትም።

ዲሲን ከመልቀቋ በፊት ከእፒቼላ ጋር የምሳ ቀጠሮ ይዛለች። ሊያገኛት የተስማማው በጉጉት ነበር። ታዲያ ጂም ጊል ስለእሷ ለሰውየው ምን ነግሮት ይሆን? የምሳ ግብግዞውንና የምግብ ቤቱን ሀሳብ ያመጣው እሱው ነው። ምግብ ቤቱ ድሮ ሮም ጣቢያ ላይ በምትሰራበት ወቅት ትወደው የነበረ ቤት ነው። ግን ሀያ ደቂቃ አርፍጿል፣ መጠጧ ውስጥ የነበረው በረዶ ቀልጦ አልቋል። አስተናጋጁ ብርጭቆዋን እንዲሞሰላት በእጇ ምልክት ሰጠችውና፣ አደባባዩ ላይ የተሰበሰበውን የሰው አጀብ በአይኖጀ ማተረች። መልኩ ምን እንደሚመስል አሰበች። /ስትጠይቀው «እኔ እራሴ አገኘሻለሁ» ነበር ያላት።/ የተለመዱት ዓይነት ከኮምፒውተር ጋር የሚኖሩ ዓይነት ማሽን መሰል ፍጥረት አድርጋ ገምታዋለች።

የምግብ ቤቱን በዝግታ እያቋረጠ የሚራመድ ወንድ ተመልከታ ሰራሷ ፈገግ አለች። እሱ የምሳ እንግዳዋ አይደለም። ከአንድ የጣሊያን ፊልም ውስጥ የወጣ ይመስላል። ሲበዛ መልከ መልካም ሲሆን ነጭ ሙሉ ሱፍ ለብሷል ኮቱ ትከሻው ላይ ልክክ ብሏል። ክብ ጠርዝ ያለውን የፓናማ ባርኔጣ አድርጓል። ደብዛዛ ቢጫ ቀለም ያለው ማንቁርቱ ላይ ቀልፉ የተከፈተ ሽሚዝ ይታያል። ከዚህ ሌላ ዝንጉርጉር ቀለም ያለው የሀር መሀረብ ከኮቱ ደረት ኪስ ብቅ ብሎ አይን ይገባል። እንዴ እንዱን እየጨበጠ፣ ሌላ ጊዜ የእንጂን እጅ እየላመ፣ ከሩቅ ሳየው እጁን እያውለበለበ በኩራት ይራመዳል። ጥቅጥቅ ባለው ሪዙ ላይ ጣቱን የማንሸራሸር ልማድ አለው። ይህ አኳኋኑ ምግባረ ልቅ ሰው ያስመስለዋል። አስተናጋጆቹ ሊያናግሩት ተደረደሩ። ሆሊውድ ውስጥ የሚሰሩ የጣሊያን ፊልሞች ላይ የሚታዩት ወንዶች ሙሉ ግልባጭ ነው። ከአንድ ምንም ከማያውቅ የኮምፒውተር ወንበዴ ይልቅ ከእሱ ጋር ምሳ በበላሁ ስትል ተመኘች። እሱን የጠበቀችው የተጨማደደና ኮቱ ኪስ ውስጥ ብዙ ብዕሮች የተደረደሩበት የፖሊስተር ሙሉ ልብስ የለበሰ ሰው ይሆናል ብላ ነበር። ከዚህ ዓይነት ሰው ጋር በሮም የምታሳልፈውን አንድ ቀን ማባከን አሳዘናት።

ከእሷ አንድ ሁለት ጠረጴዛዎች ርቀት ላይ ሲደርስ ቆመና ተመለከታት፣ አይታውን በእስደሳች የዋህ እይታ መለሰችለት። የሷ ሰውዬ የማይመጣ ከሆነ የፈለገው ይሁን፣ አንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ከተቀመጡ ሴትና ወንድ ጋር ጥቂት ቃላት ከተለዋወጠ በኋላ ወደእሷ በመምጣት ቆመ። ባርኔጣውን ሲያወልቀው በጥንቃቄ አሳምሮ የተቆረጠው ግንባሩ ድረስ ድፍት ያለ ጥቁር

ሥማ ፀጉሩ በግልፅ ታየ። ቀና ብላ ጥቂቁር የአይን ብሌኖቹን እየተመለከተች ሳለመሸኮርመም ጣረች።

«ሲኞሪና ሩል፣ እንቺ ነሽ ብዬ እገምታለሁ፣» አለ፣ በተስተካከለ ቀልድ ቢጤ በሚቃጣው እንግሊዝኛ።

የምትናገረው ጠፋት።

«ኤሚሊዮ እፒቼላ እኔ ነኝ።» አለ። «ቀጠሮ ያለን መስለኝ። መቀመጥ እችላለሁ?»

«እንዴታ፣» አለች ድንጋጤዋ ትንሽ መለስ እያለላት።

ቅንድቡን ከፍ ባደረገ ቅፅበት አንድ አስተናጋጅ ከተፍ አለ። እፒቼላ ለግማሽ ደቂቃ ያህል ከፍተኑቱ የተነሳ ልትከተለው በሚከብዳት ጣሊያንኛ ሊያናግረው ቆየና፣ አስተናጋጁ ተለያቸው።

«የእንቺን ፈንታም የማዘዙን ነፃነት ወስጀያለሁ፣» አለ። «መቼም ቅር እንደማይልሽ ነው።»

«አይለኝም፣» አለች፣ ገና ከአሁኑ እጆቹ ላይ እየቀለጠች።

«መቼስ፣» አለና ተነፈሰ፣ ወንበሩ ላይ ወደኋላ ደገፍ ብሎ እየተመለከታት፣ «እንደእንቺ አይነት ውብ የCIA ሰላይ ተመልክቼ አላውቅም።»

«የክርስቶስ ያለህ!» ብላ እናፋችበት። «ድምፅህን ዝቅ ብታደርገውስ!»

ድምፁን ከፍ አድርጎ ሳቀ። «አህ፣ ሲኞሪታ ሩል፣ እዚህ እኛን የሚያጸምጥ ምንም የለም።» «ይህን በመሰለ አለት ግድ የሚሰጠውም የለም።» እጁን አውለበለበው። «ሁሉም ከምላ በኋላ ከመቅፅበት እንዳቸው ሌላቸውን ወደአልጋ ይዘው ለመሄድ እቅድ እያወጡ ነው።»

አስተናጋጁ የብርቱካን ጭማቂ ጀግ እና ጠርሙስ ሻምፓኝ ይዞ መጣ።

«እንግሊዝ ውስጥ ያገኘሁት ግሩም መጠጥ መሆኑን ስናገር እያፈርኩ ነው፣» አለ እፒቼላ፣ ሁለቱን መጠጦች እኩል በእኩል በየብርጭቋቸው እየቀዳ። «የባክ ፊዝ ይባላል፣ ለዚህ አሳዛኝ ስፍራ የሚበዛ አስደሳችና ግሩም የመጠጥ ድብልቅ ነው።» ከፊት ለፊቷ ብርጭቆውን አስቀምጠሳት የራሱን ብርጭቆ አነሳ። «ለስኬታማ ተልዕኮዎች፣» አለ በሚያሴር ቅላፄ።

«ሚስተር እፒቼላ፣» አለች ሩል ፈጠን ብላ፣ ስለማንነቴ የተሳሳተ ሀሳብ ሳይኖርህ አይቀርም። እኔ. . . »

አንድ እጁን ከፍ አደረገው። «እባክሽን። መጀመሪያ ጥሩ ምሳ እንበላለን ከዚያ ለስላሳና መሰል ነገሮች እናወራለን።»

ሩል ከሰዓቱ መጨረሻ ገደማ የምትሳፈረው አይሮፕላን እየጠበቃት ቢሆንም ሬጋ ብላ ራሷን ለማስደሰት ሞከረች። በሰፌ ሰሀን የተጠበሰ ጻቦ መጣ፣ ተከትሉ በክምጣጣ ከሬም የተዋህደ ፓስታ፣ አይብ በጢስ የተጠበሰ አሳ፣ ይህን ተከትሉ የተከተፈ የበግ ግልገል ጥብስና ሰላጣ ደረሰ። ልክ እንደአዲስ ጓደኞች ስለ ሮምና ዋሽንግተን ሙቀት፣ የባህር ዳርቻ ላይ ስለሚገኙ ምርጥ ምግብ ቤቶች እና ስለቪኒስ ግሩም ሆቴሎች ሲያወሩ ቆዩ።

በመጨረሻ ቡና እየተጠጣ፣ እፒቼላ ወደኋላ ለጠጥ ብሎ በምስጢር አነሳና፣ «አሁን ወደስራችን። ፊርሶቭን እንድሰልልልሽ የምትፈልጊ ይመስለኛል፣ ልክ ነኝ?»

http://ethzare.wordpress.com

«አዎ ፣» መለሰች ሩል። ስለተደናገጠች ሴላ ነገር ለመመለስ አልቻለችም እሷ ዙሪያ ጥምጥም ሂጻ ልትገልፅለት ነበር የተዘጋጀችው።

«መልካም፣» አለ፣ «አደርገዋለሁ።»

«ታደርገዋለህ?» ስትል በደከመ ድምፅ ጠየቀችው።

«እንዴ። ኮሚውኒስት መሰልኩሽ እንዴ?»

«አይ፣ አልመ. . . »

«ዶሴዎችን ፎቶግራፍ እንዳነሳ ነው የምትፈልጊው?»

«ኤሚሊዮ፣ ካሜራ ወይንም ሴላ የስለላ መሳሪያ ይዤልህ አልመጣሁም። ደግሞም ስራውን ጠንቅቆ ለማያውቀው ሰው በጣም አደገኛ ነገር ሊሆን ይችላል።»

ትክሻውን ሰበቀ። «እንደፈለግሽ። ከፈለግሽ ፎቶግራፍ ለማንሳትም ወደኋላ አልልም። የራሴ ሚኖክስ ካሜራ አለችኝ።»

ራሷን በአሉታ ወዘወዘች። «አይሆንም፣ ይህንን እንድታደርግ ልጠይቅህ አልችልም።

ማወቅ የፈለግኩት ፊርሶቭ የት እንደሚገኝና ምን እያደረገ ሊሆን እንደሚችል ብቻ ነው። ተመልከት፣ ክፍያ ልሰጥህ ስልጣኑ የለኝም፣ ግን . . . »

ሊያፈጥባት ዝም አለች። «ይህን የማደርገው ለገንዘብ ይመስልሻል? የአምላክ ያለህ፣ ጊል ስለሴት አያቴ አልነገረሽም?»

«ሩሲያዊ መሆናቸውንና፣ አንተ ሩስኪ መናገር የምትችለውም ለዚህ መሆኑን አጫውቶኛል።»

«ሴት አያቴ ልዕልት ነበረች፣» አለ፣ «በአስራዘጠኝ ሀያ በአብዮቱ መምጫ ላይ አገባች። እነዚያ የቦልሼቪክ ዲቃላዎች ንብረቷን ዘርፈው ባሏንም ገደሉባት። እምስት ሳንቲም ሳይኖራት በሶስተኛ ማዕረግ ባቡር ተሳፍራ ጣሊያን ስትደርስ፣ ዕድሏ ሆኖ አያቴን አገኘችው። ብዙም ሳትቆይ የጣሊያን ልዕልት ሆነች። በጦርነቱ ጊዜ ቤተሰቦቼ ስለተገደሉብኝ ከሀያንቴ ጀምሮ የኖርኩት ከእሷ ጋር ነው። የምታናግረኝ በሩስኪ ቋንቋ ብቻ ነበር። ስለኮሚኒዝምስቶቹ ማወቅ ያለብኝን ነገር በሙሉ ነግራኛለች። የእነሱን ውድቀት ለማፋጠን የቻልኩትን ሁሉ ባደርግ በጣም ደስ ይለኛል። ላመናምናቸው ስለምፈልግ የምቀበለው የእነሱን ገንዘብ ነው።» አለ በፈገግታ ፂሙን እየዳሰሰ። «የምሰራላቸው ለጦርነት የሚሆኑ ነገሮችን ሳይሆን ጥቃትን ነገሮችን ነው።»

«ገባኝ» አለች ሩል፣ «ስለ እርዳታህም አመሰግናለሁ።»

«ታዲያ እንዳደርግልሽ የምትፈልጊው በትክክል ምንድን ነው?»

«ስለፊርሶቭ ትክክለኛ መገኛ ስፍራና በተቻለ መጠንም እያደረጋቸው ስላሉት ነገሮች። በምን ዓይነት ቦታ ላይ እየሰራ እንደሆነና፣ በዙሪያው ስላሉት የጦር መሳሪያዎች ማወቅ እፈልጋለሁ። አይተህ ማስተወስ የምትችለውን ሁሉ በዝርዝር ማግኘት እፈልጋለሁ። ቁጥራቸው ብዙ ለሆኑ ሰዎች ትልቅ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል። ብዙ ሕይወቶችን ማትረፍ ይቻላል። ገባህ?»

«እንዴታ። እንደጠየቅሽኝ አደርጋለሁ። እንዴት አገኝሻለሁ?»

የቤት ስልክ ቁጥሯን ፃፈች። «አባክህ ይህንን ቁጥር በቃልህ ያዘው። እንደተፃፈ ሶቭየት ይዘኸው አትሒድ።»

ለአፍታ ያህል ቁጥሩን መልከት አደረገው። «እሺ፣ እሺ ይገርዋለሁ።»

«በዚህ የምገኘው ምሽት ላይ ብቻ ቢሆንም፣ የስልክ መቀበያ ማሽን ስላለ የምትገኝበትን አድራሻ ወይንም ቁጥር ልትተውልኝ ትችላለህ። በማሽኑ የስላላ ደቂቃ ያህል መልዕክት መተው ትችላለህ፣ ከዚህ ሴላ ደህንነቱ የተረጋገጠም ነው። እባክህ ከሶቭየት ህብረት ሆነህ ለመደወል እንዳትሞክር። ወደሮም እስክትመለስ ወይንም ሴላ ምዕራባዊ ከተማ እስክትገባ ድረስ ታገስ። ከቻልኩኝ ተመልሼ መጥቼ አናግርህለሁ፣ ግን ለዚህ ሁኔታ ጊዜ ያለኝ አይመስለኝም።

«ስለኮምፒውተሮች ታውቂያለሽ ኪት?» ጠየቃት።

«ብዙ ስራ እሰራባቸዋለሁ።»

«ምንጩ (The Source) እየተባለ የሚጠራው ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ?»

«ሚሪላንድ ውስጥ የሚገኝ የመረጃ ተቋም ነው። ተጠቅሜበት አውቃለሁ።»

«ጥሩ። አንዳንድ ጊዜ ፋይሎቼን እዚያ አስቀምጣለሁ። የይለፍ ቃሌ ZZPI00 ሲሆን፣ የምስጢር ቃሌ ደግሞ WHOP ነው። ይህን ማስታወስ ትችያለሽ?»

«አዎ።»

«በአንድ ምክንያት መደወል ሳልችል ከቀረሁ፣ እዚያ ላይ ኪት በሚል ስም መልዕክት እተውልሻለሁ። በየቀኑ ተመልከቺው።»

«እሺ።»

«አሁን ታዲያ፣ የኔ ውብ ሰላይ፣» አለ እፒቼሉ ሒሳቡን እየከፈለ፣ «ወደ ቪላዬ መጥተሽ አብረን ፍቅር እንሰራም?»

«አስቀያሚ ሀሳብ አይደለም ኤሚሊዮ፣ ግን የሚያሳፍረኝ አይሮፕላን ይጠብቀኛል።» አለችው።

28

ሔልደር በስቶክሆልም የህዝብ ማመላለሻ መርከብ ወለል ላይ ቀጧል። መርከቧ ሔልሲንኪ ወደብ እየገባች ነው። እረፍትና ጥሩ ምግብ አግኝቷል። ባለፈው ምሽት እጅ የሚያስቆረጥም እራት በልቶ ከሁለት ስዊድናዊ ልጃገረዶች ጋር ደንሷል። በራሱ ምርጫም ብቻውን ጥሩ እንቅልፍ አግኝቷል። ማልዶ ተነስቶ፣ ምርጥ ቁርስ ከተመገበ በኋላ መርከቧ ወደሔልሲንኪ ወደብ ስትገባ ተመለከተ። ከባህሩ አትጣጫ ሲመለከቷት ውብ ከተማ ብትመስልም፣ እሱን ግን አይኖቹ ወደቡ ላይ ይዋልላሉ። ከስቶክሆልም አስፈላጊውን የስልክ ጥሪ ያደረገ ቢሆንም ምንም አልተነገረውም፣ ስለዚህ እንድ ሰው ይጠብቀኛል ብሎ ተስፋ አድርጓል። ሔልደረ ከፍ ብሎ የተዘረጋውን ጣውላ በመጠቀም ከመርከቡ ወረደ። ውስጥ ሲገባ ከዚህ በኋላ ስለሚያደርገው እያሰበ በዝግታ እየተራመደ ነበር።

http://ethzare.wordpress.com

«ካርል!» የሚል ድምፅ ከበስተኋላው እደመጠ። ሰሙን ለማስታወስ ጥቂት ጊዜ ፈጀበት። ከዚያ ፊቱን አዞረ። የማሊቡው ሚስተር ጆንስ እጹን ጨበጠው። «ካርል፣ አጎትህ ጆን ነኝ እኮ! ደህና ነህ?»

«በጣም ጥሩ አጎቴ ጆን፣» ሲል ሔልደር መለሰ ታሪክ የፈጠረለትን ግለሰብ በማግኘቱ እየገረመው።

«አክስትህ ልታገኘህ ቸኩላለች፣» አለ ጆንስ። «በል፣ መኪናው ውጪ እየጠበቀን ነው።»

ጆንስ በፍጥነት ከሰገነቱ እየመራ ወደቆመው መኪና ሲወስደው ሔልደር ተከተለው። ጆንስ ፈገግታው ሳይጠፋ ስለአሜሪካና ስለ አክስቱ እያወራለት ወደአንድለማያዊ ቮልስ እንዲሔድ ምልክት ሰጠው። መንገድ ሲጀምሩ፣ ጆንስ እንዲህ አለ፣ «ሔልደር ስላገኘሁህ ደስ ብሎኛል። ወደ እናት ሰርጓጇ ላትመለስ በቀረህ ጊዜ በጣም ፈርተን ነበር። ሶኩፍ የት ናት?»

«እዚያው ትንሿ ሰርጓጅ ውስጥ፣» መለሰ ሔልደር። «ለመውጣት አልቻለችም።»

«ገባኝ፣» አለ ጆንስ፣ የኋላ መሳቢያ መስታወቱን እየተመለከተ። «ለጥቂት ጊዜ ለመጨዋወት ባለመቻላችን ይቀርታ አድርግልኝ። ማሽከርከሩ ላይ ላተኩት።»

ጆንስ በፍጥነት ከዚያም ዝግ እያለ በማሽከርከር በነሲብ በሚመስል ሁኔታ ባገኘው መገንጠያ ላይ እየታጠፈ መንገድ ቀጠለ። አንድ ጊዜ ቀይ መብራት አሰቆመውና፣ የኋላ መስታዋቱን ያለማቋረጥ መልከተ እያደረገ ጥሶት አለፈ። በመጨረሻ፣ በዛፍ የተከለለ ጎዳና ላይ ደርሶ ቆመ። የሊቪል ልብስ የለበሰ ሰው አንድ የብረት በር ከፈቶላቸው ገቡ። ጆንስ አንድ ትልቅ ውብ ቤትን አልፎ ከበስተኋላው መኪናውን አቆመውና። «ተከተለኝ።» አለ ከመኪናው ዘሎ ወርዶ በኋለኛው ደረጃ እየሮጠ በመውጣት።

ከውስጥ፣ የእብነ በረድ ወለሎች እና ብዙ ግዙፍ ቁሳቁስ ይታያሉ። ትንሽ አሳንሱር ውስጥ ገብተው ወደሁለተኛው ፎቅ በማምራት ደብዛዛ ብርሀን ወደሚበራበት ኮሪደር አመሩ። ጆንስ አንድ የብረት በር ፊት ቆመና ደወሉን ደወለ። ትንሽ መስኮት ተንሸራትታ ተከፈተችና፣ ሁለት ሰዎች ብቅ ብለው ሁለቱንም ተመለከቷቸው።

«ይህ ስፍራ ምንድን ነው?» አለ ሔልደር።

«የሶቪየት ኤምባሲ ነው፣» መለሰ ጆንስ። «የምታውቅ መስሎኝ ነበር።»

በሩ ተከፈተና ሽሚዝ የለበሰ ሰው በሬዲዮ ማሰራጫና መቀበያ ወደተሞላ ክፍል ይዟቸው ገባ። ክፍሉ በትንባሆ ጢስ ታፍኗል።

«እንዴት እንደሚሰራ አሳየው፣» አለ ጆንስ ለሰውየው።

«እዚህ ጋር፣» አለ ሰውየው፣ ወደአንድ የኮምፒውተር ዋና መቆጣጠሪያ እያመለከተው። «ታይፕ ማድረግ ትችላለህ?» ሔልደር ጠየቀ።

«አዎ፣» መለሰ ሔልደር።

ሰውየው እንድ ስልክ አንስቶ፣ ቁጥር ተጭኖ ለአፍታ ያህል አጻመጠና መልሶ ዘጋው። በኮምፒውተሩ ላይ የ'X' ምልክቶች በተርታ ከታዩ በኋላ፣ «አለሁ፣ እዚህ ነኝ።» የሚል ዕሁፍ መጣ።

«ከዚያኛው ጫፍ ኮሎኔሉ ናቸው፣» አለ ጆንስ።

ሁለተኛው ሰው ሔልደር እንዲቀመጥ ከኮምፒውተሩ ፊት ለፊት ያለውን ወንበር አሳየው። «አንተ ታይፐ ማድረግ ብቻ ነው፣» አለ።

«በል እንጂ፣ እንሂደ፣» ብሎ ጆንስ ለሰውየው ከተናገረ በኋላ፣ ሔልደርን ከኮምፒውተሩ ጋር ክፍሉ ውስጥ ትተውት ወጡ።

ሔልደርም፣ «እሰሁ፣ ጌታዬ» ብሎ ፃፈ።

«ተልዕኮህ ተሳካ?» የሚል ጽሑፍ ተነበበ።

«ተልዕኮዎቻችንን በተሳካ ሁኔታ ፈፅመናል፣ ግን ሰርጓጅ መርከቧን በጥልቀቱ ግፊት የተነሳ ለማጣት ተገደናል።» መልሶ ፃፈ።

«ቁጥሮቹን ላክልኝ፣» አለ ኮምፒውተሩ።

ሔልደር ጓዙን ያስቀመጠበትን ስፍራበአህዝ ገለፀ። ስክሪኑ ቁጥሮቹን ደገማቸው።

«እነዚህ ትክክል ናቸው?» ጠየቀው።

«አዎ፣» ሔልደር መለሰ።

«የመቁሰል አደጋ ደርሶብህል?»

«አልደረሰብኝም ጌታዬ በጣም ደህና ነኝ፣» መለሰ ሔልደር።

«ባልደረባህ በሕየወት ተረፈች?» ተጠየቀ።

«አልተረፈችም፣» ፃፈ።

«ጆንስ ወደአየር ማረፊያው ይወስድሀል፣ እዚያም ወደሞስኮ የሚወስድህ አይሮፕላን ይጠበቅሀል። ስትደርስ እንገናኛለን። በአይሮፕላኑ ላይ የሁለተኛ ደረጃ ካፒቴይንነት ማዕረግ ያለው የባህር ሀይል ዩኒፎርም ታገኛለህ። ከደረጃ እድገቱ በተጨማሪ፣ የከፍያህን ግማሽ በመረጥከው የውጭ ሀገር ገንዘብ ታገኛለህ። እንኳን ደስ ያለህ፣ ጥሩ ስራ ሰርተሀል።»

«ከመስመሩ ለቅቄያለሁ። ሞስኮ ውስጥ እንገናኝ።»

ሔልደር ለአፍታ ያህል የኮምፒውተሩን መስኮት ሲመለከት ቆይቶ ተነሳና በሩን ከፈተው። ጆንሰንና ሌላው ሰውዬ ከውጭ ኮሪደሩ ላይ ቆመዋል። «ጨርሼያለሁ፣» አለ ጆንስ።

አይሮፕላን ማረፊያው ላይ ምንም ወታደራዊ ምልክት የሌለባት አነስተኛ የሶቭየት ህብረት ጀት አይሮፕላን ቆማለች። ከጆንስ ጋር ተጨባበጡ።

«ማሊቡ ላይ እንገናኝ፣» አለ ሰውየው በፈገግታ።

«ለእጀቡ አመሰግናለሁ . . . ስፈጠርክልኝ እዲስ ማንነትም ጭምር፣» መለሰ። «ያንተን ስልጠና ባላገኝ ኖሮ ይህን መስራት ባልቻልኩ ነበር።»

ጆንስ ትከሻውን ሰበቀ። «ስራዬ ነው። እወደዋለሁ።»

ሔልደር አይሮፕላኑን ላይ ተሳፈረ፣ ለመብረር እየተንደረደረ ሳለ ረዳት አብራሪው ምግብና መጠጥ የሞላበትን ማቀዝቀዣ አሳይቶት አነስተኛ ቦርሳና የልብስ ሻንጣ ሰጠው። አየር ላይ ሲወጡ ረዳቱ ወደ ክፍሉ ተመልሶ መጣ። «አሁን ወዲያ ወዲህ ማለት ትችላለህ፣ ካፒቴይን። የምትፈልገው ነገር አለ?»

ሔልደር ራሱን በአሉታ ወዝውዘ መልስ ሲሰጠው፣ ሰውየው ወደ አብራሪዎቹ ክፍል ተመልሶ በሩን ዘጋው። ሔልደር የልብስ ሻንጣውን ከፍቶ የደንብ ልብሱ ላይ ያለውን አዲስ ማዕረግ ተመለከተ። ሻንጣው ውስጥ ሸሚዝ፣ ሚጣና የውስጥ ልብሶች እንዲሁም የመፀዳጃ ቁሳቁስ ይገኛሉ። በሸሚዝ ኪሱ ውስጥ የሚንኮሻኮሽ ድምጽ ሰምቶ ሲፈትሸው የተጣጠፈ ወረቀት አገኘ።

http://ethzare.wordpress.com

«ደህንነትህን ሰምቼ ደስ ብሎኛል። አዲሱን ማዕረግህን የሰሩህት እኔ ሃ። በቶሎ እንደማገኝህ ተስፋ አለኝ።» ይላል ወረቀቱ።

የድሎት መቀመጫው ላይ ተለጥጦ ተቀምጦ በረጅሙ ተንፈሰ። ሕይወቱ አለች፣ ደህንነቱ ተረጋግጧል፣ የደረጃ እድገት አግኝቷል፣ የምታፈቅረው ሴት ትጠብቀዋለች። ከዚህ የተሻለ ሁኔታ ሊኖር አይችልም።

ሞስኮ ሲደርስ ግን የተሻለ ገጠመው። አይሮፕላኑ ተንደርድሮ ሲያርፍ እና ሲቆም ሽንጠ ረዥም የቅንጦት መኪና ስትጠብቀው ተመለከተ። ያውም ዚል ሔልደር መውረጃ ደረጃዎቹ መጨረሻ ላይ ቆሞ ትክ ብሎ አስተዋላት። በመላው ሶቭየት ህብረት፣ በእጅ የተሰሩት እነዚህ መኪኖች በቁጥር ከመቶ እንደማይበልጡ ይነገራል። እነዚህን ማግኘት የሚችሉት ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው መኮንኖች ብቻ ናቸው። እፍጥጠ ቆሞ እያለ ሹፈሩ ወጣና በሩን ከፈተለት። ማጆሮቭ በኋላ ወንበሩ ላይ ሲጠብቀው አገኘው። ኮሎኔሉ በጋለ ስሜት ጨበጠው።

«በመመለስህ በጣም ደስ ብሎኛል፣ ሔልደር፣» አለ ከብሩህ ፈገግታ ጋር፣ «ስለአንተና ስለተልዕኮው መሰጋት ጀምሬ ነበር፣ አሁን ግን ተመልሰህ በመምጣትህ ተጠናቅቆ ልናገኘው ችለናል፣ የጊዜ አጠባበቅህም ሽጋ ነው።» መኪናዋ ከአይሮፕላኑ በፍጥነት እየራቀች በሩን አልፋ አውራ ጎዳናውን ያዘች። «አለቆቼ ስብሰባ ላይ ይገኛሀ ለመገኘት በሚያስችል ሰዓት ነው የደረስከው። በአንድ እኔ የማቀርበው ንግግር ላይ እገዛህን እፈልጋለሁ - መኪናው ኪስ ውስጥ ፎቶግራፎችና ወረቀቶች አሉልህ።»

«እኔም በመመለሴ ተደስቼያለሁ ጌታዬ፣ እገዛ ባደርግልህ ደስ ይለኛል።»መለሰ ሔልደር። መኪናዋ በሞስኮ ገጠር ቀመስ ከተሞች አያቆራረጠ ወደ ከተማዋ ማዕከል ትበርራለች። የሞስኮቫ ወንዝን ሲያቋርጡ፣ የቅዱስ ባሲል በቀዩ አደባባይ የሚገኝ ረጅም ቤተ መቅደስ ከክሬምሊን ቤተመንግስት ግንብ አጠገብ ማንገቦብ ጀመረ።

«የሶክሉና ነገርም አለ፣» አለ ማጆሮቭ።

«አዎን ጌታዬ።»

«ዝርዝሩን ማወቅ ያስፈልገኛል?»

«የጥልቀት ፈጣን ጉዞው ሲጀመር ሌተናንት ሶክሉፍ ግራ ተጋባች፣ ጌታዬ። ምን ልታደርግ. . . ምን ልታደርግ እንደፈለገች በውል አላውቅም፣ ግን ከጓላዬ አነቀችኝ። እኔ. . . በግብግቤን መሀል ተገደለች። ለጥቂት ጊዜ ያህል ራሴን ስቼ ቆየሁ፣ ራሴን ሳውቅ ሞታ አገኘኋት። ባመለጥኩ ጊዜ በድኗን በውሀ በተጥለቀለቀው ትንሹ ሰርጓጅ ጀልባ ውስጥ ትቼው አመለጥኩ።

ማጆሮቭ እንደገባው በምልክት ገለፀለት። «ይህን መሰል ነገር ይመጣል ብዬ መጠበቅ ነበረብኝ። ወሳኝ ተልዕኮ አንድሰጣት ከባድ ጫና እየተደረገብኝ ነበር።»

«ገባኝ፣ ጌታዬ።»

«በውሀ ስር ጉዞው ላይ ተገድላለች ብሎ ማስታወቁ ተመራጭ ይመስለኛል። ራሷ ላይ ግጭት ደረሰባት እንላለን። ሰርጓጇ መርከቧም መቼም አትገኝም።»

«አዎን ጌታዬ።»

መኪናዋ ወደቀኝ ታጥፋ ሜንዝናያ ጎዳናን ያዘች፣ ከጥቂት ርቀት በኋላ ዳግመኛ ወደቀኝ ታጥፋ ትንሽ ተጓዘች። ወደከሬምሊን ቤተመንግስት እየገቡ መሆናቸውን ሔልደር ድንገት ተረዳ እንገቱ በስተጀርባ ያሉት ፀጉሮች መርገብገብ ጀመሩ። ከዚህ በፊት አጥር ግቢው ገብቶ ያውቃል፣ ግን ለጎብኚዎች ብቻ ክፍት በሆነ ስፍራ ነበር። አሁን በሮቹን አልፈው የታላቋ ሶቪየትን አዳራሽ አልፈው እየሄዱ ነው። የሶቪየትና የሌሎች ሀገር ጎብኚዎች የእግረኛ መንገዶቹን አጨናንቀዋቸዋል። መኪናው ማንም ሳያቆመው ሌሎች የብረት በሮችን አልፎ ሄደ። መንገዱ በድንገት ከጥቂት የደንብ ልብስ የለበሱ የዘብ ወታደሮች በስተቀር ወና ሆነ። ዚል ሽንጣሟ መኪና የቀዩን አደባባይ ጥግ ይዞ የተገነባውን የክሬምሊን ግንብ አጠገብ ሲደርስ ሲል ቆመ። ማጆሮቭ ሲወጣ ሔልደር ተከተለው። ሹፈሩ ወደእቃ ማስቀመጫው ሄደና ሁለት ትልልቅ ሳጥኖችንና ሌሎች ትንንሽ ቁሳቁሶችን አመጣ።

«ብታግዘው ቅር ይልህል?» አለ ማጆሮቭ፣ ወደጓዙ በአገጩ እያሳየው።

ሹፈሩ ቀድሞ ሁለቱን ትልልቅ ሳጥኖች ስለያዛቸው ሔልደር የተቀሩትን ትንንሽ ሳጥኖች እንስቶ ግርማው በሚያስፈራው መግቢያ አለፈ። ውስጥ ሲገቡ የቀዩን ጦር ሙሉ የጄኔራልነት ማዕረግ የያዘ ሰው እንዲከተሉት ምልክት ሰጣቸው። ወደሶስተኛው ፎቅ ወጡና በፀሐይ ብርሀን የደመቀ ሰፊ ኮሪደር ላይ ደረሱ። ጄኔራሉን ተከትለው ማረፊያ ክፍሉን በማለፍ፣ በተካፋች በሩ በኩል ጠረጴዛና ረጅም የኮንፈረንስ ጠረጴዛ ያለበት ፀሐይ ያደመቀው ክፍል ገቡ።

ሔልደር ከሌኒንግራዱ የክረምት ቤተመንግስት በስተቀር ከጎባቸው ክፍሎች ሁሉ ከዚህ የሚወጻደር አስቦ አላገኘም። ግድግዳዎቹ በደብዛዛ ቢጫ የሀር ጨርቅ ተሸፍነዋል። አራት ረጃጅም መስኮቶች ሲኖሩ፣ በነሙ የሀር መጋረጃ ተሸፍነው፣ ውብ ሆኖ የተከረከመውን የቤተመንግስቱን ቅጥር መናፈሻ ቁልቁል ያሳያሉ። በግድግዳዎቹ ላይ አንድ ፎቶግራፍ ብቻ ተሰቅሏል፣ የሌኒን በረጅሙ ጠረጴዛ ላይ፣ በየቦታው ከብርጭቆ የተሰራ የእርሳስ ማኖሪያና ማስታወሻ ደብተር ተቀምጠው ይታያሉ።

ማጆሮቭ ተከትሏቸው የመጣውን ሹፈር ሳጥኖቹን ጠረጴዛው እንድ ጫፍ እንዲያስቀምጡ አዘዘው። ሹፈሩ ያለከልካል። ሳጥኖቹ የያዙት ምስል አጉልቶ ማሳያ መሳሪያዎችን /ፐሮጀክተሮችን/ ነበር። የማጆሮቭ ግዙፍ ሻንጣ ውስጥ ተመሳሳይነት ያላቸው መዛግብቶችን ይዘዋል። ሁሉ ነገር ቦታውን ይዞ ከተዘጋጀ በኋላ ማጆሮቭ ሹፈሩን አሰናበተው። እሱ፣ ማጆሮቭና ጄኔራሉ ብቻ ቀሩ።

«እሺ፣ ቪክቶር አርጌቪች፣ አሰ ጀኔራሉ ሲጋራ እያቀጣጠለ፣» ይህ ለእንተ ታላቅ ቀን ነው አይደለም!»

ማጆሮቭ ራሱን ዝቅ በማድረግ አይነት ትከሻውን ሰበቀ። «እሱ ገና የምናየው ነው ጀኔራል። ትስማማለህ?»

የጀኔራሉ ፈገግታ ከሰመ። «ይህን ገና የምናየው ይሆናል።»

ከክፍሉ አንድ ጫፍ የሚገኝ በር ተከፈተ፣ ጀኔራሉ በችኮላ ሲጋራውን አጥፍቶ በተጠንቀቅ ሲቆም፣ ማጆሮቭም ተመሳሰለው። ሔልደርም ያደረጉትን አደረገ። የሲቪል ልብስ ለብሰዋል። ሌሎቹ ከፍተኛ ማዕረግ ባላቸው የደንብ ልብስ ተንቆጥቁጠዋል። ዋናውን ራስ ወንበር ብቻ በመተው ሁሉም ቦታቸውን

http://ethzare.wordpress.com

ያዙ። ሔልደር በፐራፍጻና በኢዝቬስቲያ ጋዜጦች ላይ ፎቶግራፋቸውን የተመለከቷቸው ብዙ ሰዎች እየ። በተለይም የሶቪየት ባህር ኃይል አዛዥን እድሚራ ጎርሽኮቭን። ባለስልጣኑ ከሠያ ዓመታ በላይ መንበራቸው ላይ የቆዩ ናቸው። ከእፍታ ቆይታ በኋላ፣ በእድሜ ከልሎቹ በጣም የሚያንስ ደልጻላ ቁመና ያለው ሰው ወደክፍሉ ገብቶ በጠረጴዛው ራስ ላይ የሚገኝ ወንበሩን ያዘ።

ሔልደር በኮሙኒስት ፓርቲው ዋና ፀሐፊና ፖሊት ቢሮ ፊት መቅረቡ ድንገት ተከሰተለት።

29

ሩል ያለማቋረጥ የሚጮኸው ስልክ ቀስቅሷት ከእንቅልፏ ነቃች። በጭለማው ሰዓቷን መመልከት ቢቸግራትም እምስት ሰዓት የሆነ ይመስላል። ፀሐይዋ የከፍሏን መጋረጃዎች አልፋ ለመግባት ትግል ይዛለች። ምናልባት ከቢሮ ይሆናል። ሮም እያለች ደውለውላት አያውቁም፣ ተመስገን ነው። ስልኩን አነሳችው።

«ሀሎ።»

ድምፁ ጥርት ያለ ቢሆንም መስመሩ ግን ይቆራረጣል። «ሀሎ፣ ጓደኛዬ። በዚህ ሰዓት እቤት ምን ታደርጊያለሽ?»

«ዊል? የት ነው ያለኸው?»

«ጃኮብስታድ ውስጥ ነኝ፣ ፒየታርሳሪ እየተባለም ይጠራል። የሚገኘው በፊንላድ ምዕራባዊ የባህር ጠረፍ ላይ ነው። መድረሻዬ ማለት ነው። ከዚህ በላይ ልነግርሽ አልችልም።»

«አሞኛል። አልጋ ላይ ከወጣሁ አንድ ሁለት ቀኔ ነው። ስልክ ስመልስ ያንተ የመጀመሪያዬ ነው።»

«እየተሻለሽ እንደሆነ ተስፋ አለኝ፣ ኮፐንሀገን እንደምትጠብቂኝ ይታየኛል።»

«እኔም እያሰብኩት ነው፣ ግን መምጣት ለመቻሌ ገና ርግጠኛ አይደለሁም።

«ያ ችግር አሁንም እንደቀጠለ ነው?»

«አዎ፣ ግን ትንሽ እረፍት አግኝቼያለሁ። መጨረሻውን ምን እንደሚያደርጉት ገና ርግጠኛ አይደለሁም።» በቀጥታ ስላልጠየቃት ደስ አላት። ከውጭ የሚደረጉ የስልክ ጥሪዎች እንደሚጠለፉ ጠንቅቃ ታውቃለች።«ጀልባዋን እንዴት አገኘህት?»

«ጀልባዋ ግሩም ናት። ጉዞዋን ለመጀመር ዝግጁ ነች። ዛሬ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አደራጅቼያለሁ። ጠዋት እነሳለሁ።» «የባህርተኞችህስ ነገር ተስተካከለ?»

«ከናካቴው አልሆነልኝም። ሚስቱ ከቀኗ በፊት ልትወልድ በመሆኑ፣ እስከመጨረሻው ሰዓት ድረስ መምጣት ያለመምጣቱን ሊያሳውቀኝ አልቻለም።»

«ምን ልታደርግ ነው?»

«መስተካከሉ አይቀርም። ከጀልባ ማምረቻው ሰራተኞች አንዱ ወደደቡብ እስከ ሁለት መቶ ማይሎች ገደማ ከኔ ጋር ሊመጣ ነው። ከሱ ጋር ቀን እና ሌሊት እንቀዝፋለን። አለንድ የሚባለውን የደሴቶች ስብስብ ለማለፍ

ይሪጻኛል። የሚያስቸግረኝ ይኸው ነበር። ከካር ላይ እጥለውና በሌላ መ ተሳፍሮ ይመለሳል። ከዚያን በኋላ ብቻዬን እሆናለሁ፣ ገላጣ ውህ ሰ አያስቸግርም። በንጂ ላይ ቆሜ የጎደለ ነገር አሞላለሁ። በንጂ የስዊድን ት_. ደሴት ጎትጎንድ ላይ የምትገኝ ከተማ ናት። ከዚያ እቀጥላለሁ።»

«እደጋ አይኖረውም?»

«ምናልባት። ከዚህ በፊት እንጻደረግኩት ታውቂያለሽ። እንደገና ብቻዬን ጀልባ መምራት ናፍቆኛል። የፈበረካት ኩባንያ ብቃቱ ከፍተኛ ነው።»

ሳቀች። «ኮፐንሀገን የምትደርሰው መቼ ነው?»

«የእሁድ ሳምንት እደርሳለሁ ብያለሁ፣ ችግር ከሌለ። የደረስኩበትን ከጎትላንድ ደውዬ እነግርሻለሁ።»

«እንጻልክ ይሁን» ካልደወልክ እጨነቃለሁ።

«የተጨነቅኩት እኔ ነኝ። ያንቺ ችግሮች ከኔ ይከፋሉ። ስሚ ነገሮች ከአቅምሽ በላይ ከሆኑ ለአለቃዬ ደውይለት። እርሳስ ያገኘና የግል ቁጥሮቹን ፃፈ።»

የሴናተር ካርን የቢሮና የቤት ስልክ ቁጥሮች ፃፈች።

«በችግር ጊዜ የሚጠቅም ሰው ከመሆኑም በላይ በችሎቱቹ ላይ የምታሳይውን ብቃት የሚያደንቅ ሰው ነው።»

«ከዚህ ውጭ እንደማያልፍ ተስፋ አለኝ፣ ግን የችግር ጊዜ ደራሽ እንጻለኝ ማወቁ በራሱ ጥሩ ነው።»

«ስሚ፣ መሄድ አለብኝ። ምግቡን ሁሉ የምጭነው ዛሬ ነው የጉዞ እቅጣጫዬንም ማቀድ አለብኝ። ዛሬ ጀልባዋ ላይ አድርና ነህ ሲቀድ ጉዞ እንጀምራለን።»

«እሺ፣ ተጠንቀቅ፣ ጎትጎንድ መደወል እንጻትረሳ።»

ስልኩን ዘጉት፣ ለአፍታ ያህል ናፍቆት ቆጠቆጣት። ኮፐንሀገን ላይ ለመገኘት አጥብቃ ተመኘች። ግን ከአልጋ መነሳት እንኳን ሳትችል እንዴት ኮፐንሀገን መድረስ ትችላለች? አንድ ሁለት ርምጃዎች መራመጃን ለዊል ነግራዋለች።

ምን ያህል ውጤት እንጻመጡለት ግን አልገለፀችለትም።

የቃለ መጠይቅ ባለሞያ መሆን እንደግትችል ቢያንስ ተረድታለች። ማላከሆቭ በወሬው መስጠ ይዞ ሲያደንቃት ቆይቷል፣ እሱ ሊሰጣት ከሚፈልገው በላይ ምንም ማግኘት አልቻለችም። የመስክ ተልዕኮ ባለሞያም አይደለችም። መሠረታዊ ስልጠናና በውጭ ሀገር የአጭር ጊዜ ልምድ ብታደርግም እንድን ሰላይ መምራት አትችልም። የኋላ ኋላ ኦፒቼላ እንደፈለገ ይመራት ጀምሯል። ከዚህ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንጻለባት አታውቅም። የምትፈልገው ትኩስ መረጃ ቢሆንም የኤሚሊዮ ኦፒቼላን መልዕክት እስካላገኘች ድረስ፣ መረጃውን ልታገኝ የምትችለው ከድርጅቱ ብቻ ነው። የራሷን ሰላይ ማሰማራቷን ስታስበው በእንድ መልኩ ያስደስታታልም፣ ያበሳጫታልም። በሷ ፈንታ ይህንን ማድረግ ያለበት የተልዕኮዎች ክፍል ቢሆንም የአሁኑ የCIA ጻይሬክተር መጠቅ ያለ ነገርን ይወጻል። ሽማግሌው ሳይመንም እያበረታታው ነው።

ከአልጋዋ ተፍጨርጭራ ተነሳችና ጻግሞኛ ፍለጋዋን ለመቀጠል ቆርጣ ወደቢሮዋ ለመሄድ ተዘገጃጀች።

http://ethzare.wordpress.com

ሔልደር በድማሜ ተውጦ እንደተቀመጠ ማጆሮቭ ለፖሊት ቢሮው የሚያቀርበውን ንግግር ይከታተላል። በስብሰባ ጠረጴዛው ዙሪያ የተቀመጠው ሰው በሙሉ የእቅዱ ጠቅላላ ሀሳብ በወረቀት ደርሶታል። ማጆሮቭ በሁለቱ ግዙፍ ስክሪኖች ላይ ምስሎችን እያነሱ የሚፈነጥቁ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማህደሩን የያዘውን ሀሳብ በማራኪ ሁኔታ ሲያቀርብላቸው ከወረቀቱ ይከታተላሉ። ሔልደር ምስሎቹ የስራ ጊዜያቸው ሲያበቃ ጠብቆ እየለዋወጣቸው በተቻለው አቅም ማጆሮቭ የሚናገረውን ለመከታተል ይጣጣራል። እስከ አሁን እንኳ የእንድ ሰዓት የገለፃ ክፍለ ጊዜን አሳልፈዋል።

«ጓዶች፣ በስተግራ ባለው ስክሪን ላይ በተልዕኮው የመጀመሪያ ስድስት ሰዓታት የምናገኛቸው ዋንኛ ኢላማዎችን ትመለከታላችሁ። እንደ ደረጃቸው ቅደም ተከተል አልተቀመጡም፣ ቁልፍ ወታደራዊ ተቋማት፣ ዋና የሰራዊቱና የህዝቡ አይሮፕላን ማረፊያዎች እንዲሁም በእኛ የእቅድ መስመር ላይ የተነጣጠሩ በስዊድን ደሴቶች ላይ የተጠመዱ ከባድ መሳሪያዎች ናቸው። አሁን እየተናገርኩ ሳለሁ እንኳን አንድ ሺህ አራት መቶ የሚሆኑ የስፔትስናዝ ሰላይዎች በስዊድን መሬት ላይ ይገኛሉ። የመጨረሻ ቅኝታቸውን አድርገው በእነዚህ ኢላማዎች ላይ ድንገተኛ ጥቃትን ለመሠንዘር እቅድ እየነደፉ ነው። በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ የእናንተ ፈቃድ ታክሉበት ስዊድን ውስጥ የሚኖሩት የስፔትስናዝ ወታደሮች ቁጥር ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ይደርሳል። ይህ ቁጥር ያለ ሌላ እርዳታ የውጥናችንን ሀያ ሰባት በመቶ ግብ ለማድረስ ያስችለናል።

«ይህ የሚያጠቃልለው ስትራግናስ የሚገኘውን የስቶኮልም የጦር ሰራዊት የበላይ መምሪያ፣ በስተምዕራብና የስቶኮልም አየር ማረፊያን የመሰሉ ኢላማዎችን ነው። የእነዚህ ሰራዊቶች ልዩ ሰኳዶች ከዚህ ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ካቢኔቱን እንዲሁም ሁለት መቶ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትን ለይቶ ወደፀጥታ ቀጣና ይወስዳል። ሌሎች ልዩ ሀይላት ደግሞ ልክ እንደደረሱ በሀገሪቷ ውስጥ ተሰራጭተው የሚገኙ ዝቅተኛ ሀይል ያላቸውንና የድንገተኛ ጊዜ የሬዲዮ ጣቢያዎችን ጨምሮ ሁሉንም የሬድዮና የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ይቆጣጠራሉ። ይህ የብሔራዊ ጋዜጠኞችንም ያጠቃልላል።

የፖሊት ቢሮ አባላቱ ከሔልደር ባልተናነሰ ጆሮአቸውን አቁመው ምስሉ በተቀየረ ቁጥር ወረቀቶቻቸውን ይገልጣሉ።

«ጓዶች፣ ስዊድን በሰላሳ ስድስት ሰዓታት ውስጥ ተደራጅቶ በተጠንቀቅ መቆም የሚችል ስምንት መቶ ሺህ የሚጠጋ ሰራዊት እንዳላት ታስታውሳላችሁ። በሌላ ጊዜ በተጠንቀቅ የሚገኝ ሰራዊቷ ከጠቅላላው አስር መቶኛ በታች ነው። ስለዚህ ከቀዳሚ አላማዎቻችን አንዱ የእነዚህን ሀይላት መሰባሰብ መግታት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጥሪው የደረሳቸው ከመደራጀታቸው በፊት ጦር መሳሪያ እንዳያገኙ ማገድ ይሆናል። በሀገሪቷ ውስጥ ቢመቶዎች የሚቆጠሩ የጦር መሳሪያ መጋዘኖች በስተቀኝ ባለው ስክሪን ላይ በምትመለከቷቸው ስፍራዎች ላይ ተበታትነው ይገኛሉ። ከእነዚህ ዴፖዎች መሀል ስማንያ አንድ በመቶው በተልዕኮው የመጀመሪያ አስራሁለት ሰዓታት ውስጥ ወይ ከዚያ በፊት በቁጥጥር ስር ይውላሉ፣ የተቀሩትም ከዚያን ጊዜ በኋላ በአጭር ሰዓት ውስጥ እጃችን ይገባሉ።»

እንድ ድምፅ ከጭለማው ውስጥ ተሰማ። «የስዊድን መከላከያ ኃይል ዝርዝር መረጃ እንዴት ለማግኘት ቻላችሁ?»

«ጓድ፣» መለሰ ማጆሮቭ፣ «እስከዚህን ሰዓት ድረስ በጥብቅ ሚስጥርነት ይዘነው የቆየነውን ነገር አሁን ግልፅ ማድረግ እችላለሁ። በስዊድን መንግስት ውስጥ በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ላይ የሚገኝ ለተወሰነ ጊዜ የቆየ ሰው አለን። የኮድ ስሙ ሲል ሲሆን፣ የሀገሪቷን የመከላከያ እቅዶች ሙሉ በሙሉ ሊያቀብለን የቻለ ሰው ነው። እነዚህ እቅዶች ከፊት ለፊታችሁ በስክሪኑ ላይ የምትመለከቷቸው ናቸው። ማለትም የየባህር ጠረፉ መሳሪያዎች የተጠመዱባቸው ስፍራዎች፣ እያንዳንዱ የመጠባበቂያ የጦር መሳሪያ ማከማቻ፣ እያንዳንዱ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሬዲዮ ጣቢያ፣ እያንዳንዱ አይሮፕላን፣ ታንክና የሚሳኤል ተቋም፣ እንዲሁም በሀገሪቷ የሚገኙ የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች በሙሉ ናቸው። በዘመናዊ የወታደራዊ እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ይህን ያህል መረጃን ያገኘ ማንም ወራሪ ሀይል የለም።»

በክፍሉ ውስጥ ሙሉ ፀጥታ ሰፈነ።

«ከዚህ በፊት እንደተናገርኩት፣» አለ ማጆሮቭ፣ «በዜሮ ሰዓት ስምንት ሺህ ሁለት መቶ የስፔትናዝ ሰራዊት ዘልቆ ገብቶ ይቆየናል። በለሊቱ የምድርና የውሃ ላይ ተንቀሳቃሽ እንቅስቃሴን፣ እንዲሁም በህዝብ ማመላለሻ ባረራዎችና ከሔልሲንኪ ወደስቶክሆልም በሚጓዙ ጀልባዎች ሰርገው የሚገቡ ይሆናሉ። በዜሮ ሲደመር ሀያ አራት ሰዓት ላይ በሀገሪቱ ውስጥ እንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ ጦር ይገባል ብለን እንጠብቃለን። ዋና የመንቀሳቀሻ መሳሪያችን አዲሱ የዊግ ባራሪ ቡድን ነው። በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ድንቅ የሰራዊት ማመላለሻ ባረራዎች ቁጥር ሀያ ሁለት መድረሱን ስነግራችሁ በደስታነው። እያንዳንዳቸው ከምስራቃዊው የባልቲክ ጦር ሰፈሮቻችን ከሙሀ በላይ በዝቅተኛ ከፍታ እየበረሩ 500 ሰራዊትን በማማሸ ሰዓት ጊዜ ውስጥ የከምድር ወደአየር ተወንጫፊ ሚሳኤሎችንና የባህር ኬላ ፀረ አይሮፕላን ከባድ መሳሪያዎችን ከልል ሳይታዩ ጥሰው መብረር ይችላሉ። ቀድመው ገብተው በሚቆጣጠሯቸው ጎዳናዎች ላይ ሲያርፉ በሰራዊት ማመላለሻ ሰርጓጅ መርከቦቻችን የሚደርሰው ሌላ ሀይል ጥበቃ ያደርግላቸዋል።»

«ለቁስለኞችና ለጥቃት ሰለባዎች ምትክ ምን አዘጋጅታችኋል?» አንዱ ጠየቀ።

«ተልዕኳችንን የምንፈፅመው በድንገት ስለሚሆን ብዙ ሰለባ ይኖራል ብለን አንገምትም። ቢሆንም ግን ከየምድቡ የሀያ ቢመቶ ጥፋት ይደርሳል ብለን የከፋውን ሁኔታ ብንመለከት እንኳ ከዜሮ ሲደመር ሀያ አራት ሰዓት በፊት ስማንያ አምስት በመቶ ያህሉን የዋናውን የግባችንን ከፍል ዳር እናደርሳለን ከዚያ ሰዓት በጣም ቀደም ብለው በተራ የአየር ትራንስፖርት ስዊድን ውስጥ የሚገኙ ደህንነታቸው የሚጠበቅ አየር ማረፊያዎች ላይ የሚደርሱ ሰራዊቶች ይኖሩናል።»

ለሌላ አንድ ተጨማሪ ሰዓት ማጆሮቭ የሰራዊቱን እንቅስቃሴዎች የግንኙነት ሁኔታዎችን እና ሌሎች ትጥቅና ስንቅን የተመለከቱ ሁኔታዎችን ሲያብራራ ቆየ። ከዚያም፣ ምልክት ሲሰጥ መጋረጃዎቹ ተከፈቱና ክፍሉ ጸጥሞ በብርሀን ተጥለቀለቀ።

http://ethzare.wordpress.com

«ጓዶች፣» አለ ማጆሮቭ፣ «በጣም ታግሳችሁኖል፣ ግን የመጨረሻ ሪፖርቴን ለማቅረብ እንደመንደርደሪያ የሚሆን አንድ የአቅዳችን አጠር ያለ ጉዳይ ይቀረኖል። በየዩኒቨርስቲዎቻችን ውስጥ የሚገኙ መጠቅ ያሉ የሰዊድን ተናት ፕሮግራሞች በሰዊድንኛ ቋንቋን እቀላጥፈው መናገር የሚችሉ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሲትና ወንዶችን ማፍራት ችለዋል። በስዊድን የሲቪል ሰርቪስ መርሀግብሮችም ከፍተኛ ስልጠናን በብሔራዊና በክልላዊ ደረጃ የቀሰሙ ናቸው። በሀያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ፣ ማለትም ወታደራዊ ይዞታችን ክፀና በኋላ፣ እያንዳንዱ የመንግስት ግልጋሎት ሰጭና በክልሎች ስር የሚተዳደሩ ኢንዱስትሪዎች በሙሉ በሶቪየት ቁጥጥር ስር ይውላሉ። የሬዲዮና የቴሌቭዥን እንዲሁም የህገሪቱን የጋዜጦችና መጽሔቶች ይዘት የሚቆጣጠሩት አርታኢያን ሩስያውያን ይሆናሉ። እቅዳችን፣ ስዊድኖች በእነዚህ አገልግሎቶች ረገድ ስዊድናውያን እጅግ ጥሩ አስተዳዳሪዎች በመሆናቸው፣ ላሳ አድርገን ለመያዝ ነው። የዜናው ሁኔታ በተቻለ መጠን የቀድሞ መልኩን ይዞ እንዲቆይ ይደረጋል፣ የኛ ድርሻ የሚያነጣጥረው የሶቪየት ህይል በስዊድን ማህበረሰብ ውስጥ በሚኖረው ተፅዕኖ ላይ ብቻ ይሆናል።

«ህገሪቷን በተቆጣጠርን በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ ከስዊድንና ወደ ስዊድን ገቢና ወጪ በረራዎችን ዳግመኛ እንቀጥላለን። ብዙ ስዊድናዊያንም፣ በተለይ ከአስመጪና ላኪ ንግድ ግንኙነት ያላቸው ከቀድሞ ባልተናነሰ መልኩ በረራ እንዲያገኙ በማድረግ የአለም አቀፍ በረራውን እንፈቅዳለን። ብዙ ቁጥር ያላቸውን ስዊድናውያን የጉዞ መብት ነፃ ማድረጋችን የመገዛት ስሜትን የሚያረግብም ነው ብለን እናምናለን። ወደሀገር ውስጥ የሚገባን የውጭ ህገር ገንዘብ በተቻለን ሁሉ ማበረታታት እንሻለን። አሁን ግን ዝርዝር ጉዳዩ ውስጥ አልገባም። በነገው እለት፣ በተወረረ ማህበረሰብ ውስጥ ለሚገኘው የስዊድናውያን ህይወት KGB ያወጣውን እቅድ ሙሉ ቃል እንመለከታለን። እንደምትወዱት ተስፋ አለኝ። ሌላ ጥያቄ ከሌላችሁ. . . ?»

«ቪክቶር ሰርጌይቪች፣» አለ አንድ ድምፅ፣ ከሞንቅላቱና ከአካሉ እንቅስቃሴ ሰውየው ሊቀመንበሩ መሆኑን ሔልደር አወቀ። «የከፋ የጉዳት ግምት ብለህ ስትናገር ሰምተናል፣ የከፋ የጉዳት ግምት ስለተባለ ነገር መስማት እንፈልግም። ይህ እቅድ መውጣት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አቋማችንን በጣም ግልፅ አድርገናል። በተወዳጁ በዩሪ አንድሮፖቪች የስልጣን ዘመን፣ ይህ ወረራ የሰዊድን መንግስት ወታደሮቹን ሰብስቦ በተጠንቀቅ ማቆም ከመቻሉ በፊት በድንገት መካሄድ የማይችል ከሆነ፣ ከናካቴው መካሄድ አይችልም የሚል አቋም አለ። ዳሩ ግን ሰዊድናውያን ተልዕኮአችን ከመጀመሩ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንኳን የሚመጣባቸውን ካወቁና በዜና ማሰራጫዎች የተጠንቀቅ አዋጅ ማስተላለፍ ከቻሉ፣ የሚጠብቀን ነገር የጋለና ድባቅ የሚመታን ፍልሚያና፣ በአለም ህዝብ አፍ መብጠልጠል ብቻ ይሆናል። በእነዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ የሶቪየትን ውርደት የማልቀበል ስለሆነ፣ አሁንም ደግሜ የምናገረው፣ በእነዚህ ጓዶች ፊት፣ የወረራው ትዕዛዝ የሚተላለፈው በሙሉ ለድንገተኛ ጥቃት ሙሉ ለሙሉ በራሳችን መተማመናችንን እምፄ ስቀበለው ብቻ ይሆናል። ትዕዛዙንም የማስተላልፈው እኔ ነኝ። ግልፅ ነው?»

«በጣም ግልፅ ነው፣ ጓድ ሊቀመንበር፣» አለ ማጆሮቭ በተወሰነ ደረጃ ስሜቱ ተነክቶ። «እናም አሁን፣ ስብሰባው ከማብቃቱ በፊት፣ ያለጥርጥር

በዛሬው የስለላ ሪፖርቶቻችሁ ላይ ያነበባችሁትን የአነስተኛ ሰርጓጅ መርከብ ተልዕኮ በስዊድን የውሀ ክልል ላይ ፊዕሞ የመጣውን የሶቪየት የባህር ሀይል መኮንን ላስተዋውቃችሁ እፈልጋለሁ። ጓዶች፣ ሁለተኛ ደረጃ ካፒቴይን ጆን ሔልደር።»

ሔልደር በተጠንቀቅ ቀጥ ብሎ ቆመ። የተሰባሰቡት ሁሉ ተነስተው በጭብጨባ አድናቆታቸውን ሲገልፁለት ተገረመ። ጭብጨባውን ጨርሰው እስተቀመጡም።

«ካፒቴን፣» አለ ሊቀመንበሩ፣ በጠማር እንደበት። «ፓርቲው ውስጥ በሚገኙ ባልደረቦቼ ስም፣ ላደረግከው የጀግንነት ተግባር የሶቪየት ህዝብ የተሰማውን ጥልቅ ደስታ ልገልፅልህ እወዳለሁ። አንተም እንደእኛ ሁሉ በባልደረባህ መኮንን ማለትም በካፒቴን ሌተናንት ሶኮሎፍ ሞት ማዘንህን አውቃለሁ፣ በተገቢው ጊዜ የህዝቡን ምስጋናና አድናቆት እንደምታገኝ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ።

«አመሰግናለሁ፣ ጓድ ሊቀመንበር፣» አለ ሔልደር እንደምንም ብሎ።

ሰዎቹ ሊቀመንበሩን ተከትለው ከክፍሉ ሲወጡ ሔልደር ማረፊያ ክፍሉ እንዲጠብቀው ምልክት ሰጠው። «አሁን፣ ሔልደር ይዞህ በመጣው መኪናና በእይርፐላኑ ወደማሊቡ ጉዞ ትቀጥላለህ። ራስህን አሳርፍ። ከሁለት ቀናት በኋላ እመለሳለሁ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚኖርህን ቀጣይ ሚና እንጫወታለን። ኛ ድልን መቀዳጀት መጀመርህ ነው፣ ለዚህ ቃል ልገባልህ እችላለሁ። ስለስዊድኑ ተልዕኮህና ስለዛሬው ስብሰባ ለማንም ምንም መናገር እንደማይኖርብህ መግለፅ ያለብኝ አይመስለኝም።» ጨብጦት ወደስብሰባ ክፍሉ ተመለሰ።

ወደእየር ማረፊያው በመኪና እየተወሰደ ሳለ፣ ሔልደር የጊል የቅንጦት መኪናዋ በቆዳ የተለበጡ ወንበሮችና ሌሎች ጥቃቅን ዝርዝር ሁኔታዎቹን ይመረምር ጀመረ። መኪና ኖሮት ባያውቅም መኪኖችን ይወዳል። ወደላይፓኛ በእይሮፐላን ሲጓዝ፣ ለጥ ብሎ ተኛ።

ማሊቡ የደረሰው ከእኩለለሊት በኋላ ሲሆን፣ ትሪናን ለማግኘት በማሰብ በቀጥታ ወደክፍሉ አመራ። ውስጥ ገብቶ የትራስጌ መብራቱን በዳበሳ ሲፈልግ የእንሶላ ኗኗታ ተሰማው።

«የለም፣» አለች፣ «መብራት የለም።»

አልጋ ላይ ተቀመጠና በዳበሳ ይዞ ከንዶቹ መሀል አስገባትና አቀፋት፣ ሳትፈልግ የስቃይ ጣር አሰማች።

«ምንድን ነው?» አላት። «ምንድን ነው ችግሩ?»

«ውይ ፎን፣» አጉተመተመች። «በዚህ ፍጥነት ትመለሳለህ ብዬ አልጠበቅኩም። ቢያንስ ለሁለት ቀናት ያህል የምትመጣ አልመሰለኝም። አልጋህ ላይ መተኛት ፈልጌ ብቻ ነው የመጣሁት።»

ፊቷን ሲነካው ትንሽ ጨዝት አሰምታ ተፈናጠረች። «ምንድን ነው ችግሩ?» ጠየቃት።

«ምንድን ነው? መጥፎያለሁ ትሪና።» የመብራቱን ቁልፍ አገኘተ ተጫነውና አፍጥጠ ቀረ። የፊቷ አንድ ጎን ጠቁሯል፣ እንዳይታየው አዞረችበት።

«እንደዚህ ሆኜ እንድታየኝ ስላልፈለግኩ ነው፣» አለች በትከሻዋ ላይ ሌላ ቁስል አለ።

http://ethzare.wordpress.com

አንሶላውን ጨምድዶ ሳበው። «ውይ አምላኬ፣» አለ በድንጋጤ፣ «ምን ሆነሽ ነው?» ሰውነቷ ዘጉኗል፣ ገላዋን በእጆቿ ለመሸፈን ሞከረች።

«አዝናለሁ፣» አለችው። «ፍቅር ልንሰራ አንችልም። እፈልጋለሁ፣ ግን አልችልም። በጣም ተጎድቼያለሁ።»

«ምን ተፈጠረ?» ጠየቃት። «ማወቅ እፈልጋለሁ እሁኑ።»

«ማጆሮቭ ነው፣» አለች፣ «እና ሌሎቹ።»

«ምን?»

«ከሁለት ቀናት በፊት እንድ ግብጣ ነበር፣ እና የግድ ነይ አለኝ። ያስደስትሻል አለኝ። አንድ ጀኔራልና ሌሎች ሲቶች ነበሩ። ልገናኛቸው አልፈለግኩም። ደበደቡኝ። ከዚያ ማጆሮቭ. . . አስገደደኝ. . . ከኋላዬ. . . ከዚያ ሌሎቹም፣ ውይ ጆን፣ በጣም ይሰቀጥጣል፣» አለቀሰች፣ አቅፋው አለቀሰች። «መቼም የማያበቃ መስሎኝ ነበር።»

«ውይ ትሪና፣» አለ፣ በቀስታ እያቀፋት።

«ግብጣዎቹን እወዳቸው ነበር፣» አለች፣ ስርቅታዋን፣ ሳቅን ለመቆጣጠር እየጣረች። «ከዚያ እንተ ስትመጣ ነገሮች ተለወጡ። ከጊዜ በኋላ ማጆሮቭ እንድመጣ ማድረጉን ተው። ማለቴ እኔን ለእንተ ከሰጠኝ በኋላ ማለቴ ነው። ግን ከተልዕኮህ የማትመለስ አድርጎ ያሰበ ይመስለኛል። «እንደገና ታለቅስ ጀመር።» በጣም ነበር የፈራሁት። እንድ ጊዜ እንዲት ሴት ገድሏል። ይህን ሰምቼያለሁ።»

ሔልደር ፀጉሯን እያሻሸ ምን እንደተከሰተባት ሳለማሰብ እየሞከረ፣ በውስጡ እየጋመና እየተንተከተከ የሚሄደውን ንዴት ለመቆጣጠር ይጥራል። ታግሎ ከዚህ ሀሳብ ተሳቅቆ አትኩሮቱን ሁሉ ወደእሷ ለማዞር ሞከረ ግን አቃተው። ተልዕኮው፣ የደረጃ እድገቱ የቤተ መንግስት ስብሰባው ቦታ አጡ። ሀሊናው የሚያስበው ስለእሷ ስቃይና በእለቃው ስለተፈፀመበት ክህደት ሆነ፣ ይህ ሞራት።

እንቅልፍ እስኪወስዳት ድረስ አቀፋት፣ እሱ ግን ለብዙ ሰዓታት እንቅልፍ አጥቶ ቆየ።

31

አፒቼላ ገና አይኖቹን ማሊቡ ላይ እንዳሳረፈ ነበር የደስታና የፈንጠዚያ ስሜት ይወርረው የጀመረው። ከቪየና ወደሌኒንግራድ ያደረገው ቢረራ በጣም ደባሪ ነበር፣ ምክንያቱም የሁለተኛው አይሮፕላን መስታወቶች በጥቁር ቀለም ተሸፍነዋል። የት እንዳለ ባያውቅም መኪናዋ እንድን ኮረብታ ቁልቁል ወርዳ ከባህሩ በቀጭን የምድር አካል የተለያየ ሐይቅ ጋር ወደተቆራኘ ቦታ ስታመራ የባህሩ ውሀ ሊያብረቀርቅ ታይቶታል።

በከባዱ ጥበቃ የሚደረግለትን በር ካለፈ በኋላ አፒቼላ ያስገረመውን ሁኔታ የተሳበሰ ስፍራ ተመለከተ። ወደምዕራቡ ቢጣም ማራኪ በሆኑ ወጣት ሴቶች ታጅቦ የገባባበት ሀንፃ ላይ ሶስት ግዙፍ የሳተላይት ሳህን እንቴናዎች በመመልከቱ የበለጠ ተደነቀ። ሌሎች እጅግ ማራኪ ሴቶች ሞስኮ ውስጥ ለፊርሶቭ በሰራለት አይነት ኮምፒውተሮች የሚሰሩበትን ክፍል አልፈው፣ የእንግዳ መቀበያ ስፍራውን አቋርጠው መልኩ ወዳማረ ቢሮ ገቡ። ፊርሶቭ እጁን ዘርግቶ ከተቀመጠበት ጠረጴዛ ጀርባ ተነስቶ መጣ።

«ሌሚሊዬ! እንደምን ነህ? ስላገኘሁህ ደስ ብሎኛል።»

«ሮይ!» አለ አፒቼላ ሰላምታን ከሱ ባልተናነሰ ስሜት እየመለሰ።

«መጥተህ ተቀመጥ ብዙ የምነግርህ አለኝ፣» አለ ፊርሶቭ። ለሁለቱም መጠጥ ቀላቅሎ አዘጋጀና ከዚያም ከአሚሊዬ ጋር ሶፋው ላይ ተቀመጠ።» በመጀመሪያ ደረጃ፣ እዚህ የምታውቀው ሮይ በሚል ሳይሆን ቪክቶር ማጆሮቭ በሚል ስም ነው። በምክንያት አላደንቁርህ፣ ግን ይህንን ማስተካከያ ብታደርግ ደስ ይለኛል።»

«ምን ችግር አለ፣ ቪክቶር፣» አለ አፒቼላ። «ደግሞስ ሌኒንና ስታሊን ስም መቀያየር ከቻሉ እንተስ ብታደርገው ምን አለበት?»

ማጆሮቭ ከልቡ ሳቀ። «እሺ፣ አሁን ለምን በጣም እንደፈለግኩህ ልንገርህ።»

«እባክህን ንገረኝ። ከከፍያዎቼ አንፃር ወደስራዬ ለመግባት መዘግየትን አልፈልግም።»

«እዚህ ተመልከት፣» አለ ማጆሮቭ፣ ከፍሉን እቋርጦ ወደሚሄን የስብሰባ ጠረጴዛ እየጠቆመው።

አፒቼላ ወደዚያው ተመለከተ። ሩሲያዊው በደወለ ጊዜ እየቀለደ አልነበረም። የአይ ቢ ኤም ፒሲ ኤቲ (IBM PC AT) ኮምፒውተር አግኝቷል። «መልካም፣ ጥሩ ነገር ነው ቪክቶር፣» አለ። «እዚህ ነገሮች በቀላሉ አይገኙም፣ ከ IBM ድርጅት ውጪ አውሮፓ ውስጥ ያሉት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው።»

«በስልክ እንደነገርከኝ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ መሳሪያ ሰርተህል፣» አለ ማጆሮቭ፣ ትንሽ ተጨንቋል ብሎ አሰበ አፒቼላ።

«እንዴታ፣» ፈገግ አለ፣ «ከመካከላቸው እንዱ ላይ አውሮፓ ውስጥ ትንሽ የማሻሻያ ስራ ሰርቼያለሁ።»

«ስለዚህ መሳሪያ ምን ታስባለህ?» ጠየቀው ማጆሮቭ።

«በጣም ጥሩ መሳሪያ ነው - 512K) መረጃ ማከማቻ (Memory ያለው እስከ 2 MB (Megabyte) ድረስ የ1.2 Megabyte ተንቀሳቃሽ የመረጃ ማከማቻ (Floppy disk) መጉረስ የሚችል እና የ 20 MB ቋሚ የመረጃ ማከማቻ (Hard disk)ያለው። የተለመደውን ሶስት ቅርንጫፍ ጣቢያዎች ሳይሆን አስራ ሁለት ቅርንጫፎችን ማንቀሳቀስ እንዲችል አድርጌ አድሼዋለሁ።»

«እኔም የምፈልገው ይህንኑ ነው፣» አለ ማጆሮቭ በደስታ።» ባለፈው ዓመት አንተ ለዚህ መዋቅር ከሰራኸው CPMን መሠረት ያደረገ መሳሪያ፣ ወደዚህ መለወጥ እፈልጋለሁ። ያከማቸናቸውን መዛግብት በሙሉም ማዘዋወርም እፈልጋለሁ። ይህን ማድረግ ትችላለህ?»

«መቼም፣ ይገርው የመጣሁትን ተጠቅሜ መሳሪያውን በመለጠጥ ሊሥራ ሳደርሰው እችላለሁ። እንዳዘዋውራቸው የምትፈልጋቸው መዛግብት በሙሉ የተፃፉት በወርድስታር የቃላት ማቀናበሪያ (Word Star Word Processor) ፕሮግራም ነው?»

«እም።»

«ጥሩ፣ ስለዚህ ከተዘዋወሩ በኋላ ጥቅም ላይ ማዋሉ ችግር አያመጣም።»

«ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?»

«የመለዋወጫ ችግር የማይገጥመኝ ከሆነ ጥቂት ቀናት ብቻ ይበቃዋል። ግኩፈያውን ይገር መጥቼያለሁ፣ ግን ገና ተሰርቶ አላለቀም። የማንቀሳቀሻ

http://ethzare.wordpress.com

መዋቅሩ(Operating System) እና መመሪያው በእጅህ ይገኛል ብዬ እገምታለሁ::»

«አዎ:: ያሉንን ቅርንጫፎች ከAT ው ጋር መጠቀም እንችላለን?»

«አዎ፣ ችግር የለም:: የት ነው የምሰራው?»

ማጆሮቭ እየመራ በተጓዳኝ ወደሚገኝ የስብሰባ አዳራሽ ወሰደው:: «ይሄ እንዴት ነው?»

«ግሩም ነው:: የንድፍ መውጫ ጠረጴዛና ባለመብራት ማጉያ ሌንስ ያስፈልገኛል:: ATው ወደዚህ እንዲመጣ አድርግ እባክህን፣ ቅርንጫፍ ኮምፒውተሮቹም ወይ እዚህ መምጣት አለባቸው አለዚያም ሴቶቻችሁ እስክፈልጉበት ጊዜ ድረስ እንዲጠቀሙባቸው ከፈለግክ፣ አሁን ወደሚሰሩበት መእከላዊ የማቀናበሪያ እካሉ ገመድ መዘርጋት ይኖርብኛል::»

«በቃ ገመድ እንዘረጋለን፣» አለ ማጆሮቭ:: « በእሁኑ ጊዜ ሴቶቹ በሥራ ተወጥረዋል:: ስለሴቶች ስታነሳ፣ ዛሬ ምሽት አብራህ የምትሆን የምታስፈልግህ መስለኝ::»

«እንዴታ አምን፣» አለ በፈገግታ:: «እስኪ ንገረኝ፣ ያቺ ባለወርቅማ ፀጉሯ አሁንም አንተ ጋር አለች፣ ማን ነበር ስሟ፣ ትሪና?»

ማጆሮቭ ኮስተር አለ:: «አለች ግን ጤናዋ ጥሩ አይደለም:: ይዛህ የመጣችው ባለቀይ ፀጉሯስ ረጅም?»

«ቆንጆ ነች:: በጣም ትሆነኛለች::»

«ስለዚህ እንጀምር፣ በመንገዳችን ላይ እስጎበኘህለሁ::»

አፒቼላ ማጆሮቭን ተከትሎ ከህንፃው ከወጡ በኋላ በኢሌክትሪክ የሚሰራ የጎልፍ ጋሪ ላይ ወጡ:::

«ይህ ቦታ የስፖርተ መዓከል ነው፣ ብዙ የተለያዩ እትሌቶች የሚለማመኑበት ቦታ ነው፣» አለ ማጆሮቭ፣ ጋሪውን በኮረብታ ቁልቁለት እያሽከረከረ:: «ልትጠቀምባቸው ከፈለግህ ብዙ የተለያዩ የስፖርት ቁሳቁሶች አሉ፣ ግን እንደማስታውሰው የቤት ውስጥ ስፖርት ነው የመትወደው::»

«ልክ ነህ ወዳጄ፣» አለ አፒቼላ::

«እዚያ ታች አንድ ትንሽ የባህር ዳርቻ ይገኛል፣ ከሰው ሰራሹ የውሀ አካል ቀጥሎ፣ መዋኘት ከፈለግክ:: የባቲክ ባህር በዚህ ወቅት አስደሳች ነው::» ማጆሮቭ ከመንገዱ ባሻገር ዘብ በተጠንቀቅ ወደቆመበት በር አመለከተው:::»

ወደዚያ አትጣጫ እንዳትሔድ ሳስጠነቅቅህ እገደዳለሁ:: ያ ከክልሉ ውጪ ነው:: ዘቦቹም ቁጡ ናቸው::»

«እንዳልክ ይሁን:: የባህር ዳርቻው ግን አስደሳችና ማራኪ ይመስላል::»

ማጆሮቭ ጋሪውን በድንጋይ ንጣፉ መንገድ ላይ ሽቅብ ሲመራው፣ በዛፎች መካከል ተሰይታ የተሰራች ትንሽ መኖሪያ ቤት ዘንድ ደረሱ:: «ይህ ከእንግዶች ማረፊያ ቤቶቻችን መሀል አንዱ ነው፣ እንደሚደላህ እገምታለሁ::» አንድ ወረቀት አወጣ:: «በግቢው ውስጥ የምግብ ቤቶች አሉ::» ይህ የቦታው ካርታና የያዛቸው የግልጋሎት መስጫዎች ዝርዝር ነው:: ተገልለን ነው ያለነው፣ ስለዚህ ከዋና በር ውጪ በግለፍ ለመዝናናት ማሰብ ትርጉም የለውም ደግሞም ዘቦቹ ይለፍ ያልያዘን ማኛውንም ግለሰብ እያስወጡም:: አዚሁ ቦታ ላይ ብትቆይ የበለጠ ይቀልሀል::» መንገድ እየመራው ድሉት ወደሞላበት የቤቱ ማረፊያ ክፍል ይዞት ገባ፣ ኩሽናውንና ትልቅ አልጋ የያዘውን መኝታ ቤት አሳየው::

አፒቼላ የሆነ የሚንደቀደቅ የሞተር ድምፅ ተሰማው:: «ይሄ ድምፅ ምንድን ነው?» ጠየቀ::

«አሀ፣» አለ ማጆሮቭ በፈገግታ፣ «ይሄ የሚመጣው ከመታጠቢያ ክፍሉ ነው:: ሻንጣዎችህ እዚህ ናቸው:: የሥራ መሳሪያዎችህ በሥራ ክፍልህ እንዲቀመጡ አድርጌያለሁ:: ዛሬ ካንተ ጋር ራት የምበላ አይመስለኝም፣ ግን ብቻህን እትሆንም:: እንደውም፣ እዚህ እስካለህ ድረስ ብዙም እንገናኝም:: ለጊዜው በጣም ሥራ ይበዛብኛል::»

«ችግር የለም ቪክቶር ይገባኛል::»

«የምትፈልገው ነገረ ካለ ለአልጋ ንገራት:: እሷ ትነግረኛለች::»

«አልጋ?»

«ከመታጠቢያ ቤቱ የሚመጣው የሷ ድምፅ ነው፣» ብሎ ሳቀ ማጆሮቭ:: «መልካም ምሽት ነገ እንገናኝ ይሆናል::» ብሎ ከቤቱ ወጣ::

አፒቼላ በመኝታ ክፍሉ በኩል አድርጎ ወደመታጠቢያ ክፍሉ አመራ፣ ድምፁ ጨመረ:: በሩን ከፍቶ ወደውስጥ ተመለከተ:: ባለቀይ ፀጉሯ በትልቅ ገንዳ ውስጥ ተቀምጣ በፈገግታ ታየዋለች::

«ታዲያስ አልጋ፣» አለ አፒቼላ፣ ቁልፎቹን እየፈታ::

ሩል ልክ ስምንት ሰዓት ከመሆኑ በፊት ቢሮዋ ስትደርስ፣ በስምንት ሰዓት በሚደረገው የቢሮ ሀላፊዎች ስብሰባ ላይ እንድትገኝ የሚጠቅስ ማስታወሻ አገኘች:: እያለከለከች የአመራር መቀመጫ ቢሮ ፎቅ ላይ ደርሳ ስትገባ ዳይሬክተሩ ለመጀመር እየተዘጋጁ ስለነበር የሁሉም አይኖች ወደሷ ዞሩ:: በረጅም ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰብስበዋል:: ዳይሬክተሩ ጠረጴዛው መጨረሻ ላይ ቆመዋል:: በስተቀኙ ሳየመን ሩል፣ በስተግራው ደግሞ አላን ኒክሰን ተቀምጠዋል::

ዳይሬክተሩ፣ ፕሬዚዳቱ ስCIA ዳይሬክተርነት በዕጩነት ሳይጠቁመው በፊት ስኪታማ የቀረጥ ጠበቃ ሆኖ ዋሽንግተን ውስጥ ያገለግል ነበር:: ከዚህ በፊት ያለው የስለላ ልምድ በተወረረችው የፊረንሳይ ግዛት ላይ አንድ ተልዕኮ እንዲፈፀም ከአይሮፕላን በፓራሹት የተለቀቀ ጊዜ ነበር:: ይህን ታዲያ ዘወትር ያነሳዋል::

«አሁን ሁላችንም ስለተገኘን፣» አለ ሩልን እየተመለከተ፣ «ከሁላችሁም ጋር ትንሽ መጨዋወት እፈልጋለሁ:: እንደምታቁት፣ በነገው እለት ቴክኖሎጂያችንን ለማስፋት የሚረዳንን በጀት በመጠየቅ ርዕስ ዙሪያ በስለላ ኮሚቴው ሴኔት ፊት ተገኝቼ ቃሌን እሰጣለሁ:: የኮሚቴው ሊቀመንበር የምክር ቤት አባል ካር ደግሞ እኛ በቴክኖሎጂ የመጠቀማችንን ሀሳብ አጥብቀው ይቃወማሉ:: እንደማስበው የምክር ቤት አባሉ የሚፈልጉት ብቁ ሰላይዎችን አሰልጥነን እንድናወጣ እንጂ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ እንድንጠቀምና እኔ የCIA ዳይሬክተር ከሆንኩበት ጊዜ ጀምሮ ውጤታማነቱ የተረጋገጠውን የተሳሳተ መረጃ የመስጠት ተልዕኮዎችን የሚደግፉ አይመስለኝም:: በአለም ተወዳዳሪ የሌላችሁ የስለላ ስራዎች አቀናባሪዎች የሆናችሁት እናንተ፣ አንድ ሰው ከመስክ ስለላ ላይ ሆኖ በሆዱ እየተንቋቀቀ መረጃ ካልሰጣችሁ ሥራ የምትሰሩ

http://ethzare.wordpress.com

አይመስላቸውም:: እኔ ግን ይህ የማይረባ ሀሳብ መሆኑን ስለማስብ ይህንኑ በነገው እለት ላሳውቃችሁ እቅጂያለሁ::

«ከዚህም ሌላ በዚህ ጉዳይ ላይ የኔ አቀናባሪዎችና መርማሪዎች የሚያውቁት ነገር ያለመኖሩን ጨምሬ ልነግራቸው እቅጂያለሁ፣ ዛሬ የሰበሰብኳችሁ ለዚሁ ነው:: ነገ ጠዋት ጋዜጣ ሳነብ ከታመኑ የመረጃ ምንጮች ብሎ የተፃፈና ከCIA የአመራር አካላት መሀል የሀሳብ ልዩነት መፈጠሩን የሚናገር ፅሁፍ ማንበብ አልፈልግም:: በእውነቱ፣ ይህ ጉዳይ በትንሹም ቢሆን ወደ መገናኛ ብዙሀን እንዲደርስ አልሻም:: እኔ . . . »

ዳይሬክተሩ ንግግራቸውን ገታ አደረጉ:: የመአከላዊው የአሜሪካ ቢሮ የበላይ ኸርማ ፑል ተነስቶ ቆሟል:: ሩል ስለምታውቀው እንደተናደደ ገብቷታል:: «ሚስተር ዳይሬክተር፣» አለ ፑል በዝቅተኛ ድምፅ፣ «ስላቂሪጥኩህ ይቅርታ፣ ከስለላ የበላይ አመራር አካል አምልጦ የወጣውን አንድ ሚስጥር ልትጠቅስልኝ ትችላለህ?» ብሎ በቆመበት ቀረ:: ኸርማን ፑል ጡረታ ሊወጣ ነው፣ ስለዚህ እሱን በየትኛውም መንገድ የሚነካ ነገርን መቀበል አይፈልግም::

ዳይሬክተሩ ግራ ተጋቡ:: «አሁን፣ እ . . .» ወደ አለን ኒክሰን ዘንበል ሲል ኒክሰን ከንፈሩን ሳያንቃንቅ አንድ ነገር ነገረው:: «ፑል፣ አዎ:: እናንተ ምን ያህል ታማኝ እንደሆናችሁ አውቃለሁ፣ የበላይ አመራሩ ደህንነት የላላ ነው ለማለት ፈልጌ አይደለም::»

«አመሰግናለሁ ጌታዬ፣» ብሎ ፑል ተቀመጠ::

«ማለት የፈለግኩት፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ አቋምን እንድንይዝ እፈልጋለሁ ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ስላለኝ አቋም ተቃውሞ ካላችሁ አሁኑኑ ልስማው::» ዙሪያውን ተመለከተ:: «አለ?»

የተሰበሰቡት እርስ በእርስ እየተያዩ ፊታቸውን ከሱ መለሱ፣ ግን የተናገረ ሰው አልነበረም:: ሩል የመስክ ላይ ስላዮች እጥረት መኖሩን የሚያማርሩ ቢያንስ ሁለት የቢሮ ሃላፊዎች መኖራቸውን ታውቃለች፣ ግን ከዳይሬክተሩ ይህን መሰል የስልጣን ሪገጣ ይመጣል ብሎ የተዘጋጀ አልነበረም::

«በሉ እንጂ፣ እንስማው፣» አለ ዳይሬክተሩ፣ ከዝምታቸው ድል አድራጊነት እየሸተተው፣ «አንዳችሁ አሳሳቢ የመስክ ስለላ ሥራ እጥረት የተፈጠረበትን እንድ እንኳን ከስተት ትጠቅሱልኛላችሁ?» ጥርሱን ገጥሞ የጠረጴዛውን ዙሪያ ቃኘ:: «ጥሩ፣» አለ:: «ይህን ጠብቄዋለሁ . . . » ዝም አለ፣ አይኖቹ እየጠበቡ መጡ:: «ሚሲስ ሩል?»

ሩል ተነስታ መቆሟ ራሷም ገርሟታል፣ አሁን ግን መመለሻም የላት:: «እምን ጌታዬ፣ እኔ ልጠቅስልህ እችላለሁ፣ እንደውም ከሰላሳ ቀናት በታች በሆነ ጊዜ ውስጥ የተፈጠሩ ሁለት ከስተቶችን ልጠቅስልህ እችላለሁ:: በመጀመሪያው፣ አዲስ የሶቪየት ስፔትናዝ ማሰልጠኛ ነው ብዬ የገመትኩት በላቲቪያ የባህር ጠረፍ ላይ የሚገኝና በስፖርት ማዕከልነት ሽፋን የሚንቀሳቀስ ጦር ሰፈር የሳተላይ ምስሎች መጡ:: የባህር ሰርጓጅ ሰፈር ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክቱ መረጃዎችም አሉ:: እኔ ከተልዕኮዎች ክፍል የመስክ ስለላ ሀይል እንዲመደብልኝ ብጠይቅም፣ በዚያ ስፍራ ላይ ምንም አይነት ሰው እንደሌለን ሁላችንም እናውቀዋለን:: መረጃውን ውድቅ የሚያደርግ ወይ የሚያረጋግጥ አንድ የፅሑት ሰራተኛም ሆነ አትክልተኛ በቦታው የለንም::» ዳይሬክተሩ አይናቹን እያቁረጠረጠ እፍንጯው ተን እየተፋ ይመለከታታል:: «ከሁለተኛው

ክስተት ላይ ደግሞ ፣» ቀጠለች፣ ድምጿን ላለማስረገጥና ሀይለ ቃል ላለመናገር እየጣረች:: «የሳተላይት ምስሎች እንደሚያመለክቱት በስራ ላይ የሚገኙ ቢያንስ ሁለት ሚግ አይሮፕላኖች መኖራቸው ተረጋግጧል:: እኛ ግን እነዚህ አይሮፕላኖች ሊሰሩ አይችሉም የሚል እምነት ብንይዝም ግለት ነው:: ሥራው ለብዙ ዓመታት ሲካሄድ የቆየ ቢሆንም አይሮፕላኖቹ ስራቸው ተጠናቅቆ መብረር እስከጀመሩ ድረስ የቴክኒክ መሳሪያዎቻችን ምንም አይነት መረጃ አላቀበሉንም:: ሶቪየቶች እነዚህን መሰል አይሮፕላኖቻቸው ቁጥር ብዛት ሁለት ይሁን መቶ በውል አናውቅም::» ተቀመጠች::

ዳይሬክተሩ እንዳፈጠጠባት ቀረ:: ሳይመንም አፍጥጦባታል:: አላን ኒክሰን መነፅሩን አውልቆ የአፍንጫውን ጠርዝ ያሻሸል፣ አይኖቹ ተከድነዋል::

«ይሽው ነው፣» አለና ዳይሬክተሩ ድንገት ፊቱን አጥቁሮ ወጥቶ ሔደ::

ሰብሰባው እንዳበቃ የተረዱት ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ነበር:: በመጨረሻ፣ አባላቱ በዝምታ መውጣት ጀመሩ:: ሩልም ከወንበሯ ተነስታ ወደበሩ አመራች::

«ካትሪን፣» ሲል ሳይመን ከኋላዋ ተጣራ::

ዞረች::

«እባክሽን ትንሽ ቆዪ::»

ተመልሳ ተቀመጠች:: ሳይመንና አለን ኒክሰን በጠረጴዛው ተቃራኒ አቅጣጫዎች ከተቀመጡበት አልተነሱም:: ሳይመን ፊቱን ወደኒክሰን አዞረ::

«አለን፣ ሰራተኛህን ያስፈቃድ ልደርስባት ፈልጌ አይደለም፣ግን ከካትሪን ጋር ለአፍታ እንድቆይ ፍቀድልኝ::»

«ችግር የለም ሳይመን::» ብሎ ኒክሰን ከክፍሉ ወጣ::

ሳይመን ለአፍታ ያህል በዝምታ ሲመለከታት ቆየ:: እርጅና ጀምሮታል ብላ አሰበች:: ቢጫ ፀጉሩ ላይ አሁን ሽበት እየጣለበት ነው፣ አንገሩም ከስር በኩል ትርፍ ስጋ እያወጣ ነው፣ ግን መልከመልካምነቱና ግርማ ሞገሱ አሁንም አልተለዩትም::

«ፒተር እንዴት ነው?» ፀጥታውን አደፈረሰችው::

«በጣም ደህና ነው አመሰግናለሁ:: ኮሚስቴ ጋር ግሩም ወዳጅነትን ፈጥረዋል::» ለሌላ ቅፅበት ዝም ብሎ ቆየ:: «ካትሪን ከድርጅቱ በፈቃድሽ መልቀቅ ያለብሽ ይመስለኛል::» ድምፁ አንድ አይነተ ለዛ ያለውና ስሜት የማይነበብበት ነበር እና፣ ሁኔታውን የአልሀና የጭካኔ አስመሰለበት::

ተደናገጠች:: «ይህን የማለት ምንም መብት የለህም፣» አለች የኋላ ኋላ::

«ከሥራ ጋር በተገናኘ እንጂ እኔና እንቺን ከሚመለከት ሁኔታ አንፃር አልተናገርኩትም፣» አለ:: «ለዚህ ሰራ ብቁ ነሽ ብዬ አላስብም::»

«ምን?»

«ያለመረጋጋት ምልክቶችን ማሳየት ጀምረሻል፣ ድርጅቱ በአባላቱ ላይ የሚታዩ ያለመረጋጋት አዝማሚያዎችን ችሎ ማሳላፍ እንደማይችል እንቺም ሆንሽ እኔ እናውቃለን::»

«ውይ? ታዲያ ይህ ያለመረጋጋቴ በምን ዓይነት ሁኔታ ታይቶብኛል?»

http://ethzare.wordpress.com

ራሱን ዘና ለማድረግ ይመስል እጆቹን በመዳፋቸው ገልብጦ ጠረጴዛው ላይ አኖራቸው፣ አነጋገሩ አልተለወጠም። «መሰረት የሌላቸው መላምቶችን እያመጣሽ·ነው። አልታዘዝም እያልሽ ነው።»

«ጊዜውና ኃይሉን ካገኘሁ መላምቶቼን በመረጀ እደግፋቸዋለሁ፣ ግን ጊዜና ኃይል ማግኘት አልቻልኩም፣» አለች በጋለ እንደበት። «አልታዘዝም ትላለች ብለህ ያሰብከው አሁን ገና ነው? ጥያቄ ጠየቀ፣ የማውቀውን ያህል አከብሮት አክቤበት መልስ ሰጠሁ። ሀሳችንንም እዚህ ሰብስቦ፣ ጥቂት የማይባሉ የቢሮ ሃላፊዎች ተቃውሞ ያላቸውን አንድ አቋም እንድንቀበለው ሊያስገድደን የሚችል ይመስለዋል? ይህን ማድረጉ ምክንያታዊ ይመስልሀል?»

«ጥያቄው የዳይሬክተሩ የምክንያታዊነት ብቃት አይደለም፣» ሲል መለሰ ሳይመን የድምፁ ቃና ሳይቀየር። ሀመምተኛውን የሚያናግር የሥነልቦና ሐኪም አስመስሎታል። «ጥያቄው ያንቺ ነው። ጥያቄው የአንቺ ባህሪ ነው።»

«የኔ ባህሪይ? ምን ዓይነት ባህሪይ?»

«ከትናንት ወዲያ፣ ያለፈቃድ ከሀገር ወጣሽ። ይህ እንደምታውቂው፣ የድርጅቱን ህግ መጣስ ነው።»

መሆኑን ታውቃለች። ከዚህ ከፍል መውጣት ፈለገች። «ሳይመን ከመስመር በጣም ወጥተሀል። የምሠራው ለአንተ አይደለም፣ ስለዚህ ስለባህሪዬ የመጠየቅ ምንም መብት የለህም፣ ያለመረጋጋቴን ማንሳትህ ይቅርና። እኔ የድርጅቱ ታማኝ፣ ጠንካራ አገልጋይና ከፍተኛ የውጤታማነት ክብረወሰን ያለኝ ሠራተኛ ነኝ።» ተነስታ ቆመች። «በእኔ ላይ የምታቀርባቸው ክሶች ካሉህ በግምገማ ቦርዱ ፊት ይዘህቸው ተገኝ። ፖለቲከኛ ላልሆን እችላለሁ፣ግን ጠበቃ ነኝ ራሴን እንዴት መካላከል እንዳለብኝ አውቃለሁ።» ወደበሩ አመራችና ፈጀን አዞረች። «አንድ ነገር ንገረኝ እስኪ ሳይመን» አለች። «ሰንፍላወር ምንድን ነው?»

በጥቂቱ ፈቱ የቀላ መሰላት። «እንዚህን መሰል ጥያቄዎች መጠየቅ እንደሌለብሽ ታውቂያለሽ?»

«ድርጅቱ ሊሰጠው የሚችለው የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ መብት አለኝ።» አለችው። «ሰን ፍላወር ምንድን ነው?»

በሳይመን ቅንድቦች መሀል ሁለት ቀጭን መስመሮች ተጋደሙ። «ማወቅ አያስፈልግሽም፣» አላት።

«እሺ፣ ማወቄ አይቀርም፣» ብላ ወደበሩ ማምራት ጀመረች።

«ካትሪን!» ከኋላዋ ተጣራ ::

ቆመች።

«የራስሽን መቃብር እየቆፈርሽ ነው። ስራሽን ለመቀጠል የሚያስችል ትንሽ ክብር በቀረሽ በአሁኑ ጊዜ ብትወጪ መልካም ነው። ለልጅሽ ያን ያህል ውለታ ዋይለት::»

ከክፍሉ ወጥታ በሩን ከኋላዋ ደረገመችው። ባቀጣ እየጎደደችና መተንፈስ እያቃታት ወደቢሮዋ ተመልሳ በሩን ዘግታ ኮምፒውተሯ ፊት ተቀመጠች። ኮስሞ ህይወት ዘርቶ መንቀሳቀስ ሲጀምር፣ ኤድ ራውልስ የሰጣትን የሳይመንን ባለአስር ፊደል /ቁጥር/ ኮድ ፃፈችለው።

እንደምን አደርክ ሚስተር ሳይመን። ምን ላድርግልህ?

ሰንፍላወር ብላ ፃፈችለት።

በፍለጋ ላይ።

የኮምፒውተሩ ስክሪን ላይ አፍጥጣ ትዕግስት አጥታ ጠበቀችው።

ሰንፍላወር፣ ሶቪየቶች ምንም በማያስጋቸው በምስራቅ ባልቲክ ግዛት ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር ሰራዊትና ቁሳቁስ እንዲያስገቡ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ የተሳሳተ መረጃን የማቀበል ተልዕኮ ነው። ይህ ሁኔታ ተፈላጊውን ውጤት ካመጣ ወደዚያ የሚላከው ሰራዊት የሚቀንሰው ከምስራቅ አውሮፓ ጦር ላይ፣ በተለይም ከምስራቅ ጀርመን የድንበር ክልል ላይ በመሆኑ፣ ማንኛውም ዓይነት ግጭት በዚያ ስፍራ ከተፈጠረ በምዕራብ በኩል ምንም ዓይነት ጥቃትን የመሰንዘር አቅማቸውን ይቀንሰዋል። የሚላከው የተሳሳተ መረጃ፣ እስከዛሬ ድረስ በቆራጥነት ጎራ ሳትያዝ ብቻዋን ሆና የኖረችው ስዊድንን፣ የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት በሚስጥር ለመቀላቀል ዝግጅት እያደረገች ነው፣ የሚል ነው።»

ሙሉውን ፋይል መመልከት ይፈልጋሉ?»

ሩል ማጠቃለያ ሀሳቡን ጸግመኛ እያነበበች፣ የኮምፒውተሩን ስክሪን አፏን ከፍታ ትመከታለች። «የክርስቶስ ያለህ።» አለች ሮክ ብላ። ሁሉ ነገር አእምሮዋ ውስጥ ቦተታቦታውን ይዞ እየተገጣጠመ ነው። እዎ በማለት ለኮምፒውተሩ ምላሽ ሰጠችው።

ለሚታተም ነው፣ ለስክሪን?

ማተሚያ ማሽኑን እስኪስታ «ለሚታተም» በማለት መለሰችለት። ማተሚያው እፈትና ኋላ እየተመላለሰ መፃፉን ሲቀጥል፣ አሷ በግርምት ከመሽበሷ የተነሳ ተቀምጣ ከስክሪኑ ላይ ማንበቡን ተያይዛዋለች። ቂሎች ስትል አሰበች። ጽሑፉ በኮምፒውተሩ መስኮት ላስክሪን ሽቅብ እየወጣ ይሰወራል። የተረገሙ ቂሎች።

33

አፒቼላ ባለመብራቱን ማጉያ ሌንስ አተኩሮ እየተመለከተ በኮምፒውተሩ ሰርኪውት ቦርድ ላይ አንድ ማይክሮቺፕ በጥንቃቄ በየደ። ማሊቡ የሚሉት ስፍራ ከመጣ ሶስት ቀን ሆኖታል። እዚህ በተመለከተው ሁሉ ተገርሟል ተደንቋል። ባለፉት አስራአምስት ዓመታት ውስጥ ለውጭ ንግድ ድርጅቱ እየተዋዋለ ወደሶቪየት ህብረት ከስልሳ ጊዜ በላይ ተመላልሷል። ለዚህም ፋብሪካዎችን፣ ሙከራ ቤቶችን፣ መኖሪያ ቤቶችን እና በከፍተኛ ደረጃ ህይወትን የሚኖሩ ሩሰያውያንን የቅንጦት ቪላዎች የማጀሮቨን ጨምሮ ለመጎብኘት ችሏል። ዳሩ ግን በማሊቡ ላይ ወጪ ወጥቶባቸው እንደተመለከታቸው ዓይነት ነገሮች በህይወቱ ተጥሞት አያውቅም።

በምዕራባውያን ቁሳቁስ ከተሞሉት ምግብ ቤቶችና ሞደብሮች በተጓጓኘ፣ ይህ ቦታ ሶቪየቶች እጃቸውን ሊያሳርፉበት የሚችሉትን የቴክኖሎጂ ውጤት በሙሉ የያዘ ነው። ከመሳሪያዎቹ መካከልም የሱም ብሎ ያስባቸው የአቡሩ ይገኙበታል። ፊርሶቭ ወይንም ማጀሮቭ ደውሉለት፣ አሜሪካ ውስጥ እንኳን በበቂ ሁኔታ የማይገኝ አዲስ የአሜሪካን ኮምፒውተር ማግኘቱን ሊነግረው አልተገረመም። ማጀሮቭ በተለይም ቴክኖሎጂ ነክ የሆነን

http://ethzare.wordpress.com

ማኛንውንም ነገር ለማግኘት እንደማይቸግረው ካለፈ ልምዱ ያውቃል። በጣም ያስገረመው ግን ማሊቡ ውስጥ በአሜሪካው ዌስተርን ኤሌክትሪክ የተሰራ እጅግ ዘመናዊ የስልክ መስመር መኖሩ ነው። ይህ መስመር ማጆሮቭ በራሱ የሳተላይት ጣቢያ ተጠቅሞ በአለም ላይ የፈለገበት ቦታ ሁሉ ጥሪዎችን ማድረግና መቀበል ያስችለዋል። ሶቪየቶቹ ከብዙ ዓመታት በፊት፣ ጥቂት ሙከራዎችን ካደረጉ በኋላ በግል ከሀገር ውጭ የሚደረጉ የስልክ ጥሪዎችን ከልክለዋል። በዚህ በንፅፅር ሲታይ እንስተኛ ሊባል በሚችል ስፍራ ውስጥ የተዘረጉት መሳሪያዎች እንደ ትልቅ ከተማ ማገልገል የሚችሉ ናቸው። የሳተላይት ቴሌቭዥን መቀበያውም አስደንቆታል፣ ያስደነቀው ግን የተመለከተበት የቴክኖሎጂ ውጤት ሳይሆን የሚያስተላልፈው ያልተጣሩ አሜሪካዊ ፊልሞችና ዜናዎች መሆኑ ነበር። በሶቪየት ህብረት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ኃይል ያለው ሰው ብቻ ነው ይህን መሰል ልዩ መብት ማግኘት የሚችለው።

ማሊቡ ላይ የተመለከተው ነገር አፒቼላን እንድ ነገር አረጋግጦለታል። ማጆሮቭ የKGB አባል መሆኑን፣ ይህ ደግሞ አስፈርቶታል። ለውቢቶ አሜሪካዊት ሴት ስለጉብኘቱ መረጃን ሊልክላት ቃል ቢገባላትም፣ የማወቅ ጉጉቱን የተወጣው ግን በራሱ ብቻ ነው። አፒቼላ ግን ይህን መረጃ ፍለጋ አጥር የመዝለልና በቀጻጻ የመመልከት ሀሳብ የለውም። ወኔና ድፍረቱን የሚጠቀመው ከሴቶች ጋር ላለው ግንኙነት ብቻ ነው። ጻሩ ግን ይህ ማጆሮቭና ዕፁብ ድንቅ የ «ስፖርት መዓከሉ» በኮምፒውተሮቹ የመረጃ ማከማቻ ውስጥ ተቀርፆ እንደሚቀመጥ አፒቼላ ጠንቅቆ ያውቃል፣ ምክንያቱም ኮምፒውተሮቹን ሲሰርቅና አሰራራቸውንም ሲመራመርበት ቆይቷልና።

ብየጻውን እጠናቆ የኤሌክትሪክ መስመሮች ሰሌጻውን (Xircuit Board) በተገቢው የኮምፒውተሩ አካል ላይ አገናኘው። ኮምፒውተሩን አስነስቶ INSTALL የሚለውን ቃል መታ። ተፈላጊውን ፕሮግራም የሚጭነው ሌላ ፕሮግራም የኮምፒውተሩን አካላት እየመረመረ በትክክል መስራታቸውን በማረጋገጥ ሪፖርት ሲያደርግለት በእርካታ መመልከት ጀመረ። ይህ ሲጠ ናቀቅ፣ በተለይ ያዘጋጀውን ብዙ ተገልጋይዎችን በአንድ ጊዜ ለማስተናገድ የሚያስችል የራሱን ልዩ ፕሮግራም ከጫነበት በኋላ በሁለቱ የኮምፒውተር ቅርንጫፎች እየተመላለሰ፣ ከመዓከላዊው ኮምፒውተር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሲፈትሽ ቆየ። ሁሉ ነገር ተስተካክሏል። ይህ ተዓምር የተሰራው በኤሚሊዮ አፒቼላ በራሱ ነው፣ አይደለም እንዴ?

አሁን ደግሞ በጉጉት ሲጠብቀው የቆየው ጊዜ ደረሰ። ከቀድሞ የኮምፒውተር መዋቅር ተነስተው፣ ወደ IBM ስራቱ የሚገናኙትን ገመዶች በታቸው ከሰካ በኋላ የግንኙነት ሶፍትዌሩን የያዘውን ተንቀሳቃሽ የመረጃ ማከማቻ /ፍሎፒ ዲስክ/ ወደ IBM ኮምፒውተሩ አሳረሰና የተወሰኑ መመሪያዎችን ፃፈ። የቀድሞውን ኮምፒውተር የአሰራር መዋቅር እንዳገኘ TREE የሚለውን ቃል መታ። ከመቅጽበትም የመረጃ ዶሴዎችን የያዙ ዋና ዋና የፋይል ማከማቻዎች (Directors) በኮምፒውተሩ መስኮት ሽቅብ መውጣት ጀመሩ። አሁን ከሌላ ቦታ ሆኖ የማጆሮቭን የኮምፒውተር መረጃ ከሁለት ከፍሎች ርቀት ላይ ሆኖ እየተቆጣጠረ መሆኑ ነው። በድንገት፣ የሚጠቀለለው ጽሑፍ ቀጥ አለ። ጠርነት የሚል አንድ ንዑስ የዶሴ ማከማቻ ተመለከተ።

ጦርነት? ተመሳሳይ ቃል ወይንም ምህረ ቃል መሆን አለበት። ቢሆንም ግን ከዚህ ጻይሬክተሪ የሚገኝጠሉትን ቅርንጫፍ ማከማቻዎች ተመለከተ። የባህርና የምድር፣ የአየር፣ ስንቅና ትጥቅ፣ መከላከያ፣ አይሮፕላ የሚሉ ሆነው አገኛቸው። ክለሳ የሚለውን ፋይል ከፈተው። ከዚያም ከፊት ለፊቱ፣ በእንግሊዝኛ የሚከተለውን ጽሑፍ አነበበ፣

ሰዊድንን ለመውረር የተቀመጡ እቅዶች ክለሳ

አፒቼላ ቶሎ ብሎ ከዶሴው የተወሰኑ ገፆችን ገለፀለት። በአግራሞት ተውጧል። ይህ እውን ሊሆን ይችል ይሆን? በፍጥነት ከተንቀሳቃሽ መረጃ መያዣ ማጉረሻው ውስጥ የግንኙነት መረጃ መያዣውን አውጥቶ ሲያበቃ፣ ኮምፒውተሩ ክለሳ የተሰኘውን ዶሴ እንዲቀጻው አዘዘው።

«እንዴት እየሆነልህ ነው?» የማጆሮቭ ድምጽ ከበስተኋላው ጆሮው ስር አስተጋባበት።

አፒቼላ በድንጋጤ ዘለለ። ማጆሮቭ ከአጠገቡ ካለው ክፍል ወጥቶ አሁን በትከሻው አሻግሮ እየተመለከተ ነው። «ልክ ሁሉን ነገር ሰርቼ ስጨርስ መጣህ፣» አለው እና ቶሎ ብሎ ኮምፒውተሩ ላይ ሌሎች መመሪያዎችን ፃፈ። «ከቀድሞው ባለ አስር ሜጋ ባይት ቋሚ የመረጃ ማከማቻህ ላይ መረጃዎችን ለመቅጻት ዝግጁ ሆኛለሁ። ተመልከት።» ብሎ ተዝዉን መመሪያ ፃፈ። ይጠ ብቁ። የሚል መልስ መጣለት። «ይኸው፣» አለ አፒቼላ፣ «አሁን እየቀጻ ነው።»

«መረጃ ማከማቻህ ላይ ምን ያህል መረጃ እንዳለ አላውቅም ብዙ ከሆኑ የተወሰኑ ሰዓታት ሊወስድ ይችላል። መረጃ የሚያስተላልፈው ግን በ1600 ባውድ (baud) ፍጥነት ነው። ፈጣን ነው።» ብሎ አፒቼላ ፀጉሩን ወደኋላ ላገው። «እሺ፣ ስራውን እንዲሰራ መሳሪያውን ትተነው ከመሔድ ሌላ ምንም የምናደርገው የለም። ለዛሬው ይኸው ይበቃል።»

«ወደቢሮዬ እንሒድ፣» አለ ማጆሮቭ፣ «የመጠጥ እግዛህለሁ።»

«ትንሽ ብቀምስ ደስ ይለኛል፣» አለ አፒቼላ እየተከተለው። በቀጣዩ ክፍል ገብቶ ሶፋው ላይ ተቀመጠ። ማጆሮቭ የመጠጥ ብርጭቆዎችና በቆርቆሮ ሳጥን የታሸጉ ሲጋራዎችን ይዞ መጣ።

«ይህ ስራህ የደስ ደስ ያስፈልገዋል፣ ያውም በዚህ ፍጥነት፣» አለ ማጆሮቭ።

አፒቼላ ትከሻውን ሰበቀና። «የሚያደክም ነገር አልነበረም፣» አለ፣ «ቀድሜ የሥራውን ብዙውን ክፍል አጠናቅቄዋለሁ። በርግጥ ወደትክለኛው ሰው ነው የመጣኸው።»

ማጆሮቭ ፈገግ ብሎ ፅዋውን አነሳ። «ለዚህ እንጠጣ፣» አለ። «የተለመደ ግሩም ስራህን ሰርተህል።»

«አመሰግናለሁ ቪክቶር። በስልክ መስመሮቹ በኩል መረጃን መላክ የሚያስችል አዲስ የውስጥ ለውስጥ ሞደም /የመረጃ ኮድ መቀርጎሚያ/ ገጥሚያለሁ። የቀድሞው የሚሰራው በ300 ባውድ ፍጥነት ብቻ ነበር። አዲሱ በ300፣ በ1200 ወይንም በ2400 ባውድ ፍጥነት መስራት ይችላል። መረጃዎችህን ሰው እንዳይደርስባቸው ከፈለግክም የራስህን የይለፍ ኮድ ልትጠ ቀም ትችላለህ።»

«ይህ ግሩም ነገር ይመስላል ኤሚሊዬ። ደህንነቱ እጅግ የተረጋገጠ ይሆናል?»

http://ethzare.wordpress.com

«እንዴታ። ጥቂት ቁልፎችን ብቻ ተጭነህ የይለፍ ኮዱን በፈለግክ ጊዜ ሁሉ ለመለወጥ ትችላለህ። እኔ እራሴ እንኳን ከሌላ ቦታ ሆኜ ልከፍተው አልችልም። ለፀሐፊህ እንዴት እንደሚሰራ አሳያታለሁ፣ ነገ ጠዋት ደግሞ ሰሌሎቹ ሴቶችህ ለሁለት ሰዓታት ያህል ትምህርት እሰጣቸዋለሁ። አሁን የሚጠቀሙት በወርድ ስታር ስለሚሆን እንዴት እንደሚከፍቱና እንደሚዘጉት ካልሆነ በስተቀር ብዙም የሚማሩት አዲስ ነገር አይኖርም። እንተ መጓጓዣ የምታዘጋጅልኝ ከሆነ እስከ ምሣ ሰዓት ድረስ እሔዳለሁ።»

ማጆሮቭ ለአፍታ ያህል ጣሊያናዊውን ትከ ብሎ ከመመልከት ውጪ ምንም ነገር ሳይናገር ቆየ። ከዚያም ለስለስ ባለ እንደበት፣ «ኤሚሊዪ፣ ምናልባት ችግር ካለ እንድታስተካክል የተወሰኑ ቀናት እንድትቆይ እፈልጋለሁ።»

«ምንም ችግር አይኖርም፣» ሲል አፒቼላ አቤቱታውን አሰማ። «ሁሉም ነገር ሙሉ ለሙሉ ፍተሻ ተደርጎለታል። እንደነገርኩህ አምጥቼ መግጠም ብቻ ነበር። ያም ሆነ ይህ ሮም ውስጥ ብዙ ሥራ ይጠብቀኛል፣ ስለዚህ መመለስ አለብኝ።» ፈገግ አለ። «ሰውቡን ኤሚሊዪ አፒቼላን ዘወትር የራስህ አድርገህ የማቆየት ፍላጎት ሊኖርህ አይችልም።»

ማጆሮቭ ፈገግ አለ። ድምፁ ግን አሁንም ለስላሳ ነው። «ነገ መሔድ የምትችል አይመስለኝም።» አለ። «ያለንበት ስፍራ ከሰው ተገልሎ የሚገኝ በመሆኑ፣ በጀት ጠብቆ የሚነሳ የአየር አገልግሎት የለንም። ከሌሎች ስራዎቻቸው የተነሳ አደርፐላን እጥረት አለብን፣ ከሌኒንግራድ ወደዚህ ያመጣህ አይሮፕላንም አሁን አይገኝም።»

አፒቼላ አንድ የተለየ ቅዝቃዜ ወረረው። «ገባኝ፣» አለ።

«አታስብ፣ እያዝናናንህ እናቆይሃለን፣ አለታዊ ክፍያህንም እናስብልሀለን፣ ምክንያቱም እዚህ ለመቆየት የተገደድከው በራሳችን ጥፋት ነው። ከዚህ በላይ ልናደርግልህ እንወዳለን።»

«አመሰግናለሁ። ይህ ግን የተወሰኑ ችግሮችን ያመጣብኛል። ከዚህ ሆኜ ቢሮዬ መደወል እችላለሁ? ዘንይቼ እንደምመለስ ማወቅ ይኖርባቸዋል።»

«እንዴታ። እንተ ብቻ ኦፐሬተሯ አለም አቀፍ መስመር እንድትሰጥህ ጠይቃት ከዚያም 0101 ደውል በመቀጠል የህገርህን ኮድ ከዚያም የሮምን ኮድ በመቀጠል የራስህን ቁጥር ደውል።»

«ጥሩ።» ብሎ ቮድካውን ጨለጠና ተነሳ። «መልካም፣ የተወሰኑ ነገሮችን ማስተካከል ይኖርብኛል፣ ሽማዬዋ አልጋ ከዚህ በላይ ስትጠብቀኝ እንድትቆይ ማድረግ አልፈልግም።» ትራንስፖርት እንደተገኘ ቶሎ ትነግረኛለህ አይደለም?»

ማጆሮቭ አብሮት ቆመ። «እነግርሀለሁ አንጂ። አትጨነቅ ከጥቂት ቀናት በላይ አይፈጅም።»

አፒቼላ ይቅርታ ጠይቆ ከማጆሮቭ ቢሮ ወጣ። ወደሥራ ክፍሉ ተመለሰና፣ በሩን ዘግቶ ስፍራውን መልክ ማስያዝ ጀመረ። የክለላ ዶሴውን የያዘውን የመረጃ ማከማቻ እውጥቶ፣ ዲስኩን ለሁል ጊዜ ሽፍኖ የሚይዘውን የፐላስቲክ ሽፋን በትንሽ ሰንጢ ፈለቀቀና ስስ ዲስኩን እውጥቶ የሚደብቅበት ቦታ ፍለጋ ጀመረ። አይኖቹ የኮምፒውተሩን ድብቅ ስፍራዎች ለመመልከት የሚጠቀምበት ቀጭን ባትሪ ላይ አረፉ። ከዳኑን ከፍቶ የባትሪ ድንጋዮቹን

አወጣቸው። ከዚያም የፐላስቲክ ዲስኩን ጥብቅ አድርጎ ባትሪ ድንጋዮቹ ላይ ከጠቀለለ በኋላ መልሶ ከተታቸው። ቦታው ቢጠባቸውም ማብሪያ ማጥፊያውን ሲነካው ይሰራል። ባትሪውን የጃኬቱ የውስጥ ኪስ ውስጥ ከከተተ በኋላ ብልጠቱን አደነቀ።

ከህንፃው በመውጣት የኮረብታውን ጥግ ይዞ ወደማረፊያ ቤቱ አመራ። ባለፉት ሁለት ቀናት ጊዜው የበለጠ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሚያስተውል መስሎ ተሰማው። ከብዙ ወጣቶች የተደራጀ ሰራዊት በአጠገቡ በሰምሶማ ወደጂምናዚየሙ አለፉ። አፒቼላ ፍርሀት ወረረው። ይህን ስፍራ የሚቆጣጠር አንድ ሰው በፈለገው ጊዜ አንድ አይሮፕላን ማስመጣት ያትተዋል ብሎ ማመን ተሳነው። ቤቱ ሲደርስ ሰልኩን አንስቶ የውጭ መስመር እንዲሰጠው ጠየቀ። የመደወያ ድምፅ ሲሰማ የሮሙን የስራ ቦታውን ቁጥር ደወለ። ጸሐፊው አነሳች።

«ሀሎ እንጀሊካ? አፒቼላ ነኝ።» ሀዘን ባጠላበት አንደበት፣ ከሚስተር ፊርሶቭ ጋር ለተወሰኑ ተጨማሪ ቀናት ለመቆየት ሳልገደድ አልቀረሁም። እንደእውነቱ ከሆነ በአሁኑ ጊዜ የትራንስፖርት እጥረት አለ። ገባሽ?»

«ገባኝ ሚስተር አፒቼላ። ከነገወዲያ ያለህን የፀጉር ቤት ቀጠሮ እሰርዘዋለሁ፣ ከወጣቷ ሴት ወይዘሪት ጋር ያለህን የምሳ ቀጠሮም እንደዚያው።»

«አዎን አዎ። ባለፈው ሳምንት አብራኝ ምሳ የበላችውን ሴት አስታወሻት?»

«እሜሪካዊት. . . »

«አዎን፣ እሷ። እባክሽን ደውይላትና እዚህ ለመቆየት ስለተገደድኩ ቀጠሯችን ላይ መገኘት እንደማልችል ንገሪያት። ግን በቻልኩ ጊዜ እደውልላታለሁ። እስከሳምንቱ መጨረሻ ድረስ የሆነ መልዕክት ካልደረሳት ቀጠሯችንን እንድተወውና፣ ግን እባክሽን እኔን ግን እንዳትረሳኝ ንገሪልኝ። ልክ አንዳልኩሽ ብለሽ ንገሪያት፣ እሺ?»

«አዎ፣ ሚስተር አፒቼላ። ላደርግልህ የምችለው ሌላ ነገር አለ?»

እየተደረገ ያለውን ሊገልፅ የሚችል መልዕክት ለመተው አስበ፣ ግን አልቻለም። «የለም፣ ይሄው ነው፣ ግን ለወጣቷ አሁኑኑ ደውይላት። በጣም ቅር እንደምትሰኝ አውቃለሁ።»

ስልኩን ዘግቶ በረጅሙ ተነፈሰ። በአሁኑ ወቅት እስረኛ ለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለውም፣ ካትሪን ሩል መልዕክቱ ሲደርሳት ልታደርግ የምትችለው ሊታየው አልቻለም። ብቸኝነትና ፍርሀት ነገሰበት።

34

ዊል ሊ ጀልባዋ ጋቢና ውስጥ ራሱን ትራስ አስደግፎ ቀዝቃዛ ቢራ ይጎነጫል። ፀሐፊዋ ፊቱን ታሞቀዋለች፣ ነፋሻማው አየር መልሶ ያቀዘቅዘዋል። ይህን ያህል ርካታና ደስታ ተሰምቶት የማያውቅ መሠለው። ከወደቡ ያገኘው ልጅ ማለትም ላርስን ጋር ሆነው ጀልባዋን በመዝናናት መንፈስ በፈንላንድ የባህር ድንበር ጥግ ጥግ እየነዱ የአገንድ የደሴቶች አጀብን አቋርጠው የፊለንበት እየቆሙና በየደሴቶቹ መዝናኛዎች እየተደሰቱ ቆይተዋል። ልጁ

http://ethzare.wordpress.com

ምንም እንኳን እንግሊዝኛ ቢያጥረውም ቅሉ አብሮት መሆኑ አስደስቶታል። ጀልባዋን አብረው እየመሩና ለአዲስ ጀልባ መደረግ ያለባቸውን ጥገናዎች ሁሉ እያደረጉ እዚህ ደርሰዋል። በአሁኑ ወቅት ሊ የዋናውን ሸራ መወጠሪያ የታችኛውን መሽከርከሪያ በዘይት ማራስ እንዳለበት ቢያስብም ፀሐይዋ ግን በጣም ስላስደሰተችው ሊለያት አልፈለገም።

ላርሰን ዋናውን የደሴቶች አጀብ አልፎ የምተገኘው ኮካር ደሴት ላይ ትቶታል። አሁን በገላጣ ውሀ ላይ ብቻውን ወደደቡብ አቅጣጫ እያመራ ነው። እንደገመተው ሳይሆን ብዙ መርከቦች አልገጠሙትም። በከባድ ነፋስ እየተደገፈ በአስራ አምስት ሰዓታት ውስጥ መቶ ማይል ተጉዟል፣ ይህን ያህል መጠን ላለው ጀልባ ሊመኘው የሚችለውን ያህል ፍጥነት ላይ ደርሷል። ስዊድን በስተቀኙ አንድ ሰፍራ ላይ ትገኛለች፣ ሶቪየት አስቶኒያ ደግሞ በግራው በኩል፣ ከሰባ ማይል ባልበለጠ ርቀት ላይ ትገኛለች ብሎ አሰበ። ወደሶቪየት ህብረት ተጉዞ አያውቅም፣ ከዚህ በላይ ሊቀርባት ይችል እንደሁ አሰበ። እኩለ ሌሊት ገደማ ጎትላንድ በተባለችው የስዊድን ደሴት ላይ በሚገኘው በንጂ ወደብ እንደሚደርስ ገመተ። እዚያ ሲደርስ ወደ ኮፐንሀገን የሚያደርገውን የመጨረሻ ጉዞ የሚደግፍለትን ስንቅና ቁሳቁስ ያሟላል። ኮፐንሀገን ላይ ሩል ትጠ ብቀዎለች። ይህን እያሰበና በቢራው ተጸክሞ እንቅልፍ ወሰደው፣ ከተገቢው በላይ ተኘቶ ቆየ።

የነቃው ጀንበሯ በደመና ተሸፍና ቅዝቃዜ በተሰማው ጊዜ ነበር። ተነስቶ ተቀመጠና ራሱን ማከክ ጀመረ። ሰማዩ በደመና እየተሸፈነ ነው። ጀልባዋ እንደ ባቡር እየጋለበች ነው፣ በስተቀኙ በኩል ያለው አማስ አስፈሪ ጭለማ ውጠታል። የነፋሱም ኃይል መጨመሩን ከቀጠለ የሸራውን ስፋት መቀነስ ይኖርበታል። ሰዓቱን ተመለከተ። የክርስቶስ ያለህ፣ ሶስት ሰዓት ያህል አንቀላፍቷል! በተሰዓት ሁለት ቢራ መጠጣት ጥሩ ሀሳብ አልነበረም። የሚጋጭ ነገር እንዳይገጥመው በማሰብ የፊት ለፊቱን አድማስ ቃኘ። ምንም ነገር የለም አምላክ ይመስገን። ትንሽ ዘና አለ። እንደገና ውጥረት ገባው። በስተግራ በኩል ከመንገዱ በሀያ ዲግሪ ወጥቷል። ነፋሱ አቅጣጫውን ወደደቡብ ምዕራብ በመቀየሩና ጀልባዋም ራሷን ለመሸፈር የምትጠቀምበት የነፋስ አቅጣጫ ጠ ቋሚውን በመሆኑ አቅጣጫዋን ለውጣለች። አቅጣጫውን በሚስትበት ጊዜ የሚሰማ ድምፅ ቢኖርም ግን አጥፍቶት ስለነበር ለውጡን ማወቅ አልቻለም። ጀልባዋ አቅጣጫውን ሳታ ምን ያህል ጊዜ ተጉዛ ይሆን?

ወደታችኛው ክፍል ሔደ በልዩ የሬዲዮ ግንኙነት በመታገዝ የጀልባዋን የጉዞ መስመር እየመዘገበ ያለችበትን ስፍራ የሚጠቁመውን ዴካ የአቅጣጫ መሪ ተመለከተ። ቁጥሮቹን መዝግቦ ካርታው ላይ ይህን ቦታ ፈለገው። ሊ እርሳሱ ምልክት ያደረገበትን ስፍራአፍጥጦ ተመለከተው። ሊሆን አይችልም፣ በፍፁም ብሎ አሰበ። ከትክክለኛ አቅጣጫው በሀያ ማይል ወጥቶ ወደ አለም አቀፍ የድንበር ክልል ከመጠን በላይ ተጠግቷል። ለገላጣ የውሀ ክልል ጉዞው የሚጠ ቀመው ካርታ ትንሽ በመሆኑ የኬላዎቹን ምልክት አልያዘም። ቢሆንም ግን ሶስት ሰዓት ሙሉ በተሳሳተ አቅጣጫ ሊጓዝ ቢቆይም በስዊድን የውሀ ክልል ውስጥ በመሆኑ ተሰማው። ጀልባዋ ቀን በተመለከታቸው ሁሉ የገዘፈ ማዕበል ሲመታት ተናወጠች። ሸራውን ቀንሶ በቶሎ ወደአቅጣጫው ቢመለስ ይሻለዋል።

እንደእድል ሆኖ ይህን ማድረግ አይከብድም። ማድረግ ያለበት ሸራውን በግርገብ መጠቅለያው ላይ መጠምጠም ብቻ ነው። ይህንን አደረገና ከዋናው ሸራ ላይም ትንሽ ቀነሰለት። ይህን ለማድረግ ሀያ ደቂቃ ፈጀበት ከዚያም አቅጣጫውን ወደጎትላንድ አዞረው። ሁሉን ነገር መልሶ ካሰረ በኋላ ግን ገና ትክክለኛ አቅጣጫውን እንዳላገኘ ገባው። ጎትላንድ ባልሼድስ፣ ሌላ ጊዜ እሄዳለሁ ብሎ አሰበ።

ትንሽ ወደ ምዕራብ አዘንብሎ በስተደቡብ መጓዙን ቀጠለ። በአለም አቀፍ ድንበሩ የስዊድን ክልል ውስጥ ለመሆኑ ርግጠኛ ነው። ጀልባዋ እየከነፈች ነው። አሁን ደስ ደስ ይለው ጀምሯል። ባለፉት ጥቂት ቀናት ሰንፎ ነው የቆየው። ቡና ለማዘጋጀት ወደታች ሲወርድ የአየር ግፊት መጠን መለኪያውን ተመለከተው። በፍጥነት እያሽቆለቆለ ነው። ካርታውን ተመለከተ። የሚያሰናክለው ምንም ነገር የለም፣ ግን ድንበሩ እዚህ አካባቢ ስለሆነ ጥሶት ከቋጥኝ ጋር ከመላተም የከፋ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። የጓደኛውን መርከብ ሊወርሱበት ይችላሉ። ጀልባዋ በሌላ ግዙፍ ማዕበል ተመትታ ስትናወጥ ቡናውን አፈሰሰችበት። ሲኒውን አስቀምጦ ወደሹፈር ክፍሉ መጣ።

የነፋሱ ኃይል እየጨመረ በመሆኑ ጀልባዋ ላይ ከባድ ጫና እያሳረፈባት ነው። ሸራውን አሁንም መቀነስ ይኖርበታል። በመጀመሪያ የፊት ለፊቱን ከዚያ ዋናውን ሸራ ቀነሰ። ሸራውን አርግቦ መጠቅለያው ላይ ይጠመጥመው ጀመር። ገመዱ ተወጠረና ተሽከርካሪው የሸራ ዘንግ ነክሶ አልዞር አለው። ነገሮች የሚበላሹት በመጥፎ ጊዜ መሆኑ አበሳጨው። ወደታች ወርዶ የደህንነት መጠ ቂያ ቀበቶውን አድርጎ መጣ። ቀበቶውን ከሽቦ ጋ አገናኝቶ በነፋሱ አቅጣጫ በኩል ጥግ ጥጉን ሚዛን እየጠበቀ በመዳህ ወደፈት ለፊቱ የጀልባው መለል አመራ። ሸራ የተጠቀለለበትን ቋሚ ዘንግ ተንበርክኮ ያዘው። ሊያዞረው ሞከረ። አልተሳካለትም። ሊዞርለት ካልቻለ በሸራ መወጠሪያው መጠቀም አይችልም። ነፋሱ እያርገበገበ ከጥቅም ውጭ ያደርገዋል። በረጅሙ ትንፋሽ ሳበና ባለ በሌላ ኃይሉ ዘንጉን ለማዞር ተፍጨረጨረ።

ትንሽ ዞረለት። ከዚያ ግን የጥይት ተኩስ ያህል ከባድ ድምፅ ተሰማና ሊ ጀልባው ወለል ላይ በጀርባው ተዘረጋ። ምን ተፈጠረ? ወደላይ ሲመለከት ዘንጉ ጫፍ ላይ ሸራው እንደግዙፍ ባንዲራ ይውለበለባል። ከወለሉ ላይ አፈትልኮ የተፈናጠረው ዋና ሸራ መሆኑ ገባው። እንደድመት ተፈናጥሮ ተነስቶ ወደሹፈር ክፍሉ ተፈተለከ። የሸራው ዘንግ አሁን ምንም የደገፈው ነገር የለውም፣ ጫናውን ለመቀነስ ሸራውን የሚያወርድለት ከሆነ ሊሰበር ይችላል። ይህ ሀሳብ ተከስቶለት ተወርውሮ ወደሹፈር ክፍል ሲገባና ዋናውን ሸራ ለመያዝ እጁን በዘረጋ ቅፅበት ሌላ ከቀድሞው የበለጠ የስንጥቅ ድምፅ ተሰማና ሁሉ ነገር ፀጥ አለ።

የንፋሱ ኃይል ቀንሷል፣ ባህሩም እስፈራንቱ አልታይህ አለው። ይህ አላስገረመውም። አሁን ጉዞው ተገትቷል። የሸራ መወጠሪያ ዘንጉ ከወለሉ በግምት አራት ጫማ ከፍታ ላይ ተሰብሮ ውሀው ውስጥ ወድቆ ከጀልባው ጋር በቀጭን ሽቦ ብቻ ተያይዟል። ጀልባዋ አሁን እሱ መሄድ ወደሚፈልግበት አቅጣጫ እየባዘነች ነው።

ቀጣዩን እንድ ሰዓት ተኩል በከባድ ሰራና በመራር ስቃይ ተወጥሮ ቆየ። ይህ የራሱ ጥፋት ነው። ተሽከርካሪ ዘንጉን ዘይት የማጠጣት ስራ የሱ ነበር። ይህን ሳያደርግ ቀርቷል። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ እንዲት ሊዝግ

http://ethzare.wordpress.com

እንደቻለ መገመት አቃተው። መጀመሪያውኑ ላልቶ ነበር ማለት ነው። ስንፍናን እሸንፍ ዘይት ሊቀባው ቢነሳ ኖሮ ይህን ችግር ተመልክቶ ቀድሞ ባጠበቀው ነበር። ጥሩ ሞተር መኖሩ እምላክ ይመስገን፣ አሁን ሞተሩን ተጠቅሞ ጀልባዋ ባቅራቢያው ወደሚኖኝ ወደብ ይወስዳታል። መጀመሪያ ግን የወደቀውን ዋልታ ቆርጠ መለያየት ይኖርበታል። ዋልታውን ከወደቀበት ለማምጣት አይችልም፣ ብቻውን ነው። ሽራውም አብሮት መሄዱ ነው፣ የለንደኑ ሉይድ አዲስ ይግዛ። ከቁም ሳጥን ውስጥ የሸቦ መቁረጫ አመጣና ሸቦውን ለመቁረጥ መታገል ጀመረ። ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ሽራውና ዋልታዎቹን ከጀልባው ለይቶ ለማስጠም ቻለ። እጆቹና ክንዶቹ ዝለዋል።

በድካም ዝሉ ወደታች ወረደና በፍጥነት ኃይሉን ለመተካት እንኳር ስኳር እየመጠጠ እረፍት አደረገ። ነገሮች ከዚም ሊብሱ በቻሉ ነበር ብሉ አሰበ። ቢያንስ አዲስ የቮልቮ በናፍጣ የሚሰራ ሞተር አለው። የተወሰኑ ሰሌቶችን ከሰራ በኋላ በአራት ወይ በአምስት ኖት ፍጥነት ወደባህሩ እየተንሳፈፈ መሆኑ ታወቀው የሚደላው ባይሆንም ምናልባት እስከ ጠዋት ድረስ ጎትጎንድ ይደርሳል። በድካም ስሜት ወደሹፌር ክፍሉ ተመለሰና ሞተሩን አበራው። ከዚያም ነዳጅ ሰጠውና አስነሳው። ሞተሩ ለአስር ሰከንድ ያህል ተንተፈተፈና ጠፋ። ባትሪዎቹ አቅም እስኪያገኙ ጠበቀና መልሶ አስነሳው። አሁን ወዲያውኑ ተነሳለት። የፊት ማርሽ ቀየረለት።

የበንጂን አቀጣጫ ከያዘ በኋላ ራሱን እንዲመራ አድርጎ ተወው። ጉዞው ዝግተኛ ቢሆንም ጀልባዋ የአምስት ተኩል ኖት ፍጥነት በመያዟ መጥፎ የሚባል ፍጥነት አይደለም። ድንገት በጣም ራበው። የሚንቀሳቀስ መርከብ ፈልጎ ስላጣ የሚበላ ፍለጋ ወደታች መውረድ ጀመረ። ግን ገና መሰላሉን እንደረገጠ ሞተሩ ድንገት ድምፁ ተቀየረና ፀጥ አለ። ደሞ ምንድን ነው? የዘይት ግፊት መጠን ማለጠንቀቂያው ፀጥታውን አደፈረሰው። የሞተሩን ቁልፍ ሊያጠፋ ሲንጠራራ አንድ ነገር ተመለከተ። በቀኝ በኩል ከነበረው የሽራ መጠቅለያ ጋር የተያያዘው ገመድ ተወጥሯል። ገመዱ ከውሀ ስር ካለው የሞተሩ መቅዘፊያ መዘውር ላይ እንደተጠቀለለ ያለጥርጥር ታወቀው።

በርግጥ ማወቅ አለብኝ ብሎ ሞተሩን ደግሞ አስነሳው። ባዶ ማርሽ ሆኖ ምንም ችግር የለበትም ጥርስ ሲለወጥለት ግን ማቃተት ጀመረ። እንድ እድል ብቻ አለው። የኋላ ማርሹን ሞከረው። ምናልባት የተጠቀለለው ይፈታ ይሆናል። በኃላ ማርሽ ሞተሩ ለተወሰነ ጊዜ ያለችግር ሲሰራ ቆየና ዳግመኛ መንተፋተፍ ጀመረ። ሊ ወደባዶ ጥርስ መለሰው። ጀልባዋ አሁን ያለምንም የሀይል ምንጭ ብቻዋን ቀረች።

የገባበትን ውጥንቅጥ የሚገልፅ ምንም ቃል የለም። ነፋስም፣ ሞተሩን ከድተውታል። በግምት በሶስት ኖት ፍጥነት ግብግ ያልተደረገላቸውን ሁሉ በሰላም ወደማትቀበል ሀገር እየሄደ ነው። ቦታውን አያውቀውም። በመሰልቸት ስሜት ሞተሩን አጠፋና ወደታች ወረደ። ከሹፌሩ መቀመጫ ስር ካለው ሳጥን ውስጥ ሶስት ተንሳፋፊ ርችቶችን አገኘ። በወሰዳቸው ጎዜ ሶስት በቂ ነው ብሎ አሰቦ ነበር፣ አሁን ግን ሀያ ቢሆኑለት ተመኘ። ወደላይ ተመለሰና ዙሪያውን ተመለከተ። ምንም ነገር የለም። ምንም አይነት ጀልባና መርከብ የለም። ከቀጫጭኖቹ የእጅ ርችቶች አንዱን ሲለኩለው ቀይ ብርሀን ደምቆ ታየ፣ ከዚያም በትንሿ እንሳፋፊ ፓራሹት ተደግፎ ለተወሰነ ጊዜ ሲንሳፈፍ ቆየ።

ምናልባት ከአድማስ ባሻገር መርከብ ካለ ብርሀኑን ማየት ይቻላል። በዚህ ስፍራ ላይ ግን በጣም አይጨልምም። ስለዚህ በዚህ ደብዛዛ ብርሀን ብቻ ሊታይ አይችልም። የቀሩትን ሁለት ርችቶች ተመለከተ። ሌላ ጀልባ እስኪመለከት ድረስ ሊያቆያቸው ይገባዋል።

ካርታው ወደተዘረጋበት ጠረጴዛ አመራ። የከፍተኛ ፍርሐቄንሲው ሬዲዮ እንቴና ከዋናው ዋልታ ጋር በመውደቁ ሬዲዮኑ አይጠቅመውም። ዲካ የተባለው የቦታ መጠቆሚያ መሳሪያ እንቴና ግን ከጀልባው የኋላ ዋልታ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይሰራል። የቦታውን መለያ ቁጥሮች እንብቦ በካርታው ላይ ስፍራውን ምልክት አደረገበት። የላቲቪያ የባህር ድንበር ላይ ከምትገኝ እንዲት ከተማ በእርባ ማይል ያህል ርቀት ላይ ይገኛል። ስለዚህች ከተማ ሰምቶም እያውቅም፣ ላይታኝ ትባላለች።

35

ሩል ማለዳ የመጡላትን የቴሌክስና ሌሎች የመረጃ መልዕክቶች ትመለከታለች። ባለፈው ለሊት ደሀና እንቅልፍ ስላላገኘች ራስ ምታት ይሏታል። ላይመን ከድርጅቱ እንድትወጣ ፊት ለፊት ነግሯታል። ትጻር ውስጥ ሆኖና ከፍቺያቸው በኋላ ስለስራዋ አቤቱታ ሲያሰማ ኖሯል። አሁንም አልተዋትም። ላይመን እንድ እናት ማሳየት ስለሚኖርባት ባህሪን የራሱን አመለካከት ከያዘ ሰንብቷል። እሷ ደግሞ ይህን ሀሳቡን ሞልታለት እንደማታውቅ ታውቃለች። ከተፋቱ በኋላ እንኳን ቤቷ ተቀምጣ ከሌሎች እናቶች ጋር ወሬዋን እየሰለቀች ልጇ ወደቤት ሲመጣ ወተትና ብስኩት አዘጋጅታ እንድትጠብቀው ይፈልጋል። እንቅልፍ አጣጥቶት ያሳደራትም፣ ላይመን ይህንን ልንድታደርግ ምን ያህል ሜና ሊያሳድርባት እንደሚችል ስታስብ ነው።

የድርጅቱን እንድ የውስጥ ለውስጥ ፖስታ ከፍታ በሩስኪ ቋንቋ የተፃፈ እንድ ሀትመት አወጣች። የሶቪየት ባህር ሀይል ወርሀዊ የህትመት ውጤት ሲሆን፣ እንድ ምልክት የተደረገበትን ነገር በግልፅ ለማሳየት ሰርጓል ተስተካክሎ ታተኗል። የተሰጡ ማዕረጎችንና የታቀዱ ተልዕኮዎችን ዝርዝር የያዘ ቢሆንም፣ ይህ ለየት ያለ ነገር አትኩሮቷን ሳበው። የሶቪየት ባህር ሀይል የበላይ መሞሪያ፣ ለሶስተኛው የሀቡዕ ዳይሬክተር ሊቀመንበርነት እንድ ሰው መታጨቱን ይገልፃል። ስሙ በመጀመሪያ ደረጃ ካፒቴይን ቪክቶር ሰርጌቪች ማጆሮቭ፣ ይላል። ጋዜጣው ላይ የሰፈረውን ቀን ተመለከተች ነሀሴ 18 1983 ይላል።

ሩል በእግራሞት ተዋጠች። ማጆሮቭ፣ የእንድሮፖቭ ቀኝ እጅ በሆነ ጊዜ ነበር፣ የKGB የመጀመሪያ ዋና ዳይሬክተርነትን ቦታ ያገኘው። ከዚያም ከእንድሮፖቭ ሞት ስድስት ወራት ቀደም ብሎ፣ ድንገት በባህር ሀይሉ ውስጥ የኮሞደርነት ቦታን ይዘ፣ ቀድሞ ከነበረው ማዕረግ በሶስት ወይ በአራት ያህል ወደታች የሚያወርደው ሥራ ላይ ተቀመጠ፣ እንድ ትልቅ ደረጃ ላይ የሚገኝ የሶቪየት ባለስልጣን ከስልጣን መውረዱ አዲስ ነገር ባይሆንም ሲቪል ሰራተኛ ግን ወደ ውትድርና ስራ የተዘዋወረበትን ጊዜ ልታስታውስ አልቻለችም። በእንድ ወቅት የፓርቲው ተጣባሪ መሪ የነበረው ማሌንኮቭ ከቢታው ላይ ተነስቶ የእርሳስ ፋብሪካ አስተዳዳሪ ቦታ ላይመቀመጡ ትዝ ይላታል። እስካሁን

http://ethzare.wordpress.com

ስለማጆሮቭ ያወቀችው ነገር ሁሉ የባህር ሀይል ልምድ እንዳለው አያመለክትም። ግራ አጋብቷታል።

ወደ አንድ የዶሴ ካቪኔት አምርታ፣ የፔንታጎን የስልክ ማውጫ አወጣችና በፍጥነት አንድ ቁጥር ፈልጋ አግኝታ ደወለች። አንድ ጊዜ እንደጮኸች ተነሳ።

«የባህር ኃይል ሀቡዕ ሀይል፣ የካፒቴን ስቶን ቢሮ።»

«እባክዎትን ካፒቴይን ስቶንን ፈልጌ ነበ። ካትሪን ሩል ነኝ፣ ከCIA የሩሲያ ቢሮ።»

«እንድ ጊዜ ቆይኝ፣» እንድትጠብቅ ተደረገች።

«ኬት ነሽ? ደህና ነሽ? ረጅም ጊዜ ሆነን።»

«ሀሎ ዳግ፣ አም ነኝ። ስላገኘኸው እድገት ሰማሁ። እንኳን ደስ ያለህ።

«እመሰግናለሁ። ለሥራ ነው የፈለግሽኝ?»

«አም። አንድ ቀላል ጥያቄ ልጠይቅህ። ስለ ሶቪየት የባህር ሀይል ሀቡዕ ዳይሬክቶሬት ብዙም የማውቀው የለም። የሶስተኛው ዲፓርትመንት ስራ ምንድን ነው?»

«ቀላል ነው። ሶስተኛው ዲፓርትመንት ሰፔትናዝ ነው።»

የሩል ልብ ይዘል ጀመር። ሃላፊው ማን ነው?»

«ትንሽ ሚስጥር ነው እንጂ ይህም ቀላል ነው። ማጆሮቭ ይባላል። ሚስጥር የሆነው፣ ስራውን እስካገኘበት ጊዜ ድረስ ማንም ስለሱ ምንም ነገር አለማወቁ ነው። በእሱ ላይ የተወሰነ የኮምፒውተር መረጃን አሰባስቤ ነበር፣ እና ምንም አይነት የደረጃ እድገትና አዲስ ስልጣን አግኝቶ አያውቅም። ገና ወደባህር ኃይሉ በገባ ጊዜ የስፔትናዝ ሀላፊ ሆኖ የተሾመ ይመስላል።

«እመሰግናለሁ ዳግ . . . በአሁኑ ወቅት ስፔትናዝ እያደረገ ያለው ነገር አለ? ማለቴ ያልተለመደ ነገር?»

«የለም። ያውሳ ፖለንድና ባልቲክ ሪፑብሊኮች ወስጥ ሰፍሮ ነው ያለው። ይህ ደግሞ የሚጠበቅ ነው።»

«ለምን?»

«ሀመር የተባላ ተልዕኮ ላይ ነው። ይህ እኛ የሰጠነው ስም ነው። ሶቪየቶች በየአራት ዓመቱ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ልምምድ ያደርጋሉ፣ አሁን የባልቲክ ተራ ነው። እፎይ ብያለሁ፣ ባለፈው እንዳደረጉት ምስራቅ ጀርመን ውስጥ ገብተው ሲለማመዱ ይረብሻል።»

«እመሰግናለሁ ዳግ፣ ይህ ለጥያቄዬ መልስ ይሆናል። ደህና ሰንብት።» ብላ ስልኩን ዘጋችው። ስለውትድርና ሀቡዕ ስራ የሚመለከታት ነገር ባይኖርም ሶቪየት የተለያዩ ስፍራዎችን በመለዋወጥ የምታደርገውን ልምምድ ታውቃለች ዳሩ ግን ይህ ዓመት የባልቲክ ተራ መሆኑን አታውቅም። በምስራቅ ጀርመን ይደረጉ የነበሩ ልምምዶች ግን ስቶንን ይረብሹት ነበር። አሁን በባልቲክ ላይ የሚደረጉ ልምምዶች ደግሞ እሷን ሊያስቀውሷት ደርሰዋል። ተነስታ ወደ አለን ኒክሰን ቢሮ አመራች። በቀዘቀዘ መንፈስ ተቀበላት።

«አቤት ካትሪን?»

«አለን፣ ምናልባት ይህን የምታዳምጥበት ስሜት ውስጥ አይደለህም ይሆናል። ግን ዛሬ ጠዋት አንድ መረጃ ደርሶኛል።»

ኒክሰን በረጅሙ ተነፈሰ። «አሁንም ስለፈርሶቭ ነው?»

«ፈርሶቭ ነው። ያወቅኩትን እነግርሀና አንተ የራስህ መደምደሚያ ላይ መድረስ ትችላለህ። በ1983 ኒሕሴ ውስጥ፣ ማጆሮቭ ማለትም የፈርሶቭ በትክክለኛ ስሙ፣ KGB ውስጥ የውጭ ተልዕኮዎች ስራውን በማቆም በሶቪየት ባህር ሀይል ውስጥ በኮሞደርነት ተቀጠረና፣ የልዩ የባህርና የምድር እግረኛ ሰራዊቱ ማለትም የስፔትናዝ ሃላፊ ሆነ። ይህ የደረጃ እድገት ታትሞ ወጥቷል። በአሁኑ ወቅት ሶቪየቶች በባልቲክ ሪፑብሊክ ውስጥ ልምምድ ለማድረግ እየተዘጋጀ ነው፣ የስፔትናዝ ሀይላትም ለዚሁ ልምምድ በዚያ ስፍራ ላይ ሰፍረው ይገኛሉ። ስለዚህ ከቀዩ ጦር አብላጫው ክፍል እዚያ ይገኛል ብዬ እጠብቃለሁ። ስፍር ቁጥር የሌለው ጦር መሳሪያም ይኖራል።» ከክፍሉ መውጣት ጀመረች። «ይህን ባሳውቅህ ምናልባት ይጠቅምህ ይሆናል ብዬ ገምቼ ነው።»

ኒክሰን ምንም አልተናገረም። በሩ ላይ ደርሳ ቆመችና «በነገራችን ላይ፣ አለን የሰንፍላወር ተልዕኮ ተግባር ላይ የዋለው መቼ ነበር? ረሳሁት።»

«ግንቦት ወይንም ሰኔ ሰማንያ ሶስት ላይ ይመስለኛል።»

ገባኝ በማለት ራሷን ወዘወዘች። «ልክ ነው። ቀኖቹን ማስታወስ አልቻልኩም።»

ሰንፍላወር ማወቅ እንደማይገባት ሳይከሰትለት ቢፊት ወጥታ ሄደች።

ወደቢሮዋ ተመልሳ ኮምፒውተሯን አስነሳችና፣ ለሀቡዕ ክፍሉ ምክትል ዳይሬክተር አለን ኒክሰን በሚል ርዕስ፣ አሁን የነገረችውን በዝርዝር የሚናገር ማስታወሻ መፃፍ ጀመረች። በማስታወሻውም ከዚህ በፊት ያደረጉትን ውይይትና፣ ከዚህ በኋላ መተግበር አለባቸው ብላ ስለምታስባቸው ምርመራዎች አሰፈረች። ማስታወሻውን የፋይል ቁጥር ሰጥታ ቢወረቀት ካተመችው በኋላ ለመአከላዊ መረጃ ጣቢያ የሚሆን ግልባጭ አስቀረች። ወረቀቱን የቢሮ ፖስታ ውስጥ አስገብታ የኒክሰንን ስም ፅፋበት ሳጥኗ ውስጥ ከተተችው።

አሁን በሚስጥር መስራቷ አብቅቷል፣ ይህ ክስተት መሆኑ እንደማይቀር ስለታወቃት፣ ራሷን ማዳን መጀመር የሚኖርባት ጊዜው አሁን ነው።

36

ዊል ሊ ዙሪያውን ሲመለከት ምንም ነገር አጣ። አጭሩ የባልቲክ ምሽት ያበቃው ገና ቅድም ቢሆንም፣ ንጋቱ የመጣው ጭጋግ እዝሎ ነው። ንፋሱ ረገብ ብሏል። ዳሩ ግን ውሀው ገና ስላልረጋ ጀልባውን ያንገላታታል። ወደ ሶቪየት የውሀ ክልል ከመግባቱ በፊት ምናልባት አንድ ምዕራባዊ ጀልባ ይመለከተኝ ይሆናል በሚል ግምት እኩለ ለሊት ላይ አንድ ሌላ ርችት ተኩሷል። የመጨረሻውን ርችት ግን ምናልባት ሁሉ ነገር የከፋበት ከሆነ ሲጠቀምበት አስቀምጦታል። ቦታ ጠቋሚ መሳሪያው አሁንም እየሰራ ነው፣ ወደላቲቪያ ባህር ዳርቻ እጅግ መቅረቡን ይናገራል። የጥልቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያው ጥልቀቱ እየቀነሰ ሃያ ሜትር ገደማ መድረሱን ያመለክታል። መልህቅና ጀልባ ማሰሪያ ገመድ ቢኖረውም ምንም አይፈይዱለትም። ጀልባዋ ያገጠጡ አለቶች ወዳሉበት ዳርቻ እየባዘነች ከሆነ ግን ያን ጊዜ ይጠቅመው ይሆናል።

ከምሥራቅ አቅጣጫ እንደአሳ አስጋሪ ጀልባ ሞተር ዓይነት ድምፅ ሰማ። ምናልባት የስዊድን አሳ አስጋሪዎች ጀልባ ከሆነች ወደራሳቸው የውሀ

http://ethzare.wordpress.com

ከልል ጎትተው ሊወስዱት ይችላሉ። ድምፁ እየጎላ መጥቶ፣ ውሀው ላይ በጥቂት መቶ ርምጃ ርቀት ላይ ነጭ ገመድ ተመለከተ። የአሳ አጥማጆች መረብ ይሆን? ወይንስ የሳሙና አረፋ? የጥልቀት መጠን ማመልከቻውን አየት አደረገው። ድንገት ሰምንት ሜትር ላይ ደርሷል። ነጩን ተንሳፋፊ ምርር ደግሞ ተመለከተ። የመጨረሻውን ርችት መጠቀም ያለበት ጊዜው አሁን ነው። ተኩሶት ወደሰማይ ሲወነጨፍ ተመለከተው፣ ጭጋጉ ውስጥ ገብቶ የሚሰወርበት ርቀት ላይ ሳይደርስ ተንሳፈፈ። ከገመተው በላይ ዙሪያውን ማየት ቻለ። ወደባህር ዳርቻው አየቀረበ መምጣቱን ከውሀው ባሻገር ከሚታየው ግራጫና ቋጥኝ የሞላበት ምድር መገመት ቻለ። በየጊዜው የጥልቀት መቆጣጠሪያውን መልከት እያደረገ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ደረቅ መሬቱ እየቀረበው ሲመጣ ያስተውል ጀመር። አሁን ርቀቱ ሰድስት ሜትር ያህል ደርሷል፣ ሀያ ጫማ ያህል ማለት ነው። ከጋቢናው ወጣና በጀልባው ወለል የፊተኛው አካል ላይ ቆሞ፣ መልህቁን ለመጣል ተዘጋጀ። የባህሩ ወለል ምን ሊሆን እንደሚችል አላወቀም፣ ግን ቋጥኝ ይሆናል ብሎ ገምቶ መልህቁን ቆንጥጠ እንደሚይዝለት ተስፋ አደረገ። ማስተማመኛ ባይኖረውም ለቋጥኙ ተስማሚ ይሆናል ብሎ የገመተውን የቀድሞ ዘመን አሳ አጥማጆች መልህቅ መረጠ። በአጠቃላይ ሶስት መልህቆች አሉት። ከመልህቁ አጠገብ ቆሞ የማንጠልጠያውን ገመድ እየፈታ የባህሩን ዳርቻ አቅራቢያ ይመለከታል። ከአሁን የተሻለ ጊዜ እንደሌለው አስቦ መልህቁን አነሳው።

ከዚያ ግን ብሩህ ቢጫ ቀለም ያሳትና ባለግዙፍ ሞተር አነስተኛ ጀልባ ድንገት በእሱ ጀልባና በዳርቻው መሀል ተከሰተች። በጀልባዋ ላይ ሙሉ የዝናብ ልብስ የለበሱ አራት ሰዎች አሉ። ጀልባዋን እንደተመለከቱ ሁለቱ ወደሾፈሩ እየጠቆሙ መጮህ ጀመሩ። የሞተር ጀልባዋ መሳበሉቹ ላይ እየተፈተለከች ወደሱ መጣች። የሾፈሩ አነዳድ አላማረውም። እየቀረበችው ስትመጣ ፍጥነቷን ቀነሰችና አስር ሜትር ያህል ሲቀራት ፊቷን አዞረች። ከመካከላቸው አንዱ ስዊድንኛ በሚመስል አነጋገር ጮኸ። ሊ ተገርሞ በአሉታ ራሱን ወዘወዘ።

«አልገባኝም!» መልሶ ጮኸለት። «እንግሊዝኛ ወይንም ፈረንሳይኛ ትችላላችሁ?»

«አዎ፣ እንግሊዘኛ እናገራለሁ፣» ሲል ወጣቱ መለሰለት። «ችግር ላይ መሆንህ ይታየኛል። ወደወደቡ እንጎትትህን? ገመድ አለህ?»

«አዎ፣» መለሰ ሊ። አንድ ጊዜ ቆየኝ።» ወደፊት ተራምዶ ከመልህቁ ላይ ገመዱን ፈታና ለአንደኛው ጫፉን ወረወረለት፣ እሱም ገመዱን በራሳቸው ጀልባ በሰተኋላ ካሰረው በኋላ ምልክት ሰጠው። ገመዱ ተወጠረ፣ ሊም ጀልባውን እነሱ ወደሚሄዱበት አቅጣጫ ለመምራት ቦታውን ያዘ። እንግሊዝኛ የሚናገር ሲቪል ሰው በማግኘቱ ደስ ብሎታል። አዚህ አካባቢ ያሉ ባለስልጣናት በቢጫ የመዝናኛ ጀልባ ይጓዛሉ ብሎ ማሰብ አቃተው። እነዚህን እንኳን ተናግሮ ማሳመን ሊሳካለት ይችላል።

ከዳርቻው ትይዩ ለዓንድ ሰዓት ያህል ጀልባው ስትጎተት ከቆየች በኋላ ወደትልቅ ሰርጥ የሚያስገባ የመሰለ ቀጭን መግቢያ አለፈች። ከገቡ በኋላ ወደሰሜን ተጠምዝዘው የሰርጡን መሀል ያዙ። አሁን ጭጋጉ እየገፈፈ መጥቷል። በሰርጡ ሽቅብ ሁለት ማይሉች ያህል ከተጓዙ በኋላ ብዙ የጀልባዎች የተወጠረ ሽራ መታየት ጀመረ። ከሳጥኑ ውስጥ ሌሎች ገመዶችን አውጥቶ

ከጀልባዋ ጎላና ፊት አሰራቸው። በቅርብ ወደሚገኘው የጀልባ መናኸሪያ እየቀረቡ ሲመጡ ሌሎች የመዘናኛ ጀልባዎች ወደቡ ላይ ቆመው ተመለከተ። ሁለት ሌሎች ሰዎች ገመዶቹን ለመቀበል ይጠብቁታል። የሞተር ጀልባዋ ፍጥነቷን ስትቀንስ ሊ ጀልባዋን ከአጠገባቸው እየመራ አድርሷት ገመዶቹን ለሚጠብቁት ሰዎች ወረወረ።

የሞተር ጀልባው ላይ ሆኖ የጠራው ሰው የወደቡ ጣውላ ላይ ዘሎ ወጣና እየሮጠ ወደእሱ ከመጣ በኋላ፣ «እባክህን ጀልባ ላይ ቆይ። ከአለቃዬ ጋር ተነጋግሬ የሱን መመሪያ መቀበል ይኖርብኛል።» አለው።

«መልካም፣» ሲል ሊ መልሶ «ለራሴ ትንሽ ቡና ብቻ ላዘጋጅ።»

ገመዶቹን የተቀበሉትን ሁለት ሰዎች ተመለከታቸው። «ትንሽ ቡና ትፈልጋላችሁ?» እሱንም ሆነ ጀልባውን ለማወቅ የጓጉ ቢመስሉም ምንም ቃል አልተናገሩም። ምናልባት እንግሊዝኛ አይናገሩ ይሆናል። ሲል አሰበ።

ሊ ወደታች ወርዶ ጀበናውን ጣደ። ቡናው እየፈላ ሳለ በእንድ እቅጣጫ ብቻ የሚያሳየው መስታወት በኩል ወደውጭ ይመለከታል። እሱ ወደ ውጭ መመልከት ቢችልም እነሱ ግን ወደውስጥ አይታያቸውም። ብዙም የሚታይ ነገር የለም። በውሀው በስተግራ አነስተኛ የመዘናኛ ባህር ዳርቻ ይገኛል። የተወሰኑ ሰዎች ትንንሽ ጀልባዎችን ለጉዞ ያዘጋጃሉ። ከወደቡ ጀርባ ያለው ምድር ከፍ እያለ የሚሄድ ነው። አንድ አቀበታማና በሳር የተሸፈነ መሬት ላይ እጅብ ብለው የተሰሩ ዘመናዊ ህንፃዎች ይታያሉ። የትንሽ ኮሌጅ ካምፓስ ይመስላል። ተማሪዎቹ የተማሪነት እድሜያቸውን ያለፉ ቢመስሉም ግን ግን ያውቃል? ፖሊስ ወይ ደሞ ከባሰም KGBን እንደማይጠሩበት ተስፋ አድርጓል። KGB በሶቪየት ህብረት ውስጥ ያለው የድንበር ጥበቃን እንደሚያከናውን ያውቃል። ድንገት ስለ KGB እና ስለ CIA ከዚህ የበለጡ ነገሮች እንዲሚያውቅ ትዝ አለው። «አለቃቸው» ሲመጣ የሚናገረውን አዘጋጅቶ ቢጠብቀው ይሻለዋል።

እውነቱን ለመናገር ወሰነ። ባብዛኛው። ከዚህ በሰላም መውጣት ከፈለገ ስለዋሸንግተን ወይንም በምክር ቤቱ የስለላ ኮሚቴ ውስጥ ለሴናተር ካር ስለግልገሉ መናገር አይኖርበትም። ይህን ማድረግ በራሱ ላይ እንደመጠምጠም ስለሆነ ከከፍተኛ ባለስልጣን ፊት መቅረብ አይፈልግም። እነዚህ ሰዎች የሚያውቀውን ለማወቅ ጉጉት ይኖራቸዋል። ለምሳሌ ስለ CIA በጀትና ተልዕኮዎች ብዙ ያውቃል። የቀና ቀና ሰራተኞቹን ስሞችና ማዕረግ ያውቃል። የሶቪየት የስለላ ቢሮ ዳይሬክቶሬቱን ጠንቅቆ ያውቀዋል። ትዝ አስባለው። ከሰስት ቀናት በኋላ ከሷ ጋር ኮፐንሀገን ላይ ቀጠሮ አለው። ቡናው ፈላ።

ሰራሱ ቡና ከቀዳ በኋላ ትኩስ ሆነበት። ገና ካዙኑ እያሳበው ነው። የዝናብ ጃኬቱን አውልቆ በእጅጌው ፊቱን ጠራረገና፣ ራሱን ለማረጋጋትም እየር በረጅሙ ሳበ። ቡናውን ከብራንዲ ጋር ለመበረዝ አሰቦ ተወው። መጠጥ ከቀመሰ ብዙ ሊናገር ይችላል። በድፍረት ራሰን ሆኖ ቢገኝ ይሻለዋል። የተወሰነ ነገር ብቻ በመተው በእላወቂነቱና በስንፍናው ስለገጠመው ችግር ብቻ ቢናገር ይሻለዋል። ለራሱ ሳቀ። ይህን ማድረግ አያቅተውም። ከውሀው ባሻገር ወደካምፓሱ ሲመለከት አንዲት የጎልፍ ጋሪ ሁለት ሰዎችን ጭና በኮረብታው ቁልቁል ወደወደቡ ስትመጣ ተመለከተ። ውሀው ጸር ቆመችና ሁለቱ ሰዎች አለቃውን ሊጠራ የሄደውን ወጣት አስከትለው ወደጀልባዋ መጡ። ሊ የቡና

http://ethzare.wordpress.com

ሲኒውን ይዞ ወደጀልባዋ ወለል ወጣ። ሁለቱ ሰዎች ወደቡ ላይ ቆመው ጀልባዋን በጥንቃቄ ይቃኙዋታል። እንደኛው ቀጭን ርጅም በሀምሳዎቹ የእድሜ ክልል የሚገኝ ሲሆን መነፅር አድርጓል። ሌላው በአርባዎቹ መጨረሻ ላይ የሚገኝ ሲሆን በከፊል የሸበተ ፀጉር አለው። በቁመቱ ከመጀመሪያው ሰው ይበልጣል፣ መልከ መልካምም ነው። ሊ ይህን ሰው የሚያውቀው መሰለውና ወዲያውኑ ሐሳቡን ሰረዘው። ላቲቪያ ውስጥ ማን ያውቃል?

ሪጅሙ ሰው ጀልባዋን ተመልክቶ ሲያበቃ ወደ ሊ በመዞር በሩሲያኛ መሰለው፣ ያናግረው ጀመረ። ሊ ስላልገባው ዝም ብሎ ይመለከተዋል። ሰውየው ደግሞ በሰዊድንኛ ሞከረ።

ሊ እጆቹን ዘረጋቸው። «አዝናለሁ፣» አለ «የምናገረው እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ብቻ ነው።»

«የትውልድ ሀገርህ ቋንቋ የትኛው ነው?» ጠየቀው።

«እንግሊዘኛ ነው። አሜሪካዊ ነኝ።»

«መልካም፣ በእንግሊዝኛ እንነጋገራለን፣» አለሰውየው። «ወደጀለባህ እንወጣም?»

«አዎ፣ እባካችሁ። እታች ሄደን ቡና ልጋብዛችሁ?»

«እናመሰግናለን፣ እሺ፣» አለ ሰውየው።

ሊ ተከትሏቸው ገባ።

«ዊል ሊ እባላለሁ፣» በመኝታና በካርታ ጠረጴዛው መሀል ቆመው፣ የጀልባዋን ዙሪያ በጥንቃቄ ይመለከታሉ።

«እኔ ክራመር እባላለሁ፣» አለ ረጅሙ ሰውዬ። «እሱ ሚስተር ሚንዝ ይባላል።»

«ጀበናው ገና አልበረደም፣ ትንሽ ጊዜ ጠብቁኝ። እባካችሁ ተቀመጡ።»

ሁለቱ ሰዎች የጀልባዋን ውስጥ በአይኖቻቸው መፈተሻቸውን ላይተው ሳሎኑ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጡ። «ይህች በጣም ቆንጆ ጀልባ ናት ሚ/ር ሊ።» አለ ክራመር።

ሊ፣ ክራመር ወደብሪታኒያ ለዛ በጣም እንደሚያደላ አሰበ። «አመሰግናለሁ የኔ ቢሆን ደስ ባለኝ።»

«ባለቤቱ አንተ አይደለህማ ታዲያ?» አለ ሚንዝ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መናገሩ ነበር።

«አይደለም፣ ለለንደን ተወላጁ ጓደኛዬ፣ ከተመረተበት ከፊንላንድ ወደ ኮፐንሀገን እያደረሰኩለት ነው። ጓደኛዬ ከዚያ ተቀብሎኝ ወደ እንግሊዝ ይዞት ይሄዳል።»

«ገባኝ፣» አለ ክራመር። «ታዲያ ወደዚህ እንዴት ልትመጣና እንግዳችን ልትሆን በቃህ?»

ሊ ቡናቸውን ሰጣቸውና፣ ካርታውን እንስቶ መጀመሪያ እንዴት አትጣጫውን ለመሳት እንደቻለና፣ እንዴት ሽራ መወጠሪያ ዋልታው እንደተሰበረበት ከዚያ ወደባህር ድንበራቸው ያለፍላጎቱ እንደመጣ አጫወታቸው።

«ዛሬ ጠዋት የናንተ ሰዎች ያደረጉልኝ ርዳታ በጣም አስደስቶኖል። ባላገኛቸው ኖሮ ጸርቻው ላይ ባረፍኩ ነበር።»

«ገባኝ፣ ይህ በግልፅ የታየ ነው፣» አለ ክራመር የካርታውን መስመሮች በጣቱ እየለካ ከስር ካለው የማመሳከሪያ ጋር እያዛመደ።

«ተመልከት ሚስተር ክራመር፣» አለ ሊ። «ሀገራችሁ የገባሁት ጥሪ ላይደረግልኝ በመሆኑ ጠንቅቄ አውቃለሁ፣ ለዚህ በጣም ይቅርታ እጠይቃለሁ። በተቻለ ፍጥነት ጀልባዬን ይዤ እንድሔድ ይፈቀድልኛል የሚል ተስፋ አለኝ። የጠላቂ ዋናተኛ ቂምብል መዋስ ብችል ነመዱን ከሞተሩ መዘውር ላይ ማላቀቅ እችላለሁ። ስዊድን የሚያደርሰኝ በቂ ነዳጅ አለኝ። በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍ ያለ ቦታ መድረስ ባያስፈልግ ደስ ይለኛል። ጀልባዋ ልትወረስ እንደምትችል አውቃለሁ፣ ይህንን ግን ለባለቤትየው ማስረዳቱ ይከብደኛል። ልክ ወደውህ ከልላችሁ ስገባ የመድህን ዋስትናዬን ዋጋውን እንዳጣ እገምታለሁ፣ ጀልባዋ ደግሞ ዋጋዋ በጣም ውድ ነው።»

«አዎ፣ ይህ ይገባኛል፣» አለ ክራመር። «መልካም፣ ልረዳህ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ ሚስተር ሊ፣ ግን የመሔድህ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ በእኔ እጅ ላይሆን እንደሚችል ልትገነዘብ ይገባሀል። ጥቂት ጥያቄዎችን እጠይቅሀና፣ በሙሉ እውነተኛነት እንድትመልስልኝ እሻለሁ።»

«ምንም ችግር የለም፣» መለሰ ዊል። «የምችለውን ሁሉ ልነግርህ ደስተኛ ነኝ።»

«በመጀመሪያ ፓስፖርትህንና ሌሎች የማንነትህን መገለጫዎች እንዲሁም የመርከቧን ወረቀቶች ማየት እችላለሁ?»

ሊ ፓስፖርቱንና የኪስ ቦርሳውን ከካርታው ጠረጴዛ ላይ አንስቶ ሰጠው። ሚንዞ ማስታወሻ ደብተር አውጥቶ መመዝገብ ጀመረ።

«የደቡብ ሰው ነህ ለካ፣» አለ ክራመር ፓስፖርቱን እየተመለከተ። «ጂምርጂያን ከካርታ ላይ አውቃታለሁ፣ ግን ዲሌይኖ የት ነው ያለችው?»

«ከአትላንታ በስተደቡብ ሰማንያ ማይል ርቀት ላይ፣ በክፍለግዛቱ መዐከላዊ ምዕራብ በምትገኝ ሚሪዌዘር የምትባል ከተማ ነው።»

«ታዲያ አሜሪካ በስተደቡብ ውስጥ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ውስጥ የኖረ ሰው እንዴት ለንደን ውስጥ ወዳጅ ሊኖርህ ቻለ?»

«እናቴ አየርላንዳዊ በመሆኗ ከልጅነቴ ጀምሬ በተደጋጋሚ ወደ እንግሊዝ ሄጂያለሁ። ጓደኛዬም የአባቴ ጓደኛ ልጅ ነው።»

«የእነዚህ ሁለት ግለሰቦች ስም ማን ይባላል?» ጠየቀ ሚንዝ።

«የጓደኛዬ ስም ስፔንሰር ዊልክስ ሲሆን ለንደን ውስጥ የቡና ቤት ባለቤት ነው። የአባቱ ስም ሰር ማርቲን ዊልክስ ሲሆን የሌበር ፓርቲው የፓርላማ አባል ናቸው። አባቴ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ቦምብ ጣይ አይሮፕላኖችን ያበር ነበር። ጓደኝነታቸው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው።» ለሚንዝ ጥያቄ ምላሽ እንዲሆነው ሊ የሁለቱንም ሰዎች አድራሻ ሰጠው።

«ስራህ ምንድን ነው ሚስተር ሊ?» ሲል ክራመር ጠየቀ።

«ጠበቃ ነኝ፣ ዲሊኖ ውስጥ ከአባቴ ጋር በሽርክና እሰራለሁ። ሽርክናችን ሊ እና ሊ የሚል ስም አለው።» ብሎ ከኪሱ የስራ አድራሻውን አወጣ።

«ምን ዓይነት የህግ ሥራ ነው የምትሰራው?» አለ ክራመር።

«ከሁሉም አይነት ትንሽ ትንሽ። ትንሽ ከተሞች ውስጥ የተለመደ ነው። ኑዛዜዎችን፣ ፍቺዎችን፣ የሥራ ውሎችን እናወንጀል ነክ ጉዳይዎች ላይ

http://ethzare.wordpress.com

ነው::» ሊ፣ ክራመር የተባለውን ሰው እንደሚያውቀው እየተሰማው ነው፣ የእንግሊዛዊ፣ አንጋፊ ደግሞ የበለጠ ይህን ስሜቱን ጨመረበት::

ክራመር መጠየቁን ቀጠለ:: ሚንዝ ማስታወሻ ይመስጻል:: ሊ የህይወቱን ታሪክ ማለት ይቻላል ተረከላቸው:: ሊ ድንገት፣ ይህን ሰው የሚያውቅበትን ስፍራ አስታወሰና የማይመስል ነገር ነው ብሎ ሀሳቡን ተወው:: ጻሩ ግን ውይይታቸው እየቀጠለ ሲመጣ ይህን ሀሳብ መልሶ ቀየረው:: ሰውየው የKGB አባል ነው:: ሊ እውነታዎችን ብቻ ለመናገር ባገኘው ዕድል ተደስቷል፣ ፍርሀት እንጻይሰማው ገድቦታል::»

«መልካም ሚስተር ሊ፣» አለ ማጆሮቭ፣ ከተቀመጠበት ተነስቶ:: «ለጊዜው ማወቅ የሚያስፈልገን ይህ ብቻነው:: ፓስፖርትህንና ሌሎች የመታወቂያ ወረቀቶችህን እወስድና ለአለቆቼ የተወሰኑ የስልክ ጥሪዎችን እደርጋለሁ:: እስከዚያው እንድ ጠላቂ ዋናተኛ የሞተርህን መዝውር እንጺያፀጻልህ አደርጋለሁ:: የነገርከኝ እውነት ከሆነ ቀጣይ እርጻታ ልናደርግልህ እንችል ይሆናል:: በተናገርከው ላይ የምትጨምረው ነገር አለ?» «የለም፣» አለ ሊ፣ «ግን ልታስበው የምትችለውን አይነት ማንኛውንም ጥያቄ ለመመለስ ዝግጁ ነኝ:: ስለራሴ የምለው ሁሉ ትክክለኛ መሆኑን ላረጋግጥልህ እወጻለሁ:: በሀገሮቻችን መሀከል ብዙ ያለመተማመን እንጻለ አውቃለሁ፣ ግን የነገርኩህ እውነት ነው:: የምፈልገው መሄድ ብቻ ነው::»

«እስኪ እናያለን፣» አለ ማጆሮቭ፣ ወደጀልባዋ ጋቢና ወጥቶ ወደቡ ጣውላ ላይ ወጣ:: «ከጀልባህ እንጻትወርድ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ ቦታው ይለማማህል? የምትፈልገው ነገር አለ?»

«በጣም ይለማማኛል አመሰግናለሁ:: ሰብዙ ሰዓት ነቅቼ ስለቆየሁ እንቅልፍ ባገኝ እወጻለሁ::»

ማጆሮቭ መስማማቱን ራሱን ወዝውዞ በወደቡ ላይ መራመድ ጀመረ:: ያን ጊዜ ነበር ሊ ያስጨነቁትን ሁለት ነገሮች የተመለከተው:: ወደቡ መጨረሻ ላይ ጠበመንጃ መሰል ነገር ያነገበ የታጠቀ ወታደር ቆሟል::ይህ የኮሌጅ ካምፓስ አይደለም:: ሌላው እይታ ደግሞ ከአንዲት ትንሽ ጀልባ የሚወጣ ሰው ነበር:: ሊ ወደ ታች ወረደና የርቀት ማሳያ መነፅሩን ይዞ ተመለሰና ወደተመለከተው ሰው እንጣጠረው:: በጣም ያውቀዋል::

ሊ መነፅሩን ቦታው መለሰና በካርታ ጠረጴዛው ላይ ዘፍ ብሎ ተቀመጠ ማጆሮቭን ኬት አሳይታው ከነበረው ፎቶግራፍ አስታውሶታል:: ነገር ግን ስቶኮልም ላይ ያገኘው የኒውዮርኩን ካርል ስዊንሰንን እዚህ ቦታ ላይ ማግኘቱ እጅግ ርትሞታል:: ማጆሮቭ የKGB አባል ከሆነ፣ ስዌንሰን ሰላይ ነው ማለት ይሆናል:: ታዲያ የመጣው የት ስፍራ ላይ ነው? ስቶኮልም ውስጥ ያለውን የቀናውን ቤተመንግስት ስዕል መልከት እደረገና፣ ከካርታው ጠረጴዛ ስር አስገባው:: አሁን፣ ይህን ስዕል ጻግመኛ ሲመለከተው ሌላ ነገር ተመለከተበት:: በሳሎኑ ሶፋ ላይ ጋደም ብሎ ትራስ ደገፍ አለ:: እዚህ ስፍራ ውስጥ በተገኘበት አጭር ጊዜ ውስጥ ከመጠን ያለፈ ብዙ ነገር ተመልክቷል:: ከዚህ በላይ ምንም ነገር መመልከት አልፈለገም::

ማጆሮቭ በሳልፍ ጋሪው ሆኖ ወደባህሩ አቅጣጫ ሲሔድ አፒቼላ ከመስኩቱ ሆኖ ተመልክቶታል:: ያለው ጊዜ አሁን ሲሆን እንደሚችል አሰበ:: የእንግጻ ማረፊያ ቤቱን ትቶ በመውጣት በኮረብታው ሽቅብ ወደዋና መምሪያው አመራ:: በአሁኑ ወቅት በማሊቡ ዙሪያ እሱን የማያውቅ የለም፣ ከተከለከለባቸው ስፍራዎች ገለል ብሎ እስከኖረ ድረስ የት ገባ የት ወጣ የሚጠይቀው የለም:: የበላይ መምሪያው ህንፃ ውስጥ፣ በእንግጻ መቀበያ ክፍሉ ውስጥ የተቀመጠውን የስልክ አፕሬተር አልፎ ሄደ:: ክፍሉን አልፎ ሁለት ማለትም የማጆሮቭ ቢሮና የመሰብሰቢያ አጻራሹ ይገኛሉ:: ስራውን ሲያከናውን የቆየው እዚሁ ክፍል ውስጥ ነው::

«እንደምን አደርሽ የኔ ውድ፣» አለና የስልክ አፕሬተሯን ቢፈግታ ተመልከቷት:: «ማጆሮቭ አለ?» ሲል ጠየቃት::

«አሁን የለም፣ ሚስተር አፒቼላ፣» አለች ሴቲቱ ለፈግታው አፀፌታውን እየመለሰች:: «ባህሩ ላይ ነው::»

«ነው? በዚህ ዓይነት ሦስት ጀልባ ይዞ ሊወጣ ነው? ጥሩ ሀሳብ አይደለም::» ነው እንዴ?»

«አይደለም፣ እንደእውነቱ አንድ የሌላ ሀገር ጀልባ በመምጣቷ ከካፒቴይኑ ጋር የሚነጋገረው እሱ ነው:: መቼ እንደሚመለስ ርግጠኛ አይደለሁም::»

«ችግር የለም፣» መለሰ አፒቼላ:: «ብሞደሙ ላይ የማደርገው ሙከራ አለ:: የስብሰባ አጻራሹን መስመር ከውጭ መስመር ጋር ታገናኚልኛለሽ?»

«አዝናለሁ ሚስተር አፒቼላ፣» አለች ልጅቷ:: «ከውጭ መስመር ጋር ከማገናኘቱ በፊት ከማጆሮቭ ፈቃድ ማግኘት አለብኝ::»

«እንዴታ፣» አለ ልቡ እየደለቀች:: «ጥሪ ማድረግ ፈልጌ ሳይሆን የሞደም መስመሩን ለመሞከር ያህል ነው:: ከፈለግሽ ማጻመጥ ትችያለሽ፣» ብሎ ማራኪ ፈገግታውን ለገሳት:: «አንድ ቃል አልተነፍስም፣ ቃል እገባልሻለሁ::»

«እሺ ማጻመጥ ከቻልኩ ይሁን::»

አፒቼላ በሩን ሳይዘጋ ወደስብሰባ አጻራሹ ገባ:: የመዛግብት መላኪያ ፕሮግራሙን የያዘ ፍሎፒ ዲስኩን ከሻንጣው አወጣና ወደ ኮምፒውተሩ አስገባው:: ከአጠገቡ ያለውን የጠረጴዛ ስልክ አንስቶ አላቀቀውና የማገናኛ መሳሪያ አውጥቶ በቀጥታ መስመሩን ከኮምፒውተሩ ጋር አገናኘው:: ከዚያም የመዛግብት መላኪያ ዝርዝሩን የአሜሪካን ሀገር አጻራጭ ቁጥር 0101፣ የኒውዮርክን 212፣ የምንጩን ማለትም በሜሪላንድ ሲልቨር ስፕሪንግ የሚገኘውን የመረጃ መዓከል ቁጥር መታ::

ከመዛግብት መላኪያ ፕሮግራሙ በመውጣት በዚያው ዲስክ ላይ አዲስ ፋይል ከፈተ:: ከዚያም ቀጣዩን ጽሁፍ ፃፈ::

ኖኔ ውድ

የምገኘው በባልቲክ የባህር ዳርቻ ላይ በሚገኝ ከመጠን ያለፈ ቅንጦት የሞላበት ተቋም ውስጥ፣ በብዙ መልክ መልካምና የሰፖርት ተክለ ቁመና ባላቸው ወንዶችና ሴቶች ተከብቤ ነው:: እኔ ወደርም እመለሳለሁ እያልኩ ቢሆንም እስተናባሪዬ ግን እንድቆይ የሙጥኝ ብሎ ይዞኛል:: እዚህ በጀልባ

http://ethzare.wordpress.com

መዝናናትና መዋኘት ይቻላል፣ ፀሐይዋም ግሩም ነች። እስተናባሪዬም የተለመደ እንግዳ ተቀባይነቱ አልተለየውም፣ ግን አሁን አሁን በጣም ሥራ ይበዛበታል። እግኙተሽ ይህን ዕፁብ ቦታ ብትመለኪ ደስ ይለኛል። ብዙ ልነገርሽ የምፈልገው ነገር ቢኖርም እስክምንገናኝ መቆየት ይኖርበታል። ይህን ጊዜ ናፍቄዋለሁ። የዚህን ማስታወሻ ልቅና ባዶነት ተመልክተሽ እንዳትቀየሚ፣ ግን በዚህን ወቅት ከዚህ በላይ ምንም ሳደርግ አልችልም።»

ኤሚሊዬ

አፒቼላ ፋይሉን ዘግቶ፣ የመላኪያ ፕሮግራሙን ዳግመኛ አስነሳው። «እሺ፣» አለ ወደ በሩ ፊቱን አዙሮ። «አሁን መስመሩን ልቀቂልኝ።»

«ለቅቄወቀለሁ፣» ብላ ከመስመሯ ላይ ተነስታ ክፍሉ በር ላይ መጥታ ቆመች።

«ምንድን ነው የምትሞክረው?»

«የአዲሱን ኮምፒውተር የሞደም ግንኙነት መስመር ብታት ለመፈተሽ ያህል ነው።» ብሎ ምንጩን የመረጃ ማዕከል ከፈተው። «ስሚ፣» አላት ልጅቷን፣ «ራሱን ሲፈትሽ ልታጸምጪው ትችያለሽ።» ኮምፒውተሩ ላይ ከሚገኝ የድምፅ ማጉያ፣ በመጀመሪያ የመደወያ ቍን ከዚያ ደግሞ ቁጥሮች ሲደውሉ ድምፅ ተሰማና ፀጥ አለ።

ይህ ማለት ኮምፒውተሩን እየሰጠው ነው ማለት ይሆናል። ከፊት ለፊቱ ባለው የኮምፒውተር ስክሪን ላይ ወደምንጪ እንኳን ደህና መጡ። የሚል ጽሑፍ ታየ።

አፒቼላ በቶሉ የ«ኮንተሮል» ቁልፉን ጪቁኖ ፊደልን 'P' ነካና መፃፍ ጀመረ።

አዲስ ፋይል

የአዲሱ ፋይል ስም? ኮምፒውተሩ ጠየቀው።

ኬት

ስክሪኑ ባዶ ሆነ። የኮምፒውተሩን የ'Enter' ቁልፍ ተጫንና፣ጻፈ። ለኬት የሚላክ

ፋይሉ ሲላክ ከዋናው የኮምፒውተሩ የመረጃ ማከማቻ አንድ ድምፅ ተሰማ በአሜሪካ የግንኙነት ሳተላይተ በኩል ያለፈው መረጃ ካሊቡ ከሚገኘው ይህ ኮምፒውተር በመነሳት ሜሪላንድ የሚገኘ ኮምፒውተር ደረሰ። ከዚያም አፒቼላ 'P'ፊደልን ተጫንና፣ ወደመዋቅሩ ተመለሰ። ፃፈ።

ውጣ እየመጣሁ ነው፣ ብሎ መድረሻ ኮምፒውተሩ መልእክት ላክ፣ ተገናኝተው የቆዩበት ጊዜ: 25 ሰከንዶች፣ ካለ በኋላ ደግሞ ባዶ ሆነ።

አፒቼላ የራሱ ኮምፒውተር ላይ የሚከተለውን ፃፈ።

ኬትን ደምስሰው።

ፋይሉ ተደምስሷል፣ ሲል ኮምፒውተሩ መለሰ።

ተሳክቶለታል፣ ያደረገውን የሚያሳይ ምንም ፍንጭም አልተወም። በፋይሎቹ ውስጥ የወረራውን እቅድ እስመልክቶ መረጃ መላክ ፈልጎ ነበር። ግን ሶቪየቶች ምን ዓይነት የጠለፋ ማጣሪያ መንገዶች እንዳላቸው አያውቅም። ጎበዝ ከሆኑ ከሊማቡ ወደአሜሪካ እንደተደወለ ማወቅ ይችላሉ፣ ግን ደግሞ ይህ ከስተት በየቀኑ የሚቆጠር ሲሆን ይችላል። በጣም ጎበዝ ከሆኑ ደግሞ

መልዕክቱን ሊያገኙት ይችላሉ። አትኩሮትን የማይቀሰቅሰውና የማያስጠረጥር ቢሆን ብሎ ተመኘ።

«በቃ ይኸው ነው፣» አላት ለልጅቱ። «ሁሉ ነገር ተስተካክሏል።»

«ጥሩ፣» መለሰች ልጅቷ። «ውይ ሚስተር አፒቼላ ከአልጋ ጋር መሆን ከለለቸህ፣ እባክህን ንገረኝ እሺ?»

«የኔ ውድ፣ እንዲት አስደሳች ሀሳብ ነው፣» አለና። «በዚያ ተማመኚ።» ከተቀመጠበት ተነስቶ የሥራ ቦታውን አሰነዳዳ። አሁን ፀሐይዋ ብርሀኗን በመስኮቶቹ አሳርፋ ፈንጥቃለች። «አየሩ እየተስተካከለ ይመስላል። ቀና ልዋኝ መሰለኝ። አብረን እንዋኝ?»

«ብችል በጣም ደስ ይለኝ ነበር፣» አለች።

«በቃ ሌላ ቀን እናደርገዋለን።» ከክፍሉ መውጣት ጀመረና፣ ቆመ። «እስኪ ንገረኝ፣ የኔ ቆንጆ፣ እዚህ ያለው የኮምፒውተር መስመር ቁጥርና የህገሪቱ መለያ ቁጥር ስንት ነው? ማጆሮቭ የሞደም ግንኙነት መስመሩን ከዚያኛው ጫፍ እንድሞክር ጠይቆኛል።»

ቁጥሩን ፈልጋ፣ ማስታወሻ ላይ ፃፈችለትና ሰጠችው።

እጇን ሲሰማት ተሽከረመመች። ከሕንፃው ወጥቶ ሄደ። ጀንበሯ ብቅ ጥፍት ትላለች፣ ሰማዩ እየጠራ ነው። የማጆሮቭ የጎልፍ ጋሪ በሰው ሰራሽ ሀይቁ መጊያ ላይ እንደቆመች ነች። ወደማረፊያው ተመልሶ የዋና ልብሱን ለወጠና ወደባህር ጸርቻው ፎጣውን ይዞ ሄደ። በጣት የሚቆጠሩ የማሊቡ ወጣት ወንዶች ፀሐይ ይሞቃሉ። ከእነሱ ፈንጠር ብሎ ፎጣውን ዘረጋና ተቀመጠ።

«ምንድን ነው ነገሩ?» ወደ ባይተዋሯ የመዝናኛ ጀልባ እየጠቆመ።

«እንድ ጀልባ መንገድ ስታ ነፋስ ይሏት መጥቶ ነው። ጀልባዋን ጎትቶ ያመጣው ሰው እንደሚለው ከሆነ ሰውየው እንግሊዛዊ ወይንም አሜሪካዊ ሳይሆን አይቀርም።»

«እስኪ ገምተው፣» አለ አፒቼላ። «ስንት ሰው ይዛለች?»

«ብቻውን መሰለኝ። ቀውስ መሆን አለበት።»

አፒቼላ ክርኖቹን ተደገፈና ወደባህሩ ተመለከተ፣ ጀልባዋ ላይ አልፎ አልፎ አየኖቹን ይጥላል። አንድ የተጠቀ ወታደር መጣና በባህር ጸርቻው ማጊያ ላይ ዘብ ቆመ። በመጨረሻ፣ ማጆሮቭና ጆንስ የተባለው ሰው ጀልባዋን በመትው በኮረብታው ሽቅብ የጎልፍ ጋሪውን ተሳፍረው መጡ። አፒቼላም ተነስቶ ወደማረፊያው አመራ። ከዚህ ሆኖ የባህሩ ጸርቻ ይታየዋል። ስኒ ቡና ይዞ በረንዳው ላይ ተቀመጠ።

38

ሔልደር የደረሰውን ጥሪ ተቀብሎ ማጆሮቭ ቢሮ ደረሰ። ስለስብሰባው ርዕሰ ጉዳይ የሚያውቀው ባይኖርም፣ ማጆሮቭን ለማግኘት ግን አልፈለገም። ሁለቱም ከሞስኮ ከተመለሰ በኋላ ሲገናኙ የመጀመሪያቸው ይሆናል። ሔልደር ይህ ሰውዮ በትሪና ራጉሊን ላይ በፈፀመው ግፍ የተነሳ የተለማው ቁጣ አሁንም በውስጡ ታፍኖ ይንተከተካል። ሔልደር ከማጆሮቭ ቢሮ በር ሲደርስ ማጆሮቭና ጆንስም መጡ።

http://ethzare.wordpress.com

«እሺ፣ ሔልደር፣» አለ ማጆሮቭ፣ «ግባ፣ ግባ።» በሀሳብ የተዋጠ ይመስላል። እየመራ ቢሮው ይዞት ገባ። «ተቀመጥ፣ አንድ ጊዜ ይቅርታ አድርግልኝ፣ አንድ መፍትሔ የሚሻ ሁኔታ ገጥሞናል።» ወደጆንስ ዞረና «ሚስተር ሚንዝ፣ ምን ይመስልሀል?»

«በመዓከላዊው ጣቢያ ሙሉ ቃለ መጠይቅ እንዲደረግለት ወደሞስኮ ልንልከው ይገባል ብዬ አስባለሁ። በዚህን ወቅት አንድ አሜሪካዊ በራችን ድረስ የመምጣቱ ድንገተኛ ግጥምጥሞሽ ብቻ ነው ለማለት ያስቸግረናል፣ አይደለም?»

ማጆሮቭ ጠረጴዛው ላይ ከወረወራቸው ወረቀቶች መሀል አንድ ትንሽ ካርድ አወጣና «ልክ ልትሆን ትችላለህ። ቢሆንም. . .» ሰዓቱን ተመልከቶ፣ ሒሳብ እንደሚያሰላ ሁሉ አሰብ ካደረገ በኋላ፣ ስልኩን አነሳ። «የውጭ መስመር አገናኚኝ።» አለ።

ካርዱን እየተመለከተ ቁጥሮቹን ሲመታ ከቆየ ብኋላ የድምፅ ማጉያውን ከፈተው።

ሔልደር ቁጥሮቹ ሲደውሉና ከዚያም እንዲት ሴት ስትናገር ድምፅ ሰማ።

«ደህና አደርክ ሊ እና ሊ።»

«ደህና አደራችሁ፣» አለ ማጆሮቭ የአነጋገር ቃናው የበለጠ ወደእንግሊዛዊ እያደላ። «ሚስተር ሊን ማናገር እችላለሁ?»

«የትኛውን ሚስተር ሊን ነው የፈለግከው? ቢሊን ወይንስ ዊልን?»

ማጆሮቭ ጆንስን መልከት አደረገውና «ሚስተር ዊልን ነበር እባክዎን?»

«ይቅርታ፣ ግን ዊል ከሀገር ውጪ ነው። አጋሩ አሉ እሳቸው ሊረዱህ ይችላሉ?»

«አይ፣ የግል ጉዳይ ነው። የድሮ ጓደኛው ነኝ፣ የምደውለው ከለንደን ነው። ከሀገር ውጪ ዊልን የት ሳገኘው እንደምችል ሊነግሩኝ ይችላሉ?»

«አንድ ጊዜ ይቆዩኝ፣ የጉዞ አቅድ ማስታወሻውን ላምጣ።» ወረቀቶች ሲንኮሻኮሹ ተሰማ። «ይሻውና፣ እሺ በእቅዱ መሠረት ከሆነ አሁን በጀልባ እየተጓዘ ይሆናል፣ ከሰሰት ቀን በኋላ ኮፐንሀገን ይገባል። እዚያ ያለው ሆቴል ቁጥር አለኝ።»

ማጆሮቭ ቁጥሩን ፃፈ። «አመሰግናለሁ፣ እዚያ ሳገኘው እሞክራለሁ። ደህና ይሁኑ።» ስልኩን ዘግቶ ካርዱን እየተመለከተ በሀሳብ ተውጦ ቆየ።

ሔልደር ዊል ሊ በሚለው ስም ተገርሞ፣ መናገር ተስኖታል። «ይህ ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም።» አለ ጆንስ። «ሰላይ ከሆነ ሽፋን ማበጀት ቀላል ነው። ኮፐንሀገር የሚገኘው ሆቴልም በስሙ የተያዘ ክፍል እንደሚኖረውም አያጠራጥርም።»

«ጥርጥር የለውም፣» አለ ማጆሮቭ፣ «ግን ሌላ ነገርም አለ። የመጀመሪያ /ዋና/ ጸይሬክቶሬት በነበርኩበት ወቅት የአሜሪካዊ ፖለቲከኞችን በተለይም ለፕሬዚዳንትነት ብቃት ያላቸውን መረጃ በየጊዜው እናጠናቅራለን። በስልሳዎቹ ውስጥ የምክትል ፕሬዚዳንት ሊንደን ጆንስን ይተካል ተብሎ የሚታሰብ አንድ የጆርጂያ ገዢ ነበር። በ1964 ከጆን ኬኔዲ ጋር ለዲሞክራቲክ ፓርቲው ተወዳድሯል። ዊልያም ሔነሪ ሊ ይባላል፣ ወይንም ቢሊ። ይህ ጀልባው ውስጥ ያገኘነው ሰው የሱ ልጅ መሰለኝ።»

«ይህ ሁሉ ሽፋን ነው አያልኩህ፣» አለ ጆንስ በመርዘኛ አነጋገር። «በትክክለኛ ሰው ስም ሽፋን ሰጥተውት ነው፣ በቃ። ሌሔልደር ከሰጠነው ሽፋን በምንም የተለየ አይደለም።»

«ይቅርታ ጌታዬ፣» አለ ሔልደር፣ «ግን ይህን ዊል ሊ የተባለ ሰው የማውቀው መሰለኝ።»

«ምን?» አለ ማጆሮቭ በአግራሞት ተውጦ።

«ስቶኮልም ውስጥ አያለሁ ነበር ያገኘሁት። በአጋጣሚ አንድ ምግብ ቤት ውስጥ ጠረጴዛ ተጋርተናል።»

ማጆሮቭ ስለግንኙነታቸው ዝርዝር ታሪክ ማወቅ ስለፈለገ፣ በእትኩሮት ሊያዳምጡ ቆዩ። ሔልደር ተናግሮ ሲጨርስ ጆንስ ተቀበለው።

«ይህ አጋጣሚ ነው ለማለት የሚከብድ ነው፣» አለና «ይህን ሰው ወደሞስኮ መላክ እንጂ መልቀቅ የለብንም።»

«እይሆንም፣» አለ ማጆሮቭ። «ታስቦበት የተደረገ ነገር እንዳልሆነ ግልፅ ነው፣ አይታይህም? ይህ ግንኙነታቸው ታቅዶ የተደረገ ከሆነ ሔልደር ስቶኮልም እንደሚመጣ ቀድሞ ታውቆ ነበር ማለት ይሆናል። ሔልደር ስቶኮልም መድረሱን እኛ እንኳን አላወቅንም። ቀድሞ ለመታወቅ የሚችል ቢሆን ኖሮ እንኳን፣ እና አጋጣሚ ባይሆን እንኳ በሰላም ባለቀቁት ነበር። በቦታው ላይ ኳን በቁጥጥር ስር በዋለ ነበር።»

ጆንስ ለዚህ ጥያቄ መልስ አልነበረውም። «ልክ ልትሆን ትችላለህ። ግን አሁንም መልቀቅ የለብንም። ለመንቀሳቀስ የቀረን ጥቂት ጊዜ ነው።»

«ምናልባት ርምጃ ለመውሰድ ጥቂት ስለቀረን መልቀቅ የለብን ይሆናል፣»

«እዚህ ሰፍራ ላይ ምንም አልተመለከተም፣ ከጀልባው አልወጣም መርከብ ማቆሚያዎቹ ከባህሩና ከባህር ዳርቻ አይታዩም። የደንብ ልብስ ከለበሱ አንድ ወይ ሁለት ሰዎች በቀር ሌላ ምንም አልተመለከተም። እሱን ለመልቀቅ መፍቀዳችን በጣም ቅን መሆናችንን ሊያሳይ ይችላል። የአንድን አሜሪካዊ ፖለቲከኛ ልጅ ይዞ መቆየቱ አላስፈላጊ ውስብስብነት ሊፈጥር ይችላል።» ብሎ ማጆሮቭ በመጻፉ ጠረጴዛውን መታው። «አይሆንም ዛሬውኑ ከዚህ እናስወጣዋለን። ራሴ አደርገዋለሁ፣ መጀመሪያ ግን ሔልደርን ማናገር ይኖርብኛል። እባክህን ጆንስ ይቅርታ አድርግልኝ።»

ጆንስ ራሱን እየወዘወዘ ወጥቶ ሔደ።

ማጆሮቭ ፊቱን ወደሔልደር አዞረ። «ጃን፣ ነገ እንሔዳለን።»

ሔልደር አይኖቹን አርገበገበ። «ነገ? ቀደም ብሎ ሳይነገረኝ?»

ማጆሮቭ ፈገግ አለ። «አይደለም። ቀደም ብሎ ከዚህ በፊት ሊገለፅልህ አይችልም። ለብዙ ሳምንታት፣ ለተከታታይ ልምምድ በሚል ሰበብ፣ ሰራዊቶችንና፣ ስንቅና ትጥቅ ወደባልቲክ ግዛት ስናስገባ ቆይተናል፣ የስለላ ሀይላችን እንደሚናገረው ከሆነ የምዕራባውያኑ ሀይላት በእነዚህ እንቅሲቃሰዎቻችን አልተደናገጡም። ግለትም በስዊድንም ሆነ በሌሎች ሰፍራዎች ምንም ዓይነት ያልተለመደ ቅድመ ጥንቃቄዎች አልተወሰዱም። ሁኔታዎች ለተልዕኮአችን ፍፁም የተመቻቹ ናቸው፣ አንተ ደግሞ የኔ ልጅ፣ የጠቅላላውን እቅድ ዋና ተልዕኮ የተሸከምክ ነህ።»

http://ethzare.wordpress.com

«ጌታዬ?» አለ ሔልደር ስለትሪና ራጉሊን ሙሉ በሙሉ ዘንግቶ። በተፈጠረው ሁኔታ በጣም ተገርሟል።

ማጆሮቭ ከጠረጴዛው በስተጀርባ ወደሚገኝ ማብሪያ ማጥፊያ በመሔድ ሲነካው ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ካርታ ብርሐን ሸቀቀበት። ካርታው ላይ የሚታየውን የስቶኮልም መቃረቢያ እያመለከተው። «እዚህ ስፍራ ላይ ሔልሲንኪ ስቶኮልም የንዝ ማመላለሻ ጀልባ ተከትለህ በቀድሞ ተልዕኮህ ጊዜ የሔድክበትን መስመር ሳትለቅ ትንዛለህ። ከቀድሞው የሚለየው አሁን የዊስኪ ደሪጃ ሰርንጅ መርከቧ አዛዥ መሆንህን ብቻ ነው። መርከቧን ተከትለህ የጥቂት ኪሎሜትሮች ርቀትን እስክዚህ ነጥብ ድረስ ትሄዳለህ። ዝም ብሎ ትንሽ ቆየና። «እዚህ ስትደርስ ሰርንጇን ወለሉ ላይ ታሳርፋለህ።»

ከባድ ድንጋጤን ሊፈጥርበት ቻለ። «ባህሩ ወለል ላይ ጌታዬ? ሆነ ብዬ?» አንድን የሰርንጅ መርከብ አዛዥ የቅጣት ግዳጅ ላይ ለማስቀመጥ ከዚህ የበለጠ ፈጣን መንገድ የለም። ጉሺኔ የተባለ የክፍል ጓደኛው ይህንኑ አድርጎ እንደነበር አስታወሰ። አሁን በማሊቡ የሰርንጅ መርከብ ማቆሚያ ውስጥ ደስተኛና ወፍራም ሆኖ ይኖራል።

«ከዚያም፣» አለ ማጆሮቭ፣ «ከዚያም የምታደርገውን የሚከተለውን ይሆናል።»

* * *

ሊ የመዝናኛ ጀልባው በከባድ ሁኔታ ሲቆረቆር ሰምቶ ከእንቅልፉ ነቃ። ከመኝታው ዘሎ ተነስቶ ወጣ። የKGBው ማጆሮቭ ወደቡ ላይ ቆሟል።

«ተከተለኝ፣» አለው።

ሊ ጭንቀት ወጥሮት በወደቡ ላይ ተከትሉት መራመድ ጀመረ። የታጠቀው ወታደር አሁን የለም። ማጆሮቭን ተከትሉ ከወደቡ በተጓዳኝ የሚገኝ ረጅም ጸሰ ውስጥ ገባ። በጸሱ ውስጥ ትልቅ የምትባል የመዝናኛ ጀልባ መቀመጫዋን አራት ሰዎች የዝገት መከላከያ እየቀቡላት ተቀምጣ ተመለከተ። ከጀልባዋ አጠገብ የጀልባ ሽራ መወጠሪያ ዋልታ ይገኛል።

«ይህኛው ከእንተ የሽራ ዋልታ በተወሰኑ ጫማዎች ያነሰ ነው ብዬ አስባለሁ። ግን ማስተካከያ ቢደረግለት ለጀልባ ተስማሚ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለኝም።» አለ ማጆሮቭ። ለሰዎቹ በሩሲያ ቋንቋ ትዕዛዝ ይሰጣቸው ጀመር። ቀለም ይቀቡ የነበሩት ሁሉ መሳሪያዎቻቸውን ጥለው መሽቆጥቆጥ ጀመሩ። «ይህኛው ሰው ትንሽ እንግሊዝኛ ይችላል፣» አለ ወደ አንደኛው እያመለከተ። «ጀልባህን ወደዚህ እናመጣና ከሬናችንን ተጠቅመን ዋልታውን እናስርልሀለን። ሁሉን ነገር ያስተካክሉልሀል።»

«ስለእርዳታህ ተደስቼያለሁ ሚስተር ክሬመር፣» አለ ሊ፣ በልባዊ ስሜት። «እንድሄድ ላደረግክልኝ ሁሉ የተሰማኝን መግለፅ አልችልም። የእቃዎቹን ዋጋ ብከፍል ደስ ይለኛል።»

ማጆሮቭ ፈገግ አለና። «ለህገሮቻችን ግንኙነት ማጠናከሪያ ቁጠረው።» አለና። «ግን በተቻለ ፍጥነት መሄድ አለብህ። ሰዓቱን ተመለከተ።

«እስክ እኩለ ለሊት ድረስ እንድትሔድ እናደርጋለን።»

«ለኔ ይስማማኛል። አሁኑኑ ስራ እጀምራለሁ።»

ማጆሮቭ የሊን እጅ ጨበጠ። ደህና ሁን ሚስተር ሊ። ጸማሞኛ እንገናኝም።»

ይህ ለእኔም ይስማማኛል ብሎ አሰበ፣ ሊ።

39

ሩል ምንጩን ጸማሞኛ ከመመልከቷ በፊት ለሥራ እስክትዘጋ ድረስ ጠበቀች። ከአፒቼላ ሬክሬታሪ ዐሐፊ የገረማትን የስልክ ጥሪ ደርሷታል። ሴትየዋ እንዳለችው ቀጠሯቸው ላይ መገኘት እንዳልቻለና፣ ለመዝግየት መገደዱን ነው። ይህንን የተመለከተችው ብዙም ውጤት እንዳላገኘና ተጨማሪ ጊዜ እንደሚፈልግ አድርጋ ነበር። ምናልባት ስለ ተልዕኮው ያለውን ሀሳብ ለውጦ ይሆን፣ ምናልባት ሁኔታውን ሲመለከተው ማጆሮቭ መደናገጥን ፈጥሮበት ሊሆን ይችላል። ቢሆንም «ምንጩ» ውስጥ ያለውን የአፒቼላን ፋይል በቀን ሁለት ጊዜ ትመረምረዋለች። ምንም ነገር የለም።

አሁን ጥናት ክፍሏ ውስጥ ተቀምጣ ኮምፒውተሯን አስነሳችና የአፒቼላን የይለፍ ቃላት ተጠቅማ ከ «ምንጩ» ጋር ተገናኘች።

ወደ «ምንጩ» እንኳን ደህና መጡ፣ አለ ኮምፒውተሩ።

ዶሴዎችን እንዲያሳያት በዕሁፍ አዘዘችው።

ከዚህ በፊት የተመለከተቻቸው ዶሴዎች ናቸው። መጨረሻ ላይ ግን ኬት የሚል ዶሴ አየች። ተሳክቶላታል! በፍጥነት መልዕክቱን አነበበችው። እንዳይታወቅበት መፍራቱን በግልጽ የሚያሳይ ጽሑፍ ነበር። ፖስት ካርድ መሰላት። ቢሆንም ግን ከማጆሮቭ ጋር መሆኑንና፣ ባልቲክ ውስጥ አንድ ነገር እየተደረገ እንደሆነ በግልፅ የሚያሳይ ሆኖ አገኘችው። መልዕክቱን በወረቀት እትማ ከ «ምንጩ» ወጣች።

ላንግሊ እስክትደርስ ድረስ በጓላ መስታወቷ ስትመለከት ብትቆይም የሚከተላትን ሰው አጣችው። ባለፉት ጥቂት ቀናት ወስጥ እንድ ሁለት ጊዜ አይታዋለች። ግን ባልተለመዱ ጊዜያት። በተመቸው ጊዜ ብቻ እየተከታተላት መሆኑ ታውቋታል። እየዘነበ ነበር፣ ስለዚህ በድርጅቱ የመሬት ስር መኪና ማቆሚያ ውስጥ መኪናዋን አቆመችና፣ መተሩን አጠፋች። ከመውጣቷ በፊት ግን የጎን በሩ ተከፈተና ኤድ ራውልስ ገባ።

«ታዲያስ፣ ልጂት፣» አለና «መንገድ ላይ ሆኜ አይቼሽ ነው። ደህና ነሽ?»

«አስፈሪ ነገር ነው ኤድ። ነገሮች ትክክል መሆናቸውን እያረጋገጥኩ ነው፣ ግን ማንም ርምጃ እንዲወስድ ለማስገደድ አልቻልኩም።» ማጆሮቭ በስፔትናዘ ኮማንደርነት መሾሙንና ከባልቲክ ውስጥ ስለተከማቸው ስራዊት ገለፀችለት።

«ልክ ነሽ፣» አለና። «ይህ መረጃ ኃይልን ለመሰብሰብ በቂ አይደለም። ታዲያ ምን ዓይነት ርምጃ እንዲወሰድ እንደምትፈልጊ ንገሪኝ?»

«ከዚህ በፊት፣ የተልዕኮዎች ክፍል መረጃ የሚያሰባስቡ ሰዎቹን እንዲያሰማራ ፈልጌ ነበር። ሶቪዮች እያደረጉ ያሉት ከታወቀ ለማስቆም ሊጠ ቅም ይችላል ብዬ ነበር። አሁን ግን ጊዜው ይህን ለመሰለ ነገር የዘገየ ይመስለኛል። ጊዜ ሳያጣክኑ አሁኑኑ የሚንቀሳቀሱ ይመስለኛል። አሁን መደረግ ያለበት ተመራጩ ነገር ነገሩን ወደፕሬዚዳንቱ በመውሰድ ስዊድናች

http://ethzare.wordpress.com

እንዲያውቁት ማስጠንቀቂያ እንዲላክ ማድረግ ነው:: ወይ ይህንን፣ ማድረግ አለዚያ ደግሞ፣ በቀጥታ ለስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትር ደውሉ እየተደረገ ስላለው ነገር ማሳወቅ ነው::»

«ግለት እንቺ እየተደረገ ነው ብለሽ ስለምታስቢው?»

«እም አመሰግናለሁ ኤድ ቀዝቃዛ ውሀ እንድትቸልስብኝ ነበር የምፈልገው::»

«ሶቭየቶች ርምጃ ሊወስዱ ነውብለሽ ያሰብሽው ለምንድን ነው? አዲስ ነገር ደርሶሻል?»

እንገቷን በአዎንታ ወዘወዘች:: «ማጆሮቭ ካምፐ ውስጥ አንድ ሰው አለኝ::» የራውልስ ቅንድቦች ሽቅብ ተለጠጡ:: «ምን አለሽ?»

የአፒቼላን ደብዳቤ ከቦርሳዋ አወጣችና፣ ጣሊያናዊው ማጃሮቭ ዘንድ ስለመሂዱ አጫወተችው:: መልዕክቱም እንዴት እንደመጣ አብራራችለት::

ራውልስ ሳቀና:: «ወይ ግሩም፣ ሩሲያ ውስጥ ሰላይ ማሰማራትሽን ሳይመን ቢያውቅ በጣም ነው የሚናደደው!» መልዕክቱን አነበው:: «ይህ ሰው በጣም ፈጣንና ደፋር ነው:: ይህ ደብዳቤ ግን የሚያረጋግጠው ነገር የለም::

አስካር አስካርሰን የከሰአቱ ግብቂያ ጀምበር ዓይኖቹን እያጨናቆረ በመመልከት በሕይወት የሌለውን የልጅነልጅ ያናግራል::

«ያውልህ አቢ!» አለ፣ እያመለከተ፣ ከዚያም ራሱን ግራ ቀኝ ወዘወዘ:: «አይደለም፣ አይደለም፣ እንጨት ነው እንጂ ፔሪስኮፕ አይደለም::» የልጁ ንብረት በሆነው ዘመናዊ ባለስምንት ሜትር የሞተር ጀልባ በግማሽ ሀይል ብቻ በሀያ አምስት ኖት ፍጥነት እየተገፋች ትጓዛለች:: ጀልባዋ በሙሉ ሀይል አርባ ማይል በሰዓት መሂድ እንደምትችል አስካርሰን ጠንቅቆ ያውቃል:: ሞክሮታልም::

«ሁሉም ይመለከታሉ፣ አቢ፣» አሉ ሽማግሌው:: «ግን እናገኘዋለን:: እዚያ ነው ያለው፣ እኔና አንተ እናገኘዋለን::»

ልጁ መኖሪያ ቤት አካባቢ ያለው የውሀ ክልል ባለፉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ሥራ በዝቶበት ነበር የቆየው:: መጀመሪያ በሮያል የባህር ሀይሉ የአሰሳ ጀልባዎች፣ ከዚያ ደግሞ ትንሿን ሰርጓጅ ፍለጋ፣ ከዚያ ደግሞ ይህ ተሰፋ ሲያስቆርጣቸው፣ የመዝናኛ ጀልባቸውን ይዘው ሲያስጨንቁን ቆይተዋል:: አንድ ሰርጓጅ መርከብ በተመለከቱ ቁጥር ፔሪስኮቡን አብረው ይስተዋላሉ፣ ይህ የቅርብ ጊዜው ሰርጓጅ በታየበት ጊዜ ባህር ኃይሉ ይዘነዋል ብለው አስበው ነበር:: ግን እንደሌላ ጊዜው ሁሉ ምንም ውጤት ሳያገኙበት ቀሩ:: ሩሲያዊያኑ ጸጋመኛ እነሱን ማታለሉ ተሳክቶላቸዋል:: ከ1981 የ«ዊስኪ ኦን ዘ ሮክስ» ገጠመኝ በኋላ ጀምሮ፣ ከሰርጓጆች አንዳቸውም አልተያዙም፣ ሹፈሮቻቸውም ተገድለው ወይ ፎቶግራፍ ተነስተው አያውቁም፣ ግን ሩሲያውያን መሆናቸውን ሁሉም ያውቃሉ::

ከመዝናኛ ጀልባዎቹ መሀል ከሮያል ባህር ኃይሉ አባላትም በላይ ፕሪስኮፑን ከሩቅ ተመልክቶ መለየት የሚችል ከአስካርሰን ሌላ ማንም ያለም::

ከሱ ይልቅ ለዚህ ተግባር ብቃት ያለው ማንም የለም:: ሩሲያውያኑ የሚያፈቅረውን ነገር ሁሉ ወስደውበታል:: ስለዚህ ሊበቀላቸው ቆርጧል:: ጸግመኛ ከኤቢ ጋር በጀልባ መውጣቱ ደስ አሰኝቶታል:: ልጁ የነጻጅ ወጪውን ለመሸፈን ቅሬታ የለውም፣ የሽማግሌውን የሰርጓጅ መርከብ እደን ሳይቀር ይደግፋል:: አስካርሰን አንድ ምሽት እሱ የተኛ መስሏቸው ኩሽናው ውስጥ ሲነጋገሩ ሰምቷል::

«የፈለገውን ያህል ዋጋ ቢያስወጣኝ ግድ የለኝም፣» አለ ልጁ ለባለቤቱ:: «ከኤቢ ሞት በኋላ ክፍሉ ከሚገኘው ከዚያ ወንበር ላይ የሚያስነሰው ይህ ብቻ ነው፣ የሚያስጨንቀው ይኸው ነው፣ ይህን ልሰጠው ከቻልኩ እደርገዋለሁ::»

አስካርሰን ለራሱ ፈገግ ብሎ የዚያን እለት የተሻለ እንቅልፍ አግኝቶ አደረ በሚቀጥለው ቀን ጀልባዋን ይዞ ወጣ፣ ከዚያን ቀን በኋላም አየሩ ጥሩ በሆነ ጊዜ ሁሉ ጀልባዋን ይዞ መውጣት ቀጠለ፣ ኤቢ አብሮት ስለሚሆን ደስ ይለዋል:: ወይንም ቢየንስ እንኳ የኋላ ኋላ ሰርጓጅ መርከብ ሲያገኙ ይደሰታሉ፣ ማግኘታቸውም አይቀርም::

አስካርሰን ሀይል ሳይሰጥ የጀልባዋን መሪ እሽከረከረውና ጀልባው ያሰበለትን መስመር ሲይዝለት በቅልጥፍናው ተደነቀ:: ይህን የመሰለ ፈጣን ጀልባ ኖሮት አያውቅም:: ወዶታል:: በዚህ ጀልባ ሆኖ አንድ ሰርጓጅ ማግኘቱ አይቀርም:: እሱና ኢዲ:: ሲያገኝ ታዲያ . . . እርግጠኛ አይደለም፣ ግን የልጁ ባለሁለት አፈሙዝ ጠበመንጃ አጠገቡ ተቀምጧል:: መጪረሻ ላይ አንድ ነገር ማድረጉ አይቀርም::

የጀልባዋን አቅጣጫ መልሶ ወደ ቦዩ አዞረው:: ብዙ ሳይቆይ ቤቱ ይደርሳል አሁን አሁን የልጁን ቤት የራሱ እያለ ነው የሚያስበው:: ትኩስ ቼኮላትና ብራንዲ ይጠብቀዋል:: ነገ ደግሞ ነገ፣ እሱና ኤቢ ጸግመኛ ሰርጓጅ መርከቦችን ለማደን ይወጣሉ::

የጀልባዋ ተለዋዋጭ የሽራ መወጠሪያ ዋልታ በክሬን እየተሳበ ሲመጣ ከጀልባው ላይ የቆመው ዊል ሊ ይመለከታል:: እሱና ከሰራተኞቹ መሀል እንግሊዝኛ የሚናገረው ዩሪ፣ ጫቱን ይዘው ወለሉ ላይ ወጻለው ክፍተት እየሳቡ ከወሰዱት በኋላ - ሊ ወደታች ወርዶ እየጎተተ አስገባው:: ምንም እንኳን ከቀደሞው በመጠን የሚያንሰው ተለዋዋጭ ዋልታ ጀልባዋ ወለል ላይ ትንሽ ክፍተት ቢፈጥርም ከሞላ ጎደል ገጥሞ ይሄል ማለት ይቻላል:: ክፍተቱ ውሀ እንዳያስገባ ደፈኑት::

ዋልታው ጫፍ ላይ የታሰረው እጺሰ የሽቦ ገመድ በልክ ተቆርጦ ከጀልባዋ ሁኔታ ጋር ከተስማማ በኋላ ጠብቆ ታሰረ:: ሁሉ ነገር ተሰርቶ ሲፈፀም እኩለ ለሊት ሆነ:: ከዩሪ ጋር ሽራውን ወጠሩ:: ሽራዎቹ ሁለት ብቻ ናቸው፣ እንድ አነስተኛ ባለሶስት መዓዘን ሽራም አለ:: ከተወሰኑ ማስተካከያዎች በኋላ ሁሉ ነገር ቦታ ቦታ ያዘ:: ጀልባዋ ጸግመኛ ለጉዞ ዝግጁ ሆናለች:: መዘውሩም በጠላቂ ዋናተኛ አማካይነት ነፃ እንዲሆን ተደርጓል:: መጀመሪያላይ ታስራ

http://ethzare.wordpress.com

ወደነበረችበት የወደቡ መጨረሻ ወሰዷት። ዩሪና የሰራ አጋሮቹም የነዳጅና የውሀ ታንኩቹን ሞሉ።

«ከዚህ ኮፐንሀገን ርቀቱ ምን ያህል ነው?» ጠየቀው ዩሪ። አብሬሀ ልምጣ የሚል ያስመሰለው አጠያየቅ ነበር።

«የትም ካልቆምኩና እማካይ ንፋስ ካገኘሁ በሁለት ቀን ተኩል ጉዞ የምደርስ ይመስለኛል።»

ዩሪ ዙሪያውን በጥንቃቄ ተመለከተ። «እ፣ ዊል . . . መጽሔቶች አሉሀ?»

«እንዴታ ዩሪ። እስቲ እንፈልግ ምን ይኖር ይሆን?» ትንሽ ካሰፈለገ በኋላ የኒውዮርክና የታይም መጽሔቶችን አገኘ።

ዩሪ የከፋው መሆኑ ታየበት። «አይ፣ ዊል . . . ፕሌይቦይ ይኖርሀ እንደሁ ብዬ ነው።»

ዊል አሰብ አደረገ። በጣት የሚቆጠሩ መሰል መፅሔቶችን ፈልጎ አገኘ። እግረ መንገዱን ያገኘው የብሪታኒያ የመኪና መፅሔት ዩሪ ላይ ከሌሎቹ የላቀ ደስታን ፈጠረበት።

«በጣም እመሰግናለሁ ዊል፣ ግሩም ነው፣» አለ ዩሪ መጽሔቶቹን የልብሶቹ ውስጥ ኪሶች ውስጥ እያጨቀ።

ዊል ለሌሎቹ ሰራተኞች የሚሰጠው ነገር ፍለጋ ጀልባውን ፈታተሸ፣ ጥቂት ማስቲካዎች፣ ብዕሮች እና ጀክ የተባለ ዊስኪ አገኘ። ሁሉንም በደስታ ተቀበሉት። «ጓደኞችህ ቡና ትፈልጋላችሁ?» ጠየቀ ሊ።

«አይሆንም እባክህን መሄድ አለብህ። ጀልባዋ ዝግጁ በሆነች ሰዓት እንድትሔድ ትዕዛዝ ደርሶናል። መጀመሪያ ግን ለሸራ መወጠሪያ ዋልታው መፃፍ አለብህ።»

«መፃፍ?»

ዩሪ በምልክት አሳየው። ሊ ስለሚወስደው መለዋወጫ እንዲፈርም ፈልጎ ነው።

«እንዴታ ዩሪ የት ነው የምጽፈው?»

«ቢሮው ውስጥ።»

ሊ እና አራቱ ሰዎች ከጀልባው ወጡና ወደጀልባ መጠለያው አመሩ። በእንደኛው ጥግ አነስተኛ ቢሮ ትገኛለች። ዩሪ የወሰደውን መለዋወጫ በሙሉ በሩሲያ ቋንቋ ዝርዝሩን አሰፈረ። ሊ መዝገቡን ከፈረመ በኋላ፣ የእድራሻ ካርዱን ለዩሪ ሰጠው። «አለቃህ እዚህ ቦታ ላይ ደረሰኙን እንዲልክልኝ ንገረው፣ እሺ?»

ዩሪ በተርታ የተተከለ የወርቅ ጥርሶቹን ገልጦ ፈገግ አለ። «እሺ፣ አሁን እኔ ትንሿን ጀልባ እይዛለሁ፣ አንተ ተከተለኝ።» ብሎ በወደቡ ቁልቁል ተራመደ። ሊ ወደጀልባዋ በማምራት ሞተሩን አስነስቶ ለመንሳቀስ ሲዘጋጅ ሌሎቹ ገመዱን ፈቱለት። ሊ ወደቡን በሚለቅ ጊዜ፣ ማጆሮቭ በጎልፍ ጋሪው ሽቅብ እየነዳ መጥቶ ቆመና ሲመለከተው አየ። እጁን እያውለበለበ የምስጋና ቃላት ጮኸለት። ማጆሮቭም እጁን መልሶ አውለበለበለት። ሊ መሄድ በመቻሉ ብቻ ዕድለኛ የሆነ መስሎ ተሰማው። ዩሪ ፊት ፊት እጁን አውለብልቦለት ጀልባውን እዞረ።

ዊል በተቻለው ፍጥነት ድንበሩን አቋርጦ ስዊድን ውሀ ከልል ውስጥ ለመግባት ሲል አቅጣጫውን ወደምዕራብ አቀና። እዚያ ሲደርስ ወደዴንማርክ የሚወስደውን የደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ይይዛል። ከደረቅ መሬት ሙሉ በሙሉ እስከሚርቅ ድረስ ቀጥ ብሎ ሲጓዝ ቆየ። የሳይፓጃ መብራቶች በሰሜኑ ብርሀን ውስጥ ገብተው ከተዋጡ በኋላ ጀልባዋ ራሷን እንድትነዳ መስመር አስይዞ ሰጥቷት ቡና ሊያፈላ ወደታች ወረደ። ባለፉት ሃያአራት ሰዓታት ብዙ እንቅልፍ ባለማግኘቱ ቡና የግድ ያስፈልገዋል። ከላቲቪያ በመውጣቱ ከፍተኛ እፎይታ ተሰምቶታል። ቡናው እስከሚፈላ ድረስ ነቅቶ ለመቆየተ ይታገላል። ቡናው ሲፈላ ወደሾፌሩ ክፍል ተመልሶ አድማሱን መልከት ካደረገ በኋላ ቡና ቀዳና ካርታ ጠረጴዛው አጠገብ ተቀመጠ።

ቡናውን ጨረሰ። በቻርቱ ጠረጴዛው አጠገብ በተቀመጠበት ሳይፈልገው ትንሽ እንጎላጀ። ከፊት ለፊቱ አንስተኛ ያልተለመደ ድምፅ ሲሰማ አይኖቹን ገለጠ። ደግሞ ከድኖዋቸው አሰብ ካደረገ በኋላ አፍጥጦ ፊት ለፊቱን ተመለከተ። በሳሉኑ የወዲያኛው ጥግ ከዚህ በፊት ተመልክቶት የማያውቀው ሰው ቆሟል።

እንዳቸው ከድንጋጤ የተነሳ ሌላቸው ደግሞ የሚናገረው በማጣት ዝም ብለው አፍታ ቆዩ። «እንዴት አመሸህ።» አለ እንግዳው ሰው፣ ወደሌላ ቋንቋ ወሰድ በሚያደርገው እንግሊዝኛ፣ «ኤሚሊዬ እፒቼላ እባላለሁ።»

ሊ ግን አሁንም ድንጋጤው አላናግርህ ብሎታል።

«እንግሊዛዊ ነህ?» ጠየቀው ሰውየው።

«አሜሪካዊ፣» አለ ሊ እንደምንም ብሎ።

«ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣» መለሰ ሰውየው። እኔ ጣሊያናዊ ነኝ። የሀገርህ ሰላይ ነኝ።»

«ምንድነህ?»

«እኔ የCIA ሰላይ ነኝ።» አለ በግብጣ ላይ ስለሰራው ለጠየቀው ሰው መልስ የሚሰጥ ይመስላል። «ብቅርብ ወደሚገኝ የአሜሪካ ኤምባሲ መሔድ አለብኝ፣ እባክህን።»

«አንድ ጊዜ ቆየኝ፣» አለ ሊ፣ መለስ እያለለት። «እዚህ ጀልባ ላይ እንዴት ልትገባ ቻልክ?»

«ይህን እድል ለማግኘት ቀኑን ሙሉ ስጠብቅ ነበር፣» አለ እፒቼላ። «ሩሲያውያኑ ያለ ጠባቂ ይተውታል ብዬ አልገመትኩም፣ በመጨረሻ ግን ሁላችሁም ወደጀልባው ማቆሚያ ስትሔዱ ለመግባት ቻልኩ።» ወደፊትለፊቱ አመለከተው። «እዚያ ሸራዎቹ ስር ነበረ የተደበቅኩት።»

«ተመልከት፣ እኔ ከዚህ ሀገር ላስወጣህ አልችልም፣ እኔ . . . ስለ CIA ምን ነበር ያልከው?»

«እዚህ ስፍራ ለጥቂት ቀናት ለCIA ስሰልል ነበር። አሁን እንድ የአሜሪካን ኤምባሲ እንድደርስ ርዳታ ልታደርግልኝ ይገባል። አንተ አሜሪካዊ ነህ።»

«አሁን፣ አንድ ጊዜ ቆየኝ፣ አንተ እዚህ ጀልባ ላይ ብትገኝ እነዚህ ሰዎች ምን እንደሚያደርጉኝ ታውቃለህ?»

«አምን ይመስለኛል።» አለ እፒቼላ። «ይህን ስፍራ ስለሚመራው ስለ ማጆሮቭ ብዙ ነገር አውቄያለሁ፣ እሱ ላውቅ የማይፈልጋቸውን ነገሮች እነዚህን

http://ethzare.wordpress.com

ባልነግርህ የተሻለ ነው፣ ነገር ግን ከደረሱብን አልነገረውም ብለው አያምኑም። በሉብያንካ ወህኒ ቤት ውስጥ አንዳችን ያሌላችንን እሪታ ሰንሰማ መቆየት ዕጣችን ይሆናል፣ ይመስለኛል።»

ሊ ጣሊያናዊውን በዝምታ ተመለከተው። «እ. . . መልካም።» አለ የኋላ ኋላ እንደምንም ብሎ። «አሁን ምን እናድርግ?»

«ቅድም አንዳልኩት ወደአሜሪካ ኤምባሲ እንሂድ፣» አለ አፒቼላ ለሀገን ልጅ የሚናገር ይመስል። «የት እንዳለን በትክክል የማውቅ አይመስለኝም። እንተስ ታውቃለህ?»

ሊ ወደቻርቱ ጠረጴዛ እመለከተው። «ይኸው፣» አለ። «ላይታጀን ትተን ለአንድ ሰዓት ያህል በስተምዕራብ ተጉዘናል።»

«አህ፣» አለ አፒቼላ። «ወደስቶክልም መሄድ ይኖርብናል። ከኮፐንህገን ይልቅ የሚቀርበን ይመስለኛል። አንተ ጆዴት ነህ?»

«ወደኮፐንህገን፣ አሁንም ወደዚያው ነኝ፣ ግን ቶሎ ብገላገልህ ደስ ይሰኛል። አንተ ስቶክልም መሔድ ነው የምትፈልገው?»

«ከፈቀድክ እባክህን፣» አለ አፒቼላ። «ለትንሽ ጊዜ ወደላይ ብወጣስ፣» አለ አፒቼላ የታመመ መስሏል። «ከሽራው ስር አየር አጥቼ ነበር።»

«ምንም ችግር የለም፣» አለ ሊ ከልቡ፣ «ሆድዕቃህን ማጋባት ከፈለግህ ስለእምላክ ብለህ ወደውህው ልቀቀው፣ እሺ?»

አፒቼላ እየተጣደፈ ወደላይ ወጣና የተባለውን አደረገ። «አሁን ጥሩ ስሜት ተሰማኝ፣» አለ ቁና እየተነፈሰ።

ሊ ቶሎ ቀና አለና «እዚያ ላይ ብዙ መቆየት አትችልም፣» ሌላ ጀልባ ከተመለከትን ብቻዬን ሆኜ መታየት አለብኝ።»

አፒቼላ ራሱን በመስማማት ወዘወዘ። «እም፣ አሁን ታችኛው ክፍል የሚመች ይመስለኛል። አንድ ብርጭቆ ወተት ማግኘት እችላለሁ፣ እባክህን?» እያለ በመሰላሉ ወደታች ተመለሰ።

ሊ ተከተለው። «የተረፈ ወተት የለኝም፣ የብርቱካን ጭማቂስ?» አፒቼላ የይሁንታ ምልክት ሰጠው። «ከዚህ ሌላ ምንም የለህም።»

«ሰማኝ፣ እ. . . ስምህ ማን ነበር?»

«አፒቼላ፣ ኤሚሊዬ አፒቼላ፣» መለሰ፣ እጁን እየዘረጋለት። «እባክህ ኤሚሊዬ ብለህ ጥራኝ።»

«እኔ ዊል ሊ እባላለሁ፣» አለ ሊ፣ ግራ መጋባት ወሮት። «ዊል ብለህ ጥራኝ።»

«መልካም ዊል፣ እንዴት ማሊቡ እንደመጣህ ባላውቅም በመምጣትህ ደስ ብሎኛል።»

«አዎ፣ ደስ እንደሚልህ ነው። ቦታውን ምን ብለህ ጠራኸው።»

«እንደካሊፎርኒያው፣ ማሊቡ። ሩሲያውያኑ ማሊቡ ይሉታል።»

«ተቀመጥ ኤሚሊዬ።» ሁለቱም ሳሎኑ ጠረጴዛ እጠገብ ተቀመጡ። «እዚያ ከመጣህ ሰንት ጊዜ ሆነህ?»

«ጥቂት ቀናት ብቻ። የመጣሁት ለዚሁ ለማጆሮቭ የራሱ ሰዎች ሊሰሩለት የማይችሉትን አንድ ሥራ ለመስራት ነበር። ሰርቼ ስጨርስ አንድሔድ አልፈቅድ አሉኝ።»

«ቦታው ምንድን ነው፣ ክሌጅ ነገር ነው?»

«ሊሆን ይችላል፣ ግን እዚያ የሚያደርጉትን ሁሉን ነገር አላውቅም፣ እኔም የማውቀውን ባታውቅ ይሻላል ምክንያቱም CIA ያምንህ እንደሁ አላውቅም።» አፒቼላ እጆቹን ዘረጋ። «ይቅርታ አድርግልኝ፣ የግል ነገር አይደለም፣ ገባህ።»

ሊ ከት ብሎ ሳቀ። «ይቅርታ ተደርጎልሀል ኤሚሊዬ፣ ልክ ነህ ስለዚህ ሁሉ ነገር ማወቅ የለብኝም። ይሄውልህ፣ ወደስቶክልም እመስድህሉሁ፣ ግን ኮፐንህገን ላይ ቀጠሮ አለኝ፣ ገና ካሁኑ እንኳን በእንድ ቀን ዘግይቼያለሁ። ለሁለት ቀን ተኩል ያህል ከጓደኛዬ ጋር ተስማምተህ መቆየት ይኖርብሀል።»

«አይሆንም ይህ የሚሆን አይደለም፣» አለ አፒቼላ ወይ ፍንክች በሚል ስሜት። «ሬዶዮ አለህ?»

«አም፣ ግን አንቴናው ከመጀመሪያው የሽራዋልታ ጋር ጠፍቷል። ጥቅም የለውም።»

አፒቼላ ተነስቶ ወደቻርቱ ጠረጴዛ አመራ። «ይህ ጎትጎንድ የተባለ ደሴት ስዊድን ነው?»

«አም።»

«ከሆነ ወደዚያ ውሰደኝ። ከዚያ ወደስቶክልም መግባት ለመቻሌ ርግጠኛ ነኝ። እዚያ ያለው የኤሜሪካ ኤምባሲ ዘንድ መድረስ አለብኝ። በሁለት ቀናት ውስጥ ጊዜው ሊረፍድ ይችላል።»

ሊ ቻርቱን ተመለከተ። በጎትላንድ ምስራቃዊ ባሀር ጠረፍ ላይ የሚገኘው አስተርጋርን ለመድረስ ርቀቱ ስባ አምስት ማይል ብቻ ነው። ነገ እስከ ምሳ ሰዓት እዚያ መድረስ ይችላሉ። ለኬትም መደወል ይኖርበታል። ኮፐንህገን ላይ ቀድማ ደርሳ ትጨነቃለች፣ ማጆሮቭን ማየቱንም መሰማት አለባት። «እሺ መልካም፣ ጥሩ። አስተርጋርን ላይ እጥልሀለሁ፣ ግዝፈቱ የአየር ማረፊያ የሚያስገነባበት ያስመስለዋል። ፓስፖርት አለህ?»

«አዎ አለኝ። የስዊድን መግቢያ መሀተም ግን የለውም። እንተ ከየት ነው የመጣኸው?»

«ከፈንሳንድ።»

«ፈንሳንዶች መሀተም ሳያደርጉብት ቀርተው ነው እላለሁ።»

«የሩሲያ መግቢያ መሀተም የለውም?»

«የለውም ሩሲያውያን ፓስፖርት ላይ ምልክት አያደርጉም። በዚህ ፈንታ አነስተኛ የቪዛ ደብተር ይሰጡሀል። ከሀገሪቱ ስትወጣ መልሰው ይወስዱታል።»

«ግሩም፣ የት እንዳገኘሀህ ማብራራት አይኖርብኝም ማለት ነው።» ሲል አሰበ ለእፍታ ያህል። «አስተርግራም መጥፎ ሀሳብ አይደለ ይሆናል። ለዚህ ጀልባ አዲስ ገመዶችና ሸራ መግዛት አለብኝ። ከፋብሪካው ወደኮፐንህገን ይዘውት መምጣት ይችላሉ። ጀልባ ነድተህ ታውቃለህ ኤሚሊዬ?»

«አይ፣ አላውቅም። ግን ልረዳህ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ።»

«መልካም፣ አሁን ልታደርግ የምትችለው ሹፌሩ ቦታ ላይ ሄደህ ተቀምጠህ ጀልባዎች መኖራቸውን መቃኘት ይሆናል። ከምንም ነገር ጋር መጋጨት አልፈልግም።»

http://ethzare.wordpress.com

እፒቼላ ወደ ሹፈሩ ክፍል ሲያመራ ሲ ደግሞ ወደ አስተርጋርን የሚወስዳቸውን የጉዞ መስመር ነድፎ፣ አቅጣጫ ከለወጠ በኋላ ሽራዎቹን አስተካከለ። ጠንካራ ነፋስ ይገፋቸው ጀመረ።

«እሺ፣ ሁሉ ነገር ተስተካክሏል። እኔ እንቅልፍ ስለሚያስፈልገኝ ትንሽ ልረፍ። እንተ ነቅተህ ተመልከት፣ ጀልባ ካየህ ጥራኝ፣ እሺ?»

«እንዴታ፣» መለሰ እፒቼላ። «ያልከውን እደርጋለሁ። እና ዊል. . . »

ሲ በመሰላሉ ላይ ቆመ። «አቤት?»

«ኑፍሴንና የሌሎች ብዙሃንን ነፍስ አድነህል። በጣም አመሰግናለሁ።»

«ምንም አይደለም፣» መለሰ ሊ። «ከሶቪየት ህብረት መውጣት የሚፈልጉትን ሁሉ መቼም ለመውሰድ ወደኋላ አልልም። ብቻ ገና ስዊድን አልደረስንም።»

«ያለጥርጥር እንደምንደርስ ይሰማኛል፣» አለ እፒቼላ።

«እንዳልተሳሳትክ ተስፋ አለኝ፣» ብሎ ሲ ወደመኝታው አመራ። ሀሳብ እንደሌለበት ሰው ሆኖ ተኛ።

ሩል ለሊት አስር ሰዓት ላይ ከእንቅልፏ ነቅታ ተመልሳ መተኛት አቃታት። ኤድ ራውልስ እሷ ኮፐንሀገን እያለች ድጋፍ ሊያደርግላት ቃል በገባላት ጊዜ እርይታ ተሰምቷት ነበር፣ አሁን ግን ጭንቀት ዋጣት እንደውም የጥፋተኝነት ስሜት ወረራት። የምታውቀውና የሚሰማት ደመነፍሳዊ ስሜት ሁሉ የሚጠቁማት ሶቪየት በጣም በቅርብ ጊዜ ወስጥ ስዊድንን እንደምትወር ነው። ይህ ሀሳቧ ምንም ያህል ተጨባጭነት ያጣ ቢመስልም ቅሉ ኮፐንሀገን ከመሄድ ይልቅ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ይህ መላምቷ እውነትም ይሁን ሀሰት ከሁሉ በፊት ልታስቀድመው የሚገባት መሆኑን ወሰነች። ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ የሚሰራውን ቤን ብራድሊን የሚያውቅ ጓደኛ አላት። ስልኩን አንስታ ደወለችለት።

ከዚያም ገና ሳያንሳው በፊት ዘጋችው። የተሻለ መንገድ ሊኖር ይችላል። ከአልጋዋ ወጥታ ማስታወሻዋን ፍለጋ የእጅ ቦርሳዋን ፈተሸች። ቁጥሩ ብዙ ጥቃቅን ነገሮች በተፃፉበት ወረቀት ላይ አገኘችው። ማልዶ እንደሚነሳ እንብባ ነበርና ይህንኑ ተስፋ እደረገች። ቁጥሩን ደወለች።

«ሀሎ።» አለ፣ እንቅልፍ ያልደረሰበት የሚመስል ድምፅ።

«ሴናተር ካር?»

«አዎን።»

«ካትሪን ሩል እባላለሁ፣ PCIA የስለላ ደይሬክቶሬት የሶቪየት ቢሮ ኃላፊ ነኝ።»

«እሺ፣ ከቅርብ ጊዘ በፊት ከሚስተር ኒክሰን ገር ችሎቱ ላይ ተገኝተሻል፣ ይመስለኛል።»

«አዎን ጌታዬ ተገኝቼያለሁ። ሴናተር፣ ዊል ሊ የእርስዎን የግል፣ ቁጥር ሰጥቶኝ፣ አስፈላጊ ከሆነ እንድደውልልዎት ነግሮኛል።»

«ዊልን ያገኘሽው ችሎቱ ላይ ነው?»

«አይደለም ጌታዬ፣ ዊልና እኔ. . . ከሥራችን ጋር ያልተገናኘ ግላዊ ግንኙነት አለን።»

«ገባኝ። ታዲያ እንዴት ልረዳሽ እችላለሁ ሚስ ሩል. . . ይቅርታ፣ ሚሲስ ሩል ነው መሰለኝ አይደለም?»

ሀሊናቸው ሌላ ነገር ማሰብ መጀመሩ ገባት። «እምን ጌታዬ፣ የተልዕኮዎች ምክትል ዳይሬክተር ከነበረው ከሳይመን ሩል ተፋትቼያለሁ።»

«እሀ እሞ፣ ተፋታችሁ። መልካም ታዲያ ምን ላድርግልሽ ሚሲስ ሩል?»

«በተቻለኝ ጥጥነት ስለእንድ ትልቅ ጉዳይ ነው ብዬ ስላሰብኩት ጉዳይ ላናግርዎት እፈልጋለሁ። ዛሬ ጠዋት ወደቢሮ ከመሄድዎት በፊት ቤት መጥቼ ላግኝዎት?»

«ሶስት ሰዓት ላይ ከፐሬዚዳንቱ ጋር ቀጠሮ አለኝ ሚሲስ ሩል፣ ግን ይሁንና በአንድ ሰዓት እዚህ መድረስ ከቻልሽ አገኝሻለሁ።»

«አመሰግናለሁ ጌታዬ፣ በአንድ ሰዓት እደርሳለሁ።» እድራሻውን ፃፈች። ሴናተር ይህን ጉዳይ ቢያንስ የምናገረውን እስኪሰሙ ድረስ በሚስጥር ያቆዩታ።»

«እንዴታ። አንድ ሰዓት ላይ እንገናኝ።»

ሩል በደስታና በመረበሽ የተደባለቀ ስሜቶች ተሞልታ ሻወር ወሰደችና ለባበሰች። ይህ እለት ከመፈፀሙ በፊት ስራዋን ልታጣ፣ ከባሰም ልትታሰር ትችላለች።

ከቤት ከመውጣቷ በፊት ወደጥናት ክፍሏ በማምራት የፎቶ ኮፒ ማሽኑን አስነስታ እሰካሁን የሰበሰበችውን መረጃ በሙሉ ሁለት ሁለት እያደረገች አባዛች። የሳተላይት ምስሎቹ በግሩም ሁኔታ ግልጥ እንደወጣላቸው ስትመለከት ደስ አላት። የማይቀለበስ ርምጃ ልትወስድ መሆኗን እያሰበች በማለዳው የዋሽንግተን ዋና ጎዳናዎች ላይ ማሽከርከር ጀመረች። የካር መኖሪያ የሚገኘው በቅርብ ዓመታት ውስጥ የተስተካከለ የቪክቶሪያ ክፍለ ዘመን ጥንታዊ ቤቶች በሚገኙበት በካፒቶል ሂል ላይ ነው። እላቸው ግን እዚያ መኖር የጀመሩበት በቤቶቹ መኖር ብርቅ መሆን ከመጀመሩ ከረጅም ጊዜ በፊት ነበር።

ገና ካሁኑ ከረባታቸውን ቢያደርጉም በላዩ ላይ የሐር የቤት ልብስ ጣል አድርገውበት በሩን ከፈቱላት። «ወደጥናት ክፍሉ ነይ፣» አሏት፣ ከቤቱ በስተጀርባ ወደሚገኝ የፀሐይ ብርሀን ወደፈነጠቀበት ክፍል እየቀደሟት። በቆዳ የተሸፈነ ሶፋ ላይ አጠገብ ለአጠገብ ተቀመጡ። ቡና ቀዱላት። ወዳያውኑም ወደ ዋናው ጉዳይ ተሸጋገሩ። «እሺ፣» አሉና «ጉዳዩ ስለምንድን ነው?»

ሩል ቡናዋን አስቀመጠች። አትኩሮቷን፣ በዋንዛ እንጨት ተክፋፍሉ ከወለሉ እስከ ኮርኒሱ በሚደርሱ የመጽሐፍት መደርደሪያዎች፣ በሴናተሩ በብዙ የተለያዩ ፕሬዚዳንቶች ፎቶግራፍ ያሸበረቀውን ክፍል ከመቃኘት፣ መለሰችው። ሻንጣዋን ከፈተች። «ከየት መጀመር እንዳለብኝ ለማወቅ ይከብዳል ሴናተር፣ ግን ከዚህ ብጀምር ልዩነት አይኖረውም።» ብላ ወረቀቶች አቀበለቻቸው። «ይህ ሰንፍላወር የተባለ የተሳሳተ መረጃ የመልቀቅ ተልዕኮን የሚገልፅ የድርጅቱ መዝገብ ግልጥ ነው። ሂደት ላይ ከዋለ፣ ቢያንስ ከተጀመረ በ1983 የበጋ ወቅት ጀምሮ ያስቆጠረ ነው። በከለሳው ክፍል መመልከት እንደሚቻለው፣

http://ethzare.wordpress.com

ሀሳቡ ስዊድን የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃልኪዳን ድርጅት/ኔቶን/ የመቀላቀል ምስጢራዊ ፍላጎት ያላት መሆኑን ይገልፃል። ይህ የተደረገው ሶቪየቶች በስጋት ጦራቸውን ምንም ወደማያሰጋቸው የባልቲክ ቀጠና ያስገባሉ በሚል ተስፋ ነበር። ከዚህ ሀይል የተወሰነው ሶቪየት ጦሯን በከፍተኛ ሁኔታ ካከማቸችበት ከምስራቅ ጀርመን ቀንሳ የምትወስደው እንደሚሆን ድርጅታችን ተስፋ አድርጎ ነው።»

ሴናተሩ እያነበቡ ቅንድቦቻቸውን ወደላይ ሰቀሏቸው። «እንደምታውቂው ኤጀንሲው ለሚያካሂዳቸው ህቡዕ ተልዕኮዎች የኮሚቴውን ድጋፍ ለማግኘት የመጠየቅ ግዴታ አለበት፣ ግን ፊዕሞ ወደእኛ አልመጡም። እንደምገምተው ይህ ተልዕኮ ወታደራዊ ሀይልን ስለማይጠይቅ ፈቃድ እያስፈልገውም ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ፣ እኔ ግን ይህንን አልደግፈውም። ብዙ ዓይነት ተፅዕኖዎችን ሊያስከትል ይችላል።»

«አሁንም ቢሆን አስከትሏል ቭዙ አምናለሁ። ይህ ተልዕኮ ሙሉ በሙሉ ያልተጠበቁ ቅደም ተከተላዊ ሂደቶችን ወልዷል።» ያመጣቸውን ሁሉ ቀስ በቀስ አስጨበጠቻቸው - በአክቶብር 1981 የዊስኪ ደረጃ የሶቪየት ሰርጓጅ መርከብ በስዊድን ባህር ኃይል ጦር ሰፈር አቅራቢያ ውሀ ለውሀ ስትጓዝ መገኘቷ፣ እንዲሁም ይህን ተከትሎ በስዊድን የደሴቶች የውሀ ክልል ውስጥ ሰርጓጅ መርከቦች በተደጋጋሚ መታየታቸውን፣ ስለ ፊርሶቭ ወይንም ማጆሮቭ የጋላ ታሪክና የማንነቱን መገለጥ እንዲሁም የKGB ስልጣኑን ለቅቆ የስፔትራዝ ሀይልን ወደማዘዙ ስለመሸጋገሩ አስገራሚ ታሪክ፣ የስፖርት ተቋም የሚመስለው የሀንዛዎች አጀብ የስፔትናዝ ጦር ሰፈር መሆኑን ስለሚያመለክቱ መረጃዎች፣ ስለሰራዊት ማመላለሻዎቹ ሚግ አይሮፕላኖች ስሪት መሳካት፣ በፖላንድ፣ በሊትዌኒያ፣ በላቲቪያ እና በኢስቶኒያ ስላለው የሶቪየት ኃይሎች ክምችትና ስለረዥም ጊዜ ልምምዳቸው፣ በመጨረሻም ኤሚሊዩ አፒቼላን መልምላ ስለማሰማራቷና ስለላከላት መልዕክት አብራራችላቸው።

ሴናተሩ አልፎ አልፎ ጥያቄ እየጠየቋት በአትኩሮት ገለፃዋን አደመጡ «እንደሚመስለኝ፣» አሉ፣ ቡናዋን ልትጠጣ ዝም ስትል ጠብቀው፣ «ሶቪየቶች በስዊድን ውስጥ የሆነ ዓይነት ወታደራዊ ርምጃ ለመውሰድ እያሰቡ ናቸው ብለሽ ታምኚያለሽ፣ እንደዚያ ነው?»

«ሴናተር፣ ሲያስቡት ከቆዩ የለንበቱ፣ አሁን ሙሉ ወረራ መፈፀማቸው እንደማይቀር አምናለሁ።»

ሴናተር ካር አይኖቻቸውን አርገበገቡ። «ይህ በጣም አስደንጋጭ ሀሳብ ነው ሚሲስ ሩል፣ ያውም እንቺ ካለሽበት የአመራር ደረጃ ላይ በመምጣቱ።»

«አውቃለሁ ጌታዬ፣ ግን ወደዚህ መደምደሚያ ላይ የደረስኩት በችኮላ አይደለም።»

«ለእኔ ችኩል ሰው አትመስይኝም ሚሲስ ሩል፣ በርግጥ ይህን መሠል ትንታኔ ያውም ከሴት ሲመጣ ችኩል ነው ብለው የሚፈርጁት የድርጅቱ ግለሰቦች መኖራቸውን እገምታለሁ።»

«ሙሉ በሙሉ ትክክል ነዎት ሴናተር።»

«እነዚህን እውነታዎችና መላምቶች ለበላይዎችሽ አቅርበሽ ምላሻቸው የምትጠበቂውን ያህል እንዳልሆነልሽ እገምታለሁ።»

«ይህ ትክክል ነው።»

«የወሰዱት ርምጃስ አለ?»

«እኔ እስከማውቀው ድረስ የለም፣ ምንጮቹም ጥሩ ናቸው።»

«ለምን አልወሰዱም? እሺ፣ ርምጃ ስላልወሰዱበት ምክንያት ተይውና፣ እንቺስ ርምጃ ያልወሰዱት ለምንድን ነው ብለሽ ታምኛለሽ?»

«በመጀመሪያ ደረጃ በሰንፍላወር የተነሳ ነው። ይህ እጅግ ሚስጥራዊ ተልዕኮ ነው፣ እኔው ራሴ ላውቀው አልተፈቀደልኝም። ሶቪየቶች ርምጃ ሊወስዱ ነው ብሎ እምኖ መቀበሉ ድርጅቱ ለዚህ ርምጃቸው ኃይልን ሰጥቷቸዋል ብሎ እምኖ መቀበል ይሆናል።»

ሴናተሩ መስማማታቸውን ራሳቸውን በመወዘወዝ ገለፁ። «ይህትንሽ የሚያሳፍን ነገርሊፈጥርብን እንደሚችል ታይቶኛል፣ ሆኖ ከሆነ።»

«ከዚህ ባሻገር ሴናተር፣ የቀድሞ ባለቤቴ የኔን በድርጅቱ ውስጥ ማገልገል አሳፋሪ አድርጎ ስለሚመለከተውና ሀሳቡ በእኔ በኩል በመምጣቱ የተነሳ ሊያንጓጥጠው የመቻል አዝማሚያ ስላለው እንጂ፣ ከዚህ በስተቀር አለቆቼ ይህን ዓይነት ምላሽ የሚሰጡበት ምክንያት አይታየኝም። የCIA ዳይሬክተር ራሳቸው እንኳን በዚህ ዶሴ ውስጥ የሚገኘውን አብዛኛውን መረጃበተመለከቱና ባደመጡ ጊዘ በከባድ ቁጣ ምላሽ መስጠታቸውን እውቃለሁ። አለቃዬም ይህን ጉዳይ በትርፍ ጊዜዬ እንኳን መከታተል የምቀጥል ከሆነ ከስራዬ ላይ ልነሳ እንደምችል ገልፆልኛል። የቀድሞ ባለቤቴም በፈቃዴ ስራዬን እንድለቅና ይህን ከላደረግኩ ከሥራዬ እንደምነሳ በሚጠቁም ሁኔታ ተናግሮኛል።»

«ሚሲስ ሩል፣ በመጠየቄ ይቅርታ አድርጊልኝ፣ ግን መጠየቅ ስላለብኝ ነው፣ ሙሉ እውነቱን ልትነግሪኝ ይገባል።»

«እሺ?»

«ሚሲስ ሩል፣ በCIA ውስጥ ያለሽ ስራ ከዚህ የስዊድን ጉዳይ ውጭ ጠቅላላ ምርመራ ቢደረግበት ችግር ውስጥ መኖርሽንና ለመባረር በዝግጅት ላይ የምትገኚ መሆንሽን የሚገልፅ ነገር አይተኝም?»

ሩል ፊቷ ሲቀላ እየተሰማት ቀጥ ብላ ተቀመጠች።ሪ«ሴናተር ሰላሳ አምስት ዓመቴ ነው፣ የስለላ ዳይሬክቶሬትን ቢሮ በሀላፊነት እመራለሁ። ይህን ያደረግኩ የመጀመሪያዋ በዕድሜ አናሳ ሰራተኛ ነኝ። ከዚህ ሌላ ሴት ነኝ። ይህ ጥያቄዎትን ይመልሳል?»

ሴናተሩ በሳቅ እውካኩ። «አዎ ይመልሳል ብዬ አምናለሁ። በእውነት በጣም አዝናለሁ፣ ግን ለምን ልጠየቅሽ እንደተገደድኩ ማወቅ አያቅትሽም።»

«እዎ፣ ማወቅ የምችል ይመስለኛል።» ሩል ትንሽ ረገብ ብላ መለሰች።

ሴናተሩ ሰዓታቸውን ተመለከቱ። «ልጠይቅሽ የምፈልጋቸው በጣም ብዙ ነገሮች አሉ፣ ሚሲስ ሩል፣ ግን በግማሽ ሰዓት ውስጥ ከፐሬዚዳንቱ ጋር ቀጠሮ አለኝ። ሶቪየቶች ስዊድንን በመቆጣጠራቸው ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያገኙ ማወቅ አይከበድም፣ ግን ልጠይቅሽ፣ ከሌላው አለም ከሚገጥማቸው ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ታዕቅቦዎች አንፃር ለምን ይህን ያደርጋሉ ብለሽ ትገምቺያለሽ?»

«በምላሹ አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎት ሴናተር፣ ዩናይትድ ስቴትስ ስዊድንን ከሶቪየት ወረራ ለመመከት ኒውክሊየር ትጠቀም ይመስልዎታል?»

ሴናተሩ ምንጣቱን ተመለከቱ። «አይመስለኝም።»

http://ethzare.wordpress.com

«እሺ ጌታዬ፣ እነሱን የመመከቻ ሌላ ምንም መንገድ የለም።»

«ስዊድኖች ራሰቷቸውስ? በጣም የተደነቀ የመከላከያ ኃይል አላቸው - የአየር፣ የባህር፣ በደሴቶቻቸው የውሀ ክልል ላይ የተከማቹ በመቶ የሚቆጠሩ የተጠመዱ መሳሪያዎች እንዲሁም በጣም ግዙፍና የሰለጠነ መጠባበቂያ ጦር አላት። ታዲያ ለምንድን ነው ራሳቸውን የማይከላከሉት?»

«ሴናተር፣ ስዊድኖች ከምስራቅ በኩል የሚሰነዘርን የታሰበበት ጥቃት ለመመከት ፍፁም ብቃት አላቸው። በሰላሳ ስድስት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ብቻ ስምንት መቶ ሺህ ወይንም የህዝባቸውን አስር መቶኛ ሰራዊት አሰባስበው ማደራጀት እንደሚችሉ ይናገራሉ። ይህ ግን የታሰበበት ወረራ አይሆንም፣ ሰላሳ ስድስት ሰዓታት አይኖራቸውም። የስፔትናዝ ኃይላት የባህር ጠረፍ ጦር መሳሪያዎቻቸውንና የሚሳኤል ባቢያዎቻቸውን ቀድመው በቁጥጥራቸው ስር ያውላሉ። ስለዚህም ሶቪየቶች በንፅፅር ሲታይ አናሳ የሚባለውን የባህር ጠረፍ መከላከያዎቻቸውን በፍጥነት ጥሰው ይገባሉ። ከስፔትናዝ የእንቅስቃሴ ስልት እስካሁን እንደምናውቀውም እስካሁን የሚንኙንት መስመሮችን የሚቆርጥና የስዊድን አየር ኃይልን ከምድር ሳይነሳ የሚያደባይ ልዩ ኃይል ቀድመው ልከዋል። እኔ ወታደራዊ ኤክስፐርት አይደለሁም፣ ግን በጣም በፍጥነት የሚጠ ናቀቅ ይመስለኛል።»

«መልካም - እንዴት ይህን ያደርጉታል ብለሽ እንደምታስቢ ነግረሽናል፣ አሁን ደግሞ ለምን ያደርጉታል የሚለውን መልሺልኝ።»

«ምክንያቱም ዘወትርም ስጋት ውስጥ ቆይተዋል፣ እንዲሁም ባልቲክ ላይ ኔቶ ያሰጋናል ብለው ያስቡ ነበር። ምክንያቱማ እነሱን ለመግታት ብለን ጦርነት ውስጥ ስለማንገባና ሌላም የሚቀናቀናቸው ስለማይኖር ነው። ምክንያቱማ አላሳቢ የኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ ስለሚገኙና የስዊድንን ኢኮኖሚ ለራሳቸው ጥቅም እንዲሆን አድርገው መግራት ስለሚችሉ ነው። ምክንያቱማ ሶቪየቶች አንድ ሰውም ሆነ አንድ ስንዝር መሬት በህዝብ አስተያየት የተነሳ ስለማያጡ ነው። ምክንያቱማ የሚያገኙት እንጂ ምንም የሚያጡት ነገር ስለሌለ ነው። ምክንያቱማ ለድርጊታቸው ቅጣት ስለማይመጣባቸው ነው።»

ሴናተሩ ለእፍታ ያህል ሲመለከቷት ከቆዩ በኋላ ተነስተው ወደ ጠረጴዛቸው አመሩ። «ሚሲስ ሩል፣ እንዳደርግ የምትፈልጊው ምንድን ነው? ምናልባት፣ ያለኝ ኃይል አንቺ ከምትገምቺው እጅግ ያነሰ ሊሆን ይችላል።»

«የዚህን ዶሴ ግልባጭ ለፕሬዚዳንቱ ይውሰዱላቸው። ስዊድኖቹን እንዲያስጠ ንቅቁ ይጠይቋቸው፣ ከተቻለ ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲደውሉ ያድርጉ። ሶቪየቶች ፍፁም ድንገተኛ የሆነ ጥቃት መሠንዘር ካልቻሉ ወረራ ይፈፀማል የሚል እምነት የለኝም። ስዊድኖች ጦራቸውን ካሰባሰቡና ካደራጁ ሶቪየቶች ወደኋላ ለማለት ይገደዳሉ። ስዊድኖች ማስጠንቀቂያ ከደረሳቸው ግን ርምጃው እሳት ውስጥ መግባት ሊሆን ይችላል። ለስዊድኖች እንዲያሳውቁ እፈልጋለሁ። የምፈልገው ይህን ብቻ ነው።»

«ይኸው ብቻ ነው? አንቺ ዶሴ ውስጥ ባለው ነገር ብቻ ተመርታ አንድ ሀገር ለጦርነት ዝግጁ እንድትሆን ትፈልጊያለሽ?»

«ይህ የኔ ውሳኔ አይደለም ሴናተር የፕሬዚዳንቱም ውሳኔ አይደለም። ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር ለስዊድኖች መንገር ብቻ ነው፣ ከዚህ በኋላ የራሳቸው ውሳኔ ይሆናል። ግን ይህን መረጃ ሳናወጣ ቀርተን ሶቪየቶች

ወረራውን ቢፈፅሙ ምን እንደሚፈጠር መገመት ይችላሉ? ታሪክን ወዲያ እንተወውና፣ በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ያለው የኃይል ሚዛን ላይ የሚያደርሰውን ብንዘነጋ እንኳን እዚህች ሀገር ላይ ምን ይፈጠራል? ወደ ኖርዌይ፣ ዴንማክና ጀርመን ሰራዊት ማስገባት ይኖርብናል። አዳዲስ ፀረ ሚሳኤሎችን የሚደርስብንን ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ተቋቁመን ለመፈብረክ እንገደዳለን። በአስርተ ቢሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘብ ያስወጣናል። ይህ ብቻ ላይሆን፣ የታጠቀ ሰራዊታችን ለብዙ ወራት በሙሉ ተጠንቀቅ ላይ እንዲሆን ይገደዳል። የሶቪየት ጦርም እንደዚያው። ደንገተኛ የኒውክሊየር ውንጨፋ እድል በጣሙን ይሰፋል። የአለም አስተያየትን መጥቀስ ይኖርብኛል? በአሁኑ ሁኔታ እንኳን በዚህ ሪገድ አስቸጋሪ ሁኔታውስጥ ነን። ለስዊድኖች ማሳወቅ ይኖርብናል፣ ሴናተር።»

«የምትፈልጊው ይህንን ብቻ ነዋ ታዲያ? ለስዊድኖች የሚያሳውቅ ሰው?»

«በቃ ይኸው ነው።»

«ታዲያ እዚህ ያመጣሽውን ብቻ ይዤ ፕሬዚዳንቱ ዘንድ መቅረብ አልችልም። በመጀመሪያ ደረጃ፣ በተቃዋሚ ፓርቲው ውስጥ ካለሁት ከእኔ ዘንድ በመምጣቱ ይጠረጥሩታል። ሁለተኛ፣ ቀጣይ ምርመራ የሚስያስፈልገው ጉዳይ መሆኑን ባሳምናቸው እንኳን፣ የሌሎችን አስተያየት መጠየቃቸው አይቀርም፣ በተለይም የፔንታጎንን እና የራስሽን ድርጅት። ይህ ደግሞ ጊዜ ይወስዳል፣ እንደምትይው በእጭር ጊዜ ውስጥ መሆኑ የማይቀር ከሆነ፣ መቼም . .»

ሩል ተነስታ ቆመች። «ለሰጡኝ ጊዜ አመሰግናለሁ፣ ሴናተር፣ ጸግመኛ አላስቸግርዎትም።»

«አይሆንም፣ ቆዪ ቆዪ፣» አለ፣ ክንዷን ይዘው ወንበሯ ላይ እየመለሷት። «እልደግፍሽም አላልኩም፣ ወደፕሬዚዳንቱ ሳቀርበው ስለማልችል ብቻ ነው። ምናልባት ሌላ የተሻለ መንገድ ይኖር ይሆናል።»

«ምንድን ነው?»

«አንቺ ራስሽ ለስዊድኖች እንድትናገሪ መንገድ ልናመቻችልሽ እንችል ይሆናል።»

«እንዴት?»

«ዊል ኮፐንሀገንላይ የሚገኝኘሽ ወጣት ሴት አንቺ ነሽ?»

«አዎ።»

ሴናተሩ በጠረጴዛቸው ዞረው ስልኩን አነሱ። ከማስታወሻቸው አንድ የስልክ ቁጥር ፈልገው ካገኙ በኋላ ሰዓታቸውን ተመልክተው ቁጥሮቹን ደወሉ። «በዚያ ፈንታ ወደ ስቶኮልም ሂጂ፣» አለ። «ሀሎ? ይህ የሚስተር ካርልሰን ቢሮ ነው እኔ የዩናይትድ ስቴትስ ሴናተር ቤንጃሚን ካር ነኝ። እባክዎን ሚስተር ካርልሰንን ማግኘት እችላለሁ?» መነጋገሪያውን በእጃቸው ደፍነው ወደሩል ዞሩ። «ይህ ሰው በስዊድን መከላከያ ሚኒስትር ውስጥ የቻንሰሪ ኃላፊ ነው. . . ሀሎ ሰቪን? ቤን ካር ከዋሽንግተን ነኝ። ስማ ከባድ ለሆነ ጉዳይ ነው የደወልኩልህ። አንድ ወዳጄ ወደ ስቶኮልም ትመጣለች. . .» ኪትን ተመልከቷት. . . «ነገ?» የአዎንታ ምልክት አሳየቻቸው።

«. . . ነገ፣ ጊዜ ወስደህ ብታገኛት ደስ ይለኛል። ስሟ . . .»

http://ethzare.wordpress.com

ሩል እጇን እያወናጨፈች ተርገፈገፈች። «በስልክ ስሜን አይናገሩ!»

«እንድ ጊዜ ቆየኝ።» መነጋገሪያውን በእጃቸው ሸፈኑት። «ማን ልበለው?»

«ብሩኪ ኪርክለንድ።»

«ሰሺን፣ ሰሚ ብሩኪ ኪርክላንድ ይባላል፣ ያዝከው? ጥሩ። አሁን አጻምጥ ስሺን፣ ይህች ሴት ነገሩን የያዘችው በጥብቅ መሆኑን እንድትረዳ እፈልጋለሁ። ስለዚህ የምትለውን እንድታጻምጣት። ነኝ ብላ የምትነግርህ ማንነቷ ትክክል ለመሆኑ ቃል እገባልሀለሁ፣ የያዘችው መረጃም ለእናንተ ሰዎች ጠቃሚ ነው። ሚኒስትራችሁን ልታገናኛት እንደምትፈልግ ይሰማኛል። ከዚህ በላይ ነገሩን ስላልገለጥኩልህ ይቅርታ፣ ግን ይገባህል። እም፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ዋሽንግተን ላይ ጻግመኛ እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ። አመሰግናለሁ ሰሺን፣ ደህናሁን።»

ስልኩን ዘግተው ፊታቸውን ወደሩል አዞሩ። «እንጻልኩሽ ቬን ካርልሰን የቻንሰሪ ኃላፊ ነው፣ በስዊድን መከላከያ ሚኒስትር ውስጥ ከፍተኛ የሲቪል አገልጋይነት ደረጃ ነው። በተደጋጋሚ ተገናኝተናል፣ እኔ ቤትም በእንግድነት ተገኝቶ ያውቃል። የነገርኩትን አድምጠሻል። ስታገኚው፣ ይህ እየተደረገ ያለው በደንቡ መሠረት እንጻልሆነና፣ መረጃው ከእኛ መንግስት የተላከ መልዕክት ያለመሆኑን ታብራሪለታለሽ። ግን ለኔ ያሳየሽኝን ሲመለከት አትኩሮቱ ተሰቦ ወደሚኒስትሩ ይዞሽ ሊሄድ ይችል ይሆናል። ምናልባትም ሚኒስትሩ ነገሩን ለጠ ቅላይ ሚኒስትሩ ያደርሱት ይሆናል። ከዚህ በላይ ምንም ማድረግ ስለማልችል አዝናለሁ፣ ግን ቢያንስ በዚህ ሁኔታ ከሆነ መረጃሽን በሚቀጥለው ሳምንት ሳይሆን በነገው እለት ያገኛሉ።»

ሩል ተነስታ መረቀቶቿን ሰበሰበች። ለሲናተሩ ትልቅ በሩግ ፖስታ አቀበለቻቸው። «ይህ ያሳየሁዎት ነገር ሁሉ ግልባጭ ነው። የፈቀዱበትን ያድርጉበት።

ፖስታውን ተቀበሉና። «አመሰግናለሁ። ትክክለኛውን ዕድል ባገኝ ኖሮ. . . የአንቺን ስም ከጉጻዩ ውጪ ላደርገው እምክራለሁ።»

«ይህ እሰደስቶኛል ሲናተር፣ እንደሚገባኝ ከሆነ ግን ይህን ግድረግ ሊከብድ ይችላል። ግድረግ ያለብዎትን ያድርጉ። ስላጻመጡኝና ስላደረጉልኝ ርጻታ በጣም አመሰግናለሁ።»

«ከካርልሰን ጋር ከተነጋገርሽ በኋላ ደውይልኝ። እዚህ እየተደረገ ያለውን እንድታውቂ እደርጋለሁ።»

የካርን መኖሪያ ትታ በመኪናዋ ወደ አንድ የህዝብ ስልክ አመራች። ለሊቱን በኮፐንህገን ፈንታ ወደስቶኮልም የሚበረው አይሮፕላን ላይ ቦታ ያዘች። የምታውቀው ስቶኮልም ግራንድ የተባለ ሆቴል ደውላ ክፍል ያዘች። ኮፐንህገን የሚገኘው ሆቴል ደውላም ለዊል የስቶኮልሙን ቁጥር ተወችለት።

ከዚያም ወደመኪናዋ ተመልሳ ወደላንግሊ ጉዞ ጀመረች። የሆነው ቢሆንም፣ የተለመደ የሥራ ቀን ማሳለፍ አለባት። ከዚያ ነፃ ትሆናለች፣ ይህን ነገር ለመግታት ከምታደርገው ሙከራ ነፃ ትሆናለች። ነፃ።

ሔልደር በቲያትር አጻራሹ የመጀመሪያ ረድፍ ተቀምጦ ማጆሮቭ ከሞቂት ቀናት በፊት ለፖሊት ቢሮው አቅርቦት የነበረው በፎቶግራፍ የተደገፈ ሪፖርት እየደገመ የተመልካቹን ቀልብ ሲገዛ ይመለከታል። ድፍረትና ሙሉ ብቃት ያዘለ መሆኑን ማመን ነበረበት። ከሱኔሉ ትልቅ ሥራ ሰርቷል። ማንም ምን እየተደረገ መሆኑን ከማወቁ በፊት ሀገራቱ በቁጥጥር ስር ትውላለች፣ ጠ ቅላይ ሚኒስትሩ ወይንም በድምዕና በመልክ አሳቸውን የሚመስል ሰው በፊዲዮና በቲሌቭዥን ቀርቦ፣ ዐጥታና መረጋጋት እንዲሰፍን ይጠይቃል። ውጊያ እንደሚኖር ማጆሮቭ አምኖ ተቀብሏል። ውጊያው ግን ከአንስተኛ ጦር መሳሪያዎች በቀር ሌላ ነገር በሌላቸው የተከፋፈለ የሚሊሽያ ሀይላት ጋር የሚደረግ ሲሆን፣ እነዚህ ኃይላት ወዲያውኑ ይፈረካከሳሉ። ዋና ዋና የህዘብ መኖሪያ መአከሎች - ማለትም ስቶኮልም፣ ጉተንበርግና የተወሰኑ ትንንሽ ከተሞች ግን፣ እንደሌሎች ዋና ወታደራዊ ተቋማት ማለትም እንደ ስቶኮልም ወታደራዊ ከፍል የበላይ መምሪያ ሁሉ ከመቅዕበት በቁጥጥር ስር የሚውሉ ይሆናሉ። የስዊድን ጦር ሀይላት ዕዝ ቀድመው ቦታ በያዙ ሰርጎ ገብ ሀይላት አማካይነት ከእንቅስቃሴ ውጭ ይሆናሉ። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ካልደረሰ ብቻ ይሆናል። ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተደርጎ ከሆነ ግን ወረራው ከመቅዕበት እንደሚሰረዝና የጦር ሀይላቱ እንቅስቃሴም በልምምድ እንደሚላበብ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ አላብራራም።

«እናም አሁን፣» ቀጠለ ማጆሮቭ፣ ተደንቀው ለሚያጻምጡት ሰዎች፣ «ወመጪረሻ መመሪያዎቻችሁን ለመቀበል ለየክፍላችሁና ለየሬጅመንት አዛዦቻችሁ ሪፖርት ታደርጋላችሁ። አስታውሱ፣ እናንተና ጦሮቻችሁ ልክ በለለጠናችሁት ሁኔታ ግጻጃችሁን የምትወጡ ከሆነ፣ ለመጪዎቹ ክፍለ ዘመናት ሲነገርና ሲወሳ የሚኖርን የሶቪየት ወታደራዊ ታሪክን ገፆች ትዕፋላችሁ። የሶቪየት ህዝብም አሁን ልትገነዘቡት የማትችሉትን ክብርና ልዩ መብት በላያችሁ ያዘንብባችኋል።»

አድማጩ ከተቀመጠበት ተነስቶ፣ እያጨበጨበ በእንድ ድምዕ የስፔትናዝ ልዩ መዝሙር መዘመር ጀመረ። ማጆሮቭ ፈገግታ መግሏቸው ሔልደርን በዓይኑ በሳን በኩል ወደሚገኝ በር አሳየው። «ና» አለው በጣቱ። «ወደሰርጓጅ መርከብ ማቆሚያው ልውሰድህ።»

ሁለቱ ሰዎች በኮረብታው ቁልቁል በዘበ ወደሚጠበቀው በር አመሩ። ሔልደር ትንፋሽ እያጠረው ነው። ትሪና ራጉሊንን ባለፈው ምሽት ተሰናብቷታል። ከጉጻቷ አገግማ በተደጋጋሚ የፍቅርን ዕዋ ቀምሰዋል። ተመልሼ እመጣለሁ ብሎ ቃል ቢገባላትም ይህንን የሚያውቅበት ምንም ዘዴ የለውም። ወደጦርነት እየሄደ በመሆኑ ለእደጋ መጋለጡ አይቀርም።

በመጀመሪያው ተልዕኮው ወቅት ከሞት ጋር ተፋጦ ነበር። ይህ ከታላቅ ታሪክ የሚመደብ ወታደራዊ ልምምድ በፈጠረበት ልዩ ሀሴት የተነሳ ለማጆሮቭ ተሰምቶት የነበረው ንዴት እየበረደ መጥቷል። አሁን ታጻያ፣ በህይወት መመለስ ከቻለ የተቀረውን ዘመኑን አለሞት በማያውቀው ደረጃ ላይ ተቀምጦ እንደሚያሳልፈው ታውቆታል።

«ሔልደር፣» አለ ማጆሮቭ፣ «ይህ ቀንህ ነው። ጻሩ ግን ይህን ለመገንዘብ እስኳሁን ከተጎገረህ ትንሽ ጨምረህ ማወቅ ይኖርብህል። ነገሩ

http://ethzare.wordpress.com

ከአሜሪካዊያኑ CIA ጋር የተገናኘ ነው፣ በጊዜው ቦታ ያልተሰጠው የማይረባ መስሎ ስለታየን ነበር። ስዊድን የኑቶ አባልነትን በማግኘት ጠላታችን ልትሆን መዘጋጀቷን ሊያሳምኑን ጥረት አደረጉ፣ ሐሰት መሆኑን መህላቸው ከሚገኝ ሰው በተረዳን ጊዜ እኔ በእንድሮፖቭ አመራር ስር ለነበረው ፖሊት ቢሮው አንድ ሀሳብ አቀረብኩ። አንድሮፖቭ አመራር ስር የነበረው ፖሊት ቢሮው እቅዴን ለማሳካት የስፔትናዝ ኃይልን መደበልኝ። ከታላቁ የሀገር ፍቅር ጦርነት (Great Patriotic War) ጀምሮ ሰርጓጅ መርከቦችን ወደስዊድን የውሀ ክልላት ስንልክ ቆይተናል፣ ትንንሾቹ ሰርግጅ መርከቦች ከተሰሩ በኋላ ደግሞ ለልምምድም ጭምር የስፔትናዝ ንውስ ክፍሎችን መላክ ጀመርን።»

ማጆሮቭ ከመንገድ ላይ አንድ ድንጋይ አንስቶ በመስኩ ላይ አርቆ ወረወረው።

«የስዊድን የሰርጓጅ መርከብ አደን ቴክኖሎጂ እጅግ ደካማ ነበር። ስለዚህም የውሀ ክልላቸውን አልፈን ለመግባት አይከብደንም። በዚህ ረገድ ያላቸው ብቃት እናላ ከመሆኑ የተነሳ የቴክኖሎጂ ሀይላቸውን ቢያጠናክሩ እንኳን ልንቋቋመው እንችላለን ብዬ አሰብኩ፣ ትክክል ነበርኩ። እቅዴ ተጀምሮ በድል ሂደቱን ቀጠለ። በ1981፣ ካርልስክሮና ጦር ሰፈር አቅራቢያ አንድ የዊስኪ ደረጃ ጀልባ ባህር ወለል ላይ እንድትቆም አደረግኩ። በዚህ የተነሳ የተፈጠረው ውጥንቅጥ እንደፈለግኩት ሆኖ አገኘሁት። የስዊድን የህዝብ አስተያየት በሶቪየት ህብረት ላይ ተቃውሞውን አሰማ። ፓርላሜንታቸው ሁኔታውን የሚያጣራ ቡድን አሰማራ። ከእኛ ጋር ከፍተኛ ተግባቢነት የነበራቸው ጠቅላይ ሚኒስትራቸው እጅግ ከባድ ሀፍረት ውስጥ ተዘፈቁ። ግሩም ሆነልኝ።»

«አልገባኝም ጌታዬ፣» አለ ሔልደር።

«በሁለቱ ሀገራት መካከል የጠላትነት መንፈስን ለመፍጠር፣ ይህ ትንሽ አስፈላጊ ነበር፣» መለሰ ማጆሮቭ። «ይህን የጠላትነት መንፈስም ማጠናከራችንን ቀጠልን። ራሳችንን ከእነሱ ለመከላከል የሚል ምክንያትን የሚፈጥርልን ይሆናል።» ከት ብሎ ሳቀ። «ከሀሳቤ እየቀደምኩ ነው። ከዚያ ስተት በኋላ የስዊድን የውሀ ክልልን መጣሳችንን አጠናከርን። እነስተኛ ሰርጓጅ መርከቦችን በቡድን መላክ፣ በባህር ዳርቻዎቹ ያሉትን የስፔትናዝ ኃይላትን ማጠናከርና፣ በአንድጊዜ ሀገሪቷ ውስጥ ገብተን ለብዙ ሳምንታት መኖር፣ ጦር ሰፈሮችንና የመልእክት መለዋወጫ ቤቶችን መመሰረት እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ብቃቱ እያየለ የመጣ የስለላ ኃይልን ማሰማራታችንን ቀጠልን። በመንግሥታቸው ውስጥ በሚገኘው ሲል በተባለ ሰው በሚለቀቅልን ዝርዝር የስዊድን መከላከያ ኃይል እቅዶችን የሚገልፅ መረጃ እየታገዝን፣ የባህር ዳርቻዎቻቸው ላይ የተከሏቸው ጦር መሳሪያዎችን ቦንብና ፈንጂ እጦ መድንባቸው፣ ከፈንጂዎቻችን የብቃት ደረጃ የተነሳም እስካሁን ድረስ ሊደርሱባቸው አልቻሉም። አንተ ሰቶኮልም አቅራቢያ ያስቀመጥከው የውሀ ፈንጂ እንዳልተደረሰበት ሁሉ ለማለት ነው።»

በሩ ላይ ደርሰው አልፈው ዝቡና ወደሰርጓጅ መርከቦች ማቆመያው አመሩ። ማጆሮቭ ዊስኪ ደረጃ ያላት ሰርጓጅ መርከብ የታሰረችበት ስፍራ ሊደርስ ቆመ። በላይዋ ላይ ሰራተኞቿና ወታደራዊ መኮንኖቿ ቆመዋል። «ከአንተ ተልዕኮ በኋላ፣ ስዊድናች ከባድ መረበሽ ሪፈጥሮባቸዋል። በአብዛኛው የአንተ አስተዋፅእ ምስጋና ይግባውና ለዳግመኛ ትንከሳ ዝግጁ ሆነውልናል።

«በትክክል፣ ሔልደር፣» አለ ማጆሮቭ በፈገግታ። «ተልዕኮህ ይህ ነው። ይህቺን ሰርጓጅ በስቶኮልም የደሴቶች እጀብ ውሀ ክልል ውስጥ ባህር ላይ ስታሰርፋት በስፍራው ላይ ከባድ የባህር ኃይል እንቅስቃሴን ታስነሳለህ። የስዊድኖችን እትኩሮት በሙሉ ስቶኮልም መዳረሻ ላይ ወደምትገኝ እንዲት ደቃቅ ደሴት ላይ ታሳርፋለህ።» ማጆሮቭ የቃላቱን ኃይል ለማጉላት ለአፍታ ዝም አለ። «ከዚህ በኋላ ነፍስ አድን ኃይል እንልካለን - መቼም የማይረሱት ነፍስ አድን ኃይል እንልካለን።»

ማጆሮቭ ሔልደርን አስከትሎ ሰራተኞቹን ከቀብ ላይቆጥር ሰንጉቱ ላይ ወጣና ዋናውን በር አልፎ ወደታች ወረደ። በእቅጣጫ ተቆጣጣሪው ክፍል ገብተው ወደካርታው ጠረጴዛ አመሩ። «እዚህ፣» አለ ማጆሮቭ ወደእንዲት አነስተኛ ደሴት እያመለከተ። ደሴቷ ሔልደር በቀድሞ ተልዕኮው ወቅት ያለፉት ሆጋርን የተባለች ደሴት ናት። «ከዚህ ቀደም እንደነገርኩህ የምታሳርፉት እዚህ ስፍራ ላይ ነው። የደሴቱ ደቡብ ምስራቃዊ አካል አሸዋማ ነው። በጣም ታስጠጋታለህ። በኋላ ላይ ውሀ ይሏት እንዲሄድ እንፈልግም፣ ባለፈው ጊዜ ምንም እንኳን የስፍራው አሳ አስጋሪዎች ለፖሊስ ስልክ እስኪደውሉ የምንጠብቅ ቢሆንም አሁን ግን ራሳቸው ያገኙህል፣ እዚያ ስፍራ ሊያመጡት በቻሉት ነገር ሁሉ በመታገዝ ከመቅዕበት ይወርሩህል።»

ማጆሮቭ ፊቱን ወደሱ መለሰ። «አሁን በጥንቃቄ አድምጠኝ። በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን የትኛውም ስዊድናዊ እዚህ መርከብ ላይ እንዲወጣ መፍቀድ የለብህም ይህንን አስረግጠህ ትገልፅላቸዋለህ። የመጀመሪያው የስዊድን የባህር ኃይል ሠራዊት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ የመርከቧን ጦር መሳሪያዎች በሙሉ በተጠንቀቅ ላይ ታደርጋለህ። ሰርጓጇ ላይ ለመውጣት የሚሞክር ማንኛውም ሰው ላይ ትተኩሳለህ፣ ግልፅ ነው?»

«እምን ጌታዬ፣ ግልፅ ነው፣» መለሰ ሔልደር፣ «ነገር ግን የቆመ ሰርጓጅ መርከብን ከጥቃት እየተከላከልኩ ረጅም ጊዜ መቆየት እንደማልችል ይገባህል።»

«ይህ ይገባኛል፣ ግን ለተወሰነ ጊዜ ተቋቁመህ እንድትቆይ እፈልጋለሁ፣ እጅ ከመስጠትህ በፊት።»

«እጅ መስጠት?» አለ ሔልደር እጅግ ተደናግጦ።

«ሰርጓጇን ለረጅም ጊዜ እየተከላከልኩ መቆየት አልችልም ብለህል፣ ይህን ለማድረግ እየሞከራችሁ ሁላችሁም እንድትሞቱ አልፈልግም። አትጨነቅ በስዊድን ሕግ ሥር ብዙ አትቆይም፣ መርከብህ ላይ እንደተኩሱ ምልክት በደረሰን ጊዜ ወዲያውኑ ርምጃ እንወስዳለን፣ ለዚህ ርግጠኛ ሁን።»

«ገብቶኛል ጌታዬ።»

«ጥሩ።» ብሎ ማጆሮቭ ከኪሱ አንድ ፖስታ አውጥቶ ከፈተው። «እዚህ ላይ ሶስት የኮድ ቃላት አሉ፣» አለ ወረቀቱን እያሳየው። "WHALE የሚለውን የምትለከው ዳርቻው ላይ ያለ ችግር መድረስህን ስትግልፅልን ይሆናል፣ የስዊድን ኃይላት ሲከብቡህ FOX የሚለውን ቃል ትልካለህ፣ በተተኮሰብህ ጊዜ ደግሞ BEAR የሚለውን ቃል ትልካለህ። የተፃፈበት ቅደ ተከተል ይኸው ነው።»

«ገባኝ ጌታዬ።»

http://ethzare.wordpress.com

«ሊላኩልህም ላይላኩልህም ይሚችሉ ሌሎች ሶስት የኮድ መመሪያዎች አሉ።» ከዚሁ ውስጥ ሌሎች ሶስት ባለአምስት ሆሄ ቁጥሮች የሰፈረባት ትንሽ ካርድ አወጣና። «ተመልከት፣» አለ ማጆሮቭ ወደ ግንኙነት ክፍሉ እያመራ። «ይህ ልዩ መሳሪያ በሰርጓጇ ላይ ተገጥሟል። ብቸኛ ግልጋሎቱ ባለአምስት ሆሄ ቁጥሮችን ማስነበብ ነው። ይህኛው ቁጥር ከተላከልህ፣» አለ 10101 ወደሚለው ቁጥር እያመለከተው። «ወዲያውኑ አንተ በመረጥከው ጥሩ ኢላማ ላይ ወደሰዊድኖች በጀልባዋ ጠብመንጃ ትተኩሳለህ። ገባህ።?»

«እምን ጌታዬ።»

«ይህኛው ቁጥር ከተላከልህ ደግሞ፣» አለ 10201 ወደሚለው ቁጥር እያመለከተው፣ «ወዲያውኑ እጅ ትሰጣለህ። ይህኛው ማለትም 10301 ከደረሰህ ደግሞ፣ በዚህ ፍሪኩዌንሲ፣» ሌላ ካርድ አወጣና «ያለማቋረጥ ምልክት እንዲልክ /ለድምፅ ሞገድ/ ግንኙነት ሠራተኛው ትዕዛዝ ትሰጣለህ፣ ገባህ?»

«ሙሉ ለሙሉ አልገባኝም ጌታዬ። የድምፅ ሞገድ መላኩ ምን ያደርጋል?»

ማጆሮቭ ወደ ቻርት ጠረጴዛው መልሶ ወሰደውና። «በመጀመሪያ ተልዕኮህ ወቅት የወሰድከውን ጓዝ ያስቀመጥከው እዚህ ቦታ ላይ ነው።» ጠቆመው።

«እምን ጌታዬ፣ ቦታው እሱ ነው።» የማሮጆቭ ጣት ቀጥተኛ መስመር ያዘ ሰርጓጇን ምድር ላይ የሚያቆምበት ደሴት ደርሶ ቆመ።

«እንደምትመለከተው የድምፅ ሞገድ ምልክቱን ወደ ጓዙ ማስተላለፍ ትችላለህ። አሁን ባለበት የባህሩ ወለል ላይ በሬዲዮ ግንኙነት አማካይነት ሊደረስበት አይችልም። የሚደረስበት በዚህ የተለየ ርግብግቢት (Frequency) ብቻ ያውም በድምፅ ሞገድ ምልክት ነው። ምልክቱ በሚደርሰው ጊዜ የላይኛውን አካሉን አላቅቆ ከታችኛው ጋር በሽቦ እያይዞ ያንሳፍፈዋል። ተንሳፋፊው አካሉ የሳተላይት ስርጭትን መቀበል እንደሚችል አንቴና ሆኖ ያገለግላል።»

«ስርጭቶችን የሚቀበል፣ ጌታዬ?» ሔልደር የተረዳው የመሳሪያው ግልጋሎት ማሰራጨት እንጂ መቀበል እንዳልሆነ ነበር።

ማጆሮቭ ለእፍታ ግራ የተጋባ መሰለ። «ይቅርታ አድርግልኝ፣ መሳክ እንጂ መቀበል ማለቴ አይደለም። መሣሪያው ተገቢውን መረጃ ለሚመጣው ሀይላችን ለሚያሰራጨው ሳተላይት ይልካል። አሁንም ተከተለኝ ሔልደር።»

ማጆሮቭ ወደሰገኑቱ በመውጣት ከብረቱ የውሀ መከላከያው ጋር የታሰረውን ውሀ የማያስገባ ሳጥን መሰል ነገር አላቀቀው። በውስጡ ሔልደር በግንኙነት ክፍሉ ውስጥ የተመለከተውን ዓይነት መሳሪያ ይዟል። «እዚህ እንደምትመለከተው ባለአምስት ሆሄ ቁጥሮችን የሚቀበል መሳሪያ አለ፣ እዚህም ሆነክ ታችኛው ክፍል ምልክቱ በተላከልህ ቅፅበት ለማንበብ ያስችልሀል።» መከደኛውን ቦታው መልሶ እነበረበት ገጠመው። «አሁን፣ እስካሁን የሰጠሁህን መመሪያዎች እንድትደግምልኝ እፈልጋለሁ።

ሔልደር የተባለውን ሁሉ በዝርዝር ደገመለት።

«ግሩም፣» አለ ማጆሮቭ ትከሻውን ቸብ ቸብ እያደረገው። «አሁን ከሠራተኞችህ ጋር አስተዋውቅህለሁ።» ብሎ ከሰገነቱ መውረድ ሲጀምር ወደላይ እየወጣ ከነበረው ጆንስ ጋር ተገናኙ።

«ኮሎኔል፣» አለ ጆንስ ትንፋሽ እያጠረው። «ስላቋረጥኩህ ይቅርታ፣ ግን አፒቼላ ሔዷል።»

ማጆሮቭ ተኮሳተረ። «ሔዷል? ምን ማለትህ ነው?»

«ማለቴ፣ ጌታዬ ከጦር ሰፈሩ ሔዷል።»

«ይህ የማይሆን ነው፣» አለ ማጆሮቭ ጠበቅ ባለ እንደበት። «ማንም ሰው ከዚህ መውጣት አይችልም።»

«ያልኩው እውነት ቢሆን ደስ ባለኝ ኮሎኔል ግን ሊገኝ አልቻለም። አልጋ የተባለችው ልጅ ዛሬ ጠዋት ነው መጥፋቱን ያመለከተችው፣ እኔም ወዲያውኑ ፍለጋ እንዲጀመር ትዕዛዝ ሰጠሁ።»

«እዚሁ እንድ ስፍራ ላይ ይገኛል፣ ጠብቅ፣» አለ ማጆሮቭ።

ጆንስ ፊቱ እንደከፋው ነው። «ኮሎኔል፣ ልጅቷ እንደምትሰው ትናንት ተሰዓቱን ያሳለፈው እንግዳ ማረፊያ ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጦ የአሜሪካዊው መዝናኛ ጀልባ ሲጠገን እየተመለከተ ነበር። እራቱን እንኳን እዚያው ወስዶ ነው የበላው። እምስት ሰዓት ገደማ ብቻዋን ተኛች፣ ስትነቃ አጠገቧ አጣችው።»

ማጆሮቭ በእግራሞት ተዋጠ። ሰዓቱን ተመለከተ። «መርከቧ የሔደችው እኩለ ሌሊት ላይ ነው። እስካሁን ስዊድን ውሀ ክልል ውስጥ ትገባለች፣ ምናልባትም ስዊድን ደርሳ ይሆናል። እስካሁን ጎትጎንድ ይደርሳሉ።» «እምን ጌታዬ፣» አለ ጆንስ፣ «ግን ወጣም ወረደ አፒቼላ የሚያውቀው ምንም ነገር የለም እንዴት ሊያውቅ ይችላል? ሚስጥራዊ ስፍራዎች አካባቢ እንዳይደርስ ተደርጎ ነበር የቆየው።»

ማጆሮቭ ተኮሳተረና። «ከሚስጥራዊ ስፍራዎች ሁሉ በላይ ሚስጥራዊ የሆነ እንዳይደርስ ያልተከለከለበት ቦታ አለ። የኮምፒውተሩን መረጃዎች ማግኘት ይችላል።» ለእፍታ አሰብ አደረገ። «ስለተልዕኮዋችን እውቀ ከሆነ ወደ ዴንማርክ አይሄዱም፣ በጣም ይርቃቸዋል። ወደስዊድን ወይ ወደ ስቶኮልም ይሄዱና ከስዊድን መንግስት ወይ ከአሜሪካ ኤምባሲ ጋር ግንኙነት ይፈጥራሉ።»

«የባህር አሰላ እንዲደረግባቸው ሳድርግ?»

ማጆሮቭ ለእፍታ ያህል አይብሉውን እየነከሰ ቆየ። «አይሆንም፣ ለእንቅስቃሴ እጅግ ስለተረብን ወደ ስዊድን የውሀ ክልል ጀልባዎችንና ሔሊኮፍተሮችን መላክ እንችልም። ያም ሆነ ይህ ምንም ነገር የማወቅ እድላቸው ጠባብ ነው። አፒቼላ ምናልባትም እዚህ እንዲቆይ መገደዱ ሪብሾት ሊፈረጥጥ ወስኖ ሊሆን ይችላል።»

«እንድ ሌላ ነገር አለ፣» አለ ጆንስ። «ስቶኮልም ከሚገኘው ሲል መልዕክት ደርሶናል። ካር የተባለ የአሜሪካ ሴናተር ብሩኪ ኪርክላንድ የተባለችን ግለሰብ ወደዚያ ሊልክ ነው። ነገ በሚኒስትሩ ቀጠሮ አላት። ሲል እንደሚያስበው ይህ ኪርኪላንድ የተባለ ስም የሽፋን ነው። ስለዚህ ፌሬት ፍለጋ አድርግ። ይህች ኪርኪላንድ የተባለች ሴት ስሟ ሩል ነው። ከዚህ ሌላ አፒቼላ የሩል ሰላይ መሆኑን እረጋግጠልኛል።»

«ይህ በጣም መጥፎ ነገር ሊሆን ይችላል፣» አለ ኮሎኔሉ። «ሩል አፒቼላን ስቶኮልም ላይ ልትገናኘው ነው ብሎ፣ ሲል ያመነበት ምክንያት አለው?»

«የለውም፣ ሊሆን የሚችል አይመስልም። የአፒቼላ ማምለጥ ከአሜሪካዊው ጀልባ መምጣት ጋር የተያያዘ እጋጣሚ ነው። ወደዚያ እየመጣ

http://ethzare.wordpress.com

እንደሆነ ልታውቅ አትችልም:: የሩል ወደስቶኮልም የመሄድ ምክንያቱ ሲናተሩ ነው:: ሀሳቧ መከላከያ ሚኒስትሩን ማሳወቅ መሆኑ ግልፅ ነው::»

አፒቼላ የሩልን መላምቶች የሚያረጋግጡ ፡መረጃ ይዞ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: ግን በይሆናል መሄድ አንችልም:: ያለ መረጃ ቢሆን እንኳን ሩል በሚኒስትሩ ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰው ልታሳምን ትችላለች:: መዓከላዊ ስቶኮልም ውስጥ ኃይል አለን እይደለም?»

«እዎን ጌታዬ፣ ቡድን አንድ፣ ተልዕኳቸው ፓርላሜንቱንና ቤተመንግስቱን መቆጣጠር ነው:: ሌሎች ሁለት የስቶኮልም ህይላት፣ ቡድን ሁለትና ሰስት በምዕራብ የሚገኘው የስቶኮልም ወታደራዊ አካል የበላይ መምሪያ ላይ ያነጣጠረ ነው::

ማጆሮቭ ተስማማ:: «ቡድን አንድ በስቶኮልም አየር ማረፊያ፣ በአሜሪካን ኤምባሲና በመከላከያ ሚኒስትር አንድ አንድ አባል እንዲመድብ መልዕክት ይላክለት:: ከዩናይትድ ስቴትስ በሚገባ ማንኛውም በረራ ላይ የተሳፈረች ኪርኪላንድ ወይንም ሩል የተባለች ሴት ከተገኘች በተገኘው የመጀመሪያው አጋጣሚ ትገደል:: የአፒቼላን መልክና ቁመና የያዘ ማንኛውም ሰው በአየር ማረፊያው ወይ በመከላከያ ሚኒስቴሩ ወይንም በኤምባሲው ከታየ ከመቅፅበት ይገደል:: ሲ የተባለው አሜሪካዊም ተመሳሳይ እርምጃ ይወሰድበት:: በተቻለ ሁሉ ያለግርግር እንዲፈፅሙት ንገራቸው፣ ግን በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን መፈፀም ይኖርበታል::»

«እሺ ጌታዬ::»

ማጆሮቭ ወደሔልደር ፊቱን አዞረና:: «ይቅርታ ግን አሁን መሔድ ይኖርብኛል:: ሰራተኞችህ እንዚውልህ፣» አለ በሰርጓጇ ላይ ወደቆሙት ሰዎች እያመለከተው:: «ሁሉም በጥንቃቄ የተመረጡ ሲሆን ያንተ ናቸው::» እጁን ዘረጋለት:: «መልካም ዕድል ሔልደር:: ስዊድን ላይ እንገናኝ::»

«እመሰግናለሁ ጌታዬ፣» አለ ሔልደር እየጨበጠው:: ማጆሮቭና ጆንስ ሔዱ:: ሔልደር የመርከቧን ሰራተኞች ቁልቁል ተመለከተ:: «እትኩሮታችሁን እሻለሁ፣» ሲል ሁሉም ወደሱ ፊታቸውን አዞሩ:: «ሔልደር እባላለሁ:: ከዚህ በፊት አብረን አልተጓዝንም:: ግን ሁላችንም በሚገባ ሰልጥነናል:: ይህቺን ጀልባና አባላቶቿን በደንቡ መሠረት እመራለሁ:: ስፍራ ስፍራችሁን ያዙና ለጉዞ ተዘጋጁ::» ከተወሰኑት በስተቀር ሁሉም ገቡ::

ሔልደር ትዕዛዝ ማስተላለፉን ቀጠለ:: ግን ስጋት ገብቶታል:: ይህች ጀልባና አባላቶቿ ከደንብ ውጪ ናቸው:: አንድ የሚነዘንዘው ነገር አለ ግን ምንነቱን አልተረዳውም፣ ለይቶ ሊያውቀው አልቻለም:: መንገድ ከጀመሩ በኋላ ይህን ያደርጋል፣ ካለፈው ተልዕኮው ጋር የተገናኘ ሊያስታውሰው ያልቻለው ነገር ነው:: ግን ጊዜ ይኖረዋል አስቦ ይደርስበታል::

ከዚያ አንድ ነገር ተከሰተለት:: የኮሚኒስት ፓርቲው ቀዳሚ ዋና ፀሐፊ ድንገተኛ ወረራው በማንኛውም መልኩ አጠያያቂ ሁኔታ ውስጥ ከገባ ወረራው እንዲሰረዝ እሱ ባለበት ለማጆሮቭ ሲናገሩ አዳምጧል:: ሆኖም፣ አሁን ለሔልደር በሰጠው መመሪያ ላይ የወረራውን መሠረዝ የሚገልፅ ምንም ዓይነት ኮድ አልሰጠውም::

ሩል አብዛኛውን የእለቱን ጊዜዋን ያሳለፈችው በማትኖርበት ጊዜ የሲቪየት ቢሮው ያለ እከል እንዲንቀሳቀስ ነገሮችን በማስተካከል ነበር:: አስር ሰዓት ላይ ለበታቾቿ ተለይተው የተቀመጡ የልዕኮዎችን ለመስጠት በማለት ስብሰባ ጠራች:: አስራ አንድ ሰዓት ላይ ልክ ስብሰባው ሲበተን የአላን ኒክሰን ፀሐፊ በሯ ላይ ቆማ ተመለከተች::

«ሚሲስ ሩል፣ ሚስተር ኒክሰን ቢሯቸው ሊያገኙሽ ይፈልጋሉ፣» አለቻት::

ሩል ሴትየዋ በመደወል ፊንታ ወደሷ መምጣቷ አስገርሟታል:: «በሁለት ደቂቃ ውስጥ እመጣለሁ፣» አለቻት፣ «መጀመሪያ፣ የምቆልፍባቸው የተወሰኑ ዶሴዎች አሉኝ::»

«እባክሽን አትቆዪ፣» ብላት ሄደች::

ሩል ዶሴዎቿን ቦታቸው መልሳ ክቆለፈችባቸው በኋላ ወደኒክሰን ቢሮ አመራች::

«ቀጥ ብለሽ ግቢ፣» አለቻት ፀሐፊዋ::

አለን ኒክሰን ከጠረጴዛው በስተጀርባ ተቀምጧል:: እንድ የማታውቀው ሰው ከኒክሰን አጠገብ ተቀምጧል:: «ግቢ፣ እባሽን ካትሪን፣» አለ ኒክሰን፣ እና በሩን ዝጊው::»

ሩል በሩን ዘጋችውና ከሁለቱ ሰዎች ፊት ለፊት በሚገኘው ወንበር ላይ ተቀመጠች::

«እሱ የውስጥ ምርመራ ክፍሉ ቻርለስ ሙርታይመር ነው፣» አለ ኒክሰን:: «የሚጠይቅሽ ጥቂት ጥያቄዎች አሉ፣ ልትመልሺለት ፈቃደኛ ነሽ?»

ለአፍታ ያህል ቻርልስ ሙርታይመርን ገርመም እደረገችው:: ሙርታየመር ገና ቃል ባይተነፍስም የሚናገረውን አውቃለች:: የውስጥ ለውስጥ ምርመራን የማይጠላ ማንም የለም:: «በቁጥጥር ስር እያደረግከኝ ነው እለን?»

ኒክሰን ፊቱ ቀላ:: ሙርታይመር ፈጠን ብሎ ተናገረ:: «አሁን፣ ሚሲስ ሩል፣ እዚህ ጊዜ ላይ ይህ አስፈላጊ አይመስለኝም:: ውይይታችን በቃ መልክ አይያዝም::»

«በቃል መልክ?» ጠየቀች ሩል:: «ንገረኝ እስኪ፣ ሚስተር ሙርታይመር ይህ ውይይታችን በቴፕ ይቀረፃል እንዴ?»

ኒክሰን የባሰ ፊቱ ቀላ፣ ሙርታየመር ንግግሩን ቀጠለ:: «እየተቀረፀ ቢሆን ይረብሽሻል ሚሲስ ሩል?»

ሩል አሁን መጥፎ ሁኔታ ውስጥ መግባቷ ታያት:: የድርጅቱ ሠራተኞች ከሌሎች ዜጎች ያልተናነሰ መብቶች አሏቸው:: ግን በመብቶቿ መጠ ቀሙ ጥሩ ሀሳብ መስሎ አልታያትም:: ለሳምንታት ወይንም ለወራት ከስራዋ ልትታገድና የምርመራ ክፍሉ ሜና ሙሉ ሀይል ሊያርፍባት ይችላል:: ይህን አትፈልገውም፣ ቆይ እስኪ፣ አሰበች:: ትንሽ ፈገግ ብላ፣ «አለቃዬ ለውይይት ጋብዞኝ፣ በኋላ ላይ ውይይታችን በቴፕ መቀረፁን ባውቅ፣ ይህ ሊረብሸኝ ይችላል::» አለች የድምጿን ቃና ለስለስ ለማድረግ እየጣረች:: «እንተ ብትሆን አትረበሽም ሚስተር ሙርታይመር?»

አሁን ደሞ የሙርታይመር ፊት በተራው ቀላ:: ለአፍታ ያህል ምንም ሳይናገር ከቆየ በኋላ የኒክሰንን ጠረጴዛ መሳቢያ ከፍቶ አንድ ቁልፍ ሲጫን

http://ethzare.wordpress.com

ቀጭ የሚል ድምፅ ተሰማ። «ይህ ውይይታችን እየተቀረፀ አይደለም። አሁን የተወሰነ ጥያቄዎችን ልጠይቅሽ እፈልጋሁ።»

«ችግር የለም፣» መለሰች ሩል። «ስለምን ማወቅ ትፈልጋለህ?»

ሙርታይመር ከወንበሩ ሳይ ወደፊት ዘመም አለ። «ሚሲስ ሩል እዚህ ድርጅት ውስጥ ከተቀጠርሽበት ጊዜ ጀምሮ፣ ከደርጅቱ ጋር የፈረምሽውን የቅጥር ውል የሚጥስ ማንኛውንም ነገር ፈፅመሽ ታውቂያለሽ?»

አጭበርባሪ ጥያቄ ነው ብላ አሰበች። እም ካለች ከመቅፅበት ከሥራዋ ትታገዳለች፣ አላደረግኩም ካለች በማጭበርበር ከስ ሙሉ ልሙሉ አጋልጦ ይሰጣታል፤ ቃለ መህላ ያለመፈፀም ምንም አይጠቅማትም። ማነው አንድ ዶሴን እቤቱ ወስዶ ያልሰራ ወይንም አንድን ሚስጥር እራት እየበላ ወይም አልጋ ላይ ያልተነፈሰ? ይህን ሁሉም ያደርጋል። «ይህ እጅግ ጠቅለል ያለ ጥያቄ ነው ሚስተር ሙርታይመር። መለሰች። «ለምን ለይተህ አትጠይቀኝም?»

አለን ኒክሰን ከዚህ በላይ ራሱን መቆጣጠር አልቻለም። «ይህን ጉዳይ እያቀለልሽልን አይደለም፣ ካትሪን፣» እጁተመተመ።

«ምን እንዳቀልልህ ነው የሚፈለግብኝ አለን?» አለች።

ሙርታይመር እጁን አንስቶ ዝም አሰኛቸው። «መልካም፣ የተለየ ጥያቄ እንጠይቃለን። ያለፈቃድ ከድርጅቱ ክልል ውጪ ሚስጥራዊ ንብረትን ይዘሽ ወጥተሽ ታውቂያለሽ?»

ያለፈቃድ ከሀገሪቷ መውጣቷን እያወቁ ነው ይህን የሚያነሱባት? ቢያንስ ማወቃቸውን ሳይመን ነግሯታል። ውሸቱን ይሆን እንዴ? አሁን ያለ ምንም ማስረጃ እንዲወነጅሏት መፍቀድ የለባትም። ዛሬ ወደ ስቶኮልም መሄድ አለባት። «ሚስተር ሙርታይመር፣» ትንሽ እንደመለሰቸት ያላት ለመምሰል እየሞከረች። «እኔ የዩናይትድ ስቴትስና የዚህ ድርጅት ታማኝ ዜጋና ሰራተኛ ነኝ። በኔ ላይ የምትመሰርቷቸው ክሶች ካሉ መሰርቷቸውና በተገቢው መንገድ ምላሽ እሰጣለሁ።» ወይ ተጋፈጠኝ ወይ ዝምበል አለች በልቧ። ከተጋፈጣት ከሥራዋ ታግዳ መቀጣቷ ነው። ትንፋሿን አመቀች።

ሙርታይመር ወንበሩን ተደገፈ። ሁኔታው የማፈግፈግ ቢሆን ተመኘች። «እንዳልኩሽ ሚሲስ ሩል፣ ይህ በሥራ ባልደረቦችሽ መህል የሚደረግ ውይይት ነው። ግሩም፣ አሁን ደግሞ የሥራ ባልደረቦች ሆኑ። «በዚህ መልኩ ላሰቀምጠው፣ ሚስጥራዊ ንብረቶችን ከድርጅቱ ክልል ውጪ ይዘሽ በመውጣት ክስ ብጠይቅሽ ትክጂዋለሽ?»

«ቢሆንስ ብለህ እየተናገርክ ነው?»

«ታዲያላ፣» ፈገግ አለ።

«ቢሆን ካልን፣» አለች፣ ሚስጥራዊ ንብረቶችን በመውሰድም ሆነ በማንኛውም ድርጊት ክስ ብትመሰርትብኝ መማክርቱ ባለበት ወዲያውኑ ችሎት እንዲቀመጡልኝ ጥያቄ አቀርባለሁ።»

ፈገግታው ድራሹ ጠፋ። «ገባኝ።»

ሙርታይመር አንድ ክስ ላይመሰርትባት በፊት ቶሎ ወደኒክሰን ዞረች። «አለን፣ ነገ ጠዋት ለእረፍት እሄዳለሁ፣ ከረጅም ጊዜ በፊት አንተ የፈቀድክልኝ ጉዞ ነው፣ ደሞ ብዙ ስራ አለብኝ።» ወደ ሙርታይመር እየተመለከተች። «ይህ የማይረባ ደግሞ የሶቪየት ሰርጎ ገብ ወይ ሌላ ነገር ነች

ብሉ የሚያስብ ከሆነ አሁኑኑ በትጥጥር ስር እንዲያውለኝ ንገረው። ካልሆነ ወደ ቤቴ ተመልሼ ጓዜን ላዘጋጅ።» ቆመች።

ሙርታይርመር ጎንበስ ብሉ ለኒክሰን አንድ ነገር ሹክ አለው። «ይሽው ነው በታ ካትሪን፣» አለ ኒክሰን። «ለጊዜው መልካም የእረፍት ጊዜ ይሁንልሽ። ስትመለሺ እንገናኛለን።»

ቶሉ ቶሉ እየተነፈሰች ወደበሩ አመራች። «በናፍቆት እጠብቃችኋለሁ። አለች ፈቷን ሳታዞር። በሩን ከፍታ ደርግማ ዘጋችው። ወደቢሮዋ ስታመራ አንድ በተራመደች ቁጥር ልቧ ሁለት ጊዜ ይደልቃል። ቦርሳዋን አነሳችና ከህንፃው ወጣች።

በተጨናነቀው ትራፊክ ወደቢቷ ስታመራ ለጥቂት እንደተረፈች አሰበች። ገና ለራሳቸውም ርግጠኛ ሳይሆኑ ነው የሚያስጨንቋት። ተመልሳ ስትመጣ አንድ ነገር አግኝተውባት ሊጠብቋት ይችላሉ። ያላት ብቸኛ መከላከያ ትክክል ሆና መገኘቷ ነው። ሽብር የተቀላቀለበት ሳቅ ሳቀች። ስራዋን ይዛ መቆየት የሚያስችላት አንድ ነገር ሶቪየት ስዊድንን ስትወርራት ብቻ ይሆናል።!

45

ሔልደር ዊስኪ ደረጃ መርከቧን ከላይፓጃ ይዞ ከውሀ በታች እየነዳት የሔልሲንኪ- ስቶኮልሟን ዕቃ ጫኝ ጀልባ ሊደርስባት ወደ ሰሜን አቀና። ከሠራተኞቹ ጥቂቶቹን ካሰፈው ተልእኮው ያውቃቸዋል አንዱን መኮንን ግን እያውቀውም።

«ኮልቻክ እባላለሁ፣» አለ ሰውየው። አልጨበጠውም። «የፖለቲካ መኮንን ሆኜ ተመድቤያለሁ።» በቁመት ከሔልደር ይበልጣል፣ ቀጭንና ግራጫ ገፅታ ያለው ነው። ለማንበብ የሚያስቸግር ዓይነት ገፅታ።

«ኮልቻክ፣» አለ ራሱን ከፍ ዝቅ እያደረገ። ሰውየውን መርከቡ ላይ በማግኘቱ ተገትሯል። ከማሊቡ ገፅታዎች አንዱ የፖለቲካ መኮንኖች ያለመኖራቸው ነበረ። በሶቪየት የታጠቁ ኃይላት ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዳቸው ንዑስ አከላት፣ ለንዑስ ክፍሉ አዛዥ ሳይሆን ለፓርቲው የበላይ አለቆች የሚታዘዝ የፖለቲካ መኮንን አሏቸው። የፖለቲካ መኮንኖች የጀርባ ላይ ቅማል ከመሆናቸው ሌላ ሔልደርን ጨምሮ ማንኛውም ወታደራዊ አዛዥ ይንቃቸዋል። ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ ማጆሮቭ ለምንድን ነው በፓርቲ ዝባዝንኬ ውስጥ የሚያስገባው?

«የተሰጠኝ መመሪያ በዚህ ተልዕኮ ላይ በሁሉም ጊዜያት ከአጠገብህ እንዳልለይ ነው፣» አለ ኮልቻክ።

«ገባኝ፣» አለ ሔልደር። «ታዲያ መርከቤ ላይ ታጥቀህ የጣሽው ለምንድን ነው?» ኮልቻክ ጃኬቱ ስር በትከሻ ሰገባ ውስጥ የተንጠለጠለውን ሽጉጥ እያመለከተው።

«እንድታጠቅ ታዝዣለሁ ነው፣» አለ ኮልቻክ።

ማጆሮቭ፣ ሔልደር ተልዕኮውን መወጣቱን ለማረጋገጥ ያደረገው መሆኑ ገባው። ከማጆሮቭ ትዕዛዝ ውጪ ካፈነገጠ ኮልቻክ እሱን ገድሎ

http://ethzare.wordpress.com

ተልዕኮውን ራሱ እንዲያጠናቅቅ መመሪያ እንደተሰጠው አልተጠራጠረም። ሔልደር አሁን ለፖለቲካ መኮንኑ የሚያናግርበት ስሜት ውስጥ አይደለም።

ይህን ተልዕኮ ካጠናቀቀ እነዚህን የመሳሰሉ ሰዎች አጠገቡ አይደርሱም። ካላጠናቀቀው መሞቱ ነው። «ግሩም፣» አለ ሔልደር። «መመሪያዎችህን ተግባራዊ አድርግ፣ ግን ከመንገዴ ውጣ። በጀልባዋ ላይ ስዘዋወር እንዳላላትምህ ተጠንቀቅ።»

ኮልቻክ አይኖቹን አርገበገበ። ወታደራዊ አዛዦች በዚህ መልክ አናግረው እንደማያውቁ በግልፅ ይታይበት ጀመር። «አቅጣጫህ ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው።

«እንተ ስለፓርቲህ መርሆ ተጨነቅ፣ እኔ ስለአቅጣጫዬ እጨነቃለሁ።» ገፍቶት አለፈና የግንኙነት ክፍሉ ውስጥ ገባ። በጠባብ ቦታ ላይ የነበረው የራዲዮ ግንኙነት ሰራተኛ ተነስቶ አልተቀበለውም። መነሳትም አይችልም። «ስፓርክስ፣» አለ ሔልደር፣ «በተወሰኑ ሁኔታዎች ወቅት በዚህ ርግብግቢት /ፈሪኩዌንሲ/ የድምፅ ሞገድ መልዕክት እንድታስተላልፍ ይጠበቅብህ ይሆናል፣» ብሎ ማጆሮቭ የሰጠው ካርድ አቀበለው።

«እሺ ጌታዬ፣» ብሎ የሬዲዮ ባለሞያው ካርዱን ተመለከተ። «ስለዚህና ስለልዩ የሞገድ መቀበያው ተነግሮኛል ግን ስለ ኮዶች አልተነገረኝም ነበር።»

«ኮዶቹ እኔ ዘንድ አሉ፣» አለ ሔልደር። «እኔ በሕይወት እስካለሁ ድረስ ሞገዱን የምትልከው በኔ ትዕዛዝ ብቻ ይሆናል። ገባህ?»

ሰውየው ከበስተጓላው የቆመውን ኮልቻክን ተመለከተና ፈገግ አለ።

«አዎን ካፒቴይን ገብቶኛል። በእርስዎ ትዕዛዝ ብቻ።»

ሔልደር ትከሻውን ቸብ ቸብ አደረገውና። «ጥሩ ሰው።» ሁለት ሰራተኞቹ ከሁለት ትልልቅ መዝውሮች ፊት ተቀምጠው ከፊት ለፊታቸው ያሉትን ቁጥሮች ይመለከታሉ። «የራዳር ተቆጣጠሪ፣ ከሔልሲንኪ ወደስቶኮልም የምትሔደውን የእቃ ጫኝ መርከብ ተከትለን ደሴቶቹ መሀል እንደምንገባ ተነግሮሀል?»

«አዎን ጌታዬ። ባለፈው ተልኳ ወቅት የራዳር ባለሞያው እኔ ነበርኩ ካፒቴይን። የሚደረገውን አውቀዋለሁ። ባልደረባዬም ያውቀዋል።»

«ጥሩ፣» አለና ሔልደር መኮንኖቹ በቻርት ጠረጴዛው ዙሪያ እንዲሰበሰቡ ምልክት ሰጣቸው፣ ከዚያም ተልዕኮውን በዝርዝር ገለፀላቸው።

«ጥያቄዎች አሉ?» ጠየቀ።

የተናገረ የለም። ኮልቻክ አንድ ነገር መናገር ጀመረና ዝም አለ።

«እሺ እንቀጥል።»

ተሲዓቱን ሰርጓጇ የሰሜኑን አቅጣጫ ይዛ ጉዞዋን ቀጠለች፣ የኢስቶኒያ ደሴት የሆነችውን ሒውማ አልፋ የፊንላንድ ሰላጤ ልትደርስ ትንሽ ቀርቷታል። እቃ ጫኝ መርከቧን የሚያጎናብት ሰፍራ ሲደርሱ ፍጥነታቸውን ቀንሱና ሔልደር ግዙፍ ጀልባ እስኪያገኝ በፔሪስኮፑ ሲጠቀም ቆየ። በተረጋጋ ድምፅ ትዕዛዝ ሲሰጥ ሰርጓጇ ወደጀልባዋ ጓሳ ተጠግታ ድምጿ ከጀልባዋ ድምፅ ጋር እስኪመሳሰል ድረስ ቀስ እያለች በቅርብ ርቀት መከተል ጀመረች።

«ቁጥር አንድ፣» አለ ለዋና መኮንኑ፣ «ቦታ ተረከቢኝ፣ ለእፍታ ያህል ወደክፍሌ መግባቴ ነው። ሰርጓጇ የደሴቶቹ አጀብ መሀል ስትገባ ፍጥነቷን ወደ ሰድስት ኖት ትቀንሳለች። ከእቃ ጫኝ መርከቧ ጋር እንዳታጋጪት ተጠንቀቅ። በጥቂቱ እንኳን ያልተለመደ ነገር ከተመለከትክ ጥራኝ።»

«እሺ ጌታዬ፣» አለ።

ሔልደር ለእፍታ ያህል ቆም ብሎ ቻርቱን እየተመለከተ እያንዳንዱን ገፅታውን አጠናው። በጣቱ ባህሩ ወለል ላይ ከተቀመጠው ጓዝ እስከ ማረፊያ ነጥቡ ድረስ ያለውን ክልል በጣቱ እየጠቆመ ተመለከተው። ጓዙን የከበበውን ሰፍራ ላይ የተቀመጡት የደሴቶቹ እጀብ ሰፍራውን ከቦታል። ጓዙ የሚገኘው በደረቅ መሬት በተከበበ ሰፍራ ላይ ነው። ሔልደር ወደካፒቴይኑ ክፍል አመራና መጋረጃውን ዘግቶ አልጋው ላይ ጋደም አለ።

አንድ ፍርሀት ላዩ ላይ ከማጥላቱ ሌላ ሁሉ ነገር በፍፁም ስርዓት ላይ ነው ብሎ አሰበ። ይህ ፍርሀቱ ከአንድ ተልዕኮ ቢፈት የሚሰማው ዓይነት ፍርሀት አይደለም። ይህን ስሜቱን አልወደደውም፣ ስለዚህ ምንጩን ለማወቅ ህሊናውን መፈተሽ ጀመረ። የሚረብሸው ጓዙ ነበር፣ ጓዙን ራሱ ነው ወስዶ ያኖረው። በድርጊቱም ትልቅ ርካታ ተሰምቶታል። አሁን ግን በእርካታ ፈንታ እያስጨነቀው ነው። ለምን? ውስጠ ህሊናው እየነገረው ያለው ምንድን ነው?

ይህን እያሰበ እንቅልፍ ወሰድ መጣ እያደረገው ህሊናው ራሱ አስቦ እንዲፈታው ፈቅዶለት ቆየ። ከዚያ አይኖቹ ፍጥጥ ብለው ተከፈቱ። ጓዙን የተመለከተ ሶስት ጥያቄዎች እየወተወቱት አንድ መልስ ላይ አውጠነጠኑ። ይህን ህሳብ የቀውስ ህሳብ ብሎ ተወው፣ ደግሞ ሲያስበው ግን ዳግመኛ እዚያው መልስ ላይ ደረሰ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የማጆሮቭን ቆራጥነት ሲመስክርና ሲያደንቅ ቆይቷል፣ አሁን ግን ይህን ቆራጥነት ዝቅ አድርጎ እንደገመተው ተረዳ። ማጆሮቭ፣ ድንገተኛም ይሁን አይሁን በስዊድን ላይ የሚያደርገውን ወረራ የማስቆም ምንም እቅድ የለውም። ስዊድኖች ቶሎ ከነቁና የሶቪየት መንግስት ወደጓላ ለማለት ከሞከረ፣ ማጆሮቭ ያለምንም አማራጭ ወረራውን እንዲገፉበት ያስገድዳቸዋል። ይህንን የሚያደርግበት መሳሪያውም ሔልደር ሆኗል።

ማሊቡ ላይ ጓዙን የጫኑትን ሰዎች ያደረጓቸውን ቢጫ ሪቫኖች አስታወሰ እነዚያ ሪቫኖች በጄልየት ሰርጓጅ ማቆሚያና ማስወንጨፊያው ውስጥ ወደሰማያዊነት ተለውጠው ተመልክቷል። በርግጥ ማጆሮቭ ጓዙ የያዘው የተቃጠለ የራኒየም 235 /የኒውክሊየር ቦንብ መስሪያ ንጥረ ነገር/ መሆኑን ነግሮታል። ዳሩ ግን ዝታጭ ቢሆን ኖሮ ሪቫኖቹን ወደሰማያዊ መለወጥ የሚችል አረር ማመንጨት ባልቻለ ነበር። በኒውክሌር ሰርጓጅ መርከቦች ውስጥ ባገለገለባቸው ጊዜያት ሪቫኑን ከቢጫ ወደሰማያዊ መለወጥ ችለው የሚችለው የራዲየሽን መጠን ምን ያህል መሆኑን ያውቃል።

የማጆሮቭን ስህተት አስታወሰ። የጓዙ አንቴና የሳተላይት ሰርጭቶችን መቀበል መሆኑን አምልጦት ተናግሯል። ከዚያ ግን ኦርሞት ጓዙ የሚልክ ብቻ ነው ብሎታል። ግን ይህ መሰል የውሀ ላይ መልዕክት አስተላላፊዎች ለሳተላይት አያሰራጩም። የሚልኩት በአቅራቢያቸው ለሚገኙ መርከቦች ነው። ሔልደር ማሊቡ ውስጥ በበላይ መምሪያዎቹ ህንፃ ላይ የተሰቀሉትን የሳተላይት ሰህኖች አስታወሰ። ለአንድ ሳተላይት መረጃን መላክ ይችላሉ፣ ይህም ለጓዙ ይደርሳል። ይህ የሚሆነው ግን ሔልደር የጓዙን አንቴና የሚለያየውን የድምፅ ሞገድ ስርጭት ከለቀቀ በኋላ ብቻ ነው።

http://ethzare.wordpress.com

የማጆሮቭን የማያወላዳ ቆራጥነቱን አስታወሰ። ከሰጠው ኮዶች መካከል አንዳቸውም ተልዕኮውን ከማቋረጥ ጋር ግንኙነት አልነበራቸውም። WHALE, FOX ወይንም BEAR የሚሉትን ኮዶች ለመላክ ካልሆነ በስተቀር የሬዲዮ ግንኙነት ማድረግ አይችሉም። ሰርጓጇ ከባለእምስት ሆሄያት ቁጥሮች በስተቀር ምንም ነገረ መቀበል አትችልም። ይህቺን ዊስኪ መርከብ ከግዳጇ መመለስ በፍፁም የማይቻል ነው።

የሒልደር መደምደሚያ የሷላ ኋላ ማምለጫ የሌለ ሆነ። ያ «የመልዕክት ማስተላለፊያ ጓዝ እንደእውነቱ ከሆነ የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ነው።

ተነስቶ ወደአቅጣጫ ተቆጣጣሪው ከፍል ተመሰሰ። መኮንኑን ከመቀመጫው አስነስቶት ተቀመጠና በጓዙ አካባቢ የሚገኘውን ስፍራ ዳግመኛ ተመለከተው። መሳሪያው የተቀመጠው ቦዩ መሀል ላይ ገደማ ነው። ከቦዩ በስተምስራቅ ቆሳ አለ፣ ሒልደር ትንሿን ሰርጓጅ ይዞ የገባበት ክፍተት ማለት ነው። በሰሜንና በደቡብ ደሴቶች አሉ፣ በስተምዕራብ የስቶኮልም ከተማ ትገኛለች፣ ብዙ የውሀ አካላት ያቆራርጧታል።

ቦምቡ ትልቅ አደጀለም፣ መሆንም አያስፈልገውም። ግማሽ ኪሎቶን ወይንም ቢበዛ አንድ ኪሎ ቶን ቢመዝን ነው። ማጆሮቭ፣ የሒልደር የድምጽ ሞገድ መልዕክት አንቴናውን ሲያላትቅለት ከማሊቡ ሆኖ ያፈነዳዋል። በሁሉም አቅጣጫ ከፍተኛ ኃይልን ይለቅቃል፣ ነገር ግን ከተቀመጠበት ድንጋያማ ወለል ይልቅ በሀይሉ የሚሸፈነው ውሀውና በዙሪያው ያለው አካባቢ በመሆኑ፣ አብዛኛው ሀይል የሚተላለፈው ወደላይና ወደጎን ይሆናል። በስቶኮልም በስተምስራቅ ያለው ባህር ወደላይ ይነሳል፣ ከሀይሉ አብዛኛውም ወደላይና ወደጎን ከፍተኛ መጠን ያለውን ውሀ በያቅጣጫው ይሰቃል። በሰሜንና በደቡብ ያሉት ደሴቶች የውሀ መዓበሉ ሙሉ ተጠቂዎች ይሆናሉ፣ ሌሎች ደሴቶች ዘንድ መድረሱም አይቀርም። በስተምዕራብ ያለችው ስቶኮልምም በማዕበሉ ትመታለች፣ ህንፃዎች መኪኖችንና ሰዎችን ከጠረገ በኋላ ውሀው ውቢቷን ከተማ አጥለቅልቋት ይቆያል። ቦንቡ በጣም ትልቅ አይሆንም። ማጆሮቭ ከዚህ ጥቃት በኋላ ጥቂት ከአደጋው የተረፉ ሰዎች ያሉባትን ከተማ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው አስልቶ ያደረገው ነው። ቦታውን ከተቆጣጠረ በኋላ አስፈላጊውን እድሳት አድርጎ ስራ ያስጀምራታል።

ከቦንቡ በስተምስራቅ የሚገኘው የድምፅ ሞገዱ የሚንገዘበትን ቦይ ተመለከተ። ከፍተኛ መጠን ያለው ውሀ እንደጥይት እየተወነጨፈ እዚህ ቦይ ውስጥ ይገባል። የሒልደር ሰርጓጅ መርከብ ፊት ለፊት ትጠበቀዋለች። ከቆመችበት እሸዋማ የባህር ጸርቻ ተሽቀንጥራ ገሀነም መግባቷ ነው።

ሒልደር በእጆቹ ግንባሩን አሰደግፎ ለማሰብ ሞከረ። ምናልባት እኮ ወረራው ያለችግር ተካሂዶ፣ 10301 የሚለው ቁርጥ ሳይደርሰው ሊቀር ይችላል። ምናልባት። ግን ከደረሰውስ? ምን ይፈጠራል? ሒልደር የድምፅ ሞገድ ምልክቱን የማይልክ ከሆነ፣ የፖለቲካ መኮንኑ ኮልቻክ እሱን ገድሎ ምልክቱን ይልካል።

ሒልደር ለማሰብ መሞከሩን ቀጠለ። አልቻለም። በፍርሀት ደንዝዟል።

ሩል ሻንጣዋን የመኪናው ኮፈን ውስጥ ወርውራ ወደቤቷ ተመልሳ ተፈተለከች። መዝነብ እየጀመረ ነው፣ መግቢያው ኮሪደር ላይ የተቀመጠ ታጣፊ የጃንጥላ ይዛ ወጣች። የስቶኮልምን አየር ማን ያውቃል?

ሁለቱን አጫጭር መንገዶች አቋርጣ ወደኤድ ራውልስ አነስተኛ አፓርትመንት አመራችና መኪናዋን መንገዱ ባሻገር አቁማ ሻንጣዋ ውስጥ የሚገኘን ወፍራም ፖስታ ይዛ ወጣች። ኤድ ራውልስ በሩን ሲከፍትላት፣ «ይሄውልህ አንድ ነገር ከተፈጠረ የሁሉም መረጃ ግልባጭ እዚህ ውስጥ አለልህ።» ብላ ሰጠችው።

«ኮፐንሀገን ልትሄጂ ነዋ ታዲያ?» ፈገግ አለ።

«አይደለም ወደስቶኮልም ነኝ ኤድ። በስዊድን የመከላከያ ሚኒስትር ውስጥ የቻንሰሪው ሀላፊ ከሆነ ካርልሰን ከተሰኘ ሰው ጋር በግል እንድገናኝ ሁኔታዎች ተመቻችተውልኛል። ነገ አገኘዋለሁ፣ ምንም ውዥንብር ውስጥ ላልገባ የምፈልገውን ማሳካት ብችል ደስ ይለኛል።»

ራውልስ ጥርጣሬ ገባው። «ይህ አደገኛ ነው፣ ኬት። ከአንድ የውጭ መንግሥት ጋር በቀጥታ እየተገናኘሽ ነው፣ ድርጅቱን ከዚህ በላይ የሚያስቆጣ ምንም ነገር የለም።»

«እሰ፣ ወደዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ መሔድ እችላለሁ፣ ይህ ሁለተኛ አማራጭ ነው። ይህን ማድረግ ስላልፈለግኩ ነው፣ ይህኛውን ዕድሌን የምሞክረው።»

«መልካም ልጂ፣ እዚያ ግን ብቻሽን ነው የምትሆኚው - ታውቂያለሽ ስቶኮልም ጣቢያችን እቅራቢያ ባትሔጂ ይሻልሻል።»

«እትጪነቅ፣ እነሱን እዚህ ውስጥ የማስገባት ሀሳብ የለኝም። ስቶኮልም ላይ ይህንን ካደረግኩ በኋላ፣ ኮፐንሀገን ላይ ከዊል ሊ ጋር እገኛለሁ። ከዚያ በሚቀጥለው ላምንት ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ሁሉ ከእረፍቴ እመለሳለሁ። ሌላ ምን ማድረግ እንደምችል አልታየኝም።»

ራውልስ በመስማማት ራሱን ወዘወዘ። «ትክክል ልትሆኚ ትችያለሽ። ያም ሆነ ይህ እዚህ ችግር እንዳይመጣብሽ እከታተልልሻለሁ። ደውይና የስቶኮልሙ ጉዳይ እንዴት እንደሆነ ንገሪኝ። ቢሮ ከደወልሽ እሁቱ ትሩዲ ነኝ በያቸው።»

«እሺ አዳምጠኝ። አይሮፕላን መሳፈር ይኖርብኛል። ደህና ሁን።» ጉንጩን ስማው ወደመኪናዋ ሮጠች። መኪናዋን አስነስታ ወደ አየር ማረፊያው ጉዞ ጀመረች። ዝናቡ አይሏል፣ መጨላለምም ጀመረ። የፊት መብራቶቿን አበራች። መብራት ሲያቆማት እንዳልጠፋችበት ለመመልከት ከአንድ መኪና በስተጀርባ አንገቱን ብቅ አድርጎ ሲመለከታት አየችው። ተናደደች በዚህ ሰዓት የሚከታተላት ሰው መኖሩን አልወደደችውም።

ሰዓቷን ተመለከተች። ወደኒውዮርክ በራ የስቶኮልምን አይሮፕላኗን ለመያዝ ከአንድሰዓት ያነሰ ጊዜ ነው ያላት። እንደሚከተላት ማወቋን ሳታሳውቅ ልትጠፋበት የሚያስችላት ጊዜ የላትም። ወደናሽናል አየር ማረፊያ ጉዞዋን ቀጠለች፣ ከአንድ ወይ ከሁለት መኪኖች ጀርባ እየሆነ ይከተላታል። ተበሳጨች።

አየር ማረፊያው ስትደርስ ታችኛው መኪና ማቆሚያ ውስጥ በፍጥነት ታጥፋ ገባችና አልፏት እስኪሄድ ከጠበቀችው በኋላ እሱ ካለበት ጥቂት

http://ethzare.wordpress.com

መኪኖች ርቀት ላይ መኪናዋን አቁማ ጃንጥላዋን ይዛ ወጣችና በፍጥነት መራመድ ጀመረች። ሊደርስባት ሲጣደፍ ይሰማታል ጋራጁ ውስጥ ማንም ያለም። ይህን ወዳዋለች። ትክክለኛ ቦታ ስትፈልግ ቆይታ አገኘች የማረፊያ ከፍሉቹን አልፋ አንድ ጥግ ላይ ተደብቃ ጠበቀች። ከኋላዋ ጥቂት ርምጃዎች ርቀት ላይ ነበረ። ጃንጥላውን በእጇ አጥብቃ ይዛ አነሳችው። ሲታጠፍ ከተጠ ቀለለበት ጨርቅ ጋር ያለው ብረት ጥሩ ክብደት ይሰጠዋል። የምትጠብቅበትን ስፍራ አልፎ ሄደና የተባረከ ሰው ቆመላት።

ሩል ከተደበቀችበት ወጥታ ኳንቲክ ውስጥ ሀቡዕ ግልጋሎት በምትማርበት ጊዜ እንዳስተማሯት አናቱ ላይ መታችው። ትንሿ ድምፅ አሰምቶ፣ ጉልበቶቹ ታጠፉና እግሯ ስር ዘፍ አለ። ዙሪያዋን ቶሎ ተመልከታ ስታበቃ ኮሊታውን ይዛ ትጎትተው ጀመር። የሴቶቹ መፀዳጃ ቤት ይሻላል የወንዶቹ? ማንም እንዳይኖር እየፀለየች የሴቶቹን መረጠች። በሩን ከፍታ ተመለከተች ማንም የለም። ወደአንዱ ሽንት ቤት ወስዳው ያለ የሌለ ኃይሏን ተጠቅማ መቀመጫው ላይ አወጣችውና ግድግዳውን አስደገፈችው።

በፍጥነት ኪሶቹን ፈተሸች። መጀመሪያ ሽጉጥ አገኘች። ተራ ሽጉጥ አይደለም። ሔችለርና ኮች የተባለ የማይዝግ ባለዘጠኝ ሚ.ሜ አውቶማቲክ ሲሆን፣ ሳይታወቅ አየር ማረፊያ ለመግባት ታስቦ የተሰራ ነው። በቀሚሷ የወገብ ላስቲክ ስር ሻጠቸው። የኪስ ቦርሳውን ስትፈልግ ቀበቶው ላይ የተንጠለጠለ ሰንሰለት አገኘች፣ እጁን ከኋላው ስባ አውጥታ ከሷንቧ ጋር አሰረችው። የመታችው ፖሊስ ይሆን እንዴ? ከዚያ ቦርሳውን አገኘችው። የቨርጂኒያ መንጃ ፈቃዱ ጀኔራል ማርቪን ቦነር ይላል። የሚኖረው አሌክሳንደሪያ ውስጥ ነው። አድራሻውን አገኘችው የFBI ልዩ ወኪል ጄ. ኤም ቦነር ይላል። ውይ እምላኪ ሌላ አድራሻ አገኘች። የቀድሞ የFBI አባል፣ የግል መርማሪ ይላል። በእርይታ ተነፈሰች። ግን ለምን? ወዘወዘችው።

«በል እንጂ ጂራልድ ተነስ መነጋገር አለብን፣» አለችው፣ ቦኒ ከአቆ ጥማ ለሀጩ ይዝረከረካል። ጉንጮቹን ቆነጠጠችው። «ተነስ - ተነስ ጌራ። አናግረኝ!» ቦነር ሚያው የሚል ድምፅ አሰማ። ሩል ወደኋላ ተንጠራርታ በጥፊ አቃጠለችው። «ተነስ አንተ ደደብ!» ጮኸችበት፣ «ሴቶች ክፍል ውስጥ ነህ!»

«የትኛው?» አለ ቦነር ነቅቶ። አይኖቹን ከፈተና ለማተኮር ሞከረ ሩል ደግማ አጮለችው።

አሁን እሷ ላይ ማተኮር ችሏል። «ምንድንነው. . . ?» አለ የግጹን።

«እየኝ ቦነር፣» አለችው። «ታውቀኛለህ?»

ሊንቀሳቀስ ሲሞክር እጁ በካቴና ታስሯል። ይህ ምንድን ነው ሴትዮ? ምን እያደረግሽ ነው? በሕየወቴ ከዚህ በፊት አይቼሽ አላውቅም።»

«ትግስቴ እያለቀ ነው፣ የማደርገው ይኸው ነው፣ መልስ እፈልጋለሁ።»

«ባህነም ግቢ የምነግርሽ የለኝም። ፖሊስ አሰማራብሻለሁ።»

ሩል ከወገቧ የራሱን ሽጉጥ መዘዘችና አፈሙዙን አንደኛው የእፍንጫው ቀዳዳ ውስጥ አስገብታ ራሱን ከግድግዳው ጋር አላተመችው። «ማን እንደሆንኩና የት እንደምሰራ ታውቃለህ፣ አይደለም? አሁኑኑ እዚህ ገድዬህ የድርጅቱን አንድ ቡድን አስመጥቼ ሬሳህን ማስነሳት እንደምችል ታውቃለህ። የደረስክበት ሳይታወቅ ትጠፋለህ።» ውሸቷን ነው ግን ምናልባት አያውቅ ይሆናል።

«እሺ እሺ፣» አለ የተደፈነ አፍንጫውን እያነፉነፈው። «ምንድን ነው የምትፈልጊው?»

«ባለፉት ሳምንታት እኔን እንድትከታተል የቀጠረህ ማን እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ፣» ሽጉጡን ወደአፍንጫው ገፋ አደረገችው።

«ዋይ!» አለ። «ተይኝ! እሱ ነው የቀጠረኝ። የቀድሞ ባለቤትሽ።»

«ምን?» ስትል ጮኸች። «ይህን ብትተው ይሻልህል አንተ ደደብ» ሽጉጡን የበለጠ ሰቀሰቀችበት።

እንደገና ጮኸ። «እውነቴን ነው እሱ ነው። አንድ ነገር ይፈልግብሻል። ልጅሽን መውሰድ ይፈልጋል!»

ሽጉጡን መግፋቷን ተወችው። ሳይመን ነዋ። ፒተርን ፈልጎት ሳይሆን መጥፎ ነገር እየፈለገባት ነው። ከድርጅቱ ሊያስወጣት የፈልጋል። «ምን ነግረሽዋል እስካሁን?» ጠየቀችው።

«ብዙም አልነገርኩትም። የሚነገርም የለብሽም። ስለወንድ ጓደኛሽ አውቋል።»

«ስልኬን የጠለፍከው አንተ ነህ?»

«እዎ። የሱንም እኔ ነኝ። ግን ብዙ ነገር አላገኘሁም። በትክክል አልሰሩልኝም።»

«እሺ ስለወንድ ጓደኛዬ አውቀሀል። ሌላስ ምንድን ነበር የምትፈልገው? ለምንድን ነው የምትከታተለኝ?»

«ፎቶግራፎችን ይፈልጋል።»

«የምን ፎቶግራፎች?»

«ያው አንቺና የወንድ ጓደኛሽ አልጋ ላይ ሆናችሁ።»

እሺ ቤቴን ገንጥለህ ልትገባ ነበራ? ግሩም ተጨዋች ነህ። ታዲያ ለምንድን ነው ፎቶግራፍ ያላነሳኸን?»

«እድሉን አላገኘሁም። ከዚያ ደግሞ ሰውየው ከከተማ ወጣ ሌላ ነገር ማግኘት ስላልቻልኩ አንቺን መከታተሉን ተጠልኩ። አንድ ነገር አገኛለሁ ብዬ አሰቤ ነበር።»

«ግሩም ሰው ነህ ቦነር። ከቪሮው ተባረህ መውጣትህን እወራረዳለሁ።» ፊቱን አዞረ።

«እሺ ደህና ሰንብት። ካፒቶል ሂል ላይ የራት ግብዣ አለብኝ።»

ቀና ብሎ ተቀመጠ። «ነይ ቆይኝ! የምትፈልጊውን ነገርኩሽ ፍቺኝ።» «ቀልቆ ኮት ኪስ በውስጥ በኩል አለልህ።»

«ውይ ስለክርስቶስ እባክሽን ፍቺኝ!» እያለ ይጮህል።

«መልካም እረፍት፣» ብላ መልሳ ጮኸችበት። «አንድ ሰው ይደርስልሀል። «ከግረፊያ ክፍሉ ወጥታ ቦርሳውን ቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ ወርውራው ሻንጣዋን ከመኪናዋ አውጥታ ወደተርሚናሉ አመራች። ከአስር ደቂቃ በኋላ ወደሳንፍራንሲስኮ የሚበር አይሮፕላን አገኘች። ከዚያም ወደሀዝብ ስልክ በመሄድ ለቨርጂኒያ የአውራጎዳና አሳሽ ቡድን ደወለች። «ሀሎ፣» አለች ስልኩን ሳነሳው ፖሊስ። «ቦኔ የሳንፍራንሲስኮ ፖሊስ መረማሪ ሰርጀንት ብሩኪ ኪርክላንድ ነኝ። ናሽናል አየር ማረፊያ ውስጥ ነኝ፣ የሴቶች መፀዳጃ ክፍል ገብቼ ሳለሁ አንድ ሰው ዘሎ ወጥቶ ሊደፍረኝ ሞክሯል። እንደምንም ላሸንፈው በቅቼያለሁ፣ ከሽንት ቤቱ ሷንቧ ጋር አስሬዋለሁ። በአስር ደቂቃ ውስጥ

http://ethzare.wordpress.com

አይሮፕላን መሳፈር አለብኝ፣ ስለዚህ አሁን መቆየት አልችልም፣ ነገ ስራ እንደጣሁ ቃሌን በቴሌክስ እልክላችኋለሁ እሺ? ካቴናውን በፖስታ ልትልኩልኝ ትችላላችሁ። «የተደናገጠው ፖሊስ መልስ ሊሰጣት ከመቻሉ በፊት ስልኩን ዘጋችው።

ከዚያ ሽጉጡ ትዝ አሳት። ዙሪያዋን ተመልከታ የጃኪቷን ቁልፎች ከፈተችና ከበስተጀርባዋ አስገባችው። ምን ይታወቃል። ደወሉቹ ሳያንቃጭሉባት ደህንነትን አልፋ ወደ አይሮፕላኗ ሮጠች።

ከሁለት ሰዓታት በኋላ ከኬኒዲ አየር ማረፊያ ወደስቶኮልም በረራ ላይ ተሳፈረች። ዘና ለማለት አንድ መጠጥ ወሰደች፣ ከእራት ጋር ደግሞ ሁለት ብርጭቆ የወይንጠጅ ጠጣች፣ ብራንዲ አስከተለችበት። ፊልሙ ሲጀምር እንቅልፍ ይዟት ሄደ።

47

ሔልደር ለጥቃት መሰንዘሪያነት የሚጠቀምበትን ፔርስኮፕ ይዞ እንዳለ ሌላኛው ጥግ ጋ ሲደርስ መያዣውን ለቀቀው። ልክ ይህን ጊዜ በዕይታው የገባለት እንደየፈላ ውሃ ይመስል የሚርመሰመስ ባሕር ነበረ። «እሰኪ ፍጥነቱን በአንድ የፍጥነት መለኪያኖት ያህል ቀንሱት።» የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈ።

«ፍጥነት በአንድ የፍጥነት መለኪያ ያህል ተቀንሷል፣» ሲል ሁለተኛው አፈሰር ምላሹን እንደ እሱ እየጮኸ አስተላለፈለት።

ሔልደር በፔርስኮፑ ሲመለከት ጀልባዋ ወደ ፊት እየተጓዘች ሲሆን ውሀውም ከቅድሙ ጋር ሲነፃፀር ለስለስ እያለ መጥቷል። ፔርስኮፑን በፍጥነት ወደ ቀኝ ወደ ግራ እያሂሂረ ሲመለከት ጠበብ ካለው መተላለፊያ ወጥተው ግልፅ ወደሆነው ባሕር ገብተዋል። ከበስተቀኙ በኩል ትንሽ ብቻ ራቅ ብሎ አንድ ደሴት አለ፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ ሌላ ደሴት ማለትም እንደርስበታለን ብለው ያቀዱት ቦታ ነበረ። «አሁን ፍጥነቱን በሁለት ኖት ያህል ጨምሩት፣» ሲል ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን ትዕዛዙም ወዲያው ተፈፃሚነት አገኘ። ጀልባዋን በድጋሚ ሲደርሱባት እርምጃ ለማስተካከል ሲባል አሁንም ኖቱን ቀነሱ።

ከሀያ ደቂቃዎች በኋላ ሔልደር ፔርስኮፑን መጠቀም ሳያስፈልገው እንኳ እዚያ መድረሳቸውን አወቀ። ለተጨማሪ አሥር ደቂቃዎች ጉዞ ቀጠለ። ሔልድር ይህን ግዜ እድማሱን በፔሬስኮፑ ቃኘት ቃኘት አደረገ። በዚህ ግና ከሚቱ አንድ ሰዓት ከምናምን በሆነው ብራ ፀሐይ ቀን ምንም በእይታ የሚገባ መርከብ የለም። ይህንን ጉዞ የሚያደርጉት በዓመቱ ውስጥ በእርዝመቱ ወደር በሌለው የክረምቱ ወቅት ካለው ቀን በነጋታው ነበረ። አዎን በትናንትናው ምሽት በስካንዲኒቪያ ለጉድ ነው ሲጠጣ ሲጨፈር የተመሸው። ጠጪዎቹ የቱን ያህል በደስታ እንደተኙ ጤናማ እንቅልፍ እንዳገኙም ፈፅሞ አይጠየቅም። «ከቀኝ በኩል ያለውን መቅዘፊያ ጠንክር አድርጋችሁ ተጠቀሙ፣» በማለት ትዕዛዝ ሲሰጥ እነስተኛው ሰርጓጅ መርከብ አቅጣጫውን በመቀየር ዞረ። «ይኼን አቅጣጫ ተከተል፣» አለ ልክ ያኛው ደሴት በእይታ ሲገባ። «ላይ ላዩን ለመሄድ ተዘጋጅ፣» አለና «ላይ ላዩን ሂድ»

ሔልደር በጥልቀት ያለውን ድምፅ መስጫ ተመለከተ። ከቂጡ ጋር ያለው ክፍል ወደላይ እየተነሳ መሆኑን አስተዋለ። ፔርስኮፑን በመተው መንሰላሉ ላይ ተንጠላጥሎ ከዋናው የዕቃ መጫኛ እና ማስገቢያ በር ስር ባለ

ቦታ ላይ ደረሰ። ትንሹ ሰርጓጅ መርከብ ባሕሩን ሰንጥቆ እንዳለፈ የግፊት መቆጣጠሪያ ማዘጎጦውን ሲጠመዝዘው ያ የዕቃ ማስገቢያ ክፍሉ በር ተበረገደና ውሀ ተደፋበት። እሱ ላይ ብቻም ሳይሆን ከርሱ ቀጥሎ ወዲያውኑ በነበረው ኮላክ ላይም ነበረ ውሀ የተደፋው። ሔልደር ቀሪዎቹን የመንሰላሉን መወጣጫዎች በመውጣት ላይ ወዳለው ክፍል አመራ።

ያለበትን አቅጣጫም በፍጥነት አረጋገጠ። አሁን ደሴቱና ጸርቻው በጣም ቅርብ ሆኖ ነው የሚታዩት። ከዚያም በዚሁ ላይ ባለው ክፍል ውስጥ የሚገኘውን «ወደፊት አድርግ!» ሲል ጮኸ ትዕዛዝ ሰጠ። እንድ ቀጠን ያለ ድምፅም የሰጠው ትዕዛዝ መፈፀሙን አረጋገጠ። ሔልድር በመቀጠል ኮልቻን ወይም የፖለቲካ ጉዳዮች አማካሪውን ተመለከተ። ይህ አማካሪው ዓይኖቹን በግርምት ብልጥጥ አድርጎ ፊት ፊቱን ይመለከት ነበረ። አሁን ደሴቱ ወደ እነሱ በፍጥነት እየመጣ ነው፣ ጀልባዋም ፍጥነቷን ጨምራለች። በዚህ በሳይኛው የውሀ ክፍል ላይ እስከ 18 ኖት ድረስ መጓዝ ትችላለች ይሁን እንጂ ግረፍ እስከሚችሉበት ድረስ ያህል ያህል ርቀት መሸፈን የሚያስችል ፍጥነት ሊኖራቸው አይችልም። ሔልደር ወደ ሳጥኑ ተጠግቶ ጮኸ። «ሁላችሁም ወደ መጋጠሚያው!»

ፊቱ ያለውን መስመር ያዘና ትከሻውን ጠንክር አድርጎ የመርከቡ መከፋፈያ ግድግዳ ላይ አስደገፈው። ግን ሳቁን ሊቆጣጠር አልቻለም፣ ኮልቻክ ወደዚያ ወደላይኛው ክፍል ሳይወድ በግዱ በግፊት ተወርውሮ የደረሰ ሲሆን እሱም ግድግዳ ተደግፏል፣ ለነገሩ ችግር የለም፣ ማየት አይደል የፈለገው? እስከ አሁን በመርከበኝነት ሙያው አነስተኛ መርከቦችን ወደ ጸርቻ ከማምጣቱ መሸሸን የመረጠ ሲሆን አሁን ደግሞ ይህ ሲሆን ማየት ቢፈልግ አያስገርምም። መርከቧ ብዙም ጥልቀት ወደሌለው የባሕሩ ክፍል ላይ ስትደርስና ፍጥነቷን ወዲያው በመጨመር እመር ስትል አንድ ጹብ የማለት ድምፅ ተሰማ። ከዚያም መርከቧ አሸዋ ያዛትና ጋደድ ጋደድ ብላ ፍጥነት ቀንሳ ታገለች። ሔልደር ጥርሱን ነክሶ ከዚህም የከፋ ተፅዕኖ ይመጣል ብሎ ጠበቀ ግን ሳይመጣ ቀረ። ትንሿ መርከብ ወደፊት እመር ማለቷን ቀጠለችና ታች ካለው አሸዋ ጋር ደበልጥ አካሏ ተሻሽቶ አንዴ የጩኸት ድምጽ አሰምታ ቆመች። ይህን ግዜ የመንጋደድ አካሄድ ነበረና ሔልደርም ሳይወድ በግዱ በግፊት ወደፊት ተወርውሮ ልክ መርከቧ ሙሉ በሙሉ ስተቆም ደግሞ ወደ ኋላ ተወረወረ። አገገመና ሳጥኑን ያዘው። «ሞተሩን አጥፉ!» ሲል አሁንም በጩኸት ትዕዛዝ አስተላለፈ።

ልክ ይህን ግዘ ሁሉም ነገር ፀጥ ረጭ አለ። በላይኛው ክፍል ፍፁም ሰላም ነበረ። ኮልቻክ እንደምንም ታግሎ ተነሳና ሔልድር አጠገብ ቆመ። ሁለተኛው እና ሶስተኛው አፈሰሮች ፈቃድ በመጠየቅ ወደዚህ ወደላይኛው ክፍል መጡ። ሔልደር ዙሪያውን ሲመለከት ከጸርቻው በታች ሩብ ግይል ርቀት ያህል የሚሆን ቦታ ላይ አንድ የሆነ ቤት መኖሩን ነገር ግን ምንም ሰው ለመኖሩ የሚያመለክት ነገር እንደሌላ አስተዋለ። ከዚያም በመቀጠል ሲመለከት አንድ 30 ሜማ ያህል ርዝመት አለው ተብሎ የሚገመተው የሽርሽር ጀልባ ከደሴቱ ምዕራብዊ ጸርቻ እያቋረጠ ይመጣል። ይህም ግይል ያህል ርቀት ላይ ነበረ። ሔልደር ማጉሊያ መነፅሩን አነሳው እና ተመለከተ። የጀልባው ዘዋሪ ከታች ላለው ማንም ሆነማን አንድ የሆነ ነገር በጩኸት እየተናገረ ነው። አንድ

http://ethzare.wordpress.com

ወጣት ወንድ እና ሴት ወደ ጋቢናው ቁልቁል ተመለከቱ ከዚያም የዘዋሬን የእጅ ጥቆማ ሲከተሉና ሲየዩ ከባሕር ወጥቶ መመለስ ያልቻለውን ጀልባቸውን ተመልከተው ደርቀው ቀሩ። ከዚያም ወንድየው ወደኋላ ወደባሕሩ ዘሎ ገባ።

ሔልደር የሩቅ ማሳያ መነፅሩን ጥብቅ አድርጎ ተመለከተ። ከመርከቡ ምሰሶ ላይ የVHF አንቴና ታየው። አምን ከዚህ በኋላ አይቆይም። ከዚያ በመቀጠል ሔልደር ወደ ቤቱ ተመለከተ። አንድ ሰው ከዚያ አቅጣጫ በዳርቻው ላይ በእግሩ እየመጣ ሲሆን እሱም ፒጃማ እና ጋውን ነገር ለብሷል። እሱ ካለበት ከሀምላ ከንድ ርቀት ላይ በማይበልጥ ቦታ የውሃው ጫፍ ላይ ቆመና እጁንም በማጎድጎድ በስዊድንኛ ቋንቋ፣ «እንደምን አደርክ?» አለ።

ሔልደር ከሶስተኛው አፈሰር ላይ አጉልቶ የሚናገርበትን ሚጋርን ወሰደ። «እንደምን አደርክ፣» ሲል እሱም መልሶ ተጣራ። ይህስ አስቂኝ ነው።

«ለመሆኑ እርዳታ ያስፈልግሀል እንዴ? ሲል ሰውየው ጮኸ ጠየቀ። «የሆነ ሰው ልጥራልህ?»

ይቺን ይወዳል የሰውየው ልጅ! «ኧረ አያስፈልገኝም፣» ሲል ሔልደር መለሰለት። «ወደ ቤትህ ብትመለስ የተሻለ ይሆናል። ከዚህ በኋላ በርካታ ሌሎች ጀልባዎች ይመጣሉ፣»

ሰውየው ባለበት ቆሞ ሲያይ ቆየና ራሱን በእምንታ ነቅንቆ ወደ ቤቱ መመለስ ጀመረ።

ሔልደር ወደ ሳጥኑ ተጠጋ። «ስፓርክስ፣ አለህ እንዴ?» ሲል ተጣራ።

«አቤት ጌታዬ የሚል ድምፅ መጣ።»

«ዓሣ ነባሪ ላክ!»

48

ሩል ስቶኮልም ከተማ ደርሣ ከአይሮፕላን ስትወርድ ይደካከማትና ያለአስፈላጊ ድብርት ስሜት ይሰማት ነበረ። እዚያ የደንህነት ማረጋገጫ ቢሮው ጋ ሰልፍ ይዛ ሳለ ከአንዲት ቁመተ ለግላጋ፣ ዕድሜዋ 45 ገደማ የሚገመት፣ ቀጭን፣ ስትስቅ በጣም አለቅጥ ድምፀ የሚረብሽ ሴት ጓላ ነበረች። ይህች ሴትም ከአንድ የኢሚግሬሽን ሠራተኛ ጋር አጉል ትሞዳሞድ ነበረ።

ሻንጣዋ ፈጠን ብሎ መጣሳትና በመውጫው ወደ ጉምሩክ ስታመራ አሁንም ከዚህች አሜሪካዊት ሴት ጓላ ነበረች። ከዚያም ልክ ዥው ዥው በሚሉ በሮች አልፋ ወደተርሚናሉ እንደደረሰች ቆመች። ይህን ግዜም ድንገተኛ ፍርሀት በውስጧ አደረ። ከፊት ለፊቷ የተወሰኑ ከንዶች ራቅ ብሎ አንድ ጠቆር ያለ ሱፍ የለበሰ እና የሾፈር ዓይነት ባርኔጣ ያደረገ ሰው በእጅ የተፃፈ ወረቀት ከፍ አድርጎ በመያዝ እያሳያት ነበረ። በወረቀቱ ላይ ተፅፈው የሚታዩት ሁለት ቃላት ኪርኪላንድ እና ሩል የሚሉ ናቸው።

ካርልሰን መኪና ልኮላት ቢሆን ኖሮ በአንድ የአሜሪካ ሴናተር ትውውቅ ስለተደረገላት ያን ያህል ባላስደነቃት ነበረ። ግን ላለፉት አምሥት ዓመታት ያውቀው የነበረው ስም ኪርክላንድ የሚለው ነው። ሴናተር ካር በስልክ ከነገረው በመነሳት እውነተኛ ስሟን ባላወቀ ነበረ። በስዊድን ውስጥ እውነት ለመናገር ማንም ቢሆን ሩል የምትባል ሴት እንደምትመጣ አያውቅም።

በዚያ ላይ ስዊድን ይህ ስም የተለመደ አይደለም። የይለፍ ወረቀቷ እና ትኬቷ ላይ የነበረው ስም ካላዌይ ሲሆን ይህም የግርድና ስሟ ነበረ። እናም ጋብቻ ከፈፀመች በኋላ አዲስ የይለፍ ወረቀት ለማውጣት አስባም አታውቅ።

ሩልን በማም ባስገረማት ሁኔታ ያቺ ቀውላላ አሜሪካዊት ሴት ቀጥ ብላ ወደ ሾፌሩ በመሄድ ድምጿን ከፍበማድረግ፣ «ታዲያስ እንዴት ነህ? ስሜ ኤልያኖር ኪርክላንድ ይባላል። እኔን ነው አይደለም የምትፈልገው? ስትለው ሰውየው ራሱን በአምንታ ነቀንቀና ሻንጣዋን ተቀበላት። ሩል እዚያው ባለችበት በአግራሞት ወደሆነ ጥግ እስኪሰወሩ ድረስ ተመለከተቻቸው። አሁንም ግራ እንደገባት እዚያ ኦሜሪካ ሳለች ብዙም ግዜ ሳታገኝለት የቀረችውን ዶላርን በዚህ እገር ገንዘብ ማለትም ክሮነር የመዘርዘር አገልግሎት ለማግኘት ወደ አንድ መስኮት ጠጋ አለች። ነገር ግን ልክ የገንዘብ ምንዛሬውን እንደጨረሰች እንድ ለጆሮ ፍፁም የሚሰቀጥጥ ጩኸት ከተርሚናሉ አካባቢ ሰማች።

ሩል ከብር ቦርሣዋ ዓይኗን ባማንሳት በፍጥነት ስትመለከት እንዲት አጭር ደንደን ያለች ሴትዮ ከኮሪደሩ ፈንጠር ብላ ቆማ ያየች ሲሆን ይህም ሴትዮዋ ብርክ የያዛት መሆኑን ያሳያል። ምን ተፈጥሮ ይሆን? ሴትየዋ በስዊድንኛ ቋንቋ በጩኸት የሆነ ነገር እየተናገረች ሲሆን ከዚያው በተጓዳኝም ጥግ ላይ የሆነ ነገር ጠቁማ ለማሳየትም ትሞክር ነበረ። ሩልም ወሬውን ለማየት ልክ እንድ እሷ ጓጉተው ከነበሩ ሌሎች የተወሰኑ ሰዎች ጋር ተሻምታ ሴትዮዋን ወደ ቆመችበት ተመለከተች። እዚያ ጥግ ቦታ ላይም ለጥገና የሚጠቀሙበት ክፍል ተከፍቷል። ውስጡም ወለሉ ላይ ቢቃላት ለመግለፅ የሚያስችግር የነርፍ ያህል የበዛ ደም የሚታይ ሲሆን እንዲት አሜሪካዊት ጉሮሮዋ በስለት ከፉኛ ተሰርስሮ ተዘርራለች። ጉድ! ጉድ!!!!!

ሩል ተሰብስቦ ይመለከት በነበረው ሕዝብ መሀል ወደኋላዋ በማፈግፈግ ርቃ ሄደችና ውጭ ወጥታ ታክሲ መጠበቂያው ጋ ቆመች። ባየችው ቀፋፊና ፍፁም አስደንጋጭ ነገር ውስጧ ተብከንክኗል እየተፈታተናት ስለነበረ ላለመሮህ የተቻላትን ያህል ጥረት አደረገች። ለሁለት ደቂቃ ያህል ታክሲ ስትጠብቅ ለመረጋጋት ሞከረችና ልክ ታክሲው ሲመጣም፣ «ግራንድ ሆቴል?» ብላ ጠይቃ ገባች።

ታክሲው ጉዞውን ቀጠለ። ወይ መከራ! «እንግሊዛዊ ነሽ እንዴ፣ እመቤት?» የሚል ጥያቄ ጨዋታ ጀመረ ፊቱ ላይ የተጫዋችነትና አግባቢነት መንፈስ የሚነበብበት ሾፈሩ። ልክ ራሷን ቀና አድርጋ በፈት መስታወቱ ስትመለከት ፊቱን አየችው። ይህ ሾፈር በዕድሜ ወጣት፣ ፈዘዝ ያለ ቢጫ ፀጉር ያለው ብቻ ባጠቃላይ እንደ እሷ ያሉ አሜሪካውያን በሙሉ ከአንድ ስዊድናዊ በመልክና በሁለመና የሚጠብቁትን የያዘ ልጅ ነው።

«እምን፣» ስትል መለሰች፣ «እንግሊዛዊ ነኝ»

«እና ግራንድ ሆቴል ነው ያረፍሽው?» ጥያቄው በቀላሉ የሚቆም አይመስልም።

«አይ አይደለም፣» አለች። «እዚያ የማገኛቸው ጓደኞች ኖረውኝ ነው። ወደ ገጠር ወጣ ብለን አብረን ከእነሱ ጋር እንቆያለን ብዬነው»

«የት?» አለ። ሰው በገዛ እጁ ሲያቀብጣት ዋሽታ ልትጋለጥ? «እኔም እኮ ከገጠርማው ከፍል ነው የመጣሁት»

http://ethzare.wordpress.com

እንደምንም ብላ የስዊድን ገጠር ስም ፈለገች ከየት ይምጣ? ምንም አላገኘችም። «ስሙ ጠፋኝ ባክህ፣» አለች። ታዲያ አይሞት ነገር «የስዊድን ስሞች ይዋርማሉ፣ አይያዙልኝም። ለመሆኑ ከዚህ እስከ ግራንድ ሆቴል ምን ያህል ይመስድብናል?»

«እንግዲህ ከዚህ በኋላ ወይ 35 አሊያም 40 ያህልደቂቃ ይፈጃል መሰል፣» አለ።

ኤሞ ራሷን በወንበሩ ላይ ወደ ኋላ ደገፍ አድርጋ ዓይኖጀን ጨፈነች። በጥያቄዋ ጠቆም ያደረገችው ነገር ሾፈሩን ላይገባው አልቀረም። በጉዞው ወቅት ከከተማዋ ትንሽ ክፍል ብቻ ነው ያየችው። እንዴት ሊሆን ይችላል? በጣም ፈራች፣ ተደናገጠችም ግን ታክሲው በድንገት ቀጥ ብሎ እስኪቆም ድረስ ስለ አካባቢዋ ብዙም አላሰበችም ነገር። «ምንድንነው እንተ? አለች በድንገት ቀና በማለት።

«እንዴት ምንድን ነው? ይኸው ግራንድ ሆቴል ደረስሽ»

ልክ የታክሲው በር ሲከፈት የመዝለል ያህል ነበረ ተፈናጥራ የወጣችው። አንድ ዩኒፎርም የለበሰ ዘብ ቆሟል። ከዚህ ዘብ ጓላም ትዕግስታቸው የተሟጠጠ የሚመስል አንድ ወንድና ሴት ቆመው ይጠብቃሉ። ለሾፈሩ ሂሳብ ከፍላ ወጣች። አንድ ዕቃ አውራጅና ተሽካሚ ጩሌም ተቀበሏት ወደ እንግዳመቀበያው አጀባት።

«ስሜ ካትሪን ሩል ይባላል፣» አለች ለእንግዳ ተቀባይ ዲስክ ተረኛው። «እዚህ አንድ ክፍል ቀደም ሲል ተይዞልኛል»

ፊት ለፊቱ ያለውን ሩይል አገላበጠ. . . ተረኛ እንግዳ ተቀባዩ። «እውን ልክ ኖት ወ/ሮ ሩል ክፍል ተይዞልዎታል። የይለፍ ወረቀትዎን ቢያሳዩኝ?»

ሰጠችውና ስለ ስሟ ጉዳይ ግን አብራራችለት። «ለመሆኑ ስልክ ተደውሉልኝ ይሆን እንዲ?» ክፍሉን የያዘችው ሩል በሚል ስም ነበረ። ምነው ማንም ባልደወለ እያለች በልቧ ትመኝ ነበረ።

«አዎን፣» አለ እንግዳተቀባዩ። አዬ አንድ የተጣጠፈ ወረቀት እወጣ። ግን ይሆን? ከኮፐንሀገን ሚ/ር ሊይ የሚባ፡. ሰው ደውሉልዎታል። በኋላ እደውሳለሁም ብለዋል።

«እግዜር ይስጥልኝ፣ አመሰግናለሁ፣» አለች እፎይታ እየተሰማት። «ከዚህ በኋላ ማንም ቢደውል ለኦፐሬተሩ ኮልዌይ እያልክ ብታገናኝኝ በጣም ነው ደስ የሚለኝ። እዚህ ያሉ ጓደኞቼ በዚያ ስም ነው የሚያውቁኝ።»

«እሺ፣ ምንም ችግር የለውም፣» አለ ሰውየው የሆነ ኖት እየሞነጫጨረ።

«ግን ያ ብቻም ሳይሆን መቼም እንዲ ጀምሬያለሁ ሳስቸግርህና ማንም ደውሎ ካትሪን ሩል አለች ወይ ቢል በዚህ ስም እዚህ የተመዘገበ የለም ትልልኝ?»

ሰውየው ለእፍታ ያህል አፍጥጦ ተመለከታትና አሁንም ሞንጫር አደረገ። «እርስዎ ከፈለጉ እኛ ለማንም እንግዳ የምናደርገው ነውና ፍላጎትዎን እጠብቃለሁ። በማለት ቁልፉን ሰጣት። «አልጋ የተያዘልዎት መጨረሻው ፎቅ ላይ ሲሆን ባሕሩን ወለል አድርጎ የሚያሳይ ክፍልም ነው ያሉብት፣» አለ። በመቀጠልም፣ «ግን አዝናለሁ ወ/ሮ ሩል ባሁኑ ሰዓት ከለርክ አጠገቤ ባለመኖሩ

የሚሸኝዎት አይኖርም። በጣም ይቅርታ ግን በአሳንሰር ይሂዱና ልክ እንደወረዱ በስተቀኝ የተወሰኑ ክፍሎች እንዳለፉ ክፍልዎን ያገኛሉ። ለሻንጣዎ አይጨነቁ ዕቃ ተሸካሚ ይዞሎት እንዲመጣ አልከዋለሁ፣»

«ጣጣ የለውም አረ፣ በጣም አመሰግናለሁ» አለች። ከዚያም ወደሊፍቱ ሄደች። ልክ በሩ ሲከፈትላትም ገባች። እንዱ ገና ከጓላዋ ቆመ ልክ ያኔም በሩ ተዘጋ። በቁመት ይረዝማታል የመንጋጋው ጡንቻ ተለት ያለ ሲሆን በዚያ ላይ ሰውነቱም የጸበረ እና ፊርማማ ነው። አያትና በስዊድንኛ የሆነ ነገር ሲላት ከብድ ባለው ዓይነት ፈገግ ብላ ችላ አለችው።

«ይቅርታ፣» አለ በእንግሊዝኛ። «አሜሪካዊት ነሽ?» ወይ ዛሬ ምን ዕዳ መግባት ነው? ዓይኖቹ ከብድ የሚሉ እንዲሁም ቀዝቃዛነትን የሚያንፀባርቁ ናቸው።

«የለም እንግሊዛዊት ነኝ፣» አለችና ሊፍቱ ወደየትኛው ፎቅ እንደደረሰ የሚያሳየውና ቀስ ብሎ የሚቀያየረውን መብራት አተኩራ ማየት ያዘች።

«እንኳን በደህና ወደ ስዊድን መጣሽ፣» አለ በትንሹ ፈገግታ አሳይቶ።

ኧረ ምናለ ይኼ ነገር በፍጥነት በተንቀሳቀሰና በደረስኩ ስትል ተመኘች። የማነው ሞዛዛ? ልክ ጀርባዋን እንደምታክ አድርጋ እጇን ወደኋላ አደረገች። ያኔም እጇ የሽጉጧ መያዣ ላይ አረፈ። «አመሰግናለሁ፣» አለች። ልክ ይሄኔም ሊፈቱ ቆሞ በሩ ተከፈተ። ኡፎይ!!!!!!

«ግድ የለም ቅደሚ፣» አለ ሰውየው እሷን እንደመጋበዝ እያለ።

ፈጠን ብላ በመውጣት ቀኟን ይዛ ስትሄድ በቆረጣ በትክሻዋ ላይ የኋሊት ወይ ወደ ጎን ለመመልከት ትሞክር ነበረ። ሰውየው ቀኙን ይዞ ሄዷል።

ልቧ ድው ድው እያለ በኮሪደሩ ወርዳ ክፍሏን መፈለግ ያዘች። ወደ እንድ ትንሽ ልብስ መቀየሪያ ክፍል የሚመስል የሚያስገባውን በር ከፈተች፣ እንድ ሴሳ በር ደግሞ ባለ ሶስት ሶፉ ያለው እንግዳ መቀበያ ክፍል ያስገባል። እሷ ግን እንግዳ መቀበያ ይያዝልኝ ብላ አልጠየቀችም ነበረ። ወዲያውኑም ለስለስ ያለ የወንድ ድምፅ ሰማች። ቋንቋውን ለመለየት አልቻለችም። ቁጥሩን ከቁልፏ ቁጥር ጋር አስተያየችው። ወይኔ ጉድ፣ ተመሳሳይ ነው! ክፍሏ ውስጥ ሰው አለ ማለት ነው።

ሩል ሽጉጡን ይዛ በግንጣጠር ትንፋሽ ወደ ውስጥ ውጣ በሩን ዘለቀች። ሽጉጡን ልክ ስልጠና በወሰደችበት ግዜ እንደተግረችው በሁለቱም እጇ ነበረ የያዘችው። ሁለት ወንዶች ቁጭ ብለው ቁርስ እያደረጉ ነበረ። ምን?

«ኪይት?» ሲል እንዱ ጠራት። «እንዴ! በስመ-አብ ወልድ ወ መንፈስ ቅዱስ ምነው?»

«እንዴ፣ ሊ፣» ስትል ሮሃ ተናገረች። «አፒቼላ» ይበልጥ እየሙዝቶ ነው።

«በይ ራስሽን አረጋጊ፣» ሲል አፒቼላ ትዕዛዝ ሰጣት። «ብይ ያንን የያዝሽውን ነገር ጣይው። አሁኑኑ!»

http://ethzare.wordpress.com

ሔልደር ሰዓቱን ከዚያም ደግሞ ወዲያው አጠገቡ ወለል ብሎ ያለውን ባሕርም ተመለከተ። መለስተኛ መርከቡን ወደ ዳርቻ እምጥቶ ካሳረፈው 45 ደቂቃ ያህል አልፏል። ይሁን እንጂ ያቺን የሽርሽር ጀልባ ካየበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ምንም ዓይኑ የገባ መርከብ የለም። ወደ ባለስልጣኑ ተመለሰ፣ «እሱኪ ልውረድና ቡና ቱት ልበል፣» አለው። የመጀመሪያው የባሕር ኃይል መርከብ ሲመጣ ጥራኝ፣»

የፖለቲካ ጉዳዮች ኦፊሰር የሆነው ኮልቻክ አቶን በአድናቆት ከፍቶ ይመለከተው ነበረ። «እንዲህ ባለው ግዜ እንዴት ወደ ታች ትወርዳለህ? ይኼ እኮ ኃላፊነትን መክዳት እና መተው ነው»

«አቦ በናትህ ዝም በል ኮልቻክ፣» አለው ሔልደር ድከም እያለው። «ይኼ አላዛኝ አፍህን ሳትከፍት ሥራን መሥራት አትችል እንደሆነ ለራስህ ለማረጋገጥ ሞክር እስኪ፣»

ኮልቻክ ሲታይ ሊፈነዳ የደረሰ ይመስላል። ሔልደር ግን ቢፈነዳም ጉዳዩ የሆነ አይመስልም። ግን ምን እሱ ብቻ ሌሎቹ ኦፊሰሮችም ካሳዩት የፈዝ ዓይነት አባዜ አንሱም ቢፈነዳ ምንም እንደማይመስላቸው ገባው። ሔልደር ከዚህ በኋላ መሰላሉን በመውረድ የናቪጌሽን ኦፊሰሩን ከመቀመጫው እንዲነሳ ምልክት በመስጠት ወደ ቻርቱ አመልካች በመሄድ ቁጭ አለ። ቡናው ደረሰና መጣለት።

ሔልደር ፊትለፊቱ ያለውን ቻርት ተመለከተው። በባሕር ውስጥ ወዳለው መሬት ሁለት ግዜ ለማወቅ ከመፈለግ ካደረገው ጉዞ ውጭ ግን ስለ ግዛቱ ያን ያህል አስበበት ወይ ተጨንቆበት አያውቅም። አሁን ደግሞ በጣቱ በደሴቶቹ መሀከል ከተሞቹን አሰመለከተ። እንግዲህ ሰቶከሆልም በጣም ትልቅ ከተማ ሲሆን ስቶክሆልም በጣም ትልቅ ከተማ ናት የሚል ስሜት አደረበት። ነገር ግን ከከተማዋ ትልቅነትም በላይ እዚህ ጎላ ብለው ይታዩ የነበሩ ሌሎች እነሱ ያሉ ከተሞች፣ መንደሮች እንዲሁም ትናንሽ ሰፈሮችም አሉ። ቻርቱ ይህን ብቻም ሳይሆን ቤቶችንም አንድ ባንድ ያሳይ ነበረ። ቤቶቹ ምቹ ናቸው፣ በፔርስኮፕ ያያቸው ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ እንዱ ትንሹ መርከብ ካረፈበት ቦታ ሩብ ያህል ማይል ብቻ ርቆ ነው የሚገኘው። አንድ ሰዓት ከማይሞላ ግዜ በፊት አጠር ባለ ነገር ግን ኮሚክ በሚባል ሁኔታ ከባለቤቱ ጋር ይህንን አንስቶ ተነጋግሮ ነበር። እነዚህ ሰዎች እሱን ምን እዚህ እንዳመጣው የሚያውቁት ነገር የለም። በዚህ ትንሽ መርከብ ውስጥ ያሉ በደረት የሚሳቡ ፍጡራንን የሚመስለው ኮልቻክም ቢሆን ለምን እሱ ወዲህ እንደመጣ አያውቁም። ኮልቻ የገባው ነገር ቢኖር ትዕዛዝ እንደሚቀበል ሌላ ትዕዛዝም ደግሞ እንደሚሰጥ ነበረ። ሔልደር ግን ከዚህ በጣም የጠለቀ እውቀት ነው የነበረው።

ይህ ወረራ በስዊድናውያኑ ላይ ስለሚያመጣው መዘዝ ሆነ ብሎ ላለማሰብ ይሞክር ነበረ። ከዚያ በተጨማሪም ግን ወረራው ለርሱ በግል በሚያጎናፅፈው ጥቅም ማለትም በዚህ ወረራ ውስጥ ስላለው ሚና፣ በዚህም የቴን ያህል ሹመት እንደሚያገኝ፣ እዚህ ሲመጣ ያየው ምኞት፣ ወደፊት በስራው ላይ ስለሚያገኘው ዕድገት ወዘተ በማሰብ ተጠምዷል። ሆኖም የሚያሳዝነው እነዚህ ስዊድናውያን ብዙም ሳይቆይ ልክ እንደ ቼኮች፣ ፖላንዶችና ኢስቶንያውያኖች ዕጣ የሚደርሣቸው መሆኑ ነው። የርሱ ቤተሰቦች ሶሻሊስት አቀንቃኝ ነበሩ፣

በዚህ የተነሣም ጆርመኖችን ጠልተው ሩሲያውያኑን እኛቸውን ዘርግተው ተቀበሏቸው. . . ቢያንስ መጀመሪያ የመጡ ግዜ። ዛሬ ቤተሰቦቹ በሕይወት ቢኖሩ ስለሱ ሚና አይተው ምን ይሉ ነበረ ብሎ አሰበ። ኧረ ምንም መጠየቅ አያስፈልግም። በሕይወት ቢኖሩ ምን እንደሚሉ መች አጣው?

እንግዲህ አሁን በመጨረሻ ይህ ተግባሩ ሊያመጣበት ስለሚችለው ነገር ተጨነቀ። እዚያ ባሕሩ ስር ያለው ቦምብ በገህድ የሚታየውን እንዲጋፈጥ አስገደደው። እዎን አንድ ትንሽ ሕዝብን ለመቆጣጠርና በኃይል ለመያዝ በሚደረግ ጥረት ተባባሪ እየሆነ ነው። ግጆሮቭ ያመጣለትን ሲያይ ደግሞ ይህን ረሳው። በጣም ፈቃደኛ ሆኖ በሙሉ ልብ ነው ይህን ሲሰራ የቆየው። አሁን ግን የሚችለው ደረጃ ደርሷል። ቦምብ እዚያ መኖሩን መጠራጠር እስከማይችልበት ደረጃም ደርሷል። ማመዛዘን ከዚህ በኋላ አይችልም። እዎን አሁን ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት።

«ሻምበል!» የሚል ጩኸት መጣ። «ተገናኝ»

ሔልደር በዚህ ሁኔታ ማድረግ ከነበረበት በጣም ቀስ ብሎ ተነሣ። መሰላሉን በመውጣት ላይ ወዳለው የጫፍ ክፍል ገባ። ባለስልጣኑም አቅርቦ የሚላያይ መነፅር ሰጠው። እዚያ ቻናሉ ግድም ከስቶክሆልም ሳይርቅ አንድ የቁጥጥር ጀልባ ቆሟል።

ሔልደር በጀልባ መስታወት ውስጥ ወጣት ወንዶችን ተመለከተ። በስተቀኙ ደግሞ በሌላ ቻናል ሌላ ጀልባ ብቅ አለ። ሁለቱ አንድ ላይ ሆነው እሱ ወዳለበት አቅጣጫ መጡ።

ወደ እርሱ ቀረብ ሲሉ ፍጥነታቸውን ቀነሱ ምናልባት መቶ ክንድ ያህል። አንድ ከሁለቱ መሀል አንደኛው ላይ የነበረ ወጣት ፖሊስም በድምጽ ማጎያው፣ ስማ በሶቪየት የባሕር መርከብ አዛዥ ሻምበል፣ እኔ ስዊድን ንጉሣዊ ሥርዓት ባሕር ኃይል ወኪል ነኝ። አባላቶችህን በሙሉ ማራገፊያው ላይ ይሰባሰቡ ዘንድ ባስቸኳይ ትዕዛዝ ስጥ። ከዚያም ምርመራ ስለሚኖር እንዲዘጋጁ አሳስብ። ገብቶሀል?»

ሔልደር ማይክራፎኑን እነሳና በሩሲያ ቋንቋ፣ «የሶቪየቱን ኤምባሲ ተወካይ ባስቸኳይ ማግኘት እፈልጋለሁ። ይህን ተወካይ እስካላገኘሁ ድረስ ከሌላ ከማንም ጋር እውቅና ሰጥቼ ግንኙነት አላደርግም።» ይህን ከተናገረ በኋላ የማሰራጫ ቁልፉን ለቀቀውና ወደ ላጭኑ ተጠግቶ ተደገፈ። «ተኳሽ አባላቶች በሙሉ፣ በማራገፊያው ላይ ምድባችሁን ለመያዝ ተዘጋጁ!!!»

ስዊድናዊው ፖሊስ አንድ ሰው ያቀበለውን መጽሐፍ እንስቶ የሆነ ነገር ይፈልግ ገባ። ከዚያም ስቅጣጭ በሆነ ሩሲያኛ፣ መርከባችሁ የስዊድንን የባሕር ድንበር ጥሷል። ስለዚህ በቁጥጥር ስር ውላችኋል። ይልቅ ጦር መሳሪያችሁን ለማስረከብ ተዘጋጁ።»

ሔልደር ወደ ላጭኑ ቀረብ አለና ተናገረ። «ተኳሽ አባላቶቻችሁ በሙሉ ወደ ማውረጃው ብያለሁ!!! ቶሎ በሉ፣»

ፊት ያለው ማከፈፊያ ተከፈተና ማራገፊያው ላይ ተደፋ። ልክ ያኔም መሣሪያዎቻቸውን እንደያዙ ዱብ ብለው ወረዱ። የቡድኑ ዓለቃ ሔልደር ፊት በተጠንቀቅ ትዕዛዝ ለመቀበል ቆመ።

http://ethzare.wordpress.com

ሔልደር ራሱን በእምንታ ነቀነቀ። «አሁን አቀባብሉና አተኩሩ፣ በስተግራ ባለው ሳይ አተኩሩ።» ይህንን ትዕዛዝ በፍጥነት ሲከውኑት ባድናቆት ተመለከታቸው። ጥይት እጉርሰው እንደጨረሱ ወደ ሳጥኑ ተናገረ። «ስፓርክስ!»

«አቤት ጌታዬ» ሲል ድምፁ መለሰለት።

«FOXን ላከው»

50

ሩል በቻለችው ፍጥነት በመቀመጥ አፒቼላ እና ዊል በራሳቸው በኩል ያለውን ሲያወሩላት ማድመጥ ጀመረች።

«ኤሚሊዮ እና እኔም እንቺን የምናውቅ መሆናችንን ስናውቅ በጣም ነው የተገረምነው፣» አለ ዊል። «ከዚያም አስታገርን ሂደን ኮፐንሀገን በሚገኘው ሆቴል ልዘገይ እችላለሁ የሚለውን መልዕክት ስንተውልሽ እንቺ የተውሽውን መልዕክት አገኘነው። ከዚያም ወደ ስቶክሆልም ባሕር ላይም ማረፍ በሚችል አይሮፕላን ተሳፍረን እኔ ሶፋ ያለው ሳሎን ጭምር በመያዜ ይሄንን ያንቺን ክፍል ሰረዝኩ። ኤሚሊዮ በሚቀጥለው ክፍል ያድራል። ይልቅ ቁርስ ትፈልጊያለሽ?

«አዎ፣ ይመስለኛል፣ ልብላ እስኪ» አለች ሩል። «ምንም ሆነ ምን»

ዊል ቁርስ አዘዘላት። «ለማንኛውም የምግብ ፍላጎትሽንም ያልገደልነው በመሆኑ ደስተኞች ነን። ግን ስታገኚን ደስ የሚልሽ መስሎን ነበረ የጠበቅነው።»

«ኧረ እንዴ . . . እሱማ ደስተኛ ነኝ። ግን እስኪ የደረስንበትን ላሳውቃችሁ»

«እባክሽ» አለና ጋባዣት ዊል። «ለመሆኑ እዚህ ስቶክሆልም ምን ትሠሪያለሽ?»

«ትላንት አለቃህን ላነጋግረው ሂድኩ፣ ሁሉንም ነገር ነገርኩት ከዚያም ፕሬዚዳንቱን ማነጋገር እንደምፈልግ ገለፅኩለት»

«እሺ ከዚያስ?»

«ደስ ብሎታል ብዬ እገምታለሁ፣ ግን የዚያኑ ያህል በጥንቃቄ ነው አመጣጤን የተቀበለው። ወደ ፕሬዚዳንቱ አልመራኝም ግን ስቬን ካርልሰን ከሚባልና እዚህ በሚገኘው የአገር መከላከያ ሚ/ር ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ካለው ሰው ጋ አገናኘኝ። ወደ ሚኒስትሩ እንዲሄድ ከተቻለም ደግሞ ጠ/ሚሩን እንዲያገናኙኝ እሞክራለሁ። እኔ የምልህ ኤሚሊዮ፣ ከማጆሮቭ ኮምፒውተር ሰርቀህ ያወጣኸው ማቴሪያል ይኼ ነው እንዴ?»

«አይ እሱ ኪሴ ውስጥ ነው፣» ሲል አፒቼላ መለሰች። «ሆኖም ግን ማቴሪያሉን ማንበብ የምንችለው ኮምፒውተር ስናገኝ ብቻ ነው። ለነገሩ ችግር የለም እዚህ ስቶክሆልም ውስጥ ባለ አንድ የኮምፒውተር መደብር የሚሠራ ልጅ ስለማውቅ እዚያ ሄደን ሳይሳካልን አይቀርም። ሰዓቱን ተመለከተ። «አራት ሰዓት ሳይ ይከፍታል። ለማንኛውም በቅድሚያ ቁርስ አድርጊና ከዚያ ተያይዘን እዚያው እንሄዳለን። ያመጣሁት ነገር ግን ይኼ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን አለው የተባለውን ሰው እንደሚያሳምንልኝ ነው ተስፋ

የማደርገው። ከዚያ በላይም የሆነ ነገር ይኖራል የያዝኩት። እስኪ ብቻ ለማንኛውም እናያለን።»

«ጥሩ፣» አለች።

«ይልቅ እኔ የምልሽ ሩል» ሲል ዊል አቋረጣት። «ባንቺ በኩል ያለው አፀፋ ትንሽ ግር የሚያሰኝ ሆነብኝ። ኤሚሊዮ ባመጣው ነገር በጣም ትደሰቻለሽ ብዬ ነበረ የምጠብቀው»

«አሀ. . . ወይኔ ይቅርታ እሺ፣ በእውነት ደስ ብሎኛል፣ ግን ያጋጠመኝን ሁሉ አልነገርኳችሁም እኮ።» በማለት ማለዳ ላይ አየር ማረፊያ የገጠማትን እና ያየችውን ጭምር ነገረቻቸው።

«እና ይኼ ታክሲ ነጂ ያልሽው ሆነ ብሎ አንቺን ሲጠብቅ የነበረ ይመስልሻል?» ሲል ዊል ጠየቀ።

«እኔኑ አድናሮ ሊጠብቅ እንደነበረማ ቅንጣት ታህል አልጠራጠርም። በስቶክሆልም ውስጥ ካንቺ በቀር ሩል የምተባል ሴት እንደምትመጣ የሚያውቅ አልነበረም። እና ይኼ ማለት ምን ሊሆን እንደሚችል አትገምቺም?»

«ሌላ ሰው እዚህ እንደምትመጪ መረጃውን አገኘ ማለት ነዋ፣»

«አዎን በትክክል ብለሽዋል። ታዲያ ይኼንን መረጃ ያገኙት ከዋሽንግተን ነው።»

«ምን? ዋሽንግተን? እዚያስ ቢሆን አንቺ ወደዚህ እንደምትመጪ ማን ያውቃል?»

«እርግጠኛ መሆን አልችልም፣ ግን ለማን እንደሚነግር ምንም የማትበት መንገድ የለም። ብቻ ዋናው ቁም ነገር እኔ ካርልሰንን እንዳላገኘው ሲበዛ የፈለገ እና የተጨነቀ ሰው መኖሩ ነው፣»

«እኔ ይኼ ሰው ማን ሊሆን እንደሚችል ልትገምቺ ትችያለሽ?»

ሩል በዚህ ግዜ ስለ ሰን ፍላወር ገለጻችላቸው። «ይኼ የሳየመን ዘመቻ ነው። ጉዳዩ ፍርጥርጥ ብሎ እንደሚወጣ ታውቆታል። እና ከኢጀንሲው እንድወጣ በዘዴ እያስገደደኝ ነው፣»

«ግን እኮ. . . ኧረ ተይ በናትሽ ኪት። እንቺን ለማስወጣት አስገድደሻለሁ ብሎ አይገድልሽም አይደል»

ራሷን በእሱታ ነቀነቀች። «እይ ቢያንስ ቢያንስ እኔን የሚገድልበት ግላዊ ምክንያት የለውም»

«ታዲያ ግላዊ ካልሆነ ሌላ ምን ምክንያት ይኖረዋል?»

«እይ ያው ማለት የሰንፍላወር ጉዳይ አለ። እሱን በተመለከተ ምንም ነገር ይፋ እንዲወጣ አይፈልግም።

ሆኖም ሳይመን ግን ሥራውን ጠብቆ ለማቆየት ሲል አይገድለኝም። ቢሆንም እንኳ እዚህ ኩባያ ውስጥ ያለውን ሥራ ጠብቆ ለማቆየት ያህል ብቻ ያንን አይፈፅምም።»

አፒቼላ ይህንን ግዜ ተናገረች። «ግን ዲንግርክ ውስጥ አንድ ነገር ክቶኖ ሳይበላሽ እንዳልቀረ ነው ግምቴ»

«እኔም እኮ በሀሳብ ወደኋላ ተጉዤ ለማስታወስ እየሞከርኩ ነበረ፣» አለች ሩል። «ሳይመን የሮም ጣቢያ ኃላፊ በነበረ ግዜ . . . ያው ከእኔ ጋር ስንተዋወቅ ማለት ነው እንደምታስታውሰው . . . በሶቪየት ኤምባሲ ካሉት ሰዎች ከአንዱ ጋር በጣም ይግባባ ነበር። አብረው ብዙ ያመሹ፣ ይጠጡም ነበረ።

http://ethzare.wordpress.com

እና ታዲያ በዚህ ሥራ ውስጥ እንዲህ ያለው ነገር ትንሽ ግራ አይመስልም? ከእኛ ሰዎች አንዱ የእነሱን ሰው ማልመድና በራሱ መንገድ መኮትኮት ከቻለ እንዳንዴ እኛም እሱን ልንጠመዝዘው እንችላለን ማለት ነው፤»

«ወይንም በተገላቢጦሹ ማሰብ ነው፤» አለ ዊል ዝግ ብሎ።

በሩ ተቆረቆረ። አስተናጋጁ በጋሪ የሚገፋ ትሪውን ይዞ እያንሸካሸከ ገባ። ወዲያው ቴሌቭዥኑን ከፈተው። «መቼም ይሔንን ድንቅ ነገር እንዳላያችሁ ነው?» ሲል ጠየቃቸው። «ለማንኛውም ተመልከቱ»

ሩል፣ ሲይ እና አፒቼላ በተከፈተው ቴሌቭዥን ላይ አፈጠጡ። የካሜራው እይታ ከሄሊኮፕተር ላይ ሆኖ የተቀረፀ ነገር በስተቀኝ በኩል ጥግ ላይ አንድ የሶቪየት ውስኪ ደረጃ ባሽር ሰርጓጅ መርከብ ምንም ሳይንቀሳቀስ ቆሟል። ቀረው የቴሌቭዥኑ ስክሪን በተለያዩ የስዊድን የባሕር ኃይል መርከቦች ነው የተሞላው።

«ማንኛችንም ስዊድንኛ እንናገርም፤» አለችው ሩል ለአስተናጋጁ። «ለመሆኑ ይኼ ሁሉ የት ነው የሚከናወነው?»

«በባሕር መሀከል ባለው ደሴት ላይ ያለው ቦታ ሲሆን ሆገርን ተብሎ ይጠራል። ከስቶክሆልም ሰባት ወይ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሚገኘው።» ይህን ተናግሮ ወደ ዴስኩ በመሄድ አንድ ለቱሪስት ጎብኚዎች ተብሎ የተዘጋጀ የስዊድን ካርታ አመጣ። «እዚህ ጋ ነው» አላቸው በጣቱ እያመለከተ። «ይሔ አነስተኛ ሰርጓጅ መርከብ ከዛሬ ሚት ጀምሮ እዚያ እንደቆመ ነው ለማወቅ የተቻለው። በማለት እነሱ በአግራሞት ካርታውን ሲመለከቱ ትቷቸው ወጣ።

ትሪና ራጉሊን ለመጀመሪያ ግዜ ከሳምንት በኋላ ሥራ ገባች። ፈቷ ላይ ደርሶባት በነበረው የመቀጥቀጥ አደጋ የመጣው ቁስል እየደረቀ ከመሆንም አልፎ ትንሽ ሚክ-አፕ ብትጠቀም ለተመልካች በፍፁም የማያስታውቅ ወደ መሆን ደረጃ ደርሶላታል። ፈቷ ላይ ብቻም ሳይሆን በሌሎች የሰውነቷ ክፍሎች ላይ ያሉትም ቁስሎች እንዲሁ ጠፍተዋል። አሁን ላያማት መራመድ ትችላለች።

ከዚህ ቀደም በፍፁም ጎብኝታው ወይ አይታው በማታውቀው የሕንፃ ኮምፕሌክስ ውስጥ ወደሚገኝ የዋናው መ/ቤት ክፍል ተላከች። ልክ ወደሕንፃው ስትገባ አንድ ትልቅ ክፍል መሆኑን አስተዋለች። የቴሌፎን የኮምፒውተር ተርሚናሎች የተገጠሙለት ትልቅ የቲያትር ዓይነት አዳራሽ ነው። በግድግዳው ላይ ሶስት ትላልቅ ስክሪኖች አሉ። መሀከለኛው ስክሪን የባልቲክን ትልቅ ካርታ ይዟል በዚያ ላይ በርካታ በስዊድን፣ በፖላንድ፣ ሊትዌንያ፣ ላቲቭያ እንዲሁም በኢስቶንያ የሚገኙ የጦር የአየር፣ የመርከብ እና ባሕር ሰርጓጅ አነስተኛ መርከቦችንና የእግረኛ ወታደሮችን ቦታዎች የሚያሳዩ ነጠብጣብ ምልክቶች አለብት። ግን የሶቪየትን ባህር ሰርጓጅ መርከብ ለማሳየት የተጠቀሙበት ምልክት በስቶክሆልሙ ባሕር ላይ ያለ ባዶ ቦታ ላይ ማለትም ከከተማው ጥቂት ብቻ ርቆ የሚገኝ ቦታላይ የተመለከተ መሆኑን ስታይ ገረማት። በክፍሉ መሀከል ምንም የለም. . . ብዙ ቁልፎች ካሉበት የቴሌፎን ሴት በቀር። በእንድ ነጭ መሣሪያ ግድም ማጆሮቭ ጉብ ብሏል።

«የስዊድንኛው የቴሌቭዥን ፕሮግራም ስርጭት ነው አሁን፤» ሲል አንድ ሰው ለማጆሮቭ ተጣርቶ ነገረው።

«ሶስተኛው ስክሪን ላይ አሳየን፤» ሲል ማጆሮቭ መለሰለት።

በስተቀኝ ባለው ስክሪን ላይ አንድ የሆነ ምስል ብቅ ያለ ሲሆን ራጉሊንን ባስገረማት መልኩ ጃን ሔልደር ነበረ የታየው። ጉድ!!! በሰርጓጅ መርከቡ የላይኛው ሜፍ ክፍል መሀል ለመሀል ቆሞ ፎቶግራፍ እየተነሳ ነበረ። አብረውት ሌሎች ሰዎች የነበሩ ቢሆንም እሷ ግን አሳወቀቻቸውም። ከዚያም ስክሪኑ ተሰወጠና እንደ ሰፊ ቦታ ከላይ በአየር ላይ በኮሜራ ተቀርፆ ያለው ምስል ይታይ ጀመር። ሰርጓጅ መርከቡ በደምብ የሚታይ ሲሆን በተለያዩ ሌሎች መርከቦች ተከቧል።

«ትሪና፤» የማጆሮቭ ፀሐፊ ተጣርታ ጠየቀቻት። «እዚያ መቅዘፊያ ባላት መርከብ ላይ ባለው ቦታ ለሚፈልግ ሁሉ ምግብና ሻይ ቡና ማቀራረቡን እንዳትረሺ» አለቻት።

ከዚያም ከመርከቡ መሀል ለመሀል ባለው ነፃ የሆነ መቆሚያ ቦታ በመሄድ ከወደኋላ አካባቢ ገባችና ራሷን በሥራ ጠመደች። ወረራ ለማካሄድ ተይዞ ስለነበረው ዕቅድ ታውቆ የነበረ ሲሆን ይህም በዚህ በቀናው መ/ቤት ለአንድ ዓመት ያህል ስለሰራች ነው። አሁን ደግሞ ሰላምንት ያህል ባትሰራም ከሔልደር እንደተረዳችው ወረራው በጣም በቅርቡ ይጀመራል። ግን አሁንም ቢሆን ነገሩ በእውነት እየመጣ መሆኑና ሔልደርም የዚህ ዋንኛው ማጠንጠኛ መሆኑ ረብሽዋታል። በትሪ ሻይ፣ ቡና ይዛ ወደ ማጆሮቭ ተጠጋች።

«አመሰግናለሁ፣ ራጉሊን» አላት ለስለስ ባለ አነጋገር፣ ፈገግ እያለ። «እንኳ በደህና ተመልሰሽ መጣሽ። ጥሩ የእረፍት ጊዜ እንዳደረግሽ አምናለሁ»

«አዎ፣ እግዜር ይስጥልኝ» አለች ምንም እንኳ ንዴቷ ሜፍ ሊደርስ ቢሆንም እንደምንም ብላ ራሷን ተቆጣጥራ ተናገረች። እናቱን ይኼ ዲቃላ፣ እሱ እኮ ባደረሰባት ነገር ያልጋ ቁራኛ ልትሆን ትንሽ ነበረ የቀራት።

ጆንስ ደግሞ ከማጆሮቭ አጠገብ ተቀምጧል። «ኮሎኔል» ሲል ተጣራ። «ከስቶክሆልም የመጣ ሪፖርት አለን። ኪርኪላንድ የተባለችዋ ሴትዮ አየር ማረፊያ ላይ ተጠልፋ እንድትወገድ ተደርጓል»

«በጣም እሪፍ፤» አለ ማጆሮቭ ሰፋ ያለ ፈገግታ በፊቱ ላይ እየታየ። «ለፈሬ ምስጋናዬ ይድረስ፣ በሚቀጥለው ሥርጭት ቢያገኘው ጥሩ ነው።» ሲል በረጅሙ ተንፈሰ። «ግን ምናልባትም ላይሆን ይችላል። በእንድ ወቅት በጣም ይቀራረቡ ነበር፣ እሱን ማበሳጨት እንፈልግም አይደል እንዴ?» ልክ ይህን ግዘ ዴስኩ ላይ የነበረው ስልክ ጠራ፣ ድምፁ ለየት ያለ ሲሆን በዚያች ቅፅበትም ክፍሏ ፀጥ ረጭ አለች። ማጆሮቭ ስልኩን አነሳው። «ማጆሮቭ ነኝ፤» አለ።

ሲያዳምጥ ዝምታ ነበረ። «እሽ፣ ጓድ ሊቀመንበር፤» ሲል ምላሽ ሰጠ። «አሁን ያለነው ፎክስ ጋ ነው ሔልደር በፍፁም ከእኛ ጋር ላለመተባበር መፈለጉን ባደባባይ የገለፀ ሲሆን፣ ጭራሽ ለዚህ እኩይ ተግባሩ መግለጫም በሩሲያኛ ቋንቋ ብቻ ነው ከሰዎቹ ጋር የሚነጋገረው። ባሁን ሰዓት ከኢስቶኒያ እና ፖላንድ ያሉ የ WIG ወኪሎች ምላሽ እስኪሰጡን ድረስ እንዲሁም በስዊድን ከሚገኘው SPETSNAZ ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ስለሆንን ቆመናል። ግን ብዙም ሳይቆይ ወረራውን ለመጀመር አስፈላጊ ከሆነው ደረጃ ላይ እንደምንደርስ ነው።» በማለት ፈገግ አለ። «አዎን በእርግጥም እንደዚያ ነው፣

http://ethzare.wordpress.com

ጓድ::» ስልኩን ዘጋውና ወደ ሰፈው ክፍል ዞሮ ተናገረ:: «የፓርቲው ተቀዳሚ ዋና ፀሐፊ ለሁላችሁም ሰላምታቸውን አቅርበዋል፣»

ልክ ይህን ጊዜ በትያትር ቤቱ ክፍል ውስጥ የሆነ የስሜታዊነት ጉርምርምታ ተሰማ:: ራጉሊን ሻይ፣ ቡና እና ምግብ ነገሮችን ማዞሯን ቀጠለች:: ግን በድንገት ከክፍሏ የድንጋጤ ጉርምርምታ ተደመጠ:: ልክ ቀና ስትል በስዊድኑ ስክሪን ላይ አንድ ተሰቅ ያለ መርከብ እየተጠጋ ነው:: በክፍሏ ውስጥ ብትንትን ያለ ጭብጨባ ተሰማ::

«እንዲ! እንዲ» አለ ማጆሮቭ:: «እነዚህ ሰዎች ማክረር ጀምረዋል ማለት ነው:: እንግዲህ ከዚህ በኋላ ለመተኮስ ምን ታህል ጊዜ እንደምትቀራቸው አብረን እንያ!»

ራጉሊን ኮሎኔሉን አፍጥጣ ተመለከተችው:: እና የማጆሮቭ ባሕር ሰርጓጅ መርከብ የነበረችበት ቦታ ቁይ ያለችው ለዚሁ ነበረ ማለት ነው፣ ማጆሮቭ ኮሎኔሉን ሆነ ብሎ ስዊድናውያኑን ለመጎንተልና ነገር ለመፈለግ ነው የተጠቀመበት:: በስክሪኑ ላይ በነበረው ምስል ላይ ዓይኖጅን ተከለች:: ሔልደር ከተገደለ እሷ ምን ልትሆን ነው? እሱ ሰርሷ ጥበቃ ማድረግ በማይችልበትና በሌለበት ሁኔታ በማጆሮቭ ጋጣ ውስጥ ገብታ እንደፈለገ የሚያደርጋት እንስሳ ነው የምትሆነው:: ይህ ብቻም ሳይሆን አሁንም ይሁን በኋላ ማጆሮቭ እሷን መግደሉ አይቀርም:: ማጆሮቭ ደግሞ ይህንን በማድረግ በጣም ነው የሚደሰተው:: ማዞሯን ጨርሳ ነፃ በሆነው ቦታ ከተግ ላይ በመቆም በክፍሏ የሚደረገውን በደምብ ለመቆጣጠርም ሆነ ማጆሮቭ ሳያስተውላት ከኋላው ሆና የሚነጋገረውን ሁሉ ልቅም አድርጋ ለመስማት በሚያስችላት ቦታ ላይ ቆመች::

«ለመሆኑ አፒቼላን ወይንም ሊን የተመለከተ ነገር ተደርጓል?» ሲል ማጆሮቭ ጆንስን ጠየቀው::

«አይ፣ የለም ጌታዬ» አለ ጆንስ:: «ምናልባትም ሁለቱ ወደስቶክሆልም ጨርሶ ሄደው እያውቁ ይሆናል»

«አዎን ምናልባት ላይሆን ይችላል፣» አለ ማጆሮቭ ደግሞ:: «ግን ምንም የምንጠቀመው ዕድል የለም:: በአሜሪካ ኤምባሲና በመከላከያ ሚ/ር ላይ እኛ ዘለን ወደ እርምጃ እስክንገባ ድረስ ጥብቅ ሰለላ ይካሄድ ዘንድ ነው የምፈልገው»

«ጌታዬ የመጀመሪያው ቡድን አሁን በተባሉት በሁለቱም ቦታዎች ላይ የሚሰልሉ ፐርሶኔሎች አሉት:: ወደዚህ ተመልሳችሁ ኑ አላልኳቸውም»

«በታዩበት እንዲገደሉ» አለ ማጆሮቭ:: «በዚህ ግዜ በስቶክሆልም መንገዶች ላይ ስለሚኖር የተገባ ባህሪ ለመጨነቅ ሲበዛ ዘግይተናል::»

52

ሩል ፍፁም ትዕግስት አጥታ ትጠባበቅ ነበረ:: እሷ አፒቼላ እና ሚል በስቶክሆልም ከተማ እምብርት ላይ ከሚገኝ እና በጣም ከተጨናነቀ የቢዝነስ ሴንተር ውስጥ በሚገኝ አንድ የኮምፒውተር ማዕከል ነበር የሚገኙት:: አፒሲሊያ እና ሮልፍ የሚል መጠሪያ ያለው የኮምፒውተር ሴንተሩ ባለቤት አዲስ ኮምፒውተር አውጥተው ጠረጴዛ ላይ በማድረግ እየገጠሙት ነበር::

«መቾ አጣሁት» እያለ ነበረ አፒቼላ፣ «በስካንዲኔቪያ IBM PC AT ያለው ብቸኛ ሰው ቢኖር ሮልፍ እንደሆነ ተናግሬያለሁ» ወደ ሩል ዞረ:: «ሮልፍ በመላው አውሮፓ እጅግ የተደነቀ እና ምንም የኮምፒውተር አከሰሪ ተጠይቆ የማይታጣበት ትልቅ ሱቅ ነው ያለው፣» አለ::

«ግን በጣም የበዛ ነው፣ ይቅርታ አድርጊልኝና፣» አለ ሮልፍ በደስታ ስሜት ወደ ሩል ዞሮ:: «ኤሚሊዬ ስቶክሆልም በመጣ በማንኛውም ግዜ ለራሱ ገንዘብ ማግኛ ሲል እዚህ ገብቶ ሲያግርጥ ይውላል:: እኔ ግን ለዚህ ሁሉ አገልግሎት የማገኘው ቢኖር የሱን ቁልምጫ ነው»

«ከዚያ በተጨማሪ ወቅታዊ ሞደፊኮችን፣» ሲል አፒቼላ አከለ:: «እንደውም እንደምጠብቀው ከተሳካ ላንተም አንድ አዲስ ነገር አሳይሀለሁ፣» ሞኒተሩን እና ኪ ቦርድ መፃፊያውን ከኮምፒውተሩ ጋር አገናኘውና ከዚያም እዚያው ካለው ማተሚያ ማሽን /ፐሪንተር/ ጋር ተያያዘ::

«ይኼ ማሽን እንኳን ሊቃጠል ይቅርና ጭራሽ በርቶ እንኳን አያውቅም፣» አለ ሮልፍ ጭንቅ ባለ ስሜት:: «እና ይኼንን ብታብሳሹት እስከተወለኑ ወራት ድረስ ሌላም አይኖረኝም:: እና ይኼንን ነው ለማሳያነት የምጠቀምበት::»

«አይዞህ፣ አትፍራ» አለው አፒቼላ:: «እዚህ ሰርቼ ስጨርስ ከመቃጠልም በላይ በባለሞያ ታይቶ ምናልባት የሚሻሻልበት አጋጣሚ ይኖራል፣»

«ወይኔ!!» አለ ሮልፍ ዓይኖቹን እያቅበዘበዘ::

አፒቼላ ባዶ ዲስኬት አውጥቶ የወረቀት መያዣ እሽጉን በስክሩ ድራፈር /ትንሽ መፍቻ/ በመቅደድ ማይላር የተባለውን ዲስክ ከውስጥ አወጣው:: ከዚያም ከኪሱ ውስጥ ትንሽ ባትሪ በማውጣት በስክሩ ድራይቨር ፈታትቶ ባትሪዎቹን ወደ ቤንቹ አወጣ:: ማይለሩን ፕሳስቲክ ኤንቨሎፕ ውስጥ ከተተና ኤንቨሎፑን «የታሸገ» ብሎ የፈቦት:: «ይኸው እዚህ ጋ» አለ:: «እንግዲህ ይኼ የፐሳስቲክ ኤንቨሎፕ ችግርን ይቋቋም እንደሁ እናያለን፣ በዚያውም በተጨማሪ ባልቲክን ያቋርጥ እንደሆን» ከዚያም በኮምፒውተሩ የዲስክ ማስገቢያ ውስጥ ከትቶ አንድ የሆነ ነገር ፃፈ:: ከዚያም በስክሪኑ ላይ ዝርዝር ፋይል ስሞች ወጠ ::: አሁን ደግሞ አንድ የሆነ ሌላ ነገር ታይፐ አደርጎ ሲዕፍ ፓሪንተሩ ማተም ጀመረ::

ቆሞ እዚያው ባለበት ተመለከተ:: ልክ ዶክመንቱ ሲታተም ሩልም ዓይኖጅ በግርምት ብልጥጥ ተደርገው ተከፍተው ነበረ ሲያይ የነበረው:: «ጥሩ ነው፣ ኤሚሊዬ» አለች፣ «ለመሆኑ እንዴት ነው ይህንን የምታደርገው?»

አፒቼላ ትክሻውን በግድ የለሽነት ነቀነቀ:: «የማጆሮቭን ኮምፒውተር በሌለበት ሰርቄ ነው፣» ሲል እውነቱን አወጣ:: «ታዲያ ይኼ አትሞ ሲጨርስ ደግሞ እጠልፈዋለሁ»

«ማጆሮቭ ማነው ለመሆኑ?» ሮልፍ ለማወቅ ፈለገ:: «በዚህ ቢዝነስ ላይ የተሰማራ አንድም ሳይቀር አውቃለሁ ብዬ ነበር የማስበው»

«አይ እሱ እንኳ ካንተ በጣም ለየት ባለ ቢዝነስ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፣ ውድ ሮልፍ» አለው አፒቼላ:: «መቼም ባንተ የሥራ ቦታ ይህን መሰሉን ነፃነት በመጠቀሜ ይቅርታ አድርግልኝና ጓደኞቼ ብቻቸውን ቢሆኑ ይመርጣሉ:: እና እናስቸግርህ? አለው»

http://ethzare.wordpress.com

ሮልፍ እጁን በግድ የለሽነት ወደላይ ወንጨፍ አደረገ። «ግድ ይኖርሀል? ለምን ይኖረኛል? ምን ችግሮኝ? ስንት ደምበኞች ያስቸግሩኛል፣ ግን ኤሞ ምናባቱ ለናንተ ያልሆነ ለማን ሊሆን ኤሚሊዬን ደስ ይበለው እንጂ. . . » በማለት ተነስቶ ወጣና በሩን ዘጋላቸው።

«ስማ ኤሚሊዬ፣» አለችው ሩል ሲታተም የነበረውን ዶክመንት እያየች፣ «እንተ የሙሉ ግዜ ሰላይ ነው መሆን ያለብህ፣ በእውነት!» በማለት ቀና ብላ ተመለከተችው። «ግን ይህን ኮምፒውተር ስለመጥለፍ የተናገርከው ምንድን ነው?»

መጥለፉ እንኳን ረዘም ያለ ግዜ ይወስዳል» አለ አፒቼላ። «ለማንኛውም ሁሉንም ነገር ከተሠራ በኋላ ይኼ ነው ብሎ ማስረዳቱ የሚሻል መሠለኝ»

ፕሪንተሩ የቆመ ሲሆን ሩልም የዶክመንቱን ተከታታይና ተያየዥነት ያላቸውን ወረቀቶች ከመሀል መቅደድ ጀመረች። «ስማ ይልቅ ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሂጂ ካርልሰንን ማግኘት አለብኝ። እና ኤሚሊዬ አንተ እዚህ ጥቂት እየሠራህ ቆይ። እንተ ከዚህ ባትወጣ እና አሁን መንገድ ባትንከሳወስ ይሻላል። ባለፈው ያ እርጉም ማጆሮቭ ለጥቂት ነው የሳተህ፣ አሁን ደግሞ እንተን ማየት ያላብደዋል።

«አይ አያሳስብሽ፣» አለ አፒቼላ። «እንቺ ስዊድንን ከራሻዎቹ ጥቃት ስትከላከሉ እኔን ባተሌ የሚያደርጉኝ ብዙ ነገሮች አሉ፣»

«ዊል፣» አለች። «በኋላ አደጋ ሊኖረው ስለሚችል ማንኛውንም ነገር እንድታደርግ መጠየቁ ይከብደኛል፣ ግን ከእኔ ጋር ወደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አብረን ብንሄድስ? ከሴናተር ካር አብረህ የመስራት ዕድል ታገኛለህ። በዚያ ላይ የካርለሰንን ተቀባይነትና ተዓማኒነት በመጪመሩ በኩል ጉልህ አስተዋፅኦ ሊኖርህም ይችላል»

«በኋላ አደጋ ሊኖረው የሚችል ነገር ስታይ ግልጽ አይደለም፣ የምን አደጋ?»

«አየህ ሊ ምን መሰለህ አሁን እያወራን በዚህች ደቂቃ እንኳን ቢሆን በስቶክሆልም አንተን የሚከታተለ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ማጤን ይኖርብህል እላለሁ። ዛሬ እንኳ ማለዳ ላይ እኔን አጥምደው የእድሌ ነገር ሆነና በስህተት ሌላዋን ቀንጥሰው ጣሏት። እና የሞትኩ ሊመስላቸው ይችላል። ግን በሌላ በኩል በስህተት ሌላ ሰው የመቱ መሆናቸውን ከተረዱ ብቻዋን የምትሄድ ሴት ላይ ሊያነጣጥሩ ይችላሉ። እና አየህ አብረን ብንሄድ ትኩረት የመሳባችን ዕድል የሳሳ ነው። ጥንዶች ላይ የምንፈልጋት ሴት እናገኛለን ብለው ላያስቡ ይችላሉ እነዚህ አረመኔ እብዶች!»

«አይ ጣጣ የለውም፣ አብሬሽ እሄዳለሁ» አለ።

ሩል ራሷን በአሉታ ነቀነቀችና። «ባሁን ሰዓትማ ቴሌፎንን ማመን የመጨረሻ ጅልነት ነው፣» አለች።

ታክሲው ይዟቸው ነጎደና ከአንድ አደባባይ ገንጠል ብሎ ያለ ወደሚመስል መንገድ ገባ። ከዚያም ብዙም ከማይሰብ በር አጠገብ ቆመና «ይኼ ነው እንዴ?» ሲል ቮፈሩ ጠየቀ።

«አይሰብም አይደለም?» አለ ሊ ሲወርዱ። «ምናልባትም የስካንድኔቪያ ጥንታጎን መሳይ ነገር እያለሁ ብዬ ጠብቄ ስለነበረ መሰል»፣

ሩል ምላሽ አልሰጠችውም። መንገዱ ጸር የቆመ እና አንድ ሰው በውስጡ ለመቀመጡ ጥሳው የሚመሰክርለት መኪና ያየችው አይመስልም። ወደ ውስጥ ገቡና በእንድ ትንሽ መተላለፊያ አጠገብ ደረሱ። ከዚያም ድርብ በሮች ያሉት ቦታ አለፉ። በስተቀኛቸው ትንሽ መስኮትና ከውስጡም መለዮ የለበሰ ሰው ተቀምጦ አዩ።

«ጤና ይስጥልን፣» አሉች ሩል ለዘቡ። «ለሚ/ር ካርልሰን ከዋሽንግተን ዲ.ሲ. የመጣችው ብሩክ ኪርክላንደ ልታነጋግርህ ትፈልጋች ትላቸዋለህ?»

«የሰውየው ስም?»

«ሚ/ር ሊ ነው በል። ለሚ/ር ካርልሰን ጨምረህ ለሴናተር ካር ይሠራል ትልልኝ?»

«እየጠበቁዎት ነው ግን?» ሲል ዘቡ ጠየቀ።

«አዎ ቀጠሮ አለን፣ አሁን አይደለም አንጂ፣ ግን ሚ/ር ሊን እየጠበቁ አይደለም»

ሰውየው ወዲያው በስልክ መደወል ጀመረ። ከዚያም በማም ፈጣን በሆነ የስዊድን አነጋገር የሆነ ነገር ለመናገር ረዘም ያለ ግዜ ለሚመስል ደቂቃ ጠበቀ። በኋላም ስልኩን ዘጋው። «በቃ አሁኑኑ አንድ ሰው ይመጣላችኋል፣» የሚል ነገር ነግሯቸው ወደ ምድብ ቦታው ተመለሰ።

እነሱ እንደገመቱት ከሆነ ምናልባት ሶስት ደቂቃ ካለፈ በኋላ ነጩር አንድ ሴትዮ በድርብ በሩ ሊላኛው አቅጣጫ በኩል ብቅ ያለችው። አንድ እንደ ደወል የሚመስል ጥዝዝዝ. . . የሚል ድምፅ ተሰማና በሩ ተከፈተላት። «ወ/ሪት ኪርክላንድ? እቶ ሊ? እባካችሁ ተከተሉኝ፣»

በአዳራሹ የተወሰኑ ርቀቶች ከሄዱ በኋላ በሊፍት ፎቅ ወጡና። በእብነ በረድ የተሠራ መደገፊያ ያለው ሰገነት የሚመስል ትልቅ በረንዳ ላይ ወረዱ። ከሥሩ ትልቅና ሰፊ ሥራ የበዛበት የዴስክና የቢሮ መዓት በአዳራሽ ይታያል።

«ይገርማል፣ ይኼ እኮ ባንክ እንጂ. የሚኒስቴር መ/ቤት አይመስልም፣» አለ ሊ።

«እምን፣ ልክ ነህ በፊት ባንክ ነበረ» አለች ሲትዮዋ።

ነገር ግን ከታች ምንም እንኳ ከፍተኛ ወከባ እና የሥራ ውጥረት እንዲሁም እንቅስቃሴ ቢኖርም ወደዚህ ወደ ፎቁ ብዙም የማይደርስ በመሆኑ እዚህ ፎቁ ጋ ያለው ፀጥታ የመቃብር ያህል ያስፈራ ነበረ። ሴትዮዋ ወደ ግራ ታጥፋ መራቻቸውና ከባሱጥ ቢተሠራ የእንግዳ መቀበያ ዴስክ አልፈው ሁለት በሮች ጋ ደረሱ። በስተቀኝ ያለውን በር ሴትዮዋ እንኳኳችውና ከፍታ ሩልን እና ሊን በማስከተል ቀደም ሲል ያለፉበትን አደባባይ ወለል አድርጎ ወደሚያሳይ ፍውም ምቹ እውነትም የሚኒስትር የሚያሰብል ቢሮ ገቡ። አንድ ሰው ኪሪየኤላ ተነሳና ሊቀበላቸው እጁን ዘረጋ።

«ወ/ሪት ኪርክላንድ መሰልሽኝ፣ ለማንኛውም ስሼን ካርልሰን ሰባላለሁ። ሴናተር ካር ትመጣለች ብሎኝ ነበረ፣ ግን ሰዓቱን አላወቅኑትም ነበር።» ይህ ሰው ምንም እንኳ ፀጉሩ ቢሸብትም ፊቱ ምንም መስመር ያላወጣ በመሆኑ ዕድሜውን ለመገመት በጣም የሚያሰቸግር ገፅታ ነበረው። ስለዚህ ሩልም ከሠላሳ አምስት እስከ ሃምሳ ባለው ውስጥ ይሆናል ስትል በራሷ ግምት አስቀመጠች። የዘመኑ ሥራት የሆነ ፍሬም አልባ መነፅር አድርጓል።

http://ethzare.wordpress.com

«ሚ/ር ካርለስን፣ በእውነት በእጭር ቀጠሮ ሊያነጋግሩን በመፍቀድዎ በጣም ደስ ብሎናል» አለች።

«አይ፣ ምንም አይደል፣» አለ ወደ ምቹ ከቆዳ የተሠራ ሶፋ እንዲቀመጡ እየጋበዛቸው።

«ይልቅ ምን ልርዳችሁ?» ሲል ካርለስን ልክ ከተቀመጡና ራሳቸውን ካመቻቹ በኋላ ጠየቀ።

«አረ እንዲያውም እኛ ነን እርስዎን ለመርዳት የምንፈልገው፣ ሚ/ር ካርለስን፣» አለች ሩል። «በቅድሚያ ስሜ ኪርክላንድ እንዳልሆነ ከወዲሁ መግለፅ ያለብኝ ይመስለኛል። እኔና ሴናተሩ ይህ ስም አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ብጠቀም የተሻለ እንደሚሆን ቀደም ብለን በመነጋገራችን ነው። ከዚያ በኋላ መታወቂያዋን አወጣችው። «ስሜ ካትሪን ሩል ነው፣ የአሜሪካ መንግሥትን በመወከል ከግዕከላዊው የምርመራ ባለስልጣን ወይንም CIA ነው የመጣሁት። ከዚህ በተጨማሪም የሶቪየት ቢሮ ተብሎ በሚታወቀው ውስጥ ግለትም ከሶቪየት ጎብረት የሚመጡ የስለላ መረጃዎችን በሚተነትነው ድርጅት ውስጥ የኃላፊነት ቦታም ያለኝ ነኝ።»

«አሀ፣ ገባኝ» አለ ካርለስን ያሳየችውን መታወቂያ በጥንቃቄ እየገመገመ።

ከዚህ በመቀጠል በእጇ ወደ ሊ አመለከተች። «እሱ ዊል ሊ ይባላል፣ የሴኔቱ የስለላ ኮሚቴ ቆንጽላ ተወካይ ነው፣ ከዚያ በተጨማሪም የሴናተር ካር የትርብ ረዳት ነው፣»

ዊል ለካርለስን የራሱን የሴኔት መታወቂያ አሳየው።

«ጤና ይስጥልኝ ሚ/ር ሊ፣» አለ ካርለስን፣ «ሴናተር ካር ከጥቂት ጊዜ በፊት ዲ.ሲ. በነበርኩ ጊዜ ስላንተ ሲያወራ የሰማሁት የመስለኛል፣»

«እንግዲህ ዛሬ እዚህ እርስዎ ጋ እግር የጣለን፣» አለች ሩል፣ «እኔ በምሠራበት የግዕከላዊው ስለላ ድርጅት CIA ውስጥ በቅርቡ ስለተጀመው የሰዊድን መከላከያ እጅግ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ልናሳይዎ ነው፣ ከጊዜ እጥረትና ሌሎች ባሁን ሰዓት እዚህ ዘልቄ ገብቼ ልናገራቸው በማልፈቅድ ምክንያቶች ከዚህ በላይ መጠበቅ የለብኝም በሚል ነው አመጣጤ። ይህንንም ስል የተለመደውን የመንግሥትና ዲፕሎማሲያዊ መስመሮች ተከትዬ ልምጣ ብል የሚወስደውን ግዜ በማሰብ ነው። ወደ ሴናተር ካር የሄድኩ ሲሆን ሴናተሩም ጉዳዩን በጥልቀት ከመረጃው አንፃር መርምረው ሲያበቁ ወዲያው ምንም ግዜ ሳላጠፋ አርስዎ ጋ እንድመጣ ይህም ጉዳዩ ባስቸኳይ ለመከላከያና ጠ/ሚኒስትሮችዎ እንዲደርስ እንደሚረዳ ነው የመከሩኝ፣»

«እሺ እንግዲህ፣ ወ/ሪት ሩል፣» አላት ካርለስን፣ «ልሰማና ላዳምጥ ዝግጁ ነኝ፣ በጣም ስቦኛል፣ ግን ለማንኛውም ምንድነው ልትነግሪን የመጣሽው?»

ሩል ወዲያው ከዚህ በመቀጠል እጥፏላ ቀደም ሲል ከማጆሮቭ ኮምፒውተር ውስጥ ሰርቆ ያወጣውን ዶሴ አሳየችው። በዚህ ዶሴ አናት ላይ ያለውን በክለሳ መልክ የተቀመጠ ነገር ካነበቡት፣ ምን ልነግርዎ እንደመጣሁ ከሞላ ጎደል ያጉኑታል»

ካርለስን እጠር ብሎ በክለሳ መልክ የተቀመጠውን ነገር በፍጥነት አነበበውና አሁንም በድጋሚ ፊቱ ላይ አንዳችም ለውጥ ወይንም ስሜት

ሳይታይበት አነበበው። በመቀጠልም በፍጥነት ሌሎቹን ገፆች ገለጥ ገለጥ በማድረግ ይዘታቸውን ተመልክቶ ወደ ሩል ቀና አለ፣ «በጣም አስደንጋጭ ነው፣» አላት። «በርግጥም ነኝ የምትይውን ዓይነት ሰው ከሆንሽ ማለትም አሁን የማይመስል የስለላ ልብ ወለድ ፈጠራ ዐሐፊ ካልሆንሽ በተር. . .» ቃላት ጠፍቶበት የሚመርጥ የሚፈልግ መሰለ። «ይህ ዶሴ ከየት እንደመጣ ልጠይቅ?»

«ዶሴው የተወሰደው በላቲቪያ ኮስት አካባቢ ከሚገኘው የሶቪየት ጦር ቀጠና ጣቢያ ከነበረ አንድ ኮምፒውተር ወስጥ ነው፣ ታዲያ ከተወሰደ አርባ ስምንት ሰዓትም አይሞላውም» ስትል ሩል መለሰችለት። «እኔ መቼም ይህ አሁን ያነበቡት ዶሴ ሶቪየቶች በትክክል ሃሳባቸውና ውተናቸው ምን እንደሆነ የሚያሳይ እንጂ ተራ የጦር ልምምድ እንዳልሆነ ነው የሚገባኝ። ከሌሎች ምንጮች የተገኘ ይህንኑ ነገር የሚያጠናክር መረጃ ደግሞ ላሳይዎት፣»

ሩል በፍጥነት ከእንድ ቀን በፊት ሴናተር ካር ፊት ያቀረበችውን ነገር ነገረችው። ካርልሰን ሲያጻምጣት ጭንቀቱና ሀሳብ የገባው መሆኑ ይበልጥ ግልፅ እየሆነ መጣ፣ እንዳንዴም በጥያቄ ያቋርጣት ነበረ። ስትጨርስም ካርለስን ለአፍታ ያህል ዝም አለ።

«እስኪ ንገሪኝ» አለ በኋላ ላይም። «ይህ ዕቅድ መቼ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል የሚያመላክት ማንኛውም ፍንጭ ይኖር ይሆን እንዴ?»

«ተጀምሮ ሳይሆን እይቀርም የሚል ግምት ነው ያለኝ፣» በግለት ሩል ምላሽ ሰጠች። «የርስዎ ባሕር ኃይል ደሴት መሀል ይዞት ያለው የሶቪየት የባሕር መርከብ ከዚህ ጋር የተገናኘ እንደሚሆን ነው ጥርጣሬዬ፣ እናም ምናልባትም ይህንኑ ነገር በየፋ ለመጀመር የሚያስችል አጋማሚ እንዲፈጠር ሆን ብሎ ለመተንኮስ የቆመም ሳይሆን አይቀርም። ሚ/ር ካርልሰን በነገራችን ላይ በቅድሚያ ያሳየሁዎት ዶሴ ወረራ የሚካሄደው ፍፁማዊ በሆነ ቅጽበትና ያልተጠበቀ ሁናቴ ነው ይላል። ሚኒስትርዎንና ጠ/ሚኒስትርዎን ባስቸኳይ የሀይል ማሰማራቱን ነገር ቢያሳስቧቸው ሩሲያውያኑ አሁን የተያያዙትን የጥፋት ተልዕኮ እንዲያቆሙ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። ይህን ለማድረግ ደግሞ በጣም የረፈደ አይመስለኝም፣»

«አሀ. . . ገባኝ፣» አለ ካርልሰን ወደ መስኮቱ አቅጣጫ እየተመለከተ።

«እንድ ሌላ ነገርም አለ፣» አለች። «ዛሬ ሚት በስቶክሆልም አየር ማረፊያ ሳለሁ እንዲት ኪርክላንድ የተባለች አሜሪካዊት ሴት የግድያ ወንጀል ተፈጽሞባታል። ጥቃቱ የታለመው ለእኔ እንደሆነ ቅንጣት ታህል አልጠራጠርም። እንድ የሆነ ሰው ወደ ስቶክሆልም እየመጣሁ እንደነበረ ሳያውቅ አልቀረም። ግን ከእርስዎ ሌላ እኔ ወደ ስቶክሆልም እየመጣሁ እንደነበረ የሚያውቅ አለ እንዴ?»

«አይ፣ አረ በፍፁም፣ ማንም የለም» ሲል ካርልሰን መለሰላት።

«ለመሆኑ ከሴናተር ካር ጋር ትናንት ቀደም ሲል ስለተደረገው ጥሪ በድጋሚ አውርታችኋል?»

«እንደውም፣ አላወራንም»

ሩል ተመልሳ ሶፋው ላይ ዘርፈጭ አለች። «ነው እንዲ» አለች።

«ወ/ሪት ሩል፣» ሲል ካርልሰን ጀመረ፣ «ይህንን አሁን ያሳየሽኝን ዶሴ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ብታውሺኝ? እመልሰለሁ አሁኑኑ»

«ምን ችግር አለው?» አለች ሩል።

http://ethzare.wordpress.com

ካርልሰን ፋይሉቹን ሰበሰበና ከክፍሉ ወጣ።

«የሚኒስትሩ ቢሮ ከእንግዳ መቀበያው ፊት ብሎ ነው መሰል፣» አለች ሩል ሊይን እያየች።

«ሴናተር ካር ቢሯቸው ጎንና ጎን ነው ብለውኝ ነበረ፣»

«እንዳሳመንሽው ነው የሚሰማኝ ኪት፣» አለ ሊ። በጣም እኮ ነው የተንቀጠቀጠው፣»

«ምን መንቀጥቀጥ ብቻ፣» አለች ሩል፣ «ጭራሽ መሠረቱ የተናጋም ሞምር ነው የመሰለው»

«ግን ሳይመን እንቺ ወደ ስቶክሆልም ልትመጪ እንደምትችይ አስጠንቅቋቸው ይሆናል ብለሽ ትገምቻለሽ?»

«ልጅ ስለወለድኩለት ሰው እንዲህ ብሎ ማውራቱ የቱን ያህል እንደሚከብደኝ እኔ ነኝ የማውቀው፣ ግን ሀቁ እንደዚያ የሚያደርግ የሚመስለኝ መሆኑ ነው። ሴናተር ካር ለካርልሰን እውነተኛ ስሜን ካልነገሩት ያ መረጃ ሊመጣ የሚችለው ከዋሽንግተን ነው፣ እዚያ ደግሞ አሰፍስፎ ለዚህ አሳዛኝ ሥራ የተሰማራው ሳይመን እንጂ ማንም አይደለም :: ምን ይህ ብቻ ፋታም አላገኘሁምና ሳልነግርህ ቀረሁ እንጂ እኔኑ የሚከታተልለት ሰው ቁጥር አላስኪድም ማለት ጀምሯል። ወደዚህ ስመጣ አየር ማረፊያ ላይም ይኸው እንዲከታተለኝ የተቀጠረው ሰው አስቸግሮኝ እንደምንም አልፈው ነው የመጣሁት። በስንት መከራ እንዲያናግረኝ አደረግኩት ሳይመን ልጁን እንድትሰጪው ይፈልጋል አለኝ። እኔ ደግሞ ይኼንን ላለማመን ብዙ ምክንያት አለኝ። መረጃ የፈለገው በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ ነው ግምቴ፣»

«እገናለሁ ሩል፣» አለ ዊል፣ «ሰውየውን እንደማትወጂው አውቃለሁ፣ ግን»

«እምን ልክ ነው ለፒተር በኋላ ላይ የገዛ ወላጅ አባቱ የሶቪየቶች ሰላይ መሆኑ ባደባባይ ሲጋለጥ የመጨረሻ ነው የሚያስጠላው፣ በድርጅቱ ውስጥ መረጃ እያወጣ የሚሰጥ ሰው አልነበረም። እኔ ስመለስ ግን ጉድ እንደሚወጣ ነው፣»

ሁለቱም ቁጭ ብለው በመቆየት ከዚያም ካርለሰን እስኪመለስ ቀጣዮቹን ሀያ ደቂቃዎች ያህል በክፍሏ ጎርደድ አሉ።

«ስክቡር ሚኒስትሩ ተነጋገርን።» ሲል አበሰረ። «አሁን በቀጥታ ከጠ/ሚ/ራችን ጋር በስልክ ወሬ ይዘዋል። ኃይላችን እንዲሰማራ ትዕዛዝ ሰጥተዋል። ዛሬ በእራት ሰዓት የሲቪል ደህንታዎች በሙሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ ይሆናል። ወ/ሪት ሩል መቼም እንዴት ብለን እንደምናመሰግንሽ አላውቅም በእውነት እንዲሁም ሚ/ር ሊ፣ ትልቅ ሥራ ነው የሠራችሁት»

ሩል በድንገት ከፍተኛ ድካም ተሰማት። እዚህ ድረስ ለፍታ የመጣችው ወሬዋ ሳይረፍድ ተቀባይነት ያገኛል በሚል ተስፋ ነው። «ሚ/ር ካርልሰን ስላመናችሁን እጅግ በጣም ነው የምናመሰግነው። ከዚህ ውጭ ግን በጉዳዩ ላይ ላደርግ የምችለው ማንኛውም ነገር ይኖር ይሆን እንዴ?»

«ይኖራል ብዬ አላምንም፣» ሲል ካርልሰን መለሰላት። «ነገር ግን ምናልባት በሚቀጥሉት 24 ሰዓታት ውስጥ ልናናግርሽ እንፈልግ ይሆናልና ዝግጁ ሆነሽ ብትጠብቂ መልካም ነው፣»

«ግን የእኔን እና የሚ/ር ሊን ስም ይፋ ባታደርጉትስ? እኔ እዚህ የመጣሁት አፈሲላዊ ባልሆነ መንገድ ነው። ስሜ ቢነሳ ደግሞ በኋላ አስቀያሚ ነገር ሊከተለኝ ይችላል፣»

«እሺ ችግር የለም፣» አለ ካርልሰን። «እውነትሽን ነው። ይህን ጉዳይ መስማታችንን በፍፁም ይፋ አናደርገም። በዚህ ላይ በኛ ድርጅት ውስጥ ለዚህ ጉዳይ ኃላፊነቱን መውሰድ የሚፈልጉ በርካታ ሰዎች አሉን።» በማለት ያመጣችውን ዶሴ አስረከባት። «እነዚህን በሙሉ ግልባጭ አድርገናቸዋል፣ ዋናውን ያገኘው። ወደ ሆቴልሽ ተመልሰሽ የምንለውን ብትጠባበቂ ይሻላል አላለሁ፣ የኔ መኪና ታች ይጠብቃችኋል»

ካርልሰን ወደ ታች እስከ አሳንሰሩ ይዟቸው ሄደ።

«ይገርማል ባክህ፣ ይሄ ነገር በዚሁ መጠናቀቁን በቀላሉ ማመን አቃተኝ» አለች ሩል አሳንሰሩ ወደታች ይዟቸው ሲወርድ። «ይሔ ነገር እጉል ይጓተታል እንጂ አያልቅም ብዬ ነበረ። ሁሌም በርካታ ሰዎችን ለማሳመን መከራዬን አያለሁ ብዬ ነበረ»

«በእውነት በጣም ትልቅ ሥራ ነው የሰራሽው፣» አለ ዊል። «ሰትመለሺ ደግሞ ከዚያም በላይ የሆነ ሥራ ይቀራል፣»

አሳንሰሩ ቆሞ ወጡ። «እውቃለሁ እኔም እየጠበቅኩ አይደለም?»

ወደፊት በር ተያይዘው እመሩ። ልክ እንደደረሱም ሩል ቆማ ወደ መንገዱ በመመልከት ራሷን በአምንታ ነቀነቀች። አንድ መኪና የመጣ ሲሆን ሾፈር አጠገቡ ሆኖ ይጠብቃል።

«ይኼ የካርለሰን መኪና ሳይሆን አይቀርም፣» አለ ዊል። «እዚህ ጋ ይጠብቃችኋል ብሎን ነበረ»

«እምን ብሏል እሱማ፣» አለች ቅላፂ በሌለው ድምፅ፣ «ግን የሚገርመው ሾፈሩ ዛሬ ሚት አየር ማረፊያ የጠበቀኝ እና ያገኘኝ መሆኑ ነው እንጂ፣»

አስካር አስካርሰን በተለይም ከቅርብ ሳምንታት ወዲህ አንድ የተጠ ናወታቸው ልምድ አልለት ብሏቸዋ እንቅልፍ ቶሎ አይወስዳቸውም። እንድምንም ኑጋና ሚት ላይ ወደ ላሱኑ ሲወርዱ የልጃቸው ሚስት ለቁርሥ ብላ ጠረጴዛውን እያዘገጃጀችው ነበር። ቴሌቭዥኑ ተከፍቷል፣ ይህ ግን ያልተለመደ አልነበረም. . . ልጅቷ ቲቪው የሚለውን መስማት ፈለገችም አልፈለገች ሁሌ የካፌ ቲቪ ይመስል አስጨኻ እንደለቀቀችው ነው። ከዚህ የተነሣ አስካርሰን ብዙውን ግዜ በራሱ የደረሰበት ግምት ይቺ ልጅ ጨኽቱን ትወድደዋለች ወይንም ቤቱ ጭር እንዳይል ያደርጋል በማለት መክፈቱን መርጣዋለች ወደሚል ድምዳሜ ደርሰዋል።

ግን ዛሬ ፍፁም ባልተለመደ መልኩ እንዲያው የሚለውን ልስማ እስኪ ብሎ ሲያፈጡና እሷም ካፈላችው ቡና ቀድታላቸው ቆት ማለት እንደጀመሩ ቲቪው ላይ ተለክተው ቀሩ። ጉድ፣ በቲቪው ስክሪን ላይ አንድ የሩሲያ አነስተኛ ሰርጓጅ መርከብ ነበረ የሚታየው። «ምንድን ነው ባክሽ፣ ኤልሳ?» በማለት የእንጀራ ልጃቸውን ጠየቋት። «ምን እየተካሄደ ነው ለመሆኑ?»

http://ethzare.wordpress.com

«አይ. . . አይ አበሳዬ ምነው ባልከፈትኩት ኖር፣» አለችና ቲቪውን ልታጠፋው ተጠጋች::

«አንቺ እረፊ ነው የምልሽ!» ሲል በቁጣ አዘዛት:: «ምን ትላለች ይቺ! ማየት እፈልጋለሁ አትንኪው!»

«አቦ በናትዎት ይተዉ እንጂ!» አለች ኤልሳ:: «ትርፉ ጨንራን መላጥና በጭንቀት መንገብገብ ነው:: ግድ የለዎትም ባያዩ ይሻላል»

«የለም፣ በደምብ አያለሁ!» አላት አስካርለን ፍፁም እልህ ተጋብቶ:: «አንቺ ወደ ሥራሽ ሂጂ እኔ ግን አያለሁ!»

ወደ ጓዳ ከመግባት ይልቅ አብራው መመልከት ጀመረች:: «ይህማ አደጋ ሊሆን አይችልም» አለች:: «አሁንም አደጋ ሊሆን አይችልም ባለፈው ግዜስ እዚያ ካልስኮኒያ አንዱ ተጋጪ ሲሉ ይመስል ነበር፣ ይኼንን ግን ምንም ቢሉ ምን አደጋ ነው ብዬ አልቀበለውም::

«አቦ አንቺ ዝም ብለሽ ማየቲ አትችይም እንዴ! እስኪ ልስማ፣»

አስካርለን ቲቪው ስክሪን ላይ ዓይኖቻቸውን ብልጥጥ አድርገው በማፍጠጥ የሚባለውን መስማቱን ተያያዙ:: ከሰማው መረዳት እንደቻሉትም ያ እነስተኛ ሰርጓጅ መርከብ ሆጋርን በተባለ ደሴት ላይ አርፎ ነው ያለው:: ይህንን ደሴት ደግሞ በደምብ ያውቁታል፣ በቁጥጥር ፓትሮሉ በርካታ ግዜያት አልፈውበታል:: ከወንድ ልጃቸው የመኖሪያ ቤት ሶስት ኪሉ ሜትር ያህል ብቻ ርቀት ላይ ነው የሚገኘው::

ኤልሳ የምሣ እቃ ለማዘገጃጀት ወደ ጓዳ ገባች:: የምሳ እቃዎቹን ይዛ ስትመለስ ግን የባለቤቷ አባት ሄደዋል::

አስካርለን ስትጠራቸው ከጓላቸው ሰምተዋታል ግን ሞተራቸውን እያስነሱ በዚያ በሞተሩ የሚጋጋል ድምፅ መሀል ለተወሰነ ግዜ ብቻ ነበረ የሰሙት:: መኪናቸውን በማስጮህ በስቸኳይ በደሴቱ መሀከል ወደሚገኘው ሳርማ ቦታ ሲያመሩ የኋ ጥሪ ድምፅም እየጠፋ ነበረ::

54

ሩል ከእብነ በረድ በተሠራው ግድግዳ ላይ ተደገፈችና ትንፋሿን ለመቆጣጠር ሞከረች::

ዊል አጠገቧ ግትር ብሎ እንደቆመ ነው:: «ግን እኔ የምልሽ እንደው እርግጠኛ ነሽ ግን የሾፈር ዩኒፎርም ስላደረገ ተመላለሱብሽ እንዳይሆን:: ምናልባትም የካርለሰን ሾፌር እንዳይሆን»

«አረ በፈለከው እምልልህለሁ፣ ግጥም አድርጌ ነዋ እርግጠኛ የሆንኩት!» አለችው ሩል:: «ይልቅ ሌላም አንድ ነገር ልንገርህ:: እዚህ አገር ያሉ የመንግሥት ሠራተኞች ለዚያውም በሾፈር በሚነዳ መኪና ይጠቀማሉ? እኔ አይመስለኝም ሶሻሊዝም ያመጣው የ «እኩልነት» ፈሊጥ እዚህ አገር እንደውም በከረረ መልኩ የሚጠቀሙበት ነው የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ::»

«ከዚህ የምንወጣበት ሌላ መንገድ ማግኘት ያሻናል፣» አለ ዊል ፈጠን ብሎ ዙሪያውን እየቃኘ:: አሁን የቆሙት በመውጫው ግድም ባለ እንደ ኮርደር ነገር ላይ ሲሆን ወደ ኋላ ቢያዩ የሚመራቸው ወደ ሀገሃው ብቻ ነበረ::

«ከዚያስ? ወጥተንስ የት ልንሄድ? ስትል ሩል ጠየቀችው:: «ካርልሰን እኮ ለሶቪየቶቹ እንደሚሠራ ባሁን ሰዓት ግልፅ የሆነልን ይመስለኛል:: ምን ችግር አለው ከተግውን በፖሊስ እያሳሰሰ ያስፈልገናል:: ይልቅ አሁን ወደ ሆቴሉ መመለስ እጅ መስጠት ነው የሚሆንብን ስለዚህ እዚያ አንሄድም:: ወደ መንገድም መውጣት እንችልም::»

አንድ የሆነ ጥዝ የሚል የደወል መሰል ድምፅ ተሰማና የባሕር ኃይል ዩኒፎርም የለበሰ አንድ ግዙፍ ሰው በፊት ለፊቱ በር በመውጣት ሌላ አንድ ሲቪል የለበሰ እና ሳምሶናይት ቦርሣ የያዘ ሰው እጅቦት አለፉ:: ሁለቱም ግን ሲያልፉ ሩልና ዊልን ገርመም አድርገዋቸው ነበረ:: የባሕር ኃይል መለዮ የለበሰው ሰው አንድ የሆነ ነገር በስዊድንኛ ቋንቋ ተናገረ:: ሩል ፈገግ በማለት ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች:: ሁለቱም ሰዎች ቆሙና አፈሰሱ በድጋሚ ተናገረ::

«እንደምን አድራችኋል? ሻምበል» አለ ሊይ የሰውየውን ወታደራዊ ማዕረግ እንዲሁ በራሱ ብቻ ገምቶ:: «ዛሬ ሚት እዚህ ቀጠሮ ተይዞልን ነበረ. . ይቅርታ ግን በቅድሚያ ራሳችንን እናስተዋውቅ:: እኔ ዊል ሊ እባላለሁ፣» አለ የሲኔት መታወቂያውን እያወጣ «የዩናይትድ ስቴትስ ሲኔት በስለላው ኮሚቴ ቀጥሮ ያሰራኛል፣ እሷ ደግሞ ካትሪን ሩል ትባላለች የአሜሪካው የሰለላ ድርጅት (CIA) አባል ናት» ሩል መታወቂያዋን አሳየቻቸው:: «ለመሆኑ ሴናተር ቤንጃሚን ካርልሰን ታውቋቸዋላችሁ?» ሲል የሲቪል ልብስ ለብሶ የነበረው ጠየቀ::

«አዎን፣ እንዴታ» ሲል ዊል መልስ ሰጠ:: «እንደውም ለእኔ አለቃዬ ናቸው፣ እሳቸው ናቸው ሩልን ወደዚህ ወደ ስቶክሆልም የላኳት፣»

«ለምን ሥራ ብለው ላኳት?» ሲል ሻምበሉ ጠየቀ ትንሽ ግራ የገባው እየመሰለ::

ሩል ዝም ብላ ታሪኳን መናገር ስትጀምር ዊል በፍጥነት አቋረጣትና፣ «በስቶክሆልሙ ደሴት ላይ ስላረፈው የሶቪየት ንብረት ነት ያለው እነስተኛ ሰርጓጅ መርከብ እንድ መረጃ አለን::» አለ:: «ታዲያ ይህን መረጃ ለሚ/ር ሰቬን ካልሰን፣ ማለት የቢሮው ኃላፊ መናገራችን ነበረ፣ ግን እኔ የምለው. . . ለመሆኑ ሻምበል ሚ/ር ካርልሰን የራሳቸው በሾፈር የሚነዳ መኪና ያላቸው ስለመሆኑ የምታውቀው ነገር አለ እንዴ?»

«አረ በፍፁም የላቸውም፣ የምን መኪና?» ሲል ሲቪል የለበሰው መለሰ:: «ካርልሰን ሁሌ ሚት ሚት በሞተር ሳይክል ነው የሚመጣው»

«ውጭ ላይ ግን የሾፈር ዩኒፎርም አደርጎ የቆመውን ሰው አላየኸውም?» ሲል ዊል ከተል አድርጎ ጠየቀው::

ሁለቱም ሰዎች ወደኋላ የተወሰኑ እርምጃዎችን ጠጋ ብለው ሄደው ተመለከቱና ተመለሱ::

«አላየነውም፣» ሲል ሻምበል መለሰ:: «ይህ ሰው የዚህ መ/ቤት ተቀጣሪ አይደለም፣»

ሩል ይህን ግዜ ተናገረች፣ «ሻምበል በዚህ በመከላከያ ሚ/ር ውስጥ የደህንነት ደምብ የሚጥስ ነገር ሳይሰራ እንደማይቀርና በደሴቱ ላይ ከሚገኘው

http://ethzare.wordpress.com

የሶቪየቱ ሰርጓጅ መርከብ ጋር ሳይገናኝ እንደማይቀር ነው እምነታችን። ግን ይህን አሳብቢና አስቸኳይ ጉዳይ ለምን ወደ ውስጥ ገባ ብለን እንወያይበትም?»

ሻምበሉ መታወቂያውን በድጋሚ በደምብ ተመለከተና ሲቪል የለበሰውን ሰው በጥያቄያዋ አስተያየት ሲመለከተው ያኖው ራሱን በአምንታ ነቀነቀ። «ወደ ወሰጥ ተከትሳችሁን ትገቡ?» አለ ሻምበል። ከዚያም እየመራቸው።

ግን ሩልን ባስደነገጣት ሁኔታ ያለፉት በካርልሰን ቢሮ በኩል ነበር። ከዚያም ወደ ካርልሰን ቢሮ ፀሐፊ እና እንግዳ ተቀባይ ጋ ገቡና እሷም ፍፁም በፍርሀት ተሸበረች። ፀሐፊዋም ልክ እነሱን ስታይ የገረማት መሰለች፣ «እንደምን አደራችሁ?» አለች። ቆማ ቢቸግራት።

«ለግዚው ምንም ስልክ አትደውይ» አላት ሲቪል የለበሰው ሰውዬ ወደግራው በመሆር በካርልሰን ቢሮ በኩል እያለፈ።

ከዚያም ወደ አንደ ሰፋ ያለ እና በውድ የቢሮ እቃዎችም በተንቆጠ ቆጠ ቢሮ ገቡ። «እንግዲህ ሚ/ር ሊ እና ሚስ ሩል፣» አለ አፈሰሩ። «እኔ ሻምበል ሆልምክዊስት እባላለሁ፣ ከሰዊድን ንጉሳዊው ጦርን ነው የምወክለው።» ይህን ካለ በኋላ ሲቪል ወደ ለበሰው ሰው አመለከተ። «እሱ ደግሞ ሚ/ር ጆርን ዊውትበርግ ይባላል የመከላከያ ሚኒስትር ነው። ለመሆኑ ምን ልትነግሩን የምትፈልጉት ጉዳይ ኖሮ ነው ወደዚህ እንድንመጣ የጠየቃችሁት?»

ሩል ከፍተኛ የሆነ የእፎይታ ስሜት ተሰምቷት በዚህ ስሜት ተውጣ ስለነበረ በደምብ ለመናገር አልቻለችም። ግን ሊ ፈጥኖ ይህን ክፍተት ሞላው። «ክቡር ሚኒስትር እንግዲህ ዛሬ ሟች ካርልሰንን እንዳላናገሩት ነው የሚሰማን፣» አለ።

«ዛሬማ ከነጋ በስትራትስበርግ በሚገኘው የሰቶክሆልም ወታደራዊ ቀጠና ነው ያሳለፍኩት፣» አሉ ሚኒስትሩ።

«ክቡር ሚ/ር» አለች ሩል አሁን እንደምንም ከስሜቷ እያገገመች። «እባክዎን በዶሴው በላይ ያለውን ማጠቃለያ ያንብቡት፣» በማለት ከፋይሏ አውጥታ ሰጠችው።

ዌስትበርግ ገፁን በማንበብ ዶሴውን ለሻምበሉ ሰጠውና ሩል ደግሞ ፋይሏን በትንሽ የኮንፈረንስ ጠረጴዛ ላይ ዘረጋጋችው። ይህንን ነገር በዚህ መልኩ ስታሳይና ስታቀርብ ባለፉት ሶስት ቀናት ብቻ እንኳ ሶስተኛ ስለሆነ በጣም ተለማምዳው ነበረ። ፈጠን ብላ በማሳየትም የሰዊድን የጦር ኃይሎች ምንም ፋታ ሳይሰጡ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው አበክራ ማሳሰብ ጀመረች። በርግጥ በዚህ ሰዓት የእንቅልፍ እጦት እያስቸገራት ነበረ። «ልትዳላችሁ?» በማለት ጌጠኛ የውሀ ጠርሙስና ብርጭቆ አነሳች።

«እንዲታ፣» ሲል ዌስትበርግ መለሰ። «ወ/ሮ ሩል ወደ ሌላ ነገር ከማለፋችን በፊት ለሴናተር ካር መደወል ይኖርብናል።

ሲ ይህን ግዜ ተናገረ። «የቤት ቁጥሩን እሰጣችኋለሁ፣» አለ በማስታወሻው ሜር ሜር አድርጎ ወረቀቱን ቀዶ እየሰጣቸው። «በዋሽንግተን ገና ነው ሰዓቱ፣ ግን ብንቀሰቅሰው ይነጫነጫል የሚል ግምት አልነበረኝም።»

«ሴናተሩን መረበሽ ግን ያለበን መስሉ አይታየኝም።» የሚለው ድምፅ ከኋላቸው ነበረ የመጣው፣ ሁሉም ወደ በሩ ዞሩ። ካርልሰን ሽጉጥ በእጁ ይዞ ነበረ እንደ ጅብራ ተገትሮ የቆመው። «ወ/ሮ ሩል ስትነግራችሁ የነበረችው ነገር

ማረጋገጥ እችላለሁ፣» አለ። «ያለችው ሁሉ ምንም ማነት የሌለው ሀቅ ነው፣ በስራዋም ልትመሰገን ይገባል፣» በማለት ይበልጥ ወደ ክፍሏ ዘልቆ ገባ።

«አመሰግናለሁ ሚ/ር ካርልሰን፣» አለችው ሩል ብዙም እንዳልተመቻት በሚያስታውቅ ቃና ለራሷ ውሀ እየቀዳች። «ይሁን እንጂ በጉዳዩ ላይ ከእኔ ይበልጥ ረዘም ላለ ግዜ እየሠራሀ ነበረ፣ አይደለም እንዴ?»

«ሙሉ በሙሉ ልክ ነሽ ወ/ሮ ሩል» ሲል ካርልሰን ምላሽ ሰጠ። «ለረጅም ግዜ ነው የሠራሁት ይሁን እንጂ ሥራዬ ደግሞ እንቅስቃሴ በማስጀመርና ሰራዊት በማሰማራት እንዲቋረጥብኝ አልፈቅድም። ክቡር ሚ/ር. . ይሰሙኛል? ከፈለኩ ሁልሽንም እዚህ እደፋሻለሁ! ግን ግድ የለም አብራችሁኝ እዚህ በዝምታ እና በትዕግስት የሚሆነውን እንድትጠባበቁ ነው የምፈልገው። በእንድ ሰዓት ወይ ከዚያም ባነሰ ግዜ ውስጥ ይህ ቦታ በሶቪየት ጎብረት ቁጥጥር ሥር ይውላል ልክ ስቶክሆልምና አብዛኛው ስዊድንም እንደሚሆነው ማለት ነው። ታዲያ ሁላችንም ይህ እንዲሆን ስንጠብቅ ዝርዝሩን እንግራችኋለሁ።» ይህን ካለ በኋላ ወደ ኮንፈረንስ ጠረጴዛው በመራመድ ስልኩን አንስቶ በጥንቃቄ ቁልፎቹን እየተመለከተ የፈለገውን መርጦ ነክቶ ደወለ። «ወ/ሪት ሆልም፣» አለ በአካባቢው ለነበረችው ፀሃፊ «በሕንፃው ፊት ለፊት እየጠበቀ ያለ ሰው አለ። ሰውየውን ወደዚህ ይመጣ ዘንድ ትልኪልን? በቀጥታ ይምጣ፣ እግዜር ይስጥልኝ እሺ!» በማለት ስልኩን ዘጋው።

ልክ ካርልሰን ይህንን ሲያደርግ ሩል የውሀ ጠርሙሱንና ብርጭቆውን ባንድ ግዜ ፊቱ ላይ ወረወረችበት፣ ልክ እንደ ቅርጫት ኳስም የገፋችው መሰለ። ካርልሰን ምንም እንኳን ሽሽት ቢልም ጠርሙሱ ግን ፊቱን አማኝቶት ነበረና መነፅሩን ሰበረበት። ወደኋላው ሲወድቅም ሽጉጡ እምባረቀና ዴስኩ ላይ ያለውን ቴሌፎን አደቀቀው። ሩል ሽጉጧን በሁለቱም እጆቿ ይዛ እየተጠባበቀች ቢሆንም መተኮሱ አስፈላጊ አልነበረም።

ሲ በመጀመሪያ ካርልሰን ጋ የደረሰ ሲሆን ሻምበል ሆልምኪውስት ብዙም አልራቀም ነበር። ካርልሰን በስዊድንኛ እየጮኸ ከፉኛ ቢፍጨረጨርም ሁለቱ ግዙፍ ሰዎች አፈፍ አድርገው ያዙት። ሻምበልም ጭንቅላቱን አፍኖ ያዘው። «አፍህን ዝጋ አንተ ዲቃላ!» ሲልም በእንግሊዝኛ ጮኸበት።

«ታች ያለውና የተጠራው ሰውዬ ምናልባትም የሶቪየት SPETSNAZ ትጥረኛ ነፍሰ ገዳይ ነው፣» አለችው ሩል ለሚኒስትሩ፣ «ዛሬ ሟች ራሱ በስቶክሆልም አየር ማረፊያ እንጂን ሲገድላት ተመልክቻለሁ፣ የገደላትም እኔን መስላው ነው። ስለዚህ ሰው እንድ ነገር አሁኑኑ ባፋጣኝ ብናደርግ እላለሁ፣»

ሚኒስትሩ ስልኩን እነሱና ፈጠን ባለ ስዊደንኛ አወሩ። «የሲኩሪቲ ጠባቂ ሰውየውን እስከ አሁን እላስገባውም። ፖሊስ እንዲጠራና ፖሊሶቹ እንዲያነጋግሩት እንዲያደርግ ነግሬዋለሁ፣»

«እና ግን እመኑኝ ክቡር ሚ/ር?» በማለት ሩል ጠየቀች። «ወይንስ አሁንም ለሴናተር ካር መደወል ነው የሚፈልጉት?»

«ካርልሰን እንዳለው፣» ሲሉ ሚኒስትሩ መለሱ፣ «ሴናተሩን አሁን መረበሽ አያስፈልግም።» ይህን ካሉ በኋላ ወደ ባሕር ኃይሉ ሹመኛ ፈታቸውን መለሱ።

«ሆልምክዊስት፣ ለጦር ቀጠና ቡድኖቹ ይህ የሶቪየቱ መርከብ በምንም ሁናቴ የፈለገውን ያህል ትንኮሳ ቢያደርስብን እንኳ እንዳይተኮስበት ጥብቅ

http://ethzare.wordpress.com

ትዕዛዝ ስጥልኝ:: በመቀጠልም እዚህ ሂሊኮፕተር እምጣልን:: እኔው ራሴ እዚያ ደሴት ላይ ሄጀ ነገሮችን በበላይነት መቆጣጠር ይኖርብኛል:: ከዚያም ጠቅላይ ሚኒስትሩን ደውለህ የተፈጠረውን ሁሉ ንገራቸው ግን በተመሣሣይ ግዜም እላቸው ጋ ያለውን ጥበቃ እጅግ አጠናክረው:: ከዚህ ሌላም የጠላት ወገን ስላለን የሚያመክነውን የፖሊሳችንን ክፍል በመጥራት እዚህ ድረስ ተገኝተው ባስቸኳይ ካርልሰንን እያውጣጡ እንዲመረምሩት ትዕዛዝ ስጥ:: ይሄ ሰውዬ የሚያውቀውን ሁሉ ማወቅ አለብኝ::» ስልኩን እንስቶ ደውሉ በስዊድንኛ ትዕዛዝ ይሰጥ ጀመረ::

ሁለት ሽጉጥ ቀደም ሲል የሰሙ እና መሣሪያ ደግነው እንጣጥረው ያሉ የፖሊስ አባለት በሩ ላይ የደረሱ ሲሆን ወዲያው ካርልሰንን በካቴና አሰሩት::

ሚኒስትሩ ስልኩን ዘጉ:: «ካርልሰንን ወደ ቢሮው ውሰዱልኝ፣» ሲሉ ትዕዛዝ ሰጧቸው:: «እዚያ ስለምናውጣጣው እንጻይወጣ ዘግታችሁ አቆዩልኝ፣» ከዚህ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሩል መልሱ:: «እያንዳንዱ የወታደራዊ ቀጠና እና ዋና ዋና የሚባሉ የሲቪል ይዞታዎችም ቢሆኑ አሁኑኑ በጥብቅ ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ ከዚያም አጠቃላይ የሆነ እንቅስቃሴ ይጀመራል ይህን ግዜ ከውጭ አንድ ሳይረን መጮህ የጀመረ ሲሆን ሌላ ሳይረንም ተከተለ:: «ይኸውና አንግዲህ፣» ሲሉ ፈገግ አሉ:: «እንዲህ ፈጣን ምላሽ ባንድ ትዕዛዝ ማግኘት መቻል ጥሩ ነው፣ በጣም አሳረፈድንም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ወሪት ሩል ሚር ሊይ ከእኔ ጋር እንዲመጣ ትፈልጊያለሽ?»

ከርቀት ላይ በጣም እየቀረበ የሚመጣ የሂሊኮፍተር ቾፍ ቾፍ የሚል ድምፅም ይሰማል::

«ከስቶክሆልም ይልቅ እዚህ የተሻለ ደህንነት ሳይኖር አይቀርም፣» አለች ሩል::

ትሪና ራጉሊን በቴአትር መመልከቻ መሰሉ አጻራሽ እንጻለች ስክሪኑ በፍጥነት ከቀይ ወደ አረንጓዴ እንደዚሁም በተገላቢጦሽ ሲለዋወጥ በማየት ተደሰተች::

«WIG የመጀመሪያው ቡድን እየሄደ ነው፣» ጆንስ እንዲህ ብሎ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲናገር ራጉሊን በኢስቶኒያ ያለው የአይሮፕላን ቀለም በፍጥነት ሲለዋወጥ አስተዋለች::

ማጆሮቭ በጥቁሩ ስልክ ላይ አንድ የሆነ ቁልፍ ተጫነ:: «በጎተንበርግ የምትገኙ የቡድን አምስት አባላት ተንቀሳቀሱ!» ሲል ተጣርቶ ተናገረ:: «በኖርዌይ ያሳችሁ የቡድን ሰባት አባላት ሂዱ!»

«ለመንቀሳቀሻ በቂ የሆነ ነገር አለን ኮሎኔል፣» ሲል ጆንስ ሙሆ ተናገረ:: «አሁን መሄድ እንችላለን፣»

«አይሆንም፣» አለ ማጆሮቭ፣ «ገና ከአምስት ያህል ዩኒቶች መስማት አለብን ሊቀመንበሩ ትዕዛዝ እንዲሰጡ ከማድረጌ በፊት ሙሉ በሙሉ እነዚህ ስምሪት ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ይኖርብኛል፣»

«በካርልስክሮና ያለው የቡድን አራት አባላት ሪፖርት አድርገዋል፣ ጌታዬ!» ሲል አንድ ሰው ተጣርቶ የተናገረ ሲሆን ይህን ግዜም በስክሪኑ ላይ የሚታየው ቀለም ወደ አረንጓዴነት ተለወጠ::

ማጆሮቭ ተገትሮ ቆሞ ያለ ሲሆን በድንገት ግን ጭንቀትና ሀሳብ የገባው መሰለ:: «በስቶክሆልም ካለው ቡድን አንድ ስትራግናስ ወዳለው ቡድን ሶስት መሄድ የለብንም:: ለመሆኑ ከነርሱ ምን ሪፖርት ነው ያገኘነው? ያለ ሁለቱ ውልፍ ማለት እንችልም፣»

«አልገባኝም፣» አለው ጆንስ:: «ቡድን አንድ ከማንም በላይ በደምብ ቦታው ላይ ከደረሰ ቆይቷል:: ታዲያ ሌሎቹን ምን ያቆያቸል?»

«አሁንም አፒቼላንና ሊን አያሰሱ ነው፣» አለ ማጆሮቭ በድጋሚ እየተቀመጠ:: «ክትትሉን ረስተው በድጋሚ እንዴ እንዲሰባሰቡ ምልክት ስጣቸው:: ዝግጁ እንዲሆኑ እፈልጋለሁ፣ ባስቸኳይ!»

ጆንስ የሚጠራ ስልክ ነበረና እንስቶ የተወሰኑ ቃላትን ከተናገረ በኋላ ወደ ማጆሮቭ ፊቱን መለሰ:: በስትራግናስ ከሚገኘው ሶስተኛው ቡድን የተሰጠን ምልክት አለ:: የስቶክሆልሙ የጦር መሪቤት የሆነ ልምምድ በማድረግ ላይ ያለ ነው የሚመስለው:: መግቢያዎች የተዘጉ ሲሆን ወታደሮችም በተለያዩ የጦር መኪኖች ውስጥ ሆነው የግቢውን ወሰን እየጠበቁ ነው::»

«ይህማ ሊሆን አይችልም!» ሲል ማጆሮቭ በጩኸት ተናገረ:: «እስከ ሳምንት ድረስ ለልምምድ ሲባል የተያዘ ምንም ፕሮግራም የለም፣ ካርልሰን ፕሮግራሞቹን ነግሮኛል፣»

ጆንስ ሌላ ቀልፍ ተጭኖ እደመጠ:: «ኮሎኔል፣ ቡድን አንድ በስቶክሆልም ውስጥ የሲቪል መከላከያ ሳይረን ማድመጡን ሪፖርት እያደረገ ነው፣ ለመሆኑ ምን እየተካሄደ ነው?»

ልክ ሲናገር ራጉሊን በቴያትር መሰሉ አጻራሽ በስተቀኝ በኩል ያለው ስክሪን ቀደም ሲል በስቶክሆልም ደሴት ከነበረው መርከብ በአንድ ስቱዲዮ ውስጥ ዴስክ ላይ ያለን ሰው ለማሳየት ሲለወጥ ተመለከተች::

«በሶስተኛው ስክሪን ላይ ድምፅ ስጠኝ!» ሲል ማጆሮቭ ጮሆ ተናገረ::

«. . .በስቶክሆልም ውስጥ ለሚገኘው ማዕከላዊ ስቱዲዮዎችን፣» አለ አንድ ድምፅ አሰማና ጀመረ:: «የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በመላው ስዊድን የከተት አዋጅ አውጇል:: ግን ማንኛውም ወታደራዊ ዘመቻ ካሁን ሰዓት ጀምሮ ተሰርዟል:: የጦር ሠራዊት አባላት የሆኑ በሙሉ ለየዩኒቶቻቸው ባስቸኳይ ሪፖርት እንዲያደርጉ እናሳስባለን:: በሪዘርቭ ክፍል ያሉ የጦሩ አባላት እና የሲቪል መከላከያውም በሙሉ ከዚህ ቀደም ወደ ተመደቡበት ይሄዱ ዘንድ ይህንን ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላልፈናል:: የጦሩ ሪዘርቭም ሆነ የሲቪል መከላከያው አባላት ያልሆኑ የስዊድን ዜጎች ሁሉ አሁን ባሉበት ቦታ ላይ እንዲቆዩ ታዘዋል:: ቀደም ሲል ዝመቱ ያልተባሉ የፋብሪካና የቢሮ ሠራተኞችም ባሉበት እንዲቆዩ:: በሌላ በኩል ግን ማንኛውም የግል ሞተር መኪኖች ለወታደራዊ እንቅስቃሴ መንገዱ ፍፁም ምቹና ነፃ ይሆን ዘንድ እንዲቆሙ ታዘዋል:: ለመላው ስዊድናውያን በሙሉ መስመሮቹ ለአስቸኳይ ግዜ እንዳይጨናነቁ ሲባል ቴሌፎን አጠቃቀማችሁን በጣም እንድትገድቡት ይፈለጋል:: የመንግሥት ሥራ አስፈፃሚ አባላት፣ ባለስልጣናት እንዲሁም የፓርላማው አባላት በሙሉ ለሕይወታቸውና ለደህንነታቸው ይበልጥ ተመራጭ

http://ethzare.wordpress.com

ወደ ሆኑ ቀደም ሲል ወደየተመደቡላቸው ሥፍራዎች ተበታትነው ሄደዋል። የመከላከያ ሚኒስትሩ ወደ ሆጋርን ማለትም ስቶክሆልም ደሴት ወደሚገኘው ቦታ የበረሩ ሲሆን ይህም ከዛሬ ለሊት ጀምሮ በሥፍራው ገብቶ በሚገኘው የሶቪየት መርከብ ዙሪያ የሚደረገውን ለመቆጣጠር ሲሉ ያደረጉት ነው። ሌሎች ተጨማሪ ቀደም ሲል የተላለፈው የክተት ጥሪ ለማፍረስ የሚተላለፉ ትዕዛዞችን በየ አካባቢ ራዲዮኖቻችሁ መሰማት ተችላላችሁ።» በማለት ይህንኑ መድገም ጀመረ።

ማጆሮቭ በድጋሚ ብድግ ብሎ ነበረ። «እኔ ይህንን አላምንም፣ ይህማ በፍፁም አይሆንም» ሲል ጮኸ። የተለየ የደወል ድምፅ ያለው ነጩ ዴስኩ ላይ ያለው የቴሌፎን ቀፎ በድንገት ከፍሏ ባንድ እግሯ ያቆማት ይመስል ጮኸ። ወዲያውኑ ጭጭ አለ። ማጆሮቭ ስልኩን እንደ ተናዳፊ ተሳቢ እንስሳ ይመስል በማድፈጥ ተጠጋው፣ ስልኩ ግን አሁንም መጥራቱን ቀጥሏል። በመጨረሻም አነሳው።

«ማጆሮቭ ነኝ፣ ማን ልበል? አምን አውቄያለሁ። ጓድ ሊቀመንበር በስዊድን ቴሌቭዥን ሪፖርቱን ሰማነው እኮ። ይኼ ምናልባትም በእኑል የመከላከል ቀልድ ሊያታልሉን ሲሉ የፈጠሩት ማወናበጃ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ከሚገኙት ዩኒቶች ትዕዛዝ እየተቀበልኩ ነበር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ሠራዊቶቼን ዝግጁ ሆነው እንዲቆዩ ለማድረግ አችል ዘንድ ፈቃድ ይሰጠኝ። አምን፣ ጓድ ሊቀመንበር፣ ከሠሳሳ ደቂቃ በላይም አይፈጅም።» በማለት ስልኩን ዘጋው።

«በእኑል የመከላከል ቀልድ ሊያታልሉን ሲሉ የፈጠሩት ማወናበጃ ይሆናል?» ጆንስ ዴስኩ ጋ ቆሞ ማጆሮቭን ጮክ በሉ እየጠየቀው ነበረ። «ቡድን እንድ እኮ በስቶክሆልም መጠነ ሰፊ የሆነ አለመረጋጋት እንዳለ ሪፖርት አድርጓል፣ ቡድን ሶስት ደግሞ እንደሰማነው በስትራግናስ መቢት መግቢያ መውጫዎች መታሸጋቸውን አመልክቷል። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ እንተ ያልከው በእኑል የመከላከል ቀልድ ሊያታልሉን ሲሉ የፈጠሩት ማወናበጃ የሚል ነገር ሊኖር አይችልም።»

«አቦ አፍሀን ዝጋ!» ሲል ማጆሮቭ እንደ ብራቅ ጮኸበት። «ከሁሉም ዩኒቶች የሚመጣው ሪፖርት በስዊድን አፈር ላይ ይሆን ዘንድ አሁኑኑ ይደረግልኝ! አስፈላጊ ከሆነ ይኼንን ያልኩትን አስተላልፈው!»

ጆንስ ወደ ስልኩ በመሄድ ቁልፎቹን ነክቶ ትዕዛዞችን አስተላለፈ። ራዲሊን ቮድካ በጠርሙስ ይዛ ብርጭቆም በማንሳት ማጆሮቭ ተቀምጦ ወደነበረበት ጥቂት እርምጃዎችን በመሄድ ጠረጴዛው ላይ አደረገችለት። ቮድካውን በብርጭቆ ቀዳችለት። «ይኸው ኮሎኔል፣» አለችው የተሰማትን ወደር የለሽ ደስታ መቆጣጠር ተስኗት። «ሳያስፈልግህ አይቀርም፣»

«ዛር በይ ካጠገቤ» ሲል ማጆሮቭ ቢጮህባትም ቮድካውን አንዴ አንስቶ የገለበጠው ሲሆን ጭራሽ ሌላ ቀዳ። «ሪፖርቶቹ የታሉ ጆንስ?»

«ኮሎኔል፣» ሲል ጆንስ መልሶ ተጣራ፣ የሌሎቹ ሪፖርቶች የቡድን አንድ ድምዳሜ የሚያረጋግጡ ናቸው። በመላ አገሪቱ እውነተኛ የሆነ የድንጋጤ ና ሽብር ስሜት ነግሷል። ለሪዘርቭነት የተያዙ የሠራዊቱ አባላት ቁልፍ በሚባሉ ዒላማዎች ዙሪያ ተሰማርተዋል። እና ኮሎኔል ማጆሮቭ የቱን ያህል እንደሚያስፈራ ቢገነዘቡም ሃቅ መሆኑ ግን ይሰማኛል፣»

ማጆሮቭ ድንገጠ ብሎ እንደተቀመጠ በባዶነት ስሜት ስክራኑ ላይ አፍጥጧል። የስዊድኑን ጦር ወታደር እንቅስቃሴ የሚያመለክተው ቀይ ቀለም በስክሪኑ ላይ ቦግ ብሏል። ነጩ ቴሌፎን ጠራ።

ፀጥታ በክፍሉ ልክ እንደ ቅድሙ ነገሰ። ግን አሁንምነጩ ስልክ ጭርር ብሎ ሲጮህ ፀጥታው ተረበሸ። በዚህ ግዜም የሁሉም ሰው ዓይን ማጆሮቭ ላይ ሆነ።

* * *

56

ሔልደር በዊስኪ ጀልባው ሰገነት ላይ ቆሞ ዙሪያውን ተመለከተ ። እንድ ልክ ያልሆነ ነገር አለ። ፀጥ ረጭ ብሏል።

ነገሩን ኮልቻክም አስተውሎታል። የክዳቱ መጀመሪያ ላይ ነው። ኑፋሉ ሀይሉን ቀንሶ የባሕሩን ጠለል የህይቅ ያህል እንዲረጋጋ አድርጎታል። በጣም ይሞቃል፣ በጀልባዋ ዋና መትረየስ ላይ የተመደቡት ወታደሮቹ የፊዘዙ ይመስላሉ። ይህን ግዜ ነበር፣ ከውሀው ወዲያ ማዶ የሚያላዘን ድምፅ የተሰማው። ሔልደርና ኮልቻክ እኩል ፊታቸውን ሲያዞሩ ከግማሽ ማይል ርቀት ላይ የስዊድን አውዳሚ የጦር ጀልባ በዝግታ ወዳሰብት ስትመጣ ተመለከቱ። ከዚህ በፊት መሬት ወደዚያችው የሰርጓጅ መርከብ ከባሀር ጠለሉ ትደዩ ተወድረው የነበሩት መትረየሶች አሁን ወደላይ እያዞሩ ነው። በሁለት መቶ ርምጃ ርቀት ላይ በሁለት አላሽ ጀልባዎች የሞሉት ተኳሾች የመሳሪያዎቻቸውን አፈሙዝ ወደላይ አነጣጥረው ትተዋቸው ፈንጠር ብለው ቆመዋል።

«ምንድነው እሱ?» ጠየቀ ኮልቻክ። «ምን እየተፈጠረ ነው?»

የኮልቻክ ሹክሹክታ ሔልደርን አስገረመው። «ሊተውን ነው፣» አለ ሔልደር። «እትተኩሱባቸው ተብለዋል።»

ሔልደር በትንኮሳ ጦርነት የመቀስቀስ ሀሰብ የለውም። ለማጆሮቭ ታሪካዊ ህልም ብሎ የማንኛውም ሩሲያዊ ወይንም ስዊድናዊ ሕይወት እንዲጠፋ አይሻም።

«ለዚህ ምላሻቸው የኮድ ትዕዛዝ እስኪደርሰኝ ምንም ርምጃ አልወስድም፣« አለ ሔልደር። «ቀደም ብዬ የገመተኩት ነገር ነበረ።»

«ለመሆኑ በፍፁም ርግጠኛ አይደለሁም፣» መለሰ ኮልቻክ። «በርግጠኝነት፣ ይህ ሁኔታ እንዲቀጥል መፍቀድ የለብንም።»

ሔልደር ጆሮውን አቆመ። «ምንድን ነው?»

«ምኑ?» ጠየቀ ኮልቻክ። «እኔ ምንም. . . እዎ አሀ።»

ከግይሌይ አቅጣጫ፣ ወደስቶኮልም ከሚያመራው ቦይ በኩል የአደጋ ጊዜ ሳይረን ይሙሃል።

«በደሴቶቹ ላይ ከሚኖኑ እነስተኛ መንደሮች አንዱ ላይ እሳት ተነስቶ መሆን አለበት።

«በሁለቱ ላይ ነው እሳቱ የተነሳው፣» አለ ሔልደር ፊቱን ወደደቡብ እያዞረ ሌላ የአደጋ ጊዜ ሳይረን መደመጥ ጀምሯል። ከቅርብና ከሩቅ ሌሎች የአደጋ ጊዜ ሳይረኖች መሠማት ጀመሩ። ሁለቱም በቆሙበት ሆነው ጆሮዎቻቸውን አቁመዋል።

http://ethzare.wordpress.com

«ምን እየሆነ ነው?» ኮልቻክ ጠየቀ። «እኛን ለማረጋጋት ብለው እያወናበዱን ነው እንዴ?»

ሒልደር ፈገግ አለና። «እንተን ሊያረጋጉህ ሊሆን ይችላል፣ ኮልቻክ፣ ግን ማወናበጃ አይደለም። ስዊድኖች እየተዋከቡ ነው።»

«እንዳቀድነው ተሳካልን ማለት ነው?»

ከምስራቅ በኩል የሚመጣ አዲስ ዓይነት ድምፅ ሰማ። መጀመሪያ ላይ ሌላ ሳይረን መስሎት ነበር፣ ከዚያማን ድመፁ ተለውጦ ሌላ ዓይነት መልክ ያዘ። እየቀረበ ነው።

«ወረራ የሚባል ነገር አይኖርም፣» አለ ሒልደር። «ስዊድኖች ተጠንቀቅ ማስታወቂያውን አስምተዋል እየተደራጁ ነው። ድንገተኛ ወረራው ከሽፏል። ወረራ የሚባል ነገር አይኖርም።»

ሒልደር በጀልባዋ የጥግ መደገፊያ ላይ ዘመም ብሎ። እንዲት ጀልባ በጣም በፍጥነት እየተጠጋች ነው።» የመዝኛ የቅንጦት አይነት ጀልባ ትመስላለች። ምናልባት እንዱ ነገር የሳበው ስዊድናዊ ሁኔታውን ለመመልከት እየመጣ ይሆናል። ከዘስተጀርባ የመጣ ሌላ ድምፅ ሰምቶ ፊቱን እዞረ ከምዕራቡ በኩል እንዲት ሔሊኮፍተር ዝግ ብላ እየበረረች ወደ ስቶክሆልም አቅጣጫ እየመጣች ነው።

«ወረራማ መኖሩ አይቀርም!» አለ ኮልቻክ የሙጥኝ ብሎ። «ማጆሮቭ ይኖራል ብሎ ነግሮናል!»

«እንደእውነቱ ከሆነ ኮልቻክ፣ የተወዳጁ ፓርቲያችን ዋና ፀሐፊ ድንገተኛነቱ ከጠፋ ወረራ እንደማይኖር ለማጆሮቭ ሲነግሩት እኔ እዚያ ነበርኩ።» ሒልድር መነጋገሪያውን አነሳ። «ቁጥር አንድ።»

«እቤት ጌታዬ?» የዋና መኮንኑ ድምፅ ተሰማ።

«ነሞ ባንዲራ ስቀል፣»

«ምንድን ነው የምትለው?» ኮልቻክ ጮኸ። «የተኩስ ልውውጥ እስኪደረግ ድረስ እጅህን እንዳትሰጥ ታዘሀል!»

ሒልደር በፍጥነት እየተጠጋች ያለችውን የሞተር ጀልባ ለመመልከት ፊቱን አዞረ። «እያዳመጥክ አልነበረም ማለት ነው ኮልቻክ? አብቅቷል። አሁን ለትንሽ ጊዜ ያህል የስዊድንን ዱቡልቡል ሥጋ ስትበላ መቆየትህ ነው።»

ሌላ ድምፅ ሒልደርን መልስ ከመስጠት አስቆመው። ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሮኒክስ ድምፅ በሰነነቱ አስተጋባ፣ ተከተለ፣ አምስት ጊዜ ተደገመ።

«ኮድ ተልኮልናል!» አለ ኮልቻክ የሬዲዮ ሞገድ መቀበያው ወደተቀመጠበት እያመራ።

ሒልደር ተከተለው። በመቀበያው ላይ የተገጠሙት ብርሃን አመንጪ መሳሪያዎች 10301 የሚል ቁጥር ያስነብባሉ።

«ይኸው!» አለ ኮልቻክ። «ወረራው አሁንም ቀጥሏል! የድምፅ ሞገድ ምልክቱን ላክው!»

ዋና መኮንኑ ነሞ ባንዲራ ይዞ ገባ።

«ስቀለው፣» አለው ሒልደር።

ኮልቻክ ወደራዲዮ መገናኛ መሳሪያው ራመድ አለ። «ሬዲዮ ሀሳፊ በመነጋገሪያው ጮኸ። «የድምፅ ምልክትህን ላክ።»

«ማንው የሚናገረው፣ አብዝምትን?» ድምፅ ተሰማ።

«ኮልቻክ ነኝ፣ የፖለቲካ መኮንንህ፣ የድምፅ ሞገዱን ላክ።»

«እገናለሁ ጌታዬ፣» መለሰ የሬዲዮ ግንኙነት ባለሞያው። «ይሀን ምልክት መላክ የምችለው ግን ከኮፒቴይኑ ትዕዛዝ ሲደርሰኝ ነው።»

ኮልቻክ ሽጉጡን መዘዘ፣ «ሒልደር!» ጮኸ፣ «ይሀንኑ ትዕዛዝ ስጥ፣ ካለዚያ በቆምክበት ተኩሼ እመታሀለሁ።»

ዋና መኮንኑ ለዝምታ ቆሞ ይመለከታል። እሱም ሆነ ካፒቴይኑ ሽጉጥ አልታጠቁም።

ሒልደር አሁን በጣም እየቀረበ የመጣውን የሞተር ጀልባ መመልከት ጀምሯል። በያንስ አንድ ሽማግሌ በጀልባዋ ላይ ይመለከታል። ጀልባዋ በአርባ ወይ በሀምሳ ኖት እየተጓዘች መሆኗን ገመተ። ወደ ፖለቲካ መኮንኑ ፊቱን አዞረ።

«ኮልቻክ፣ ያንን ሞገድ ከለቀቅኩት እኛ ካለንበት በጥቂት ርቀት ላይይ በደሴቶቹ መሀል የኒውክሊየር ቦምብ ይፈነዳል።»

«ምን?»

«የማውቀው እኔ ራሴ ስላስቀመጥኩት ነው። ከፈነዳ ስቶክሆልም ብቻ ሳትሆን እኛም ድምጥማጣችን ይጠፋል። ገባህ»?

«የሚገባኝ የተሰጠኝ ትዕዛዝ ነው!» ጮኸ ኮልቻክ። «መመሪያውን ለሬዲዮ ባለሞያው ስጥ፣ አለዚያ አንተን ገድዬ እኔ ራሴ አደርገዋለሁ»

ሒልደር ነጩን ባንዲራ ይዞ በድጋሚ የቆመውን ዋና መኮንን ተመለከተ።»

«ባንዲራውን ስቀለው፣» አለው።

ኮልቻክ ሽጉጡን አንስቶ ሒልደር ጭንቅላት ላይ ተከሰ።

* * *

ሩል በሔሊኮፍተሩ ወደታች ስትመለከት አንድ የሞተር ጀልባ ባህር ሰርጓጅ መዳለችበት ክፍል ስታመራ ተመለከተች። «ሚኒስትር፣ ያንን ይመልከቱ፣» አለች፣ እየጠቆመቻቸው።

ሚኒስትሩ፣ ሲ እና አብራሪው አንድ ላይ እንገታቸውን ጠመዘዙ። የሞተር ጀልባዋ አንድ ሰው ብቻ ይዛ፣ በውሀው ላይ ከቆመችው ሰርጓጅ ጎን ለጎን እየከነፈች ከመጣች በኋላ ሙሉ ለሙሉ ፊቷን ወደሰርጓጇ አዞረች። አንድ የስዊድን አሳሽ ጀልባ ዘግይቶ ያሳድዳት ጀመረ። በሌሎች ጀልባዎች ላይ ያሉ ሰዎች ይጠቋቆሙ ጀመር። አውዳሚ ጀልባ ላይ ያሉት ተሳፋሪዎችም ለመመልከት ወደጀልባዋ ጥግ አመሩ።

«የክርስቶስ ያለህ፣» አሉ ሚኒስትሩ፣ «ሰርጓጇን ሊላተም ነው።»

* * *

አስካርሰን ሁለቱንም ነዳጅ መስጫዎች መጪረሻቸው ድረስ ከፍተው ታጠፉ። ሁለቱ ግዙፍ ሞተሮች በመጪረሻ ሀይላቸው ያጓራሉ። አስካርሰን አቅጣጫቸውን በለገነቱና በዋናው የጀልባ መትረየስ መህል አደረጉ። ከአጠ ገባቸው መቀመጫ ላይ ያለውን ባለ ሁለት እፈሙዝና ተፈናጣሪ ጥይት የሚተፋ ጠብመንጃ አነሱ። ጀልባዋ ቀጥ ብላ በሙሉ ፍጥነት የረጋውን ውሀ እየሰነጠቀች ትከንፋለች። አስካርሰን እንድ እግራቸውን ወደመቀመጫው ስር አስይዘው ሁለቱንም የጠብመንጃውን አፈሙዞች በጉንድሽ እጃቸው ከንድ ላይ አሳረፉና

http://ethzare.wordpress.com

ጣታቸውን ወደምሳጩ በመስደድ በጥንቃቄ አለሙ። ጀልባው ሀምሳ ርምጃ፣ ሰላሳ ርምጃ ያህል ቀርቷታል። አስካርሰን ሀሊናቸው ያቃጨለን አንድ ትውስታ ተከትለው ኢላማቸውን አስተካከሉ።

«አሁን ኤቢ፣ አሁን!» ብለው ከልጃቸው ልጅ ጋር ተነጋገሩና ሁለቱንም ምላጮች ሳቧቸው።

* * *

ሔልደር ተንገዳግዶ በቀጥታ ወደሰርጓጃ የምትከንፈውን ጀልባ ለመመልከት ዞር አለ። ጥይቷ ፊቱን ሲያዞር የጭንቅላቱን ጋላ ግማ ባርኔጣውን አውልቃው ሄደች። አሁን፣ በቁጣ የጋለው ኮልቻክ ላይቀር የምትከንፈውን ጀልባ ለመመልከት ፊቱን አዞረ። ከሔልደር ጎን ሆኖ ወደ ጀልባዋ ጠርዝ ተፈተለከ።

ከመጠን ባለፈ ፍጥነት ወደነሱ እየቀረበች ነው። የጀልባዋ መትረየስ ተኳሾች፣ የሚገስግሰውን አደጋ ለማምለጥ ግማሾቹ ወደውሀው ሌሎች ወደጀልበዋ ወለል ተወረወሩ።

ሔልደር ጠብመንጃውን ልክ ከመተኮሱ በፊት ተመለከተው። ጀልባዋ ከሰርጓጇ ጋር ስትላተምና ተኩሱ ሲያምባርቅ አኩል ሆነ።

ሔልደር ከሌሎቹ ጋር ራሱን በሰርጓጇ ወለል ላይ ወረወረ። ጀልባዋ ልክ እንደውሀ ላይ ተንሸራታች በሰርጓጇ ወለል ላይ ተፈናጥራ በመዝለል፣ በግምት በወዲያኛው በኩል ሰላሳ ርምጃ ርቀት ላይ በአፍጢሟ አረፈች፣ ሌላው አካሏ በመቀጠል ዘሎ ብሎ ውሃው ላይ አረፈ። ውሀው ለሁለት ተከፍሎ ወደኋላ ተነሳ። ወደ ደሴቲቱ መከንዴን ቀጥላ የውሀው ጥልቀት እየቀነሰ መጥቶ አሸዋው ላይ በሳኗ ተንሸራትታ ቆመች። ሩል በጀልባዋ ወለል ላይ የተጋደመ ሰው ተመለከተች።

«አብራሪ!» አሉ ሚኒስትሩ። «ባህሩ ዳርቻ ላይ አሳርፉት።»

* * *

ሔልደር ለጥቂት ጊዜ ብቻ ሀሊናውን ስቶ ቆይቶ ተነሳ። ከሰገነቱ ስር ተጋድሟል፣ ዋና መኮንኑ በላዩ አንገብጎል።

«‹ካፒቴን! ካፒቴን! ትሰማኛለህ?» ይላል ዋና መኮንኑ።

ሔልደር በእንድ ክርኑ ተደግፎ ቀና ሲል መንጋጭላው ላይ ከባድ ህመም ተሰማው።

«እንገትህ ላይ ሁለት ፍንጣሪዎች እግኝተውሀል፣» አለ ዋና መኮንኑ፣ «ፊትህ ላይ ደግሞ ሁለት ወይ ሶስት የሚሆኑ። መጥፎ አይመስለኝም።»

ሔልደር የስቃዩ ብዛት ምቱ መጥፎ የሆነ አስመሰለበት፣ መንጋጭላው የተሰበረ መስሎታል። መጥፎነቱ ግን የኮልቻክን ያህል አይደለም። የባለሁለት አፈሙዙን ተፈናጣሪ ጥይቶች ሙሉ በሙሉ በፊቱ ተቀብሏቸዋል። ፀጉር፣ ደምና አንጎል ተፈንጣጥሯል።

ሔልደር በዋና መኮንኑ ደጋፊነት ከወደቀበት ተነስቶ የጀልባዋ የጥግ መደገፊያ ይዞ ቆመ። ሔሊኮፍተሯ እያረፈች ወዳለችበት የባህር ዳርቻ ተመለከተ። ግዙፉ የሞተር ጀልባ አሸዋው ላይ ተኮፍሷል። ለሰላሳ ንፋስ መንፈስ በመጀመሩ ፀጉሩን ያርገበገበዋል። «ያ ቂል ግን እንደሆነ አላውቅም፣» አለ ለዋና መኮንኑ። «ግን በዚህ ውጥንቅጥ ጦርነት ላይ የተተኮሰው የመጨረሻ

ጥይት የሱ እንደሚሆን ተሰፋ አለኝ። ያንን የተረገመ ነጭ ባንዲራ ስቀለው፣ ደሞ ፍጠን!»

57

ትሪና ራጉሊንም፣ ግዙፉ የሞተር ጀልባ በሰርጓጇ ላይ ዘሎ ሲያልፍ ከሌሎቹ ጋር በአግራሞትና በድንጋጤ ተውጣ እየተመለከተች ነበር። የስዊድን ቱሊቭዥን ካሜራ በሰርጓጇ ሰገነት ላይ እንጥሮሮ አቀረበው። ቢሔልደር ገፅ ፊት ላይ ደም ኮለል ብሎ ሲወርድ ተመለከተች። ከወደቀበት ተነስቶ ለሌላ መኮንን ትዕዛዝ ሰጠ። ከእፍታ በላይ ከሰርጓጇ በላይ ነጭ ባንዲራ ታየ።

ማጆሮቭ ዳግመኛ ከተቀመጠበት ዘሎ ተነሳ። «የተረገምክ ጆንስ፣ ያንን ምልክት እንድትልክ አዝገይህ ነበር!»

«ተልኳል ጌታዬ፣» ጆንስ መለሰ፣ «መድረሱም ተረጋግጧል። ግን ቦንቡን በሳተላይት ልናገኘው አልቻልንም።»

«ሰርጓጇ የድምፅ ሞገድ ምልክቱን አልላከችም፣» አለ ማጆሮቭ፣ ጠረጴዛውን በቡጢ እየደለቀ። «በሬዲዮ አማኖቸው - ከተገደድክ በግልፅ አድርገው።»

«ግን እኮ ጌታዬ፣» አለ ጆንስ። «ብአንተ ትዕዛዝ መሠረት ሬድዮናቸውን ዘግተውታል። እያዳምጡንም። ሬዲዮናቸው ዝግ ነው።»

«የተረገመ ሔልደር!» ጮኸ ማጆሮቭ ጠረጴዛውን እየደበደበ። «የተረገመ! እንዲገደል አፈልጋለሁ! ስቶኮልም ያለውን ቡድን እንድን አግኝ። መናገር ከመቻሉ በፊት እንዲገደል አፈልጋለሁ! እጅግ ወሳኝ ትዕዛዜን በማን አለብኝነት ጥሷል! ለፈንጂው ምልክቱን ሳይልክ ተርፏል!»

«ፈንጂ ጌታዬ?» አለ ጆንስ በአግራሞትና ግራ በመጋባት።

«ከቡድን እንድ ጋር ግንኙነት ፍጠር!» ሲል ማጆሮቭ ጮኸ።

«እንችልም ጌታዬ፣ እስካሁን ስዊድናውያን ማስጠንቀቂያ ከደረሳቸው የሚተገብሩትን ርምጃ ይመስዳሉ። እስካሁን የመለሳሉ።»

«ሔልደር ወደዚህ እንዲመለስ እፈልጋለሁ! ከስቶኮልሙ ባቢያ ጋር ተገናኝ ኃይል እንዲያሰማሩበት አድርግ!»

«የስቶክሆልም ባቢያን በቀጥታ የምንገናኝበት ምንም መንገድ የለንም ኩሱኔል፣» መለሰ ጆንስ። «ከኤምባሲው ጋር የምናደርገው ግንኙነት ሁሉ በመአከላዊ ሞስኮ ማለፍ ይኖርበታል።»

ራጉሊን ማጆሮቭን ተደናግጦ ስትመለከተው ይህ የመጀመሪያዋ ነበር። ወደቴሌቭዥኑ ተመለከተች። የስዊድን ባህርተኞች ወደሩሲያዊው ሰርጓጅ እየተመሙ ነው። ከሠገነቱ ላይ ቃሬዛ ሲወርድ ተመለከተች። በደም የተሸፈነው የሔልደርን ፊት ሌላ መኮንን በጨርቅ ሲጠርግለት ተመለከተች። አሁን ስዊድን እጅ ውስጥ ነው። ከዚህ ሁኔታ መከሰት በኋላ መቼም አይለቁትም።

ነጩ ስልክ እንቃጨለ። ማጆሮቭ ራሱን ሊቆጣጠር እየሞከረ ቆሟል፣ ስልኩ በተደጋጋሚ ይጮሃል። ከፍሉ ፀጥ ረጭ ብሏል፣ ሁሉም አይኖች ኩሱኔሉ ላይ ተተክለዋል።

http://ethzare.wordpress.com

በመጨረሻ፣ መቀመጫውን ያዘና ስልኩን እነሳው። «ማጆሮቭ፣» አለ። «እይደለም ጓድ ሊቀመንበር፣ ማስጠንቀቂያው የሀሰት ያለመሆኑን አረጋግጠናል። የወረራ እቅዱ እንዳይተገበር ትዕዛዝ ሰተቼያለሁ። አይደለም ጓድ ሊቀመንበር፣ ስዊድኖች እጅ የወደቀ አንድም ሰው የለም. . . እም፣ ከሰርጓጅ መርከቧ አባላት በስተቀር። እነሱ እጅ ከመስጠት ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። እነሱን በተለይም ካፒቴይኑን ለማስመለስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አሁኑኑ ድርድር እንዲጀምር እጠይቃለሁ። ከፍተኛ ብቃት ካላቸው አባላቶቻችን እንዱ ነው. . . ሞስኮ ላይ አግኝተውታል። እሺ፣ ጓድ ሊቀመንበር፣ ነገ ጠዋት፣ እዚያ እገኛለሁ።»

ማጆሮቭ ስልኩን ዘጋው። «የወረራ ዕቅዱ መሠረዙን የሚገልፅ ትዕዛዝ ስጥ።» አለው ለጆንስ። «ነገ ጠዋት ሰስብሰባ ሞስኮ ተጠርቼያለሁ። ዕቅዱ ጊዜው ተላለፈ እንጂ አልተሰረዘም። ታያለህ።»

«እሺ ኮሎኔል፣ እንዴታ፣» መለሰ ጆንስ በለሆላስ።

ራጉሊን ተነስታ ትልቁን ስክሪን ትመለከታለች። አረንጓዴ ምልክቶቹ እንድ በእንድ ወደቀይ ከተለወጡ በኋላ ጠፉ። በክፍሉ ውስጥ ያለው ድባብ ከስሜታዋ ጉጉት ወደሰቀቀን ተለወጠ። ሰዎች በዝምታ ነገሮችን ወደማስተካከሉ ተሰማሩ። ወዲያውኑ ዋናው ስክሪን ጨለመና የቴሌቭዥኑ ስክሪን ብቻ ቀረ። ቃሬዛው ጀልባ ላይ ተጭኖ ወደደሴቲቱ ሲወሰድ ራጉሊን ትመለከታለች። የሰቪየት ዲፕሎማቶች እሱን የማስመለሱ ድርድር ቢሳካላቸው እንኳን ሔልደር ተመልሶ እንደማይመጣ አወቀች። የማጆሮቭን ከፍተኛ ትዕዛዝ ስለጣሰ ተመልሶ መምጣት አይችልም። አሁን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በብቸኝነት ጭለማ ተውጣለች።

የቲያትር አዳራሹ መብራቶች መጥፋት ጀመሩ። የደንብ ልብስ የለበሰ መኮንን ራጉሊን ወደቆመችበት መጣ። «ቡና ትስጪኛለሽ?» ሲል ጠየቃት ያንዘውን ጦር መሳሪያ ባንኮኒው ላይ እያስደገፈ። ራጉሊን ቡና ቀዳችለትና መሳሪያውን ተመለከተች። ሔልደር የነገራት ዓይነት ከፊል አውቶማቲክ ባለተስፈንጣሪ ጠብመንጃ ነው። በቅርበት ተመለከተችው፣ ማቀባበያውንና መጠበቂያውን በዓይኖቿ ፈልጋ አገኘች። መሳሪያው እንድ ሙሉ ካርታ ጥይት ጎርሷል።

58

ሩልና ሊ፣ ሆጋርን በሚገኘው የባህር ዳርቻ መኖሪያ ቤት በረንዳ ላይ እንደቆሙ፣ የሰርጓጅ መርከቧ አዛዥ በቃሬዛ ተጭኖ መጣ። መኖሪያ ቤቱን የባህር ኃይሉና ጋዜጠኞች ወደዚያው የማዘገሞ ጣቢያንት ለውጠውታል። የተደናገሩት የቤቱ ባለቤቶች ቡናና ሳንድዊች በማቅረብ ርዳታ ለማድረግ ይሞክራሉ። ሁሉም የአሳ አስጋሪውን የአስካርሰንን ታሪክ ያወራሉ። እሱም ለጋዜጠኞች ጥያቄ መልስ እየሰጠ እዚያው ይገኛል።

ሁለት ባህርተኞች ቃሬዛውን በዝግታ በረንዳ ላይ አኑረው ቀጣይ መመሪያ ይጠባበቃሉ። ሩል ገና በፋሻ ያልተጠቀለለውንና አብጦ በደም የተጨማለቀ ፊት ትመለከታለች። ሰውየው ለመናገር እየሞከረ ነው። ጎንበስ አለች፣ እሱ ግን ከእሷ ወዲያ ለመመልከት ይሞክራል።

«ታዲያስ ሊ፣ አለ የግዴን።»

«ያምላክ ያለህ፣» አለ ዊል፣ ጎንበስ እያለ። «አ. . . ሔልደር ነህ አይደለም?» የባህር ሰርጓጅ አዛዡ ቅንድቦች ወደ ላይ ተለጠጡ። «ስሜን እንዴት አወቅከው?»

ሊ ፈገግ አለ። «ሰቶኮልም ላይ ሆነህ የላልከው ንድፍ፣ የሰጠሽኝ እንኳን፣ «ሔልደር» ብለህ ነው የፈረምከበት።»

ሰውየው ላቅ እንደማለት አለ። «ውይ! ማንነቱ እንዳይታወቅ ያላደረግኩት አልነበረም!»

«ሽፋንህ እንከን አይወጣለትም፣ አለ ዊል። «ፈርማውን ያስተዋልኩት ገና ትናንት ነው።»

ሩል ሁለቱን ሰዎች አቷን ከፍታ ትመለከታቸዋለች። «ምን እየተፈጠረ ነው?»

«በጓላ እነግርሻለሁ፣» አለ ዊል።

«ሊን ወደሩሲያ ተመልሼ አልሄድም፣» አለ ሔልደር። «ምዕራቡ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ እጠይቃለሁ።»

ዊል የምክር ቤት አባልነት አድራሻውን ከኪሱ ፈልጎ አወጣ። «በዚህ ልታገኝኝ ትችላለህ፣ ልረዳህ እምችል ከሆነ አግኝኝ።»

ሔልደር ካርዱን ተመለከተ። «የገጠር ጠበቃው» እ? ያንተ ሽፋንም በጣም ግሩም ነበር። ማጆሮቭንም አሞኝተዝዋል።»

«አልዋሸሁትም፣» አለ ዊል። «ብቻ እውነቱን ሙሉ ለሙሉ አልነገርኩትም።»

«ልክ ለኔም ሙሉ እውነቱን እንዳልነገርከኝ ማለት ነው፣» አለ ሔልደር። ስለቦምቡ አልነገረኝም።»

«ቦምብ? የምን ቦምብ?» ጠየቀች ሩል።

«ከዚህ ብዙም ሳይርቅ በደሴቶቹ መሀል ቦምብ አለ የኒውክሊየር ፈንጂ።»

«ሚኒስትር!» በፊት ለፊቱ በር በኩል ተጣራች። «ወደዚህ ቢመጡ ይሻላል።»

ሚኒስትሩ መጡ። ሔልደር ቦምቡ የተቀመጠበትን ኑጥብ እና አንቴናን ስለሚዘረጋው የድምፅ ሞገድ ምልክት ሲነግራቸው ሩል ስታደምጥ ቆየች። «እትጪነቁ» አለ ሔልደር ለሰውየው። «አንቴናው ተለይቶ ካልተላቀቀ ሊፈነዳ ይችልም።»

ሚኒስትሩ ቤቱ ውስጥ ገብተው ተሰወሩ።

የጋዜጠኝነት መለያ የለጠፈ ሰው ወደሩል እና ሊ ተጠጋ። «እንተ ሮል ሊ አይደለህም?» ጠየቀው።

«ልክ ነህ፣» አለው ተገርሞ።

«እኔ የክሰስ ጋዜጣ የስካንዲኒቪያ ወኪል ነኝ። ፍሬድ አለን እባላለሁ። ዋሽንግተን ውስጥ ለሴናተር ካር ትሰራ የለም?»

«አዎ፣ አሁን ግን እረፍት ላይ ነኝ።»

«እረፍት?» ጋዜጠኛው እንባረቀ። «እዚህ ሁሉ መሀል ወስዶ የጨመረህ ምን አይነት እረፍት ነው?»

ሚኒስትሩ መጡ። «ይህ ወጣት የዚህ ሁሉ ታሪክ ጀግና ነው፣» አሉ። «እና. . . ሩል አይኖቻቸውን እያየች ራሷን ወዘወዘች።

http://ethzare.wordpress.com

«እሺ፣» አለ ጋዜጠኛው። «ስለዚህ ጉዳይ ባጠቃላይ መስማት እፈልጋለሁ።»

«አሁን እይሆንም፣» አለ ዊል። «ለምን በኋላ እንነጋገርም? እሺ?»

«ለሌላ ሰው አሳልፈህ እንደማትሰጥ ቃል ከገባህልኝ ብቻ። ነገሩን ከምንጩና ከመጀመሪያው ማግኘት እፈልጋለሁ።»

«ቃል እገባልሀለሁ፣» ወደሚኒስትሩ ፊቱን አዞረ። «ሚኒስትር ቄስትበርግ እንደሚገባኝ ከሆነ አየር ማረፊያዎቹና ወደቦቹ በሙሉ ተዘግተዋል። ዛሬ ምሽት ወደኒውዮርክ የምንሔድበት አይሮፕላን እንድናገኝ ሊረዱን የሚችሉ ይመስልዎታል? አንድ ሰዓት ገደማ የሚነሳ አይሮፕላን ያለ ይመስለኛል።»

«እንዲታ ሚስተር ሊ፣» መለሱ ሚኒስትሩ። «ነገሩን የሚያመቻችላችሁ ሰው ጋር ወደአየር ማረፊያው እንድትሔዱ አደርጋለሁ።» ሩልንና ሊን ከጋዜጠኛው ገንዘቡ ወሰዳቸው። «ሚስ ሩል፣» አሉ በለሆሳስ። «ስቶኮልም በሚገኘው ግራንድ ሆቴል ውስጥ ሩሲያ ስዊድንን ለመውረር ያወጣችውን እቅድ ይገርያለሁ የሚል ጣሊያናዊ በጨረታ ሊሸጠው ነው የሚል ሪፖርት ደርሶኛል። ስለዚህ ጉዳይ የምታውቂው ነገር አለ?»

59

ትሪና ራጉሊን የቲያትር አዳራሹን ዙሪያ ተመለከተች። አሁን ባዶ እየሆነ ነው። የመሀሉን ስክሪን ብርሀን በመጥፋቱ ቦታው ደብዝዟል። ተጨማሪ ሰዎች እየወጡ ሔዱ። አሁን በግዙፉ ክፍል ውስጥ ጆንስ፣ ማጆሮቭና ዘቡ ብቻ ቀርተዋል። ዘቡ ቴሌቭዥን ለማየት ፊቱን አዙሯል።

ሔልደር ስዊድናቹ ስለወሰዱት ከስክሪኑ ላይ ተሰውሯል። ከእሷም ተወስዶባታል፣ ስለዚህ ከማጆሮቭ ጋር ቀርታለች።

ማጆሮቭ ከጆንስ ጋር ብቻውን የቀረ ይመስል ፀጥታውን አደፍርሶ መናገር ጀመረ።

«የሚቀጥለው ሳምንት ይህን ግዜ የፖሊት ቢሮ አባል ሆኜ በተመረጥኩ ነበር፣» አለ ማጆሮቭ። «ሊቀመንበሩ ራሱ ነበር ቃል የገባልኝ።»

«አዝናለሁ ጌታዬ።»

«ውይ፣ አሁንም መሆኑ አይቀርም፣» አለ ማጆሮቭ። «ግን በሚቀጥለው ሳምንት አይሆንም። ነገ፣ ሞስኮ ሄጄ ፖሊት ቢሮው ፊት እቀርብና ስለተፈጠረው ነገር የቻልኩትን ያህል አሳምሬ እናገራለሁ። ስዊድኖች ስለዕቅዳችን እንዴት እንዳወቁ የሚመረምር ኃይል አሰማራለሁ፣ ይህ ለተወሰነ ጊዜ በሥራ ጠምዶኝ ይቆያል።»

«ቅጣት ይመጣብኛል. . . »

«ለውድቀት ቅጣት?» ማጆሮቭ አቋረጠው «በፍፁም አልሰጋም። ዋና ፀሐፊውና ሌሎች ሁለት አባላት የማውቀውን እነሱን የተመለከተ የጋራ መረጃ በመጠቀም ጥበቃቸውን አነኖለሁ። ወሳም ወሬደ፣ የስፔትናዝን ኃይላት ማንም ሌላ ሩሲያዊ ሊያደርገው ከሚችለው በላይ የከፍተኛ ብቃት ባለቤት አድርጌያቸዋለሁ። ይህ በተለይ በዚህ ስኬት ቀዳሚ ተጠቃሚ በሚሆነው በአድሚራል ጎርሽኮቭ ግምት ውስጥ ይገባልኛል። አይደረግም ጆንስ፣ ወደኔ የመያደላ ብዙ ነገር አለ። አሁንም የዋሽንግተኑ ፈሬት የኔ ነው፣ በግል ስመራው የነበርኩት እኔ ነኝ። ፈሬት ብቻውን ሲአይኤ ውስጥ ባለው ከፈተኛ ደረጃ የተነሳ የማንኛውንም ሰው የሥራ እድገት ደረጃ ለማስጠበቅ በቂ ነው። ተርፌ ሀብት በሀብት እሆናለሁ፣ አንተንም ይገደህ እሔዳለሁ፣ አትፍራ።»

«አትተርፍም፣» አሰኝ ራጉሊን፣ ከመቅፅበት የኑሉም አትኩሮት አረፈባት። ወታደሩ ሲጠጋት ወዲያውኑ ተኩላ መታችው። ይህ በቂ ሆነ። መሳሪያውን እንደያዘች ተጠጋች። ጆንስ ደርቆ ቀርቷል፣ ማጆሮቭ ከተቀመጠበት ተነስቶ ፊቱን ወደእሷ አዞረ።

«ራጉሊን፣» አለ ማጆሮቭ በለሆሳስ። «እሱን መሳሪያ አሁኑኑ ብታስተምጪ ምንም የሚለወጥ ነገር አይኖርም። የወታደሩን ነገር ለኔ ተይው፣ እኔ አስተካክለዋለሁ። እዚህ ያለሽን ቦታ ማንም አይነካብሽም።»

«አሁንም ያለኝን ቦታ የምፈልግ ይመስልሀል?» ራጉሊን ጠየቀች? በጥቂቱ ዞር ብላ ጆንስን መታችው። ወደኋለ ተገልብጦ ጠረጴዛ ላይ ወደቀ። «ቀሪ የወጣትነት ሕይወቴን እንደ እንስላ በጋጣህ ውስጥ ማላስፍ የምፈልግ ይመስልሀል? ለማንም እንግዳ መደሰቻ እየሆንኩ በትዕዛዝህ እየተደበደብኩና እየተገረፍኩ መኖር የምፈልግ ይመስልሀል?»

ማጆሮቭ አሁን አይኖቹን ላይዋ ላይ ተክሎ በጠረጴዛው ዙሪያ ቀስ እያለ መረመድ ጀምሯል። ራጉሊን ወደቲያትር አዳራሹ በሚወስደው ደረጃ ላይ የእግር ኮቴ ሰማች።

«አሁን እየመጡ ነው ትሪና፣» አለ ማጆሮቭ። «መሳሪያውን ካስቀመጥሽ እነ እከላከልልሻለሁ።»

«ከዚህ በፊት ያደረግከልኝ ጥበቃ አስደስቶኛል፣ ማጆሮቭ፣» አለች ራጉሊን። «ያንን ሁኔታ የመድገም ፍላጎት የለኝም። «ብላ መሳሪያውን ወደአውቶማቲክ ለውጣ ምላጩን ሳበችው።

የጥይቶች ፍንጥርጣሪዎች አካሉ ላይ ያለማቋረጥ ሲያርፉ ማጆሮቭ ወደኋላ እየተራመደ ተርገፈገፈ። ሁለተኛው ዙር እሩምታ ግን ከገደቡ ላይ ገልብጦት በደረጃዎቹ ላይ እየተገለባበጠ ቲያትሩ መድረክ ላይ ወስዶ አጋደመው። አካላቱ ተብሳስኮና በደም ተጨምቆ ምንጣፉ ለይ ተዘርግቷል። የትያትር አዳራሹ በር ተከፈተና ሁለት የደንብ ልብስ የለበሱ ወታደሮች ዘለው ገቡ። ትሪና ራጉሊን አፈሙዙን ወደራሷ አዙራ፣ የጋለውን ብረት ወደእቴ ካስገባች በኋላ ምላጩን ሳበችው። የጥይቶቹን ድምፅ እንኳን አልሰማችም።

60

ሩል፣ ሊን ከኋላዋ በቅርብ አስከትላ ግራድ ሆቴል ወደሚገኘው መኝታ ክፍል ገባች። የማረፊያ ክፍሉ ውስጥ ሰው ባይኖርም ብርጭቆዎችና የተተረከሱ ሲጋራዎች አዝረከርከውታል። ቁሳቁሱም ተመሰቃቅሰዋል።

«የክርስቶስ ያለህ፣» አለች «ይህ ቦታ እውሉ ኑፋሰ የመታው ይመስላል ሊሚሊዪ!» አለች በጩኸት።

«እዚህ ነኝ! እባካችሁ ግቡ!»

«እንተ ብትቀድም ይሻላል፣» አለችው ለሲ፣ ወደመታጠቢያ ክፍሉ በር እያመለከተችው።

http://ethzare.wordpress.com

ሲ ራሱን ወደውስጥ ብቅ አድርጎ ሳቀ::» ምንም ችግር ያለ አይመስለኝም፣» አለ::» ደሞስ ያን ያህል አይናፋር አይደለሽም::»

ሁለቱም ወደመታጠቢያ ክፍሉ ገቡ:: ኤሚሊዬ* አፒቼላ አረፋ በሞላበት ውሀ ውስጥ እስከጆሮው ድረስ ተነክሮ፣ በእፉ ትልቅ ሲጋራ ይሟል::

«ታዲያስ!» አለ ሲጋራውን እንደነከሰ:: «ተልዕኮሽ መሳካቱን ሰማሁ!»

«ኤሚሊዬ፣» አለች ሩል፣ «የሩሰያን የወረራ እቅድ ለጋዜጠኞች የመሸጥህን ነገር ሰማሁ የምሰማው ምንድን ነው?»

አንድ እጁን ከአረፋው ውስጥ ብቅ አድርጎ ፎጣ ላይ ጠረገውና፣ ከአፉ ላይ ሲጋራውን አነሳ:: «አሀ፣ አዎ፣» አለ ውብ ጥርሶቹን ብልጭ እያደረገ:: «ለተወሰነ ሰዎች ደወልኩና ጨረታ አዘጋጀሁ:: ከአንድ የአሜሪካ የቴሌግራ ድርጅት ሰላሳ ሺህ ዶላር አግኝቼያለሁ:: ካፒታሊዝም ደስ አይልም?»

ኤሚሊዬ፣ ያ መረጃ የCIA ምብረት ነበረ፣» አለች ሩል ጠጠር አድርጋ

«አሀ ምን?» አፒቼላ ደነፋ:: «ምን ያህል ከፍለውበታል?»

«መቼም፣» ሩል ደንገጥ አለች፣ «ከድርጅቱ ግን ቲፕ አልቀበልም:: ያም ሆነ ይህ አንቺን የሚያስቆጣ ምንም ነገር የለም:: ላንቺ ከዚያ የበለጠ ነገር አዘጋጅቼልሻለሁ::»

ሽንት ቤቱ ክዳን ላይ ተቀመጠች:: «እሺ ምን ዓይነት ነገር?»

አፒቼላ ሲጋራውን አሾለው:: «አልጋው ላይ አንድ ሻንጣ አለ::»

«እኔ አመጣዋለሁ፣» ብሎ ዊል፣ ርካሽ የፐላስቲክ ሻንጣ ይዞ መጣ::

ሩል ሻንጣውን ከፈተችው:: ውስጡ ሁለት ወፍራም የኮምፒተር ዲስክ መያዣዎች አሉ:: «ምንድን ነው?» ጠየቀች::

አፒቼላ ሲጋራውን ቢረጅሙ ከሳበ በኋላ፣ «የማሊቡን ኮምፒውተሮች እያደስኩ ላለሁ፣» አለ፣ «ራሴ የሰራሁትን በጣም የተሰየ የኤሌክትሪክ መስመሮች ሰሌዳ ገጥሜ ነር:: ለማጆሮቭ ኮምፒውተሮቹ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችላቸው የግንኙነት መስመር ነው ብዬ ነገርኩት:: ነገሩ ግን የሚሰራው ያንን ብቻ አልነበረም:: ስቶኮልም ውስጥ በሚገኝ ተመሳሳይ ኮምፒውተር ተጠ ቅሜ ማሊቡ ላይ የሚገኘውን የማሊቡን ኮምፒውተር በስልክ በማግኘት እዚህ ባለ ቁልፍ ላንቀሳቅሰው ቻልኩ:: ከዚህም በላይ፣ ኮምፒውተራቸው እዚህ ያለውን ኮምፒውተር እንደሌላ የኮምፒውተር ማከማቻ መረጃ እንዲያስበው ማድረግ ቻልኩኝ::» አፒቼላ ዳግመኛ ሲጋራውን ላቦና እንከን የሌለው የጢስ ቀለበት ሰራ:: «ከዚያ በቃ እሱ መረጃ ማከማቻ ላይ ያለውን ሁሉ ሮልፍ መረጃ ማከማቻ ላይ ቀዳሁት:: ካፒቺ?

«ካፒቾ፣» አለች ሩል ፊቷ እያበራ::

«እና ከእነዚያ ሽግቡ ታፋዎችሽ በላይ የተቀመጡት ዲስኮች ውስጥ የማሊቡ ኮምፒውተር ጠቅላላ መረጃ ይገኛል፣» አለ አፒቼላ በሲጋራው እየጠ ቆመ:: «በርግጥ ሁለት ቡድን ናቸው፣ ምንግዜም መጠባበቂያ ግልባጭ ያስፈልጋል::»

«ንገረኝ እስኪ፣» አለች ሩል፣ አይኖቿን እያጠበበች፣ «ማጆሮቭ ይህን ማድረግህን ያውቃል?»

«በፍፁም አያውቅም፣» አለ አፒቼላ:: «አሁን በዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ የሚጠቀሙበት መዋቅር ይኖረዋል:: እኔ በቃ ከእነዚያ ተጠቃሚዎች አንዱ

ነኝ፣ ስለዚህም ኮምፒውተሩ እስከሰራ ድረስ እየተጠቀምኩበት መቆየት እችላለሁ::»

«ይህ ስጦታ ነው እንዴ?» ጠየቀች ሩል እየተጠራጠረች::

«ከእኔ ለእንቺ የተሰጠ፣» አለ ግሊያናዊው በፈገግታ:: «CIA በማሊቡ ኮምፒውተር መጠቀምን መተጠል ከፈለገ ግን እጅግ በጣም ለልዩ ሰራዊ አንድ መቶ ሺህ ዶላር እፈልጋለሁ::»

«ይሀን ጥያቄ በእንተ ስም ለድርጅቱ ለማቅረብ ወደኋላ አልልም፣ ኤሚሊዬ:: ምንም ዓይነት ችግር ይኖራል ብዬ አልገምትም::»

«ጥሩ፣» አለ:: «ዙሪክ በሚገኘው የባንክ ሒሳብ ቁጥሬ ውስጥ ገንዘቡ ሲገባልኝ የኤሌክትሪክ መስመር ሰሌዳውን (Circiut Board) በመርከብ እልክላችኋለሁ፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥሩ እዚያ ፖስታ ላይ ተጽፎ ይገኛል:: ካሰ በኋላ ገፅታው ኮስተር አለ:: «ፖስታው ውስጥ ሌላ ስጦታ አዘጋጅቼልሻለሁ::»

ሩል ከፖስታው ውስጥ ብዙ ወረቀቶችን አወጣች:: «ይሄ ምንድን ነው?»

«ሩይሉቹን እየቀጸሁ ሳለ፣ ከመካከላቸው ጥቂቶቹ በምስጢር ቃል የተፃፉ መሆናቸውን አወቅሁ:: የምስጢር ኮዱን ያዘጋጀሁት ወደማጆሮቭ በፊት በሔድኩ ጊዜ ስለነበር ለመፍታታ አልተቸገርኩም:: የማጆሮ

ቭ የግል መዛግብት ነበሩ፣ ስዊድንና ዩናይትድ ስቴትስ ሚስጥራዊ አካላት ውስጥ የሚሰሩ ሁለት ግለሰቦች መኖራቸውን የሚጠቁም መረጃን ይዘዋል:: ስማቸው እልተጠቀሰም ነገር ግን ስዊድናዊው ሲል በሚባል፣ አሜሪካዊው ደግሞ ፈሬት በሚባል ስሞች ይታወቃሉ::»

«ሲል ያለጥርጥር ካልሰን የተባለው ሰው ነው፣» አለች ሩል ወረቀቶቹን እያገላበጠች::

«ፈሬትስ?» ጠየቃት ሲ . . .

ሩል ግላባሚን አቁማ ማንበብ ጀመረች:: «ይህ እንዴ እንደተመለመሉ የሚተነትን ጽሑፍ ነው፣» አለች፣ «ያለጥርጥር ማንኑቱን ግልፅ ያደርገዋል::» ገፆቹን በማንበብ ላይ ሳለች ከባድ ሀዘን ዋጣት::

«አዝናለሁ ኪት፣» አለ ሲ:: «እንዳላስደሰትሽ አውቄያለሁ::»

ሩል ተነስታ ቆመች:: «የማስብበት ጥቂት ደቂቃዎች ያስፈልጉኛል፣ ዊል::» ብላ ወደማረፊያ ክፍሉ ተመልሳ ትልቅ ወንበር ላይ ዘፍ አለች:: ግማሽ ሰዓት ሙሉ ስለችግሩ እያሰበች አማራጮችን ስትመዝን ቆየች:: በመጨረሻ ስልኩን አነሳችና እፐሬተሯ ዩናይትድ ስቴትስን የስልክ ኮድ እንድትሰጣት ጠየቀች:: ወደCIA ዋና መሳከል ደውላ ዳይሬክተሩን ለማግኘት እንደምትፈግ ተናገረች::

«የCIA ዳይሬክተር ቢሮ፣» የሚል የወንድ ድምፅ ሰማች::

«ካትሪን ሩል ነኝ፣» አለች፣ የሶቪየት ቢሮ ኃላፊ:: እባክዎን አሁኑኑ ከዳይሬክተሩ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ::»

ድምፁ ከመቅፅበት ቀዘቀዘ:: «በጊዜው ዳይሬክተሩ የሉም፣ ሚሲስ ሩል:: ጉዳዩ ስለምንድን ነው?»

«እባክዎን የምደውለው ከስቶኮልም መሆኑን ሳዳይሬክተሩ ይንገሩልኝ፣» አለች «ሊያናግሩኝ እንደሚፈልጉ አምናለሁ::»

http://ethzare.wordpress.com

«እንድ ጊዜ ይጠብቁ ሚሲስ ሩል።» አለ ሰውየው

ከጥቂት ሰኮንዶች ቆይታ በኋላ ሽካራ የወንድ ድምጽ ተሰማ፣«ስቶኮልም? ስቶኮልም ውስጥ ምን እያደረግሽ ነው ሚስ ሩል? ቴሌቭዥን አትመለከቺም፣ እዚያ ቦታ ላይ ምን እየተደረገ እንደሆነ ታውቂያለሽ?»

«የማናግረው ዳይሬክተሩን ነው?» ጠየቀች ሩል በጨዋ ደንብ።

«እልተሳሳትሽም፣ አሁን ስቶክሆልም ምን እያደረግሽ እንደሆነ በቶሎ ማወቅ እፈልጋለሁ። ደሞ ይህ መስመር ደህንነቱ የተጠበቀ ነው?»

«ደህንነት የለውም ግን በዚህ ውይይታችን ወቅት ሚስጥራዊ ስለሆኑ ጉዳዮች አይደለም የምንጫወተው። ስቶኮልም ውስጥ ምን እያደረግኩ እንደሆነ ነገ ጠዋት ኒውዮርክ ላይ እንግርህለሁ።» አለች ሩል።

«ነገ ጠዋት የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ስብሰባ አለብኝ፣ ኒውዮርክ ውስጥ የመገኘት ምንም አይነት አላማ የለኝም።»

«በጣም በጥንቃቄ አድምጠኝ፣» አለች ሩል። «ይህ እጅግ አሳሳቢ ነገር ነው። ሳይመን ሩልስ፣ አለን ኒክሰን፣ ኤድዋውልስንና አንተን ነገ ጠዋት አሰራ ሁለት ሰዓት ላይ የስካንዲኒቪያ አየር መንገዶች መዋቅር አንደኛ ደረጃ የእንግዶች ማረፊያ ውስጥ እንዳገኛችሁ።»

«ስለምንድን ነው የምታወሪው ሴትዮ?»

«በዚህ መልኩ ሳስቀምጠው፣ በዚያ የመጀመሪያ ደረጃ እንግዶች ማረፊያ ቁጥሩ የበዛ የጋዜጠኞች እጀብ ይኖራል። እዚያ የማላገኛችሁ ከሆነ ከነሱ ጋር እንጋገራለሁ። እመነኝ ይህንን ጋዜጦች ላይ ልታነበው በፍፁም አትፈልግም።»

ረጅም ፀጥታ ተተካ። «ምን እያደረግሽ እንደሆነ ታውቂያለሽ ሚስ ሩል?» ጠየቁ ዳይሬክተሩ። «የሥራሽ ሁኔታ በምን ዓይነት አስጊ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ ታውቂያለሽ? ወደላንግሊ ተመልሰሽ ስተመጪ ምን እንደሚጠብቅሽስ?»

«እንተና ያልሷቸው ሰዎች ነገ ጠዋት አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ኒውዮርክ የማትመጡ ከሆነ ወደላንግሊ አልመለስም። ካልተገኛችሁ የሚቀጥሉትን ወራት በአብዛኛው ጊዜዬን የማሳልፈው ቴሌቭዥን ላይ ይሆናል። ተግባባን?»

ሌላ ረጅም ፀጥታ። «መልካም ሚሲስ ሩል፣ እንመጣለን።»

«እንድ ሌላ ነገር አለ፣» አለች ሩል፣ «የተቀሩት ሌሎቹ ስለቀጠሮአችን እስክንገመዋት ድረስ ማወቅ የለባቸውም። በየቤታቸው ደሙለሀ ሔሊኮፕተር የሚሳፈሩበት ጊዜ ብቻ ስጣቸው።»

«ሌላ ነገር አለ?»

«እም፣ ሁለት የFBI ወኪሎች እንዲኖሩ እፈልጋለሁ። ከእናተ ጋር በሔሊኮፍተሩ መምጣት የለባቸውም፣ ሌሎችም እነዚህ ሰዎች እንደሚመጡ ማወቅ የለባቸውም። ማወቅ ያለብህ ነገር ቢኖር እኔን ለመያዘ ወይንም ለማፈን ማንኛውም ዓይነት ሙከራ ከተደረገ፣ ዜና ማሰራጫዎች ስለያዝኩት ዜና ሙሉ መረጃን እንዲያገኙ ቅድመ ዝግጅት ማድረጌን ነው።»

«መልካም፣ ምን ዓይነት ጣጣ ነው!»

«እንድ ሌላ ነገር ይቀራል፣» አለች ሩል። «ሳይመን ልጇን ወደስብሰባው ይዞት እንዲመጣ ንገረው። ፒተር ከሌለ እንነጋገርም፣ ገባህ?»

«ገባኝ፣» አሉ ዳይሬክተሩ፣ በተሸነፈ ስሜት።

ማጅራቷን በእጆቿ እሻሸችው። ገላዋን ታተባ ትንሽ እንቅልፍ የማታገኝ ከሆነ ጠዋት ይህን ነገር ማሳካት እይቻላትም። ማሳካት ደሞ ይኖርባታል።

61

ኒውዮርክ ላይ ባረፈች ጊዜ አስገራሚ ንቃትና ተህድሶ ሞልቶባታል። በግዙፉ እንደኖ ደረጃ ለመኝታም የሚያገለግል መቀመጫ ላይ በሁለት ቀናት ውስጥ የመጀመሪያ እውነተኛ እረፍቷን አግኝታለች። አጠገቧ ወዳለው ሊ ፊቷ አዞረች።

«እሺ እሁን ሁሉን ነገር አስተካክለነዋል?»

«ምን ጥያቄ አለው።»

የኮምፒውተር ዲስኮችንና የማጆሮቭን ፋይሎች የያዙ ወረቀቶች ግልባጭ ሰጠችው። «እስክንወጣ ድረስ ከማረፊያ ቤቱ ውጭ ቆየን። የጠረሀቸው የጋዜጣ ሰዎች ቢጠብቁን ጥሩ ነው።»

«ይመጣሉ፣ ሶስቱም ማለትም የኒውዮርክ አለታዊ ጋዜጦች፣ የዋሽንግተን ፖስት፣ ታይምና ኒውስዊክ እንዲሁም፣ የሬዲዮና ሶስቱም የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ይገኛሉ። ሴናተር ካር ስማቸውን እንድጠቀም ፈቅደውልኛል።»

«እሺ ከዚህ ስብሰባ ላይ ተይገር ከተወሰድኩ አንተ አነጋገራቸውና የማጆሮቭን መዛግብት ለሁሉም አዳርስ። አሁን ሰለጉዳዩ ከኔ ያልተናነሰ እውቀት አለህ። ስለዚህ ነገሩን ለሌሎች ታሳውቃለህ ብዬ እምንቴን የጣልኩት አንተ ላይ ነው። ማለቴ ከስብሰባው የምወጣው እንገቴ ተቆርጦ ከሆነ።»

«አንገትሽ አሁን ባለበት ቢሆን ደስ ይለኛል፣ እንዳትሰጪያቸው።»

* * *

የአብራሪው ድምፅ ከየማጉያዎቹ ተሰማ። «ሚሲስ ሩል የተባሉ ግለሰብ ለበረራ አስተናባሪዋ ራሳቸውን እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን?»

ሩል ለአንድ አስተናባሪ እጇን ሰታውለበልብ፣ ወደሷ መጣች።

«ሚሲስ ሩል ነሽ? አይሮፕላኑ በር ላይ ሰው ይጠብቅሻል የሚል መልዕክት ስለደረሰን ከአይሮፕላኑ መጀመሪያ እንድትወርጂ እንፈልጋለን፣ እባክሽን።»

«ጥሩ፣» በማለት ሩል መለሰች፣ ከተቀመጠችበት እየተነሳች። ዊልን ጠቀሰችው። «ለትንሽ ጊዜ የማታቀኝ መስለህ ብትታይ ጥሩ ነው።»

ስቦ አስቀምጧት ሳማት። «ዛሬ ማታ ራት እጋብዝሻለሁ?»

እሷም ሳመችው። «ዛሬ ምሽት ነፃ ሴት እሆናለሁ፣ እኔ ነኝ የምጋብዝህ። ውለታህ አለብኝ አስታወስክ?» ፈገግ አለ። «ማይሰን ብላቼ ቀድሜ ቦታ እይዛለሁ። ጥቁር ከረባት ላድርግ?»

«ወደህ ነው።» ፊቷን አዙራ አስተናጓጇን በመከተል፣ ከአይሮፕላኑ እንቅስቃሴ ጋር ሚዛኗን እያስተካከለች ሔደች። በሩ ተከፈተና ሙሉ ሰማያዊ ሱፍ የለበሰ ግለሰብ ገባ።

«ሚሲስ ሩል ነሽ?» ጠየቃት መታወቂያውን እያሳያት። «እኔ ልዩ ወኪል ማዲሰን የFBI አባል ነኝ። እባሽን ተከተይኝ።»

http://ethzare.wordpress.com

ወኪሉ ፍተሻውን አሳልፋት ወደእንደኛ ደረጃ እንግዶች ማረፊያ ክፍል መሰዳት። በሩን አልፋ ስትገባ እንድ ትንሽ ልጅ ተጠመጠመባት።

«እማዬ፣ እማዬ!» አለ ፒተር፣ በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ ሳቅ አሰሙ።

«ስላገኘሁሽ ደስ ብሎኛል። የት ነበርሽ?»

ሩል ልጇን አጥብቃ አቅፋው ስታበቃ ልትመለከተው ወደኋላ መለስ አደረገችው። «ሁሉንም በኋላ እነግርሀለሁ፣» አለችው። «እስከዚያው ድረስ አንድ ነገር እምተቼልህለሁ።» ከሻንጣዋ እንድ የተጠቀለለ ነገር አወጣች።

ልጁ መጠቅለያውን ፈታው። «ካሜራ!» ጮኸ፣ «እንዴት እንደፈለግኩ አወቅሽ?»

«ግምቴ ተሳክቶልኝ ነው፣» አለችው። «ለማ ፒተር፣ ለትንሽ ጊዜ ያህል እዚያ ጋር እንድትቀመጥ እፈልጋለሁ። እኔ ስብሰባውን እስክጨርስ አንተ የካሜራውን መመሪያ አንብብ፣ ከዚያ አብረን እንሔዳለን እሺ?»

«ስሚ» አለ ከፍ ባለ ድምፅ እያንሾካሾከ። «እባዬ በእንድ ነገር በጣም ተናዷል። በሊቢት መነሳቱን የወደደው አይመስለኝም ደሞ ፍርሀት ገብቶታል። ይህን ያህል ተጨንቆ አይቼው አላውቅም።»

«ስለነገርከኝ አመሰግናለሁ የኔ ፍቅር አሁን ሔደህ ተቀመጥ እሺ? እዚያ ጋ ጣፋጭ ምግቦችና የብርቱካን ጭማቂ የሚታዮኝ ይመስለኛል።»

ልጁ ካሜራውን ይዞ ተፈተለከ።

ወኪል ማዲሰን ወደተዘጋ በር አመለከታት። «የስብሰባ ክፍሉ ያውና፣» አለ።

«ተጠርጓል?» ጠየቀች።

ሰለሁሉም ነገር አስበንበታል፣» አለ በፈገግታ።

«አንተና ጓደኛህ እንዳትገቡ እፈልጋለሁ፣ እባካችሁ። በቁጥር ስር የሚውል ሰው አለ። ማስረጃውን ታዳምጣላችሁ።»

ማዲሰን በማረፊያ ክፍሉ ለተቀመጠ ሌላ ሰው ምልክት ሰጠ። «እሱ ልዩ ወኪል ዋርድ ይባላል። ዋርድ ወደሰብሰባው እንገባለን። በቁጥር ስር የሚውል ግለሰብ አለ።»

«ታጥቃችኋል?» ጠየቀች ሩል።

«አዎን፣ የኔእመቤት፣» መለሰ ማዲሰን።

«ጥሩ፣» አለች። «እንሒድ፣» በሩን ከፍታ ወደክፍሉ ገባች፣ ሁለቱ ወኪሎች ተከተሏት። ዳይሬክተሩ ከእነሰተኛ የስብሰባ ጠረጴዛ ተቃራኒ ጫፍ ተቀምጠዋል፣ አለን ኒክሰን በስተቀኛቸው፣ ኤድ ራውልስ በስተግራቸው ተቀምጠዋል። ሳይመን ከዳይሬክተሩ በስተጀርባ በአንድ ጎን ቆሟል። ሩል በጠረጴዛው አንድ ጫፍ ተቀመጠች። የFBI ወኪላቱ ከበስተጓላዋ ቆሙ።

«መልካም ሚሲስ ሩል፣ እንወቀው፣» አሉ ዳይሬክተሩ።

«እንደምን አደራችሁ ክቡራን፣» አለች ሩል። «እኔን ለማግኘት ግሬሳችሁ ስለተነሳችሁ አመሰግናለሁ።»

«የመረጥነው ነገር አልነበረም ሩል፣» አለ ኒክሰን። «አሁን ነገሩን እንሰማ።

ሩል ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠችውን የፕላስቲክ ሻንጣ ከፈተች። «ክቡራን እስካሁን ድረስ ትናንትና ሶቪየት ህብረት ስዊድን ላይ ወረራ ለማድረግ መሞከሯን አውቃችኋል።»

ሳይመን፣ «ብዙ ዓይነት ሪፖርቶች እየደረሱን ነው። ገና እንድ ሳይ አላቀናበርናቸውም።» አለ።

ሩል እንዳልሰማች ሆና አለፈችው። «ወረራው የታቀደው የተነጣጠረው ሳይጋኛ ከሚገኘው ማሊቡ የተባለ የሶቪየት ጦር ሰፈር ሲሆን፣ አቀናባሪውም በእንድ ወቅት የKGB የውጭ ጉዳይ ተልዕኮዎች ኃላፊ በነበረው ማጆሮቭ በተባለ ሰው ነው።»

«እዎ፣ እዎ፣ ሩል ስለመላምትሽ በሙሉ ጠንቅቀን እናውቃለን፣» አለ ኒክሰን።

«መላምት መሆኑ ቀርቷል አለን፣» አለች፣ ከሻንጣዋ ከምር የኮምፒውተር ዲስኮችን እያወጣች። «በማሊቡው ኮምፒውተር ላይ ያሉት መረጃዎች ሁሉ እነዚህ ላይ ይገኛሉ፣ የወረራውን እቅድ ጨምሮ። በጥንቃቄ ከተመረመሩ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ መሆኑ ያሳየናል።»

«እንዴት አገኘሽው?» ጠየቀ ሳይመን።

«እሱን በኋላ ሳይመን፣» አለች ሩል። «አሁን ግን እነዚህ ቅጂዎች የማጆሮቭን የግል ፋይሎችም ጨምረው መያዛቸውንና ብዙ ነገሮችን ግልፅ እንደሚያደርጉም ለመናገር እወዳለሁ።»

ሳይመን ወደፊት ጠጋ አለ። «ኬት፣ ይህ ጊዜውም ስፍራውም አይደለም።»

«በተቃራኒው ሳይመን፣» መለሰች፣ «ጊዜውም ቦታውም ይህ ነው። አሁን እስክጨርስ ድረስ አፍህን ዝጋ።» ንዴቷን ለመቆጣጠር በጣም እየጣረች ነው።

«ቀጥይ ሚሲስ ሩል፣» አሉ ዳይሬክተሩ።

እነዚህ የማጆሮቭ የግል ፋይሎች፣» ቀጠለች፣ «ስዊድንን ለመውረር ያቀናበረው ዕቅድ ስዊድን መከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ በሚገኝ ሰላይ ድጋፍን እያገኘ መሆኑን ይገልፃሉ። ይህ ሰላይ ሲል ይባላል። ትክክልኛ ስሙ ስቬን ካርልሰን ነው። ትናንት በቁጥጥር ስር እስከዋለበት ጊዜ ድረስ በሚኒስቴሩ ውስጥ የቻንሰሪው ኃላፊ ሆኖ አገልግሏል። ከዚያን ግዜ ጀምሮ ወሬ ሲያቀብል መኖሩን ተነግሮኛል።»

ሩል ከበደቷን ከአንድ ጎን ወደሌላ አስተካከለች። የማንነቷ እንድ አካል እየወተወታት ቢሆንም ከዚህ ቀጥሎ የምትናገረውን ራሷም ፈርታዋለች። «ፋየሎቹ ከዚህ ሌላ ማጆሮቭ በCIA ውስጥ ጭምርም ሰላይ እንዳለው ይናገራሉ፣» አለችና ዝም አለች፣ አድማጮቿ ሀውልት ሆነዋል። «ፈራት ይባላል፣ ትክክለኛ ስሙ አልተጠቀሰም። መዛግብቱ ግን ስለ ኋላ ታሪኩ የተወሰነ ነገር ይናገራሉ። በአስራዘጠኝ ሰባ እና በሰባ አንድ ስቶኮልም ውስጥ የመስክ ሰላይ በነበረበት ጊዜ ከማጆሮቭ ጋር ተገናኘ፣ በጊዜው ማጆሮቭ፣ ፊርሶቭ በሚል መጠሪያ በሶቪየት ኤምባሲ ውስጥ የጣቢያ ኃላፊ ሆኖ ያገለግል ነበር። እዚያም ገና በማላቀው ሁኔታ በማጆሮቭ እማካይነት ተመለመለ። የሰውየውን ማንነትና ድርጅቱ ውስጥ ያለውን ታሪክ ግምት ውስጥ ስናስገባ ፣ ለመገንዘብና ለመገመት አስቸጋሪ ነው። «ቢጥቂቱ ወደ ኤድ ራውልስ ዞር ብላ፣ «ምን ነበር ኤድ፣ ሴት ነበረች? ሚስጥርን የማውጣት ማስፈራሪያ?»

ከፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ ወደራውልስ ዞሩ። ራውልስ ፊቱ ቢገረጣም ምንም አልተናገረም።

http://ethzare.wordpress.com

«ለመቀጠል፣» አለች፣ «ራውልስ ከዚህ ሴላ እንደሚለው ከሆነ ስቶኮልም ውስጥ ማላከሆቭን አግኝቶታ፣ ለጥቂት ጊዜ። ግን ከሁለት ዓመታት በፊት ማላከሆቭ ድንገት ኒውዮርክ ሊገኝ በወሰነበት ጊዜ እንዲመራውና እንዲቆጣጠረው የመረጠው ማንን ነበር? በርግጥ ኤድራውልስ ነዋ። በወቅቱ ኤድ ከማጆሮቭ በሚያገኘው መረጃ አማካይነት ከዚያ በፊት አስር ወርቃማ የሥራ ጊዜያትን አሳልፏል። ሁሉም ግን የከሀገር ውጭ ስራ ነበር፣ እናማ ማጆሮቭ ላንግሊ ላይ ጆሮ ጠቢ እንዲኖረው ፈለገ ስለዚህ ማላከሆቭን ላክ በማን አማካይነት፣ በኤድ ራውልስ።»

ሳይመን ተቀምጦ ራሱን ሁለት እጆቹ ውስጥ ቀብሯቸዋል።

ሩል በረጅሙ አየር ስባ ቀጠለች። «ከዚያም ኤድ፣ በድንቅ ስራውና ከማላከሆቭ ጋር በፈፀመው አመርቂ ርምጃ የተነሳ የተልዕኮዎች ክፍል ምክትል ዳይሬክተር በመሆን ተሾመና፣ የድርጅቱን ፋየሎች ለማጆሮቭ እንደልቡ የሚልክበትን ቦታ አገኘ። ከዚያ ሁለት ግኝቶች ላይ ደረሰ። መጀመሪያ፣ ሰንፍላወር የተሰኘና፣ ሶቪየቶች፣ ስዊድን ከኬቶ ጋር ልትዋሀድ መሆኑን የሚናገር የተሳሳተ መረጃን የመስጠት ተልዕኮ። ይህ ተልዕኮ ለማጆሮቭ የወረራ እቅዱን የሚመሠርትበትን የመጀመሪያ ሀይል የሰጠው በመሆኑ ስኬታማ ነበር። ሁለተኛ፣ እኔ ማጆሮቨን እየተከታተልኩ መሆኑን ደረሰበት፣ ማንም እንዳላመነኝም አወቀ። ይህን ጊዜ ብልጥ ሆነ።»

«ይህን ሁሉ እየገመትሽ ነው እንዴ ሩል?» ሲሉ ዳይሬክተሩ ድንገት ጠየቋት። «ወይንስ ይህም ከመላምቶችሽ እንዱ ነው?» ሲሉ ድንገት ጠየቋት።

ድንገት ኤድ ራውልስ ቱግ አለ። «እፍህን ዝጋና አዳምጥ፣ እንተ ትልቅ ፈዛዛ፣» አለ ለዳይሬክተሩ፣ «ከፍተኛ ብቃት ያላት ባለሞያ ነች የምትናገረው። እንድ ነገር ልታስተምርህ ትችል ይሆናል።»

«አመሰግናለሁ ኤድ፣» አለች ሩል። «ራውልስ ስለማጆሮቭ የወረራ እቅዶች ስለሚያውቅ ሰንፍላወር ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ ቦምብ መሆኑ ይገባዋል፣ እናም ሳይመን እንተ ቢሮ ውስጥ ባደረግነው ስብሰባ ላይ ስለመላምቶቼና ሀሳቦቼ በሰማ ጊዜ ማክሸፈያውን እንዳገኘ አወቀ። ከጀርባዬ ያለጥርጥር ስለእኔ መጥፎ እያወራላችሁ እኔን ግን መደገፍ ጀመረ። ማላከሆቭን አግኝቶኝ አስደሰተኝ። በቢሮ ውስጥ ለውስጥ ፖስት ውስጥ የማጆሮቭን የሹመት እደገት የሚጠቅስ የቆየ ወታደራዊ ጋዜጣ ላከልኝ። እውነት ለመናገር ትልቅ እገዛ አደረገልኝ። ርግጥ ነው፣ እንዳይላካልኝ አድርጎ ነበር ያቀደው፣ ግን የስዊድንን ወረራ ከተሳካ በኋላ ጋዜጦች ስለሰንፍላወርና እኔ ስዊድኖችን የሚያስጠነቀቅ አንድ ሰው ፍሰጋ ስላደረግኩት ከፍተኛ ጥረት ማሳወቁ አይቀርም። ድርጅቱ በሁለቱም መንገድ ቢሆን አጣብቂኝ ውስጥ መግባቱ አይቀርም፣ ምክንያቱም ድርጅቱ ሶቪየቶች ራሳቸውን የባልቲክ አዋሳኝ ለመጠበቅ ርምጃን እንዲወስዱ ምክንያት ሆኗቸዋል፣ ከዚህም ሴላ ድርጅቱ ስዊድኖች የሚመጣባቸውን ለማስጠንቀቅ ሳይቻለው ቀርቷል።»

አሁን ዳይሬክተሩ ፊታቸው ገረጣ። አለን ኒክሰን ቢጠረጴዛው ላይ ካለው ጠርሙስ ውሀ እንዲቀዳላቸው ምልክት አሳዩት።

«እና፣» ቀጠለች፣ «ወረራው ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ መብጠልጠል ከጋዜጠኞች በድርጅቱ ላይ ይዘንብ ነበር። ሳይመን የሰንፍላወርን ሀሳብ አልሞ በመጠንሰሱ የተነሳ ከሥራው ይለናበታል፣

ታዲያ ማን ይተካዋል? ያለጥርጥር ሰንፍላወር በተጠነሰሰበት ጊዜ ምስራቅ አውሮፓ ውስጥ የነበረውና ከደሙም ንፁህ የሆነው ኤድ ራውልስ ማለትም ምክትሉ ይተካዋል። ከዚያ ደግሞ ሚስተር ዳይሬክተር የፕሬዚዳንቱ የስልጣን ጊዜ እስኪፈፀም ድረስ ቦታህ ላይ ትቆያለህ ብለን ብንገምት እንኳን - ይህ እጠ ራጣሪ ነው - አዲስ ፕሬዚዳን መሾሙ አይቀሬ ይሆናል። ከፖለቲካ ብቃትህ አኳያ ያንተ መሾም በሴላ በሞያው በተካነ ግለሰብ ይተካል። ስለዚህ ለCIA ዳይሬክተርነት ማን ይታጫል። ማላከሆቭን ከሶቪየቶች ያስከዳው ጀግና ኤድ ራውልስ። ሩል ዝም አለችና የምትጠጣው ውሀ ቀዳች። «አሁን ሁላችንም ይህን ሁኔታ ተረድተናል?»

ሁሉም ከኤድራውልስ በስተቀር ጠረጴዛውን ትክ ብለው ይመለከታሉ። እሱ ግን የFBI ወኪላቱን እየተመለከተ ነበር።

ሩል ወደጓላዋ ዞር አለች። «መልካም፣ ወኪል ማዲሰን።» አለች። «አሁን ሚስተር ራውልስን በቁጥጥር ስር ማድረግ ትችላለህ።» የማጆሮቭን ዶሴዎች ፎቶ ኮፒ ከሻንጣዋ አውጥታ ጠረጴዛው ላይ አኖረችው። «እዚህ ውስጥ ከሱን የሚደግፉ መረጃዎችን በሙሉ ታገኛላችሁ። በጓላ ላይ ቃሌን አሰጣችኋለሁ። የማምለጫ ጊዜ ላያገኝ ማላከሆቭንም በፍጥነት በቁጥጥር ስር ማዋል ይኖርባችኋል። ኤድ፣ የማላከሆቭን አዲስ አድራሻ ትሰጣቸዋለህ አይደለም?»

ራውልስ በእምንታ ራሱን ወዘወዘ። መናገር የሚችል አይመስልም።

«ሚስተር ራውልስ?» አለ ማዲሰን።

ኤድ ራውልስ በዝግታ ተነስቶ ቆመ። ማዲሰንና ዋርድ ግድግዳውን አስደግፈውት ይፈትሹት ጀመረ።

«መርፌ ወይንም ክኒን ፈልገህት፣ በሕይወት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ እፈልጋለሁ።»

ወኪሎቹ ለተጨማሪ ሶስት ደቂቃ ሲፈትሹት ቆዩ። «ምንም የለበትም፣» አለ ማዲሰን፣ የራውልስን እጆች ወደጓላ አዙሮ ካቴና እያጠ ለቀላቸው። «እንሒድ ሚስተር ራውልስ።»

ከክፍሉ መውጣት ሲጀምሩ ራውል ሩል የተቀመጠችበት ቦታ ደርሶ ቆመ።

«ኬት፣» አለ፣ «ስቶኮልም አየር ማረፊያ ላይ ስለተፈጠረው የማውቀው ነገር የለም። እዝናለሁ፣ እውነቴን ነው።»

ሩል ተነስታ በመቆም፣ ወደጓላ ዘመም አለችና በመጻፏ የቻለችውን ያህል መታችው። ራውልስ ወፍራም ቢሆንም፣ ወኪል ዋድ ላይ ተንሳፎ ተለጠፈ።

«አሁን ከዚህ አስወጡት፣» አለች ሩል፣ በንዴት ድምጿ እየተርገበገበ። ሌሎቹም ከተቀመጡበት ተነሱ። «ተቀመጡ ሁላችሁም፣» ስትል ሮዝችባቸው።

«ገና አልጨረስኩም፣» በየመቀመጫቸው ተመለሱ።

«አሁን ከቡራን፣ ከዚህ ጉዳይ ምን ያህሉ ለህዝብ ይውጣ የሚለው ቀረን።»

«ካትሪን፣» ሳይመን እቅረጣት፣ «ይህ ለህዝብ ይውጣ የሚለው ሀሳብ የምር ሊሆን አይችልም።»

http://ethzare.wordpress.com

«ለመሆኑ ርግጠኛ ሁኑ፣» አለች ሩል። «አሁን የምንወያየው ምን ያህሉ ይውጣ የሚለውን ብቻ ይሆናል። የኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው። ሚስተር ዳይሬክተር፣ ከዚህ ክፍል ስንወጣ፣ ውጪ ለተሰበሰበው የጋዜጠኞች ቡድን አጭር መግለጫ ትሰጣለህ። ይኸውም በCIA ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ላይ የሚገኝ ባለስልጣን በቁጥጥር ስር መዋሉንና ለሶቪት ሀብረት በመሰላሉ ተከሶ ችሎት እንደሚቀርብ የሚገልፅ ይሆናል። የመገናኛ ብዙሀን ሰፊ ሽፋን መስጠ ታቸውና የኮንግረሱ መርማሪ አካልም ከቦ ምርመራ እንደሚያደርግበት የታወቀ ይሆናል፣ ዳሩ ግን ድርጅቱ ይህን የጎደፈ ስሙን ማንሰራራት አያቅተውም። ድርጅቱ መቀበል የማይችለው የእናተን የሶስታችሁን ክቡራን በሥራ ላይ መቆየት ይሆናል።»

«ምን?» ሲል አሰን ኒክሰን የመጮህ ያህል ጠየቃት። «እንድንለቅ ትጠ ብቂያለሽ?»

«ከመሀከላችሁ እንዳችሁም ሥራ ላይ ልትቆዩ የመቻላችሁ ዕድል አይታይም፣ አለን። እንድትለቁ ብቻ አይደለም የምጠብቅባችሁ፣» አለች ጣቷን እየጠቆመችበት። «ያለኮንግረሱ ፈቃድ ሰምንት ተኩል ሚሊዮን ሰዊድናውያን በሩሲያ ወረራ ስር እንዲወድቁና፣ ሌሎች የCIA በሺህ የሚቆጠሩ ሰራተኞችም አደጋ ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርግን ተልዕኮ ጠንሰሰህል፣ ከዜኔዲክት አርኖልድ ቀጥሎ በድርጅቱ ውስጥ አሰ የተባለን ከሠዲ በምክትልነት መርጠህ ተንቀሳቅሰህል። ይህ ከኮንግረሱም ሆነ ከመገናኛ ብዙሀን ወቀሳ አያመልጥም።»

ወደኒክሰን ጠቆመች። «አንተ አለን ደግሞ ከተልዕኮዎች ዳይሬክተር ምክትል ጋር ተመሳጥረህ የሰንፍላወርን ህልውና ለመሸሸግ ሞክረሀል፣ ያደረግኩትን የሶቪየትን እቅድ የማጋለጥ ጥረት አግደሀል፣ ያውም ከስራዬ እንደምዘዋወር ወይንም ለውስጥ ውስጥ ምርመራ እካሱ አሳልፈህ እንደምትሰጠኝ በመዛትም ጭምር። ኮንግረሱ ምርመራ ካደረገብህ በኋላ ከሳይመን የተለየ ዕጣ አይገጥምህም።»

ወደዳይሬክተሩ ጣቷን ቀሰረች። «አንተ ጌታዬ፣ የሰንፍላወርን ተልዕኮ ፈቅደህል አበረታተህል፣ ከተሾምክበት ቀን እንስቶም የሰው በሰው ስለላ ህይል እንዳይኖር አፍንሽው ቆይተህል በዚያ ፈንታ ከፍተኛ ቴክኖሎጂን መርጠህል። ለምትመራው የአሜሪካ የስለላ ህይል ከባድ አደጋ ነህ። ከዚህ ሁሉ ድርጊቶችህ መህል እንዱ ወዳጅህ ፕሬዚዳንቱ ጆሮ ከደረሰ፣ ከስራህ ያባርሩህል።»

ሩል መናገር አቆመች። ሲሳም መናገር የሚፈልግ ሰው ያለ አይመስልም። የዳይሬክተሩ ፊት አመድ የተነካበት ይመስላል። ሩል ይታመማሉ ብላ አሰባ ነበር፣ ግን መናገር ጀመሩ።

«ከሥራችን በፈቃዳችን እንድንለቅ እንጂ ከኛ ሌላ ምንም አትቀበይም፣ ሚሲ ሰሩል?» ሲሉ ሲጠይቋት፣ ድምፃቸው ባዘለው የተማፅኖ ቃና ተነካች።

«የሁላችሁም ስም እንዲጎድፍ አልፈልግም፣» አለች ሩል። «ጠ ረታችሁንም እንድታጡ አልፈልግም። በስሳሳ ቀናት ውስጥ የፌስጋችሁትን ምክንያት አቅርባችሁ ሥራችሁን ካለቀቃችሁ ይህ ሁሉ ለመገናኛ ብዙሀን ይደርሳል። በማንኛውም ምክንያት የተነሳ ይህንን ራሴ ለማድረግ ባልችልም፣ ጉዳዩ ለህዝብ የሚደርስበትን አስፈሳጊ ቅድመ ዝግጅት ሁሉ ማድረጌን ስነግራችሁ እንደምታምኑኝ ተስፋ እያደረግኩ ነው።»

«አምንሻለሁ ካትሪን፣» አለ ሳይመን በለሆሳስ።

«ከጋዜጠኞች ጋር ከመገናኘታችሁ በፊት፣ ምላሻችሁን አሁኑኑ መስማት እሻለሁ።» አለች።

አንድ በአንድ ሦስቱም እሺታቸውን በራሳቸው ንቅናቄ ገለፁላት። «መልካም ሚስ ሩል፣» ዳይሬክተሩ። «ድል አድርገሻል። ቃል እገባልሻለሁ። በአንድ ወር ውስጥ ስራዬን እለቃለሁ።»

«እኔም እንደዚያው፣» አለ ኒክሰን።

«መልካም ካትሪን፣» ሳይመን በረጅሙ ተነፈሰ። «ግን እንቺስ? እውነት ከሥራሽ የቀረሽ ጥቅም አለ ብለሽ መቼም አታምኚም፣ ታምኛለሽ? ከጋዜጠ ኞች በስተቀር ጠቋሚን የሚወድ ማንም የለም። በድርጅቱ ውስጥ ያለ ማንም ቢሆን ካሁን በኋላ በአንቺ ላይ እምነት አይኖረውም።»

«ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፣ ሳይመን» መለሰች። «ውጣም ወረደ፣ ሶስታችሁም መልቀቃችሁን ካየሁ በኋላ እኔም በፈቃዴ ስራዬን መልቀቁ እይቀርም።»

ዳይሬክተሩ ተነስተው ቆሙ። «ሌላ ነገር ከሌለሽ ይህን ጉዳይ ዳር እናድርስ።»

«ሌላ ነገር የለኝም፣» አለች ሩል። «ጋዜጠኞቹን በእግሳቡ እንድታስተናግዳቸው ከነሱ ጋር እተውሀለሁ።»

ሶስቱ ሰዎች እስኪቀድሟት ጠበቀችና ወደእንግዳ ማረፊያው አመራች።

«ና ፒተር፣» ጠራችው ልጇን። «ዊል ጋ እንሒድ።»

«ዊልም እዚህ ነው? እንዴት ደስ ይላል!»

«እም፣ ከዚያ ወደቤት የምትወስደንን መንኮራኩር እንሳፈራለን።»

«ግን የሔሊኮፍፐተሯን ያህል የሚያስደስት አይሆንም፣» አለ ፒተር።

ወደ ዋሽንግተን በሚወስዳቸው መንኮራኩር እየተጓዙ ሳለ፣ ፒተርን ታቅፋ ላይ አስተኝታ፣ ሩል ስለስብሰባው ለዊል አጫወተችው።

«ታውቃለህ፣» አለች፣ «እንዳንድ ጊዜ ድል ማድረግ ያን ያህል አስደሳች አይደለም። ብዙ ሰዎች ከስራቸው ተፈናቀሉ፣ የኤድ ራውልስን በቁጥጥር ስር መዋል ተከትሎም በድርጅቱ ውስጥ ከባድ ምስቅልቅል ይፈጠ ራል።»

«የራስሽን ጥቅም ስላልመረጥሽ ወድጀሻለሁ፣» አለ ሊ፣ «ግን ምናልባት ድርጅቱ ይህን መሰል ስር ነቀል ነውጥ ይፈልግ ነበር። አሳራው ከለከነ በኋላ የተሻለ ስፍራ ሆኖ ይቀር ይሆናል። ይህን ያደረግሽውም እንቺ ትሆኖለሽ።»

«አመሰግናለሁ፣» አለች፣ «ስግ፣ ስዊድኖች ከጋዜጠኞች ጋር ተነጋግረው ሲያበቁ እና አንተም ቃል እንደገባኸው ከዚያ ዘጋቢ ጋር ቃለ ምልልስ ካደረግክ በኋላ ብዙ ወሬ መወራቱ አይቀርም። ይህን ታውቃለህ። ይህን መሰል አትኩሮት ደግሞ ጆርጂያ ወስጥ የሚደረገውን የሲኔት ውድድር በደል ለመወጣት ያስችልሀል።»

«ይህ አንድ ሀሳብ ነው፣» አለ ዊል። «አስኪ የሚመጣውን እንመልከት። የሲናተር ሚስት ብትሆኚ ምን ይሰማሻል?»

«አስኪ የሚመጣውን እንመልከት፣» አለች ሩል፣ እጁን ጨመቅ እያደረገችው።

http://ethzare.wordpress.com

«ሒት፣» አለ ዊል፣ «ከድርጅቱ በፈቃድሽ ስራሽን እንደምትለቂ ነግረሻቸዋል። እውነት ታደርጊዋለሽ?»

ካተሪን ሩል ብሩህ ፈገግታን አሳየችው። «እስኪ የሚመጣውን እንመልከት።» አለች።

ተፈፀመ

http://ethzare.wordpress.com

- ኦፕሬሽን በሚጠርም ሁኔታ የዓለምን የበላይነት ማለትም በኢኮኖሚ፣ በጦር ሚዛን እና በመሳሰሉት የበላይነትን ለመቀዳጀት ሲባል የሩሲያ KGB እና የአሜሪካኑ CIA በሰው ሃገር ላይ ያዘጋቸል በማለት ተመሰርቷል ማን ይሳካለት ይሆን?

- የ KGB ው የስለላ መረብ ሃላፊ ላቀደው ታላቅ ሴራ ማስፈፀሚያ የሰውን ልጅ እንደ እንሰሳ ከመጠቀሙም በላይ እንደ ቀልድ አያይዞ ይሆን ታላቅ ማስጠርና የሚፈፅምበት ቀን ተቃርቧል ይፈፅመው ይሆን?

- የ CIA ዋ ሰላይ አንድ አስደንጋጭ የ KGBን ሚስጥር ከመስማትም አለፋ ትደርስበታለች ግን አለቆቿ ሚስጠሩን በማጣመል ስማ በማጠፋ ራሷ አይመጣን አደጋ ላይ በመጣል ትጋፈጠዋለች።ታጋልጠው ይሆን?

KGB ያጠመደው የኒውክለር ቦንብ CIA ሳይደርስበት የመፈንዳው ጊዜ ተቃርቧል ይህ ጎረቤት ሀገርንም ሆነ አካባቢውን የሚያወድም ታላቅ የቦንቡ ማስጠርና ከተለማ በጋላ ሃገሮችን ሽብር ውስጥ ከመክተቱም በላይ እልህ አስጨራሽ አርጠርብ ይደረጋል ። ይከሽፋ ይሆን?

- ሴሷ ከደረሰባት የአንሰሳዊ ድርጊት እና አሱ ከደረሰበት በደል የተነሳ የመበቀያ ጊዜና ሁኔታ በመድረስ እንዳረፉት የልባቸውን የበቀል መልስ ለመመለስ ተቃርበዋል ይፈፅመት ይሆን።

- ይህ መፅሐፍ ለፍቅር ሲባል ከአላማ ውጪ የሚደረግ ጉዞን ፣ ለገንዘብ ሲባል የጣምራ ሰላይነት ሚናን ፣ ከደረሰባቸው በደል የተነሳ የበቀል ፅዋን የመጐንጨት እና የተጠበቀው እንዳልተጠበቀ የሆኑና ያልሆኑ ድርጊቶች እየተፈፀሙ የአንባቢን ተልብ በመግዛት ከመጀመሪያ ገፅ አንስቶ ሚስጢሩ እስከሚፈታ የመጨረሻው ገፅ ድረስ በትኩት የሚነበብ መፅሐፍ ነው።

AMH Woo
Woods, Stuart
Bekelejaw selay 2008
hutl m 3
03010928408003
DFB

ዋጋ ብር 22

http://ethzare.wordpress.com